# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሳኔዎች



## ቅጽ-8

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውሣኔዎች

## ቅጽ - 8

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የጥናትና የሕግ ድጋፍ መምሪያ

ህዳር 2003 ዓ.ም

አዲስ አበባ



## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዝዳንት መልዕክት

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት የሚሠጠው የሕግ ትርጉም በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው፤ በዚህ ረገድ የሚሠጡ የሰበር ውሣኔዎችን ፍርድ ቤቱ አሣትሞ ማሠራጨት እንዳለበት አዋጅ ቁጥር 454/97 አንቀጽ 2/1/ ሥር ተደንግጓል፡፡ በዚሁ መሠረትም እስካሁን ድረስ አስገዳጅ የሆነ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸው ፍርዶች ከቅጽ 1 እስከ ቅጽ 7 ድረስ በማሣተም ለሚመለከታቸው ሁሉ እንዲሠራጩ ተደርገዋል፡፡

እነዚህ ፍርዶች የሀገራችን ፍርድ ቤቶች የሚሠጧቸው ፍርዶች ወጥነትና ተገማችነት እንዲኖራቸው በማድረግ ረገድ የማይናቅ ሚና እየተጫወቱ እንደሆነ ይታመናል፡፡ ይህን ቀጣይ ለማድረግ ቅጽ 8፣ 9 እና 10 እነሆ ለሕትመት በቅተዋል፡፡

አስገዳጅ የሰበር ውሣኔዎች ሥራ ላይ ከዋሉ አጭር ጊዜያቸው ነው፤ በአንፃራዊነት የብቃትም ሆነ የልምድ ውሱንነቶች በመኖራቸው እነዚህ እጥረቶች በሰበር ፍርዶቻችን ላይ አልፎ አልፎ መንፀባረቃቸው አልቀረም፡፡ በዚህ መስክ የረጅም ዘመናት ታሪክ ያሏቸው ሀገሮችም በተመሣሣይ ሁኔታ ውስጥ ያለፉ በመሆናቸው እኛም አቅማችንን በማጠናከር የእነዚህን አገሮች ተሞክሮዎች በማገናዘብና የሀገራችን የሕግ ባለሙያዎች በፍርዶቻችን ላይ የሚሠጡትን ገንቢ አስተያየቶችና ትችቶች ግብዓት በማድረግ ኃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ጥረታችን እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ እየገለጽሁ የሕግ ትምህርት ቤቶቻችን፣ ሌሎች የሕግ ባለሙያዎችና ህብረተሰቡ በአጠቃላይ ለጥረታችን እውን መሆን የማይተካ ድርሻ አላቸውና ከጎናችን እንዲቆሙ ጥሪየን አስተላልፋለሁ፡፡

ተገኔ ጌታነህ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ፕሬዚዳንት

# በ2001 ዓ.ም. የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸውን ውሣኔዎች

## ዝርዝር ማውጫ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን | ገጽ |
|---|---|---|---|---|---|
| | **የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት** | | | | 1 |
| 1 | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ የሚሰጥ ፍርድ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) | 33945 | አቶ ሣልህ ሁሴን እና ደግፌ ደርቤ | ጥቅምት 20/2001 | 2 |
| 2 | ማንኛውም ክርክር ሊወሰን የሚገባው በቀረበው ማስረጃ እና በህጉ መሰረት ብቻ ስለመሆኑ | 36848 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና መኰንን ግርማይ (ሦስት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 5 |
| 3 | በክርክር ሂደት ተቃዋሚ ወገን መጠራት ያለበት ምስክር ከመሰማቱ በፊት ስለመሆኑ | 35946 | እነ አቶ ማማሽ ወ/ስላሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 27/2001 | 7 |
| 4 | መጥሪያ ለምስክር እንዲደርስ በሚል ፍ/ቤቶች ሊልኩ የሚችሉበት አግባብ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103 | 36479 | ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ኃይሉ ወልዱ | ጥቅምት 25/2001 | 9 |
| 5 | በሌለበት ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነበት ተከራካሪ ፍ/ቤት ህጉን አስመልክቶ በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ለማለት የሚችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 78 | 36412 | ተስፋሁን ዋኘው እና በጃክ አግሮ ኮሜርሻል ኢንተርፕራይዝ | ጥቅምት 13/2001 | 12 |
| 6 | የቃል ክርክር ለመስማት እና የጽሁፍ መልስ ለመቀበል በሚል ፍ/ቤቶች በአንድ ቀጠሮ ሁለት ተግባራትን ለማከናወን የሚሰጡት ትዕዛዝ ከሥነ-ሥርዓት ውጪ ስለመሆኑ | 36380 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ | ጥቅምት 18/2001 | 16 |
| 7 | የበላይ ፍ/ቤቶች ውሣኔን ወደጐን በመተው በሥር ፍ/ቤቶች የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ | 37725 | እነ በቀለ ድሪብሣ (ሁለት ሰዎች) እና የምክር በሪሁን | ጥቅምት 6/2001 | 18 |
| 8 | በግልፅ የቀረበን ክርክር በተቆጠረ ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ እንዲጣራ/እንዲነጥር/ ሣይደረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | 37105 | ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግ/ ማህበር እና ሰለሞን አበበ ኮከብ | ጥቅምት 25/2001 | 21 |
| 9 | ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል /ትተዋል/ ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢያዊ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሳቸው ስምምነት ባደረጉ ጊዜ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 350(1) እና (2) | 37678 | ድራጋዶስ ጀ ኤንድ ፒ.ጆይንት ቬንቸር እና ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር | ህዳር 18/2001 | 23 |
| 10 | በሥር ፍ/ቤት ዳኝነት ያልተጠየቀበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ታይቶ ሊወሰን የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348(1), 182(2) | 37762 | ገወኔ ኢንተርፕራይዝ ኃ/ተ/የግ/ማህበር እና አቶ የሱፍ ይማም | ታህሣሥ 9/2001 | 26 |
| 11 | ከሥራ ውል ጋር በተያያዘ የሚጠየቁ ክፍያዎች ሳይነጣጠሉ በአንድ ላይ መቅረብ ያለባቸው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 216(4), 5 | 38601 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት እና ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር | ታህሣሥ 14/2001 | 29 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 12 | • ክርክር ከሚካሄድበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ መብትና ጥቅም እንዳለ የተረጋገጠ እንደሆነ በክርክር ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>• በውርስ አጣሪ ሪፖርት ላይ ጥያቄ (ተቃውሞ) አለማቅረብ ሚስት/ባል የሆነን ወገን የጋራ ነው በሚለው ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚያግድ ስላለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | 37742 | ወ/ሮ አልማዝ ጉንፌ ኦሪቲ<br>እና<br>ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን | ታህሣሥ 7/2001 | 31 |
| 13 | በአንድ መንግስታዊ መዋቅር ሥር የሚገኙ ሁለት ራሳቸውን የቻሉና የህግ ሰውነት ያላቸው ተቋሞች የመንግሥትን ጥቅም የሚያስጠብቁ አካላት በመሆናቸው ብቻ እንደ አንድ መቆጠር የሌለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358<br>አዋጅ ቁጥር 1/1995,18/1997,2/1995,4/2000 | 37502 | የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ህግ ጉዳዬች ቢሮ እና እነ ወ/ሮ የኃላሸት ገመዳ ቤኛ (ሁለት ሰዎች) | ታህሣስ 2/2001 | 33 |
| 14 | ፍ/ቤቶች ለክርክር ፍትሐዊነት ተገቢ ነው ብለው ሲያምኑ ማናቸውንም አይነት ማስረጃ አስቀርበው መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 145,345,327/3/ | 29861 | ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን እና እነ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 14/2001 | 36 |
| 15 | የክርክር ዋነኛ ጭብጥ በሆነ ጉዳይ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ፍ/ቤት በድጋሚ “ስህተት ለማረም” በሚል ምክንያት ሊለውጥ ወይም ሊያሻሽል ስላለመቻሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 208 | 37303 | ኤ.ሲ..ዲ አይ/ቮካ-ኢትዮጵያ እና እነ ሃይደር አሊ (ስምንት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 40 |
| 16 | ዳኝነት የሚጠየቅበት መብትና ጥቅም በግልጽ ተለይቶ ያልተመለከተበት አቤቱታ የክስ ምክንያት እንደሌለው የሚቆጠር በመሆኑ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33, 231 | 38419 | የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ያሲን ጀማል | የካቲት 5/2001 | 42 |
| 17 | ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ክርክር መሠረት በማድረግ አግባብነት ያለውን ጭብጥ ሳይመሰርቱ የሚሰጡት ውሣኔ ህጋዊ ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 37391 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ ስዩም ማሞ (ሁለት ሰዎች) | የካቲት 3/2001 | 45 |
| 18 | በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው /መብታቸው/ ሊነካ የሚችል የሆነ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.40 | 39540 | ናስ ፉድስ የድ/ዳ/ጨ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ<br>እና<br>እነ ስንዱ ደጀኔ (ዘጠና ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 47 |
| 19 | አንድ ጉዳይ ከዚህ ቀደም በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት የሚቻልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.5 | 36780 | ወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ እና አቶ ገ/ኪዳን እንግዳ | መጋቢት 3/2001 | 50 |
| 20 | ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክርን የክርክሩ ምክንያት የሆነው ንብረት የሚገኘው ወይም ውል የተደረገው በአንደኛው ክልል እንኳን ቢሆን የመዳኘት ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀጽ 5(2) | 36460 | መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ እና እነ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጀ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 57 |
| 21 | በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀን ዳኝነት አስመልክቶ ግልጽ ፍርድ አለመስጠት ስህተት ስለመሆኑ | 39144 | አቶ ልዑልሰገድ ቦኄ እና ኢትዮ ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግል ማህበር | መጋቢት 24/2001 | 60 |
| 22 | የቀረበበትን ክስ ያመነ ተከሣሽ ባመነው መሠረት ውሣኔ ለመስጠት የሚከለክል በቂ የህግ ምክንያት እስከሌለ ድረስ ውሳኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ | 38597 | እነ ጋሻው መንግስቴ ካሣ (ሁለት ሰዎች) እና ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር | ሚያዝያ 6/2001 | 63 |
| 23 | በአንድ ዘንግ የሚመደቡ ተከራካሪዎች እና አንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ ያለማድረግ መሠረታዊ የሥነ-ሥርዓት ግድፈት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 11(5) | 40024 | ሸራተን አዲስ እና እነ<br>አቶ እያሱ መገርሣ | ሚያዝያ 29/2001 | 65 |
| 24 | የሥር ፍ/ቤቶች የፈፀሙትን ሥህተት ለማረም በሚል በሥር ፍ/ቤት ተከራካሪ ከነበሩ ወገኖች መካከል አንዱ ወገን ያቀረበውን አቤቱታ መነሻ በማድረግ ሌላኛው ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር ውሣኔ መስጠት ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348(1) | 34504 | አቶ አበባው የሺድንበር<br>እና<br>አቶ ካሣ በቀለ | ሚያዝያ 6/2001 | 68 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 25 | በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሚሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 329(1), 182(2) | 37761 | ገብረመስቀል ንጉሴ እና አዲስ ልብስ ስፌት አ.ማ | ሚያዝያ 20/20001 | 70 |
| 26 | ክስ በሚሰማበት የቀጠሮ ዕለት የይግባኝ ባይ አለመቅረብ ጋር በተያያዘ መዝገብ ሲዘጋ የሚችለው መልስ ሰጪው ይግባኙን ሙሉ በሙሉ ክዶ የተከራከረ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ | 38181 | የኢትዮጵያ መንግዶች ባለስልጣን እና እነ ወ/ሮ ትዕግስት ወንድይፍራው (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 4/2001 | 73 |
| 27 | ፍ/ቤት ተከራካሪ ወገን ያቀረበው የሰነድ ማስረጃ የሚጠቅም ያልሆነ እንደሆነና የሰው ምስክር በተጨማሪነት የቆጠረ እንደሆነ ፍትሐዊ የሆነ ውሣኔን ለመስጠት የምስክሮችን ቃል መስማት ያለበት ስለመሆኑ | 42706 | ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ እና አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር | ግንቦት 25/2001 | 75 |
| 28 | በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መለወጥ ወይም መሻሻል ተከትሎ ማናቸውም ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመሰጠቱ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ የሚሰጥ ትዕዛዝ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ እንጂ የግድ የሚሰጥ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 349(1) | 37741 | አቶ መኮንን ዘውዴ እና እነ አቶ ተሾመ ሽፈራው (ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 4/2001 | 77 |
| 29 | ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቶች የቀረበላቸውን ጉዳይ ለማስተናገድ ስልጣን ያላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 9(2) | 38452 | የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ አለም ገብሩ | ሰኔ 11/2001 | 79 |
| 30 | አንድን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማንሣት ስልጣን የለኝም ያለ ፍ/ቤት ጉዳዩ በበላይ ፍ/ቤት ታይቶ በፍሬ ጉዳዩ ላይ እንዲያከራክር ጉዳዩ የተመለሰለት እንደሆነ ሌላ ተጨማሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን መሠረት በማድረግ ጉዳዩን ለማየት አልችልም ማለት የማይገባው ስለመሆኑ | 39014 | አለሙ መግራ እና እምነቱ እንዳሻው ህንፃ ተቋራጭ | ሰኔ 23/2001 | 81 |
| 31 | የይግባኝ ማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ተከራካሪ ወገን የሚያቀርበው የማስፈቀጃ ማመልከቻ በበቂ ምክንያት የተደገፈ መሆን/አለመሆኑን ፍ/ቤቶች በጥሞና መመርመር ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 326(1) | 38145 | ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ እና አቶ ተስፋዬ ደምሴ | ሰኔ 30/2001 | 83 |
| 32 | አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች (የሙያ) ማስረጃው በፍ/ቤቱ በኩል በጭብጥነት ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት ያለው እና በህግ ተቀባይነት ያለው እስከሆነ ድረስ ቀርቦ መሰማት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 111, 249 እና 257 | 38683 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ሣህሉ ወ/ማርያም | ሰኔ 25/2001 | 85 |
| 33 | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤቶች የሥር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሳይመረምሩ እና ለውሣኔያቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ መሻር የማይችሉ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(1) | 38844 | የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን እና ጋድ ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማህ | ሰኔ 25/2001 | 87 |
| 34 | ተከራካሪ ወገኖች በፍ/ቤት ትዕዛዝ እንዲቀርብላቸው የሚጠይቁት ማስረጃ የተያዘውን ጉዳይ ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ዕልባት ለመስጠት የሚያስችል እስከ ሆነ ድረስ ጥያቄውን ፍ/ቤቶች ሊቀበሉት የሚገባ ስለመሆኑ | 36979 | ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና ሚስተር ሽሬሃሪ ብራማቫሪ ጉፓል | ሐምሌ 23/2001 | 91 |
| 35 | ሦስተኛ ወገኖች በፍ/ቤት በመካሄድ ላይ ባለ ክርክር እንዲገቡ የሚያስፈልግበት ሁኔታ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 | 41544 | ሰላም የህዝብ ማመላለሻ (አ.ማ) እና ኒያላ ኢንሹራንስ አ.ማ | ሐምሌ 8/2001 | 93 |
| | **አሰሪና ሰራተኛ** | | | | 95 |
| 36 | የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀፅ 2/ሰ/ | 35197 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ እና ኤፍሬም ንዋየማሪያም | ጥቅምት 13/2001 | 96 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 37 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች የተቀጠሩበት የፕሮጀክት ሥራ ሲጠናቀቅ የሥራ ውላቸው የሚቋረጥ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 10/1//ሠ//ሀ/ | 35621 | ሰንሻይን ኮንስትራክሽን እና እነ አቶ ፍቃዱ ገቢሣ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 99 |
| 38 | በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ.377/96 ባልተሸፈነ ጉዳይ ላይ በአሠሪና በሠራተኛ መካከል የተደረገ የህብረት ስምምነት መፈፀም ያለበት ስለመሆኑ | 36692 | አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት እና ተስፋዬ መኰንን | ጥቅምት 25/2001 | 101 |
| 39 | ሠራተኞች ለሚፈፅሙት ጥፋት በህብረት ስምምነት የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡ በሆነ ጊዜ አሰሪው በሠራተኛው የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት መወሰን የሚችል ስለመሆኑ | 37027 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት አሰለፈች ደስታ | ጥቅምት 11/2001 | 103 |
| 40 | አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በህግ ከተደነገገው ማዕቀፍ ሳይወጣ/ሳይጥስ/ የሥራ ሰዓቱን ማሻሻል ስለመቻሉ<br>አዋጅ 377/96 አንቀፅ 61/1/ | 36518 | ሜታ አቦ ቢራ አ.ማ እና እነ ሳሙኤል ተፈራ (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 4/2001 | 105 |
| 41 | የአሰሪ ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደል ያለማስጠንቀቂያ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1/ተ/ | 35484 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና አቶ ደረጀ ማሞ | ህዳር 25/2001 | 107 |
| 42 | አሰሪ ሠራተኛውን በሣምንት ዕረፍቱ ሥራ እንዲሰራ ለማድረግ የሚችል ስለመሆኑ | 37815 | አለማየሁ ጠቅላላ ሥራ ተቋራጭ እና አቶ አብዮት በፈቃዱ | ህዳር 2/2001 | 109 |
| 43 | በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የሥራ ቀናት" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(3) | 36377 | የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት እና ተሾመ ኩማ | ህዳር 2/2001 | 111 |
| 44 | የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም/ እና የጡረታ አበል ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ | 37048 | የሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሣህሉ ምትኩ | ህዳር 2/2001 | 113 |
| 45 | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ መውጣት በራሱ አንድን ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ለመመለስ መብት የሚሰጥ ስላለመሆኑ | 37256 | አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር እና ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን | ህዳር 4/2001 | 116 |
| 46 | ለአምስት ተከታታይ ቀናት በሥራ ገበታ ላይ ያለበቂ ምክንያት አለመገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ስለመሆኑ | 37402 | የንኮማድ ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ቡሽራ በቀለ | ህዳር 11/2001 | 119 |
| 47 | ከሥራ ጋር በተገናኘ በሚፈፀም ድርጊት መነሻነት በሠራተኛው ላይ በፖሊስ የሚደረግ ምርመራ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ | 37573 | የውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት እና አቶ መሐመድ አደን | ህዳር 16/2001 | 122 |
| 48 | የሥራ ውል በስምምነት ተቋረጠ ለማለት የሚቻለው ስምምነቱ በፅሁፍ የተደረገ እንደሆነ ስለመሆኑ | 37575 | ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ እና ብርሃኑ ልደት ወልዴ | ህዳር 2/2001 | 124 |
| 49 | በአሰሪ በተደረገ የሥራ ዝውውር ቅሬታ አድሮብኛል በሚል ምክንያት ከሥራ መቅረት የህግ ድጋፍ የሌለው ስለመሆኑ | 37778 | አዲስ መለዋወጫ ዕቃዎች አስመጪ አከፋፋይ አ.ማ እና አቶ ካሣሁን ከበደ | ህዳር 4/2001 | 126 |
| 50 | በአሰሪና በሠራተኛ መካከል የሥራ ውል ግንኙነት አለ ለማለት የሚቻልበት አግባብ | 03171 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፓሬሽን እና ወ/ት ትርሲት ደገፋ | ህዳር 16/2001 | 129 |
| 51 | አዲስ መዋቅርን ተግባራዊ ያደረገ ተቋም/ድርጅት/ ሠራተኞቹን "ራሱ ባወጣው መስፈርት" መሰረት ሊመድብ ስለመቻሉ | 36210 | አቃቂ መለዋወጫ ዕቃዎችና መሣሪያዎች አ.ማ እና አቶ ኃይለ ሳልቫቶር | ህዳር 2/2001 | 132 |
| 52 | • አንድ ሠራተኛ በአሰሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በሚል ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበት የሚችልበት አግባብ<br>• በአሰሪና ሰራተኛ ሕጉ ውስጥ "የአሰሪ ንብረት" በሚል የተገለፀው ሐረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27/1//ሸ/ | 34669 | አድማስ ኮሌጅ እና ሠለሞን ሙሉአለም | ታህሣሥ 2/2001 | 134 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 53 | የተረከበው የአሠሪ ንብረት የጠፋበት ሰራተኛ ንብረቱን ለግል ጥቅሙ ወይም ለሌላ ሶስተኛ ወገን ጥቅም ያዋለው ያለመሆኑን ካላስረዳ በቀር የንብረቱ መጥፋት ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል በቂ ምክንያት ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ)(ቀ) 14(2)(ለ)(2) | 39118 | ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አቶ በፈቃዱ በላይ | ታህሣሥ<br>23/2001 | 136 |
| 54 | በህብረት ስምምነት ወይም በሌላ አካኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ያልተመለከተ ቢሆንም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 3787/96 አንቀፅ 27/1/ | 36591 | ማታዶር አዲስ ጎማ አ.ማ<br>እና<br>ደረጀ ኡመታ | ታህሳስ 14/2001 | 139 |
| 55 | የሥራ መሪ በሆነ የሥራ መደብ ላይ በጊዜያዊነት መስራት ግለሰቡን የሥራ መሪ ከመሆን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 3/2/ /ሐ/ | 36894 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ ሙላት ታረቀኝ | ታህሳስ 30/2001 | 141 |
| 56 | ለተወሰነ ጊዜ በተደረገ የሥራ ውል ግንኙነት ለሠራተኛው የሚከፈል የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተዋዋይ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ የሚፈፀም ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 35/2/ | 37201 | ማታዶር አደስ ጎማ አክሲዮን ማህበር እና<br>እነ አቶ ኤልያስ በቀለ<br>(አስራ አራት ሰዎች) | ታህሣሥ<br>30/2001 | 143 |
| 57 | የጥበቃ ሥራን የሚሠራ ሠራተኛን በተመለከተ የሥራ ውሉ ያለአግባብ ተቋርጧል በሚል ሲወሰን በአሠሪውና ሠራተኛው መካከል ሊኖር የሚገባው ከፍተኛ መተማመን የሚሻክር በመሆኑ ሰራተኛው ወደ ሥራ እንዲመለስ የሚሰጥ ውሳኔ ተገቢ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43 | 37454 | ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል<br>እና ከበደ ሰይፉ | ታህሣሥ<br>16/2001 | 146 |
| 58 | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተፈረደለት ሠራተኛ ለመመለስ ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቶ የሥራ ክርክሮችን የሚወስነው አካል ሠራተኛው አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎች ተከፍሎት ከሥራ እንዲሰናበት ሊወሰን የሚችለው በመጀመሪያው ፍርድ መሠረት ያልተፈፀመ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 43/3/ | 38255 | አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>አለምሰገድ ኃይሉ | ታህሣሥ<br>23/2001 | 149 |
| 59 | የሥራ ውሉን በፍቃዱ የቋረጠ ሠራተኛ የህብረት ስምምነት የሚፈቅድለት ከሆነ ኘሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት የማግኘት መብት የሚኖረው ስለመሆኑ | 37551 | አቶ ድካምየለህ ጥበቡ እና አርሾ የህክምና ላብራቶሪ ኃ/የተ/የግል/ማህበር | ታህሣስ 9/2001 | 152 |
| 60 | የስራ ውል የተቋረጠው ከህግ ውጪ ነው ተብሎ በተወሰነ ጊዜ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ወገን/ሠራተኛ/ ሊወሰኑለት የሚገቡ ክፍያዎች | 34476 | ኩመላ በጅሣ እና ብሔራዊ አስጐብኚና ጉዞ ወኪል | ታህሳስ 2/2001 | 155 |
| 61 | አንድ የሥራ ዘርፍ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም በዚሁ ዘርፍ ሠራተኞችን ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል ቀጥሮ ሊያሰራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሐ) | 40305 | የኢትዮጵያ ፐልኘና ወረቀት አ.ማ<br>እና<br>እነ አቶ ታመነ ጫላ | ታህሣሥ<br>21/2001 | 158 |
| 62 | አንድ ሠራተኛ ይሰራው የነበረ የሥራ መደብ መሰረዝ ወይም አለመኖር ለሥራ ውሉ መቋረጥ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1) (መ) | 40804 | ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ እና እነ ተክሉ ኡርጌ ኢደኤ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 26/2001 | 160 |
| 63 | አንድ ሠራተኛ ወደ ሥራ ሲሄድና ከሥራ ወጥቶ ወደቤቱ ሲመለስ አሰሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሰበት መሆኑ ከተረጋገጠ ሦስተኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋፅኦ መኖር አሰሪው የጉዳት ካሣ ላለመክፈል እንደመከላከያ ሊሆነው ስላለመቻሉ እና የጉዳት ካሣው በጉዳት የተነሣ ህይወቱን ላጣው ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፈልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 95/2/, 96/1/, 98/2/, 97/1/, 107/1//ሐ/, 110/ 112 | 36194 | ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ<br>እና<br>ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ | ጥር 28/2001 | 162 |
| 64 | በድርጅት ውስጥ በተደረገ የመዋቅር ማሻሻያ የሥራ መደብ የተሰረዘ እንደሆነ የሥራ መደብ የተሰረዘበትን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚቻልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) | 38811 | ርሆቦት ሆሊ ሴቪየር ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና አቶ አማረ አድማሱ | የካቲት 17/2001 | 167 |
| 65 | በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለ የሥራ መደብ በሌላ 3ኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የስራ ውል ለማቋረጥ ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 28 | 38435 | ኤስ.ኦ.ኤስ የህፃናት መንደር እና እነ አቶ ከበደ ኩምሣ (ስድስት ሰዎች ) | የካቲት 17/2001 | 169 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 66 | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የሥራ ውል የሚቋረጠው ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስለመሆኑ | 38023 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ እና ብርሃኑ ደስዬ | የካቲት 17/2001 | 171 |
| 67 | በአሰሪያቸው ላይ ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ሠራተኞች የአሰሪውን ንብረት በዋስትና ከያዙ ባለገንዘቦች ይልቅ የቅድሚያ ክፍያ መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 167<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀጽ 2857(1)<br>አዋጅ ቁ. 186/94 አንቀጽ 80<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ህገ- መንግስት አንቀፅ 13(2) | 40921 | አቢሲንያ ባንክ (አ.ማ)<br>እና<br>አብዱ አህመድ<br>(ሁለት መቶ ስልሣ ስድስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 173 |
| 68 | የአንድ ሠራተኛን ድርጊት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የሥራውን ባህሪ ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ | 41115 | ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል/ማህበር እና አቶ ሞገስ ሽፈራው | የካቲት 26/2001 | 175 |
| 69 | አሠሪ የአንድን ሠራተኛ ደሞዝ እና ሌሎች ጥቅማጥቅም ሣይነካ በተመሳሳይ የሥራ መደብ ላይ አዛውሮ ሊያሠራ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 13(2) እና (7) | 40938 | ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርኘራይዝ<br>እና<br>አቶ ኃይሉ መንግስቱ | መጋቢት 24/2001 | 178 |
| 70 | አንድ ሠራተኛ የአሠሪው ንብረት የሆነን ገንዘብ ማጉደሉ የተረጋገጠ እንደሆነ አሠሪው ሠራተኛውን በፍ/ብሔር ክሶ ገንዘቡን የማስመለሱ ጉዳይ እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ሊያቋርጥ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 42292 | የኢትዮጵያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ከበደ አቡነቴ | መጋቢት 24/2001 | 180 |
| 71 | በአሠሪው ወደሌላ ቦታ ተዛውሮ እንዲሠራ የተደረገ ሠራተኛ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም የተዛወረበት የሥራ ገበታ ላይ ለ5 ተከታታይ ቀናት የቀረ እንደሆነ የሥራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያበቃ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27 (1)(ለ) | 41623 | አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር እና አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ | መጋቢት 8/2001 | 182 |
| 72 | • ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛን ከሥራ የማገድ ተግባር ሠራተኛን እንደማሰናበት የማይቆጠር ስለመሆኑ<br>• አሠሪው ከ30 ቀናት በላይ ሠራተኛው ለታገደበት ጊዜ ደሞዝ እንዲከፍል የሚደረግበት አግባብ<br>• ከሥራ ያለአግባብ ታገድኩኝ በሚል የቀረበን ክስ በማስተናገድ ላይ ያለ ፍ/ቤት በክርክሩ ሂደት ሠራተኛው ከሥራ የተሰናበተ መሆኑን ካወቀ የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ጉዳዩን ማየት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(4) | 41411 | ሙሉሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት<br>እና<br>አቶ በለጠ ተገኝ | ግንቦት 11/2001 | 184 |
| 73 | • አንድ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ከጉዳቱ በኋላ የቀድሞ ስራውን መስራት መቀጠሉ ብቻ አሰሪውን የጉዳት ካሣ ከመክፈል ነፃ የማያወጣው ስለመሆኑ<br>• በሥራ ላይ ከሚደርስ ጉዳት ጋር በተገናኘ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ውስጥ የተመለከተውና "የመስራት ችሎታ" የሚለው ሃረግ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ እና የጉዳት ካሣ መጠንና ሊወሰን የሚችልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 109, (1) እና (3) , 107, 99(1), 102(3)<br>አዋጅ ቁ.345/95 አንቀጽ 33 | 43370 | የግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ጌታቸው ገድሌ | ግንቦት 12/2001 | 187 |
| 74 | • የድርጅት ምርታማነትን ለማሳደግ፣ የአሰራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ የሚደረግበት አግባብ<br>• ቅነሣ የሚደረግበትና ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ), 29(3) | 42752 | እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ<br>(ሰላሳ ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል(NTO) | ግንቦት 12/2001 | 190 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 75 | በሠራተኛ እጅ የሚገኙ የአሠሪ ንብረቶች መመለስ ወይም  አለመመለስ ጉዳይ ሠራተኛው የሥራ ውሉ በተቋረጠ ጊዜ የሚያነሣቸውን ልዩ ልዩ ክፍያዎችን ለማስተናገድ ግምት ውስጥ መግባት ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 36, 38 | 39464 | ሐረር ቢራ አክሲዮን ማህበር<br>እና<br>አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ | ግንቦት 25/2001 | 193 |
| 76 | ቀድሞ ይሰራበት የነበረን የሥራ መደብ በመሰረዙ ምክንያት ሠራተኞችን በማሰናበት ፋንታ በክፍያ አነስተኛ ወደሆነ ሌላ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ያደረገ አሠሪ ለሠራተኞቹ በቀድሞው ደመወዝ መሠረት እንዲከፍል የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | 41786 | የኢትዮጵያ አየር መንገድ እና እነ አቶ አሰፋ አቤቦ (ሦስት ሰዎች) | ግንቦት 26/2001 | 195 |
| 77 | በጥበቃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ እንዲጠብቅ የተሰጠው የአሰሪ ንብረት የጠፋ እንደሆነ ሰራተኛው ለንብረቱ መጥፋት አስተዋጽኦ ያለማድረጉን ማረጋገጥ ካልተቻለ በስተቀር በሃላፊነት ሊያስጠይቀው  የሚችል ስለመሆኑ | 39650 | የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክ እና እነ ቄስ ሰፊነው ደሣለኝ | ግንቦት 27/2001 | 198 |
| 78 | በተጭበረበረ ማስረጃ ሥራ የተቀጠረ ሠራተኛ በሥራ ላይ እያለ የማጭበርበር ድርጊቱ የታወቀ/የተደረሰበት/ ከሆነ ማጭበርበሩ የተከሰተው ሥራውን በማከናወን ላይ እንዳለ ተቆጥሮ ሊያስናብተው የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27(1) (ሐ) | 39543 | የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ በረከት ተ/ማርያም | ግንቦት 4/2001 | 200 |
| 79 | ለፕሮጀክት ሥራ የተቀጠሩ ሠራተኞች ቅነሣ በሚካሄድበት ወቅት አሰሪው በአዋጅ ቁ.377/96 ላይ የተመለከተውን የሠራተኞች ቅነሣ ሥነ-ሥርዓት መከተል የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30(1) | 39042 | ዮቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማህበር እና ጀማል መሐመድ | ግንቦት 26/2001 | 202 |
| 80 | የሥራ መደብ ዝውውርን በመቃወም ቅሬታን በማሰማት ላይ መሆን በስራ ቦታ ላይ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊ ምክንያት የሚወሰድ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) | 38189 | ሮፖ`ክ ኢንተርናሽናል ኃላ/የተ/የግል ማህበር እና ይደርሳል አእምሮ | ግንቦት 27/2001 | 204 |
| 81 | አሠሪ የሥራ መሪ የሆነን ሠራተኛውን ያሰናበተው ያለበቂ ምክንያት ቢሆንም እንኳን ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በስተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ እንዲመልስ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ | 37982 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና አቶ ታደሰ ዘነበ | ሰኔ 16/2001 | 207 |
| 82 | ለሥራ ማስኬጃነት የተቀበሉትን የአሰሪ ገንዘብ አጉድሎ መገኘት ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ሊያሰናብት የሚችል ጥፋት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 27(1)(መ) | 41720 | የእንጨት መሠንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት እና ረዲ እንዳለ | ሰኔ 9/2001 | 210 |
| 83 | የሥራ ውል የተቋረጠው በህጉ አግባብ ነው ተብሎ የተወሰነ እንደሆነ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የማይከፈል ስለመሆኑ | 39861 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖ`ሬሽን እና አቶ ሣምሶን በለጥካቸው | ሰኔ 18/2001 | 212 |
| 84 | በቃል ከሥራ ተሰናበትኩ በሚል ክስ የሚያቀርብ ሠራተኛ አሰሪው ከሥራ ያሰናበተው ስለመሆኑ የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ | 43610 | ናይኮ ኃላ/የተ/የግ/ማህበር እና አቶ ሰለሞን ተሰማ | ሐምሌ 21/2001 | 214 |
| 85 | አሠሪ የሆነ ወገን የሥራ ቅልጥፍናን፣ ውጤታማነትን፣ የኢንዱስትሪ ሰላምን ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሠራተኛ የተቀጠረበትን ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች በጠበቀ ሁኔታ አዛውሮ ለማሰራት የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 2 (1), 4 | 44033 | መንበረ ፓትሪያሪክ ጠቅላይ ጽ/ቤት<br>እና አቶ ይበልጣል አጥናፉ | ሐምሌ 22/2001 | 216 |
| 86 | በህግ ወይም በሕብረት ሥምምነት የተመለከተው የጡረታ እድሜ ሣይደርስ በመንግሥት መመሪያ በጡረታ እንዲገለሉ የተደረጉ ሠራተኞችን በተመለከተ አሰሪ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ለመክፈል የማይገደድ ስለመሆኑ | 42906 | የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ<br>እና እነ ትዕግስት ማሞ<br>(ሰማንያ አንድ ሰዎች) | ሐምሌ 21/2001 | 218 |
| 87 | የኮንስትራክሽን ሥራ የሚሰራ ድርጅት የሥራው መጠን በቀነሰ ጊዜ ሠራተኞችን ለማሰናበት የማስጠንቀቂያና ሌሎች የቅነሳ ሥነ-ሥርዓቶችን ሳይከተል ቅነሳ ለማካሄድ የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30 | 42075 | አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር እና እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ | ሐምሌ 16/2001 | 221 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 88 | የሥራ ውል እንደተቋረጠ የጡረታ አበል ለማግኘት መብት ያለው ሠራተኛ የሥራ ስንብት የማይከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39<br>አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2) (ሰ) | 39808 | ናዝሬት ሣሙና ፋብሪካ<br>እና<br>ዘውዴ ኃ/ማርያም | ሐምሌ 21/2001 | 223 |
| 89 | የሥራ መሪ ከሠራተኛ ሊለይ የሚችልበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 3, አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2 | 42901 | የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻ እና ማከፋፈያ ድርጅት እና ወ/ሮ ንግስት ለጥይበሉ | ሐምሌ 21/2001 | 225 |
| 90 | በአሰሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄድ የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሰሪው ገንዘብ ይከፈለኝ በሚል በሠራተኛው ላይ ክስ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ | 39471 | ኤርሚያስ ሙሉጌታ አና በከልቻ ትራንስፓርት አ/ማ | ሐምሌ 29/2001 | 227 |
| 91 | በሃይማኖት ተቋም ውስጥ መንፈሳዊ(ሃይማኖታዊ) አገልግሎት የሚሰጥ ሰራተኛ ከተቋሙ ጋር ያለው የስራ ግንኙነት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ የሚሸፈን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 | 18419 | ሐመረወርቅ ቅ/ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ዲያቆን ምህረት ብርሃን(ስድስት ሰዎች) | ግንቦት 4/1998 | 229 |
| | **ቤተሰብ** | | | | 232 |
| 92 | የውርስ ሀብት ክፍፍልን መነሻ ያደረገ ክስ የግዴታ ውርስ ከተጣራ በኂላ መቅረብ የሌለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1000(1) | 34703 | እንዳሻው ፍቃዱ እና እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ(ሰባት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 233 |
| 93 | ኑዛዜ ሲነበብ የነበሩ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም በሚል የሚያቀርቡት የመቃወም አቤቱታ ኑዛዜው በተነበበ በአሥራ አምስት ቀን ውስጥ መቅረብ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 973 | 36604 | ወ/ሮ ፅጌ መንግስቱ እና እነ አቶ ወንድይራድ መንግስቱ(ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 25/2001 | 235 |
| 94 | ከጋብቻ በፊት የግል የነበረን ንብረት መነሻ በማድረግ በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘ ንብረት የግል ሆኖ ሊቀጥል የሚችለው በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 58(2), 57, 62(2) | 37275 | ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው እና ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ | ጥቅምት 18/2001 | 237 |
| 95 | ግልፅ ኑዛዜ ህጋዊ እንዲሆን መሟላት ያለበት ፎርማሊቲ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 | 36777 | አቶ ወንድም አገኝ ዘውዱ እና እነ አቶ ታፈሰ ወንድአፈራሽ (ሶስት ሰዎች) | ጥቅምት 25/2001 | 241 |
| 96 | ህፃናትን ማዕከል ያደረጉ ክርክሮች የልጆችን ጥቅም ባስጠበቀ መልኩ መስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ | 35710 | ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ እና ወ/ሮ ሰላሚዊት ንጉሴ | ታህሣስ 16/2001 | 243 |
| 97 | የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ ይኼው ግለሰብ እንደ ምስክር ተደርጐ ባይፃፍም ምስክር ተደርጐ ሊቆጠር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443,881,882 | 37562 | አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ እና አቶ ግርማ ታፈሰ (ሁለት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 248 |
| 98 | ጋብቻ ህጋዊ ውጤት የሚኖረው በህግ አግባብ ተፈፅሟል ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 28(3) | 41896 | ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ እና እነ ወ/ሮ አዲስዓለም ፀጋ (ሦስት ሰዎች) | የካቲት 26/2001 | 251 |
| 99 | የሟች እዳን ለመክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው በውርስ የተገኘውን ሀብት እንጂ የወራሾች የግል ሃብት ስላለመሆኑ | 38691 | አቶ ለገሰ ቢራቱ እና አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ | የካቲት 24/2001 | 253 |
| 100 | የአንደኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት በሌለኛው ተጋቢ የተሸጠ እንደሆን ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ካወቀበት ቀን ጀምሮ በ 6 ወር ውስጥ እንዲሁም በማናቸውም ሁኔታ ደግሞ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለመጠየት ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 69(2) | 38126 | ዲያቆን ኃይለጊዮርጊስ ወንድምሲያምረኝ እና እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 256 |
| 101 | በኑዛዜ የተገኘ ንብረት በ10 (አሥር) ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተጠየቀ በስተቀር በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ | 38152 | የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች እና እነ አቶ ይልማ አስፋው | ሚያዝያ 29/2001 | 258 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 102 | የይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠን ፍርድ ከመረመረ በኋላ የጉዳዩን ጭብጥ በመያዝ ወደ ሥር ፍ/ቤት የመለሰው እንደሆነ አስቀድሞ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠውን ፍርድ እንደሌለ የሚያስቆጥረው ስለመሆኑ | 37313 | እነ አቶ መሐሪ ተ/ማሪያም (ሁለት ሰዎች) እነ የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ግንቦት 18/2001 | 261 |
| 103 | ወራሽ የሆኑ ወገኖች የሚያቀርቧቸውን ተገቢነት ያላቸው ማስረጃ በሙሉ አሰባስቦ በመስማት ያልተከናወነ የውርስ ማጣራት ሪፓርት በህግ አግባብ የተከናወነ ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241, 270 እና 345 | 42525 | እነ አቶ አብዱልዋሲቅ አርጋው እና ወ/ሮ አልዋያ አባበሊስ | ግንቦት 27/2001 | 264 |
| 104 | የተናዛዡ ህጋዊ ንብረት ባልሆነ ነገር ላይ የተደረገ ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅም እንኳን የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 865 | 32817 | ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ እና እነ ወ/ሮ ቴቴ ዘውዴ(ሦስት ሰዎች) | ሰኔ 11/2001 | 266 |
| 105 | የገበያ ዋጋን መሠረት ያላደረገና የግንባታ ዋጋ ግምት ላይ ብቻ ተመርኩዞ የሚደረግ የውርስ ሀብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ | 40510 | ቴዎድሮስ መንበሩ እና ገ/ህይወት ታደሰ | ሰኔ 23/2001 | 269 |
| 106 | ጋብቻ በሁለት የተለያዩ ሥርዓቶች የተፈፀመ ቢሆንም አንድ ጊዜ በህግ አግባብ የተደረገ ፍቺ በቂና ሙሉ ህጋዊ ውጤት የሚያስከትል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 75(ሐ) | 40781 | ፍቅረስላሴ ካህሣይ እና ወ/ሮ ሮማን ታደሠ | ሐምሌ 30/2001 | 271 |
| 107 | በውርስ ሃብት ክፍፍል ላይ ተወላጅ የሆነ ሰው ከሩብ በላይ ጉዳት የደረሰበት እንደሆነ ክፍፍሉ እንዲቀር ለመጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ሕ/ቁ. 11/22,913,1060,1037-1051,942 | 18394 | ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ እና ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ | መጋቢት 21/1999 | 274 |
| | **ውል** | | | | 278 |
| 108 | የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ ሊካስ የሚችል በሆነ ጊዜ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 | 35472 | አቶ መሐመድ ካሣሁን<br>እና<br>አቶ ሰለሐዲን ኑር | ጥቅምት 6/2001 | 279 |
| 109 | የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723"ን" መስፈርት አላሟላም በሚል ውል እንዲፈርስ የተደረገ እንደሆነ ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት እንዲመለሱ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723,1815 | 34803 | መ/ር መኳንንት ወረደ እና እነ መስከረም ዳኛው (አራት ሰዎች) | ጥቅምት 11/2001 | 282 |
| 110 | ከአንሻሮነት ውል ጋር በተያያዘ ለሚኖር የጉዳት ሃላፊነት ካሣ ሊወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 595, 596, 597<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1790, 2090, 2091, 2092, 2141, 2102 | 32854 | ወ/ሪት ማርታ አድማሱ<br>እና<br>እነ አቶ በረከት ሰብስቤ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | 293 |
| 111 | የተከራዩትን ቤት ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ለውል ማፍረስ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | 36520 | የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ እና አቶ ይብራህ ግርማይ | ጥቅምት 27/2001 | 296 |
| 112 | መሐይምነትን ወይም ዓይነስውርነትን መሠረት በማድረግ ውል እንዲፈርስ የሚቀርብ አቤቱታ በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719,1845 | 29363 | ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ እና አቶ ጥላሁን አርምዴ | ህዳር 18/2001 | 299 |
| 113 | የማይንቀሣቀስ ንብረት የሽያጭ ውል ተደረገ የሚባለው በውል ውስጥ ያሉ ወገኖች በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውሉን ከተፈራረሙበት ቀን ጀምሮ እንጂ የአስተዳደር ጉዳዮች ተጣርቶ የመስሪያ ቤቱ ማህተም ካረፈበት ቀን አንስቶ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723(1), 2015(ሀ) | 36740 | አቶ አብዱልዋሐብ ኢብራሂም እና እነ ወ/ት መሰለች ከፍያለች (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 23/2001 | 302 |
| 114 | በማኅበር በመደራጀት የተሠራ ቤትን ለሶስተኛ ወገን ከማስተላለፍ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የሚነሣ ክርክርን አስመልክቶ የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1723 | 36294 | ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ<br>እና<br>እነ በቀለ ገመዳ ዳኖ (ሁለት ሰዎች) | ህዳር 9/2001 | 305 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 115 | በአሰሪ ወይም በ3ኛ ወገን ወጪ ትምህርትን ተከታትሎ ለማገልገል በሚል የተገባን ውል (ስምምነት) የጣሰ ሰው ግዴታውን በአማራጭ ሊወጣ የሚችል ስለመሆኑ | 33473 | ወ/ሮ ሃርሴማ ሰለሞን እና የአርባ ምንጭ ዩኒቨርስቲ | ህዳር 16/2001 | 307 |
| 116 | የዕቃ አስተላላፊነት ሃላፊነትና ተግባር ዕቃን የማጓጓዝና የማስረከብ ሥራን የሚያካትት ስለመሆኑ | 32571 | አቶ ሚፍታህ ከድር እና የባህር ትራንዚት አገልግሎት | ታህሣሥ 9/2001 | 311 |
| 117 | ክርክር የሚካሄድበት ጉዳይን አስመልክቶ በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ጊዜ የሌለ እንደሆነ ስለ ውሎች በጠቅላላ በሚለው ክፍል የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677፣1845 | 34940 | ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ<br>እና<br>አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዩ | ታህሣስ 28/2001 | 314 |
| 118 | • ፍ/ቤት የቀረበለትን የውል ይሰረዝልኝ፣ ጥያቄ ወደጐን በመተው የውል የፎርማሊቲን የተመለከተ ጭብጥ በማንሣትና ምክንያቱን በመለወጥ ውሣኔ መስጠት የማይገባው ስለመሆኑ<br>• በፍ/ብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት መሰረት ጭብጥ ለመመስረት የሚቻልበት አግባብ | 32299 | እነ አቶ ሰለሞን ከተማ (ሁለት ሰዎች)<br>እና እነ ሴንትራል ቬኑ /የተ/የግል ማህበር (አራት ሰዎች) | ጥር 7/2001 | 316 |
| 119 | በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ጋር በተያያዘ በቅን ልቦና ዋጋ ሰጥቶ ስለመዋዋል የተመለከተው ድንጋጌ የንግድ መደብርን በተመለከተ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1161<br>የንግድ ሕግ ቁ. 124 | 34586 | አቶ አያሌው ድልነሳው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ<br>(አራት ሰዎች) | ጥር 28/2001 | 321 |
| 120 | በውል ግንኙነት ውስጥ የራስን ግዴታ ሳይወጡ ሌላው ወገን ግዴታውን አልተወጣም በሚል የሚቀርብ ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757 | 39568 | አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም እና አቶ ገብሬ ጉንጤ | መጋቢት 24/2001 | 324 |
| 121 | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጐት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ያላሳወቀ እንደሆነ ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት የመጠየቅ መብቱ በ10 ዓመት ይርጋ የሚታገድበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1731(1), 1732, 1789 እና 1845 | 38935 | እነ አቶ ወልደፃዲቅ ብርሃነ (ሁለት ሰዎች) እና አቶ ስንታየሁ አያሌው | መጋቢት 3/2001 | 327 |
| 122 | በፍ/ብሔር ጉዳዮች የይርጋ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ጀምሮ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1846 | 36756 | አቶ ፀጋዬ ምትኩ እና እነ ወ/ሮ አበበች ምትኩ (ሁለት ሰዎች) | መጋቢት 17/2001 | 331 |
| 123 | ለብድር በዋስትና መልክ የተሰጠን ንብረት ለተበዳሪው መመለስ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥር ስለመሆኑ | 41571 | ማህደር አእምሮ እና ሳእክ ገ/መድህን | ሰኔ 2/2001 | 334 |
| 124 | በህግ ፊት በማይፀና ውል አማካኝነት የተሣሠሩ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ይመለሱ በሚል ውሣኔ መስጠት የሚቻለው መመላለሱ አንደኛውን ወገን በእጅጉ የሚጐዳ ወይም ሌላኛውን ያልተገባ ጥቅም ሊያስገኝ የሚችል አለመሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ | 39336 | ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ እና እነ አዱኛ እጅጉ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 7/2001 | 337 |
| 125 | በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቋሚል ለማለት የሚያበቃ ስለመሆኑ | 39170 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና<br>እነ አቶ ክንዴ አፍራሶ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 340 |
| 126 | የባለዕዳውን ዕዳ ለባለገንዘብ የከፈለ ወገን በባለገንዘቡ መብቶች ላይ በመዳረግ (subrogation) ባለገንዘቡ የነበረውን መያዣን መሰረት ያደረገ የቀዳሚነት መብት ሊሰራበት የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1968 - 1974 | 39778 | ሕብረት ባንክ አ/ማ<br>እና<br>አቢሲኒያ ባንክ አ/ማ | ሐምሌ 30/2001 | 344 |
| 127 | ፈራሽ የሆነን የስጦታ ውል ተከትለው የተሰሩ ስራዎችን ቀሪ ማድረግና ተዋዋዬችን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻለው በቅን ልቦና የተዋዋለ 3ኛ ወገን መብትን የማይጐዳ በሆነ ጊዜ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1815,1816,1817 | 41116 | ፍሌንስቶን ኢንጅነሪግ እና እነ ወ/ት ሐና ተስፋዬ (ስድስት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 350 |
| 128 | የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት እንደተሰጠ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2863 - 2874 | 39256 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ ሞሣ ነጋሽ (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 353 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 129 | በብድር የተሰጠን ገንዘብ እጥፍ ለመቀበል በሚል የሚደረግ የብድር ስምምነት የህግ መሰረት የሌለው ስለመሆኑ | 43372 | አቶ ደረሱ አለሙ እና አቶ ሙሊሣ ወርቁ | ሐምሌ 22/2001 | 361 |
| 130 | ስልጣን ያለው የአስተደደር አካል የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብትነቱን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሰጠው ሰው ጋር የተደረገ የንብረቱ የመያዣ ውል የተሰጠው የምስክር ወረቀት የተሰረዘ ቢሆን እንኳን መያዣ ተቀባዩ በቅንልቦና አለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር የፀና ሆኖ የሚቀጥል ስለመሆኑ | 41388 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ከፍያለው ሞልቶት (ሁለት ሰዎች) | ሐምሌ 30/2001 | 363 |
| 131 | የማይንቀሣቀስ ንብረት ገዥ ውል እንዲፈፀምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በአስር ዓመት ጊዜ ውስጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 384(ሀ), የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2892(3) | 39725 | እነ ወ/ሮ አለምሸት ካሣሁን (ሦስት ሰዎች) እና አቶ ሽመልስ እንዳለ | ሐምሌ 23/2001 | 366 |
| 132 | የማይንቀሣቀስ ንብረትን በተመለከተ የሚደረግ የስጦታ ውል የማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም በህግ የፀና ውል ተደርጐ ሊወሰድ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443, 881, 1723(1) | 39803 | አቶ አለኸኝ ገ/ህይወት እና እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ (ሦስት ሰዎች) | ሐምሌ 2/2001 | 369 |
| | **አፈፃፀም** | | | | 372 |
| 133 | በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ተካሄዶ ሽያጭ የተፈፀመ እንደሆነ ሽያጩ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጥ ሥርዓቱ የተነሣ መብት ወይም ጥቅም ያለው ሰው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት መድረሱ የተረጋገጠ እንደሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 445 | 31963 | አቶ አብዱልሐኪም ሁሴን እና እነ አቶ ቀነኒ ሁንዴ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 20/2001 | 373 |
| 134 | የፍርድ ባለመብት ባለመቅረቡ የተዘጋ የአፈፃፀም መዝገብ ፍርድ ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ በ10(አሥር) ዓመት ይርጋ ካልታገድ በቀር ሊንቀሳቀስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 384 | 35018 | በዛብህ አበበ እና የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ | ጥቅምት 18/2001 | 376 |
| 135 | • የፍርድ አፈፃፀም ክርክር የሚጀመረው የፍርድ ባለመብት የሆነ ወገን በፍርዱ መሰረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ሲያቀርብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/<br>• የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለሰጠው ፍ/ቤት ወይም የአፈፃፀም የውክልና ስልጣን ለተሰጠው ፍ/ቤት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 371,372 | 21359 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ (ሁለት ሰዎች) | ጥቅምት 28/2001 | 378 |
| 136 | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥሮች 358 እና 418 ተፈፃሚ የሚሆኑበት አግባብ | 32143 | መሐመድ አስማኤል ተርቢ እና መሐመድ አህመድ ኑር | ጥቅምት 18/2001 | 382 |
| 137 | የአንድ ንብረት ወቅታዊ ዋጋ ማለት ንብረቱ ለጨረታ ሽያጭ ቀርቦ የሚያወጣው ዋጋ ስለመሆኑ | 37503 | አቶ ወልደዮሐንስ ኃብተየስ እና ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ | መጋቢት 24/2001 | 384 |
| 138 | የማይንቀሣቀስ ንብረት በሐራጅ ጨረታ ሊሸጥ የሚችልበት ሥነ- ሥርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 426,428(2) | 39175 | ወ/ሮ በለጡ ጋሼ እና እነ አንዱአለም ቴድሮስ (ሦስት ሰዎች) | መጋቢት 24/2001 | 386 |
| 139 | በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት በአይነት ካልተገኘ እና የንብረቱ ዋጋ በልጦ ከተገኘ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው ንብረቱን በአይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378, 392 | 39485 | የህፃን ሠላማዊት ቴድሮስ ሞግዚት እና መምህር ሚካኤል ግደይ | መጋቢት 17/2001 | 389 |
| 140 | በህግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠ ውሣኔ በይግባኝ እስካልተሻረ ድረስ የሞራል ወይም የህሊና አስተሳሰብን መሠረት በማድረግ ብቻ ዋጋ አልባ ሊደረግ የማይችል ስለመሆኑ | 38041 | ታደሠ ገ/መስቀል እና እነ ሙሉጌታ ዘካርያስ (ሰባት ሰዎች) | መጋቢት 22/2001 | 392 |

# ፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት

የሰ/መ/ቁ. 33945

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** አቶ ሣልህ ሁሴን - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ደግፌ ደርቤ - ከጠበቃ ጣሰው ማሞ ጋር ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

አመልካች ግንቦት 05 ቀን 1997 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ተጠሪ በስማቸው ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በቀድሞው አጠራር ከፍተኛ 09 ቀበሌ 07፣ በአሁኑ አጠራር በአራዳ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 የሚገኘውን ቁጥሩ 207 እና 206 የሆነ ቤት በመያዣነት አስይዘው ብር 12000.00 /አስራ ሁለት ሺህ/ ተበድረው ቤቱን እንዳስረከቧቸው፣ በስምምነቱ ወቅት የማይንቀሳቀስ ንብረት መሸጥና መለወጥ ችግር ስለነበር ገንዘቡ የ10 ዓመት መክፈያ ጊዜ ተወስኖለት ኀዳር 20 ቀን 1990 ዓ.ም. ማብቃቱን፣ ኀዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በተፃፈ የብድርና የዋስትና ውል ቤትን መሸጥና መለወጥ በመንግሥት ሲፈቀድ አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ በመጨመር ከወሰዱት ብር 12000.00 ጋር ተደምሮ በብር 17000.00 /አስራ ሰባት ሺህ ብር/ ቤቱን በሽያጭ ለማስተላለፍ ተጠሪ ውል መፈረማቸውን፣ የቤቱን የእድሣት ወጪዎችም አመልካች እንዲሸፍኑ ተጠሪ ፈቃዳቸውን በውሉ የገለጹላቸው ሆኖ ተጠሪ ከወሰዱት የቤቱ መያዣ ብድር ጋር የእድሣት ወጪ ሲደመር ድምሩ ብር 18787.90 /አስራ ስምንት ሺህ ሰባት መቶ ሠማኒያ ሰባት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ መሆኑን፣ የቤት ሽያጭም ከ1982 ዓ.ም. ጀምሮ በመንግሥት መፈቀዱን ዘርዝረው ተጠሪ በስምምነቱ መሠረት የብድሩን ገንዘብ በወቅቱ ካለመመለሣቸውም በላይ የቤቱን ስመ ንብረት በሽያጭ ለማስተላለፍ በአማራጭ የገቡትን ግዴታ ስላልፈፀሙላቸው አመልካች ብር 5000.00 /አምስት ሺህ/ ለተጠሪ ጨምረውላቸው የቤቱ ስም በአመልካች እንዲዛወር ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ለማስረጃነትም የጽሑፍና የሰው ምስክሮችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡

የአሁኑ አመልካች የክስ ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪ እንዲደርስ ተደርጎም ተጠሪ በተደረገላቸው ጥሪ መሠረት ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጓል፡፡ ፍ/ቤቱም የአመልካችን ክስና ማስረጃ መርምሮ በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገ ውል የመያዣ ውል ሣይሆን የወለድ አገድ ውል ነው፣ ውሉ በተደረገበት ወቅት የወለድ አገድ ግንኙነት የሚገዛው በአዋጅ ቁጥር 47/67 ስለነበር ይኸው አዋጅ የወለድ አገድ ውልን የሚከለክል በመሆኑ ውሉ ሕገወጥ ስለሆነ ፈራሽ ነው፣ ተዋዋዮች ወደ ነበሩበት ይመለሱ፣ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ያስረክቡ፣ ተጠሪ ከአመልካች የወሰዱትን ገንዘብና የቤት ማደሻ ብር በገቡት ውል መሠረት ለከሣሽ ያክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶች ኀዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ተጠሪ ቀርበው ባልተከራከሩበት እና የተጠየቀ ዳኝነት በሌለበት ሁኔታ ቤት እንዲረከቡ መወሰናቸው ያላግባብ በመሆኑ ውሣኔው ተሽሮ ኀዳር 20 ቀን 1980 ዓ.ም. በውል ያገኙት መብት ተጠብቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በጉዳዩ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የተሠጠውን ውሣኔ የሕግ አግባብነት ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት፣ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 ድንጋጌን ያገናዘበ፣ የአመልካች ጥያቄ ግን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2851 ድንጋጌ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፈው ባቀረቡት የመልስ መልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ ዋናው ጉዳይ ገብተው ለመከራከር ሥነ-ሥርዓቱ የማይፈቅድላቸው መሆኑን ገልፀውና የሰበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች፡-

1ኛ/ የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ከጠየቁት ዳኝነት በተለየ ሁኔታ የሰጡት ውሣኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? እና

2ኛ/ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ወይስ የለውም? የሚሉት ሆነው ተገኝተዋል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፡- አመልካች ከተጠሪ ጋር ተደርጓል በሚሉት ስምምነት አከራካሪውን ቤት ተረክበው በይዞታቸው ሥር አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን ገልፀው የሚከራከሩ ሲሆን የጠየቁት ዳኝነትም ቀሪውን ብር ለተጠሪ ጨምረው የቤቱ ስመንብረት እንዲዛወርላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ነው፡፡ ይህንኑ የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤት ቀርበው ክስር ያልተከራከሩበት ሆኖ የስር ፍ/ቤት ግን የውሉን ሕጋዊነት በራሱ ጊዜ በማንሣት ሕገ-ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ ውሉ ፈራሽ ነው በማለት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ለተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የስር ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የአሁኑ አመልካች በግልጽ ባላመለከቱት እና ባልጠየቁት ዳኝነት ላይ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 182/2/ ድንጋጌ ሥር የተመለከተውን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የዳኝነት አሠጣጥ የስልጣን አድማስ በግልጽ የሚፃረር ነው፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም በይግባኝ ሠሚነቱ ስልጣን የስር ፍ/ቤትን የውሣኔ አሠጣጥ ማረም ሲገባው በተመሣሣይ ምክንያት ተቀብሎ ማጽናቱ የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን ያላገናዘበ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ስለውሉ ሕጋዊነት ክርክር ባልተነሣበት ሁኔታ በራሱ ጊዜ ማንሣቱም የክርክር አመራር ስርዓቱ በሚፈቅድለት ሁኔታ አይደለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ከተወሰነ በኋላ አሁን በሰበር ችሎት ያቀረቡት ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም፡፡ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ሣይቀርቡ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ለበላይ ፍ/ቤት ሊያቀርቡ የሚችሉት ክርክር ከስር ክስ ተያይዘው የቀረቡትን የከሣሽን ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ያገናዘበ መሆን ያለመሆኑን መሠረት በማድረግ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በዚሁ የክርክር ደረጃ ያነሱት ክርክር ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ አልፈነዋል፡፡ በዚህም መሠረት የስር ፍ/ቤት የውሣኔ አሠጣጥ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ መሆኑ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ፡- በመጀመሪያው ጭብጥ እንደተገለው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ስመ ንብረቱ እንዲዞርላቸው ይወሰን ዘንድ ነበር፡፡ የስር ፍ/ቤትም የዚህኑ ጥያቄ አግባብነት በመመርመር ውሣኔ መስጠት እየተገባው ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት ያለው መሆን ያለመሆኑን የስር ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ በሕጉ አግባብ የሰጠው ውሣኔ ባይኖርም ከተጠየቀው ዳኝነት ይዘት በሰበር ችሎቱ ከዚህ በፊት በተመሣሣይ ጉዳይ ከተሰጠው የሕግ ትርጓሜና ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ዓላማ አኳያ ሲታይ በዚህ ችሎት ለጉዳዩ እልባት መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የሚያስከስስ ሊሆን ይችላል አይችልም? የሚለው ነጥብ ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከአመልካች ክስና ክርክር ማረጋገጥ የተቻለው ከተጠሪ ጋር በተደረገው ስምምነት ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ቤት አመልካች ተረክበው ለረጅም ጊዜያት በይዞታቸው ስር አድርገው የሚገኙ መሆኑን፣ ቤቱን የሚመለከቱ አስፈላጊ ሰነዶችም በተጠሪ እጅ ይገኛሉ ተብሎ በክሱ አለመገለጹንና የዳኝነት ጥያቄ ያልቀረበበት መሆኑን በተጠሪ በኩል መፈፀም አለበት የተባለው የቤቱ ስመ ንብረት ማዞር ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የስም ዝውውር ተግባር የሚፈፀመው በመንግሥት አስተዳደር ክፍል ፊት እንጂ ሻጭ ነው የተባለው ወገን ሊፈጽም ይገባል ተብሎ ከሕግ ወይም ከውል ይመነጫል ሊባል የማይችል ግዴታ ነው፡፡ የስም ዝውውር ጥያቄ የሚስተናገደው የባለ ሀብትነት የምስክር ወረቀት በሚሠጥ የመንግሥት አስተዳደር አካል ገዢው ውልና አስፈላጊ ሠነዶችን ይዞ ሲቀርብ እንጂ በፍ/ቤት ክስ ቀርቦ ዳኝነት የሚሰጥበት አይደለም፡፡ አንድ ክስ ሊቀርብ የሚገባው የክስ ምክንያት ሲኖረው ሲሆን የክስ ምክንያትም ተከሣሽ ለከሣሽ ሊፈጽመው የሚገባው ግዴታ መኖሩ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ መስጠት የሚቻልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሲረጋገጥ የሚታወቅ ነው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ተጠሪ የስም ዝውውሩን እንዲፈጽሙ ይወስንልኝ ብለው ዳኝነት መጠየቃቸው በተጠሪ በኩል ሊፈፀም የሚገባ የሕግ ወይም የውል ግዴታ የሌለ መሆኑን ስለሚያሣይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231/1/ሀ/ መሠረት ፍሬ ነገሩ የማያስከስስ ነው ተብሎ መወሰን ያለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13295 ጥቅምት 16 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 51107 ኀዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም. የፀና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሸሯል፡፡
2. አመልካች የስም ዝውውር ጥያቄ ታይቶ ይወስንላቸው ዳኝነት ጠይቀው እያለ ከተጠየቀው ዳኝነት በተለየ ሁኔታ ውሉ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ቤቱን እንዲያስረክቡ መባሉ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓትን የተከተለ አይደለም ብለናል፡፡
3. የአመልካች የስም ይዛወርልኝ ጥያቄ የሚያስከስስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 36848

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ኤ/ኃይል ኮርፖሬሽን

**ተጠሪዎች፡-** 1. መኰንን ግርማይ - ቀረቡ፡፡

2. በዶ ዘለቀ - ቀረበ

3. ፈጠነ አያዩ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የኤሌክትሪክ ምሰሶ ጉድጓድ ለመቆፈር ጊዜያዊ ሠራተኞች በመሆን ሠርተናል፤ በኂላም ወደ ሪዳት የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት አሸጋግሮን ስንሰራ ከቆየን በኂላ ካለማስጠንቀቂያ ከስራ ስላሰናበተን ወደ ስራችን ተመልሰን ቋሚ ሠራተኞች እንድንሆን ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎችም በስራ ላይ ደረሰብን ለሚሉት ጉዳት ያወጡት ወጪ ይተካላቸው ዘንድ በተጨማሪ ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ በእሱ እና በተጠሪዎች መካከል የተደረገ የስራ ውል እንደሌለ በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱ ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበለትን ክርክር ከሰማ በኂላ ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ናቸው፤ የስራ ውላቸው የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፤ በመሆኑም አመልካች በሕጉ መሠረት የሚከፈሉትን ክፍያዎች እንዲሁም በስራ ላይ ሣሉ ለደረሰባቸው የአካል ጉዳት ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪዎች የአመልካች ሠራተኞች ተብሎ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አከራካሪው ነጥብ በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውልን መሠረት ያደረገ ግንኙነት ነበር ወይስ አልነበረም? የሚለው ነው፡፡ ከስር ጀምሮ ከቀረበው የአመልካች ክርክር እንደሚታየው ተጠሪዎች በተባለው የምሰሶ ጉድጓድ ቁፋሮ ወይም የኤሌክትሪክ መስመር መዘርጋት ስራ አልተሣተፉም አይልም፡፡ ክርክሩ ይህን ስራ የሰሩት ከኔ ጋር የስራ ውል አድርገው ሣይሆን፣ ስራውን እንዲሠራ ኮንትራት ከተሰጠው ግለሰብ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ነው የሚል ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም ይህን ጭብጥ በመያዝ ማስረጃ እንደሰማና በዚህም አመልካች ስራውን በኮንትራት የሰጠው ግዛው ወንዳፍራሽ ለተባለ ሰው እንደሆነ፣ ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የቅጥር ግንኙነት

እንደሌላቸው፣ ግዛው ወንዳፍራሽ ክፍያውን ሲፈጽም እንደቆየ ማረጋገጡን በአንድ በኩል ሲገልጽ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተከሣሽ /አመልካች/ ከሱ ጋር የቀን ስራ ሲሰሩ አለመቆየታቸውን ሙሉ በሙሉ አልካደም፤ ክፍያው ሲፈፀም የነበረው ከአመልካቹ በተገኘ ገንዘብ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ እንደሰጠ ለመገንዘብ ችለናል፡፡

በበኩላችን እንደምናየው አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የተደረገ የሥራ ውል እንደሌለው በግለጽ በማመልከት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች የተባለውን ስራ ሲሠሩ የቻሉበትን ምክንያትም ከመግለፁም በላይ፣ በቆጠረው ማስረጃም እንደክርክሩ ጭብጥ አስረድቷል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ በውሣኔዎቻቸው ላይ በሚገባ አስፍረው ግንዛቤ አግኝተው ሣለ ተቃራኒ የሆነውን ውሣኔ መስጠታቸው ትክክል አይደለም፡፡ ማንኛውም ክርክር ሲወሰን የሚገባው በቀረበው ክርክር ማስረጃ እና በሕጉ መሠረት ብቻ ነው፡፡ እነዚህን መሠረታዊ ቁምነገሮች በማለፍ የሚሰጥ ውሣኔ በማንኛውም መለኪያ ሕጋዊ ሊሆን አይችልም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔም ከቀረበው ክርክር፣ከተሰማው ማስረጃ እና ከሕጉ ውጭ የተሰጠ በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 06165 መጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 05200 መጋቢት 1 ቀን 2000 ያፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የስራ ውል ግንኙነት ስለሌለ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ የመሠረቱት የስራ ክርክርን የሚመለከተው ክስ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ወስነናል፡፡ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 35946

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች**፡- 1. አቶ ማሙሽ ወልደስላሴ
2. ወ/ሮ አፀደ ወልደስላሴ } ጠበቃ ውብሸት ሥነ ጊዮርጊስ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ወ/ሮ ሰብለ ወንድይራድ - ቀረቡ
2. ወ/ሮ የሺ ሙላት - አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች ባቀረቡት አቤቱታ ወ/ሮ ውዴ ወልደስላሴ ባደረባቸው ሕመም ምክንያት ነሐሴ 21 ቀን 1989 ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፤ ሟች በሕይወት እያሉ ነሐሴ 9 ቀን 1989 ዓ.ም እማኞች ባሉበት ባደረጉት ኑዛዜ በድሬዳዋ ከተማ ከፍተኛ 1 ቀበሌ 06 በአሁኑ አጠራር በቀበሌ 04 የሚገኘውን የቤት ቁጥር 839 ለእኛ ለአመልካቾች አውርሰውናል፤ ሁለተኛ አመልካችም አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው ሞግዚት አድርገው ሾመውኛል፤ ስለዚህ በምናቀርበው ማስረጃ ተረጋግጦ የወራሽነት ማረጋገጫና አካለመጠን ላልደረሰችው ተማሪ ኮከብ እሱባለው የሞግዚትነት ማስረጃ ይሰጠን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የአመልካቾችን ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ እንዲቀርብ ትእዛዝ በሰጠው መሰረት የአሁን አመልካቾች በተቃዋሚነት ቀርበው ቀደም ሲል አመልካቾች ተመሳሳይ አቤቱታ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበው ጥያቄያቸው ውድቅ የተደረገ ሲሆን በይግባኝም ጸንቷል፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ በድጋሜ ያቀረቡ ስለሆነ ፍ/ቤቱ ውድቅ ሊያደርገው ይገባል በማለት የተከራከሩ ሲሆን በአማራጭም ሟች ውዴ ወ/ስላሴ አድረገውታል የተባለው ኑዛዜ በእድሜም ሆነ በጤንነት ረገድ እራሳቸውን በማያውቁበት ጊዜ የአሁን አመልካቾች እራሳቸው ፈጥረው ያዘጋጁትና በሕግ ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ከመሆኑም በላይ አመልካቾች የወ/ሮ ውዴ ልጅነትም ሆነ የሩቅ ዝምድና ስለሌላቸው የኑዛዜ ወራሽነት ጥያቄው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ አቤቱታው አስቀድሞ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ አግኝቷል የተባለውን በተመለከተ ፍ/ቤቱ አቤቱታውን ሳይቀበለው የቀረው አንድ ኑዛዜ ከተደረገ በኋላ በዚሁ ኑዛዜ መሰረት ወራሾች የንብረት ክፍፍል ከሚያደርጉ በስተቀር ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲጸድቅ ሕግ ስለማያስገድድ ኑዛዜ ይጽደቅልን በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ውሳኔ

ከመስጠቱ በስተቀር የኑዛዜ ወራሾች ናችሁ ወይንም አይደላችሁም የሚል የመጨረሻ ውሳኔ ስላልሰጠ ጉዳዩ አስቀድሞ እልባት አግኝቷል ተብሎ የቀረበው ክርክር አግባብነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የኑዛዜውን ሕጋዊነት አስመልክቶ የተነሳውን ክርክር በተመለከተም ሟች በጤነኛ አእምሮና በነጻ ፈቃዳቸው ኑዛዜውን ስለማድረጋቸው በአመልካቾች ምስክሮች የተረጋገጠ ስለሆነና ሟችም ንብረታቸውን ለፈለጉት ሰው በኑዛዜ የማስተላለፍ መብት ስላላቸው ተጠሪዎች የአመልካቾችን የኑዛዜ ወራሽነት በመቃወም ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ በሌላ በኩልም ሟች ኑዛዜ ያደረጉበት ቤት ባለሐብትነቱ በከፊል የእራሳቸው በከፊል ደግሞ የሟች ባቤታቸው የነበረ ስለሆነ ከእራሳቸው ድርሻ አልፎ የሟች ባቤታቸውንም ድርሻ ጨምሮ ያደረጉት ኑዛዜ ሕገ ወጥ ስለሆነ በድርሻቸው ልክ የተደረገው ኑዛዜ ብቻ ትክክል ነው ብሎ በዚሁ ልክ አመልካቾች ወራሾች ናቸው በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለድሬዳዋ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ቢያቀርቡም የሥር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ የሚሻው ነጥብ የተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነት በሥር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠው አግባብነት ባለው ሁኔታ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚህም አኳያ ጉዳዩን እንደመረመርነው ተጠሪዎች የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው አቤቱታቸውን ለድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ አቤቱታው የቀረበለትም ይሄው ፍ/ቤት በቅድሚያ የአመልካቾችን/የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክር ከሰማ በኋላ ተቃዋሚ ካለ ይቅረብ በማለት የጋዜጣ ጥሪ አድርጓል፡፡ እዚህ ላይ ተቃዋሚ ቢኖር ይቅረብ ተብሎ የተሰጠው ትእዛዝ አግባብነት ነበረውን የሚለው ነጥብ እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት የነበረበት አመልካቾች አቤቱታቸውን እንዳቀረቡ ማስረጃ ከመስማቱ በፊት መሆን ይገባው ነበር፡፡ ተቃዋሚ የሚጠራበት አላማ የቀረበውን አቤቱታ ከማስረጃውና በአጠቃላይም ከሚቀርበው ክርክር አኳያ የበኩሉን ማስረጃና ክርክር እንዲያቀርብ እድል ለመስጠት ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ ምስክሮች ከተሰሙ በኋላ ተቃዋሚ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠቱ ተቃዋሚው በምስክሮች አመሰካከር ላይ የሚያነሳውን ክርክር/The right to confront witnesses/ የሚያጠብና ጉልህ የሆነ የሥነ- ሥርአት ጉድለት መፈጸሙን የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካቾችን /የአሁን ተጠሪዎችን/ ምስክሮች ከሰማ በኋላ ተቃዋሚዎችን መጥራቱ እንደዚሁም ይ/ሰሚው ፍ/ቤት ይህንኑ ጉድለት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የድሬዳዋ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00409/99 በሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0134/99 ኅዳር 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሽረነዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የድሬዳዋ ከተማ ነክ ፍ/ቤት የተጠሪ ምስክሮችን በድጋሜ በመጥራት ግራ ቀኙ ባሉበት በመስማት ክርክሩን በድጋሜ ተመልክቶ እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36479

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ጉደር አግሮ ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ/- ጠ/አለም ወ/አረጋይ

**ተጠሪ**፡- አቶ ኃይሉ ወልዱ - አልቀረቡም

## ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው የቀረበው የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው በሕገ ወጥ መንገድ ነው ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ሲሆን ለሠበር ችሎት የቀረበው የሕግ ጥያቄም ለምስክሮች ስለሚሰጥ መጥሪያ አደራረስ የሚመለከት ነው፡፡

ተጠሪ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን ገልፀው ሕጉ የሚፈቅድላቸው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ ያሽከረክሩት የነበረው መኪና ለአቶ አገኘሁ የኔነህ በመሸጡና ከሣሽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከገዢው ጋር አዲስ የስራ ውል በማድረግ በስራ ቦታ ላይ ያልተገኙ በመሆኑ እንደሆነ ተከራክሮ ስንብቱ ሕጋዊ ነው እንዲባልለት ጠይቋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡንና ማስረጃዎቹን መርምሮ የተጠሪ ምስክሮች ተጠሪ መኪናው ከተሸጠ በኋላም የድርጅቱን መኪና በመያዝ ያገለግሉ እንደነበር አስረድተዋል፤ ተጠሪ መኪናው መሸጡ እንዳልተገለፀላቸው ያስረዱ ሲሆን አመልካች ግን ተጠሪ መኪናው መሸጡን ማወቅ ነበረባቸው ወይም አሣውቄአለሁ የሚል ክርክር ስለሌለው ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በማለት ተጠሪ የኪሣራ እና የስንብት ክፍያዎች እንዲሁም የሐምሌ ወር 1998 ዓ.ም ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ይግባኝ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በአቤቱታው ተጠሪ ሲያሽከረክሩት የነበረው መኪና በመሸጡ ተጠሪ መኪናዋን ከገዙት ግለሰብ ጋር ለመስራት ተስማምተው በስራ ቦታቸው ባለመገኘታቸው የሥራ ውሉ መቋረጡን መኪናዋን የገዙትን ግለሰብ በምስክርነት ቆጥረናቸው ምስክሩ ሆን ብለው በመሠወራቸው መጥሪያውን ልንሰጥ ስላልቻልን በሚኖሩበት አካባቢ ባለው ፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት እንዲደርሣቸው በድጋሚ መጥሪያ እንዲታዘዝልን ያመለከትን ቢሆንም

ፍ/ቤቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 116 እና 118/2/"ን" በተሣሣተ መንገድ በመተርጎም መጥሪያው በመሐላ ቃል በተደገፈ አቤቱታ ለፍ/ቤቱ ስላልተመለሠ በድጋሚ መጥሪያ አይታዘዝም ማለቱ ስህተት ነው ብለዋል፡፡

የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል ተብሎ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡ የታዘዘ ሲሆን ተጠሪም ቀርበው ሕጉ በሚፈቅደው ቃል መሐላ አቅርበው ምክንያታቸውን መግለጽ ሲችሉ ስላላቀረቡ የፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ተገቢ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ያላግባብ ተሰናብቻለሁ በማለት ክስ ሲያቀርቡ አመልካች ደግሞ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ የነበሩት መኪና በመሸጡ ተጠሪ ንብረቱን ከገዙት ሰው ጋር ለመስራት በመዋዋል በስራ ቦታቸው ባለመገኘታቸው የስራ ውሉ

ተቋርጧል ሲል ተከራክሯል። አመልካች ይህንን አባባሉን እንዲያስረዱለት መኪናውን ገዙ የተባሉትን ግለሰብ በመስክርነት ቆጥሯቸው የነበረ መሆኑንና ምስክሩን አግኝቶ መጥሪያ መስጠት ባለመቻሉ ግን መጥሪያው ምስክሩ በሚኖሩበት አካባቢ በሚገኝ ፖሊስ ጣቢያ አማካኝነት እንዲደርሣቸው ጠይቆ ፍ/ቤቱ ይህንን ሁኔታ በቃለ መሐላ አስደግፎ ባለማቅረቡ ድጋሚ መጥሪያ እንዲሰጥ የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ስህተት መሆኑን ገልጿል። በእርግጥ ተያይዞ በቀረበው የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ላይ ይህ ስለመሆኑ የተገለፀ ነገር ባይኖርም ተጠሪ በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ ይህንኑ አረጋግጠዋል። ስለሆነም አመልካች ለምስክሩ የተላከውን መጥሪያ ምስክሩን አግኝቶ መስጠት አለመቻሉን በቃለ መሐላ በማስደገፍ አለማረጋገጡ በድጋሜ መጥሪያ እንዳይታዘዝ ያስከለክለዋል ወይ? የሚለውን ይህ ችሎት ተመልክቷል።

አመልካች ስንብቱ ሕገ-ወጥ አይደለም በማለት አጠብቆ የሚከራከረው ተጠሪ የሚነዱት መኪና በመሸጡና ተጠሪም መኪናውን ከገዙት ሰው ጋር ለመስራት ተስማምተው ከስራ ቦታቸው ላይ ባለመገኘታቸው በበቂ ምክንያት ተሰናብተዋል በማለት ነው። ይህ ለመሆኑም መኪናውን የገዙት ግለሰብ ቀርበው እንዲመሠክሩ ጠይቋል። አንድ ተከሣሽ ለቀረበበት ክስ የሚያቀርበውን ማስተባበያ በማስረጃ እንዲያስረዳ መብት አለው። እኛም እንደተገነዘብነው አመልካች የቆጠራቸው መስክር መሰማት ለውሣኔ አሰጣጥ ጠቃሚ እና አስፈላጊ መሆናቸውን ነው። በእርግጥ የተከሣሽ መከላከያ ማስረጃዎች ልቅ በሆነ መንገድ የሚቀርቡ ሣይሆኑ የሥነ-ሥርዓት ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት መሆን ይገባዋል። ስነ - ስርዓቱን ተከትሎ የሚቀርቡ ማስረጃዎችን ግን ያለ ሕጋዊ ምክንያት ውድቅ ማድረግ የተከሣሹን የመከላከል መሠረታዊ መብት የሚያጣብብ ነው።

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 116 ስለምስክሮች መጥሪያ አሠጣጥ ሲገለጽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 118 ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ ሁሉ ለተከሣሾች መጥሪያ ስለመስጠት በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት የሚፈፀም ቢሆንም ከቁጥር 103 እስከ 105 የተመለከቱት ድንጋጌዎች ግን ተፈፃሚ እንደማይሆኑ ያመለክታል። የሥር ፍ/ቤት አመልካች ለቆጠራቸው ምስክር የተላከው መጥሪያ ምስክሩ ባለመገኘታቸው ሲመለስ በቃለ መሐላ መረጋገጥ ነበረበት በማለት ለምስክሩ ድጋሚ መጥሪያ እንዳይላክ መከልከሉን ተገንዝበናል።

በእርግጥ ለተከሣሹ መጥሪያ በሚላክበት ወቅት መጥሪያ ሰጪው ተገቢውን ፍለጋ አድርጎ ተከሣሹን ማግኘት ያልቻለ ከሆነ መጥሪያ መስጠት ያልቻለበትን ምክንያት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መመለስ እንዳለበት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.103 ያመለክታል። በመሆኑም መጥሪያ በድጋሚ ለተከሣሽ የሚላከው መጥሪያ ሰጪው የተከሣሹን አለመገኘት በቃለ መሐላ አረጋግጦ መጥሪያውን ሲመልስ ነው። ከፍ ሲል እንደተገለፀው ለምስክር የሚሰጥ መጥሪያ አደራረስ ለተከሣሽ በሚላክበት ዓይነት ቢሆንም ይህ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 103 ግን በምስክር ጉዳይ ላይ ተፈፃሚነት እንደማይኖረው በሥነ ሥርዓት ሕጉ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ምስክሩን ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ መጥሪያው በግድ በቃለ መሐላ በተደገፈ አቤቱታ ካልተመለሠ በቀር በድጋሚ መጥሪያ ሊላክ አይገባም የሚባልበት የሕግ መሠረት የለም።

በሌላ በኩል ግን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 118/2/ሀ/ ሥር እንደተመለከተው እንዲቀርብ የተፈለገው ምስክር ለጉዳዩ አወሣሰን ጠቃሚ ከሆነ ፍ/ቤቱ የተላከው መጥሪያ ለባለአድራሻው በሚገባ ያልደረሰው መሆኑን አረጋግጦ ባለጉዳዩ ተገቢውን ኪሣራ ከፍሎ መጥሪያ እንዲወስድ ማድረግ አለበት። በተያዘው ጉዳይም አመልካች የሥራ ውሉ ተቋረጠ የሚለው ተጠሪው መኪናውን ገዙ ከተባሉት ግለሰብ ጋር ስራ በመጀመሩ በሥራ መደቡ ላይ ባለመገኘቱ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ መረጋገጡ ለውሣኔው አስፈላጊ ነጥብ መሆኑ አያጠያይቅም። ስለሆነም ይህንን እውነታ ያስረዳሉ የተባሉት ምስክር መጥሪያ ያልደረሣቸው መሆኑ ከተረጋገጠ በድጋሚ እንዲደርሣቸው አስፈላጊ ይሆናል። በቀጠሮ መለወጥ ምክንያት በተጠሪ ላይ የሚደርስ መጉላላት ካለም ፍ/ቤቱ አመልካች ተገቢውን ኪሣራ እንዲከፍል ለማዘዝ ይችላል እንጂ ለምስክር ስለሚደረስ መጥሪያ ተፈፃሚነት በሌላው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 103 መሠረት መጥሪያው ያልደረሰበት ምክንያት በቃለ - መሐላ መደገፍ ነበረበት በሚል የአመልካች ጥያቄ ውድቅ መደረጉ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው።

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24475 በ23/5/2000 ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63168 በ21/06/2000 የተሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ አመልካች የቆጠሯቸው መኪናዋን ገዝተዋል የተባሉት ምስክር መጥሪያ ደርሷቸው ምስክርነታቸውን ከሰጡ በኋላ ተገቢ ነው ያለውን ውሣኔ እንዲሰጥ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተመልሷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 36412

ጥቅምት 13 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ተስፋሁን ዋኘው - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** በጅያክ አግሮ ኮሜርሻያል ኢንተርፕራይዝ - ተወካይ ሙላት ታግሎ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካችና በሌላ ግለሰብ ላይ መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በሰሜን ጎንደር አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረተው የንብረት ጉዳት ካሣ ክስ ነው፡፡ የክሱ ሂደት ቀጥሎም አመልካች የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ይዘው አለመቅረባቸውና ክሱ በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮም አለመቅረባቸው ተረጋግጧል ተብሎ ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ብይን ከተሰጠ በኋላ አመልካች በሌሉበት ክርክሩ እንዲታይ የተሰጠው ብይን ተነስቶ ወደ ክርክሩ ገብተው ለመከራከር እንዲፈቀድላቸው አለኝ ያሉትን ምክንያት ገልፀው ጥያቄ ቢያቀርቡም የስር ፍ/ቤት ሣይቀበላቸው ቀርቶ በመጨረሻም በአሁኑ ተጠሪ የቀረበለትን ክስ እና ማስረጃ መርምሮና ተገቢ ነው ያለውን ማስረጃ ሁሉ በማስቀረብና በመመልከት የአሁኑን አመልካችና አንድ ላይ ተከሦ የነበረውን ግለሰብ ለንብረት ጉዳቱ አላፊ በማድረግ የብር 70,500.00 /ሠባ ሺህ አምስት መቶ/ ካሣ በአንድነትና በነጠላ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኑ አመልካች ይግባኛቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል ያሉበትን ምክንያት ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የፍ/ቤቱ መጥሪያ ደርሶ ያልቀረቡት በውሃ ሙላት ምክንያት መሆኑን፣ በብይኑም ሆነ በዋናው ውሣኔ ላይ በአንድነት ይግባኝ የመጠየቅ መብት በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተጠበቀላቸው ሆኖ እያለ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ በዋናው ውሣኔ ላይ ብቻ ይግባኝ እንደቀረበ በመቁጠር መወሰኑ ከጭብጡ ውጭ መሆኑን በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካችን በብይኑ ላይ በይግባኝ ሣትመጣ በፍሬ ነገሩ ላይ ይግባኝ ማለት አትችልም ሲል ይግባኙን አለመቀበሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ተጠሪ ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርቧል፡፡ የመልሱ ይዘትም በአጭሩ የሚሞላ ውሃ የተባለው ሐሰት መሆኑንና ይልቁንም የመኪና መንገድ ያለ መሆኑን ይግባኙ የቀረበውም በዋናው ጉዳይ ላይ መሆኑንና መጥሪያውም በጊዜው የደረሰ መሆኑን በመግለጽ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት መከራከሩን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ይህንኑ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ትእዛዝ፣ ከግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ የቀረበውን የአመልካችን ይግባኝ

ያለመመርመሩ አግባብነት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉን የተከተለ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ክርክሮች የሚመሩት በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ መሠረት ነው፡፡ ይኸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ አካቶ ከያዛቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የተከራካሪ ወገኖች በክርክሩ ወቅት ያለመቅረብና ውጤቱ ነው፡፡ በዚህም መሠረት መጥሪያ ተልኮለት በተገቢው መንገድ የደረሰው መሆኑ በተረጋገጠበት ተከሣሽ ላይ ፍ/ቤቱ ሊክተለው የሚገባው ሥርዓት ጉዳዩ ተከሣሹ በሌለበት የሚሰማበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 70/ሀ/ ስር ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ መንፈስ የሚያሣየውም በፍ/ቤቱ መጥሪያ መሠረት ያልቀረበ ተከሣሽ በክርክሩ ሂደት ለማንሣት የሚችላቸውን የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ክርክሮች እንዲሁም በማስረጃ አሰማም ሂደት የመስቀለኛ ጥያቄ የማንሣት መብቱን ሣይጠቀም የሚቀር መሆኑን ነው፡፡ ለተከሣሽ እነዚህ መብቶች የሚቀሩ ሆነው በከሣሽ በኩል የቀረበው ክስ ተያይዘው ከቀረቡት ማስረጃዎች ጋር ተመርምሮ እና በጉዳዩ ላይ መፈፀም ያለበት ሌላ አስፈላጊ ሥርዓት ሁሉ ከተፈፀመ በኋላ ተገቢ ውሣኔ መስጠቱ ፍ/ቤቱ ሊያከናውነው የሚገባው ተከታዩ ሂደት ነው፡፡ ሌላው በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከተው ሥርዓት ተከሣሹ ሊከተለው የሚገባው መፍትሔ ነው፡፡ ክርክሩ በሌለበት እንዲቀጥል የተደረገበት ተከሣሽ በተከታዩ ቀነ ቀጠሮ ቀርቦ በቂ ሆኖ በሚገመት እክል ምክንያት በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ ያለመቅረቡን ካስረዳ መከላከያውን አቅርቦ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.72 ያስገነዝባል፡፡ እንዲሁም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ አንድ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ከሆነ ውሣኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትእዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት የማመልከት መብት እንዳለው ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በእነዚህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች መሠረት አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ተከሣሽ በተከታዩ ያለው የሥነ-ሥርዓት መፍትሔ ምንድነው ነው? ወደክርክሩ ልግባ ወይም በሌለሁበት የተሰጠው ውሣኔ ይነሣልኝ የሚለው ጥያቄ ውድቅ ሲሆንበት በዚሁ ይግባኝ ማቅረብ ወይስ በዋናው ጉዳይ ውሣኔ እስኪሰጥ ድረስ በመጠበቅ በሁሉም ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ? የሚሉት ጥያቄዎች የሥነ-ሥርዓት ሕጉን በመመልከት ግልጽ ድንጋጌ ማግኘትና ምላሽ ለመስጠት የሚቻልባቸው ባይሆኑም የውሣኔ አሰጣጥና የይግባኝ አቀራረብ ሥርዓትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን በመፈተሽ ግን ምላሹን ለማግኘት አስቸጋሪ የሚሆን አይደለም፡፡

በዚህም መሠረት ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ የተሰጠበት ተከሣሽ ከላይ በተገለፁት የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች አቤቱታውን አቅርቦ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት ካላገኘ በዚሁ ብይን ላይ ቅሬታውን ለበላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ከማሣየት የሚከለክለው የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ አለመኖሩን የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የሚደነግጉት ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ እስከሚሰጥ ድረስ ተከሣሹ ጠብቆ በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር አጠቃልሎ ይግባኝ ሊያቀርብ ይገባል ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከይግባኝ አቀራረብ የጊዜ ገደብ ሥርዓት ጋር ሊጣጣም የማይችልበት ሁኔታ ከመኖሩም በላይ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ እስኪሰጥ ተጠብቀው በዋናው ጉዳይ ላይ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር ተጠቃልለው ይግባኝ ሊቀርብባቸው ይችላል ተብለው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 320 ንዑስ ቁጥሮች ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በባህርያቸው ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸው ሆነው መሠረታዊውን መብት ሊያጣብቡ የማይችሉ ከመሆናቸው ጋር ተዳምሮ ሲታይ የይግባኝ መብት የሚከለክል ሥርዓት የለም፡፡ አንድ ተከራካሪ ወደ ክርክሩ ገብቶ እንዲሣተፍ እድል መስጠት የሕግ ሥርዓት የግድ የሚለው ሲሆን ይህንን ዕድል መንፈግ መሠረታዊውን መብት ማጣበብ በመሆኑ ቅሬታ ያለው ወገን በይግባኝ ሥርዓት ጥያቄውን አቅርቦ ጉዳዩ እንዲታይለት ማድረግ መብቱ ነው፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስም አመልካች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ትእዛዝ እንዲነሣላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ሲያጣ በዚሁ ነጥብ ብቻ ቀደም ብለው ይግባኛቸውን ለበላይ ፍ/ቤት ሣያቀርቡ በዋናው ጉዳይ ውሣኔ ሲሰጥ ግን ይግባኛቸውን አቅርበዋል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም አመልካች ጉዳዩ ባለሁበት ይታይልኝ በሚል ጥያቄ ሲያቀርቡ ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም ተብሎ ብይን ሲሰጥ በዚሁ ብይን ላይ ይግባኝ ብለው መምጣት ሲገባቸው ውሣኔ ሲሰጥ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ብለው መምጣታቸው ሥነ-ሥርዓታዊ አይደለም በሚል ምክንያት ፍሬ ጉዳዩን ሣይመረምር መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ አመልካች በዚህ የሠበር ችሎት የሚከራከሩት ወደ ክርክሩ ሊገቡ አይገባም የተባለው ያላግባብ መሆኑንና በይግባኝም በዚሁ ነጥብና በዋናው ጉዳይ ወደ በላይ ፍ/ቤት ከመሄድ

የሚከለክል ሥርዓት የለም በሚል ነው፡፡ ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ወደ ክርክሩ አይገቡም የተባለው ባግባቡ መሆኑንና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡትም በዋናው ጉዳይ ላይ ብቻ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡

የአመልካች ወደ ክርክሩ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገው በቂ ምክንያት እያለኝ ነው በማለት ያቀረቡት ጥያቄ በሥነ-ሥርዓት ሕጉ መመዘኛው ምን እንደሆነ በግልጽ ያልተመለከተ ሲሆን ባለው አሠራርም ፍ/ቤት የሚቀርብለትን ማስረጃ በመመርመርና የራሱን የህሊና ሚዛን መሠረት በማድረግ ሊያስተናግደው የሚችለው በመሆኑ በዚህ ረገድ የሚደርሰው ድምዳሜ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ በሠበር ችሎት ሊታረም የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካችን ክርክር የምንቀበለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በዚህ ችሎት ሊታይና ምላሽ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ አመልካች በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

አመልካች ወደ ክርክሩ ለመግባት ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት ካጡ በኋላ ጉዳዩ በሌሉበት ታይቶ ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡ ለጉዳዩ አግባብነት ሊኖረው የሚችለው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 78/1/ ነው፡፡ የዚህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ የአማርኛና የእንግሊዝኛው ትርጓሜ ሙሉ ይዘቱ ቀጥሎ የሠፈረው ነው፡፡ ይኸውም

«<u>ቁ.78 ተከሣሽ በሌለበት የተሰጠውን ውሣኔ ስለማንሣት</u>

1/ አንድ ተከሣሽ በክርክሩ ላይ ቀርቦ መልስ ሣይሰጥ ወይም ተገቢውን መከራከሪያ ሣያቀርብ በመቅረቱ በሌለበት አንድ ውሣኔ ወይም ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ውሣኔው ወይም ትእዛዙ መሰጠቱን በተረዳው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቀርቦ ትእዛዙ ወይም ውሣኔው እንዲነሣለት ሊያመለክት ይችላል፡፡»

**«Art. 78- <u>Setting aside decree ex-parte against defendant</u>**

> **1. Any defendant against whom a decree is passed or order made ex-parte or in default of pleading <u>may,</u> within one month of the day when he became aware of such decree or order, apply to the court by which the decree was passed or order made for an order to set it aside.»**

ከእነዚህ ትርጓሜዎች መረዳት የሚቻለው በድንጋጌው መሠረት ጥያቄ የማቅረብ ምርጫ የተከሣሹ ሆኖ አስገዳጅነት የሌለው ሥርዓት መሆኑን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 72 መሠረት ጥያቄ አቅርቦ ተቀባይነት ያጣ ተከሣሽም በዚሁ ነጥብ ብቻ ይግባኝ ማቅረብ ያለማቅረቡ ምርጫው ነው፡፡

በሌላ አገላለጽ ተከሣሹ ወደ ክርክሩ ልግባ በማለት ወይም በሌለሁበት የተሰጠው ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ይነሣልኝ ብሎ ጥያቄ ማቅረብ ወይም ይህንኑ በመተው ለበላይ ፍ/ቤት የይግባኝ አቤቱታ የማቅረብ ምርጫው በሥነ-ሥርዓቱ የተተወለት መብት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ለበላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ በተሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ሲያቀርብ የይግባኝ አቀራረብ አድማሱ በተወሰኑት ነጥቦች ላይ ብቻ መሆን እንዳለበት የይግባኝ አቀራረብን በተመለከተ የተደነገጉት ድንጋጌዎች መንፈስ ያስረዳል፡፡ እንደሚታወቀው የፍትሐብሔር ሙግት አካሄድ ሥርዓታችን በተከራካሪ ወገኖች መነሣት ያለባቸው የክርክር ነጥቦች እንዳሉ ያሣያል፡፡ በክርክሩ ሂደት ተነስተው በፍ/ቤቱ ተገቢ ያልሆነ ውሣኔ ተሰጠብኝ የሚለው ወገንም ነጥቡን ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ የይግባኝ ቅሬታ ነጥብ መሆን ያለበት ግን በበታች ፍ/ቤት የተነሣ ነጥብ እንጂ አዲስ ሊሆን እንደማይገባ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 329/1/ ያሣያል፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ የተወሰነበት ተከሣሽ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሲያቀርብ ሊኖር የሚችለው በስር ፍ/ቤት በተከራካሪነት ቀርቦ ያላነሣውን ነጥብ እንዳያነሣ ነው ከሚባል በስተቀር ሙሉ በሙሉ ይግባኝ ሊያቀርብ አይችልም የሚባልበት ሥርዓት የለም፡፡ እንደዚህ ዓይነት ተከራካሪ በፍ/ቤቱ የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ክሱን፣ የማስረጃዎችን አግባብነት፣ ተቀባይነት እና ጥንካሬ ባግባቡ ያላገናዘበ ሁኔታ አለ የሚል ከሆነ ይግባኝ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ፍ/ቤቱ የከሣሽ ክስ ተከሣሽ በሌለበት ስለታየ ብቻ የተጠየቀው ዳኝነት ይሰጣል ተብሎ የማይጠበቅ ስለመሆኑ የዳኝነት አሰጣጥ ሥርዓት ያስገነዝባል፡፡ ፍ/ቤት ከሣሹ ያቀረበውን ክስ አባሪ ሆነው ከቀረቡት ማስረጃዎች አግባብነት፣ ተቀባይነትና ጥንካሬ አኳያ በመመርመር ተገቢውን ዳኝነት መስጠት የእለት ተዕለት የሥራ ድርሻው ነው፡፡ በዚህ አኳኋን ታይቶ የተሰጠ ውሣኔ አይደለም የሚል ተከሣሽ በክርክሩ ሂደት ተሣታፊ ያልነበረ ቢሆን አዲስ ክርክር ከማንሣት በመለስ የይግባኝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በዋናው ጉዳይ ላይ ያቀረቡት ይግባኝ ሣይመረመር የተዘጋው ጥያቄያቸውን የሚከለክል ግልጽ ሥርዓት በሌለበት ሁኔታ በመሆኑ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16249 መጋቢት 03 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች ወደ ክርክሩ ሊገቡ ጥያቄ አቅርበው ተቀባይነት ካጡ በኋላ በሌሉበት ጉዳዩ ታይቶ በተሰጠው ውሣኔ ፍ/ቤቱ በሕጉ መሠረት ውሣኔ አልሰጠም በሚሉ ነጥቦች ተወስነው በፍሬ ጉዳዩ ላይ ይግባኝ ለበላይ ፍ/ቤት ከማቅረብ የሚከለክላቸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌ የለም ብለናል፡፡

3/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች ይግባኝ ማቅረብ የሚችሉ መሆኑን ተገንዝቦ ፍሬ ጉዳዩን በመመርመር በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

4/ በዚህ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 36380

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረፈጅ አቶ አደም ንጉሴ ቀረቡ

**መልስ ሰጭ፡-** አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅ - ቀርበዋል፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለውሳኔ ሲሆን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የዚህ የሰበር አቤቱታ መነሻ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን በይግባኝ እያከራከረ እያለ ይግባኝ ባይ የነበረው የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ ይግባኙን ለመስማት በተቀጠረበት እለት አልቀረበም፡፡ መልስ ሰጭ የነበረው አቶ ታረቀኝ ገ/ፃዲቅም ክዶ ተከራክሯል፡፡ ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ በማለት የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ/መ/ቁ. 60818 ላይ የሰጠው ትእዛዝ ነው፡፡

የአሁን አመልካች የተዘጋው መዝገብ ተንቀሳቅሶ ጉዳዩ እንዲታይለት ለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ በዚያው መዝገብ የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት መዝገቡ ይንቀሳቀስ ዘንድ ይግባኝ ባይ ያቀረበው ምክንያት በቂ ባለመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት ያለው አይደለም በማለት አሰናብቶታል፡፡

ይህ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት መዝገቡን ለመዝጋትም ሆነ የተዘጋው መዝገብ እንደገና ሊንቀሳቀስ አይገባውም ሲል የሰጠው ዳኝነት መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በሚል ክርክሩን ዘርዝሮ በማቅረቡ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በበኩሉ መዝገቡ ለቃል ክርክር ተቀጥሮ በነበረበት እለት ይግባኝ ባይ ያለመቅረቡን በመገንዘብ የተሰጠው ትእዛዝ ተገቢ ነው፤መዝገቡን መልስ ለመቀበልና የቃል ክርክር ለመስማት በሚል መቀጠር የሚፃረረው የሥነ-ሥርአት ሕግ ባለመኖሩ የሥር ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ይጽናልን ሲል ተከራክሯል፡፡

እኛም ሁለቱም ወገኖች በሰበር ደረጃ ያቀረቡትን ክርክር ከይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የይግባኝ መዝገብ ግልባጭ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

የአሁን አመልካች በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ይግባኝ ባይ በመሆን የአሁን መልስ ሰጭ ደግሞ በመልስ ሰጭነት ተሰይመው በሚከራከሩበት ጉዳይ መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተቀጥሮ የነበረው የግራ ቀኙን ክርክር ለመስማት እና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ ለመቀበል በሚል እንደነበረ በዚሁ እለት ፍ/ቤቱ በመዝገቡ ላይ ካሰፈረው ለመረዳት ተችሏል፡፡

በዚሁ እለትም ግራ ቀኙ መቅረባቸውን ለማረጋገጥ ጥሪ በተደረገላቸው ጊዜ ይግባኝ ባይ ሊቀርብ እንዳልቻለም የተካደ ጉዳይ አይደለም፡፡

ይሁን እንጂ በተያዘ ቀጠሮ የቃል ክርክር ማድረግና የመልስ ሰጭን የጽሑፍ መልስ መቀበል በክርክር አካሄድ ሁለቱም እራሳቸውን የቻሉ ሥርአቶች እንጂ አንዱ ሌላውን ሊተካ የሚችል ወይም ደግሞ ተመሳሳይ የክርክር ደረጃዎች አይደሉም፡፡ የሁለቱም ሥርአት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት የተለያየ ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ አኳኋን ከማዘዙ በፊት ግልጽ በሆነ አኳኋን መዝገቡ ለምን እንደተቀጠረ ለይቶ አለማዘዙ በጉዳዩ አመራር የተፈፀመ ስህተት ነው፡፡

በተለይም የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም ከነበረው ቀጠሮ በፊት መዝገቡ ለቃል ክርክር በሚል ተቀጥሮ እያለ መልስ ሰጭ ጊዜ አጥሮኛል በማለት ባመለከቱት መሰረት ተለዋጭ ቀጠሮው ለየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሆን ተደርጓል በማለት አመልካች ላቀረበው ክርክር መልስ ሰጭ ይህንኑ አላስተባበለም፡፡ ይህም ከሆነ ከየካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፊት በነበረው ቀጠሮ መልስ ሰጭ ቀርቦ የቃል ክርክር ማድረግ እየቻለ ቀጠሮ አጥሮብኛል ማለቱ በተከታዩ ቀጠሮ ክርክሩን በጽሑፍ ለማቅረብ እንደፈለገ ስለሚያመለክት መዝገቡ ለየካቲት 14 ቀን ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ ነበር ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በመሆኑም ከላይ እንደተገለፀው በአንድ ቀጠሮ የቃል ክርክር እና የጽሑፍ መልስ ፣መልስ ሰጭ እንዲያቀርብ ብሎ ማዘዙ ሥነ-ሥርአታዊ ካለመሆኑም በላይ መዝገቡ ተቀጥሮ የነበረው የቃል ክርክር ለማድረግ እንደሆነ በግልጽ ያልተመለከተ ስለሆነ ይግባኝ ባይ በቀጠሮው እለት አልቀረቡም እንኳ ቢባል ስለጉዳዩ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ተፈፃሚነት ያለው አይደለም፡፡

የይግባኝ ባይ በቀጠሮው የመቅረብና ያለመቅረብ ጉዳይ ፍ/ቤቱ እንደጀመረው የክርክሩ አቅጣጫ መልስ ሰጭ ላቀረበው የጽሑፍ ክርክር የበኩሉን የመልስ መልስ ለማቅረብ መቻሉ ወይንም ለማቅረብ ያለመቻሉ ጉዳይ ነው፡፡

የአሁን አመልካች መዝገቡ መታየት በጀመረበት እለት በመዝገብ መደራረብ ምክንያት በሌላ ችሎት በመጠራቱ እንጂ በፍ/ቤቱ ቅጥር ግቢ ይህንኑ ጉዳይ እየተከታተልኩ ነበር የሚለው ክርክሩ በማስረጃ ከተረጋገጠ የመልስ መልሱን የማቅረብ መብቱን ለማስጠበቅ እንጂ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 74 ጋር ሊገናኝ የሚችል አይደለም፡፡

ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 339 እንደተደነገገው የይግባኝ ክርክሩን ለመስማት ሊከተል ከሚችለው ሥርአት አንዱን ለይቶ መከተል ሲገባው በአንድ ጊዜ ሊፈፀሙ የማይችሉትን ሥርአቶች አቀላቅሎ እንዲፈፀም በማዘዙ ምክንያት እና ከሁለቱ ሥርአቶችም መዝገቡ የተቀጠረው መልስ ሰጭ የጽሑፍ መልሱን ለማቅረብ በሚል ነው የሚለውን ነጥብ የመዝገቡ ግልባጭ ስለሚያስረዳ መዝገቡ የተቀጠረው የቃል ክርክር ለማድረግ በሚል ነው፤ በዚሁ እለትም ይግባኝ ባይ አልቀረቡም፤መልስ ሰጭም ክዶ ተከራክሯል የሚለውን መነሻ በማድረግ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሰረት ተዘግቷል ሲል የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሥነ- ስርአት ህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 60818 የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም እና የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጣቸው ትእዛዞች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ቀጠሮ በእራሴ ጉድለት ምክንያት ሳይሆን በቀጠሮ መደራረብ ነው የሚለው ክርክሩ ከቀረበው ማስረጃ አኳያ ታይቶ ተከታዩ ሥርአት (የመልስ መልስ የማቅረብ መብቱ) ይጠበቅለት እንደሆነ አስፈላጊው እንዲፈጸም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37725

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. በቀለ ዲሪብሣ ቀረቡ፡፡

2. ወ/ሮ ደስታ ከፈኔ - ተወካይ ተስፋዬ በቀለ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** የምክር በሪሁን - ጠበቃ አቶ ጌትነት የሻነህ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የቀረበው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ/መ/ቁ. 10906 የሰጠው ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66589 ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ግንቦት 7 ቀን 2000 ዓ.ም የሰበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ በአመልካቾች እና በሌሎች ሁለት ሰዎች እንደዚሁም በአዲስ አበባ ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ላይ ክስ መስርቶ ሕጋዊ ውሣኔ አሰጥቻለሁ በማለት ያቀረበው የአፈፃፀም ክስና ክርክር ነው፡፡ የክርክሩም ፍሬ ጉዳይ ተጠሪ ያቀረበው የቤት ሽያጭ ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ሲሆን የክርክሩ ይዘትም የአሁን አመልካቾች ለወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መጋቢት 18 ቀን 1984 ዓ.ም በተፃፈ ውል በአዲስ አበባ ወረዳ 17 ቀበሌ 12/13 ቁጥሩ 552 የሚገኘውን ቤት ሸጠው ይህንኑ ቤት ተጠሪ ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ግንቦት 21 ቀን 1989 ዓ.ም የገዛሁት ስለሆነ ቤቱን እንዲያስረክቡኝ በስሜ እንዲያዞሩ የሚል ክስ ሲያቀርብ እነ በላይነሽ ካሣዬም በአመልካቾች ላይ ክስ ያቀርባሉ፡፡

የአሁን አመልካቾች በሕግ በሚፀና አኳኋን ለወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ቤት አልተሸጠም፤ ተጠሪም ከእኛ ጋር የገባው ውል ስለሌለ ክስ ሊያቀርብብን አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን ጉዳዩ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ከዚያም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ ቀርቦ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጠሪ አመልካቾችን የሚጠይቅበት ምክንያት እንደሌለ በመግለጽ እንደውሉ ሊፈጽሙ አይገደዱም በማለት በመዝገብ ቁጥር 76720 ኅዳር 13 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአፈፃፀም ክስ አቅርቦ ፍርድ ቤቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ የሻረው በመዝገብ ቁጥር 25551 መጋቢት 29 ቀን 1998 የሰጠውን ውሣኔ ነው፤ ይፈፀም የተባለው መስከረም 2 ቀን 1999 ዓ.ም በመዝገብ ቁጥር 15170 የተሰጠ ውሣኔ ነው፤ ስለዚህ አፈጻጸሙ ይቀጥል የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በይግባኝ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኙን በፍታብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡

አመልካቾች የከፍተኛው ፍርድ ቤት እንደ ውሉ ሊፈጸም ይገባል በማለት የሰጠው ፍርድ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ተሽሯል፤ ተጠሪ ቤት ሸጣልኛለች የሚላት ወ/ሮ በላይነሽ በቤቱ ላይ መብትና ይዞታ የሌላት መሆኑና ውሉም አስገዳጅነት እንደሌለው ተረጋግጧል፤ ከዚህ በኋላ በአፈፃፀም ቤቱን ለተጠሪ እንድናስረክብ የተሰጠው ትእዛዝ በፍርድ የተሻረና የማይፀና ውሣኔን ለማስፈፀም የተሰጠና መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት ሊሻር ይገባዋል በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሻረው አመልካቾች ከወ/ሮ በላይነሽ ጋር ተከሳሽ መሆን የለባቸውም በማለት ነው፤ ፍርድ ቤቱ እነ ወ/ሮ በላይነሽን አስመልክቶ የተሰጠውን ውሣኔ አልሻረም፤ እኔ የአፈፃፀም ፋይል የከፈትኩት በወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ እና በአቶ ጉልላት ሞላ ብቻ ላይ እንጅ በአመልካቾች ላይ አይደለም፤ ስለዚህ በሥር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም፤ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካቾች የአፈፃፀም ትእዛዝ የተሰጠበት ጉዳይ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት በግልጽ የተሻረ ነው፤ ስለዚህ የተሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረታዊ ስህተት አለበት የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

በሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪ የአፈፃፀም ክስ ያቀረበበት ቤት የአመልካቾች ንብረት የሆነና፣አመልካቾች ለበላይነሽ ካሳዬና ለአቶ ጉልላት ሞላ ሸጠውት እነ ወ/ሮ በላይነሽ ለእኔ ሸጠውልኛል የሚለው ቤት ነው፡፡ አመልካቾች ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ጋር በሕግ የፀና የቤት ሽያጭ ውል የለንም የሚል ክርክር ያነሱ ሲሆን በአፈፃፀሙ ቤቱን እንዲለቁና ለተጠሪ እንዲያስረክቡ እየተገደዱ ያሉት እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ሣይሆኑ አመልካቾች ናቸው፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመረምረው ተጠሪ በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ላይ አስወስኛለሁ በሚል ፍርድ መነሻ አመልካቾችን በአፈፃፀም ለማስገደድ ይችላል ወይስ አይችልም? የሚለው ነጥብ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ተጠሪ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ለእሱ ቤት የሸጡለት መሆኑን በፍርድ ቢያረጋግጥ እንኳን የቤቱ ስመ ንብረት እና ይዞታ በአመልካቾች ስም በመሆኑ በፍርድ ሊያስፈጽመው የሚችል ውሣኔ የለም፡፡ ምክንያቱም በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ እና በተጠሪ መካከል የቤት ሽያጭ ውል አለ መባሉ ብቻውን ተጠሪ ገዝቸዋለሁ የሚለውን ቤት ለመረከብ እና ስመ ንብረቱን ለማዛወር የሚያስችል መብት አያሰጠውም፡፡ ተጠሪ የቤቱ ስመ ንብረት እና ይዞታ እንዲዛወር ለማድረግ የሚችለው እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ የሸጡለት የራሳቸው ንብረት የሆነ ቤት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ ለእኔ ሸጠውልኛል የሚለው ቤት ስመ ንብረቱም ሆነ ይዞታው በአመልካቾች ስም ያለ ነው፡፡ ተጠሪ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ቤቱን የሸጡልኝ ከአመልካቾች ገዝተውት ነው የሚል ክርክር እና ክስ ቢያቀርብም በአመልካቾች እና በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መካከል በሕግ የፀና የቤት ሽያጭ ውል የለም በማለት አመልካቾች ክደው ተከራክረዋል፡፡ በዚህ ጭብጥ ላይ ቤቱን ገዝተዋል የተባሉት በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ በአመልካቾች ላይ የውል ይፈፀምልን ክስ አቅርበው በፍርድ የተረጋገጠ መብት አላገኙም፡፡

በመሆኑም በመጀመሪያ በአመልካቾችና በእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ መካከል በሕግ የሚፀናና አመልካቾች የባለቤትነትና የይዞታ መብታቸውን እንዲለቁ የሚያስገድድ ውል ያለ ስለመሆኑ ውሣኔ ባላገኘበት ሁኔታ ተጠሪ እነ በላይነሽ ካሣዬ ከአመልካቾች የገዙትን ቤት ለእኔ ስለሸጡልኝ በውሉ መሰረት ይፈፀምልኝ የሚል ክርክር በማቅረቡ ብቻ አመልካቾች ንብረታቸውን ለተጠሪ ለቅቀው እንዲወጡ ትእዛዝ የሚሰጥበት ምክንያት የለም፡፡

ይህንንም ነጥብ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍትሀብሔር ይግባኝ መዝገብ ቁጥር 25551 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቶበታል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በውሣኔው አመልካቾች ከእነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ጋር አድርገውታል ስለተባለው የቤት ሽያጭ ውል በተመለከተ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት የሌለው መሆኑን በግልጽ ካሰፈረ በኋላ አመልካቾች ተጠሪ ካቀረበባቸው ክስ ጋር ተያይዞ እንደውሉ እንዲፈጽሙ አይገደዱም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተጠሪ በይግባኝ እልባትና ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ የተሰጠው ውሣኔ ስህተት አለበት የሚል ከሆነ ለሰበር ሰሚ ችሎት ከሚያቀርብ በስተቀር እነ በላይነሽ ካሣዬን ነጥሎ በመክሰስ በተዘዋዋሪ መንገድ የአመልካቾችን ቤት ለመረከብ የተከተለው የክርክር ስልት ተገቢ አይደለም፡፡ አፈፃፀሙን የያዘውም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካቾች ለተጠሪ ቤቱን እንዲያስረክቡ ሊገደዱ የማይገባ መሆኑን በግልጽ በማስፈር የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠበትን ጉዳይ ወደ ጐን በመተው በአፈፃፀም ተከሳሽ እነ ወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬ ናቸው የሚል ምክንያት በመስጠት አመልካቾች ቤታቸውን ለተጠሪ አስረክበውና ለቅቀው እንዲወጡ የሰጠው ትእዛዝ ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠውን ግልጽ ውሣኔ ዋጋ የሚያሣጣና የሚሽር በመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ሥርአትን የሚጥስና የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሣኔ ገዥነትና የበላይነትን የሚፃረር መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ትእዛዝ ነው

ብለናል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ይህንን ትእዛዝ የሕግና የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለበትም በማለት የአመልካቾችን ይግባኝ መሰረዙ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. ተጠሪ በወ/ሮ በላይነሽ ካሣዬና አቶ ጉልላት ሞላ ላይ ያስወሰነው ውሣኔ አልተሻረም በሚል ሰበብ አመልካቾች ቤቱን ለተጠሪ ለቅቀውና አስረክበው እንዲወጡ በመዝገብ ቁጥር 109064 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 66539 ሚያዝያ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 25551 ሚያዝያ 25 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በሰበር ሰሚ ችሎት ያልተሻረ ወይም ያልተሻሻለ ውሣኔ በመሆኑ ህጋዊ አስገዳጅነትና ተፈፃሚነት ያለው ውሣኔ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካቾች ቤታቸውን እንዲለቁና ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በአፈጻጸም መገደድ የለባቸውም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ተከራካሪዎች በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37105

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኃ.የተ.የግል ማህበር

መላኩ መለሰ /ነገረ ፡ ፈጅ/ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ሰሎሞን አበበ ኮከብ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል፤ ስለዚህ ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ እና ያልተሰጠኝ የዓመት ፈቃድ ተሰጥቶኝ ወደስራዬ እመለስ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ በተደነገገው መሠረት የስራ ውል ሊያቋርጥ የሚችል ጥፋት በመፈፀሙ ነው፤ ለአምስት የስራ ቀናትም በስራው ላይ ሣይገኝ ቀርቶአል በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ ተጠሪ የሦስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደሥራው ይመለስ፤ ለመጨረሻዎቹ ሁለት ዓመታት የሚገባውን የዓመት እረፍትም በማካካሻ እረፍት መልክ ይሰጠው በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ተጠሪ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ቢከራከርም፤ አመልካች ግን የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈፀመው የስራ ውልን የሚያቋርጥ ድርጊት ምክንያት ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ በአመልካቹ ክርክር እንደተገለፀው ተጠሪ የእምነት ማጉደል ወንጀል ፈጽሟል በሚል ተጠርጥሮ በፖሊስ ምርመራ ተደርጎበታል፡፡ የተጠሪ ስራ የሎደር ኦፕሬተርነት ሲሆን፤ 120 ሊትር ናፍጣ ወስዶ ለግል ጥቅሙ አውሏል በሚል ነው በፖሊስ ተይዞ ምርመራ ሊጣራበት የቻለው፡፡ በዚህ ምክንያት ታስሮ በፖሊስ ቁጥጥር ሥር የቆየ ሲሆን፣ ከተለቀቀ በኋላም ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ሥራው ላይ ሣይገኝ እንደቀረ በአመልካች ክርክር ተገልጿል፡፡ የእምነት ማጉደልን በተመለከተ አመልካች የቆጠረው ማስረጃ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ይህን የምርመራ መዝገብ አስቀርቦ አልተመለከተም፡፡ የፖሊስ የምርመራ መዝገብ በራሱ በቂ አስረጂ ሊሆን አይገባም በሚል ሣያስቀርበው እንደቀረ ከሰጠው ውሣኔ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራው ላይ አልተገኘም የሚለውን ክርክር በተመለከተም ፍ/ቤቱ በቂ የሆነ ማጣራት ሣያደርግ እንዳለፈው ነው ውሣኔው የሚያሣየው፡፡

በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተካደ ወይም ያልተማመኑበት የፍሬ ነገር ነጥብ የሚነጥረው በማስረጃ ነው፡፡ በግራ ቀኝ ተከራካሪ ወገኖች የተቆጠረው ለጉዳዩ አግባብነት ያለው ማስረጃ በአግባቡ መሰማት አንዱና ዋነኛው የፍርድ አመራር ስርዓት መሠረታዊ መርህ ነው፡፡ በእርግጥ በተከራካሪ ወገን የቀረበ ማስረጃ ሁሉ ያለምንም ምክንያት መሰማት አለበት ማለት አይደለም፡፡ የተቆረጠው ማስረጃ ለተያዘው ክርክር አግባብነት የሌለው ሆኖ ከተገኘ ውድቅ የሚደረገው እንዲሁ በደፈናው ሣይሆን፣ ምክንያቱን በግልጽ በጽሑፍ በማስፈር ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ/ቁ.138/፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው የስር ፍ/ቤቶች ወደ ውሣኔ ያመሩት በአመልካች የተቆጠረውን ማስረጃ አስቀርበው ሣያዩ እና ሣይመረምሩ ነው፡፡ ማስረጃው በፖሊስ ምርመራ የተደረገበት የምርመራ መዝገብ ሲሆን፣ ይህም ቢያንስ ተጠርጣሪው /ተጠሪ/ የሰጠው ቃል፣ ተፈፀመ ስለተባለው ወንጀል በተመለከተ የተሰሙ ምስክሮች፣ የመርማሪውን አስተያየት ወይም ግኝት እንደሚይዝ ይገመታል፡፡ አመልካች የምርመራ መዝገቡን በአስረጂነት የቆጠረውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ መገመት የሚያስቸግር አይደለም፡፡ በመሆኑም ፈራጅ የሆነው አካል (ፍ/ቤቱ) ይህን መዝገብ አስቀርቦ ሣይመለከትና ከተያዘው ጭብጥ ጋር አገናዝቦ ሣይመረምር ብቃት ያለው ማስረጃ አይደለም ወደሚለው መደምደሚያ ሊደርስ አይችልም፤ አይገባምም፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ያየነው ከስራ መቅረትን በተመለከተ የተነሣውን ክርክር ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት ይህን ነጥብ ያለፈው ተጠሪ የቀረው በፖሊስ ቁጥጥር ስር ስለነበር ነው በሚል ነው፡፡ እዚህ ድምዳሜ ላይ ሊደርስ የቻለበትን ምክንያት ግን በዝርዝር አልገለፀም፡፡ ተጠሪም በዚህ ድምዳሜ እንደማይስማማ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክር ገልጿል፡፡ ከስራ ቀረሁ የሚለው በመታሰሩ ምክንያት ሣይሆን፣ ታሞ ሐኪም ቤት ሲመላለስ /ሲታከም/ ስለነበረ ነው፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች ደምረን ስንመለከት ፍ/ቤቱ ወደ ውሣኔ ያመራው ምንም ዓይነት ማስረጃ ሣይሰማ እንደሆነ ነው፡፡ በግልጽ የቀረበን ክርክር በተቆጠረው ማስረጃ ወይም አግባብነት ባለው መንገድ ሣያጣሩ /ሣያነጥሩ/ መወሰን ደግሞ ዋነኛው መሠረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀም ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21629 ጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 60830 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ ቁ. 21629 ክርክሩ እንዲቀጥል በማድረግ እና በአመልካች የተቆጠሩትን ማስረጃዎች በመስማት ክርክሩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ውሣኔው ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡ ይፃፍ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37678

ኅዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ድራጋዶስ ጄ ኤንድ ፒ. ጆየንት ቬንቸር - ጠበቃ አቶ ዱቻ ፈለቀ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ሳባ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር ጠበቆች

1. ሲራጅ አብደላ
2. ድልነሣው ታደሰ አቶ ኒቆድሞስ ጌታሁን ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በግልግል ዳኝነት ጉባዔ ከተሰጠ ውሣኔ ጋር በተያያዘ የይግባኝ አቀራረብን የሚመለከት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥን እንደተመለከትነው አመልካች ከኢትጵያ መንገዶች ባለሥለጣን ጋር ከአዲስ አበባ እስከ ጅማ ድረስ ያለውን አውራ መንገድ የማሻሻያና መልሶ ጥገና ሥራ ለመሥራት ውል ተዋወሎ ከመንገድ ሥራ የተወሰነውን በንዑስ ሥራ ተቋራጭ /sub- contract/ ውል ለማሰራት በነበረው ፍላጎት ከተጠሪ ጋር የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል እንደተዋዋሉ በዚህም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል አንቀጽ 17 ላይ በውሉ አፈፃፀም ረገድ በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እንደሚወሰን በተስማሙት መሠረት በክፍያ አፈፃፀም ረገድ በመካከላቸው አለመግባባት በፈጠሩ ተጠሪ አቤቱታውን ግራ ቀኙ ለመረጡት የግልግል ተቋም አቅርቦ ተቋሙም በሚሰራበት የግልግል ደንብ /rules of procedure/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ የካቲት 3 ቀን 1999 ዓ.ም ውሣኔ መስጠቱን ተገንዝበናል፡፡

ከዚህ በኂላም የሥር ተከሣሽ የአሁን አመልካች የግልግል ጉባዔው በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ ይግባኝ ያቀረበው ይግባኝ ሊቀርብበት በሚችል ምክንያት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ጉዳዩን በመመርመር አለመግባባቱ በግልግል ዳኝነት እንዲታይ አስቀድሞ ግራ ቀኙ እንደተስማሙ፣ጉዳዩን በግልግል ዳኝነት የተመለከተውም ተቋም በአዋጅ ቁጥር 341/95 መሠረት ሥልጣን በተሰጠው አካል እንደተቋቋመ፣ ይግባኝ ባይ ጉባዔው ጉዳዩን እንዲመለከት ከፈቀደ በኂላም በክርክሩ ሂደት ሙሉ በሙሉ እንደተካፈለ፣ የግልግል ጉባዔው የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ እንደሌለውም የግልግል ጉባዔው በሚመራበት ደንብ ላይ እንደተመለከተና ይግባኝ ባይ ይህ የደንቡ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ቢከራከርም ግራ ቀኙ ወገኖች ወደ ግልግል ተቋሙ ሲሄዱ ተቋሙ ክርክሩን የሚመራበት የእራሱ ሥርዓት እንዳለው ስለሚታወቅ ይግባኝ ባይ በተቋሙ በመዳኘት እስከመረጠ ድረስ በተቋሙ አሠራር የማይገዛበት ምክንያት ስለሌለ በዚሁ መሠረት በግልግል ውሣኔው ላይ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎ በግልግል ደንቡ ላይ የተቀመጠውን እንደተቀበለው ስለሚቆጠር በዚህ ረገድ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ መብቱን ቀሪ ባደረገበት ሁኔታ ስለሆነ አግባብነት የለውም በማለት ይግባኙን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ሰበር ችሎቱ የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የግልግል ተቋሙ የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይበልበት ነው መባሉ ተጠሪ ባለበት ለሰበር ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍና በቃል አከራክሯል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን የሥነ-ሥርዓት ደንብ /rules of procedure/ እና እንደዚሁም በግራ ቀኙ ወገኖች የተደረጉ የተለያዩ መፃፃፎችን ለጉዳዩ አወሳሰን እንደሚረዳ በማመኑ ችሎቱ አስቀርቦ ተመልክቷቸዋል፡፡

የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በዚህ ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥም አመልካች ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረበው የይግባኝ አቤቱታ ይግባኝ የሚባልበት ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ የካቲት 25 ቀን 1996 ዓ.ም የንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውል ሲዋዋሉ በውሉ አፈፃፀም ረገድ አለመግባባት ሲፈጠር ይሄው አለመግባባት በአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ሥር በተቋቋመው የግልግል ተቋም ታይቶ እልባት እንደሚያገኝ መስማማታቸውን የተገነዘብን ሲሆን ይህን ተቋም /forum/ በመምረጥ ረገድ ስምምነት ስለመደረሱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

አመልካች አጥብቆ የሚከራከረው የግልግል ተቋሙን በመምረጥ ረገድ በመካከላችን ስምምነት ቢኖርም የግልግል ተቋሙ በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ ግራ ቀኛችን አልተስማማንም፡፡ የግልግል ተቋሙ የሚመራበት የግልግል ደንብ ላይ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ እንደማይባልበት ቢጠቀስም ይህ የደንቡ ቃል በሕገ መንግሥት የተረጋገጠን የይግባኝ መብትን የሚፃረር ከመሆኑም በላይ የግልግል ዳኞች በሚሰጡት ውሣኔ ላይ ከፍ/ቤት ይግባኝ ለማቅረብ ይቻላል ተብሎ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/1/ ላይ የተመለከተውንም የሚጋፋ ስለሆነ ተፈፃሚነት የለውም በማለት ነው፡፡

ተጠሪም በበኩሉ በንዑስ ሥራ ተቋራጭነት ውሉ መሠረት የተፈጠረውን አለመግባባት በአዲስ አበባ ንግድና ዘርፍ ማኅበራት ም/ቤት ሥር ለተቋቋመው የግልግል ዳኝነት ተቋም አቤቱታው ሲቀርብ ጉባዔው የተጠሪን ክስ እንደዚሁም የግልግል ተቋሙ የሚመራበትን ደንብ ለአመልካች በሸኚ ደብዳቤ እንዲላክና አመልካችም ስለ ደንቡ አንዳንድ ማከራከሪያ ከጠየቀ በኋላ ተቀብሎ የግልግል ጉባዔውን የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ የተከራከረ ሲሆን ይህም አመልካች ደንቡን ተቀብሎ ሙግቱን መቀጠሉን የሚያሣይ ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች በደንቡ ለመግዛት ሙሉ ፈቃድን ስለሰጠ የጉባዔው ውሣኔ ይግባኝ አይባልበትም ተብሎም በዚሁ ደንብ ላይ የተጠቀሰውንም እንደተቀበለው ይቆጠራል በማለት ይግባኙን ሣየቀበል መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

አመልካችና ተጠሪ አለመግባባትን በግልግል ለመፈታት በውል የመረጡት የአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት የግልግል ተቋም የሚመራበት የግልግል ደንብ የውል ክርክርን ለግልግል ስለማቅረብ በሚደነግገው አንቀጽ 1/1/ ሥር ተዋዋይ ወገኖች ውላቸውን በሚመለከት ለሚነሱ ማናቸውም አለመግባባቶችና ክርክሮች በአዲስ አበባ ንግድ ም/ቤት የግልግል ተቋም የግልግል ደንብ ውሣኔ እንዲያገኝ በጽሁፋቸው ሲስማሙ በዚሁ መሠረት እነዚህ አለመግባባቶች በተቋሙ የግልግል ደንብ ውሣኔ እንደሚሰጣቸው መደንገጉን ተገንዝበናል፡፡

በዚህ የግልግል ደንብ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ሁለቱ ተከራካሪ ወገኖች ወደዚህ የግልግል ተቋም ሲሄዱ የግልግል ተቋሙ ግራ ቀኙን ማከራከር ከመጀመሩ በፊት ተከራካሪ ወገኖች በዚህ የሥነ-ሥርዓት ደንብ የሚይዙ ስለመሆኑ የጽሁፍ ስምምነት መቀበል እንደሚገባው አከራካሪ አይሆንም፡፡

በእርግጥ የግልግል ጉባዔው ተጠሪ ያቀረበውን ክስና የግልግል ተቋሙም የሚመራበትን ይህንኑ የግልግል ደንብ አያይዞ ለአመልካች እንደላከና አመልካችም ይህንኑ ደንብ መሠረት አድርጎ ክርክሩን መምራቱን መገንዘብ ቢቻልም ሁኔታው ደንቡን ካወጣው ተቋም ሃሣብ /intention/ አንፃር ሲታይ ደንቡን ጠቅላላ ድንጋጌ ተከራካሪ ወገኖች ተገንዝበው በዚሁ መሠረት ለመገዛት ወስነዋል ለማለት የሚቻለው በደንቡ አንቀጽ 1/1/ ላይ እንደተመለከተው ግልጽ የሆነ የጽሁፍ ስምምነት ሲኖር ነው፡፡

በሌላ በኩልም አመልካች ደንቡ ደርሶት የደንቡንም የተለያዩ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ሙግቱን የቀጠለ ስለሆነ ደንቡን እንደተቀበለውና በዚሁ ደንብ አንቀጽ 20/2/ መሠረትም የይግባኝ መብቱን እንደተወ ይቆጠራል ቢባል እኳን ይግባኝ መሠረታዊ መብት እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ መሠረታዊ መብት ተፋላሚ ወገኖች አስቀርተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በተገነዘቡ ጊዜ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘም ተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብታቸውን አስቀርተዋል ወይንም ትተዋል ለማለት የሚቻለው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሙሉ በተረዱበት ደረጃ እርስ በርሣቸው በሚያደርጉት ስምምነት ሲሆን ነገር ግን አለመግባባቱ በግልግል ተቋሙ ዓማካይነት እንዲታይ ጥያቄው በቀረበ ጊዜ /At the stage of submission/ የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ ተገንዝበዋል ለማለት የሚቻልበት ደረጃ ላይ ናቸው ስለማይባል በዚህ ሁኔታ ይግባኙን ለማስቀረት የሚሰጡት ፈቃድ በሕጉ ላይ እንደተቀመጠው የነገሩን አካባቢ ሁኔታ በሚገባ በመገንዘብ እንዳደረጉት የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በኢትዮጵያ የፍትሐብሔር ሕግ ሥነ-ሥርዓት ላይ ተመሥርተው ማብራሪያ የፃፉትም ፕሮፌሰር አለን ሴድለር ይህንኑ በማብራሪያቸው ላይ አንፀባርቀውታል፡፡

አመልካች የይግባኝ መብቱን ለመተው አድርጎታል የተባለው ስምምነት የነገሮችን አካባቢ ሁኔታዎች በሚገባ ካለመገንዘብ ነው ከተባለ ደግሞ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 350/2/ ድንጋጌ መሠረት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው ማለት ነው፡፡

ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አመልካች የይግባኝ መብቱን ያስቀረ ስለሆነ ያቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ሣይቀበለው መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 29612 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የይግባኝ መብቱን ቀሪ ያላደረገ ስለሆነ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን መርምሮ የበኩሉን እንዲወስን ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37762

ታህሣሥ 09 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ገዋኔ ኢንተርፕራይዝ ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ተስፋዬ ጎላ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ዮሱፍ ይማም - ቀረበ -

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ውል ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን የጉዳት ኪሣራ የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ውል ተጠሪ ለአመልካች የመጥረጊያ አለላ በማቅረብ ወደ ውጭ ለመላክ የገባውን ግዴታ ለመወጣት ያመቸው ዘንድ በተጠሪ እግር ተተክቶ በተጠሪ ሠራተኞች የልማቱን ስራ ለማካሄድ ብር 170,609.14 /አንድ መቶ ሰባ ሺህ ስድስት መቶ ዘጠኝ ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ ማውጣቱን፣ የተጠሪ የውሃ ፓንፕና ትራክተሮች በዕዳ በመሬት ባለይዞታዎች በመያዛቸው ምክንያት ለዚህ ዕዳ አመልካች ብር 103,445.80 /አንድ መቶ ሦስት ሺህ አራት መቶ አርባ አምስት ብር ከሠማኒያ ሣንቲም/ ወጪ ማድረጉን፣ አመልካች ያጣው የገቢ ትርፍ ዝርዝር ድምሩ ብር 285,980.00 /ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰማኒያ ብር/ መሆኑን፣ ተጠሪ ያለምንም ማስጠንቀቂያ ውሉን በማፍረሱም የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው ውል መሠረት ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ የገደብ መቀጫ የመክፈል ግዴታ ያለባቸው መሆኑን በመዘርዘር በአጠቃላይ ብር 471,589.14 /አራት መቶ ሰባ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር ከአስራ አራት ሣንቲም/ ከወጪና ኪሣራ ጋር ተጠሪ እንዲከፈል ይወሰንለት ዘንድ በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት በዞን ሦስት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርበው ታኅሣሥ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በግራ ቀኙ ውል መኖሩን ሣይክዱ በውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች፣ ለመሬቱ ባለይዞታዎች ተከፈለ ለተባለው ወጪም አላፊነት የሌለባቸው መሆኑንና የአመልካች ማስረጃዎች አግባብነት እና ተቀባይነት የላቸውም የሚሉባቸውን ምክንያቶች በመዘርዘር መልስ አቅርበዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተውን ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ተገቢ ናቸው ያላቸውን ሁለት ጭብጦችን መስርቶ የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች በኩል ወጡ ለተባሉት የተለያዩ ወጪዎች አላፊነት የለባቸውም፣ የገደብ መቀጫውን ግን ተጠሪ ለውሉ መፍረስ ምክንያት ነው ባይባሉም ከአንዳንድ ሁኔታዎች አንፃር ሊከፍሉ የሚገባ ሆኖ ተገኝተዋል በማለት ተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ለአመልካች እንዲከፍሉና የአመልካች የወጪና ኪሣራ ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የአሁኑ አመልካች ሕጉ ያስቀመጠውን መስፈርት ተጠቅሞ ውሉን ማፍረስ ሲገባው በሕጉ መሠረት አልፈፀመም የሚል ምክንያት በመዘርዘር የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የአሁኑ አመልካች ለአሁኑ ተጠሪ በውሉ አንቀጽ 5.2 ስር የተመለከተውን የገደብ መቀጫ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ ሊከፍል ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ሚያዝያ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ

ክስ ባላቀረቡበት ጉዳይ ባለእዳ እንድንሆን የተወሰነው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ተከራክረው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ እንዲፀና ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ በሠበር ችሎቱ እንዲታይ በመደረጉ ተጠሪ ቀርበው ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ በመልሣቸውም ላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም የተደረገውን ውል መሠረት በማድረግ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩም ሆነ የገደብ መቀጫውን ለአመልካች ለተጠሪ እንዲከፍል መወሰኑ ስህተት ባለመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ነ/ፈጅ በበኩላቸው የተጠሪን መልስ በመንቀፍ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ህዳር 10 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም አመልካች ለተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ እንዲከፍል መወሰኑ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት በአመልካችና በተጠሪ መካከል ውል መኖሩ መታመኑ፣ በተጠሪ በኩል በስር ፍ/ቤት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አለመቅረቡ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ለአመልካች በስር ፍ/ቤት ክስ የመሠረተው የአሁኑ ተጠሪ የካቲት 27 ቀን 1993 ዓ.ም እና ነሐሴ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ከአመልካች ጋር በተዋዋሉት መሠረት የመጥረጊያ አሰላ ምርት ለማቅረብ ግዴታ ገብተው የቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ ተቀብለው ምርቱን ሣይሠበስቡና ለአመልካች ሣያስረክቡ የመስኖ እርሻውን ጥለው በመጥፋታቸው በአመልካች ላይ የተለያዩ ወጪዎች መከሰታቸውን በመግለጽ የእነዚህ ወጪዎች ድምር እና የገደብ መቀጫ ለውሉ አለመፈፀም በጉዳት ካሣነት እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ነው፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ደረሱ ለተባሉት ወጪዎች ተጠሪ አላፊነት የለበትም በማለት ከወሰነ በኋላ ለገደብ መቀጫው ግን ተጠሪን ተጠያቂ አድርጓቸዋል፡፡

እንግዲህ የአሁኑ ተጠሪ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ያልተስማሙበትና ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታ ያቀረቡበት ነጥብ የገደብ መቀጫውን በተመለከተ ስለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል ከዚህ ውጪ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች በመሆኑ ልጠየቅ አይገባም ከማለት ውጪ የደረሰብኝ ጉዳት ስላለ አመልካች ሊከፍሉኝ ይገባል በማለት በሥርዓቱ መሠረት የጠየቁት ዳኝነት አለመኖሩን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡

በመሠረቱ በመጀመሪያ ደረጃ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅር የተሰኘ ወገን ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኙን የሚያቀርበው የበታች ፍ/ቤትን ውሣኔ ለማስለወጥ፣ ለማሻሻል ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ ለማድረግ ነው፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው ያቀረበው ክስ ኖሮት ያላግባብ ውድቅ ከሆነበት ወይም የተጠቀው ዳኝነት በአግባቡ ሣይታይ የታለፈ ከሆነ ነው ዳኝነት ደግሞ በከሣሽነት ወይም በተከሣሽነት ሊጠየቅ ይችላል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ የሚያስተናግደው በበታች ፍ/ቤት የተደረገውን የክርክር እና የተጠየቀውን ዳኝነት ይዘት እንዲሁም አግባብነቱን በመመልከት ነው፡፡ በበታች ፍ/ቤት ተከሣሽ የነበረ ወገን የተከሣሽ ከሣሽነት ሥርዓቱን አሟልቶ ሣይጠይቅ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ፍርዱ ተለውጦ የፍርድ ባለመብት እንዲሆን ይወሰንለት ዘንድ ዳኝነት የሚጠይቅበት እና ተቀባይነት የሚያገኝበት ሥርዓት አለመኖሩን ስለይግባኝ ፍርድን ለመቃወምና ለፍርድ እንዲሻሻል ወይም እንዲጣራ ስለማመልከት የተደነገጉት ከቁጥር 320 እስከ 370 የተመለከቱት የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ስለይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣን የሚደነግገው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ በተለይ ሲታይም ፍ/ቤቱ ማናቸውም ይግባኝ የቀረበለትን ፍርድ ወይም ውሣኔ ለማፅናት፣ ለማሻሻል ወይም ለመሻር የሚችል መሆኑን ከመደንገጉ ውጪ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት የመስጠት ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ አያሣይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 182/2/ ስር የተመለከተው የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ስልጣንም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አስተያየት መስጠት ወይም መወሰን ይገባው ነበር ብሎ በሚገምተው ጉዳይ ላይ ትእዛዝ ወይም ውሣኔ ለመስጠት የሚችል ስለመሆኑ፣ በተጨማሪም ተገቢ መስሎ የታየውንና ነገሩን ለማስፈፀም ተስማሚ ነው ብሎ የሚገመተውን ማናቸውንም ሌላ ውሣኔ ወይም ብይን ወይም ትእዛዝ ወይም ፍርድ መስጠት ስለመሆኑ የተገለፀ ቢሆንም በዚህ ድንጋጌ መሠረት የተሰጡት የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ሥልጣንና ተግባራት የሚከናወኑት በበታች ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ ሥርዓቱን የጠበቀ ክርክር ሲቀርብና የተጠየቀ ዳኝነት ሲኖር ነው፡፡ አንድ ተከራካሪ በሥነ-ሥርዓቱ መሠረት ክስ ባልቀረበበት ጉዳይ ባለዕዳ የሚሆንበት ሕጋዊ ምክንያት የለም፡፡

በመሆኑም ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አመልካች በመሆኑ የገደብ መቀጫውን በውሉ መሠረት ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ክስ ባላቀረበበት ሁኔታ ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት አይደሉም ወደሚለው ድምዳሜ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ከደረሠ በኂላ ተጠሪ የገደብ መቀጫው ለአመልካች ሊከፍል አይገባም በሚል ውሣኔ መቆም እየተገባው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተጠየቀ ዳኝነት መስጠቱ ሥነ-ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በላይ ለውሣኔው መሠረት ያደረጋቸው የፍትሐብሔር ድንጋጌዎችም አግባብነት የሌላቸው ናቸው፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ ለተጠሪ እንዲከፈል የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የጠየቀውን ዳኝነት ስንመለከተው የአሁኑ ተጠሪ ለውሉ አለመፈፀም ተጠያቂ ስለመሆናቸው እርግጠኛ ያልሆነ ስለመሆኑ ከውሣኔው ላይ "... ውል አፍራሽ ተከሣሽ ነው ባንልም ..." በሚል ከገለፀው ሁኔታ መረዳት የሚቻል ከመሆኑም በላይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ለውሉ መፍረስ ምክንያት የሆነው የአሁኑ አመልካች ነው በማለት የወሰነው በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ማስረጃዎችን መዝኖ በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ በዚህ ችሎት የሚታይበትን አግባብ አላገኘንም፡፡ በይዘቱ የማስረጃ ምዘና ነውና፡፡

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1771/2/ በተመለከተው መሠረት ተጎጂው ወገን የጉዳት ኪሣራ የመጠየቅ መብት የሚኖረው የውሉ አለመፈፀም በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ የበታች ፍ/ቤት በማስረጃ ምዘና የተለያዩ ከመሆናቸው ውጪ በውሉ ወይም በሕጉ አተረጓጎም ረገድ የተለያዩበት ሁኔታ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለገደብ መቀጫው ተጠያቂነት የለባቸውም በማለት የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው የውሣኔ ክፍል የሚለወጥበትን ሕጋዊ ምክንያት ስላላገኘን በዚህ ረገድ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## **ው ሣ ኔ**

1/ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 968 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2/ ተጠሪ ለውሉ መፍረስ ምክንያት አይደሉም የተባለው የውሣኔ ክፍል እንዳለ ሆኖ የገደብ መቀጫውን በተመለከተ ግን አመልካች ለተጠሪ ብር 15,000.00 /አስራ አምስት ሺህ/ ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡

3/ አመልካች የዞኑ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ያጽናልኝ ሲል ያቀረበውን ጥያቄ አልተቀበልነውም፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ 38601

ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**:-የኢትዩጵያ እህል ንግድ ድርጅት - ብርሃኑ አሻግሬ ቀረበ

**ተጠሪ**:- ወ/ሮ ከድጃ ሳቢር ቀረበች ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው የአሁንዋ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተችው የአመልካች ሠራተኛ ለነበረው በሞት ለተለየው ባለቤትዋ ሊከፈል ይገባ ነበር ያለችውን ክፍያ እንዲከፈላት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የተጠሪ ባለቤት በሕይወት እያለ ክስ መስርቶ ከተከራከርን በኂላ በሕጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎች ሁሉ ተከፍለዋል፡፡ ተጠሪ በአሁኑ ደረጃ ያቀረበችው ክስ የሚስተናገድበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከመረመረ በኂላ፣ ብዙዎች በክሱ የተመለከቱት ክፍያዎች ውድቅ ያደረገ ሲሆን፣ ከዓመት ዕረፍት ፈቃድ ጋር ተያይዞ ያቀረበው የክፍያ ጥያቄ ግን በመቀጠል አመልካች እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሰኔ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ ያቀረበው፤ተጠሪ ለባለቤቴ ሊከፈል ይገባው የነበር ነው በማለት ያቀረበችው የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት ያለው ነው ወይ? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ እንደተመለከተው የተጠሪ ባለቤት የነበረው መሐመድ ሁሴን ከአመልካች ጋር አድርጎት የነበረው የስራ ውል መቋረጥን መነሻ በማድረግ በአመልካች ላይ ክስ መስርቶ ሲከራከር ከቆየ በኂላ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ሞቶአል፡፡ ከዚህ የተነሣም ተጠሪ ክርክሩን ስትከታተል ቆይታለች፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር በመመርመር አመልካች የማስጠንቀቂያ እና የስራ ስንብት ክፍያዎች እንዲሁም ወጪና ኪሣራ ይከፈል ሲል ወስኖአል፡፡ ተጠሪ በስምዋ አዲስ ክስ የመሠረተችው ከዚህ በኂላ ነው፡፡ አመልካች የክሱን መቅረብ የተቃወመውም እነዚህን ሁኔታዎች መሠረት በማድረግ ነው ፡፡

ከፍ ሲል እንደገለጽነው ተጠሪ በክስዋ ላይ ያመለከተችው የተለያዩ ክፍያዎች እንዲሰጡአት ሲሆን፣ ከዚህም አንዱ የዓመት ዕረፍት ፈቃድ የሚመለከት ነው፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የተቀበለውም በዚህ ረገድ የተጠየቀውን ክፍያ ብቻ ሲሆን፣ ለመቀበሉ የሰጠው ምክንያትም አመልካች በማመንም ይሁን በመካድ መልስ አልሰጠበትም የሚል እንደሆነ ከውሳኔው ተመልክተናል፡፡ በበኩላችን እንደምናየው አመልካች የክሱን መቅረብ በአጠቃላይ ተቃውሞ ተከራክሮአል፡፡ ለዚህ የሰጠው ምክንያትም የተጠሪ ባለቤት መስርቶት በነበረው ክስ ተጠቃሎ የተጠየቀ ወይም አንድ ላይ ሊጠየቅ ይገባው

የነበረ ነው የሚል ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በዚህ መልክ የቀረበውን የአመልካች ክርክር በመገንዘቡ በውሳኔው ላይ አመልክቶአል፡፡ ይህ መሰል መቃወሚያ ሲቀርብም አግባብነት ያለውን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሳኔ መስጠቱ ተገቢ ይሆናል፡፡

ማንኛውም የፍትሐብሔር ክስ ሲቀርብ ስለ ክሱ አቀራረብ በተመለከተ የተቀመጡትን የፍ/ብ/ስ/ስ/ሕግ ድንጋጌዎች ሊከተል እንደሚገባ የሚያከራክር አይደለም፡፡ የተጠሪ ባለቤት አቅርቦት የነበረው ክስ ከአመልካች ላይ የሚፈለገውን መብት የሚዘረዝር እና ክሱን ለማቅረብ ምክንያት የሆኑትን ሁሉ አጠቃሎ የያዘ እንደነበር ይገመታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ክሱ የተወሰኑትን ክፍያዎች ሳያካትት ቀርቶ ነበር አልተባለም እንጂ ቢባልም ኖሮ ከፍ/ቤት የተገኘ ፈቃድ ሳይኖር በሌላ አዲስ ክስ ሊጠየቅ እንደማይችል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.216 (4) ተመልክቷል፡፡ይህ ጉዳይ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 5 አንፃር ሲታይም በአዲሱ ክስ (ተጠሪ ባቀረበችው) እና ቀደም ሲል ክርክር ተደርጎበት የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘው ክስ መካከል ልዩነት የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ለሁለተኛ ጊዜ ያቀረባቸው ክስ በድጋሚ የሚታይበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔም ከዚህ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 07717 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64777 ግንቦት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348 (1) መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ የጠየቀችው የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ እንደ ሌሎች ክፍያዎች ተቀባይነት የለውም፡፡ ሊከፈላት አይገባም ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

የሰ/መ/ቁ. 37742

ታህሣሥ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አልማዝ ጉንፋ ኦሪቲ ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ፀሐይ ሊበን የሺጥላ አለሙ ጠበቃ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተመረመው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የስር ጣልቃገብ አመልካች ሲሆኑ ተጠሪ የስር ከሳሽ ነበሩ፡፡ ጣልቃ ገብ አመልካች በአሁን ተጠሪ ላይ ባቀረቡት መቃወሚያ ተጠሪ ከሟች ጋር አብሬ ያፈራሁትን ቁጥሩ 373 የሆነውን ቤት ተከሣሾች ያካፍሉኝ ሲሉ ክስ ያቀረቡት እኔ በጣልቃ ገብ አመልካች (የአሁን አመልካች) ከሟች ባለቤቴ ከነበሩት አቶ ታምሩ አሽናፊ ጋር በባልና ሚስት የጋራ ንብረት በመሆኑና በመሐከላችን በተነሳው ያለመግባባት በፍ/ቤት ውሣኔ ስንለያይ ንብረቱ የጋራችን በመባሉ እኔ ለልጆቼ ስል ሳልካፈል ትቻለው(አልወሰድኩም) ነበር፡፡ ስለዚህ በመብቴ ላይ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ጣልቃ እንድገባ በማለት እንዲፈቀድላቸው ጠይቋል፡፡

የመጀመሪያ ደ/ፍ/ቤትም መዝገቡን በመመርመር በሰጠው ብይን የአሁን አመልካች የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው ላይ መሰረት ያደረጉት የሟች አቶ ታምሩ አሽናፊ ሚስት መሆናቸውን እና ከሳሽ (የአሁን ተጠሪ) ክስ ያነሱበት ቤት ከሟች ጋር አብረን ሰርተናል በማለት ነው፡፡ ይህ የጣልቃ ልግባ ምክንያት ደግሞ አመልካችን ጨምሮ(የስር ጣልቃ ልግባ ባይን) የአሁን ተጠሪና የሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ክርክር ባነሱበት የመ/ቁ. 0057 ላይ የውርስ ንብረት አጣሪ ተሹሞ ሪፖርቱ የፀደቀበት ክርክር ነው ጣልቃ ልግባ ባይ በዚህ የጣልቃ ልግባ አቤቱታቸው በውርስ ንብረት አጣሪ ሪፖርት መሰረት ክርክር በተነሳበት የቤት ቁ. 373 ላይ ድርሻ አለኝ የሚል የጣልቃ ልግባ ምክንያት አላቀረቡም ይህ ከሆነ ደግሞ ከሣሽ ተጠሪ በውርስ አጣሪው ሪፖርት መሰረት በቤት ቁጥር 373 ላይ ክፍፍል ተደርጐ ድርሻዬ ይሰጠኝ ሲሉ ክስ ባቀረቡበት መዝገብ ላይ ጣልቃ ልግባ ባይ (አሁን አመልካች) በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41/2/ መሰረት የጣልቃ ገብነታቸውን ማመልከቻ በክሱ ውስጥ ይገባኛል የሚሉብትን ምክንያት ሳይዘረዝሩና ሳይገልጹ ጣልቃ ልግባ ያሉት ጥያቄ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ባይ(የአሁን አመልካች) በፍ/ቤቱ በተሰጠው ብይን ባለመስማማት ለፌደራል ከ/ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን በማከራከር ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የተሰጠውን ብይን ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከ/ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲታይ የተወሰነው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረበችው የጣልቃ ልግባ ጥያቄ ውድቅ የተደረገበትን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ከሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከህጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የዚህን ክርክር አመጣጥ በአጭሩ ስናየው ለአመልካች የጣልቃ ልግባ ምክንያት ከሟች ባለቤታቸው (አቶ ታምሩ አሸናፊ) ጋር በሚስትነት አብረው ያፈሩአቸው የጋራ ንብረት እንደነበረና ከሟች ጋር ያለመግባባት በመፈጠሩ ምክንያት በፍ/ቤት ተፋተው ንብረቱን በተመለከተ ለልጆቻቸው ጥቅም ሲሉ ሳይካፈሉት እንደቆየ እና የአሁን ተጠሪ በንብረቱ ላይ ውሳኔ እንዳያሰጡብኝ በማለት ነው፡፡

እንግዲህ ከዚህ መገንዘብ እንደቻልነው የአመልካች ጥያቄ ክርክር በተነሳበት ባለው ቤት ላይ መብት አለኝ የጋራ ንብረቱን እንደሚስትነቱ አልተካፈሉም እያሉ ነው አመልካች ከሟች ጋር ባልና ሚስት እንደነበሩ በፍ/ቤት እንደተፋቱ የተካደ ነገር የለም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር ከጉዳዩ (ከክርክሩ) ጋር ተያያዥነት ባለው ጉዳይ መብትና ጥቅም እንዳለ ከተገለፀ ጣልቃ ለመግባት በቂ ምክንያት ነው በያዝነው ጉዳይም አመልካች የሟች ሚስት የነበሩ መሆናቸው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ሌላው የሥር ፍ/ቤት አመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ይህን ጥያቄ አላቀረቡም ብሏል ይህ ደግሞ የአመልካች በውርስ አጣሪው ሪፖርት ላይ ጥያቄ የለማቅረብ የጋራዬ ነው ባሉት ንብረት ላይ ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚከለክላቸው አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ባለመብትነት የሚወሰነው ወደ ክርክር ከተገባና ግራ ቀኙ ከተከራከሩበት በኋላ ስለሆነ ነው፡፡

በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት አመልካች በክሱ ውስጥ ያገባኛል የሚሉትን ምክንያት አልዘረዘሩም መብታቸውን አልገለፁም በማለት ጥያቄውን ውድቅ ማድረጉንና የከፍ/ቤቱም ይህን ማረም ሲገባው ማጽናቱ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16228 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61828 በመጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት ያለው በመሆኑ ጣልቃ ገብተው ይከራከሩ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በፌ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የግራ ቀኙን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኋላ በሕጉ መሰረት እንዲወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 341 መሰረት መዝገቡን መልሰናል፡፡

4.ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37502

ታህሣሥ 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ ከተማ አስተዳደር ፍትህና ሕግ ጉዳዮች ቢሮ - ነ/ፈጅ ታረቀኝ ሞላ ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ የኒኣሸት ገመዳ ቤኛ - ቀርበዋል፡፡

2. ወ/ሮ ጌጤ ገመዳ ቤኛ - ወኪል ቀርበዋል፡፡

ጉዳዩን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች ግንቦት 01/2000 ዓ.ም. በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. የሰጡት ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ናቸው በማለት እንዲሻሩለት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክር ጣልቃ ለመግባት ተቃዋሚ የነበር፣ በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ደግሞ ይግባኝ ባይ ሆኖ የተከራከረ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎችም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች በከፍተኛ ፍ/ቤቱ ደግሞ መልስ ሰጭዎች በመሆን ተከራክረዋል፡፡

በስር ፍ/ቤት ለቀረበው ክርክር መነሻው የአሁኑ አመልካች ኀዳር 09/2000 ዓ.ም. በተፃፈ ያቀረበው መቃወሚያ ሲሆን ይዘቱም የስር ፍ/ቤቱ ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ በቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12፣ የቤት ቁጥር 486 የሆነውን ቤት ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ከሥር ተከሣሾች ከነበሩት /የቦሌ ክ/ከተማ ቀበሌ 12 አስ/ጽ/ቤት እና አቶ ለአዚም በደዊ/ እንዲረከቡት መወሰኑ ባለ ንብረት የሆንኩት በክርክሩ ባልተሳፍኩበት በመሆኑ በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ. 358፣ 360 መሠረት ጣልቃ አስገብቶ በማከራከር ቀደም ብሎ የተሰጠውን ፍርድ ውድቅ ያደርግልኝ የሚል ነው፡፡

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ስር ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ተጠሪዎች ታህሣሥ 24/2000 ዓ.ም. በሰጡት መልስ የመቃወም አመልካቹና ሁለተኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካልና ተመሣሣይ ክርክር ያላቸው ስለሆኑ አመልካቹ በመጀመሪያው ክርክር እንደተሳተፈ ስለሚቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358/360 መሠረት ያቀረበው ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትም በኮ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም. በሰጠው ብይን የመቃወም አመልካቹና ቀደም ብሎ ማለትም ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በተሰጠው ፍርድ ውስጥ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካልና ተመሣሣይ ክርክር ያላቸው በመሆናቸው የመቃወም አመልካቹ በመጀመሪያው ክርክር እንዳልተሳተፈ ስለማይቆጠር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358/360 መሠረት ያቀረበው ጣልቃ የመግባት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ በይግባኝ ቀርቦለት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. በሰጠው ትእዛዝ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

ከላይ የሰፈሩትን የስር ፍ/ቤቶቹ ብይኖች በመቃወም የአሁኑ አመልካች ግንቦት 01/2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም አከራካሪው ቤት መንግሥት በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት ወርሶ የሚያስተዳድረው ሃብት ሲሆን ለተጠሪዎቹ የተወሰነላቸው አላግባብና አመልካች በክርክሩ ሳይሳተፍ ነው፤ አመልካችና ስር አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት የየራሳቸውን ህጋዊ ሰውነት ያላቸው የተለያዩ አካላት እንጂ አንድ አይነት ባለመሆናቸው የስር ፍ/ቤቶቹ በክርክሩ ጣልቃ ገብቼ እንዳልከራከር ማድረጋቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው ብሏል፡፡

ተጠሪዎችም ሐምሌ 17/2000 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ የሰጡ ሲሆን ይዘቱም አመልካችና ቀደም ብሎ የሥር ፍ/ቤቱ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 361/1995 /የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር/ አንቀጽ 2 መሠረት የከተማው አስተዳደር የተለያዩ እርከኖች ስለሆኑ ክርክራቸው ተመሣሣይ እንጂ የሚለያይ ባለመሆኑና የአመልካችና የቀበሌው ስልጣን የሚመነጨው ከከተማው አስተዳደር ነው፤ አመልካች የከተማው አስተዳደር አንድ የሥራ ክፍል እንጂ ራሱን የቻለ አካል ባለመሆኑ ቀበሌው ቀደም ብሎ ተከራክሮበት የተወሰነው ጉዳይም የከተማው አስተዳደር ክርክር ተደርጎ መወሰድ ስላለበት የአመልካች ጥያቄ ተገቢነት የለውም፡፡ የስር ፍ/ቤቶቹ የፈፀሙት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም የሚል ነው፡፡

አመልካችም መስከረም 29/2001 ዓ.ም. በተፃፈ የመልስ መልስ የሰጠ ሲሆን አጭር ይዘቱም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 2/1995 አንቀጽ 29 እና እንደገና በተሻሻለው የከተማው አዋጅ ቁጥር 4/2000 /የአዲስ አበባ አስተዳደር የአስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ/ መሠረት የተቋቋመ ሲሆን የቀበሌ አስተዳደር አካላት የተቋቋሙት ደግሞ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክፍለ ከተሞችና ቀበሌዎች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1995 እንዲሁም የዚሁ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 18/1997 መሠረት የተቋቋሙና የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር ያላቸው አካላት ናቸው የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እንደሰፈረው ሆኖ ይህ ፍ/ቤትም አመልካችና የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት አንድ አካል ናቸው ወይስ አይደሉም? የሁለቱ አካላት ክርክር ተመሣሣይ ሊሆን ይችላል ወይስ አይችልም? የሚሉ ጭብጦችን በመመስረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መረዳት እንደተቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ እንዳይከራከር በስር ፍርድ ቤቱ የተከላከለው ቀደም ብሎ በክርክሩ ተሳትፎ የተወሰነበት የተጠቀሰው ቀበሌ ካቀረበው ክርክር ተመሳሳይ ክርክር የሚያቀርብና በመሠረቱ አንድ አካል ናቸው በሚል ነው፡፡ በርግጥ እነዚህ ሁለት አካላት በአንድ መንግስታዊ መዋቅር /በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር/ ስር የሚገኙ አካላት ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በአንድ የክልል ወይም የከተማ መንግሥታዊ መዋቅር ስር መገኘታቸው ብቻ አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ተመሣሣይ ጥቅምን የሚወክሉ አካላት ናቸው ወደሚል መደምደሚያ የሚደርስ አይደለም፤ እነዚህ ሁለት አካላት የከተማ መስተዳድሩ የተለያዩ እርከኖች ወይም አካላት ሆነው የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር እንዳላቸው በአዲስ አበባ ከተማ ምክር ቤት ከወጡት አዋጅ ቁጥሮች 2/1995፣ 4/2000፣ 1/1995 እና 18/1997 መገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ቀበሌውና አመልካች አንድ አካል ናቸው በመባል በሥር ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ብይን ተገቢነት የሌለውና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

ቀበሌው በክርክሩ ቀደም ብሎ ከቀረበው ክርክር አመልካቹ የተለየ ሌላ ክርክር ሊያቀርብ አይችልም የተባለውም ቢሆን ክርክራቸው ተመሣሣይና አንድ አይነት ጥቅም የሚወክል መሆኑና አለመሆኑ የሚታወቀው አመልካቹ በክርክሩ እንዲገባ ተደርጎ የሚያቀርበውን የክርክር አይነትና የሚወክለውን ጥቅም ቀበሌው አቅርቦት ከነበረው በማነፃፀር የሚታወቅ እንጂ አስቀድሞ ተመሣሣይ ክርክር አለው የሚል ግምት በመያዝ አይደለም፤ ከዚህ ትንታኔ አኳያም መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

<u>**ው ሣ ኔ**</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 44930 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም. እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 66633 ሚያዝያ 30/2000 ዓ.ም. የሰጡት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡

2. አመልካችና የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቱ ጥቅምት 29/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ አንደኛ ተከሣሽ የነበረው የቦሌ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 12 አስተዳደር ጽ/ቤት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር የሚገኙ የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት፣ ስልጣንና ተግባር ያላቸው የተለያዩ አካላት በመሆናቸው አመልካቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ ይከራከር፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ግንቦት 04/2000 ዓ.ም. በዚህ ችሎት የተሰጠው እግድ ተነስቷል፤ ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 29861

ጥር 14 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱል ቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ ህጽአት ፍስሐጽዬን - ከጠበቃ ይርጉ ሠንበቱ ጋር ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡-1ኛ ወ/ሮ አልማዝ ተረፈ - አልቀረቡም

2ኛ በአ.አ ከተማ መስተዳደር ዞን 04 ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ ሣሙኤል ድጉማ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበው በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 36844 ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ 26905 የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል በሚል አመልካች የሠበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኗ አመልካች ከሣሽ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ እንደቅደምተከተላቸው አንደኛ እና ሁለተኛ ተከሣሽ ነበሩ የስር ከሣሽ ግንቦት 22 ቀን 1994 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት ክስ በአ.አ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 03 ክልል ውስጥ ቁጥሩ 314 የሆነውን ቤት ለአንደኛ ተጠሪ ከታህሳስ 23 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ ማከራየታቸውን ገልፀው ተጠሪ ያለባቸውን የቤት ኪራይ ከፍለው ቤቱን እንደነበረ አድርገው ለአመልካች እንዲያስረክቡ ሁለተኛ ተከሣሽም ቤቱን ያላግባብ አንደኛ ተከሣሽ በብር 355,000.00 /ሦስት መቶ አምሣ አምስት ሺህ ብር/ ሸጦ በመገኘቱ ከነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ ቤቱን የሚሠጠውን የአገልግሎት ኪራይ ከአንደኛ ተከሣሽ ጋር ባልተነጣጠለ ሁኔታ እንዲከፍልና ቤቱን ለቀው እንዲያስረክቡ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል የአሁኑ አንደኛ ተጠሪም በክሡ ገንዘብ ሙሉ በሙሉ የዳኝነት ገንዘብ አለመከፈሉን የቤት ኪራይ ገንዘብ በክፍያ ግምት የሚታገድ መሆኑንና አመልካች ኢትዩጵያዊ ስላልሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤት መሆን የማይችሉና ክስ ለማቅረብም መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አቅርበው በፍሬ ነገር ረገድም የቤት ኪራይ ውሉ በውሉ መሠረት እንዲራዘም አለመደረጉን ቤቱን ለመረከብ የቀረበ ሠው ካለመኖሩም በላይ የቤቱ ባለቤት የሆኑት ግለሠብ በሞት የተለዩ እና ባለቤት ነኝ የሚሉት አመልካችም አሜሪካን ሀገር የሚኖሩ በመሆኑ የሚረከብ ሠው ያላገኙ መሆኑን ቀበሌ መጥቶ የቤቱን ባለቤት እንዲናገሩ ጠይቋቸውም ከአገር እንደወጡ የተደረገ መሆኑን ገልፀውላቸው ቤቱ ለሽያጭ በጨረታ በመቅረቡ ተጫርተው ነሐሴ 28 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ውል ከአስተዳደር ጽ/ቤቱ መግዛታቸውን ጠቅሰው በግዥ ያገኙትን ቤት የሚመልሱበት ምክንያት የለም ሲሉ ተከራክረዋል፡፡

የአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት በጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ስም የሚታወቅና አመልካች መብት የሌላቸው መሆኑን በመጥቀስ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ቤቱን በመንግስት በወጣው መመሪያ መሠረት መሸጡን እና የሽያጭ ገንዘቡን በዝግ አካውንት ማስቀመጡን በመግለፅ ያላግባብ የተጠቀመው ነገር በሌለበት ሁኔታ ተጠያቂነት የለም ሲል ተከራክሯል ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የሽያጭ ውሉ ህገ ወጥ ነው በማለት ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡ ከ28/12/93 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ የቤቱን ኪራይ

ባልተነጣጠለ ኃላፊነት እንዲከፍሉ እና ወጭና ኪሣራን በተመለከተ የአመልካችን ዝርዝር የማቅረብ መብት በመጠበቅ ወስኗል። በዚህ ውሣኔ የአሁኑ ተጠሪዎች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን በተናጠል ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅረበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የይግባኝ መዝገቦችን አንድ ላይ አጣምሮ በመመርመር አመልካች በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ኣላስረዱም፣ የኪራይ ገንዘቡም በጊዜ ማለፍ እንደተከፈለ የሚቆጠር ነው የሚሉ ምክንያቶችን በመዘርዘር የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ከሻረ በኋላ ህጋዊ መብት አለኝ የሚል ሠው ካለ በህጉ አግባብ ክስ ከማቅረብ ውሣኔው የማያግደው መሆኑን በመግለፅ ወስኗል የአሁኑ የሠበር አቤቱታ አቅራቢውም ይህንኑ ውሳኔ በመቃወም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቢያቀርቡም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል። የሠበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካች ጠበቃ ሚያዚያ 02 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት 7 /ሠባት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በፍ/ቤቶቹ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ አመልካች የሟች ሚስት መሆኔን በመ/ቁ 79/83 አሣውቁና ማስረጃ ለፍ/ቤት ቀርቦ እያለ አለመታየቱ ያላግባብ መሆኑ ቤቱ በባል ስም ብቻ መመዝገቡም አመልካችን መብት የላቸውም ለማለት የተሻሻለው የቤተሠብ ህግ የማያስችል መሆኑን የቤት ኪራዩን በተመለከተም ውሣኔው የፍ/ብ/ህ/ቁ 2968 ድንጋጌን መንፈስ አለማገናዘቡንና የኪራይ ገንዘቡ እንደተከፈለ ይቆጠራል መባሉ ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው ውሣኔው እንዲሻርላቸው ዳኝነት መጠያቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በተሠጠው ትዕዛዝ መሠረት ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን ሠጥተዋል። አንደኛ ተጠሪ ሠኔ 13 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የአመልካች በመ/ቁ 79/83 ተሠጠ የሚሉትን ማስረጃ በስር ፍርድ ቤት ያላቀረቡት መሆኑን ፣ ስለኤርትራዊ መሆንና አለመሆን ሲከራከሩም ኤርትራዊ አይደለሁም ሣይሉ በትውልድ ኤርትራዊ ብሆንም የወጣሁት በፖለቲካ አይደለም ብለው መከራከራቸውን፣ የኪራይ ውሉ ስላልተራዘመ ውል አለ ሊባል እንደማይችልና የክፍያ ግዴታ አለመኖሩን፣ ቤቱን በግዥ ምክንያት በመያዛቸውም የኪራይ መክፈል ግዴታ እንዴሌለባቸውና የሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል ሁለተኛ ተጠሪ በበኩሉ ሠኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ ማመልከቻ አመልካች በስር ፍ/ቤት የሟች ብርጋዴ ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስት ስለመሆናቸውም ሆነ ልጆቻቸውም ወራሽ ለመሆናቸው አረጋግጠው ማስረጃቸውን ከክስ አቤቱታቸው ጋር አያይዘው አለማቅረባቸውን፣ በቤቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ያላስረዱ መሆኑን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ኢትዩጵያዊ ለመሆናቸው ያቀረቡት አንዳችም ክርክር አለመኖሩ የኪራይ ውሉ የውሉ ጊዜ ካለቀ በኋላ የኪራይ ገንዘብን ተጠሪ የሚከፍልበት ምክንያት አለመኖሩን ዘርዝሮ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ ባግባቡ በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል። አመልካች ተጠሪዎች በሠጡት መልስ የመልስ መልሳቸውን ሠጥተዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር ግራ ቀኙ ለማጣሪያ ጥያቄ የሠጡትን መልስ የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም ለክርክሩ መነሻ በሆነው ቤት አመልካች ክስ ለማቅረብ ህጉን መሠረት ያደረገ ጥቅም ወይም መብት የላቸውም ተብሎ መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል።

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በተወካያቸው አማካኝነት ክስ ሲመሠርቱ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት ንብረታቸው መሆኑን መጥቀሣቸውን የአሁኑ ተጠሪዎች ባቀረቡት መከላከያ መልስ አመልካች በቤቱ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መከራከራቸውን አመልካችም በተጠሪዎች በኩል ለቀረበው ለዚሁ ክርክር በሠጡት የመልስ መልስ አመልካች ከእነልጆቻቸው የብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስትነትና የልጆቹን ወራሽነት በፍርድ ቤት በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 ጥቅምት 10 ቀን 1984 ማስወሠናቸውንና ውሣኔው በእጃቸው የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው መከራከራቸውን የስር ፍ/ቤትም ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የአመልካች መሆኑን አንደኛ ተጠሪ አምኖ በመቀበል መከራየታቸውን የኪራይ ውሉና በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 መወሠኑ በቀረበው ክስና ክርክር አመልካች ማስረዳታቸውን በመግለፅ አመልካች ባቀረቡት ክስ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያላቸው መሆኑን አስረድተዋል እንዲሁም ተጠሪዎች በቤቱ የተሻለ ማስረጃ አቅርበው አላስረዱም በሚል ምክንያት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም የሚለውን የተጠሪዎችን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጉን የአሁኑ ተጠሪዎች ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ይግባኝ የቅሬታ ነጥቦች ከሆኑት ውስጥ በተጠሪዎች በኩል የቀረበው መቃወሚያ መታለፍ ያላግባብ መሆኑ አንዱ እንደነበርና ይህንኑ

ነጥብ በተመለከተም ከፍተኛው ፍ/ቤት በጭብጥነት ይዞ ከመረመረው በኋላ በስር ፍርድ ቤት ውድቅ መደረጉ ያላግባብ መሆኑን ጠቅሶ አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መወሠኑን ነው ፡፡ የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካች በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 በፍ/ቤት የተረጋገጠ ማስረጃ አለ የሚሉት በክርክሩ ሂደት ተያይዞ ያልቀረበ እና የማያውቁት መሆኑን ለዚህ ችሎት በሠጡት መልስ ገልፀው ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ ሊፀና ይገባል በማለት የሚከራከሩ መሆኑንም ተረድተናል፡፡ በአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት የሚያሣየው አመልካች የሚች ብርጋዴር ጄኔራል ገብረአብ ወልዳይ ሚስትነትን እና የልጆቻቸው ወራሽነት በፍ/ቤት ውሣኔ አረጋግጫለሁ የሚሉት ሠነድ በስር ፍርድ ቤት ስለመኖሩ ከመጠቆሙ ውጪ የአመልካች ክስ አባሪ ሆኖ ቀርቦ ተጠሪዎች ይዘቱን በመመልከት ያልተከራከሩበት የስር ፍ/ቤትም ቢሆን አመልካች ባቀረቡት ክስና ክርክር አስረድተዋል ከማለት ውጪ ራሡ የሰነዱን ይዘት በመመልከት ማረጋገጡን በውሣኔው ላይ ያልጠቀሠ መሆኑን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ ከሣሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት አዘጋጅቶ ከሚያቀረበው የክስ ማመልከቻ ጋር በክሱ መሰማት ወቅት ለጉዳዩ ማስረጃ ይሆኑኛል የሚሏቸውን የሠውም ሆነ የጽሁፍ ማስረጃዎችን ዝርዝርና ዋናውን ወይም ትክክለኛ ግልባጮቻቸውን ማቅረብ ያለበት ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 223 ድንጋጌ ያሣያል በተለይም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 137/3/ የሠነድ ማስረጃዎችን በተመለከተ ማንኛውም ተከራካሪ ወገን ከአቤቱታው ጋር በማያያዝ ወይም ከቀነ ቀጠሮ በፊት ወይም በመጀመሪያው ቀን ቀጠሮ ካልቀረበ በቀር ማስረጃው ሊቀርብ ወይም ይቅረብልኝ ተብሎ ሊጠየቅ እንደማይችል ተመልክቷል፡፡ ይሄው ጥያቄ ተቀባይነት የሚያገኘው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 256 ስር በተመለከተው አኳኋን ማስረጃዎቹ ሣያቀርቡት የቀሩት ከባድና በቂ በሆነ ምክንያት መሆኑን ፍ/ቤቱ ሲረዳ ብቻ ነው፡፡

የማስረጃ አቀራረብን በተመለከተ በሥነ ሥርዓት ህጉ የተመለከተው ሌላው ደንብ የይግባኝ ሠሚውን ፍ/ቤት ሥልጣን የሚመለከት ነው በዚህም መሠረት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 345 ድንጋጌ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሡ አስተያየት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውም ዓይነት ሠነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ ዓይነት ማስረጃ በተጨማሪነት እንዲቀርብለት የማዘዝ ህጋዊ ሥልጣን ያለው ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 145 /1/ ድንጋጌም በሌላ ፍ/ቤት የሚገኝ ሠነድ የፁሁፍ ማስረጃ ወይም ፍርድ የተሠጠበት መዝገብ ለውሣኔው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍ/ቤቱ በራሡ አነሣሽነትም ሆነ በተከራካሪዎቹ ጠያቂነት እንዲቀርብለት ማዘዝ የሚችል ስለመሆኑ ያስረዳል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት ውሣኔ የሠጠው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ሚስትነታቸውን በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 አረጋግጠዋል በማለት በውሣኔው ላይ የገለፀው ሁኔታ በውሣኔው ግልባጭ መኖሩን እየተመለከተ ነው የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሠሚው ችሎትም በዚህ ረገድ ቅሬታው ቀርቦለታል፡፡ እንዲህ ከሆነ በአመልካች የተጠቀሠው የፍ/ቤት መዝገብ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በየደረጃው ጉዳዩን ባዩት ፍ/ቤቶች አነሣሽነት ጭምር ሊቀርብና ተጠሪዎች በሠነዱ ይዘት የሚያቀርቡት ክርክር ከታየ በኋላ ውሣኔ መስጠት በተገባ ነበር ይሁን እንጂ የስር ፍርድ ቤት ሠነዱ ሣይቀርብለት እና ለተጠሪዎች ሣይደርስ ሠነዱ መኖሩን ማመኑ ይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤቶችም የአመልካችን መብትና ጥቅም ያረጋግጣል የተባለው የፍ/ቤት መዝገብ በስር ፍርድ ቤት የውሣኔው ግልባጭ ተገልጾ እያለ መዝገቡ ከሚገኝበት ፍ/ቤት በህጉ በተሠጣቸው ሥልጣን መሰረት እንዲቀረብ ሣያደርጉ የአመልካች በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም የላቸውም በማለት መወሠናቸው የክርክሩን አመራር ከላይ በተመለከቱት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ የማስረጃ አቀራረብ ደንቦች መሠረት አለመምራታቸውንና በውጤቱም በቤተሠብ ህጉ የተመለከቱትን የአመልካችን መብቶች የጎዳ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት የማስረጃ አቀራረብ ሥርዓት ድንጋጌዎች በማይደግፉትና የፍርድ አካሄዱ ባልተሟላ ሁኔታ በመሆኑ በየርከኑ ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ እና ትዕዛዝ ሙሉ በሙሉ ሊሻሩ የሚገባና የስር ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የቀረቡትን ሁሉንም መከራከሪያ ነጥቦችን እና ስለመኖሩ የተጠቆመውን የፍ/ቤት መዝገብ ሠነድ በማስቀረብ ተመልክቶ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ማድረጉ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ 26905 የካቲት 02 ቀን 1999 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ 36844 ሐምሌ 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 07632 ታህሣስ 28 ቀን 1997 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች በሥ/ፍ/መ/ቁ 79/83 አለ ያሉትን የሚስትነትና የልጆቻቸውን ወራሽነት ማስረጃ በማስቀረብና ተገቢውን በመፈፀም እንዲሁም ተገቢነት አላቸው የሚሏቸውን ማስረጃዎችን ሁሉ በማስቀረብ በግራ ቀኙ ሁሉም የመከራከሪያ ነጥቦች እንደገና ተገቢውን ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ተመልሶለታል ይፃፍ፡፡

3/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ.ት

የሰ/መ/ቁ. 37303

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው መንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ኤ.ሲ.ዲ.አይ/ቮካ- ኢትዮጵያ - ስራጅ ዓብደላ/ጠበቃ/ ቀረበ

**ተጠሪዎች**፡- 1. ሃይደር ዓሊ

2. ሑሴን ሰዒድ ዓብደላ

3. ግርማ ሐጎስ ገ/ጊዮርጊስ

4. ሽምሰዲን መሐመድ ዓሊ

5. አርባ ሑመድ ጠበቃ አወል ሰይድ ቀረበ

6. ወ/ሪት ዛህራ እንድሪስ

7. መሐመድ ኢብራሂም ዑመር

8. ወንድሙ አባቡ አስማረ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተነሣውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአፋር ብ/ክ/መንግስት በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱትም ሳይከፈል ቀርቶአል ያሉትን የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ነው፡፡ የወረዳው ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኂላ፣ተጠሪዎች በጠየቁት መሰረት የበረሃ አበል እንዲከፈላቸው ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሳኔውን በመቃወም ለክልሉ የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የከፍተኛው ፍ/ቤት በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔ የሚሽር ውሳኔ የሰጠው ጥር 20 ቀን 2000 ዓ.ም በነበረው ችሎት ሲሆን፣በሌላ በኩል ደግሞ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም መዝገቡን በማስቀረብ ሌላ ትእዛዝ ሰጥቶአል፡፡ ትእዛዙም እንዳየነው "....ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ግ ቁ. 208 አስተካክለናል፡፡ ተጠሪዎች ጉዳያቸውን በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 142/1/ መሰረት ለአስማሚ እንዲያቀርቡ ብለናል፡፡ የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የከፍተኛው ፍ/ቤት

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የተደረገ እርማት ነው፤ በሚል የሰጠውን ትእዛዝ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በሕጉ መሰረት ሊከፈለን ሲገባ ሳይከፈለን ቀርቶአል ያሉትን የበረሐ አበል እንዲከፈላቸው ሲሆን፣የወረዳው ፍ/ቤትም ሊከፈል አይገባም በማለት ከአመልካች የቀረበውን የመከላከያ ክርክር ባለመቀበል የተጠየቀው የበረሐ አበል መጠኑን ጭምር በመግለጽ እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ አመልካች ለከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ያቀረበውም አበሉ እንዲከፈል መወሰኑ ትክክል አይደለም በማለት ነው፡፡ ከዚህ የተነሣም የከፍተኛው ፍ/ቤት አበሉ ሊከፍል ይገባል ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የተጠየቀው አበል አይከፈልም በማለት ግልጽ የሆነ ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ በወረዳው ፍ/ቤት ተሰጥቶ የነበረውን ውሳኔም ሙሉ በሙሉ ሽሮአል፡፡

የክርክሩ መነሻ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት የሚታይ የስራ ክርክር ሲሆን፣የሚመራውም በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርአት ሕጉ እና አግባብ ባላቸው የአዋጁ ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡ በአዋጅ አንቀጽ 138 እንደተመለከተው በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት የተጀመረ የስራ ክርክር ውሳኔ ካገኘ በኋላ በይግባኝ የሚታየው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎት ነው(የአዋጁ አንቀጽ 139) በመደበኛው የስራ ክርክር ሂደትም ይግባኝ ሰሚው የስራ ክርክር ችሎት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ችሎት በሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ያለው ተከራካሪ ወገን ከዚህ በኋላ አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው ለሰበር ችሎት ነው፡፡ ከዚህ ውጪ በሆነ ሁኔታም ውሳኔው ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል አይችልም፡፡ ይህ እንግዲህ አጠቃላይ ሂደቱ(ስርአቱ) ሲሆን፣ውሳኔውን በመቃወም ወደ በላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ለማለት ወይም አቤቱታ ለማቅረብ የሚፈልግ ተከራካራ ወገን ውሳኔውን በሰጠው ፍ/ቤት ሊታረም የሚገባ ወይም የሚችል ስህተት አለ ብሎ ካመነ ወደ በላይ ፍ/ቤት አቤት ከማለቱ በፊት ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት አቤቱታ የሚያቀርብበት ስርአት እንዳለም ይታወቃል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ጥያቄ የሚነሳውም እዚህ ላይ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 208 ርእሱ እንደሚያመለክተው "ስህተትን ስለማረም" በሚል የተደነገገ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት አቤቱታ የቀረበለት ፍ/ቤት (ውሳኔውን የሰጠው) ሊያርም ወይም ሊያስተካከል የሚችለው በሰጠው ውሳኔና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ግልጽ ነው፡፡ በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሳኔ ስህተትን ማረም በሚል ሊያሻሽል ወይም ሊለውጥ አይችልም፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሳኔ የሰጠበት ክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ተጠሪዎች የጠየቁት የአበል ክፍያ ተገቢነት ያለው ነው ወይስ አይደለም የሚል ነው፡፡ ይህም ፍ/ቤቱ ከመረመረው በኋላ ጥያቄው ተገቢነት የለውም የሚል ውሳኔ ሰጥቶበታል፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 የተመለተውን ድንጋጌ መሰረት በማድረግ በኋላ የሰጠው ትእዛዝ ግን ከጉዳዩ ጋር በፍጹም የሚገናኝ አይደለም፡፡ ከተጠቀሰው ቁ. 208 ድንጋጌም ጋር የሚገናኝ አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ ከመጀመሪያውኑ ሊያስተናግደው የሚገባ አልነበረም፡፡ ስለዚህም  በዚህ ረገድ የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በአፋር ብ/ክ/መ/የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0974 መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38419

የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 19/20 አስተዳደር ጽ/ቤት - ነ/ፈጅ አቶ ወንደሰን በቀለ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ያሲን ጀማል - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የይግባኝ ችሎትና የሰበር ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ስለጠየቀ ነው፡፡

የክርክሩ ፍሬ ጉዳይ የአሁን ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 08 ቀበሌ 06 የቤት ቁጥር 636 በሆነ የይዞታ ማረጋገጫ የካርታ ቁጥሩ 00487 የሆነ የግል ይዞታ አለኝ፡፡ ስለሆነም ተጠሪ በዚህ ይዞታ ላይ ለሠራሁት የግል ቤቴ ኪራይ መክፈል አለብህ በማለት ቁጥሩ አ/አ/ክ/ቁ. 19/002/92 የሆነ ደብዳቤ ሰኔ 10 ቀን 1995 የፃፈልኝ ስለሆነ፣ ደብዳቤው እንዲሰረዝልኝና ኪራይ መክፈል እንደማይገባኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ከሥር በተከሳሽነት ቀርቦ ከሣሽ /ተጠሪ/ ከይዞታቸው ውጭ በመንግሥት ባዶ ቦታ ላይ ያለ ፈቃድ በሕገ ወጥ መንገድ ቤት ሠርተው ተገኝተዋል፡፡ ይህንን በመግሥት ቦዶ ቦታ ላይ የተሠራ ቤት ቁጥሩ 636/ሀ/ የሚል ቁጥር ከሰጠነው በኂላ ከሣሽ /ተጠሪ/ የንግድ ሥራ እንዲያከናውኑበት በመስማማት ተከሣሽ /ተጠሪ/ በመኖሩ በቀበሌ ለመክፈል ተስማምተው የኪራይ ውል ፈርመው በገቡት የኪራይ ውል መሠረት ኪራይ እንዲከፍሉ ከመጠየቃችን በስተቀር በሕጋዊ ይዞታቸው ላይ ለሠሩት ቤት ኪራይ እንዲከፍሉ አልጠየቅንም በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት አመልካች /ተከሣሽ/ ተጠሪ /ከሣሽ/ በባዶ የመንግሥት መሬት ላይ ቤት ሠርተው ካገኘ ቤቱን እንዲፈርስ ከማድረግ በስተቀር ኪራይ የመጠየቅና የመሰብሰብ ስልጣን የለውም፡፡ ስለዚህ አመልካች /ተከሣሽ/ ከተጠሪ /ከሣሽ/ በሕገ ወጥ መንገድ ተሰርቷል ከሚለው ቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቋረጥ በማለት ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለአዲስ አበባ ከተማ ነክ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን ይግባኙ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ተሰርዞበታል፡፡ አመልካች ውሣኔው በሰበር እንዲታይ ለከተማ ነክ ሰበር ሰሚ ችሎት አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጎበታል፡፡

አመልካች በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ እየከፈልኩ ልጠቀምበት በማለት ጥያቄ በማቅረባቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የኪራይ ውል ተፈጽሟል፡፡ ተጠሪ ከጳጉሜ 2 ቀን 1988 ዓ.ም. እስከ 1995 ዓ.ም. የቤት ኪራይ ሲከፍሉ ቆይተው 1995-1998 ያለውን ውዝፍ ኪራይ እንዲከፍሉ ደብዳቤ ተጽፎላቸው፡፡ ከዚህ በኂላ ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ተገቢነት የሌለውና የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ ቤቱ የተሠራው በሕጋዊ ይዞታዬ ላይ ነው፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ የሰጡት ያለኝን ማስረጃ መሠረት

በማድረግ ነው። የኪራይ ውል አለን በማለት ያቀረቡት ክርክር በማስረጃ የተደገፈ አይደለም፣ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡትን ውሣኔ በማጽናት እንዲያሰናብተኝ በማለት ምላሽ ሰጥተዋል። በሥር የተደረገው ክርክርና በሰበር አመልካችና ተጠሪ ያቀረቡት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ እኛም ጉዳዩን መርምረናል። ጉዳዩን እንደመረመርነው፣ የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካች ጥያቄ የክስ ምክንያት አለው ብለው መቀበላቸውና አመልካችንና ተጠሪን አከራክረው አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ መቀበሉን፣ እንዲያቋርጥ በማለት መወሰናቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል።

ተጠሪ ለሥር ፍርድ ቤት ያቀረበው ጥያቄ ይዘት አመልካች ተጠሪ በወረዳ 8 ቀበሌ 6 ቁጥሩ 636/ሀ/ ለሆነው የድርጅት ቤት ያለበትን ውዝፍ ኪራይ እንድከፍል የፃፈው ደብዳቤ እንዲሰረዝልኝና ኪራይ እንዳልከፍል ይወስንልኝ የሚል ነው። አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ፣ ከተጠሪ ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1988 ዓ.ም. በተደረገ የቤት ኪራይ ውል ተጠሪ የተከራየው መሆኑንና እስከ 1995 ድረስ ኪራይ ሲከፍል ቆይቶ፣ 1995 በኋላ ኪራይ መክፈሉን ስላቆመ ማስጠንቀቂያ የተፃፈለት መሆኑን ነው። ከዚህም የምንረዳው የአመልካችና የተጠሪ ግንኙነት ጳጉሜ 2 ቀን 1988 በተደረገው የቤት ኪራይ ውል ላይ የተመሠረተ መሆኑን ነው። ተጠሪ፣ ከአመልካች ጋር የተደረገው የኪራይ ውል ሕጋዊ ውጤት ሊሰጠው የሚገባው አይደለም በፍርድ ታይቶ ፈራሽ መሆን አለበት የሚሉበት፣ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1696 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1710 ከተዘረዘሩት አንዱ ወይም ሌላ ውሉ እንዳይረጋ የሚያደርግ ምክንያት አለኝ ብለው የሚያስቡ ከሆኑ ምክንያታቸውን በማስረጃ በማስደገፍ ከአመልካች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል እንዲፈርስ መጠየቅ ነበረባቸው ተጠሪ ይህንን አላደረጉም።

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ጳጉሜ 2 ቀን 1988 የፈፀሙት ውልን ፈራሽ ሣያደርጉ፣ አመልካች በዚህ ኪራይ ውል መሠረት ውዝፍ የቤት ኪራይ እንዲከፍሉ የፃፈው ደብዳቤ እንዲሰረዝላቸው የኪራይ ገንዘብ እንዳይከፍሉ እንዲወስንላቸው ያቀረቡት ጥያቄ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 33 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተጠሪ ከአመልካች የሚጠይቁትን መብትና ጥቅም በግልጽ የማያሣይና የክስ ምክንያት የሌለው ነው። የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ ያቀረበውንና ይህንን የክስ ምክንያት የሌለውን ጥያቄ ለአመልካች መጥሪያ ከመላኩ በፊት መርምሮ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 231 ንዑስ አንቀጽ 1/ሀ/ መሠረት ውድቅ ማድረግ ነበረበት። የሥር ፍርድ ቤት ከላይ የተገለጹትን ድንጋጌዎች በሚጥስ አኳኋን፣ ተጠሪ ከአመልካች የሚጠየቀውን አመልካች የፃፈው ደብዳቤ ይሠረዝልኝ እና የቤት ኪራይ እንዳልከፍል አቤቱታ በመቀበል ማከራከሩንና ቤቱን በሕገ ወጥ መንገድ ተጠሪ በመግንስት ባዶ ቦታ ላይ የሠራው ቢሆንም ቤቱ እንዲፈርስ ከማድረግ በስተቀር ተጠሪ ኪራይ እንዲከፍል ማድረግ አመልካች ስልጣን የለውም ከሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የቤት ኪራይ ውል ያላገናዘበና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው።

የአዲስ አበባ ከተማ ነክ፣ የይግባኝና ሰበር ችሎትም የሥር ፍርድ ቤት የክስ ምክንያት የሌለውን የተጠሪን ጥያቄ አላግባብ በመቀበል የሰጠውን ውሣኔ ማጽናታቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ተጠሪ የቤት ኪራይ ለአመልካች እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ሆኖ እያለ በየደረጃው ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ ለአመልካች እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የሌለው ሆኖ እያለ በየደረጃው፣ ያሉ የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች አመልካች ከተጠሪ የቤት ኪራይ መቀበሉን እንዲያቆም የሰጡት ውሣኔ፣ ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል።

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 02157 መጋቢት 20 ቀን 1998 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል። ይፃፍ።
2. የአዲስ አበባ አስተዳደር ከተማ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤትና በመዝገብ ቁጥር 03331 ጥቅምት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል።
3. የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመዘገብ ቁጥር 06001 መጋቢት 19 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል። ይፃፍ።

4. ተጠሪ አመልካች በቁጥር 19/002/95 ሰኔ 10 ቀን 1995 ዓ.ም. የፃፈው ደብዳቤ ይሰረዝልኝ የቤት ኪራይ ገንዘብ እንዳልከፍል ይወስንልኝ በማለት፣ ያቀረበው ጥያቄ የክስ ምክንያት የለውም ብለናል፡፡
5. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሳቸውን ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የካቲት 5 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ፣ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37391

የካቲት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ - ጠበቃ ንጉሴ ገዛኸኝ ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች**፡- 1. ስዩም ማሞ - ቀረበ፡፡

2. በየነ አበራ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሰረት በአሰሪና ሰራተኞች መካከል የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ ከሣሾች የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረቱት ጥፋት ሳንፈጽም የገንዘብ ቅጣት/ከደመወዛችን ላይ እየተቀነሰ/ እንድንከፍል ተወስኖብናል፡፡ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶናል፡፡ ስለዚህ ቅጣቱና ማስጠንቀቂያው ይሰረዝልን ዘንድ ይወሰንልን በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች ግንቦት 6 ቀን 1999 ዓ.ም በማታው ፈረቃ የነበረውን የስራ ጫና ለማደላደል አለቃ በሚወስነው የአሰራር አፈጻጸም ስርአት መሰረት ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በመሄድ እንዲሰሩ አመራር ቢሰጣቸው አመራሩን ሳይቀበሉ በመቅረታቸው ነው ቅጣቱ የተወሰነባቸው፡፡ ቅጣቱ የተወሰነው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት በመሆኑ ሕጋዊ ነው፡፡ የሚሰረዝበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ስለመከራከሩ ኅዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የካ ምድብ የስራ ክርክር ችሎት ከፃፈው የመልስ ማመልከቻ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በዚህ መልክ ክርክር የቀረበለት የስራ ክርክር ችሎትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ፣ በከሣሾች ላይ ቅጣቱ የተወሰነው በማታ ሽፍት አንሰራም ብለዋል በሚል እንጂ ከነበሩበት ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዛውረን አንሰራም ብለዋል በሚል አይደለም የሚል ምክንያት በመስጠት በአመልካች የተሰጠው ቅጣት እንዲሰረዝ ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስራ ክርክር ችሎትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውን በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ተሰጥቶ የነበረውን የቅጣት ውሳኔ በፍ/ቤቶቹ በተሰጠው ውሳኔ የተሰረዘበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለጸው ተጠሪዎች ቅጣት የተወሰነባቸው በአለቃቸው የተሰጣቸውን የስራ መመሪያ ለመቀበል ፍቃደኛ ሆነው አልተገኙም በሚል ነው፡፡ መስከረም 8 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ እንደሚታየው በአለቃቸው የተሰጣቸውን ትእዛዝ በመቀበል በስራ ቦታው እንደተገኙ ገልጸዋል፡፡ ይህም የሚያሳየው ለቅጣቱ መነሻ ሆኖአል የተባለው ጥፋት /የአለቃ መመሪያ አለመቀበል/ አለመፈጸማቸው በመግለጽ መከራከራቸውን ነው፡፡ አመልካችም ኅዳር 2 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው መልስ የበኩሉን የመከላከያ ክርክር ያቀረበ ሲሆን፣ይዘቱም ከላይ የተመለከተው ነው፡፡

እንግዲህ ከግራ ቀኝ ወገኖች የቀረበው የጽሑፍ ክርክር በግልጽ እንደሚያመለክተው አከራካሪው ጭብጥ ቁልጭ ብሎ መውጣቱን ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 247/1/ እንደተደነገገው የነገር ጭብጥ የሚመሰረተው አንደኛው ተከራካሪ ወገን ያመነውን የሕግ ወይም የፍሬ ነገር አግባብ ሌላው ተከራካሪ ወገን በማስተባበል የካደ እንደሆነ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ በአመልካች ለቅጣቱ መወሰን መሰረት ሆኖአል ያለው የፍሬ ነገር አግባብ በተጠሪዎቹ ተክዶአል፡፡ በመሆኑም ይህ የፍሬ ነገር ጭብጥ እንደየሁኔታው ግራ ቀኝ ወገኖች ከሚያቀርቡት ማስረጃ አንፃር ታይቶ የሚነጥር ነው፡፡ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ እውነታ ካለ አግባብ ካለው ሕግ አንፃር በመመርመር አግባብ ወዳለው ውሳኔ መድረስ ይችላል፡፡

አቤቱታ በቀረበበት ውሳኔ እንደሚታየው ክርክሩ ከፍ ሲል በተመለከተው አኳኋን አልተመራም፡፡ የክርክሩ አመራር የክርክር አመራር ስርአት ወይም አግባብ ተከትሎ ካልተከናወነ ፍትሐዊ ውሳኔ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡ አንድን ክርክር በመምራት ላይ ያለ ፍ/ቤት ሊያከናውናቸው ከሚገባቸው መሰረታዊ ነገሮች አንዱና ዋነኛው የክርክሩን ጭብጥ ለይቶ ማውጣት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በስር ፍ/ቤቶች ሳይከናወን የቀረውም ይኸው ተግባር ነው፡፡ ትክክለኛው ጭብጥ ባለመያዙም የደረሰበት ድምዳሜ ትክክል ነው ሊባል አይችልም፡፡ በመሆኑም አቤቱታ የቀረበበት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37409 ጥር 28 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37391 መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ለተወሰነው ቅጣት መሰረት ሆኖአል የተባለውን ጥፋት ፈጽመዋል ወይስ አልፈጸሙም? የሚለውን የፍሬ ነገር ጭብጥ በግራ ቀኝ ወገኖች በሚቀርብለት ማስረጃ መሰረት እንዲያነጥር /እንዲያረጋግጥ/፤ በመቀጠልም በፍሬ ነገር ረገድ አጣርቶ የደረሰበትን ድምዳሜ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝቦ ከመረመረ በኋላ የመሰለውን ውሳኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር ምክንያት ያወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ከፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ የመጣው ቁ. 37409 የሆነው መዝገብ ወደ መጣበት ይመለስ፡፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39540

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ናስ ፉድስ የድ/ዳ/ጨ/ፋብሪካ ተከራይ - ጠበቃ ወንድዬ ግርማ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- እነ ስንዱ ደጀኔ (93 ሰዎች)

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪዎች የካቲት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ በአመልካች ድርጅት ለረዥም ዘመናት በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተቀጥረው ሲሰሩ ቆይተው መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም የስራ ውላቸው መቋረጡን፣እንዲህ ሲደረግም ሊከፍላቸው የሚገባ የስራ ስንብት ክፍያ፣የ60 ቀን ክፍያ፣የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ፣ያልተወሰደ የአመት እረፍት ክፍያ ሣይከፈላቸው መቅረቱን ዘርዝረው በህብረት ስምምነቱ መሰረት ለእያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ በ42% ተባዝቶ የ2 ዓመት ከስድስት ወር ተቆርጦ የተያዘባቸው የአገሎግሎት ክፍያ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሊዝ ውሉ መሰረት የፕራይቬታይዜሽንና የመ/ል/ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ ወደ ክርክሩ እንዲገባ እንዲታዘዝለት የአገልግሎት ክፍያ ጥያቄም ጊዜውን በተመለከተ ግልጽነት የሌለው በመሆኑ የሥነ-ሥርዓት ጉድለት እንዳለበት በመዘርዘር በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ለክሱ ኃፊነት የሌለበት መሆኑን ያሣያሉ ያላቸውን መከራከሪያ ነጥቦችን አንስቶ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የአመልካችን መከራከሪያ ነጥቦችን ውድቅ አድርጐ ለክሱ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ 42% ለሁለት ዓመታት፣21% ደግሞ ለስድስት ወራት የአገልግሎት ካሣ ክፍያ በአመልካች ሊከፈላቸው ይገባል ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከተው የፋብሪካው ባለቤትና አከራይ በክርክሩ ጣልቃ እንዳይገባ መደረጉ፣አመልካች ፋብሪካውን ከመከራየቱ በፊት ላለ እዳና ሐላፊነት ከፋይና አስከፋይ መደረጉ ከህጉና ከኪራይ ውሉ ውጪ መሆኑንና ጉዳዩም ቀደም ሲል በተመሣሣይ ሁኔታ ክስ ቀርቦበት የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው በማለት ዘርዝረው የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ እንዲሻር ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች በወኪሎቻቸው አማካኝነት ታህሣስ 09 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመንቀፍና የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ተገቢነት በመግለጽ ውሣኔው ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የካቲት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ በጉዳዩ የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በክርክሩ እንዲገባ አመልካች ጠይቆ በበታች ፍ/ቤቶች ጥያቄው ውድቅ ተደርጐ ለክፍያው ኃላፊ መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪዎች ለረዥም ዘመናት በተለያዩ የስራ ዘርፎች በፋብሪካው ተቀጥረው የሚሰሩ መሆኑን፣ ፋብሪካውን የሚያስተዳደረው የነበረው የፕራይቬታይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ መሆኑን፣ ፋብሪካውን የአሁኑ አመልካች ከአስተዳዳሪው አካል በኪራይ ከየካቲት ወር 1999 ዓ.ም ጀምሮ ለሁለት ዓመታት ያህል መከራየቱን ነው፡፡ እንግዲህ አመልካች የፋብሪካው ተከራይ መሆኑ ከተረጋገጠ ከፋብሪካው ጋር ተያይዘው የሚነሱት መብትና ግዴታዎች የኪራይ ውሉንና አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች በመመልከት ምላሽ የሚያገኙ ናቸው፡፡ አመልካች ለተጠሪዎች ጥያቄ በተከራይነቱ ኃፊነት የሌለበት መሆኑን፣የተከራዩ እና አከራዩ መብትና ግዴታም በውሉ ላይ መዘርዘሩን ጠቅሶ አከራይ ወደ ክርክሩ እንዲገባ ይታዘዝለት ዘንድ አመልክቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም አመልካች በዋቢነት የጠቀሰውን የኪራይ ውሉን አንቀጽ ሰራተኞች የክፍያ ጥያቄውን በቀጥታ ለአከራይ እንዲያቀርቡ የማያስገድድ፣አመልካችም በመዋቅሩ ምክንያት ከስራ ለሚያሰናብታቸው ሰራተኞች ተገቢውን ክፍያ ከፈፀመ በኋላ ወጪውን ከአከራይ እንዲጠይቅ የሚያስችል ነው በማለት የራሱን እምነት በመግለጽ ወደ ክርክሩ እንዲገባ የተጠየቀውን አካል ሳይጠራ አመልካችን ኃላፊ አድርጐ ወስኗል፡፡

በመሰረቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ክስ ሲቀርብና የክሱም ምክንያት የብዙ ሰዎች መብትና ጥቅም የሚነካ ሆኖ ከእነሱ ውስጥ አንዱ ወይም ከፊሉ ክስ ባቀረቡ ጊዜ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም ፍርድ የክርክሩ ተካፋይ ያልሆኑትን ወገኖችም መብትና ጥቅም የሚነካ ሲሆን በክሱ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆኑ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ መስጠት የአለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 39/1/ እና 40/2/ ድንጋጌ ስር ተመልክቷል፡፡ እነዚህ ወገኖች ተካፋይ ሣይሆን የሚሰጠው ውሣኔ ወይም ፍርድ ውጤት የማይኖረው ስለመሆኑም ተጠቃሽ ድንጋጌዎች መንፈስ ያስገነዝባል፡፡ በመሆኑም በክሱ ውስጥ መግባት ያለበት ተከሣሽ የሆነ እንደሆነ ፍ/ቤቱ የክርክሩ ተካፋይ እንዲሆንና ለቀረበው ክስ መልስና መከላከያውን እንዲያቀርበው ሊያዘው የሚችል ስለመሆኑ ሥነ-ሥርአት ህጉ አስቀምጧል፡፡ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ማለት ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ጥቅማቸው፣መብታቸው ወይም ግዴታቸው የሚነካ በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ ያልሆኑ ሰዎች ስለመሆናቸውም ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40 ድንጋጌ ይዘት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የፋብሪካው ተከራይ ሆኖ የኪራይ ውሉ የሚቆይበት ዘመንም ሁለት ዓመት ስለመሆኑ የአከራይና ተከራይ ጥቅም፣መብት ወይም ግዴታዎች በኪራይ ውሉ መዘርዘሩን አመልካች ያስረዳ ሲሆን ከኪራይ ውሉ ይዘት አኳያ ሲታይም በጉዳዩ ላይ የሚሰጥ ውሣኔ የአከራይን ጥቅም፣መብት ወይም ግዴታ ሊነካ አይችልም ሊባል የማይገባው ነው፡፡ በመሆኑም አከራይ በክርክሩ የግድ ተከፋይ መሆን የሚገባው ወገን /Indispensable party/ ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤት በኪራይ ውሉ ላይ የተመለከተውን አንድ አንቀጽ ብቻ ነጥሎ በመውሰድ የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ ስነ-ስርአታዊ ባለመሆኑ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22768 ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03845 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. የፋብሪካው አከራይ የተባለው የፕራይዜታይቬሽንና የመንግስት ልማት ድርጅቶች ተቆጣጣሪ ኤጀንሲ በክርክሩ ውስጥ የግድ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወገን በመሆኑ ለቀረበ ክስና መልስ መከላከያውን እንዲያቀርብ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ሰጥቶ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ ይሰጥበት ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመልስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 36780

መጋቢት 03 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የወ/ሮ አወጣሽ አብርሃ ወኪል - ክብሮም አስመላሽ - ጠበቃ ካላዩ መሃሪ -ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- የአቶ ገ/ኪዳን እንግዳ - ወኪል ኃ/ሥላሴ ገ/ኪዳን - ጠበቃ ገ/አምላክ - ገ/ጊዮርጊስ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የሥነ-ሥርዓት ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ ግምቱ ብር 1500.00 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የሆነ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ጣቢያ አድነት ውስጥ የሚገኝ በምስራቅ 533፣በምዕራብ አደባባይ፣ በሰሜን 530፣ በደቡብ 534 የሚያዋስነው ፣ ስፋቱ በካሬ 600/ስድስት መቶ/ የሆነ የሚች አባታቸው ባሻይ አብርሃ ኪዳኑ ይዞታ በመሆን ከ1960 ዓ.ም ግብር የገበረበት ቦታ መኖሩን በዚህ ቦታ የአሁኑ ተጠሪ በነባር ይዞታነት ይገባኛል ብለው በቓልህ ትግራይ ጋዜጣ በ15/04/1995 ዓ.ም ተራ ቁጥር 755 በስማቸው ተጠንቶ መውጣቱን አመልካች ቦታውን በተመለከተ የይገባኛል ጥያቄ ለሚመለከተው የአስተደደር አካል ቢያቀርበም በመቐለ ዞን ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በቁጥር 10709 /354/94 በቀን 22/5/1995 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ጉዳዩን በፍርድ ጨርሰው እንዲቀርቡ ማዘዙንና የሚች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ማረጋገጣቸውን ዘርዝረው የቦታው ግማሽ 300 ካ.ሜ እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በመቀሌ ደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነታቸው ቀርበው በሠጡት መልስ በከሣሽ ክስ የተቀመጠው በመቓልሕ ትግራይ ጋዜጣ ከወጣው ጋር የማይገናኝ እና በጉዳዮ ላይ ተከራክረውበት ውሣኔ ተሰጥቶ ተከፋፍለው በየግል ይዘው እንደሚገኙ ገልፀው በክሱ ላይ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርበው ተከራክረዋል ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር በቃል በሠማበት ወቅት ከሣሽ እየጠየቁ ያሉት ስለተከፋፈሉት ሣይሆን ስለነባር ይዞታ መሆኑን መግለፃቸውን ተቀብሎ ተገቢውን ማጣራት ከአደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በመቓልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በቀን 15/04/1995 ዓ.ም በአሁኑ ተጠሪ ስም ተጠንቶ የወጣ ቦታ ለአመልካችም በአባተቸው ድርሻ ግማሽ 300 ካ.ሜ ሊደርሳቸው ይገባል በማለት ወስኗል በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሠኘት ይግባኛቸውን ለመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ ሲያፀና ተጠሪ ጉዳዩን በድጋሚ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይኸው ፍ/ቤትም የወረዳውን ፍ/ቤት ውሳኔ በማጽናት ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ ከዚህ በኋላ ተጠሪ አቤቱታቸውን ለክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ችሎቱ የበታች ፍ/ቤቶች በተጠሪ በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያለፉት ከሥነ-ሥርዓት ውጪ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ ጉዳዩ በፍርድ ያለቀ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሯል የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የሠበር ችሎት ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአሁኗ አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 5/አምስት / ገጽ የሠበር አቤቱታ በክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቦታ በፍ/መ/ቁ 2/90 አዋሣኙ ከተጠቀሰው የተለየ ስለመሆኑ የዞኑ እና የወረዳ ፍ/ቤቶች አጣርተው በወሰኑት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ከሚደነግገው ውጭ ጉዳዮ በፍርድ ያለቀ ነው ተብሎ መወሰኑ

መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ነው በማለት ዘርዝረው የክልሉ ሠበር ችሎት ውሣኔ ተሽሮ ሌሎች ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሣኔ እንዲፀናላቸው ዳኝነት መጠየቃቸቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የአመልካች የሠበር አቤቱታ የቅሬታ ነጥቦች ተቀባይነት የሌላቸው የክልሉ የሠበር ችሎት ውሣኔ አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ዘርዝረው ውሣኔው ሊፀና ይገባል ሲሉ በ22/01/2001 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ ማመልከቻ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም የፃፉት የመልስ መልስ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ዓብይ ጭብጥ ለክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ በመጨረሻ ውሣኔ ያገኘ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም በፃፉት ክስ አዋሣኙንና ስፋቱን የገለፁበት ቦታ ቀደም ሲል በወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ ከተጠቀሰውና እኩል እንዲካፈሉ በ07/05/1991 ዓ.ም ፍ/ቤቱ ከወሰነው ቦታ ጋር ተመሣሣይ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይህ ስለመሆኑም የወረዳው እና የዞኑ ፍ/ቤቶች ያረጋገጡት ሲሆን ፍ/ቤቶች የተጠሪን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ውድቅ ያደረጉበት ምክንያት አመልካች በክስ ማመልከቻ ላይ የጠቀሱት አዋሣኝና ስፋት በመ/ቁ 2/90 የተወሰነውን የሚመለከት ቢሆንም ክሱ ሲሰማ በጋዜጣው ላይ የወጣውን ቦታ ስለመሆኑ በመግለፃቸውና በፍሬ ነገር ክርክር ወቅትም በማስረጃ ተጣርቷል በሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የፍትሐብሔር የክርክር አመራር ሥርዓት ዓይነተኛ ዓላማ የክርክርን ሂደት ለማቀላጠፍና አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ መቋጫ ለማበጀት መሆኑ ይታመናል፡፡ የፍትሐብሔርን ክርክር አንድ ደረጃ ላይ ሲደርስ እልባት እንዲደረግበት በማቀድ ከተደነገጉት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ጽንሰ ሐሣቦች አንድ የመጨሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች /Res judicata/ የሚለው ሲሆን ይህ ጽንሰ ሀሣብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ/ 5 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያገኙ ጉዳዮች ማለት በማናቸውም መልክ በሕግ በተቋቋመ ፍ/ቤት ቀርበው የመጨረሻ ውጤት ያገኙ ጉዳዮችን የሚሸፍን መሆናቸውንና በፍርድ፣ በብይን፣በውሣኔ፣ በትእዛዝ፣ ወይም በጊዜያዊ አገልግሎት ባለው ትእዛዝ የመጨረሻ ውጤት አግኝተው በሌላ መልክ ለመንቀሣቀስ የማይችሉ የክርክር ነጥቦችን ሁሉ የሚያጠቃልል ጉዳይ መሆኑን መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 ስር በተመለከተው አኳኋን አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በፍርድ ያለቀ ነው ለማለት መረጋገጥ ካለባቸው ሁኔታዎች ውስጥ ቀደም ሲል ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የነበሩ ጉዳዮች በድጋሚ በቀረበው ክስም ላይ በቀጥታ በፍሬ ነገር ጭብጥ ሆነው መቅረባቸው፣ ቀደም ሲል የነበረውን ክርክር አሁን በክርክር ተሣታፊ በሆኑ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወይም ተላልፎላቸው በነበረ ወገኖች መሆኑንና እነዚህ ጉዳዮች ቀደም ሲል በተካሄደው ሙግት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈባቸው መሆኑን ነው፡፡

ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ በመጨረሻ ፍርድ መቃወሚያነት ሲቀርብ ተቀባይነት የሚኖረው ይኸው ጉዳይ በድጋሚ በቀረበው ክርክር ላይ መቅረቡ ሲረጋገጥ ነው ቀጥተኛ የፍሬ ነገር ጭብጥ የሚለው ሐረግ አጠቃላይ ይዘቱ ሲታይም በመጀመሪያው ክርክር ላይ ከአንደኛው ወገን ተጠይቆ በሌላኛው ወገን የተካደ ወይም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የታመነና በዚሁ ላይ የፍርድ ውሣኔ ያረፈበት የክርክር ነጥብ መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም በመሆኑም በድጋሚ በቀረበው ክስ በቀድሞው ክርክር ተሣታፊ በነበሩ ወገኖች ወይም ከእነሱ መብት በተላለፈላቸው ወገኖች የሚካሄድ መሆኑና በሁለተኛው ክስም የተያዘው የፍሬ ነገር ጭብጥ ከመጀመሪያው ጋር ተመሣሣይ ሆኖ የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት መሆኑ ከተረጋገጠ እንዲሁም ጉዳዩ የመጨረሻ ፍርድ አርፎበታል የሚል ተቃውሞ በተከራካሪ ወገን ከተነሣ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 እና 244(2) ድንጋጌዎች የምንገነዘበው ነጥብ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች በ01/07/1995 ዓ.ም ለወረዳው ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አዋሣኙና ስፋቱ የተጠቀሰው ቦታ በመ/ቁ 2/90 በፍርድ ያለቀ በፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረትም ግራ ቀኙ ተከፋፍለው በየግላቸው የያዙት መሆኑን በሁለቱም የበታች ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው ከወረዳ ፍ/ቤት እስከ ክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሠሚ ችሎት የተጠሪ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት ያጣው አመልካች በክሱ ላይ አዋሣኙን የጠቀሱት ቦታ በፍርድ ያለቀ መሆኑ ቢረጋገጥም በቃል ክርክር ወቅት በጋዜጣው የወጣውን ይዞታ የሚመለከት መሆኑን ስለገለፁና ይህም ቀደም ሲል በፍርድ ካለቀ ጉዳይ የተለየ መሆኑን በተደረገው ማጣራት ተረጋግጧል በማለት መሆኑን ከላይ ገልፀናል እንግዲህ

አመልካች በአቤቱታ ፁሑፋቸው አዋሣኙን የጠቀሱት ቦታ ውሣኔ ያገኘ መሆኑ አከራካሪ አይደለም አከራካሪው ነጥብ በክሱ መሠማት ወቅት በአቤቱታ ጽሑፍቸው የጠቀሱት ሣይሆን በጋዜጣው የወጣው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል በሚል ተቀባይነት ማግኘቱ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

እንደሚታወቀው የአቤቱታ ፁሑፎች የሚመሩት በሥነ-ሥርዓቱ በተመለከተው ሥርአት መሠረት ነው፡፡ ህጉ ይህን ያደረገበት መሠረታዊ ዓላማም የፍርድ ሂደቱን ለማቀላጠፍ በተቻለ ፍጥነት እልባት ለመስጠት ነው ፡፡ የአቤቱታ ጸሐፊዎች የሚመሩበት ሥርአት መኖር ተከራካሪ ወገኖች ክስ በቀረበበት ጉዳይ ላይ በሚያዘው ጭብጥ ወይም ፍሬ ነገር ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ የሚረዳቸው ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል የአቤቱታ ጽሑፉች ሥርአት ባለው መልክ እንዲቀርቡ ማድረግ ፍ/ቤቱ የክርክሩን ጭብጥ ለመመሥረትም ያግዘዋል፤ በመሆኑም በአቤቱታ ጽሁፍ ላይ ያልተገለፀ ፍሬ ነገር ፍርድ ቤቱ ጭብጥ የሚመሰርትበት አይሆንም፡፡ ጭብጥ ባልተመሠረተባቸው የክርክር ነጥቦች ላይ ደግሞ ክርክሩ በሚሠማበት ወቅት ማስረጃ ሊቀርብባቸው አይችልም፡፡ ምክንያቱም ማስረጃ የሚሠማው በተጠየቀው ጥያቄ ወይም በቀረበው የመከላከያ መልስ ላይ በግልጽና በዝርዝር በቀረቡት ነጥቦት ላይ ብቻ ነው፤ ሆኖም ፍ/ቤቱ የነገሩን ሁኔታ መርምሮ ሌላኛው ወገን ክሱን ወይም መልሱን እንዲያሻሽል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 91 እና 251 ድንጋጌዎች በተመለከተው መሠረት ሊያዝ ይችል ይሆናል፡፡ ከዚህ የሥነ-ሥርዓት አካሄድ ውጪ በአቤቱታ ፁሑፍ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች በመተው በቃል ክርክር ወቅት የተገለፀውን ፍሬ ነገር መሠረት በማድረግ በሌላ ተከራካሪ ወገን የቀረበውን ተቃውሞ ውድቅ ማድረግ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ ነው የሚባልበት የክርክር አመራር ሥርዓት ምክንያት የለውም በተያዘው ጉዳይም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው ላይ የጠቀሱትን ነገር በቃል ክርክር ወቅት አለመሆኑን ገልፀዋል ተብሎ የክስ አቤቱታውን ባላሻሻሉበት ሁኔታ ተቀባይነት ማግኘቱ፤ የአቤቱታ ጸሐፊዎች የሚመሩበትን ሥርዓት ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ተገኝቷል፤ በመሆኑም አመልካች በአቤቱታ ጽሑፋቸው የገለፁትና የዘረዘሩት ፍሬ ነገር ከመ/ቁ 2/90 ከቀረበውና የመጨረሻ ፍርድ ካረፈበት ጉዳይ የተለየ ነው ለማለት የሚቻል ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት ግራ ቀኙ የሚከራከርበት ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 5 መሠረት የመጨረሻ ፍርድ ያረፈበት ጉዳይ ነው ሲል የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ ስለሆነ ውሣኔው መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት አልተቻለም በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## **ው ሳ ኔ**

1. የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሠበር ችሎት በመ/ቁ 21439 ታህሣስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት በአብላጫ ድምጽ ፀንቷል፡፡
2. አመልካች መጋቢት 01 ቀን 1995 ዓ.ም  በፃፉት የአቤቱታ ጽሑፍ አዋሣኙንና ስፋቱን የጠቀሱት ቦታ በመ/ቁ  2/90 የመጨረሻ ፍርድ ያገኘ ጉዳይ ነው ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት

## **የ ል ዩ ነ ት   ሐ ሳ ብ**

እኛ ስማችን በሶስተኛው እና በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምነው ዳኞች አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ ባለመስማማታችን የልዩነት ሀሳባችንና ምክንያታችንን ከዚህ በታች በዝርዝር ገልፀናል፡፡

1. አብላጫው ድምጽ በውሣኔው በመጀመሪያው ገጽ በግልጽ እንዳሰፈረው አመልካች ተጠሪ የአባቱን የጋራ የይዞታ ቦታ ሊያካፍለኝ ይገባል የሚሉትን ቦታ ለማመላከት ሁለት አይነት አገላለጾችን ተጠቅመዋል የመጀመሪያው የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጠቀም ተጠሪ በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ጣቢያ ሐድነት ውስጥ የሚገኘውና

በመሥራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530፣ እና በደቡብ 534 የሚያዋስነው ስፋቱ 600 ካ.ሜትር ቦታ በማለት በክሳቸው የገለፁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላቸው የሚፈልጉት ነባር የይዞታ ቦታ የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 ቀን 1995 ዓ.ም በመቃልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 በተጠሪ ስም የወጣው ነባር የይዛታ ቦታ የአባታቸው የጋራ ይዞታ ስለሆነ ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ውሣኔ እንዲሰጥላቸው በክስ ማመልከቻቸው የጠየቁ መሆኑን የወረዳውና የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ይህንን የአመልካች የክስ አቀራረብ ከሥነሥርአት ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ስንመለከተው ከሳሽ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተለየ ነገር በሚሆንበት ጊዜ ነገሩን በመለየት በሚያስችል ሁኔታ ክሱን አብራርቶ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 225 ንዑጽ አንቀጽ 1 ይደነግጋል በተለይም የከሳሽ ክስ የማይንቀሳቀስ ንብረትን የተመለከተ በሆነ ጊዜ ከሳሽ በክስ ማመልከቻው የማይንቀሳቀሰውን ንብረት ለይቶ ለማወቅ የሚያስችሉ ምልክቶችን በክስ ማመልከቻው መግለጽ ያለበት መሆኑንና ይህንንም ግዴታውን የሚወጣው

- የማይንቀሣቀሠውን ንብረት የሚለየው የአካባቢ ወሰን በሆነ ጊዜ የአካባቢ የወሰን ምልክቶችን በክሱ ውስጥ በመግለጽ የክስ ማመልከቻው ማቅረብ እንዳለበት ወይም ከዚህ በአማራጭም፣
- የማይንቀሣቀሰው ንብረት በዕርስት መዝገብ የተመዘገበ በሆነ ጊዜ ንብረቱ በዕርስት መመዝገቢያ መዝገብ ላይ የተሰጠውን ቁጥር በመጥቀስ ክሱን ማቅረብ እንዳለበት የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ አመልካች ለወረዳው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 ከተደነገጉት የማይንቀሣቀሥ ንብረት መለያ መንገዶች አንደኛውን አማራጭም ብቻ ሣይሆን ሁለቱንም አማራጮች በመጠቀም የክስ ማመልከታቸውን ገልፀዋል፡፡ አመልካች በክሳቸው ቦታውን ለመለየት የሚያስችሉ የወሰን ምልክቶችን የገለፁ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሳስ 15 ቀን 1995 ዓ.ም በመቓልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ተጠሪ እንዲያካፍላቸው ተጠይቀዋል፡፡

አመልካች በክስ ማመልከቻቸው ውስጥ የቦታ መለያ የወሰን መልክቶችን በመጥቀስ የገለፁት ቦታውና የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በተራ ቁጥር 755 የገለፀው ቦታ በአንድ መልዕካ ምድር ላይ የሚገኝ አንድ ቦታ አይደለም፡፡ አመልካች የወሰን ምልክቶችን በመጥቀስ የጠየቁት ቦታና የመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቀልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቀጥር 755 የወጣው ቦታ በተለያየ መልዕካ ምድር የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ናቸው፡፡ የሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በቁጥር 755 በመቓልሕ ትግራይ ጋዜጣ ያወጣው ቦታ በወሰን ምልክቶች ሲገለጽ በምሥራቅ አቶ ኪዳኑ ፈቃዱ በምዕራብ አቶ አብርሀ ኪዳኑ በሰሜን መንገድ በደቡብ አቶ ግደይ ገብሩ የሚያዋስኑት 600 ካሬ ሜትር ቦታ እንደሆነ፣ በመቓልሕ ትግራይ ጋዜጣ በዝርዝር የተገለፀ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በእኛ እምነት አመልካች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁርር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 የተደነገጉትን ሁሉንም አማራጭዎች በመጠቀም በክስ ማመልከቻቸው የጠየቁት ቦታ ሁለት የተለያዩ ቦታችን ነው፡፡ የአመልካች ክስ ግልጽነት የጐደለው መሆኑ አከራካሪ ባይሆንም አመልካች ክስ ያቀረበችው በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ ሚገኘው በምስራቅ 533፣ በምዕራብ አደባባይ፣ በሰሜን 530 በደቡብ 534 የሚገኘውንና ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 1/90 በወረዳው ፍርድ ቤት ተከራክረው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘውን ቦታ ነው የሚለው መደምደሚያ አመልካች የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት በክስ ማመልከቻዋ ያቀረበችውን ጥያቄ ተጠሪ አመልካች ክስ እንዳላቀረበችበት ተደርጐ የተሰጠ በመሆኑ ተገቢ ነው የሚል እምነት የለንም፡፡ በእኛ እምነት አመልካች የወሰን ምልክቶችን በመግለጽ የጠየቀችው ቦታና ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 የገለፀውን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ያቀረበችው ጥያቄ ሁለት የተለያዩ ራሳቸውን የቻሉ ቦታዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ተጠሪ እንዲያካፍላት ጠይቃለች ከሚባል በስተቀር አመልካች በመቐለሕ ትግራይ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩ የተገለፀን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ክስ አላቀረበችም በማለት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትና አብላጫው ድምጽ የደረሱበት መደምደሚያ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 225 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ አመልካችና ተጠሪ ለሚከራከሩበት ቦታ ያሰጠውን የቦታ መዝገብ ቁጥር በመጥቀስ የቀረበችውን ጥያቄ እንደ ትክክለኛ የክስ አቀራረብ አማረጭ

ባለመውሰድ የተሰጠና የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ ክስ ለማቅረብ ትክክለኛው እና ብቸኛው የክስ አቀራረብ ሥርዓት የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጥቀስ ክስን ማቅረብ እንደሆነ በመቁጠር የተሰጠ በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

2. ከላይ በዝርዝር እንደገለጽነው አመልካች በክስ ማመልከቻዋ የቦታ ወሰን ምልክቶች በመጥቀስ የጠየቀችው ቦታና በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በመዝገብ የሥራና ከተማ ልማለት መምሪያ ያወጣውን ቦታ ተጠሪ እንዲያካፍላት ያቀረበችው ጥያቄ ሁለት በተለያየ መልዕካምድር የሚገኙ የተለያዩ ቦታዎች ናቸው፡፡ አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ሁለት የተለየዩ ቦታዎችን ገልጾ የጠየቀች መሆኗንና ተጠሪ ጉዳዩ ከዚህ በፊት በውሣኔ አልቋል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ መሆኑን የተረዳው የወረዳው ፍርድ ቤት ተጠሪ ባቀረበው የመጀመሪያ መቃወሚያ ብይን ከመስጠቱ በፊት ፣
   - አመልካች ዳኝነት እንዲታይላቸውና በፍርድ ተጣርቶ የሚፈልጉት በክሳቸው የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ከገለጿቸው ቦታዎች የትኛውን ቦታ እንደሆነ እንዲያብራሩና መልስ እንዲሰጡ፣
   - ተጠሪ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 2/90 ተከራክረን የመጨረሻ ውሣኔ አግኝቷል በማለት የሚቃወመው በአመልካች ክስ ከተገለፁት ሁለት ቦታዎች የትኛው እንደሆነ እንዲያብራራና መልስ እንዲሰጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 በሚደነግገው መሠረት ተገቢውን የቃል ምርመራ ያደረገ መሆኑንና ፍርድ ቤቱም ባደረገው የቃል ምርመራ አመልካች የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጠቀም በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ የሚገኘው በምስራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530፣ በደቡብ 534 የሚዋሰነው ቦታ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ በዝገብ ቁጥር 2/90 ተከራክረውበት የመጨረሻ ፍርድ የገኘና ቦታውንም አመልካችና ተጠሪ እኩል ተካፍለው በይዞታቸው ሥር አድርገው የሚገኙ መሆኑን አጣርቷል፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት የምትፈልገውና ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆናት ቦታ በመቀሌ ከተማ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 /1995 በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩ የተገለፀውና ነባር የይዛታ ቦታ ፍርድ ቤቱ ባደረገው የቃል ምርመራ በማያሻማ ሁኔታ ግልጽ ሆኗል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ባደረገው የቃል ምርመራ አመልካች ተጠሪ እንዲያካፍላት የጠየቀችውና በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ 755 ዝርዝሩና አዋሳኝ የድንበር ምልክቶቹ የተገለፀው ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ያልተከራከሩበትና ውሣኔ ያላገኘ መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም ፍረድ ቤቱ አመልካች በመቀልሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 ዝርዝሩና አዋሳኝ ድንበሮቹ የተገለፁት ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የይዞታ መብት አላት ወይስ የላትም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ከዚህ ቦታ አመልካች ግማሹ ማለትም ሶስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ በይዞታነት ይገባታል በማለት ወስኗል፡፡ በእኛ እምነት የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካች ክስ ውስጥ ሁለት የተለያዩ ቦታዎች ተገልፀው መቅረባቸውን በመረዳትና አመልካች በዳኝነት ታይቶ እንዲወሰንላቸው የሚፈልጉት በክሳቸው ከገለፁት ውስጥ በየትኛው ቦታ ላይ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ተገቢውን የቃል ምርመራ በማድረግ የክርክሩን መሠረተዊ የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ መሥርቷል ይኸም የወረዳው ፍርድ ቤት የተከተለው የጭብጥ አመሰራረት ሥርዓት ፍርድ ቤት ጭብጥ ሊመሠርት ስለሚችልባቸው መንገዶች በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገና የሥነ-ሥርዓት ጉድለት የሌለበት ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የጉዳዮን መሠታዊ ጭብጥ የያዘው በፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 (ሀ)መሠረት አመልካች በክስ ማመልበቻዋ ያቀረበችውን ጥያቄ የተጠሪ መልስ ፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428 (ሐ) በተደነገገው መሠረት የቃል ምርመራ ሲያደርግ አመልካችና ተጠሪ የሰጡትን መልስና ማብራሪያ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎትና አብላጫው ድምጽ የወረዳው ፍርድ ቤት በጭብጥ ሲመሠረት የሥነ-ሥርዓት ሕግ ድንጋጌዎችን እንዳልከተልና መሠረታዊ የሆነ የሥነ ሥርዓት ሕግ ጥሰት እንደተፈፀመ አድርገው የሰወጡት ትርጓሜና የደረሱበት መደምደሚያ አሳማኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

3. ከላይ ከክርክር እንደገለፀነው አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 1/90 በወረዳው ፍርድ ቤት ተከራክረው የመጨረሻ ውሳኔ ያገኘው በመቀሌ ከተማ ደቡብ ወረዳ ሐድነት ጣቢያ ሚገኘው በምሥራቅ 533 በምዕራብ አደባባይ በሰሜን 530 እና በደቡብ 534 የሚያዋስኑት ቦታ ነው፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት የፍትሐብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428(ሀ) እና የፍታብሐር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 428(ሐ) ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ ከጭብጥነት የያዘውና የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ በመስማትና በመመዘን ውሣኔ የሰጠው የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ ታህሣሥ 15 ቀን 1995 በመቐልሕ

ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 የገለፀው ቦታ ነው፡፡ ቦታው በአዋሳኝ ምልክቶች በሚያሳየው በምስራቅ አቶ ኪዳኑ ፈቃዱ፣ በምዕራብ አቶ አብርሀ ኪዳኑ በሰሜን አደባባይ በደቡብ አቶ ግደይ ገብሩ የሚያዋስኑት ስድስት መቶ ካሬ ሜትር ቦታ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠውምና የዚህ ቦታ ግማሽ የአመልካች ግማሹ ደግሞ የተጠሪ ይዞታ ቦታ ነው በማለት ነው፡ የሥር ፍርድ ቤት የክርክሩ ጭብጥ አድርጐ በያዘው በዚህ ቦታ ላይ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው አያውቁም፡፡ ይኸ ቦታ አመልካችና ተጠሪ በመዝገብ ቁጥር 1/90 ተከራክረው ውሣኔ ካገኘው ቦታ የተለየና ራሱን የቻለ ቦታ ነው፡፡ ይህንን መሠረታዊ ፍሬ ጉዳይ የወረዳው ፍርድ ቤት ብቻ ሣይሆን የወረዳው ፍርድ ቤት ውምኔ በይግባኝ ያቀረበላቸው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 272 በሚደነግገው መሠረት በአካል ከቦታው በመገኘትና ተገቢውን ማጣራት በማድረግ ውሣኔ የሰጡ መሆኑን ከዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የውሳኔ ግልባጭ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም አመልካች የሰበር አቤቱታ አቅርበውበት በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 1/90 ተከራክረው የመጨረሻ ውሣኔ ካገኘው ቦታ የተለያየና ራሱን የቻለ ቦታ ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጐ የመሠረተውና የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ የሰጠበትና ጉዳዩ መጀመሪያ በይግባኝ ያየው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ተጨማሪ ማጣራት በማድረግ ውሳኔ ሰጥቶበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የፀና ውሳኔ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ ያልተከራከሩበትና ውሳኔ ያላገኘ ጉዳይ ነው፡፡ አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው በመዝገብ ቁጥር 2/90 ውሳኔ ያገኘ ቦታ የወረዳው ፍርድ ቤት የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ አድርጐ፣ ከያዘው የአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሳኔ ከሰጠበትና ጉዳዩንም በይግባኝ አይተው ያፀደቁት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሳኔ ከሰጡበት ጉዳይ የተለየ ነው፡፡

አመልካችና ተጠሪ ከዚህ በፊት ተከራክረው ውሳኔ ያገኘው ቦታና በዚህ ጉዳይ የመቀሌ ወረዳ ፍርድ ቤት የዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በጭብጥነት ይዘው ውሳኔ የሰጡበት ቦታ የተለያዩ መሆናቸውን የሥር ፍርድ ቤቶች ውሣኔ በግልጽ እያሳየ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አላግባብ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ በመጥቀስ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትና በዚህ ችሎት ሊሻርና ሊታረም የሚገባው ነው የሚል እምነት አለን፡፡ በያዝነው ጉዳይ በጭብጥነት የተያዘውና በየደረጃው ያሉ የትግራይ ፍርድ ቤቶች አጣርተው ውሳኔ የሰጡበት ቦታ ከዚህ በፊት አመልካችና ተጠሪ ተከራክረው በውሣኔ ካለቀው ቦታ የተለየ በሆነበት ሁኔታ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ 1 ተፈፃሚነት እና አግባብነት የሌለው በመሆኑ በድንጋጌው መንፈስና ዓላማ እንዲሁም ይዘት ጋር የማይጣጣም ትርጉም የመስጠት የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠውን ውሳኔ አብላጫ ድምጽ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ማጽናቱ አግባብነት ያለው ነው ብለን ባለማመናችን በሐሳብ ተለይተናል፡፡

4. በእኛ በኩል በበታች ፍርድ ቤቶች በተለይም ክርክሩን በመጀመሪያ አይቶ ውሣኔ በሰጠው በወረዳ ፍርድ ቤት በአመልካችና በተጠሪ መካከል የነበረውን ሙግት በሚመለከት በሚመራበት ወቅት የፈፀመው የሥነ ሥርዓት ጉድለት ቀላል የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች በክስ ማመልከቻዋ ከገለፀቻቸው ሁለት ቦታዎች ውስጥ የወሰን መለያ ምልክቶችን ጠቅሶ የጠየቀችው ቦታ ከዚህ በፊት በውሣኔ የተቋጨ እንደሆነ አመልካች ክስ ለማቅረብ ምክንያት የሆነውና በፍርድ ተጣርቶ እንዲወሰንላት የምትጠይቀው በመቐለሕ ትግራይ ጋዜጣ በተራ ቁጥር 755 መዝገቦ የመቀሌ ሥራና ከተማ ልማት መምሪያ የወጣው ቦታ እንደሆነ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 241 መሠረት ባደረገው የቃል ምርመራ ግልጽ ሆኗል፡፡

ስለሆነም በአመልካች በክስ ውስጥ የወሰን መለያ ምልክቶችን በመጥቀስ ያቀረበችውን የክስ ክፍል ሙሉ በሙሉ በማውጣት በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 የተጠቀሰውን ቦታ አዋሻኝ የድንበር መለያ ምልከቶች በመግለጽ ክሷን አሻሽላ እንድትቀርብ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 91 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በራሱ አነሳሽነት ትእዛዝ በመስጠት ጉዳዮን ለክርክር ክፍተት በማይፈጥርበት ሁኔታ አይቶ መወሰን እየቻለ ፍርድ ቤቱ ይህንን ሥርዓት አልተጠቀመበትም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ ፍርድ ቤቱ አመልካች ክሷን እንድታሻሽል ሣያደርግ ክርክሩን ማስቀጠሉ የመከላከል መብቴን የሚያጣብብና የሥነ ሥረዓት ጉድለት ያለበት ነው የሚል እምነት ካለው በወቅቱ የወረዳው ፍርድ ቤት ይህንን የሥነ ሥርዓት ጉድለት እንዲያርመው በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር

207 መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት የነበራቸው ቢሆንም ተጠሪ ይህንን መብታቸውን ያልተጠቀሙበት መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ግልባጭ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

የወረዳው ፍርድ ቤት በአመልካችንና የተጠሪን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ ውሣኔ የሰጠው በመቐልሕ ትግራይ ጋዜጣ ተራ ቁጥር 755 በሥራና ከተማ ልማት መምሪያ በተጠሪ ስም የወጣው ነባር የይዞታ ቦታ ላይ አመልካች መብት አላት ወይስ የላትም የሚለው ጭብጥ በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 248 ድንጋጌዎች መሠረት በመመሥረት በመሆኑ የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ክሷን ሳታሻሽል የአመልካችንና የተጠሪን ክርክር ሰምቶ ውሳኔ መስጠቱ የተጠሪን የመከላከል መብትና የፍትህ መጓደልን ያስከተለ መሠረታዊ የሥነ ሥርዓት ጉድለት ነው ብሎ ለመደምደም የሚያስችለን ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ምክንያቱም ይኸ የወረዳው ፍርድ ቤት የሥነ ሥርዓት ጉሉት የፈፀመበት የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ቀርቦበት የከፍተኛው ፍርድ ቤትም የበኩሉን ተጨማሪ ማጣራት ካደረገ በኂላ አጽድቶታል፡፡ ውሣኔ ድጋሚ ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ቀርቦበት በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ፀድቋል፡፡

አንድ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ ቀላል ሥነ-ሥርዓት ጉድለት የተፈፀመ ሲሆንና የሥን ሥርዓት ጉድለት የፈፀመው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ይግባኝ ቀርቦበት በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የፀደቀ ከሆነ ውሣኔው በተፈፀመው ቀላል ሥነ ሥርዓት ጉድለት ምክንያት ብቻ ውድቅ እንደማይሆን በፍታብሔር ሥነ ሥርዓት 212 ተደንግጓል፡፡ ስለሆነም የወረዳው ፍርድ ቤት አመልካች ክሷን እንድታሻሽል ሣያደርግ አመልካቹንና ተጠሪን አከራክሮ መወሰኑ እንደ መሠረታዊ የህግ ስህተት የሚቆጠርና ውሳኔውን ውድቅ ለማድረግ የሚያስችል ምክንያት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በዝርዝር በገለጽናቸው ምክንያቶች የወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔና በይግባኝ ቀርቦላቸው ያዩት የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የበታች ፍርድ ቤቶች ጭብጥ አድርገው ያልያዙትንና ውሣኔ ያልሰጡበትን ጉዳይ አግባብ በመጥቀስ የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 5 ንዑስ አንቀጽ 1 አላግባብ በመተርጐም የሰጠው ውሣኔ የሥር ፍርድ ቤቶች ጭብጥ አድርገው በመያዝ ውሣኔ የሰጡበትን ፍሬ ጉዳይ ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ ይኸ የሰበር ችሎት ሊሽረውና የተፈፀመውን መሠረታዊ የህግ ስህተት ሊያርመው ይገባል በማለት የልዩነት የውሣኔ ሀሳባችንና ምክንየታችንን ገልፀናል፡፡

የማይነበብ የሁለት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 36460

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡-መሐመድ ሰዓዳይ ረጃ - ጠበቃ አበራ ባሰው ቀርበዋል

**ተጠሪዎች**፡- 1/ አቶ ዓብዱልቃድር መሐመድ ፈረጅ - ቀርበዋል

2/ የህፃን ፊልሚያጀላኒ ሞግዚት ሻ/ሸዋነሽ አሰጋሽኝ - አልቀረቡም

3/ አቶ ሙክታር መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

4/ የአቶ ማሕሙድ መሐመድ ፈረጅ ወራሾች - አልቀረቡም

5/ ወ/ሮ ጀሚላ ጁሃር መሐመድ - አልቀረቡም

6/ ወ/ሮ ዘምዘም መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

7/ ወ/ሮ አለማ መሐመድ ፈረጅ - አልቀረቡም

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ክርክር ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሰ/መ/ቁ. 22079፣ ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይሻርልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት በተካሄደው ክርክር የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ የነበሩ ሲሆን ስር ከሣሾቹ ጥቅምት 28 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ ክስ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም ሰኔ 15 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገው ውል ሕጋዊ ስላልሆነ እንዲፈርስና በተከሣሾቹ እጅ በዚሁ ምክንያት የገቡትን ቤቶች ይመለሱልን የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም ባቀረቡት ተቃውሞ እርሣቸውም ሆነ ከሣሾቹ በኢትዮጵያ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም በውጭ አገር የምንኖር ስለሆነ በአዋጅ 25/88 ዓንቀፅ 5/2/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እንጂ የከተማው ወረዳ ፍ/ቤት ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለውም ብለዋል፡፡

ከሣሾችም በጠበቃቸው በኩል ከላይ ለሰፈረው ተቃውሞ ታህሣሥ 23 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ መልስ የሰጡበት ሲሆን ይዘቱም ምንም እንኳ ከሣሾች በተለያዩ ክልሎች የሚኖሩ ቢሆንም ውሉ የተፈፀመው እና አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት የሚገኘው በመቀሌ ከተማ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን የማየት ስልጣን አለው፤ አዋጅ ቁ. 25/1988 ዓንቀፅ 5/2/ በውል ላይ በተመሠረተ ክርክር አይደለም፤ ተቃውሞው ውድቅ ሊሆን ይገባል የሚል ነው፡፡

የሥር ወረዳ ፍርድ ቤቱም የቀረበው ተቃውሞና መልስ ከላይ ከተመለከተው የአዋጁ ይዘት በማገናዘብ ጉዳዩ የፌዴራል ፍ/ቤቶች ስልጣን ስለሆነ ክርክሩን የማካሄድ ስልጣን የለኝም በማለት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ብይን ሰጥቷል፡፡

ስር ከሣሾቹ ከላይ በሰፈረው ብይን ቅሬታ በማሣደር ወደ መቀሌ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ክርክር ከተካሄደ በኂላ ፍ/ቤቱ ሚያዚያ 05 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ብይን ክርክር የተነሣበት ቤት በመቀሌ ከተማ የሚገኝ በመሆኑ እንዲሁም ውሉ የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ የስር ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና 25/1/ሀ/ መሠረት ስልጣን አለው በማለት የስር ፍ/ቤት ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

ጉዳዩ በስር ተከሣሹ ይግባኝ አቅራቢነት በትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የታየ ሲሆን ይህ ፍ/ቤትም በፍ/ይ/መ/ቁ. 20127፣ ጥቅምት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የወረዳ ፍ/ቤቱ ስልጣን የለኝም የሚል ብይን ከሰጠ በኂላ ስር ከሣሾቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ መሠረት ክሣቸውን አሻሽለው ወደ ወሰነው ፍ/ቤት ወይም ወደሌላ ፍ/ቤት ማቅረብ የሚፈቅድ ሆኖ እያለ ከፍተኛ ፍ/ቤቱ የወረዳውን ብይን መሻሩ ተገቢነት የለውም በማለት የወረዳ ፍ/ቤቱ የሰጠውን ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

በዚህ የጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ቅሬታ በማሣደርም ስር ከሣሾቹ ጉዳዩን ወደ ትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ያቀረቡት ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኂላ በመ.ቁ. 22079፣ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን ለመሻር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245/3/ አጣቅሶ ከሣሾቹ ክሣቸውን አስተካክለው ለሚመለከተው ፍ/ቤት ያቀርባሉ እንጂ ይግባኝ ማለት አልነበረባቸውም ማለቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት እንደሆነና ስር ከሣሾቹ ይግባኝ ከማቅረብ በሕግ አይከለከሉም በማለት የጠቅላይ ፍ/ቤቱን ውሣኔ ሙሉ በሙሉ በመሻር የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ብይን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ከላይ የሰፈረውን የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልን በማለት መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበዋል፤ መሠረታዊ ይዘቱም የቀረበው ክስና ተቃውሞ በአዋጅ ቁ. 25/1988፣ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት በፌዴራል ፍ/ቤቶች የሚታይ እንጂ በክልል ፍ/ቤት አይደለም፤ የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 245 አተረጓጎም ረገድ የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ችሎት ስህተት ፈጽሚል ብሎ ማረም ቢችልም ለመሠረታዊ የክርክራችን ነጥብ የሰጠው መልስ የለም፤ ስለሆነም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሚል የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎችም ሐምሌ 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፤ ይዘቱ ሲታይም እየተከራከሩበት ከመጡት ክርክር ያልተለየ በመሆኑ ደግሞ መዘርዘር ሣያስፈልግ ታልፏል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራና ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ በመገንዘብ ፣

በክሱ የተመለከተውን ጭብጥ የመዳኘት ስልጣን ያለው የትኛው ፍርድ ቤት ነው? የክልሉ ፍርድ ቤት ወይስ የፌዴራል ፍ/ቤት?የሚለውን መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው ተከራካሪ ወገኖች በኢትዮጵያ ግዛት ውስጥ በተለያዩ ክልሎች እንዲሁም ከኢትዮጵያ ውጭ እንደሚኖሩ ነው፤ ግራ ቀኙ ወገኖችም በዚህ ነጥብ የሚካካዱ አይደሉም፡፡ አመልካቹ እያቀረቡት ያለው ክርክር ነዋሪነታቸው በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚደረግ ክርክር በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 25/1988 ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ጉዳዩን የመዳኘት ስልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ናቸው የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ደግሞ አከራካሪው ጉዳይ በመቀሌ ከተማ ውስጥ በሚገኝ ቤት የሚካሄድ ስለሆነና ውሉም የተፈፀመው በዚሁ ከተማ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 24/1/ እና 25/1/ሀ/ መሠረት ክርክሩን የመዳኘት ስልጣን ያለው አራካሪው ቤት ባለበት የተቋቋመው የመቀሌ ደቡብ ወረዳ ፍርድ ቤት እንጂ የፌዴራል ፍርድ ቤት አይደለም ባይ ናቸው፡፡ አዋጅ ቁጥር 25/1988 የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን በማቋቋም ብቻ ሚናው የታጠረ አይመስልም፤ከዚህም አልፎ በፌዴራል ፍርድ ቤቶችና በክልሉ ፍርድ ቤቶች መካከል ስልጣን የሚደለድል መሠረታዊ ሕግ ነው፡፡ በዚህ አዋጅ ዓንቀጽ 5/2/ መሠረት ነዋሪነታቸው በተለያዩ የክልል መስተዳድሮች በሆኑ ሰዎች መካከል የሚካሄድ ክርክር የሚስተናገድው በፌዴራል ፍርድ

ቤቶች ነው በማለት በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይህ መሠረታዊ ይዘት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ውስጥ በዓንቀጽ 24/1/ እና 25/1/ሀ/ እንደተመለከተው አከራካሪው የማይንቀሣቀስ ንብረት በአንድ ክልል ስለተገኘ ብቻ ወይም ውሉ የተፈፀመው በአንድ ክልል በመሆኑ ብቻ ጉዳዩ የክልል ፍርድ ቤቶች ተፈጥሯዊ ስልጣን እንዲኖራቸው የሚያደርጋቸው አይደለም፤ ስለሆነም በመጀመሪያ ከስረ -ነገር ስልጣን አኳያ አከራካሪው ጉዳይ ሲታይ የፌዴራል ፍርድ ቤት ስልጣን መሆኑ አጠያያቂ አይደለም፤ ፌዴራል ፍርድ ቤቶችም ስልጣናቸው በሆኑ ጉዳዮች በእያንዳንዱ ክልል በቀጥታ መዋቅራቸውን ዘርግተው ወይም ደግሞ ለሚመለከተው የክልል ፍ/ቤት ውክልና በመስጠት ዳኝነት እንደሚሰጡ ነው፡፡ ስለሆነም የመቀሌ ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት አከራካሪው ቤት በመቀሌ ከተማ በደቡብ ወረዳ በመገኘቱ ብቻ ወይም ውሉ በዚሁ አካባቢ በመደረጉ ወይም የሚፈፀም መሆኑን ብቻ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በአዋጅ ቁጥር 25/88 ዓንቀጽ 5/2/ የተመለከተውን ድንጋጌ ተፈፃሚ እንዳይሆን ስለሚያደርግ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆነው ተገኝተዋል፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የመቀሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 04156፣ ሚያዝያ 05 ቀን 1999 የሰጠው ብይን እንዲሁም የትግራይ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 22079 ጥር 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡
2. በመቀሌ ከተማ፣ የደቡብ ወረዳ ፍ/ቤት ጥር 14 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወገኖች እየተከራከሩበት ያለው ጉዳይ በአዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 5/2/ መሠረት የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ስልጣን ነው፤ ስለሆነም ተጠሪዎቹ ክሣቸውን ከፌዴራል ፍርድ ቤት ውክልና በተሰጠው የሚመለከተው የክልሉ ፍ/ቤት አቅርበው ይከራከሩ ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 39144

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ልዑልሰገድ ቦኔ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ኢትዮ - ሌዘር ኢንዱስትሪ ኃላ/የተ/የግል ማህበር - የቀረበ የለም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች ታኀሣሥ 23 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ ያቋቋሙት የስራ ቅጥር ውል ያላግባብ መቋረጡን ዘርዝረው የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነቱ ቀርቦ አመልካች ከስራ የተሰናበቱት የማታለልና የማጭበርበር ተግባር መፈፀማቸው በማጣራት ተረጋግጦ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች ከስራ የተሰናበቱበት መንገድ በሕጉ አግባብ አለመሆኑን ዘርዝሮ ስንብቱ ሕገወጥ ነው ካለ በኋላ ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄን በተመለተ ግን የስራ ግንኙነቱ መልካም አይሆንም በሚል ምክንያት ባለመቀበል በምትኩ አመልካች የስድስት ወር ደመወዝ በካሣነት ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ በስር ፍ/ቤት አመልካች ካሣ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ የተሰጠው ውሣኔ የስራ ዋስትናን ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ መሆኑ በምክንያትነት ይዞ በስር ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ ከሻረ የአመልካችን ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄ አስመልክቶ ግን በግልጽ ዳኝነት አላሳረፈበትም፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማሻሻል ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 08 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2 /ሁለት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ውሣኔ የዳኝነት አሰጣጥ ተፈፀመ የሚሉትን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን ሲለውጥ ለአመልካች የሚገባውን ዳኝነት በግልጽ ያልጠቀሰ በመሆኑ ይኸው ታርሞ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ለሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርቦ መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሰምቷል፡፡ ተጠሪ የአመልካች ጥያቄ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የማይገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሠረት ውሣኔው በሰጠው ፍ/ቤት ሊስተናገድ ይገባ የነበረ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአመልካች ጥያቄ ለሰበር ችሎቱ መቅረቡ ሥነ ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ነው?፣ሥነ ሥርዓቱን በጠበቀ መንገድ ነው ከተባለስ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ከሻረው በኋላ በአመልካች ወደ ስራ እንድመለስ ይወሰንልኝ የዳኝነት ጥያቄ ላይ ግልጽ ውሣኔ ሣያሣርፍ ማለፉ ተገቢነት አለውን? የሚሉት ነጥቦች በጭብጥነት ሊታዩ የሚገባ ሁነው አግኝተናል፡፡

<u>የመጀመሪያውን ነጥብ በተመለከተ</u>፡- ጉዳዩ መሠረት ያደረገው አዋጅ ቁጥር 377/96 ዓ.ም ሲሆን ይህንኑ አዋጅ መሠረት አድርገው የሚቀርቡ ክርክሮች የሚመሩት በ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ እና በአዋጁ በተመለከቱ ድንጋጌዎች መሠረት ነው፡፡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የስራ ክርክርን የማየት የዳኝነት የሥረ ነገር ሥልጣን ከተሰጣቸው አካላት አንዱ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በቁጥር 138 መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ማየት የጀመረው የስራ ክርክር ውሣኔ ካገኘ በኋላ በይግባኝ የሚታየው በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የሥራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 139 ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ይህ የሥራ ክርክር ይግባኝ ሰሚው ችሎት በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ አንቀጽ 139 በንዑስ ቁጥር ሁለት ድንጋጌ ስር አስቀምጧል፡፡ የስራ ክርክር ይግባኝ ሰሚ ችሎት በሚሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለበት ወገን አቤቱታውን ሊያቀርብ የሚችለው በሰበር ሥርዓት ነው፡፡በመሆኑም በስራ ክርክር ችሎት የተሰጠ ውሣኔ ሊፀና፣ ሊለወጥ ወይም ሊሻሻል የሚችልበት ሥርዓት ይኸው ስለመሆኑ በቀላሉ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ የይግባኝ ቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት ወጪ ጉዳዩን የተመለከተው ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና የሚያስተናግድበት ሥርዓት በሥነ-ሥርዓት ሕጋችን ተመልክቷል፡፡

ከእነዚህ ሠርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ሥር የተመለከተው ስህተት የሚታረምበት ሥርዓት ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አቤቱታ የቀረበለት ውሣኔው የሰጠው ፍ/ቤት ሊያርም ወይም ሊያስተካክል የሚችለው በሰጠው ውሣኔ እና ትእዛዝ ላይ የአፃፃፍ ስህተት፣የቁጥር አፃፃፍ ጉድለት ወይም ያልታሰበና ባለማስተዋል የተዘለለ ድንገተኛ የቃል ስህተት መኖሩን ካረጋገጠ ብቻ ነው ስለሆነም በክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ አከራክሮ የሰጠውን ውሣኔ ስህተትን ማረም ወይም ማስተካከል በሚል መነሻ ውሣኔውን ሊያሻሽል ወይም ሊለወጥ አይችልም፡፡ የክርክሩ ዋነኛ ጭብጥ ላይ ክርክር ተካሂዶ ውሣኔ ከተሰጠ እና በዚሁ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን አቤቱታ ሊያቀርብ የሚገባው ለበላይ ፍ/ቤት ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይም አመልካች ቅሬታ አድሮባቸው ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡት የስር ፍ/ቤት ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄአቸውን ሣይቀበለው ቀርቶ በሕጉ በአማራጭ የተቀመጠውን መፍትሔ /relief/ በመወሠኑ ሁኖ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ሆኖም በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት በግልጽ አልጠቀሰም፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሠረት ሊታረም ወይም ሊስተካከል ይገባ የነበረ ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ ይልቁንም በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት በፌ/ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10/1/ መሠረት ለሰበር ችሎቱ ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ መሠረታዊ የክርክር ነጥብ ነው ስለሆነም የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው ሆኖ ባለማግኘታችን አልፈነዋል፡፡

<u>ሁለተኛውን ነጥብ በተመለከተ</u> ፡- ፍርዱ የክርክሩን ሂደት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮችን ባጭሩ መያዝ እንደአለበት፣ ለአፈፃፀም የማያስቸግር መሆን የአለበት ስለመሆኑ ስለፍርድ አሰጣጥ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት ድንጋጌዎች መንፈስ የሚያስገነዝበን ጉዳይ ነው፡፡ ፍርዱ የሚፈፀመውን ክፍል በግልጽ ካላመለከተ በፍርድ መፍትሔ /relief/ የመሰጠቱን ዓላማ የሚያጓድለው ይሆናል፡፡ ስለሆነም አንድ ፍርድ ሲሰጥ የውሣኔ አፃፃፍ ይዘትና ቅደም ተከተልን መሠረት ያደረገ ከክርክሩ ሂደት እስከመደምደሚያው የያዘው ነገር ግልጽ መሆን አለበት፡፡ ከዚህ ውጪ ያለው የፍርድ አፈፃፀም አካሄድ የተሟላ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ በያዝነው ጉዳይም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢ አለመሆኑን በምክንያት አስደግፎ ከሻረው በኋላ በይግባኝ ደረጃ እንዲወሰን በአመልካች የተጠየቀውን ዳኝነት በግልጽ ሣያሰፍር ማለፉ በፍርድ መፍትሔ የመስጠቱን ዓላማ ያጓደለና የውሣኔውን አፈፃፀም አስቸጋሪ የሚያደርገው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በፍርዱ ሊሰጥ የሚገባውን መፍትሔ በተመለከተ በግልጽ አለመጥቀሱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ስለተገኘ ሊታረም የሚገባው ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 60794 ሚያዝያ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/5/ መሠረት ተጠሪ ለአመልካች የአንድ ዓመት ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራው ይመልስ ብለን ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 38597

ሚያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች፡-** 1. ጋሻው መንግስቴ ካሣ
2. አለሙ አብሬ ደነቦ } ጠበቃ ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ናይል ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር - ጠበቃ ምናለ አለሙ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሣውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር አመልካቾች ከሣሾች የነበሩ ሲሆን፣በተጠሪ ላይ ክስ የመሰረቱት የስራ ውላቸው ከሕግ ውጪ መቋረጡን በመግለጽ ልዩ ልዩ ክፍያዎች እንዲከፍላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ ተጠሪም ለክሱ በሰጠው መልስ ከክፍያዎቹ አንዱ የሆነው የፕሮቪደንት ፈንድ የተጠየቀው በሕጉ የተመለከተው የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ነው የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና ሌሎች የስረ-ነገር ክርክሮች በማንሳት ክሱ ይሰረዝ ዘንድ ጠይቆአል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ፣የስራ ውሉ የተቋረጠው በአግባቡ ነው እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ በመቀጠልም ለከሣሾች ሊከፈል የሚገባው የስንብት ክፍያ ብቻ ነው፤ የካሣ እና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያዎች ተቀባይነት የላቸውም በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የበኩሉን ክርክር ከሰማ በኋላ፣ውሳኔውን አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካቾች ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ያቀረቡትን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ቀደም ሲል ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ የፕሮቪደንት ፈንድ ለመክፈል ፈቃደኛ መሆኑ ወይም ማመኑ ተገልፆ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የፕሮቪደንት ፈንድ አይከፈልም በማለት የሰጡትን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም መጀመሪያ የአሁኖቹ አመልካቾችን ጨምሮ 53 ሰራተኞች በተጠሪ ላይ ክስ እንደመሰረቱ እና ተጠሪ የበኩሉን የመከላከያ መልስ ከሰጠ በኋላ የአሁኖቹ አመልካቾች ክስ ለብቻው ተነጥሎ እንዲታይ ስለታዘዘ በዚሁ መሰረት አመልካቾች ሌላ ክስ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ለመጀመሪያው ክስ በሰጠው መልስ(ሚያዝያ 7 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈው) የፕሮቪደንት ፈንድ እና ሌሎች ክፍያዎች ለከሣሾች ሊከፈል እንደሚገባ እንደሚያምን በግልጽ ያመለከተ ሲሆን፣አመልካቾች ተነጥለው ለመሰረቱት ክስ በሰጠው መልስ ግን የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ጥያቄው በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚል መቃወሚያ ማቅረቡን ተመልክተናል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የአመልካቾች ክስ ተነጥሎ እንዲቀርብ የታዘዘው በፍ/ቤቱ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ይህን ትእዛዝ ሊሰጥ የቻለው የሁለቱ ሰራተኞች የስራ ውል የተቋረጠው ከሌሎች ሰራተኞች በተለየ ሁኔታ ነው በመባሉ እንደሆነ

ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ለመረዳት ችለናል፡፡ በአጠቃላይ ሲታይ ግን የፕሮቪደንት ፈንድ እና የሌሎች ክፍያዎች ጥያቄ የቀረበው በሁሉም ሰራተኞች ነው፡፡ ተጠሪ በመልሱ ላይ ያመነውም ይህንኑ በአጠቃላይ ነው፡፡ በመሆኑም በስነ-ስርአት ሕጉ መሰረት ክርክሩን ለመለወጥ ይችል ዘንድ ጥያቄ አቅርቦ ሳይፈቀድለት እግረ መንገድ ባነሳው የይርጋ መቃወሚያ ተጠቃሚ ሊሆን አይችልም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም የይርጋ መቃወሚያ በአግባቡ አቅርቤአለሁ አላለም፡፡ አጥብቆ የተከራከረው አመልካቾች የፕሮቪደንት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ብዬ መልስ አልሰጠሁም በማለት ነው፡፡ ይህ አባባሉ ደግሞ ሚያዝያ 7 ቀን 97 ዓ.ም የሰጠውን ግልጽ የመከላከያ መልስ የሚቃረን ነው፡፡ ስለዚህም አመልካቾች የጠየቁት የፕሮቪደንት ፈንድ የማይከፈልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23556 በኀዳር 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61971 ሚያዝያ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. አመልካቾች የጠየቁትን የፕሮቪደንት ፈንድም ተጠሪ ሊከፍል ይገባል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 40024

ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- ሸራተን አዲስ- አቶ ኃይሉ ንጋቱ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**:- እነ አቶ እያሱ- መገርሣ ቀረቡ

በዚህ መዝገብና በሰበር መዝገብ ቁጥር 40390 የተያዘው ክርክር ተጣምረው መታየታቸው የበታች ፍርድ ቤት በሁለት የተለያዩ መዝገቦች የሰጠውን ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው መሆኑን ለመመርመርና ተገቢውን ውሣኔ ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘነው በዚህ መዝገብ የቀረበውን ክርክር በሰበር መዝገብ ቁጥር 40024 ከቀረበው ክርክር ጋር መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የከፍተኛው ፍ/ቤት ሌላ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 62996 ሰኔ 4 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው በመሆኑ በሰበር ታይተው ይታረሙልኝ በማለት ነሐሴ 13 ቀን 2000 ዓ.ም እና ነሐሴ 3 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፉ የሰበር አቤቱታዎች በማቅረብ ሁለቱን መዝገቦች በማስከፈቱ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪዎች በከሳሽነት ቀርበው ተከሳሽ (የአሁን አመልካች) 1996 ዓ.ም ጀምሮ በዳቦና ኬክ አዘጋጅነት ቀጥሮ ሲያሰራን ቆይቶ ነሐሴ 19 ቀን 1999 ዓ.ም የስራ ውላችንን ያላንዳች ምክንያት ያቋረጠብን በመሆኑ የስራ ውሉን አላግባብ በማቋረጡ የካሣና የስራ ስንብት ክፍያ፣ ክፍያ ለዘገየበት፣የሰርቪስ ቻርጅ ብር 2000(ሁለት ሺህ ብር)፣ በሌሊት የሰራንበት፣ ቅዳሜና እሁድ የሰራንበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እና የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ተለውጦ ከስድስት ወር ደመወዛችን ጋር ይከፈለን የሚል ክስ አቅርበዋል፡፡

አመልካች በተከሳሽነት ቀርቦ ከስድስት ወር በፊት ያቀረቧቸው የተለያዩ የክፍያ ጥያቄዎች በይርጋ ይታገዳሉ፤ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል የተረጋገጠ መብት የላቸውም ተብሎ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳይ ረገድም ከሳሾች (ተጠሪዎች) የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ ነው፤ ስብሰባና ሰርግ ሲኖር እየተጠሩ ለተወሰነ ጊዜ የሰሩ ቢሆንም በተከታታይ ለሶስት ዓመት አልሰሩም፤ የሰርቪስ ቻርጅ እና የአዳሪ ክፍያ የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ስለሆነ ሊጠይቁ አይገባም፤ ቅዳሜና እሁድ ለመስራታቸው ማስረጃ አላቀረቡም በማለት ተከራክሯል፡፡

የስር ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ የሰማ ሲሆን አመልካች አንድ ምስክር አቅርቦ ምስክሩ ተጠሪዎች ስራ ሲበዛ ለማቃለል የተቀጠሩና ደካማ የስራ ውጤት በማሣየታቸው የተሰናበቱ መሆኑን የመሰከረ ሲሆን ተጠሪዎች ራሳቸው በምስክርነት ቀርበው ላልተወሰነ ጊዜ መቀጠራቸውንና በተከታታይ መስራታቸውን መስክረዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ መዝኖ የስራ ውሉ የተደረገው ለተወሰነ ጊዜ ነው፤ ከሳሾች (ተጠሪዎች) ያቀረቡት የስራ ስንብት ክፍያ፣ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ተፈፃሚነት የለውም፤ ትርፍ ሰዓት መስራታቸውን ባለማስረዳታቸው ጥያቄቸው

ተቀባይነት የለውም፤ የሰርቪስ ቻርጅ ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠረ ሰራተኛ ብቻ የሚከፈል መሆኑን ተከሳሽ (አመልካች) አላስረዳም፣ ይክፈል፤ የሁለት ዓመት ፈቃድ በገንዘብ ቀይሮ ይክፈል፤ የተለያዩ ክፍያዎች ከስድስት ወር በፊት ያሉት በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ፤ የቅዳሜና እሁድ ክፍያ በይርጋ የማይታገደውን ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት አመልካች የራሱን የይግባኝ ቅሬታ ተጠሪዎች ደግሞ የራሳቸውን የይግባኝ ቅሬታ በማቅረብ ሁለት የይግባኝ መዝገቦች በማስከፈት ክርክር አድርገዋል፡፡ በመጀመሪያ ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ያቀረቡትን የይግባኝ ቅሬታና የአመልካችን ክርክር በከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰማው ችሎት ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው፤ ስለሆነም የስራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ለእያንዳንዳቸው የሁለት ወር ክፍያ በሕጉ መሰረት ተሰርቶ እንዲከፈላቸው በማለት ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ውሣኔ ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረበውን የይግባኝ ቅሬታና ተጠሪዎች ለይግባኙ የሰጡትን መልስ በመዝገብ ቁጥር 62996 ሰምቶ የወሰነው ሌላው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ችሎት ቅዳሜና እሁድ የሰሩ መሆኑን ተጠሪዎች ያላስረዱ መሆኑን በመግለጽ የስር ፍርድ ቤት ቅዳሜና እሁድ ለሰሩበት ይከፈላቸው ማለቱ ተገቢ አይደለም በማለት የቅዳሜና እሁድ ክፍያ ብቻ የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ሰኔ 4 ቀን 2000 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች በሁለቱም መዝገብ የሰጧቸው ውሳኔዎች መሰረታዊ ስህተት እንዳለባቸው በመግለጽ እነዚህን ሁለት የሰበር መዝገቦች አስከፍቷል፡፡ አመልካች በዚህ መዝገብ ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ እንደተቀጠሩ ይቆጠራል በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ካሣና ሌሎች ክፍያዎች መወሰኑ ተገቢ አይደለም በማለት ያመለከተ ሲሆን፤ አመልካች በሰበር መዝገብ ቁጥር 40390 ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የሰርቪስ ቻርጅ የሚከፈለው ላልተወሰነ ጊዜ ለተቀጠሩ ሰራተኞች ብቻ ሆኖ እያለ ብር 2000 (ሁለት ሺህ ብር) ይክፈል መባሉ ተገቢ አይደለም፤ ስለዚህ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች አመልካች በሁለቱም መዝገቦች ያቀረባቸውን የሰበር አቤቱታዎች በመቃወም መልስ ሰጥተዋል፡፡ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩና በተከታታይ ያለማቋረጥ ሲሰሩ እንደነበር የአመልካች ምስክር ገልጿል፤ ምስክሩ በስራ ድክመት ተባረሩ የሚል ቃል የሰጠ ቢሆንም ይህንን የሚደግፍ ማስረጃ አልቀረበም፤ የሰርቪስ ቻርጅ እንዲከፈለን መወሰኑ በአግባቡ ነው፤ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ ባቀረቧቸው መልሶች ተከራክረዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥ፣ የከፍተኛ ፍ/ቤት ሁለት የተለያዩ ችሎቶች የተጠሪዎችንና የአመልካችን ይግባኝ መርምረው የሰጡት ውሣኔና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው በከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩ ታይቶ የተወሰነበት ስርዓት በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውና ይግባኝ ባዮች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ስለሆኑ የካሣ ክፍያ፣ የማስጠንቀቂያ ክፍያ እና ሌሎች ክፍያዎች እንዲከፈሉ የተሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚሉት ጭብጦች እልባት ማግኘት ያለባቸው ሆነው አግኝተናቸዋል፡፡

1. የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ ቅሬታ የተሰማቸው አመልካችም ተጠሪዎችም ናቸው፡፡ ሁለቱም በውሣኔው ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ ሆኖም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በአመልካች ቅሬታ አቅራቢነት ከተከፈተው የይግባኝ መዝገብ ቁጥር 62996 በተጠሪዎች ቅሬታ አቅራቢነት ከተከፈተው የይግባኝ መ/ቁጥር 62985 ጋር በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 11 ንኡስ አንቀጽ 5 መሰረት በማጣመር እንዲታይ ማድረግ ሲገባው ከአንድ ውሣኔ የተነሱ ሁለት ይግባኞች በሁለት የተለያዩ ችሎቶች እንዲታዩ በመደረጋቸው እርስ በርሳቸው የሚቃረኑና አንድ ላይ ሊፈፀሙ የማይችሉ ሁለት ውሣኔዎች ተሰጥተዋል፡፡ የስነ- ስርአት ሕጉ በአንድ ዘንግ ከሚመደቡ ተከራካሪዎችና በአንድ ጭብጥ ላይ የሚቀርቡ ክርክሮች ተጣምረው እንዲታዩ የሚደነግገው በተመሣሣይ ጉዳይ እና ጭብጥ የተለያዩ ችሎቶች የተለያየ ውሣኔ እንዳይሰጡ ለመከላከልና የስራ ቅልጥፍና እና የውሣኔ ወጥነትን ለማረጋገጥ ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሁለቱ የይግባኝ መዝገቦች ተጣምረው እንዲታዩ ባለማድረጉ ተጠሪዎች ይግባኝ ባሉበት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሎ የፍርድ ባለመብት የሆኑበት፣ አመልካች ይግባኝ ባለበት መዝገብ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሎ ፍርድ ያገኘበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የሁለቱን ችሎቶች ውሣኔዎች በጋራ አይቶ ማስተካከያ ካልተደረገ በስተቀር እርስ በርሳቸው የሚቃረኑና በአንድ ላይ ሊፈጸሙ የማይችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሥነ-ሥርአት ግድፈት ያለበት ነው፡፡

2. ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ተጠሪዎች በአንድ ወቅት በነበረ የስራ ብዛት ምክንያት ተቀጥረው ለተከታታይ ሲሰሩ ቆይተው ባሳዩት የስራ ድክመት የተሰናበቱ መሆኑን በማስረጃ የአመልካች ምስክር የመሰከረ መሆኑን በመመዘንና የተጠሪዎችን የምስክርነት ቃል በመመዘን ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሰራተኞች ናቸው፤ የስራ ውላቸውም የተቋረጠው ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ነው በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የሰጠው ውሣኔ በመዝገቡ አመልካችና ተጠሪዎች ያቀረቡትን ማስረጃ በመመዘን የሰጠውና መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ በአግባቡ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ለተጠሪዎች መክፈል የሚገባቸውን ክፍያዎች በተመለከተም የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 የስራ ስንብት ክፍያ የካሣ ክፍያና የማስጠንቀቂያ ለእያንዳንዳቸው የሁለት ወር ደመወዝ በሕጉ መሰረት እንዲከፍል የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62996 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች እንዲከፍል የወሰነውን የቅዳሜና እሁድ ክፍያ ብቻ በመሻር አመልካች ለተጠሪዎች ከመጋቢት 29 ቀን 1999 እስከ መስከረም 29 ቀን 2000 በወር ብር 2000(ሁለት ሺህ ብር) የሚታሰብ የሰርቪስ ቻርጅ ክፍያ፣ የሁለት ዓመት የዓመት ፈቃድ በገንዘብ ቀይሮ እንዲከፍል የሰጠውን ውሣኔ በራሱ ብቻውን ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የሌለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ጉዳዩ በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 11 ንኡስ አንቀጽ 5 መሰረት ተጠቃልሎ ባለመታየቱ በሁለቱ መዝገቦች የተሰጡ ውሣኔዎች የተለያዩና እርስ በርስ የሚቃረኑ ከመሆናቸው ውጭ በይዘታቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለባቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62996 የሰጠው ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62985 ከሰጠው ውሣኔ ጋር ተጣጥሞ ተፈፃሚ ሊሆን በሚችልበት ሁኔታ በማጣመር አጽንተናል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች የተቀጠሩት ላልተወሰነ ጊዜ ነው ብለናል፡፡ አመልካች የተጠሪዎችን የስራ ውል ያቋረጠው የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎችን ሣይከተል ከሕግ ውጭ በሆነ መንገድ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች የተጠሪዎችን ውል ከሕግ ውጭ በማቋረጡ፣
    - የስራ ስንብት ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 40 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት፣
    - የካሣ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር አንቀጽ 377/1996 አንቀጽ 43(4)ሀ መሰረት፣
    - የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ የሁለት ወር ደመወዛቸውን፣
    - የስድስት ወር የሰርቪስቻርጅ ክፍያ በሁለት ሺ ብር (2000) ሒሳብ
    - የሁለት ዓመት የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ በገንዘብ ተሰልቶ፣ ሊከፍላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ ብለናል፡፡

የዚህ ፍርድ ግልባጭ ተገልብጦ ከመዝገብ ቁጥር 40390 ጋር ይያያዝ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 34504

ሚያዝያ 6 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ አበባው የሺድንበር አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሣ በቀለ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የጉዳዩ መነሻ የመንዝ ጌራ ምድር ወረዳ ፍ/ቤት መስከረም 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 14/95 በሆነው በ10/7/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው እግድ ትዕዛዝ ስላልተነሳ በመዝገቡ ላይ ክርክር መቀጠል አልተቻለም ሲል መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 16552 በሆነው ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ብይኑን አጽንቶታል፡፡ እንደገና በይግባኝ የመረመረው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በሆነው መዝገብ ኀዳር 13 ቀን 2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት መልስ ሰጭ የሆነውን የአሁኑን አመልካችን ሳይጠራውና ሳያከራክር "ምንም እንኳን ሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም" በማለት ተጠሪ ጣልቃ ገብቶ እንዲከራከር የተሠጠ ውሣኔ የሌለ በመሆኑ የመጀመሪያው ክስ ቢዘጋለትም እንደ ገና እንዲንቀሳቀስለት በተወሰነው መሠረት ክርክሩ እንዲቀጥል የተፈጠረው ስህተት ተስተካክሏል በማለት ውሣኔውን በመለወጡ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ታህሣሥ 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ ለተጠሪ ደርሶት ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ አቅርቧል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ በአጭሩ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በመሠረቱ በፍ/ቤቶች የተከራካሪ ወገኖች ማንኛቸውም አቤቱታና ቅሬታ በዳኝነት ሊታይ የሚችለው በሕግ በተመለከቱ ሥርዓቶች ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ምንም እንኳን የሥነ-ሥርዓት ሕጉ ባይፈቅድም በማለት በበታች ፍ/ቤቶች የተፈጠረውን ስህተት ለማረም የአሁኑን አመልካች ሳይጠራውና ሳያከራክረው የአንደኛውን ወገን ቅሬታና ክርክር ብቻ በመስማት ውሣኔ ላይ መድረሱ የአንደኛውን ወገን የመሰማት መበት የተጋፋና ከሥነ - ሥርዓት ሕግ ውጪ ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ ሥር በግልጽ እንደተመለከተው ይግባኝ የቀረበለት ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሠረት ያልሠረዘ እንደሆነ ይግባኙ የሚሰማበትን ቀነ ቀጠሮ ወስኖ መልስ ሰጭው ቀርቦ እንዲከራከር መደረግ እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ይህን በሕግ የተመለከተውን የመሰማት ሕገ-መንግሥታዊ መብት /the right to be heard/ ባልጠበቀ መልኩ የተሰጠው ውሣኔ በየትኛውም መመዘኛ ፍትሐዊና የሕግ መሠረት አለው ለማለት የሚቻልበት አግባብ የሌለ በመሆኑ አንደኛውን ወገን ሳይጠራና ሳያከራክር የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 44/2000 በ13/3/2000 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁጥር 338/1/ መሠረት ግራ ቀኙን አከራክሮ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት እንዲመለስ ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለናል፡፡
4. የውሣኔው ግልባጭ ለአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37761

ሚያዝያ 20 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ገብረመስቀል ንጉሴ- ጠበቃው ቀርቧል

**ተጠሪ**፡- አዲስ ልብስ ስፌት አ/ማ- ጠበቃው ቀርቧል፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውል ግንኙነትን መሠረት የደረገ የገንዘብ ክፍያ ጥያቄን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በመሐከላችን በተደረገው የመኪና ጥገና ውል መሠረት መኪናዬን ለጥገና ተረክቦ የነበረ ቢሆንም በአግባቡ ያልጠገነ በመሆኑ የከፈልኩትን የጥገና ስራ ዋጋ ይመልስልኝ፤ መኪናው ቶሎ ተጠግኖ ባለመመለሱ ለሠራተኞች ትራንስፖርት ወጪ ያደረግኩትንም ይተካልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በተገባው ውል መሠረት መኪናውን ጠግኜ በአግባቡ አስረክቤአለሁ፤ ከሣሽ መኪናውን ፈትሾ ከተረከበና ዋጋውንም ከከፈለ በኋላ ሲገለገልበት ቆይቶ ዋጋውን መልስ ሊለኝ አይችልም፤ ለሠራተኞች ትራንስፖርት ወጣ የተባለው ገንዘብም እኔን አይመለከትም በማለት በአንድ በኩል የተከራከረ ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በውሉ መሠረት መኪናውን በድጋሚ ተረክቤ የመለዋወጫ ዕቃዎችን ከውጪ ሐገር በመግዛት የሠራሁ ስለሆነና ከሣሽም በዚሁ ስለተስማማ ለመለዋወጫ ዕቃዎች ያወጣሁትን ገንዘብ ይተካልኝ በማለት የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ መሥርቷል፡፡

ክሱን የሰማው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሁለቱን ወገኖች ካከራከረ በኋላ የተጠሪን ክስ ሙሉ በሙሉ ውድቅ በማድረግ አመልካች ያቀረበውን የክፍያ ጥያቄ ተቀብሏል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ባለመስማማቱ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፤ ፍ/ቤቱም የተጠሪን ክስ በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ሲያፀና አመልካች ባቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ ሽሯል፡፡ በዚህም አመልካች ለመለዋወጫ ዕቃዎች አወጣሁት ያለው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም ብሏል፡፡ በመጨረሻም አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱ ውሣኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ሰርዟል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የተጠሪን መኪና /አውቶቡስ/ ሲጠግን ለመለዋወጫ ዕቃዎች ያወጣው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተገለፀው የተከራካሪዎቹ ግንኙነት የተመሠረተው በውል ላይ ነው፡፡ አመልካች በውሉ የገባው ግዴታ የተጠሪን አውቶቡስ /መኪና/ በጋራዡ ጠግኖ ለማስረከብ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ጠግኖ ለተጠሪ ከማስረከቡም በላይ፤ በውሉ የተመለከተውን የጥገና ዋጋውንም ወስዷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአውቶቡሱ ርክክብ ከተፈፀመ በኋላም ተመልሶ ወደ ጋራዥ ገብቷል፡፡ አመልካችም በውሉ በገባው የዋስትና ግዴታ መሠረት ነፃ የቴክኒክ አገልግሎት በመስጠት መኪናውን ጠግኖ ለተጠሪ አስረክቧል፡፡ የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ የመሠረተውም በዚህ ጊዜ ለገጠማቸው የመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ ያወጣው ወጪ እንዲተካለት ነው፡፡

በአመልካች እና በተጠሪ መካከል በተደረገው ውል የአመልካች ግዴታ የመለዋወጫ ዕቃዎችን በራሱ ወጪ ገዝቶ መግጠምን አያጠቃልልም፡፡ የመለዋወጫ ዕቃ ወጪ የሚሸፈነው በተጠሪ ነው፡፡ በእርግጥ ከብር 1000 /አንደ ሺህ ብር/ በላይ የሚያወጣ የመለዋወጫ ዕቃ ሲገዛ ተጠሪ መፍቀድ እንዳለበት በውሉ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና ተጠሪ አመልካች ላቀረበው የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ በሰጠው መልስ የመለዋወጫ ዕቃዎቹ እንዲገዙ አልፈቀድኩም የሚል ክርክር እንዳላቀረበ በስር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ በግልጽ ተመልክቷል፡፡ የተባሉት የመለዋወጫ ዕቃዎች በመኪናው ላይ አልተገጠሙም የሚል ክርክርም የለውም፡፡ ይልቁንም መኪናው ለሁለተኛ ጊዜ ጥገና ወደ ጋራዡ እንደገባ የክፍያ ጥያቄ እንደሚነሣ ያወቀና ይህንም ለአመልካች በፃፈው ደብዳቤ ገልጾ እንደነበር በፍ/ቤቱ ውሣኔ ላይ ተመልክቷል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ገንዘቡ ለአመልካች እንዲከፈል የወሰነው እነዚህን ምክንያቶች እግምት ውስጥ በማግባት እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ እንዳየነው ፍ/ቤቱ አመልካች የመለዋወጫ ዕቃዎቹን አልገዛም ወይም ለመኪናው ጥገና አላዋላቸውም እሚል ድምዳሜ ላይ አልደረሰም፡፡ ገንዘቡ አይከፈልም ያለው ዕቃዎቹ የተገዙት ከተጠሪ ዕውቅና ውጪ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ብቻ ነው፡፡ ከላይ እንዳመለከትነው ተጠሪ ከኔ እውቅና ውጪ የተገዙ ናቸው የሚል ክርክር አላቀረበም፡፡ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረበው ክርክርም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብቻ ሣይሆን፣ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክርም የመለዋወጫ ዕቃዎቹ ከኔ እውቅና ውጪ የተገዙ ናቸው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አለማቅረቡን ነው ያረጋገጠው፡፡ በሰበር ችሎት የተከራከረው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ክርክሩ ባይቀርብለትም በይግባኝ ሰሚነት ስልጣኑ ትክክል የመሰለውን የመከራከሪያ ነጥብ በመያዝ አከራክሮ መወሰኑ ትክክል ነው በማለት ነው፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ የሚከራከረው ከአመልካች ጋር ያለውን የውል ግንኙነት መሠረት በማድረግ እንደመሆኑ ውሉን መሠረት በማድረግ የሚቀርቡትን የመከራከሪያ ነጥቦች አንስቶ ሊከራከር ይገባል፡፡ በራሱ በተጠሪም እንደታመነው የመከራከሪያ ነጥቡን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አላቀረበውም እንጂ ቢያቀርበውም ኖሮ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 329/1/ እንደተመለከተው ተቀባይነት የሚኖረው አልነበረም፡፡ በእርግጥ ፍ/ቤቱ የተባለውን ነጥብ በራሱ ማለትም በፍ/ቤቱ የተነሣ ሣይሆን፣ ተጠሪ በይግባኝ ማመልከቻው ገልጾት የነበረ እንደሆነ ነው በውሣኔው ላይ ያመለከተው፡፡ ይህም የሚያሣየው ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 182/2/ በተደነገገው መሠረት የሰጠው ውሣኔ አለመሆኑን ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 329/1/ የተመለከተውን ክልክላ በማለፍ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ያልተነሣን ክርክር መሠረት በማድረግ ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ውሣኔ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሊወስን ሲገባው ያልወሰነው ጉዳይ የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ.182/2/ አኳያ የሚያይበት የሕግ ምክንያት ነበር የሚባልም አይደለም፡፡ ስናጠቃልለው አመልካች ለመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ ያወጣው ገንዘብ ሊከፈለው አይገባም በሚል የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የሕግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ውሣኔው መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 32885 የካቲት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 43808 ሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች ለመኪናው ጥገና ለዋሉ የመለዋወጫ ዕቃዎች መግዣ አወጣሁት ያለውና ክስ የመሠረተበት ገንዘብ እንዲከፈለው በማለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ፀንቶአል፡፡

3. በሰበር ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 38181

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ጌታቸው አካሣ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ትዕግሥት ወንድይፍራው - ጠ/ላቀ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ባህሩ አህመድ - በሌሉበት

## <u>ፍ ር ድ</u>

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ክስ በሚሠማበት ቀጠሮ የከሣሽ /የይግባኝ ባይ/ አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ በክሱም የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውን መኪና ሁለተኛ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በግልገል ግቤ ወንዝ ላይ የተሠራው ድልድይ ላይ ጉዳት በማድረሣቸው ተጠሪዎች ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የከሣሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው መልስ ሰጪዎች ባሉበት የሚጣራ ነጥብ በማግኘቱ ይግባኙን ለመስማት ቀጠሮ ሠጥቷል፡፡

ይግባኙ በሚሠማበት ዕለትም አመልካች ባለመቅረቡና የአንደኛ ተጠሪ ጠበቃም መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ስለጠየቁ ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ዘግቷል፡፡ አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እንዲፈቀድ አመልክቶ ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ በቅሬታውም አንደኛ ተጠሪ የተከሠሠበትን ነገር ሣይክድ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ ለሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ መስጠት እንዳልተቻለ ለፍ/ቤቱ ተገልፆ የርሣቸው ጥሪ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ እያለ ጉዳዩን ለመስማት የሚያስችል ሁኔታ ሣይኖርና ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ ሣይጠሩ መዝገቡ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ በቀጠሮው እለት ያልቀረብንበት በቂ ምክንያት እያለ መታለፉ ስህተት ነው፤ በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ መዝገቡ ተከፍቶ እንዲታይ አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ታዘው ሁለተኛ ተጠሪ አልቀረቡም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሠምቷል፡፡ ከፍ ሲል የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊመለስ የሚገባው የይግባኝ ቅሬታው በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ ያልቀረበ ቢሆንም አንደኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ክደው ሣይከራከሩ መዝገቡ መዘጋቱ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ስለ ባለጉዳዮች ፍ/ቤት መቅረብና ሣይቀርቡ መቅረት በሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የሚገኘው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ሣይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሣሹ ቀርቦ

የተከሠሠበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተከሣሽ ላመነው ጉዳይ ውሣኔ መስጠት እንደሚችል ተከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን እንደሚዘጋውና ተከሣሹን እንደሚያሠናብት ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ከሣሽና ተከሣሽ እያለ የሚናገር ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በይግባኝ የሚቀርቡትንም ክርክሮች አጠቃሎ ስለሚይዝ እንደነገሩ አግባብ ከሣሽ የሚለው ቃል ይግባኝ ባይን ተከሣሽ የሚለው ደግሞ መ/ሰጪን የሚተካ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ ቁጥር 32/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ቅሬታው በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ነው፡፡ በዚህ የሥነ ሥርዓቱ ድንጋጌ ደግሞ ይግባኙ በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ያልቀረበ ከሆነ መ/ሰጪው ይግባኝ የቀረበበትን ነጥብ በከፊል ወይም በሙሉ ካመነ በእምነቱ መሠረት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሠጥ መሆኑን ነገር ግን ይግባኙን ክዶ የተከራከረ ከሆነ መዝገቡን መዝጋት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የይግባኙ መዝገብ መዘጋት የሚወሰነው መ/ሰጪው ለቀረበበት የይግባኝ ቅሬታ ከሚሠጠው መልስ አኳያ ታይቶ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መ/ሰጪ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መካድ ማመኑ ሣይረጋገጥ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዝገቡ ሊዘጋ የሚችልበትን ሁኔታ ድንጌጋው አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የአንደኛ መልስ ሰጪን መልስ ሣይመለከት መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ከአመልካች አቤቱታ እንደተመለከትነው ሁለተኛ ተጠሪ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ የተላከላቸውን መጥሪያ መ/ሰጪውን አግኝቶ መስጠት አለመቻሉ ለፍ/ቤቱ ተገልፆለት ሁለተኛ ተጠሪ እንዲቀርቡ ምትክ መጥሪያ ሳይላክ በእንጥልጥል ላይ የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም ተጠርተው ያልቀረቡ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ የቀረበ ማስተባበያ የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ እንዲጠሩ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሣይሠጥ አመልካች ይግባኝ በሚሠማበት ቀን አልቀረበም በማለት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ይግባኝም አብሮ መዘጋቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዝገብ የሚዘጋው ይግባኝ ባዩ የይግባኝ ቅሬታውን ክዶ ከተከራከረ በመሆኑ የአንደኛ ይግባኝ ባይ መልስ ተጠይቆ ሳይረጋገጥ መዝገቡ መዘጋቱም ሆነ ለሁለተኛ ተጠሪ መድረስ አለመቻሉ ተገልፆ ሳለ በምትክ መጥሪያ እንዲቀርብ ሣይታዘዝ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዘጋቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33199 ግንቦት 5/2000 ዓ.ም. እንዲሁም በዚህ መዝገብ ግንቦት 14/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የተዘጋው መዝገብ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 42706

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ላየን ሴኩሪቲ ኩባንያ - አልቀረበም

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥላሁን ገ/እግዚአብሔር -ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ውሣኔ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሳሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በጥበቃ ሰራተኛነት በአመልካች ድርጅት ሳገለግል ቆይቼ ምንም ሳላጠፋ ከሥራ አሰናብቶኛል ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ይህ ካለሆነ የአንድ ወር ደሞዝና ሌሎች የስንብት ክፍያ ይከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም በሰጠው መልስ ተጠሪ መጠጥ ጠጥተው ወደ ሥራ በመግባት አምቧጋሮ ይፈጥራሉ፣ ከባልደረባቸው አይግባቡም በዚህም መሠረት የማስጠንቀቅያ ጽሑፍ ቢሰጣቸውም ሊታረሙ ባለመቻላቸው የ10 ቀን ደሞዝ ተቀጥተዋል ስለዚህ ስንብታቸው በአግባቡ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም አመልካች ተጠሪን ለማሰናበት ምክንያት ናቸው ሲል የገለፀው ወይም ያቀረበው ማስረጃ እርስ በርሱ የሚቃረን ነው በተለይም በ8/7/2000 እና በ11/8/2000 ለተጠሪ የተፃፉት ማስጠንቀቂያ የሚጣረስ በመሆኑ አመልካች ያቀረበው ማስረጃ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በመሆኑም የተጠሪ የ1 (አንድ) ወር ደሞዝ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ክፍያን አስመልክቶ በተጠሪ ጥያቄ መሠረት እንዲከፈለው ሲል ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄን አልተቀበልኩም ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኙን አቅርቧል፡፡ መዝገቡ የቀረበለት ፍ/ቤት የሥር ውሣኔ ጉድለት የለበትም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ጥር 13/2001 ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

በዚህም መሠረት የሰበር ችሎትም ተጠሪን በማስቀረብ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ እንዲታይ የተወሰነውም አመልካች ክሱን ለማስተባበል ያቀረባቸው ምስክሮች ሣይሰሙ ውሳኔ የመሠጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ሲታይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሥራ ተቀጥሮ በመስራት ላይ እያለ አመልካች ያለ ጥፋት አሰናበተኝ ስለዚህ ወደ ሥራ ይመልሰኝ ካልሆነም በሕግ የተቀመጠውን ይክፈለኝ ሲሉ በጠየቁት መሠረት አመልካችም ተጠሪ ጥፋት በመፈፀማቸው ነው ያሰናበትኳቸው ሲል ተከራክሮ፤ ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪ የፈፀሙትን ጥፋት አላስረዳም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል ወደሥራ የመመለስ ጥያቄን ውድቅ በማድረግ የተለያዩ ክፍያ ለተጠሪ እንዲከፈለው ውሣኔ ሰጥቷል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ውሣኔውን ጉድለት የለበትም በማለት አፅንቷል፡፡

እኛም ከላይ የተጠቀሰውን የውሣኔ አሰጣጥ መሠረት በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሰምተናል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አመልካች ያቀረበው ማስረጃ በተለያዩ ጊዜ ለተጠሪ የተፃፈ ማስጠንቀቂያ የስንብቱን ምክንያት በአግባቡ የማያረጋግጥና የተጣረሰ (የሚጋጭ) ነው በማለት ነው፡፡ ስለ አመልካች የሰው ማስረጃም ቢሆን በውሣኔው ላይ የጠቀሰው ነገር የሌለ እና መስማት የማያስፈልገው እንኳ ቢሆን የገለፀው ነጥብ የለም አመልካች በመከላከያው መልስ የሰው ምስክር እስከቆጠረ ድረስና የቀረበው የሠነድ ፅሁፍ በአግባቡ የተጠሪን ጥፋተኝነት የሚያረጋግጥለት ከሆነ አግባብነት ያለው ውሣኔ ለመስጠት ሲባል የአመልካችን ምስክር መስማትና ወደ ውሣኔ ሊመጣ ይገባ ነበር፡፡ ምክንያቱም የአመልካች የቀረበበትን ክስ የመከላከል መብቱ ሊታለፍ የማይገባው ህጋዊ ነጥብ ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤት የቀረቡትን የሰው ምስክር ሣይሰማ ወደ ውሣኔ መድረሱ እና የከፍተኛው ፍ/ቤት ሣያርመው ማለፉ አግባብነት ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 13385 በቀን 15/9/2001 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 75596 በቀን 12/5/2001 የተሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአመልካችን የሰው ምስክር በመስማት ይወሰን በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 341 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
3. በዚህ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 14227 ላይ ተላልፎ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል ለሚመለከተው ይጻፍ፡፡
4. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 37741

ሰኔ 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- አቶ መኮንን ዘውዴ- ቀረቡ

**ተጠሪ**:- 1. አቶ ተሾመ ሽፈራው- አልቀረቡም

2. ወ/ሮ ዘርፌ ጎባቸው- አልቀረቡም

3. አቶ ጌታቸው መንገሻ- ወራሽ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በኦሮሚያ ክልል ሰሜን ሸዋ ዞን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ሲታይ ሦስተኛ ተጠሪ በገንዘብ እዳ ምክንያት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በደራ ወረዳ ፍ/ቤት ከሰው ካስፈረዱ በኂላ ንብረትነቱ የፍርድ ባለእዳዎቹ /የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች/ የሆነ ቤት በፍርድ አፈፃፀም ተሸጦ እዳው እንዲከፈል ተብሎ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቶ ይሄው ቤት ለአመልካች ተሸጦ እዳው እንደተከፈለ መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ከዚህ በኂላም የፍርድ ባለእዳዎች የይግባኝ ቅሬታ ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ ይግባኝ ባዮች ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ለመ/ሰጭ /ለስር ከሳሹ/ ይክፈሉ ተብሎ የተሰጠውን ዋናውን ውሳኔ በመሻር በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በኂላም ፍርዱን ያስፈጸመው የወረዳ ፍ/ቤት ዋናው ውሳኔ የተሻረ መሆኑን መሰረት በማድረግ የተሸጠውን ቤት ተከሳሾች እንዲረከቡት በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህንኑ ቤት በፍርድ አፈፃፀም በኩል በተደረገ ሽያጭ ገዝቼዋለሁ የሚሉት የአሁን አመልካች ይህንኑ የወረዳውን ፍ/ቤት ትእዛዝ በመቃወም የይግባኝ ቅሬታቸውን ለሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

ከዚህም በመቀጠል የይግባኝ ቅሬታቸውን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ዋናው ውሳኔ ከተሻረ ተከራካሪ ወገኖች ቀድሞ ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ ጥያቄ ካቀረቡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ መሰረት ወደነበሩበት እንዲመለሱ መደረግ አለበት፤ ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ተሸጧል የተባለው ቤት ለስር ተከሳሾች እንዲመለስ ሲታዘዝ የሽያጩን ገንዘብ የስር ከሳሽ እንዲመልሱ መደረግ ሲገባው ይህ ያልተከናወነ ስለሆነ በዚሁ መሰረት የሽያጩን ገንዘብ የስር ከሳሹ ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በማሻሻል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም መሰረታዊ የሕግ ስህተት አልተፈጸመም በማለት ወሳኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት እንደዚሁም የስር ከሳሹ በተጠሪነት ተጣምረው ባለመገኘታቸው እሳቸውን ሦስተኛ ተጠሪ በማድረግ ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤታታውም እንደሚከተው ተመርምሯል፡፡

በአንድ ፍ/ቤት የተሰጠ ፍርድ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የተለወጠ ወይም የተሻሻለ እንደሆነ ማናቸውም ተከራካሪ ወገን ነገሩን በመጀመሪያ ለተመለከተው ፍ/ቤት ሲያመለከት የተወሰደው ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲመለስ ተስማሚ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 349/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ንብረትነቱ የአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች የሆነው ቤት በፍርድ አፈፃፀም ለአሁን አመልካች ተሸጦ የሽያጩም ገንዘብ የፍርድ ባለመብት ለነበሩት ለአሁን ሦስተኛ ተጠሪ ተከፍሏል፡፡ የአሁን አመልካችም ይህንኑ በፍርድ አፈፃፀም በሽያጭ ያገኙትን ቤት አሳልፈው ለሌላ ወገን መሸጣቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የሰነ-ስርአት ሕጉ ድንጋጌ መሰረት ፍርዱ በይግባኝ በተለወጠ ጊዜ በዚሁ መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ፍርዱ ከመፈጸሙ በፊት ወደነበሩበት እንዲመለሱ ትእዛዝ መስጠት የሚቻል ሲሆን ነገር ግን በዚህ ጉዳይ ቤቱ በፍርድ አፈጻጸም ለአመልካች ከተሸጠ በቤቱ ላይም ለውጥ ከተደረገበት በኋላ እንደገና ለሌላ ወገን የተሸጠ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ ቤቱ ለስር ተከሳሾች /ለአሁን አንደኛ ተጠሪዎች/ ይመለስ መባሉ ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ የድንጋጌውም ይዘት ሲታይ ፍ/ቤቱ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ተገቢ መስሎ የታየውን ትእዛዝ መስጠት እንደሚችል የሚያሳይ ፈቃጅ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ ድንጋጌ አይደለም፡፡

ስለሆነም ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ ይገባል ተብሎ እስከ ኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

**<u>ው ሳ ኔ</u>**

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 48176 በ4/9/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 42032 በ17/5/99 የሰጠው ውሳኔ፣የሰሜን ሸዋ ዞን ከ/ፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11335 በ28/9/98 የሰጠው ትእዛዝ እንደዚሁም የደራ ወረዳ ፍ/ቤት በ24/8/98 የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በፍርድ አፈፃፀም የገዙትን ቤት ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የቤቱን የሐራጅ ሽያጭ ገንዘብ የስር የፍርድ ባለመብት የነበሩት የአሁን ሦስተኛ ተጠሪ አቶ ጌታቸው መንገሻ ለአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ሊመልሱ ይገባል ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
5. በዚህ ችሎት ውሳኔ መሰረት እንዲፈጸም ግልባጩ ለደራ ወረዳ ፍ/ቤት ይተላለፍ ብለናል፡፡
6. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38452

ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፦ ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፦ የአ.አ ከተማ ቤቶች ኤጀንሲ - ነ/ፈጅ አቶ ተስፋዬ ዘመድኩን - ቀርበዋል

**ተጠሪ**፦ አቶ ዓለም ገብሩ - ጠበቃ አቶ አታክልት ኃ/ስላሴ ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አቤቱታው የቀረበው አመልካች ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59626 ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 72799 ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመባቸው ስለሆኑ ይሻሩልኝ በማለቱ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ በስር ፍ/ቤቱ ተከሣሽ በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣ ስር ከሣሹ ሚያዚያ 09/1999 ዓ.ም ያቀረቡት የተሻሻለ ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ተከሣሹ የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች ለመሸጥ ጨረታ ባወጣው መሠረት በ6ኛ ዙር የጨረታ ሂደት በመሣተፍ በኮልፌ ቀራኒዮ ክ/ከተማ በቀበሌ 15/16 በአስኮ ሣይት የሚገኙትን ቁጥራቸው AS-B7-00193 እና AS-B8 -00243 የሆኑትን ሁለት ቤቶች እያንዳንዳቸውን በብር 81,330 /ሰማንያ አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሰላሣ ብር/ ዋጋ በማሸነፍ የካቲት 21 ቀን 1998 እና መጋቢት 04 ቀን 1998 ዓ.ም የተፃፈ የሽያጭ ውል በማሰር የቤቶቹን ዋጋ ለተከሣሹ የከፈልኩ ብሆንም የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር ቤቶቹን ሊያስረክበኝ ስላልቻለ ቤቶቹን እንዲያስረክበኝ፣ የባለቤትነት ማስረጃም እንዲሰጠኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቱም ስር ተከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ትእዛዝ ደርሶት ስላልቀረበና ክርክሩን ለማካሄድ በተቀጠረበት ቀንም በመቅረቱ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ አዟል፡፡ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም ተከሣሹ በክስ የተጠቀሱትን ቤቶች በጨረታ ለከሣሹ እንደሸጣቸውና ዋጋቸውንም ተቀብሎ ውል እንዳሰረ በመግለጽ ቤቶቹን ለከሣሹ ማስረከብ እንዳለበት ወስኗል፡፡ በአሁኑ አመልካች ይግባኝ ባይነት ጉዳዩ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢቀርብም ፍ/ቤቱ በመ/ቁ. 59626፣ጥር 21 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት አጽንቶታል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ፍርድ በመቃወምም አመልካቹ ሰኔ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ የሰበር አቤቱታ ያቀረበ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም አከራካሪው ጉዳይ ማለትም ቤቶቹ በአመልካቹ የሚተዳደሩ በመሆናቸው እንዲሁም የአዲስ አበባ አስተዳደር አስፈፃሚና የማዘጋጃ ቤት አገልግሎት አካላት ከሚዋዋሏቸው ውሎች ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች በአዋጅ ቁጥር 361/95 አንቀፅ 41 መሠረት የዳኝነት ስልጣኑ የአዲስ አበባ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤት ስልጣን አይደለም፤ የስር ፍ/ቤቶቹ ስልጣን ሣይኖራቸው የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ እንዲሁም ተጠሪው ቤቶቹን የገዛቸው ለጨረታ በተቀመጠው መነሻ ዋጋ ነው፤ ሆኖም የከተማው አስተዳደር ያወጣው የጨረታ መመሪያ የጨረታ አሸናፊ ለመሆን ከጨረታው መነሻ ዋጋ በላይ መሸጥ እንዳለበት ስለሚያመለክት ሽያጩ ሕጋዊ ባልሆነበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶቹ የሽያጭ ውል አለ በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ስለሆነም ውሣኔው ይሻርልን የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ሚያዚያ 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቹ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ጠቅሰው የተከራከሩበት አዋጅ ቁ. 362/95 አንቀጽ 41 የሚል እንጂ አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀጽ 41 የሚል አይደለም ስለሆነም በስር ፍ/ቤት ያልተጠቀሰውን በዚህ ሰበር ችሎት መከራከሪያ ሊያደርጉት አይችሉም፤ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶቹ የፈፀሙት የሕግ ስህተት ስለሌለ ውሣኔያቸው ይጽደቅልኝ ብለዋል፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልክ በመገንዘብ፣ ይህን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያለው ፍ/ቤት የትኛው ነው? በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል በሕግ የሚፀና የቤት ሽያጭ ውል አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካቹ ባቀረበው ክርክር ይህንን ጉዳይ የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንጂ የፌዴራል ፍ/ቤቶች መሆን የለባቸውም፤ ይህንንም የስልጣን ጉዳይ የስር ፍ/ቤቶቹ በራሣቸው አነሣሽነት ስልጣን እንደሌላቸው መበየን ሲገባቸው ወደ ዋናው ክርክር ገብተው ውሣኔ መስጠታቸው ተገቢነት የለውም ሲሉ ተጠሪው ግን ከላይ የቀረበውን ክርክር ባለመቀበል አከራካሪውን ጉዳይ በተመለከተ የስር ፍ/ቤቶቹ ስልጣን የላቸውም ሊባሉ አይገባም ብለዋል፡፡

እንደሚታወቀው አመልካቹ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካል ሲሆን የክርክሩ መነሻም እሱ የሚያስተዳድራቸውን ቤቶች አስመልክቶ የተደረገ የሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ የተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 41 እንዳሰፈረው ደግሞ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈፃሚ አካላት ወይም በስሩ ያሉ ሌሎች አካላት የሚገቧቸውን ውሎች በተመለከተ እንዲሁም የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድራቸው ቤቶች ጋር በተያያዘ የሚነሱትን ክርክሮች የመዳኘት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች መሆናቸውን በግልጽ አስፍሯል፡፡ ተጠሪው ባቀረቡት ክርክር አመልካቹ በስር ፍ/ቤት የጠቀሰው አዋጅ ሌላ ነው ከማለት ውጭ ከላይ የሰፈረውን የዳኝነት ስልጣን በቀጥታ አላስተባበሉትም፡፡ የስር ፍ/ቤቶቹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 9/2/ መሠረት ስልጣን የሌላቸው መሆናቸውን በራሣቸው አነሣሽነትም ቢሆን ጉዳዩን አንስተው ተገቢውን ብይን መስጠት ማለትም የክሱ ማመልከቻ ተቀባይነት የለውም ብለው መዝጋት ሲገባቸው አከራካሪውን ጉዳይ የማየት ስልጣን እንዳላቸው አድርገው በክርክሩ ዋና ነጥብ ውሣኔ መስጠታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59626፣ጥር 21/2000 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/ቁ. 72799፣ ሰኔ 11/1999 ዓ.ም የሰጧቸው ፍርዶች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች አከራካሪውን ጉዳይ የማየት ስልጣን የላቸውም፤ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ያላቸው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤቶች ናቸው ብለናል፡፡

3/ ሰኔ 12/2000 ዓ.ም እና ሐምሌ 28/2000 ዓ.ም የተላለፉት እግዶች ተነስተዋል፤ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 39014

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብልዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ዓለሙ መግራ - ቀረበ

**ተጠሪ**፡- እምነቴ እንደሻው ህንፃ ተቋራጭ - ነ/ፈጅ ግርማ ወርቁ ቀረቡ

መዝገቡን መርመረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው ፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ አመልካች ከሳሽ ሲሆኑ ተጠሪ ተከሳሽ ነበር ጉዳዩ የስራ ክርክር ሆኖ መጀመሪያ አመልካች ባቀረበው ክስ መነሻ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 19802 በ5/10/99 ዓ.ም በዋለው ችሎት አመልካች የስራ መሪ እንጂ ሰራተኛ አይደለም በማለት ክሱ በብይን ውድቅ ሲደረግ ይግባኝ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 57097 በሆነው ኀዳር 11 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ብይንን መሻር አመልካች የስራ መሪ ሳይሆን ሰራተኛ ነው በማለት በፍሬ ነገር ላይ ውሳኔ እንዲሰጥት በማዘዝ ለመጀመሪያ ፍ/ቤት ጉዳዩ ተመለሰ፡፡ ከዚህ በኋላ ክርክሩ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲካሄድ ሐምሌ 13/99 ዓ.ም በተፃፈ መቃወሚያ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የሚለውን መቃወሚያ ቀርቦ ፍ/ቤቱ በማለፍ በፍሬ ነገር ላይ የስራ ውል የተቋረጠው አለአግባብ ነው የ6 ወር ካሳና የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና የየካቲት ወር ደመወዝ እዲከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን ለመዳኘት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ተጠሪ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው በመሻሩ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ቅሬታ፡-

የተጠሪ ቅርንጫፍ ቢሮ አዲስ አበባ ከተማ ያለ ስለመሆኑ በማረጋገጥ ግንቦት 3 ቀን 2000 ዓ.ም በወጣው ሪፖርተር ጋዜጣ ገጽ 8 የቅጥር ማስታወቂያ ላይ አድራሻ አ.አ መሆኑን የገለጸ ከመሆኑም በላይ በተመሳሳይ የስራ ክርክር በመ/ቁ. 29465 ፣37317 እና 38403 በየካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 21206 በቂራ ምድብ ችሎት ጉዳዮች የታዩ መሆኑን በመግለጽ የግዛት ክልል ስልጣን የለም የተባለው ስህተት በመሆኑ ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው፡፡

ይህ ችሎት የግዛት ክልል ስልጣን የለም የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ያስቀርባል ተብሎ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አካሄደዋል፡፡ የተጠሪ የቃል ክርክር አዲስ አበባ ያለው የእቃ ገቻ እና የፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት እንጅ ዋና መ/ቤቱ አዋሳ ነው በማለት ውሳኔው እንዲፀና ጠይቀዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር ከዚህ በላይ በአጭሩ የተመዘገበው ሲሆን እኛም እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ አመልካች የስራ መሪ ነው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት ጉዳዩ አይታይም ተብሎ ክሱ በብይን ውድቅ ተደርጐ በይግኝ ታይቶ እንደገና እንዲታይ ተወስኖ ሲመለስ የአሁኑ ተጠሪ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን እንደገና ሊያይ የሚችልበት የግዛት ክልል ስልጣን የለውም ስልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ነው ጉዳዩ እንዲታይ እንዲመለስ የተደረገው በማለት

በይግባኝ እንዲታረምለት አልጠየቀም፡፡ በውሳኔው ተስማምቶ በፍሬ ጉዳይ ላይ ለመሟገት ከመለሰ በኋላ እንደገና የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ክርክር የሚያነሳበት የሕግ አግባብ የሌለ ከመሆኑም በላይ ይልቁንም የድርጅቱ ቅ/ጽ/ቤት አ/አበባ ከተማ ለም ሆቴል አካባቢ ኃይሌ ገ/ስላሴ መንገድ እንደሆነ አመልካች በቅሬታው የጠቀሰውን የተጠሪ ጠበቃ በክርክራቸው የእቃ ግዥ እና ፕሮጀክት ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ያለው መሆኑን በማረጋገጥ የተከራከረ በመሆኑ የግዛት ክልል ስልጣን የለውም በማለት የከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 63124 ግንቦት 6 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቱ የግዛት ክልል ስልጣን አለው ብለናል፡፡ በመሆኑም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፍሬ ጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሳኔ በሕጉ አግባብ መሆን አለመሆኑን ከሕግና ከማስረጃ አንፃር በማገናዘብ ተገቢውን እንዲወስን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 341 መሰረት ለከፍተኛ ፍ/ቤት እንዲመለስ ወስነናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ
4. መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡
5. መ/ቁጥር 19802 በመጣበት ሁኔታ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38145

ሰኔ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ አያልነሽ ዘገየ- ጠ/ሙሉጌታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ተስፋዬ ደምሴ- ጠ/ጌታቸው ሞላ ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአመልካችና የተጠሪ ጋብቻ በፍቺ ከፈረሰ በኋላ የንብረት ክፍፍሉን በተመለከተ ባለሙያ አጣርቶ ለፍ/ቤቱ ውጤቱን የገለጸ ሲሆን ፍ/ቤቱም የቀረበውን ውጤት በአብዛኛው ተቀብሎ በተወሰኑ ጉዳዮች ራሱ መርምሮ ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ ፍ/ቤቱ ራሱ መርምሮ ውሣኔ ከሰጠባቸው ነጥቦች ውስጥ አንደኛው የእቁብ ገንዘብን የሚመለከት ነው፡፡ ንብረት አጣሪው በአቶ ታደሰ ተክሌ የሚሰበሰብ እቁብ መኖሩን አረጋግጠው ሁለቱም የእቁብ ገንዘቡን እኩል መካፈል ስላለባቸው ተጠሪ ለአመልካች ብር 247,500(ሁለት መቶ አርባ ሰባት ሺህ አምስት መቶ ብር) እንዲከፍሉ ሲወስኑ በተጠሪ የሚሰበሰበውን እቁብ ግን ፍ/ቤቱ እንዲያጣራው አሣስበዋል፡፡ በዚህ መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ የዚህን ገንዘብ ግማሽ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ ሲወስን በአቶ ታደሰ ተክሌ የሚሰበሰበውን እቁብ በተመለከተ ስለማጽደቁ በውሣኔው ሣይጠቅስ አልፏል፡፡

አመልካችም ለችሎቱ በአቶ ታደሰ ተክሌ ዳኝነት ይሰበሰብ የነበረውን እቁብ በተመለከተ በንብረት አጣሪው የቀረበውን ውሣኔ ፍ/ቤት ሣያጸድቅ ስላለፈው ይታረምልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም ይህንኑ ማጽደቁን በውሳኔው ሳያሰፍር ያለፈው በዝንጋታ በመሆኑ ይህንንም እቁብ ግራ ቀኙ እንዲካፈሉት የሚለው ዓረፍተ ነገር ቀደም ሲል በሰጠው ውሣኔ ውስጥ እንዲካተት በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ በአመልካች የቀረበው ጥያቄ በይግባኝ የሚስተካከል እንጅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት የሚስተካከል አይደለም በማለት የፍ/ቤቱን ትእዛዝ ሽሯል፡፡ በዚህ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ጠይቀው ይግባኛቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

ከዚህ በኋላ አመልካች የስር ፍ/ቤት በአቶ ታደሰ ተክሌ ሲሰበሰብ የነበረውን እቁብ አስመልክቶ አጣሪው የሰጠውን ውሣኔ ሣያጸድቅ ማለፉ ስህተት ነው በማለት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ይግባኝ የቀረበበት ጉዳይ የይግባኝ ማቅረቢያው ጊዜ ያለፈ በመሆኑና የይግባኙ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈውም በበቂ ምክንያት ስላልሆነ ይግባኙ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጐታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለዚህ የሰበር ችሎት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አመልካች ያቀረቡት ይግባኝ ጊዜው ያለፈበት ነው ተብሎ ውድቅ የመደረጉን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጐ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በቃል አሰምተዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የንብረት አጣሪው በአቶ ታደሰ ተክሌ ከሚሰበሰበው እቁብ ተጠሪ የወሰዱት 495,000 (አራት መቶ ዘጠና አምስት ሺህ ብር) ግማሽ ለአመልካች እንዲከፈላቸው ወስነዋል፡፡ ፍ/ቤቱ የንብረት አጣሪውን ውሣኔ ሲያጸድቅ ግን ይህን የእቁብ ገንዘብ በተመለከተ የተሰጠውን ውሣኔ ሣያጸድቅ አልፎታል፡፡ አመልካች ይህ የታለፈው ነጥብ

እንዲታረምላቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 መሰረት ለፍ/ቤቱ ጥያቄ ሲያቀርቡ ፍ/ቤቱ ይህን ነጥብ ሣያጸድቅ ያለፈው በዝንጋታ መሆኑን በማጤን አጣሪው የሰጡትን ውሣኔ አጽድቋል፡፡ ተጠሪ ግን ይህን ትእዛዝ ተቃውመው ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የአመልካችዋ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው በይግባኝ እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ ይህ ውሣኔም በፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ፀድቋል፡፡ እንግዲህ ከክርክሩ ሂደት አመልካችዋ ይህን ክርክር ያስነሣውን የእቁብ ገንዘብ በተመለከተ በዳተኝነት ትተውት የተቀመጡ ሣይሆን ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርበው በክርክር ሂደት ላይ ነበሩ፡፡ ሣይፀድቅ የታለፈው የእቁብ ገንዘብ እንዲታረም ተገቢ ነው ባሉበት የሥነ-ሥርአት መንገድ ጥያቄ አቅረበው የነበረ ቢሆንም ጥያቄው የቀረበበት ሰርአት የሥነ-ሥርአት ሕጉን የተከተለ ነው አይደለም በሚል በተነሣ ክርክር የተወሰነ ጊዜ ማለፉን ተገንዝበናል፡፡ የመጨረሻ ፍ/ቤቱም ጥያቄው ሊስተናገድ የሚገባው በይግባኝ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ አመልካችዋ ሣይዘገዩ ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ በእርግጥ አመልካችዋ ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ባቀረቡበት ወቅት ይግባኝ የተጠየቀበት ውሣኔ ከተሰጠ የ60 ቀናት ጊዜ አልፏል፡፡ አመልካችዋ ያቀረቡት ይግባኝ ጊዜው ያለፈ መሆኑን ፍ/ቤቱ የተረዳው ዋናው ይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በመሆኑ አመልካችዋ ጊዜው ያለፈበት ይግባኝ ማቅረቢያ ማስፈቀጃ አላቀረቡም፡፡ ፍ/ቤቱም ጊዜው ማለፉን እንደተረዳ የማስፈቀጃ ማመልከቻ እንዲቀርብ ማድረግ ሲገባው ይህንን ባያደርግም አመልካችዋ ይግባኝ ሣያቀርቡ ጊዜው ያለፈበትን ምክንያት ግን ተመልክቶ በቂ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

አንድ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈበት ምክንያት በቂ መሆኑን ሲረዳ ይግባኙ እንዲቀርብ ሊፈቅድ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 326/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ የቀረበለት ምክንያት በቂ መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሊመረምረው ይገባል፡፡ በእርግጥ በቂ ምክንያት የሚባሉትን ነገሮች ሕጉ ዘርዝሮ ያላስቀመጣቸው በመሆኑ ለመወሰን አስቸጋሪ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የምክንያቱ በቂ መሆን አለመሆን በእያንዳንዱ ጉዳይ ከሚቀርቡ ፍሬ ነገሮች ጋር ተገናዝበው ሊመዘኑ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችዋ ተጠሪው ከወሰዱት የእቁብ ገንዘብ ግማሹ የሚገባቸው ለመሆኑ በአጣሪው ተወስኖላቸው ይህንን ነጥብ ፍ/ቤቱ ሣያጸድቅ አልፎታል፡፡ ይህ ጉዳይ ሊታረም የሚገባው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 208 ነው ወይስ በይግባኝ ነው የሚለው ጉዳይ ክርክር እየተደረገበት ስለነበር እንጂ ጊዜው ያለፈው አመልካች መብታቸውን ሣይጠይቁ ዳተኝነት አሣይተው አለመሆኑን በመዝገቡ ከቀረቡት ፍሬ ነገሮች መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜው ያለፈው በበቂ ምክንያት አይደለም በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርአት ሕግ በአግባቡ ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 59015 መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አልካች ይግባኝ ሣያቀርቡ ጊዜው ያለፈባቸው በበቂ ምክንያት ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ያቀረቡትን ይግባኝ ተቀብሎ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሰረት መልሰናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ የስር ፍ/ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38683

ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ ስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት- ነ/ፈጅ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ ሳህሉ ወ/ማሪያም- ከጠበቃ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በተጠሪ ላይ ባቀረበው ክስ ከግንቦት 5 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ ተከሳሽ በከሳሽ ድርጅት በገንዘብ ያዥነት ሲሰሩ በኃላፊነት ከተረከቡት ገንዘብ ላይ ብር 72,710.48 (ሰባሁለት ሺህ ሰባት መቶ አስር ብር ከአርባ ስምንት ሣንቲም) በጉድለት እንደሚፈለግ በኦዲት ምርመራ የተረጋገጠ ስለሆነ ይህንኑ ገንዘብ ከወለድ ከወጭና ኪሳራ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽም ቀርበው በከሳሽ ድርጅት በገንዘብ ያዥነት መስራታቸውን አምነው ነገር ግን በኃላፊነት ሲያንቀሳቅሱት የነበረው ሂሳብ በየወቅቱ ኦዲት እየተደረገ በጉድለት የሚፈለግ ገንዘብ እንዳልነበር ከግንቦት 5 ቀን 1991 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 1996 ዓ.ም ድረስ በከሳሽ መ/ቤት በገንዘብ ያዥነት በሰሩበት ጊዜ ገንዘብ ስለማጉደላቸው በኦዲት እንዳልተረጋገጠ ገልጸው ክሱ ከኪሳራ ጋር ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ጉዳዩን መርምሮ ተከሳሽ በክስ የተጠየቀውን ገንዘብ ስለማጉደላቸው ከሳሽ በማስረጃነት ባቀረበው የኦዲት ሪፖርት ላይ ያልተረጋገጠ ስለሆነ ክሱ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ከሳሽ በዚህ ውሳኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ከፍተኛ ፍ/ቤቱ ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ክሱን ያስረዱልኛል በማለት የቆጠራቸውን የባለሙያ ምስክሮች የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሳይሰማ ውሳኔ መስጠቱ ለሰበር ቀርቦ መመርመር እንዳለበት በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን አቤቱታው ለሰበር ሊቀርብ ይገባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ ተጠሪ በኃላፊነት ሲያነቀሳቅሱት የነበረውን ሂሳብ መርምረው ጉድለት መኖሩን ያረጋገጡት ኦዲተሮች ቀርበው የሙያ ምስክርነት ቃላቸውን እንዲሰጡ አመልካች በማስረጃነት የቆጠራቸው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃነት የሚጠቅሳቸው ምስክሮች፣ሰነዶች ወይም ሌላ አስረጂዎች እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ ከመስጠቱ በፊት ማስረጃው በጭብጥ ተይዞ ከሚፈታው ፍሬ ነገር ጋር አግባብነት(Relevance) ያለው ስለመሆኑና በሕግ ተቀባይነት ያለው ማስረጃ (Admissible Evidence) ስለመሆኑ ማጣራት እንደሚገባው ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል መርህ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የጠቀሳቸው ምስክሮች ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በኃላፊነት ሲያንቀሳቅሱት የነበረውን ሂሳብ መርምረው ጉድለት መኖሩን በኦዲት ያረጋገጡ መሆኑን አመልካች በማስረጃ ዝርዝሩ ላይ ጠቅሷል፡፡ እነዚህ የሙያ ምስክሮች ጉድለት ስለመኖሩ የሚያረጋግጡ ናቸው ከተባለ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ፈጽመዋል ወይንስ አልፈጸሙም? ተብሎ በጭብጥነት ከሚያዘው ፍሬ ነገር ጋር የተያያዘና አግባብነት ያለው የምስክርነት ቃል እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም ሌላ በምስክሮቹ የሚሰጥ የሙያ ምስክርነት ቃል በሕግ ተቀባይነት የሌለው (Inadmissible) አይደለም፡፡ አመልካች በዚህ መልኩ የቆጠራቸው ምስክሮች ቀርበው መሰማታቸው ክርክሩ ከሚመራበት የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 111፣249 እና 257 አኳያ እንደዚሁም ከማስረጃ አቀራረብና አቀባበል አኳያ ተገቢነት ያለው ሆኖ ሳለ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እነዚህን ምስክሮች ሳይሰማ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ውሳኔ መስጠቱ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህንኑ ጉድለት በይግባኝ ሳያርም መቅረቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22762 በ07/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62605 በ21/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አመልካች የቆጠራቸውን የሙያ ምስክሮች በመስማት ውሳኔ እንዲሰጥበት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38844

ሰኔ 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ መንገዶች ባለሥልጣን- ነገረ ፈጅ ፋሲል በለጠ

**ተጠሪ**፡- ጋድ ቢዝነስ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር- አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 57204 ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍትሀብሔር ይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 33400 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ከሳሽ አመልካቹ ተከሳሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ለመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ለአመልካች አንድ ሺ ቶን አስፋልት በዘጠና ቀን ውስጥ ለማቅረብ የተስማማ መሆኑንና አመልካች በበኩሉ ብር 3,565,000

(ሦስት ሚሊዮን አምስት መቶ ስልሣ አምስት ሺ.ህ) ለመክፈል ተስማምቷል፤ ሆኖም

- አስፋልቱ ከሚመጣበት ግብጽ ሐገር እቃውን በመጫን በስዊዝ ካናል በኩል በወቅቱ በነበረው የአሜሪካና ኢራቅ ጦርነት ምክንያት ከመጋቢት 11 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ ሚያዝያ 25 ቀን 1995 ሊተላለፉ ባለመቻላቸው፣
- የስዊዝ ቦይ ተከፍቶ እቃውን የጫነው መርከብ ሰኔ 19 ቀን 1995 ዓ.ም ጅቡቲ ሲደርስ የምግብ እርዳታ የጫኑ መርከቦች ወደቡን በማጨናነቃቸው አስፓልቱ ሣይራገፍ ሊዘገይ ችሏል፤

ከሳሽ (ተጠሪ) አስፓልቱን በወቅቱ ያላደረሰው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን ለተከሳሽ (አመልካች) ያሣወቀና ማስረጃ ያቀረበ ቢሆንም ተከሳሽ (አመልካች) አላግባብ አስፓልቱ ለዘገየበት በሚል ምክንያት ብር 356,000(ሦስት መቶ ሃምሣ ስድስት ሺ. ብር) ከዋጋው ቀንሶ ያስቀረ በመሆኑ ይህንን ገንዘብ ከነወለዱ ብር 420,670 (አራት መቶ ሐያ ሺ. ስድስት መቶ ሰባ ብር) እንዲከፍል ይወስንልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡

አመልካች በበኩሉ በውላቸው መሰረት ከሳሽ(ተጠሪ) ባለማቅረቡ በውሉ መሰረት በቅጣት መልክ መቀነስ ያለበትን ገንዘብ የቀነሰ መሆኑን፤ በአሜሪካና ኢራቅ ጦርነት አስፓልቱን የጫነችው መርከብ መተላለፊያ አጥታ መቆሟን የሚያሣይ ማስረጃ ተጠሪ ያላቀረበ መሆኑን፤ በጅቡቲ ወደብም አስፓልቱን በማራገፍ ሒደት የገጠመ ችግር የነበረ ስለመሆኑ ከወደቡ አስተዳደር ያቀረበው ማስረጃ የሌለ በመሆኑና ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር የገጠመው መሆኑን በውላችን አንቀጽ 10 መሰረት ለተከሳሽ (አመልካች) ያላሳወቀ በመሆኑ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ሳያጋጥመው ከሳሽ

(ተጠሪ) እቃውን በማዘግየቱ በውሉ መሰረት በቀጣት መልክ ያስቀረነውን ክፍያ ለከሳሽ (ተጠሪ) የምንመልስበት ሕጋዊ ምክንያት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የከሳሽንና(ተጠሪን) ተከሳሽን (አመልካችን) ክርክርና ማስረጃ በመመርመር ተጠሪ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር አስፓልቱን ያላቀረበ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሚያዚያ 25 ቀን 1995 ዓ.ም ስለስዊዝ ቦይ እና የአሜሪካና የኢራቅ ጦርነት ይዞት የወጣውን ዜና እና ዩንቨርሳል የተባለ የእቃ አስተላለፊ ድርጅት አስፋልቱን የጫነው መርከብ በጅቡቲ ወደብ አስራ ስምንት ቀን ቆሟል በማለት የፃፈውን ደብዳቤ ነው፤ እነዚህ ማስረጃዎች አስፓልቱን የጫነው መርከብ በስዊዝ ቦይ መተላለፊያ በማጣቱም ሆነ የጅቡቲ ወደብ በመጨናነቁ የዘገየ መሆኑን የሚያስረዱ አይደሉም፤ ስለዚህ ከሳሽ (ተጠሪ) አስፓልቱን በውሉ በተገለፀው የጊዜ ገደብ ያላደረሱት ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ምክንያት መሆኑን ያላስረዱ ስለሆነ ተከሳሽ (አመልካች) በቀጣት መልክ ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ ለከሳሽ (ተጠሪ) የሚከፍልበት ምክንያት የለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪን ይግባኝና የአመልካችን መልስ ከተቀበለ በኂላ ቅሬታውንና መልሱን እንደመረመርነው ምላሽ ማግኘት ያለበት ጭብጥ ይግባኝ ባይ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት አለ ያለው ነገር መኖሩ በማስረጃ ተረጋግጧል ወይስ አልተረጋገጠም? ከአቅም በላይ የተባሉት ምክንያቶች በሕጉ ይካተታሉ ወይስ አይካተቱም? በመሆኑም እነዚህን ምክንያቶችን በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793/ሀ/ እና (መ) የሚሸፈኑ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ገንዘቡ ለይግባኝ ባይ ሊከፈል አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብ አይደለም" በማለት አመልካች ብር 356,500 (ሦስት መቶ ሐምሣ ስድስት ሺ አምስት መቶ ብር) ውሣኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ከሚታሰብ ወለድ ጋር ለተጠሪ እንዲከፍል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ ተጠሪ አስፓልቱን ማቅረብ ከነበረበት በሰማኒያ ሶስት ቀን ዘግይቶ አቅርቧል፤ ተጠሪ መዘግየቱ የተፈጠረው ከአቅም በላይ መሆኑን የሚያስረዳ የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ ምክንያትና ማስረጃ አላቀረበም፤ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ማስረጃውን መርምሮ የሕግ ድንጋጌዎችን አገናዝቦ የሰጠውን ውሣኔ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ማስረጃውን ሣይመረምርና ሣይመዝን ከተጠቀሰው የሕግ ድንጋጌ ጋር ያላቸውን ግኑኝነት ሣያገናዝብ በጭብጥነት የያዛቸውን ጭብጦች ሣያይ የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793(ሀ) እና (መ)"ን" በመጥቀስ የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፤ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ውሣኔ ማጽናቱ ተገቢ ባለመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ በአሜሪካና በኢራቅ ጦርነት ምክንያት በስዊዝ ቦይ መርከቦች እንዳይተላለፉ በመከልከሉና በጅቡቲ ወደብ በነበረው መጨናነቅ እቃውን በወቅቱ ለአመልካች ያላስረከብኩ መሆኑንና ይህም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑን በማገናዘብ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የሌለበት ስለሆነ የአመልካች የሰበር አቤቱታ እንዲሰረዝልኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካችም የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍ/ቤት ተጠሪ አስፓልቱን ሣያቀርብ የቀረው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔና ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይህንን ውሣኔ በማጽናት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መፈታት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ጉዳዩን እንደመረመርነው የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በውሉ መሰረት ለመፈጸም የገደበው ከአቅም በላይ የሆነ ነገር አላጋጠመውም ከሚለው መደምደሚያ ላይ የደረሰው በአሜሪካን እና ኢራቅ ጦርነት ምክንያት የስዊዝ መተላለፊያ ቦይ የተዘጋ መሆኑንና ለዚህ ጊዜም አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ታግዳ የነበረች ስለመሆኗ በቂ ማስረጃ አልቀረበም፤ በማስረጃነት የቀረበው በጋዜጣ ላይ ታትሞ የወጣ ዜና ይህንን አያስረዳም፤ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ የጅቡቲ ወደብ በመጨናነቁ ምክንያት ለማራገፍ ባለመቻሏ ነው ለሚለው ፍሬ ጉዳይ ከጅቡቲ ወደብ አስተዳደር የቀረበ ማስረጃ የለም፤ ከግል እቃ አስተላላፊ ድርጅት የተፃፈው ደብዳቤ ታአማኒነትና ክብደት የለውም በማለት ነው፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ መወሰን ያለባቸውን ሁለት ጭብጦች ከያዘ በኋላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በተጠሪ የቀረቡትን ማስረጃዎች ተአማኒነትና ክብደት ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ የሰጠውን ምክንያትና ማብራሪያ የማይቀበልበትን ምክንያት ሳይገልጽ ማስረጃዎቹን ሳይመዝንና ከሕጉ ጋር ያላቸውን ተዛማጅነት ሣያብራራ በአንድ መስመር ተጠሪ እቃውን ያላቀረበው በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793(ሀ) እና(መ) መሰረት ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ስለ ውሣኔ አሰጣጥ በፍትሀብሔር ሥነ-ሥርአት ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን የሚጥስ፣ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ በግልጽ በተቀመጠ ምክንያት ሣይሆን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን የመሻር ስልጣን ስላለው ብቻ የሻረው መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው መሆኑን ለማስረዳት በወቅቱ በአሜሪካና በኢራቅ መካከል ጦርነት መኖሩንና በዚህ ምክንያት በስዊዝ ቦይ መተላለፊያ ችግር የነበረ መሆኑን በጋዜጣ የተዘገበ ዜና ማቅረቡ ብቻውን በቂ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠው ትርጉም ከፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ተጠሪ በዚያን ወቅት አስፓልቱ በመርከብ ተጭኖ የነበረ መሆኑን፣ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ጉዞዋን ጀምራ ስዊዝ መተላለፊያ ቦይ ስትደርስ በጦርነቱ ምክንያት መተላለፊያ በመዘጋቱ ስንት ቀን እንደቆመች እና በዚህ ምክንያት በውሉ የተገለፀው የጊዜ ገደብ ያለፈ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ተጠሪ እነዚህን ዝርዝር ሁኔታዎች የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪ የተፈጠረው ጠቅላላ ሁኔታ እሳቸው ውሉን ለመፈጸም ባደረጉት ጥረት ላይ የፈጠረውን እርግጠኛ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ባላስረዱበት ሁኔታ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ስለ ጦርነቱ ሁኔታ የተዘገበ ዜና ለስር ፍርድ ቤት በማቅረብ ውሉን ያልፈጸምኩት ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን አስረድቻለሁ በማለት ያቀረቡት ክርክርና የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የተጠሪን ክርክር በመቀበል የሰጡት ውሣኔ የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ (1)"ን" መሰረታዊ መርህ የሚጥስ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በሁለተኛ ምክንያትነት ያነሱት የጅቡቲ ወደብ መጨናነቅ ስለ ወደቡ አስተዳደርና ወደቡ መርከቦችን በማስተናገድ በኩል ስለገጠመው ችግር ማስረጃ የመስጠት ስልጣንና ሐላፊነት ካለው የጅቡቲ ወደብ አስተዳደር የተሰጠ አይደለም፡፡ ተጠሪ ወደቡ በመጨናነቁ አስፓልቱን የጫነችው መርከብ ቆማ የነበረ መሆኑን ዩኒቨርሳል የተባለ እቃ አስተላላፊ ድርጅት የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት ያቀረበ ቢሆንም ይህ ማስረጃ ተጠሪ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 ንኡስ አንቀጽ 1 በተደነገገው መሰረት ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ አስፓልቱን ለአመልካች ሣያቀርብ የቀረ መሆኑን የማስረዳት ብቃትና ተአማኒነት የሌለው መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ከበቂ ምክንያት ጋር አስቀምጧል፡፡ በሌላ በኩል ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች ይህ ማስረጃ በምን ምክንያት ተአማኒነት ሊሰጠው እንደማይገባና ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው ስለመሆኑ በቂ አስረጂ አድርገው እንደወሰዱት አልገለፁም፡፡

በአጠቃላይ ሲታይ ተጠሪ ውሉን በወቅቱ ያልፈጸመው በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 የተደነገጉት ከአቅም በላይ የሆኑ ሁኔታዎች ያጋጠመው መሆኑን ማስረጃ አቅርቦ የማስረዳት ሸክሙን በአግባቡ ያልተወጣ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት ማስረጃዎቹን ከሕጉ ድንጋጌ ጋር በማገናዘብ የወሰነ ሲሆን ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽረናል ከሚሉ በስተቀር ተጠሪ እርግጠኛ በሆነ ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ምክንያት ውሉን ሣይፈጽም የቀረ ስለመሆኑ የሰጡት ምክንያትም ሆነ ማብራሪያ የለም፡፡

በእኛም በኩል ተጠሪ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ስላጋጠመው ውሉን በጊዜው ሣይፈጽም የቀረ መሆኑን ለመደምደም የሚያስችሉ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና 1793 ድንጋጌዎች የሚሸፈኑ ሁኔታዎች በመዝገቡ በተደረገው ክርክር የሌሉ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩን በይግባኝ ያዩት ፍርድ ቤቶች የስር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በአግባቡ ሣይመረምሩ እና ለውሣኔአቸው በቂ ምክንያት ሣይሰጡ ተጠሪ እቃውን በወቅቱ ያላቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ነው በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትን ውሣኔ መሻራቸው የፍትሀብሔር ስነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 182 ንኡስ አንቀጽ 1 የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና የፍትሀብሔር ሕግ ቁጥር 1793 ድንጋጌዎችን የሚጥስና መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ እቃውን በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ያላቀረበው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አይደለም ብለናል፡፡
3. አመልካች ተጠሪ በውሉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ አስፓልቱን ባለማቅረቡ ለተጠሪ ከሚከፍለው ክፍያ በመቀጫ መልክ ቀንሶ ያስቀረውን ገንዘብ የመመለስ ግዴታ የለበትም፡፡ ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 36979

ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-**ቤዛ አማካሪ መሀንዲሶች ኃ/የተ/የግ/ማህበር - ጠበቃ ግርማ ኃ/መስቀል ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ሚስተር ሽሬሃሪ ብራማቫሪ ጉፓል - ጠበቃ አቶ ሀይልዬ ሣህለ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 57672 የካቲት 3 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት ስላመለከተ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርቦ ተከሳሽ(የአሁን አመልካች) አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት መብቴ እንዲጠበቅልኝ በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ ከሳሽ (ተጠሪ) የድርጅቱ ክፍለሀጉራዊ ሥራ አስኪያጅ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው፤ ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ችሎት መታየት የለበትም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ክሱን ዘግቶታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኂላ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ የያዘውን የሥራ መደብ ስያሜ በመመልከት ብቻ የሥራ መሪ ነው ማለት ስለማይቻ ስልጣን የለኝም ያልከው አላግባብ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክረህ ወሰን በማለት ጉዳዩን ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሶለታል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመሠረቱ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማከራከር ስልጣን የለኝም በማለት ያዘጋው በአግባቡ ነው፡፡ ከተጠሪ ጋር የተደረገው የሥራ ውል እና ከኢትዮጵያ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር በአመልካች ተጠያቂነት ለተጠሪ የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ ማስረጃ ተጠሪ ሪጅናል ማኔጀር እንደሆኑ የሚያረጋግጡ ናቸው፡፡ ይህንን ማስረጃ ፍርድ ቤቱ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት አስቀርቦ እንዲመለከትልን ጠይቀናል፡፡ ፍርድ ቤቱ የጠየቅነውን ማስረጃ አስቀርቦ ሣይመለከት ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ጉዳያቸው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ይታያል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው በአመልካችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት የሚገባ ስለመሆኑ በውሉ አንቀፅ 7 እና አንቀጽ 12 የተመለከቱትን ሀይለ ቃሎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አመልካች የተጠሪን የሥራ ዝርዝርና የድርጅቱን መዋቅር በማቅረበ ተጠሪ ሥራ መሪ መሆናቸውን አላስረዳም፡፡ ይህ ከሆነ

“ክፍለሀጉራዊ ሥራ አስኪያጅ” የሚለውን ስያሜ በማየት ብቻ ሥራ መሪ ናቸው ሊባል ስለማይገባ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የለበትም ስለዚህ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጠተዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቀርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በፅሑፍ በሰበር ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪው የሥራ መሪ መሆኑን በመግለፅ ያቀረበውን መቃወሚያ በመቀበል መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ በሌላ በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የሥር ፍርድ ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡ አመልካች ተጠሪን እንድቀጥር የሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ያቀረብኩት አቤቱታ መነሻ ለተጠሪ የውጭ አገር ዜጋ በመሆናቸው ከሠራተኛ እና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር የተሰጣቸው የሥራ ፈቃድ በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 145 መሠረት ፍርድ ቤቱ አስቀርቦ እንዳይላቸው ጠይቀው ፍርድ ቤቱ ይህንን ማስረጃ ሣያስቀርብ ተጠሪ የሥራ መሪ አይደሉም በማለት ውሣኔ እንደሰጠባቸው በመግለፅ በሰበር ተከራክረዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ መሆናቸውን የሥራ ፈቃድም ያገኙት በዚሁ የሥራ ሀላፊነት ለመሠማራት መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት እንዲቀርብ የጠየቁት ማስረጃ የሥር ፍርድ ቤት ያላስቀረበው በመሆኑ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር 345 ንዑስ አንቀፅ 1(ሀ) መሠረት ማስረጃውን በማስቀረብ ውሣኔ መስጠት ነበረበት፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች እንዲቀርብላቸው የጠየቁት ማስረጃ ሣያስቀርብ መወሰኑ ከላይ የተጠቀሰውን የህግ ድንጋጌ የሚተላለፍ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስኗል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ከሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲቀርብላቸው የጠየቁትን ማስረጃ በማስቀረብና ጉዳዩን በማጣራት ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩን በፍታብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 343 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ
   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 41544

ሐምሌ 08 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሠላም የሕዝብ ማመላለሻ አ/ማ - ጠ/ረዳይ ባራኪ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - አልቀረቡም፡፡

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ በመልካችና በሌላ ግለሠብ ላይ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የመሠረተው ክስ ነው፡፡ በክሱም ተጠሪ የመድን ሽፋን የሰጠውን መኪና ንብረትነቱ የአመልካች የሆነ መኪና በሥር ሁለተኛ ተከሣሽ ሲሽከረከር ገጭቶ ጉዳት በማድረሱ ጉዳቱን ለማስጠገን ያወጣውን ወጪ ተከሣሾች እንዲተኩለት ጠይቋል፡፡

የአሁኑ አመልካች ጉዳት አደረሰ የተባለውን መኪና በጨረታ አቶ ተክሉ አስፋው ለተባሉ ግለሰብ ስለተሰጠ ተጠያቂነት የለብኝም መኪናውን የገዙት ግለሰብ በክሱ ውስጥ እንዲገቡ ተደርጎ እኔ ልሰናበት በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤት ግን አመልካች መኪናው ለሌላ ግለሰብ ሸጥኩ ይበሉ እንጂ የባለቤትነት ስሙ በገዢው ያልተዛወረና መኪናው አሁንም በአመልካች ስም ስለሚታወቅ ለጉዳቱ ኃላፊነት አለበት በማለት በክሱ የተጠየቀውን ገንዘብ እንዲከፈል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም መኪናውን ገዝተዋል የተባሉት ግለሰብ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ተጠይቆ የሥር ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ሣይቀበል ማለፉ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ግራ ቀኙም ቀርበው የቃል ክርክሩ ተሠምቷል፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት መኪናውን ገዙ የተባሉት ግለሰብ ወደ ክርክሩ ሊገቡ ይገባል? ወይስ አይገባም? የሚለውን ጭብጥ ከሚመለከተው ሕግ አኳያ መርምሯል፡፡

በተጠሪ መኪና ላይ ጉዳት አደረሠ የተባለው መኪና የአመልካች የነበረ ሲሆን አመልካች መኪናዋን ለሌላ 3ኛ ወገን ቢሸጡም የባለቤትነት ስሙ በገዢው ስም አልተዛወረም፡፡ የመኪና ባለቤትነት የሚተላለፈው እንደሌለ ማንኛውም ተንቀሣቃሽ ንብረት ንብረቱን ገዝቶ ወይም በሌላ መንገድ አግኝቶ በእጅ በማድረግ አይደለም፡፡ መኪና ላይ ተንቀሣቃሽ ንብረት በመሆኑ ባለቤትነት የሚተላለፍበት መንገድ በልዩ በሕግ ተደንግጓል፡፡ በዚህም መሠረት የንብረቱ ባለሃብትነት የሚታለፈው የባለቤትንት ስሙ በገዢው ስም ሲዛወር ነው፡፡ ይህን በተመለከተ የሰበር ችሎት በመ/ቁ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በተያዘው ጉዳይም አመልካች መኪናውን ለሌላ ሰው ቢሸጡም የመኪናው የባለቤትነት ስም በአመልካቹ በመሆኑ በባሌቤትነት የሚታወቀው አመልካች ነው፡፡ የመኪና ባለቤት ደግሞ መኪናው በደረሰው ጉዳት ያለጥፋት ኃላፊ መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2081/1/ ተመልክቷል፡፡

በሌላ በኩል ግን አመልካች መኪናውን ለ3ኛ ወገን ሸጦ ገዢው መኪናውን መረከቡንና ጉዳቱ በደረሰ ጊዜም መኪናዋ በገዢው ይዞታ ሥር ነበር በማለት ተከራክሯል፡፡ የመኪናው ባለቤት ባይሆንም እንኳን መኪናውን ለግል ጥቅሙ

ሲገለገልበትና ሲጠቀምበት የነበው ሰው መኪናው በይዞታው ሥር በነበረበት ጊዜ ለደረሰው ጉዳት በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2082/1/ መሠረት ኃላፊ ነው፡፡ በአጠቃላይ የመኪናው ባለቤትም ሆነ ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ መኪናውን ሲጠቀምበት የነበረ ሰው ሁለቱም ኃላፊነት አለባቸው፡፡ የመኪናው ባለቤትም ያለው መብት ተጎጂውን ከካሠ በኋላ በአደጋው ጊዜ መኪናውን ይዞ ሲገለገልበት የነበረውን ሰው የካሰውን የገንዘብ መጠን እንዲተካለት መጠየቅ ነው /የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2983/1/ ስለሆነም አመልካች መኪናውን ሸጦ ለሌላ ሰው ያስረከበ ቢሆንም የባለቤትነት ስሙ በገዢው ስም ባለመዛወሩ በሕግ የመኪናው ባለቤት ሆኖ የሚወሰደው እሱ ነው፡፡ ባለቤት በመሆኑም ለጉዳቱ ኃላፊ ነው፡፡

የአመልካች ኃላፊነት እንዳለ ቢሆንም ግን የመጨረሻው የመካስ ኃላፊነት የሚወድቀው መኪናውን ይዞ ሲገለገልበት የነበረው ሰው ላይ ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደገለጽነው የመኪናው ባለቤት ተጎጂውን ከካሠ በኋላ ይህንን ካሣ የሚተካው መኪናውን ሲጠቀምበት የነበረው ሰው ነው፡፡ ተከሣሽ የሆነ ሰውም በክሱ ውስጥ የሌለ ሦስተኛ ወገን ከክሱ ጋር ድርሻ ካሣውን መክፈል አለበት በሚል ይኸው ሰው ወደ ክሱ እንዲገባለት መጠየቅ የሚችል መሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ በክሱ እንዲገባ የሚጠየቀው ሰው ካሣውን የሚከፍልበት ምክንያትና የድርሻውም ልክ መገለጽ እንዳለበት ይኸው የሥነ-ሥርዓት ሕግ ያስገድዳል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች ከተሟሉ ግን ፍ/ቤቱ ጥያቄውን ውድቅ የሚያደርግበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሦስተኛ ወገኖች ወደ ክሱ እንዲገቡ የሚዳረጉት በአንድ ጉዳይ ሊነሱ የሚችሉትን የመብት ጥያቄዎች በሙሉ በአንድ ክስ መወሰን እንዲችልና በተመሣሣይ ጉዳይ ሊቀርቡ የሚችሉ የተነጣጠሉ ክሶችን ለማስቀረት ነው፡፡ በመሆኑም ተከሣሹ ጣልቃ እንዲገባ በሚጠይቀው ሰው ላይ የሚያነሣውን ጥያቄ ሌላ የተነጠለ ክስ ማቅረብ ሣያስፈልገው በተጀመረው ክስ ሊወሰን ይችላል፡፡ ስለሆነም ተከሣሹ ለክሱ ኃላፊነት ካለበት ጣልቃ ገቡ በቀጥታ ለከሣሽ ሊከፈል ሊወሰን ይችላል ከዚህም በተጨማሪ ጣልቃ ገቡ በክሱ ውስጥ ከገባ በኋላ በክሱ ውስጥ እንዳለ የሚቆጠር በመሆኑ /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 43/2// ለቀረበው ክስ ያለውን መከላከያ የማቅረብ እድል ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 43 አላማ ከአንድ ግንኙነት የሚመነጩ ጥያቄዎች በሙሉ ተጠቃለው በአንድ ክስ እንዲያልቁ እና የተነጣጠለ ክስ ማስቀረት በመሆኑ ፍ/ቤቶች በሥነ-ሥርዓት ሕጉ የተመለከቱት መስፈርቶች እስከተሟሉ ድረስ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ የሚችሉበት የሕግ መሠረት የለም፡፡

በተያዘው ጉዳይ ጉዳት ያደረሰው መኪና ጉዳቱን ባደረሰበት ጊዜ ጣልቃ እንዲገቡ በተጠየቁት ግለሰብ ይዞታ ሥር በመሆኑ ግለሰቡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2082/1/ መሠረት ኃላፊ ሊሆኑ የሚችሉ ስለሆነና የደረሰውን ጉዳት በሙሉም የመካስ ግዴታ ሊወድቅባቸው የሚችል በመሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2083/1/ ሥር መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ወደ ክርክሩ ጣልቃ ሊገቡ የሚገባቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም የሥር ፍ/ቤት ጣልቃ እንዲገቡ የተጠየቁት ግለሰብ ያለባቸውን ኃላፊነት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 43 መሠረት ጣልቃ ሣያስገባ መወሰኑ የሥነ ሥርዓቱን ድንጋጌ ያልተከተለና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 56353 መጋቢት 5/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 36956 ጥቅምት 7 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡
2. አደጋው በደረሰ ጊዜ አደጋውን ያደረሰው መኪና ሲጠቀሙበት የነበሩት ግለሰብ በክሱ ውስጥ ጣልቃ ገብተው ተከራክረው ተገቢው ውሣኔ እንዲሰጥ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሠረት ጉዳዩን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# አሠሪና ሠራተኛ

የሰ/መ/ቁ. 35197

ጥቅምት 13 ቀን 2001

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ኤፍሬም ንዋየማሪያም - ጠበቃ ቴዎድሮስ ተስፋዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ሕግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሚያዝያ 24 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ተጠሪ ከየካቲት 29 ቀን 1987 ዓ.ም ጀምሮ በአመልካች ድርጅት ተቀጣሪ ሆነው ሲሠሩ ቆይተው ስራውን በገዛ ፈቃዳቸው ሲለቁ ፕሮቪደንት ፈንድን ጨምሮ የሚገባቸውን ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን አመልካች የከፈላቸው ቢሆንም የስራ ስንብት ክፍያ ያልከፈላቸው መሆኑን ገልፀው የስራ ስንብት ክፍያ ብር 14,994.18/አስራ አራት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና አራት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ እና ይኸው ክፍያ ለዘገየበት ደግሞ የሦስት ወር ደመወዝ ብር 9,879.00 /ዘጠኝ ሺህ ስምንት መቶ ሠባ ዘጠኝ ብር/ በድምሩ ብር 24,873.18 / ሃያ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ሦስት ብር ከአስራ ስምንት ሣንቲም/ አመልካቹ እንዲከፍል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ለተጠሪ የሚገባውን ጥቅማ ጥቅም መክፈሉን፣ የስራ ስንብት ክፍያ ደግሞ ፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ጡረታ ላለው ሠራተኛ እንደማይከፈለው በአዋጅ ቁጥር 494/98 መደንገጉንና በዚህም ምክንያት ክፍያ ሊጠየቅ እንደማይገባ፣ የታመነ ክፍያም በወቅቱ የከፈለ በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት ተብሎ የሚቀጣበት የሕግ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈላቸው መሆኑን ማመናቸውን በመግለጽና አዋጅ ቁጥር 494/98 ደግሞ አንድ ሰው ሁለት ጊዜ እንዲከፈለው የሚፈቀድ አለመሆኑን በምክንያትነት በመውሰድ ተጠሪ የስንብት ክፍያ ጥያቄ አይገባቸውም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ባለመስማማትም ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ፍ/ቤቱ ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡ አመልካች ጥር 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት ያለባቸውን ምክንያቶች ዘርዝሯል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈለው ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈለው የማይገባ መሆኑን በአዋጅ ቁጥር 494/1998 ተደንግጎ እያለ ከአዋጁ መንፈስ ውጪ መተርጎሙ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡

ይህ ችሎትም የአመልካችን የሰበር አቤቱታ በመመርመር ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ የተከፈላቸው መሆኑ ተረጋግጦ እያለ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፈላቸው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑን ለማጣራት ተጠሪን ያስቀርባል ብሎ ተጠሪ ሚያዝያ 02 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ የመልሣቸው ይዘትም በአጭሩ፡- የአመልካች የሠበር አቤቱታ የክርክር ነጥቦች ከሕጉ ዓላማና መንፈስ ውጪ መሆናቸውን በጉዳዩ ላይ የተሰጠው

የፍ/ቤቱ ትርጓሜ ግን ተገቢነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 06 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የሠበር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ፣ የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር አግባብነት ካለው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለው? ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን መልቀቃቸውንና የፕሮቪደንት ፈንድም በወቅቱ ተከፍሏቸው የተሰናበቱ መሆኑን በማመን የሚከራከሩ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ይህ ቢረጋገጥም የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት በሕግ የተጠበቀ መሆኑን ተጠሪ አጥብቀው የሚከራከሩ ሲሆን አመልካች የተጠሪ ጥያቄ የሕግ መሠረት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙን ክርክር እልባት ለመስጠት አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ይዘት እና መንፈስ መመልከትን የግድ ይሏል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች ለጉዳዩ አግባብነት ያለውን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓ.ም ሲሆን ይህ አዋጅ ከአሻሻላቸው የአዋጅ ቁጥር 377/96 ድንጋጌዎች አንዱ ስለስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አንዱ ነው፡፡ የማሻሻያ አዋጁ በዚህ ረገድ ያስቀመጠው ድንጋጌ ሙሉ ይዘቱ በሚከተለው መልኩ የተቀመጠው ነው፡፡ ይኸውም

"የሙከራ ጊዜውን የጨረሰ ሠራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለው ሲሆንና በጡረታ ሕግ የተቀመጠው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከስራ ሲገለል ከአሠሪው የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት አለው፡፡" /አንቀጽ 2/ሰ/ ይመለከቷል/ የሚል ሲሆን የድንጋጌው የእንግሊዝኛ ትርጉሙም፡-

> **"A worker who had completed his probation shall have the right to get severance pay from the employer where he has no entitlement to a provident fund or pension right and his contact of employment is terminated up on attainment of retirement age stipulated in the pension law"** በሚል ይደነግጋል፡፡

ከድንጋጌው የአማርኛና የእንግሊዝኛ ትርጉም በቀላሉ መገንዘብ የሚቻለው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ የስራ ስንብት ክፍያ ከአሠሪው የማግኘት መብት የሌለው መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የፕሮቪደንት ፈንድ እና የስራ ስንብት ክፍያዎች በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ ምንጭ የማግኘት መብት ላይ በሕጉ ክልከላ ተደርጓል፡፡

እንደሚታወቀው የስራ ስንብት ክፍያ ዓይነተኛ ዓላማው በስራ ላይ የቆየ ሠራተኛ አዲስ ስራ ፍለጋ ላይ እያለ ሊደርስበት የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ችግር በመጠኑም ቢሆን ለመቀነስ ነው፡፡ የፕሮቪደንት ፈንድ ዓላማም ከዚሁ የተለየ አይደለም፡፡ አላማቸው አንድ ዓይነት ከሆነ ሁለቱም የክፍያ ዓይነቶች በተመሣሣይ ጊዜ ከአንድ ምንጭ እንዲከፈሉ ማድረግ አሠሪን ሁለት ጊዜ እንደመቅጣት ከሚቆጠር በስተቀር ፍትሐዊነት አይኖረውም፡፡ በመሆኑም ሕግ አውጪው የፕሮቪንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሠራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ከአሠሪው የስራ ስንብት ክፍያ የመጠየቅ መብቱን የነፈገው ከላይ የተገለፀውን አሠሪን ሁለት ጊዜ እንዳይከፍል ለመጠበቅ ነው ተብሎ ከሚታሰብ ውጪ ሌላ ምክንያት ሊኖር አይችልም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ሆነው ክፍያም የተፈፀመላቸው መሆኑን እያመኑ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ /ማሻሻያ/ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/ሰ/ ሥር በተመለከተው አኳኋን በሕጉ የከለከሉትን የመብት ጥያቄ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተቀብሎ ውሣኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተናል፡፡

በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57691 ታኅሣሥ 21 ቀን 2000 ዓ.ም ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈላቸው ይገባል ሲል የሰጠው የውሣኔ ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/1998 ዓ.ም አንቀጽ 2/ሰ/ ስር በተደነገገው መሠረት የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ያለው ሠራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የለውም ብለናል፡፡
3. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቁራ ምድብ 2ኛ የስራ ክርክር ችሎት በመ/ቁ. 26971 ሠኔ 20 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 35621

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሰንሻይን ኮንስትራክሽን - አልቀረበም

**መልስ ሰጭ፡-** 1. አቶ ፍቃዱ ገቢሣ - አልቀረቡም

2. አቶ ታዬ ዋሚ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የታች ተከሣሽ ሲሆን የአሁን መ/ሰጭ የታች ከሣሾች ነበሩ፡፡ መ/ሰጭ በታች ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት በመቀጠር በአናፂነት ሙያ ሲያገለግሉ ቆይተው ሌላ ሣይት (ቦታ) ሥራ እያለው ሥራው አልቋል በማለት ያለ ቅድመ ማስጠንቀቂያ የሥራ ውላችንን አቋርጦብናል ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማስጠንቀቂያ የሁለት ወር የዘገየበት የስንብት የስድስት (6) ወር ክፍያ እና የትርፍ ሰዓት ክፍያ እንዲወሰንልን በማለት ጠይቋል፡፡

ተከሣሽ (የአሁን አመልካች) ጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም በጽሁፍ ባቀረበው መልስ ከሣሽ (መልስ ሰጭ) ደመወዝ የሚከፈላቸው በቀን ታስቦ እንደሆነና ከአመልካች ድርጅት ጋር የፈፀሙት ጊዜያዊነት ያለው የሥራ ውል የተመደቡበት የአናፂነት ሥራ በሚኖርበት ጊዜ ብቻ የሚከፈላቸው መሆኑን ገልጾ የስራ ውሉ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 24(1) መሰረት በሕጋዊ መንገድ እንደተቋረጠ በመግለጽ ተከራክሮ ክሱ ውድቅ እንዲደረግ ጠይቋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ የመልስ ሰጭ የሥራ ውል መቋረጡ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ ይዞ መዝገቡን መርምሮታል፡፡ በዚህም መሰረት በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሠ) መሰረት ሥራው ምንም እንኳ የአሠሪው ቋሚ ሥራ ቢሆንም አልፎ አልፎ የአናፂነት ሥራው ሲኖር የሚሰራ መሆኑን ተረድቻለሁ በማለት አመልካች መልስ ሰጭን ማሰናበቱ በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 10(1)(ሀ) መሰረት በአግባቡ ነው ሲል ወስኗል፡፡

መልስ ሰጭም በተሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት የታች ፍ/ቤት ማስረጃ ሣያጣራ ወሰነብን በማለት ለከፍተኛው ፍ/ቤት አቤቱታቸውን አቅርቧል፡፡

የከፍተኛው ፍ/ቤትም በቀረበለት አቤቱታ መሰረት የአሁን አመልካች መልስ እንዲሰጥበት ካደረገ በኂላ ይግባኝ ባይ (የአሁን መልስ ሰጭ) የተቀጠሩት ለየትኛው ፕሮጀክት ነው? ፕሮጀክት በመጠናቀቁ ነው ወይስ አይደለም የተሰናበቱት? የሚለውን ጭብጥ መሥርቶ ከመረመረ በኂላ በቅጥር ውል ላይ “ለምን ስራ፣ እስከመቼ” የሚለውን የሚያስረዳ ባለመሆኑ የአሁን መልስ ሰጭ (የታች ከሳሽ) የተቀጠሩት በአዋጁ አንቀጽ (10) ስር በተደነገጉት መሰረት ነው ተብሎ የሚወሰድበት ምክንያት የለም በማለት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በመሻር ስንብቱ ያለ አግባብ ነው በማለት ለአሁን መልስ ሰጭ የ8 ወር ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈላቸውና ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሳኔ በመሻሩ ቅር ተሰኝቶ ሲሆን የጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም የጉዳዩን አመጣጥ ካጠና በኂላ የሥር ፍ/ቤት ማስረጃ መስማት እየቻለ መልስ ሰጭ የተቀጠረበት ሥራ መጠናቀቁ እየተገለፀ ወደ ሥራ ይመለሱ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ጉዳዩን አስቀርቦታል፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱትን ጭብጦች በመያዝ ግራ ቀኙ በጉዳዩ መልስ እና የመልስ መልስ እንዲያቀርቡ በማድረግ አከራክሯል፡፡

በታች የተሰጡትን ውሳኔዎች ከህጉ በማገናዘብ እንዳየነው መልስ ሰጭ "በፊንጫ ለምለም" ፕሮጀክት ውስጥ በአናፂነት ሥራ ሲሰሩ እንደቆዩ በመግለጽ ሥራ በሌላ ሣይት (ቦታ) እያለ ሥራ አልቋል በመባል መሰናበታቸው ከሕግ ውጭ ነው ሲሉ ባቀረቡት ክስ መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አከራክሮ ስንብቱ በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 10(1) (ሀ) መሰረት ሕጋዊ ነው ሲል ወስኗል፡፡ ይግባኝ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የመልስ ሰጭ የቅጥር ሁኔታ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 10(1)(ሠ) ከተዘረዘሩት ውጭ ስለሆነ ስንብቱ ህጋዊ አይደለም በማለት የተጠየቀውን ክፍያ እንዲከፍላቸውና ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ በመወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 348/1/ መሰረት የታች ውሳኔን ሽሮታል፡፡

በመሰረቱ ከላይ ከተነሱት ክርክሮች መገንዘብ እንደተቻለው መልስ ሰጭ በአመልካች ድርጅት ለምን ስራ እንደተቀጠሩ በሚለው ነጥብ ቀድሞውንም አልተከራከሩም (አልተካካዱም) የአናፂነት ሥራ ደግሞ በግንባታ ሥራ ውስጥ ወቅቱን ጠብቆ የሚሰራ እና ከተወሰነ ጊዜ በኂላ የተጀመረው ግንባታ እንደሚጠናቀቅ ግልጽ ሆኖ ሳለ ለምን ስራ እና እስከመቼ ይሰራሉ? የሚለውን ነጥብ ማየቱ በተያዘው ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡ መልስ ሰጭ ቢሆኑም በክሳቸው ውስጥ ድርጅቱ ሌላ ቦታ(ሣይት) እንዳለው በመግለጽ ሥራው አላለቀም በማለት ይከራከራሉ፡፡

በመሰረቱ በሌላ ቦታ ተጨማሪ (ተመሣሣይ) ሥራ መኖሩ የተባለውን የፕሮጀክት ሥራ አላለቀም የሚያስብል አይሆንም፡፡ ድርጅቱም የግድ ከአንድ ፕሮጀክት ወደ ሌላው ፕሮጀክት ሰራተኞችን ይዞ እንዲዞር የሚያስገድደው የሕግ ነጥብ አይኖርም፤ ምክንያቱም ድርጅቱ የራሱ የሆነ የአሰራር ስርአት ይኖረዋል ተብሎ ስለሚገመት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የሥራውን መጠናቀቅና መኖር በድጋሚ በማስረጃ ማጣራት እየተቻለ ይህ ሣይደረግ በከፍተኛው ፍ/ቤት ስንብቱ ያለ አግባብ ነው መባሉና መልስ ሰጭ የጠየቁት ክፍያ ተከፍሎአቸው ወደ ስራቸው ይመለሱ ተብሎ መወሰኑ የአዋጁን አንቀጽ 10(1) (ሠ)"ን" ያላገናዘበ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23063 በሰኔ 6 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ፀንቷል ይፃፍ፡፡
2. በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57553 በታህሳስ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ስንብቱ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ.ቁ. 36692

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብድልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አንበሳ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት

ነገረፈጅ ፋሲካ በለጠ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ተስፋዬ መኰንን - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የሚታይ የስራ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ ሲሆን፣ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው ከሐምሌ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ ለድርጅቱ ሠራተኞች በሙሉ የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ ተደርጎአል፡፡ እኔም የድርጅቱ ሠራተኛ በመሆኔ ጭማሪው ሊሰጠኝ ሲገባ አለአግባብ ተከልክያለሁ፡፡ ስለዚህም ጭማሪ እንዲሰጠኝ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ ሦስት አራተኛውን ጊዜ በስራ ላይ ስላልነበረ ጭማሪውን ሊያገኝ አይችልም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር የመረመረ ሲሆን፣ በመጨረሻም የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል ተጠሪ በጠየቀው መሠረት የደመወዝ ጭማሪው ይሰጠው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በተመሣሣይ ሁኔታ ወስኖአል /የስር ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል/፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 22 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በድርጅቱ ፀንቶ ያለው በሕብረት ስምምነት ጭማሪው የማይደረግበትን ምክንያት አስቀምጦአል እየተባለ አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ሕጋዊ የሚሆንበት አግባብ ምንድነው? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ነጥቡን ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሁለቱ ወገኖች ክርክር እና በሥር ፍ/ቤቶች ከተሰጡት ውሣኔዎች ይዘት መገንዘብ እንዲቻል ነው ተጠሪ በተባለው የበጀት ዓመት ውስጥ የዓመቱን 3/4 /ሦስት አራተኛ/ ጊዜ በስራ ላይ አልነበረም፡፡ በወቅቱ ፀንቶ በነበረው /ባለው/ የህብረት ስምምነት አንቀጽ 29/5/ እንደተመለከተው ይህን ያህል ጊዜ በስራው ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ ጭማሪው እንደማይሰጠው ደግሞ አላከራከረም፡፡ የስር ፍ/ቤቶች ይህንኑ በሚገባ ስለመገንዘባቸው በውሣኔዎቻቸው ላይ የገለፁ ሲሆን፣ ጭማሪው መሰጠት አለበት በማለት የወሰኑት ግን በሕብረት ስምምነቱ የሌለን ምክንያት መሠረት በማድረግ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡ ይህ ተጠሪ አመልካች በወሰደው የስራ ውል ማቋረጥ እርምጃ ምክንያት በክርክር ስለመቆየቱ የሚገልጽ ነው፡፡

በእርግጥም አመልካች የስራ ውሉን አቋርጦ ስለነበር ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረበው ክስ መሠረት ክርክር ከተደረገ በኋላ ወደስራው እንዲመለስ ተወስኖለታል፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ሁኔታ ለእርከን ጭማሪው እንደበቂ ምክንያት አድርገው የወሰዱት ተጠሪ በስራው ላይ ሊገኝ ያልቻለው አመልካች በወሰደው ሕገ ወጥ የስራ ውል ማቋረጥ ምክንያት ነው፡፡ ይህንኑም በፍ/ቤት ተረጋግጦ ተወስኖአል በማለት ነው፡፡ በበኩላችን እንደምናየው የእርከን ጭማሪ አሰጣጥን በተመለከተ የተደነገገው የሕብረት ስምምነቱ አንቀጽ 29/5/ በግልጽ የሚያመለክተው በበጀት ዓመቱ ውስጥ 3/4ኛው ጊዜ በስራ ላይ ያልተገኘ ሠራተኛ የእርከን ጭማሪ የማይሰጠው እንደሆነ ነው፡፡ ድንጋጌው ይህን ያህል ግልጽ ከሆነ ደግሞ ትርጉም የሚያስፈልገው አይሆንም፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ሕገወጥ በሆነ ምክንያት ነው ወይስ አይደለም? በሚል ጭብጥ ላይ ተመስርቶ ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔም ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የጠየቀውን የእርከን ጭማሪ ሊያገኝ ይገባል ብሎ ለመወሰን የሚያስችል የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 34178 በታህሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 63056 የካቲት 7 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. ተጠሪ በክሱ የጠየቀውን የአንድ እርከን የደመወዝ ጭማሪ እንዲያገኝ የሚደረግበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37027

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ግርማ ማርቆስ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ አሰለፈች ደስታ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት የሥራ ክርክር ክስ ነው፡፡

ተጠሪ ለፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ የወሰደባቸው የዲሲፕሊን እርምጃ እንዲሻር፣ ተጠሪ ወደ ቀድሞ የስራ መደብ እንዲመልሳቸው እና የተቋረጠውን የደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደባቸው ጥፋተኛነታቸው ተረጋግጦ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል ብሏል፡፡ ፍ/ቤቱም አመልካች የወሰደውን እርምጃ አሻሽሎ ተጠሪ በ4 ቀን ደመወዝ እንዲቀጡና ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ወደ ቀድሞ ስራቸው እንዲመለሱ፤ በደመወዝ ላይ የተደረገው ጭማሪም ተስተካክሎ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ አመልካች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የአመልካችን ይግባኝ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ ሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ በህብረት ስምምነቱ የጥፋት አይነቶችና የቅጣት ደረጃዎች ተዘርዝረዋል፡፡ አንድ ሰራተኛ ጥፋት ሲፈጽም እርምጃ የሚወሰድበት ስለጥፋት አይነቶች እና ስለ ቅጣት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሲሆን የጥፋቱን ክብደት ከሚያሳዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ የሆነውን ቅጣት መቅጣት ይቻላል፡፡ የጥፋት አይነቶች እና የቅጣት ደረጃዎች የተቀመጡት የተፈፀመውን ጥፋት ክብደት ለመመዘን እንዲያመች እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን ለመወሰን አይደለም የሚል ነው፡፡

ተጠሪም ቀርበው በሰጡት መልስ ስህተቱ የተፈጠረው በእርሣቸው ስህተት ባለመሆኑና ከድርጅቱ የውስጥ አሰራርና አመራር ጉድለት በመሆኑ አቤቱታው ተቀባይነት እንደሌለው ተከራክረዋል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡን መርምሯል፡፡ የሥር ፍ/ቤት በህ/ስምምነት ውስጥ ከተዘረዘሩት የቅጣት አይነቶች ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ በአንድ ጥፋት በ4ኛ ደረጃ የተቀመጠውን ቅጣት እንዲቀጡ መወሰኑ ሕጋዊ አይደለም በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የቅጣት ደረጃው ቅደም ተከተልን የሚያሣይ ሣይሆን በተፈፀመው ጥፋት ክብደት ተገቢውን ቅጣት ለመወሰን የተቀመጡ ናቸው በማለት ተከራክሯል፡፡

ከመዝገቡ ለመረዳት እንደተቻለው የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥፋተኛነት ተቀብሎ ወደ ቅጣት ውሣኔው ትክክለኛነት አምርቷል፡፡ አመልካች ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ ሊቀጡ የሚገባው የህ/ስምምነቱ ከዘረዘረው ቅጣቶች በቅደም ተከተል ነው ወይስ ህ/ስምምነቱ እንደጥፋቱ ክብደት ቅደም ተከተል ሣይጠበቅ ቅጣቱ ይጣል የሚለው ነ1ው፤ አከራካሪ የሆነው፡፡ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም በሰጡት መልስ ምንም የፈፀሙት ጥፋት የሌለ ከመሆኑ ውጪ ቅጣቱ በምን ሁኔታ መፈፀም እንዳለበት ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የተጠሪን ጥፋተኛነት አረጋግጠው በሰጡት ውሣኔ ላይም የቀረበ አቤቱታ ባለመኖሩ ተጠሪ ጥፋተኛ ናቸው አይደለም ወደሚለው ነጥብ መግባት አስፈላጊ አይሆንም፡፡ አንድ ሰራተኛ

ጥፋተኛ ሆኖ ከተገኘ ቅጣቱ እንዴት ነው ሊወሰን የሚገባው የሚለውን ስንመለከት የአመልካች መ/ቤት ህብረት ስምምነት እንደሚያሣየው ለተለያዩ የጥፋት አይነቶች የተለያዩ ቅጣቶች ተመልክተዋል፡፡ ተጠሪ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት የተመደቡበትን ስራ በቸልተኛነት አለመስራት ጥፋት ለምሣሌ በ5 የተለያዩ የቅጣት ደረጃዎች ሊያስቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም በመ/ቤቱ የሕብረት ስምምነት አንቀጽ 22(12)(ሀ) ሥር በአንድ ሰራተኛ ላይ የዲሲፒሊን እርምጃ ሲወሰድ የሚወሰነው ቅጣት ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያስረዳው ሰንጠረዥ መሰረት ሆኖ የጥፋቱን ክብደት ከሚያሣዩት ደረጃዎች ለጥፋቱ ተመጣጣኝ በሆነ የቅጣት ደረጃ ሊቀጣ እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ስለጥፋትና ስለቅጣት አይነት በሚያሣየው ሰንጠረዥ ግርጌም የቅጣት ደረጃው የሚያመለክተው እንደጥፋቱ ክብደትና ቀላልነት የጥፋቱን ደረጃና ለደረጃውም የሚወሰነውን ቅጣት እንጂ የጥፋት ቅደም ተከተልን እንዳልሆነ በማሳሰቢያነት ተቀምጧል፡፡ በመሆኑም ከህ/ስምምነቱ አንድ ሰራተኛ ጥፋተኛ ሆኖ ስለተገኘ ቅጣቱ የሚጣልበት በሰንጠረዡ ላይ በሰፈረው ደረጃ ቅደም ተከተል ሣይሆን የጥፋቱ ክብደት ታይቶ ተመጣጣኝ ነው ተብሎ በሚገመተው የቅጣት ደረጃ እንደሆነ ተገንዝበናል፡፡

በተያዘው ጉዳይም አመልካች ተጠሪ በቸልተኛነት ሥራ ባለመስራት በመ/ቤቱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት በማድረሣቸው የጥፋታቸው ክብደት በደረጃ አራት ላይ የተመለከተውን የቅጣት አይነት ያስቀጣቸዋል በማለት በዚሁ መሰረት እርምጃ ወስዷል፡፡ የጥፋቱን ክብደት በመመዘን ይመጥናል የሚለውን ቅጣት የመወሰን ተግባር ደግሞ ለአሰሪው ሊተው የሚገባ አስተዳደራዊ ስራ መሆኑን እናምናለን፡፡ ስለሆነም አመልካች ተጠሪ ጥፋተኛ ለሆነበት ድርጊት የተመለከተውን ቅጣት መወሰኑ ህገ ወጥ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የስር ፍ/ቤቶችም የህብረት ስምምነቱን በአግባቡ ሣያጤኑ ቅጣቱ ሊወሰን የሚገባው በቅደም ተከተል ነው በማለት የሰጡት ውሣኔም ከላይ በሰፈሩት ምክንያቶች ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 21035 በሐምሌ 2 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58454 በየካቲት 26 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. አመልካች በተጠሪ ላይ የወሰደው እርምጃ የህ/ስምምነቱን መሰረት ያደረገ በመሆኑ የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም ፡፡
3. ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ወጪና ኪሣራ ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36518

ጥቅምት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሜታ አቦ ቢራ አክሲዮን ማህበር - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ፡-** እነ ሳሙኤል ተፈራ (4 ሰዎች) - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ ሕግ መሰረት የሚታይ ክርክር ሆኖ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ተከሣሽ ተጠሪዎች ከሣሾች ነበሩ፡፡ ተጠሪዎች አመልካችን የከሰሱት በድርጅቱ ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ የሕክምና ሰራተኞች መሆናቸውን ገልፀው ከጽሁፍ ሥራ ጋር በተያያዘ የተቋረጠባቸውን ክፍያ፣ በሽፍት ለሰሩት ሥራ ሊከፍል የሚገባውን ክፍያ እና የአልጋ ክፍያ እንዲከፍላቸው እንዲሁም የጽዳት ሰራተኛ እንዲመድብላቸው በመጠየቅ ነው፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ አመልካች ቢራ አምርቶ ለመሸጥ የተቋቋመ ድርጅት ነው፤ ተጠሪዎችም ስራቸው የመጀመሪያ የህክምና እርዳታ መስጠት ነው፤ ድርጅቱ ባወጣው የፈረቃ ድልደላ መሰረት እሁድ ስራ ላይ ለዋለ ሰራተኛ በቀጣዩ ቀን 24 ሰዓት እረፍት ይሰጠዋል፤ በሣምንት 48 ሰዓት ይሰራሉ፤ ላልሰሩበት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም፤ በሽፍት ሥራ ለሚሰራ ሰራተኛ የአልጋም ሆነ የእራት ክፍያ የሚፈጸምበት ህጋዊ ምክንያት የለም፤ የሕክምና መሣሪያቸውን የማጽዳት ሐላፊነት የተጠሪዎች ስለሆነ የጽዳት ሰራተኛ ልመድብላቸው አይገባም፤ በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍ/ቤቱም ክርክሩን መርምሮ ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት እንደሚሰሩ እና እሁድ ቀን በሥራ ላይ ከተገኙ በሚቀጥለው ቀን 24 ሰዓት የሚያርፉ መሆናቸውን በመረዳት ተጠሪዎች በሣምንት 48 ሰዓት ብቻ መስራታቸው እየታወቀ በሽፍት ሥራ እንሰራለን በማለት ብቻ ያቀረቡት የክፍያ ጥያቄ እና የጽዳት ሰራተኛ ይመደብልን ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማታቸው ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ተከራክረዋል፡፡

የከፍተኛ ፍ/ቤቱም በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ በማሻሻል በአዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 61/1/ መሰረት የማንኛውም ሰራተኛ የስራ ሰዓት በቀን ከስምንት ወይም በሣምንት ከ48 ሰዓት አይበልጥም ስለሚል እና የተጠሪዎች ቅሬታ በሣምንት ከ48 ሰዓት በላይ ሰራን ሣይሆን በቀን 16 ሰዓት ሰራን ነው ስለዚህ እንደሰራተኛ በቀን ከ8 ሰዓት በላይ መሥራት ግዴታ ባለመሆኑ አመልካች ተጠሪዎች በቀን 8 ሰዓት ብቻ እንዲሰሩ የሥራ ጊዜውን ያመቻች በማለት በማሻሻል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ማመልከቻ በከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡

ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በከፍተኛው ፍ/ቤት ለተጠሪዎች የሥራ ሰዓት ይመቻችላቸው በማለት የመወሰኑን አግባብነት ከአዋጁ እና ከሕብረት ስምምነቱ አኳያ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ስናየው ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ሲሰሩ ድርጅቱ ባወጣው የሥራ ሽፍት መሰረት ተስማምተው ሲሰሩ የቆዩ እና በድልድሉ መሰረት እሁድ ቀን ከሰሩ በሚቀጥለው 24፡00 ሰዓት እንደሚያርፉ ተገንዝበናል፡፡ አንድ ድርጅት እንደስራው ፀባይ በሕግ ከተደነገገው ማእቀፍ ሳይወጣ (ሳይጥስ) የሥራ ሰዓቱን ለማሻሻል የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ ተጠሪዎችም በዚሁ ተስማምተው በሣምንት ከ48 ሰዓት በማይበልጥ መልኩ በሽፍት ሲያገለግሉ ቆይተው የሌላቸውን (ያልሰሩበትን) የትርፍ ሰዓት ክፍያ የሚጠይቁበት የሕግ ድጋፍ የላቸውም፡፡ ሌላው የጽዳት ሰራተኛ እንዲመደብላቸው የጠየቁትንም በሚመለከት ቀድሞውኑም ተጠሪዎች የህክምና ባለሙያ በመሆናቸው የራሳቸውን የሕክምና መሣሪያ ሌላ ሰው ያጽዳልን ማለታቸው ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ የሰራተኛ ምደባው ውድቅ ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪዎች በሕጉ አግባብ በአመልካች ድርጅት እንደሚሰሩ ግልጽ ሆኖ ሳለ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የድርጅቱን የስራ ፀባይ ግምት ውስጥ ሳያስገባ አዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 61(1) ለመባል ከፈለገው አላማ ጋር በቅጡ ሳያገናዝብ የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴ በሚገድብ መልኩ በሣምንት ተጠሪዎች 48 ሰዓት መሥራታቸውን እየገለፀ ከአዋጁ መንፈስ ውጭ 8 ሰዓት ብቻ ለተጠሪ ይመቻችላቸው ብሎ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል መወሰኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 11276 በቀን ሰኔ 4 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
2. በከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57620 በጥር 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡ ተጠሪዎች ምንም አይነት ክፍያ ሊጠይቁ አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ኪሳራ ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 35484

ኅዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ አየር መንገድ - የቀረበ የለም

**ተጠሪ፡-** አቶ ደረጀ ማሞ - አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ መስከረም 15 ቀን 1999 ዓ.ም በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም በአጭሩ፡- በአመልካች ድርጅት ከጥር 06 ቀን 1989 ዓ.ም ጀምሮ በፀሐፊነት የስራ መደብ ተቀጥረው እየሰሩ መቆየታቸውን፣ ከዚሁ የስራ መደብ ላይ የቲኬት ሽያጭ ስራ መደብ ደርበው እንዲሰሩ ተደርጐ የብር 5,918.00/አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ አስራ ስምንት ብር/ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተባቸው መሆኑን፣ በዚህም ምክንያት የድርጅቱን ገንዘብ ለግል ጥቅም አውለዋል ተብለው ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ዘርዝረው ስንብቱ ሕገ ወጥ በመሆኑ ያለማስጠንቀቂያ የተሰናበቱበት ክፍያ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ እና ወጪና ኪሣራ እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉት መሆኑን አለመካዳቸውን በመጥቀስ በሕብረት ስምምነቱ አባሪ/1/ሀ(3) መሰረት የተወሰደባቸውን እርምጃ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ የቃል ክርክርና የተከሣሽን ምስክር ቃል ከሰማ በኋላ ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት የተገኘባቸው መሆኑ ቢረጋገጥም ጐደለ የተባለውን የገንዘብ መጠን ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል የቀረበ አሣማኝ ማስረጃ ባለመኖሩ አመልካች የሕብረት ስምምነቱን ጠቅሶ ተጠሪን ማሰናበቱ አግባብ አይደለም በማለት ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ የአሁኑ አመልካች በዚህ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥር 29 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ፡- ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ በእጃቸው ሊገባ የቻለውን ብር 5,918.00 ሊጐድልባቸው የቻለው በስልጠና ማነስና ከስራ ጫና የመጣ ነው ከማለት ውጪ ገንዘቡን ለግል ጥቅሜ አላዋልኩም በማለት ባልተከራከሩበት ሁኔታ ገንዘቡን ካልመለሱ ደግሞ ለግል ጥቅማቸው እንዳዋሉ ህጋዊ ግምት የሚወሰድበት ሆኖ እያለ የስር ፍ/ቤቶች የደረሱበት ድምዳሜ ተቀባይነት በሌለው መመዘኛ ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ ጥፋተኛ ስለመሆናቸው የቀረበ ማስረጃ በሌለበት እና መከላከያ ባልቀረበበት ጉዳይ የክርክር ጭብጥ ተነስቶ የሰበር አቤቱታ መቅረቡ ያላግባብ በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የተጠሪን የመልስ ይዘት

በመንቀፍ የሰበር አቤቱታውን ደግሞ በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ ወደ እጃቸው የገባውን የአመልካች ገንዘብ ማጉደላቸው ተረጋግጦ እያለ ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በአመልካች በኩል አሣማኝ ማስረጃ አልቀረበም ተብሎ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የቲኬት ሽያጭ ሰራተኛ ሆነው ሲሰሩ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተባቸው ስለመሆኑ ያመኑ መሆኑ ከመረጋገጡም በላይ በአመልካች በኩል የቀረቡት የሒሣብ ባለሙያም በኦዲት ሪፖርቱ የተገኘውን ውጤት በተመለከተ በሰጡት አስተያየት ገንዘቡ መጉደሉን ያስረዱ ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤትም የተገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ፍሬ ነገር ተረጋግጦ እያለ አሣማኝ ማስረጃ አልቀረበም የተባለው ተጠሪ ገንዘቡን ለግል ጥቅማቸው ያዋሉ ስለመሆኑ በማስረዳት ረገድ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ የስር ፍ/ቤት ድምዳሜ በሕጉ ላይ ያልተመለከተውን መስፈርት መሰረት ያደረገ ነው ከሚባል በስተቀር ሕጋዊ መሰረቱ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1(ተ) ስር በተመለከተው አኳኋን የአመልካች ድርጅት አለ በማለት የሚከራከረውንና በተጠሪም ያልተካደውን የህብረት ስምምነት አባሪ 1(ሀ)(3)"ን" ያላገናዘበ ነው በዚህ ድንጋጌ መሰረት የድርጅቱን ወይም በድርጅቱ ኃላፊነት የሚገኝ ንብረት ጥሬ ገንዘብ ወይም በድርጅቱ የስራ ግንኙነት ምክንያት ሰራተኛ እጅ ሊገቡ የሚችሉ የደንበኞችን የሰራተኞችን ንብረት/ገንዘብ መስረቅ፣ መደበቅ፣ ለግል ጥቅም ማዋል ወይ እንዲወሰድ መተግበር ወይም እምነት ማጉደል ወይም የድርጅቱን ንብረት ወይም ቅጥር ግቢ ህገ ወጥ ለሆነ ተግባር መጠቀም ወይም ሌላ ወገን እንዲጠቀምበት ማድረግ ሰራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ማባረር የሚቻል ስለመሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህ ድንጋጌ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ስለማዋሉ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ በመስፈርትነት አያስቀምጥም፡፡ ይልቁንም የገንዘብ ጉድለት/እምነት ማጉደል/ ስለመከሰቱ መረጋገጥ ብቻ ሰራተኛውን ከስራው ያለማስጠንቀቂያ ለማሰናበት የሚያስችል መሆኑን በግልጽ ያስረዳል፡፡ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት ሰራተኛ ገንዘቡን ለግል ጥቅም ያላዋለ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ይኖርበታል እንጂ ይህንኑ የገንዘብ ጉድለት መኖሩን ያስረዳ አሰሪ እንዲያስረዳ አይጠበቅም፡፡ የገንዘብ ጉድለት የተከሰተበት መሆኑ የተረጋገጠበት ተከሣሽ ገንዘቡን ለግል ጥቅሙ ያዋለው ነው ተብሎ ህጋዊ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ የማስረጃ ሕግ መርሆዎች የሚያስገነዝቡት ነጥብ ነውና፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የገንዘቡ ጉድለት መከሰቱን አምነው ገንዘቡን ለድርጅቱ መመለሣቸውን ባላስረዱበት ሁኔታ የአመልካች ድርጅት ማስረጃ አሣማኝነት የለውም መባሉ በጉዳዩ ላይ የቀረበው ማስረጃ የሚመዘንበትን መርህና በግራ ቀኙ መካከል ገዥነት ያለውን የህብረት ስምምነት ይዘት ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች የተጠሪ ከስራ መሰናበት ህገ ወጥ ነው በማለት የደረሱበት ድምዳሜ ህጋዊነት የሌለውን መነሻ ሐሣብ በመያዝ ሆኖ ስለተገኘ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ብለናል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከመጀ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ.39196 ጥቅምት 19 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 60895 ጥር 15 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው ባግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37815

ህዳር 02 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዓለማየሁ ጠ/ሥራ ተቋራጭ - ጠ/ሃይለማርያም ኢቲቻ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ አብዮት በፈቃዱ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ ያለአግባብ ከስራ ስለተሠናበቱ የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለቀረበበት ክስ በሠጠው መልስ አስቸኳይ ስራ ስላለ በሣምንት እረፍት ቀን ስራ እንዲገቡ ተጠይቀው እምቢተኛ ሆነው በአመልካች ላይ ጉዳት በማድረሣቸው ነው ሲል ተከራክሯል ፍ/ቤቱም ተጠሪ በእሁድ ቀን ለምን አልሠሩም ተብለው መባረራቸው ተገቢነት ስለሌለው በግራ ቀኙ የተቆጠሩትን ምስክሮች ማስቀረብ ሣያስፈልግ ስንብቱ ህገወጥ በመሆኑ የተለያየ ክፍያ እንዲከፈላቸው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የይግባኝ ሠሚ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ ቅሬታ ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ለስራ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በእረፍት ጊዜ መስራት በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ የሚጥለው ግዴታ በመሆኑ ውሣኔው ስህተት ነው የሚል ነው፡፡ ሠበር ችሎትም ይህንኑ ነጥብ ለማጣራት ተጠሪ እንዲቀርቡ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በፅሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን ቅሬታ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው አመልካች ተጠሪን ከስራ ማሠናበቱን ሣይክድ ያሠናበታቸው ግን በሣምንት እረፍት ቀን አስቸኳይ ስራ ገጥሞ እንዲሠሩ ተጠይቀው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በድርጅቱ ላይ ጉዳት በማድረሣቸው መሆኑን ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም በሣምንት እረፍት ቀን ሠራተኛው እንዲሠራ በአሠሪው ታዞ ፈቃደኛ አለመሆኑ ከስራ ለማሠናበት በቂ ምክንያት መሆን አለመሆኑን መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 69(1) መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ በሠባት ቀናት ጊዜ ውስጥ ያልተቆራረጠ ከ24 ሠዓት የማያንስ የሣምንት እረፍት ሊያገኝ እንደሚገባ በአስገዳጅነት ተቀምጧል በመሆኑም በመርህ ደረጃ ማንኛውም ሠራተኛ አንድ ሣምንት ጊዜ ውስጥ ከአንድ ቀን ያላነሠ የሣምንት እረፍት የማግኘት መብት አለው፡፡ ከዚህ አጠቃላይ መርህ በተለየ ሁኔታ ግን ሠራተኛው በሣምንት እረፍቱ ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የሚቻል መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 71(1) ሥር ተመልክቷል፡፡ ይኸውም በዚሁ ድንጋጌ ከፊደል ሀ-ሐ የመለከቱት ምክንያቶች ሲያጋጥሙና የድርጅቱን መደበኛ ተግባር የሚያደናቅፍ ሁኔታዎችን ለማስወገድ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ሠራተኛው በማንኛውም የሣምንት የዕረፍት ጊዜው እንዲሠራ ማድረግ ይችላል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች

ሀ/ አደጋ ሲደርስ ወይም የሚደርስ መሆኑ ሲያሠጋ

ለ/ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ሲያጋጥም

ሐ/ በአስቸኳይ የሚሠራ ሥራ ሲያጋጥም ናቸው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች የሚከራከረው አስቸኳይ ስራ አጋጥሞ ተጠሪ በእረፍት ቀናቸው እንዲሠሩ ቢጠየቁ ፈቃደኛ ሣይሆኑ በመቅረት በአሠሪው ላይ ጉዳት በመድረሱ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ነው፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ምንም እንኳን በመርህ ደረጃ አንድ ሠራተኛ በሣምንት ውስጥ ከ24 ሠዓታት ያላነሠ የሣምንት እረፍት የማግኘት መብት ቢኖረውም በአስቸኳይ የሚሠራ ስራ ባጋጠመ ጊዜ ግን በማንኛውም የሣምንት እረፍት ሠራተኛው ሥራ የመሥራት ግዴታ ህጉ ጥሎበታል፡፡ በአዋጁ አንቀፅ 13(7) ሥር ሠራተኛው የአዋጁን ድንጋጌዎች ጨምሮ የህብረት ስምምነቱን፣ የስራ ደንቡንና በህግ መሠረት የሚተላለፍ መመሪያዎችንና ትዕዛዞችን የማክበር ግዴታ አለበት ሠራተኛው እነዚህን ህጎችና ደንቦች የሚጥስ መሆኑ ከተረጋገጠ የስራ ግዴታውንና ኃላፊነቱን ባለመወጣቱ አሠሪው ሊያሠናብተው የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡

በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የአዋጁን ድንጋጌ ባለማክበራቸው የተሠናበቱ መሆኑን አመልካች ተከራክሯል፡፡ አመልካች አስቸኳይ ስራ በማጋጠሙ ተጠሪ በሣምንት እረፍታቸው እንዲሠሩ መጠየቁን እና ተጠሪ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጿል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በአዋጁ አንቀፅ 71(1)(ሐ) ሥር የተመለከተው ሁኔታ መከሠት አለመከሠቱን በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ሲገባው በሣምንት እረፍት እንዲሠሩ መጠየቁ ብቻ ህገ-ወጥ ነው በማለት በግራ ቀኙ የተቀጠሩትን ማስረጃዎች ሣይሠማ የሠጠው ውሣኔ ከፍ ሲል የተመለከቱትን የአዋጁን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ በ37659 በ28/6/2000 የሠጠው ውሣኔና

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 6704 በ8/9/2000 የሠጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡

2/ ተጠሪ በሣምንት እረፍታቸው እንዲሠሩ የታዘዙት በአዋጁ አንቀፅ 71(1)(ሐ)

መሠረት አስቸኳይ የሚሠራ ስራ አጋጥሞ መሆን አለመሆኑን የግራ ቀኙን

ማስረጃ ሠምቶ በማጣራት ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥ ጉዳዩ ለፌ/መ/ደረጃ

ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 343(1) መሠረት ተመልሷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 36377

ኅዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያና የጅቡቲ ምድር ባቡር ድርጅት - ወይንሸት እንድሪስ ቀረበ፡፡

**ተጠሪ፡-** ተሾመ ኩማ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው ክርክሩ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲጀመር ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተውም የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል፡፡ ስለዚህም ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈጸመው ሕገ ወጥ ድርጊት ምክንያት ነው፡፡ ድርጊቱ ከሥራ የሚያሰናብት ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን ፍ/ቤቱም ክርክሩን ከሰማ በኋላ፣ አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው ድርጊቱ ከተፈጸመ ከአንድ ወር በኋላ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት ተጠሪ የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው እንዲመለስ ወስኖአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 5 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች የወሰደው የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በይርጋ የታገደ ነው የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከአመልካች የቀረበውን የስረ-ነገር ክርክር አልሰማም፡፡ ባጭሩ ብይኑን የሰጠው የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው ለውሉ መቋረጥ ምክንያት ነው የተባለው ድርጊት /ጥፋት/ ከተፈጸመ አንድ ወር ካለፈ በኋላ በመሆኑ በይርጋ ታግዶአል በማለት ነው፡፡ በመሆኑም በአሁኑ ደረጃ ሊመረመርና ውሣኔ ለሰጠው የሚገባው ነጥብ በእርግጥ ለክርክሩ አወሳሰን በዋቢነት የተጠቀሰው የአዋጅ ቁ. 337/96 አንቀጽ 27/3/ የሚለይው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንደሚለው ነው ወይ የሚለው ነው፡፡ ከዚህም ጋር በማያያዝ ድርጊቱ በተፈጸመበት እና አመልካች የሥራ ውል የማቋረጥ እርምጃ በወሰደበት መሃከል ያለው ጊዜ ምን ያሕል ነው የሚለው የፍሬ ነገር ሁኔታም መታየት ያለበት ነው፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር በተለይ ደግሞ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪ ጥፋቱን /ድርጊቱን/ ፈጸመ የተባለው መስከረም 24 እና 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ሲሆን፣ አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ የወሰደው ጥቅምት 25 ቀን ነው፡፡ ይህ እንግዲህ በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠ ሲሆን፣ ሕጉ ምን ይላል የሚለውን ደግሞ ቀጥለን እንመልከት፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 27 አሠሪው ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ የሚችልባቸውን

ምክንያቶች /ሁኔታዎች/ በዝርዝር የያዘ ነው፡፡ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /3/"ም" አሠሪው የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ የሚቀርበትን ምክንያት ይዟል፡፡ ይህም የሚሆነው /የስራ ውሉን ለማቋረጥ ያለው መብት በይርጋ ቀሪ የሚሆነው/ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱን ካወቀበት ከ30 /ሠላሣ/ የሥራ ቀናት በኂላ እንደሆነ በሕጉ በግልጽ ተቀምጦአል፡፡ እዚህ ላይ በሚገባ ሊተኮርበት የሚገባውም "የስራ ቀናት" የሚለው ሐረግ ነው፡፡ በሕጉ አባባል አሠሪው መብቱን በይርጋ የሚያጣው /የሚቀርበት/ ሠላሣ ቀናት ወይም አንድ መሆን አለባቸው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ከመስከረም 24 ቀን ጀምሮ እስከ ጥቅምት 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ድረስ ያለው ጊዜ የሚታሰበው ቢያንስ እሁድን ጨምሮ ነው፡፡ እሁድ የስራ ቀን አይደለም ብለን ብንወስድ አራት እሁዶች እንዳሉ እንገነዘባለን፡፡ በዚህ ስሌት መሠረትም አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃውን የወሰደው ተጠሪ ፈጸመ የተባለው ድርጊት /ጥፋት/ መከሰቱን ባወቀ በ26ኛው የስራ ቀን ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እንዳለው የአመልካች መብት በይርጋ የታገደ ወይም ቀሪ የሆነ አይደለም፡፡ ተጠቃሎ ቢታይ በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞአል፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25115 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57680 ጥር 21 ቀን 2000 በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. አመልካች የስራ ውል የማቋረጥ መብቱ በይርጋ አልታገደበትም ብለናል፡፡ ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር በዚያው መዝገብ እንዲቀጥል በማድረግ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ወይስ ከሕግ ውጪ ነው በሚለው ጭብጥ ላይ ከግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር ከሰማ በኂላ የመሰለውን ውሣኔ ይስጥ በማለት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341 መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37048

ህዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብድልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሚድሮክ ኮንስትራክሽን ኢትዮጵያ ኃ/የተ/የግ/ማ -ነ/ፈጅ መ/ኩ መለሰ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሳህሉ ምትኩ - አልቀረቡም ከተባለ በኋላ እንዳልካቸው ይላቅ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ስንብት ክፍያ የሚከፈልበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡

በአሁኑ ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው የለቀቁ ቢሆንም ከአምስት አመት በላይ የሰሩ በመሆኑ የስራ ስንብት እንዲፈቀድላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በሰጠው መልስ ተጠሪ ከአምስት አመት በላይ የሰሩ ቢሆንም የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ አይገባቸውም በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ አያገኝም በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጓል፡፡ በዚህ ላይ ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ በጡረታ ህግ የተመለከተውን መደበኛ የጡረታ እድሜ ላይ ደርሶ ከስራ እስካልተገለለ ድረስ ክፍያ አይከለክልም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሮ ለተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ እንዲሰጣቸው ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስለወጥ ነው፡፡

ይህ ችሎት የአመልካችን አቤቱታ መርምሮ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆን አለመሆኑን ለመመርመር አቤቱታውን ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ ስህተት ተፈጽሞበታል ከተባለው ውሳኔና አግባብነት ካለው ህግ አኳያ መርምሯል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የስራ ስንብት ክፍያ መብትን የሚመለከት ነው፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 ስር የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፈል የሚገባውን ሁኔታዎች ዘርዝሮ አስቀምጧል በዚሁ አንቀጽ ከፊደል "ሀ" እስከ "ረ" ድረስ ተዘርዝረው በተቀመጡት ሁኔታዎች መሰረት የሰራተኛው ጥፋት ባልሆነ ምክንያት አሰሪው የስራ ውሉን ሲያቋርጥ ወይም በአሰሪው ጥፋት ወይም በሰራተኛው የጤና ሁኔታ ሰራተኛው በፈቃዱ ስራውን ሲለቅ የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ያለው መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ /ማሻሻያ/ አዋጅ ቁጥር 494/98 በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 39(1) ስር አዲስ ድንጋጌዎችን ጨምሯል፡፡ በዚህም መሰረት

ሰ. የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም ጡረታ መብት የሌለው ሲሆንና በጡረታ ህግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ከስራ ሲገለል፣

ሸ. ቢያንስ አምስት ዓመት በአሰሪው ዘንድ የስራ አገልግሎት ኖሮት በህመም ወይም በሞት የስራ ውሉ ሲቋረጥ ወይም የስራው ላይ የሚያስቀይ ከስልጠና ጋር የተያያዘ ለአሰሪው የውል ግዴታ ሳይኖርበት ስራውን በገዛ ፈቃዱ ሲለቅ

ቀ. በኤች አይ ቪ ኤድስ ህመም ምክንያት በራሱ ጥያቄ የስራ ውሉ ሲቋረጥ

የስራ ስንብት ክፍያ ማግኘት የሚችል መሆኑን ተቀምጧል፡፡

ይህ የተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/1998 አንቀጽ 2 ቀደም ሲል በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 39 (1) ስር ያልተካተቱ አዲስ ሁኔታዎች ተጨምረዋል ይኸውም አንድ ሰራተኛ በገዛ ፈቃዱ ስራውን ቢለቅ እንኳን የተወሰኑ ሁኔታዎች እስከተሟሉ ድረስ የስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ተሰጥቶታል፡፡ እነዚህም ሁኔታዎች ከፊደል "ሰ" እስከ "ቀ" የተመለከቱት ናቸው ፡፡ በተለይ ከተያዘው ጉዳይ ጋር አግባብነት ያላቸው በፊደል "ሰ" እና "ሸ" የተመለከቱት ናቸው፡፡ በፊደል "ሸ" እንደተመለከተው ቢያንስ አምስት ዓመት ከሰራና በህመም ወይም በሞት ስራ ውሉ ከተቋረጠ ወይም ከስልጠና ጋር በተያያዘ ስራው ላይ የሚያስቀይ ለአሰሪው የውል ግዴታ ከሌለበት የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት ይኖረዋል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ በተናጠል ሳይሆን በፊደል "ሸ' ስር ከተመለከተው ጋር ተገናዝቦ ሊታይ ይገባዋል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰራተኛ ከ5 ዓመት በላይ የሰራ ቢሆንም እንኳን የስንብት ክፍያ ማግኘት የሚችለው የፕሮቪደንት ወይም የጡረታ መብት ከሌለውና የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ከስራ ከተገለለ ነው፡፡

የስር ፍ/ቤትም እነዚህ ሁለት ንዑሳን ቁጥሮች በአንድነት ተገንዝበው መተርጎም ያለባቸው መሆኑን ቢቀበልም የስንብት ክፍያ የሚከለከለው የፕሮቪደንት ፈንድ መብት ኖሮት የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ከስራ ከተሰናበተ ወይም የጡረታ መብት ኖሮት የጡረታ እድሜው ደርሶ ከስራ ከተሰናበተ መሆኑን አትቷል፡፡ በሌላ አነጋገር የስንብት ክፍያ በመከልከል የፕሮቪደንት ፈንድ መብት መኖርና የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ መገለል በአንድነት ተሟልተው ሲገኙ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም የጡረታው ዕድሜ ሳይደርስ በገዛ ፈቃዱ ከስራ የለቀቀ ሰራተኛ የፕሮቪደንት ፈንድ መብት ያለው ቢሆንም ዕድሜው ደርሶ በጡረታ የተገለለ ባለመሆኑ ምክንያት የፕሮቪደንት ፈንድ የማግኘት መብት ያለው ነው በማለት ለድንጋጌው ትርጉም ሰጥቶታል፡፡

ይህ ችሎትም እነዚህ ሁለት ንዑሳን ቁጥሮች ግልፅ ባለመሆናቸው ትርጉም የሚያስፈልጋቸው መሆኑን አምኗል፡፡ ድንጋጌዎች ግልፅ ባልሆኑ ግዜም በመጀመሪያ ሊተረጎሙ የሚገባው የህግ አውጭውን ሐሳብ በመፈለግ መሆኑ የሕግ አተረጓጎም መርህ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም የእነዚህ ድንጋጌዎች አላማ ማወቁ ተገቢ ይሆናል፡፡

የስራ ስንብት ክፍያ ዋነኛው አላማ አንድ ሠራተኛ ከስራ ሲሠናበት ችግር ላይ እንዳይወድቅ ራሱን እንዲያቋቁም ለመርዳት ነው፡፡ እንዲሁም የኘሮቪደንትና የጡረታ አላማም ቢሆን አንድ ሠራተኛ ዕድሜው ደርሶ በጡረታ ቢገለል የሚጦርበት የማህበራዊ ዋስትና ስርዓት ነው፡፡ በእርግጥ ኘሮቪደንት ፈንድና ጡረታ ተመሣሣይ አላማ ያላቸው ቢሆንም የጡረታ ክፍያ የሚጀምረው አንድ ሠው የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ሲሠናበት ሲሆን አከፋፈሉም በአንዴ ሣይሆን በየወሩ የሚከፈል ነው ፕሮቪደንት ፈንድ ግን ሰራተኛው ከስራ ሲወጣ (የጡረታ ዕድሜው ደርሶ ሊሆን ይችላል ወይም ሳይደርስ) በአንድ ግዜ የሚከፈል ነው፡፡ በመሆኑም በአከፋፈል በኩል በሁለቱ መሃከል ልዩነት መኖሩ ሊዘነጋ አይገባም፡፡ በአከፋፈል ያለው ልዩነት እንዳለ ሆኖ ግን ሁለቱም ክፍያዎች ሰራተኛው ከስራ ሲሰናበት ችግር እንዳይገጥመው የሚከፈሉ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ አላማን የሚጋሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አንዱ ሰራተኛ ከስራ በሚወጣበት ጊዜ የፕሮቪደንት ፈንድ ወይም ጡረታ የሚከፈለው ከሆነ በድጋሚ የስራ ስንብት ክፍያ እንዳይከፈለውና በሁለት መንገድ ተጠቃሚ እንዳይሆን ታስበው የወጡ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል አንድ ሰራተኛ ለ5 እና 6 ዓመታት ሰርቶ የጡረታ ዕድሜው ሳይደርስ በራሱ ፈቃድ ከስራ በመልቀቁ ብቻ ከፕሮቪደንት ፈንድ በተጨማሪ ስንብት ክፍያ እንዲያገኝና ሌላው ደግሞ እስከ ጡረታ ዕድሜው ድረስ በመስራቱ ፕሮቪደንት ፈንድ ካለው ስንብት ክፍያ እንዲከለከል ማድረጉ በሰራተኞች መሃከል ልዩነት የሚፈጥርና ፍትሐዊ ባለመሆኑ ህጉ ይህን ልዩነት የመፍጠር አላማ ይዞ የወጣ ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

በመሆኑም አንድ ሰራተኛ አምስት አመትና ከዚያ በላይ የሰራ ከሆነና በራሱ ፈቃድ ስራ ከለቀቀ የስራ ስንብት ክፍያ ለማግኘት የሚችለው ስራ በለቀቀበት ሰዓት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ወይም የጡረታ መብት ተጠቃሚ ካልሆነ ብቻ ነው፡፡

ስራውን በለቀቀበት ሰዓት ፕሮቪደንት ፈንድ የሚከፈለው ወይም በጡረታ መብቱን መገልገል የሚጀምር ከሆነ ግን 5 አመትና ከዛ በላይ መስራቱ ብቻውን የስንብት ክፍያ መብት አያስገኝለትም፡፡ ስለሆነም ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የጡረታ እድሜው ደርሶ በጡረታ ከስራ እስካልተገለለ ድረስ ፕሮቪደንት ፈንድ ማግኘት ይችላል በማለት የደረሰበትን መደምደሚያ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ይህንኑ የህጉን ድንጋጌ በተመለከተ በመ/ቁ 35197 የተሰጠውን የህጉን ትንታኔም መመልከት ይቻላል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 59262 በየካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል ፣
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 26613 በሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሳኔ ፀንቷል ፣
3. ተጠሪ የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ተጠቃሚ በመሆናቸው የስራ ስንብት ክፍያ ሊያገኙ አይገባም ብለናል ፣
4. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37256

ኅዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዲስ አበባ የምግብ አዳራሽ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ኢሣያስ ኃይሉ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ የውብዳር ጥላሁን - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ድርጅት ውስጥ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በወር ብር 536.90 (ሦስት መቶ ሰላሣ ስድስት ብር ከዘጠና ሣንቲም) እየተከፈላቸው በገንዘብ ያዥነት እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ በዓቃቤ ሕግ በኩል ክስ በመመስረቱ የስራ ውላቸው ተቋርጦ መቆየቱንና በኋላም ይኸው ክስ በመዘጋቱ ምክንያት አመልካች ከታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. ጀምሮ ወደ ስራ የመለሣቸው ቢሆንም የተቋረጠውን ደመወዝ ያልከፈላቸው መሆኑንና ወደ ቀድሞው ስራ ያልመለሣቸው መሆኑን በመዘርዘር ከሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ያለውን ደመወዝ ወደ ሥራ እስከተመለሱበት ቀን ያለውን አስቦ እንዲከፍላቸውና ወደ ቀድሞው የገንዘብ ያዥነት ሥራቸው ከደመወዝ ጭማሪና ከኪሣራ ጋር እንዲመልሣቸው ይወስንላቸው ዘንድ በአመልካች ላይ ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም. በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ ጉዳዩ በመደበኛ ፍ/ቤት ሊታይ የማይችልበትን ምክንያት በመጥቀስ በመጀሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ከመከራከሩም በተጨማሪ በፍሬ ነገር ረገድም ተጠሪ ከስራ የታገዱበት ገንዘብ አጉድለው በመገኘታቸውና የተወሰነ ገንዘብ መልሰው ቀሪውን ገንዘብ ለመመለስ ፈቃደኛ ሆነው አለመገኘታቸውን፣ ወደ ሥራ የተመለሱትም ካላቸው የቤተሰብ ኃላፊነት ታይቶ መሆኑን ወደ ቀድሞው የሥራ መደብ ለመመለስ ያልቻለው ከተጠሪ ጥፋት አንፃር መሆኑንና ባልነበሩበት ጊዜ የደመወዝና የጥቅማጥቅም ጥያቄ ማቅረብ የማይችሉ መሆናቸውን በነጥብነት በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ከሠማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ በአመልካች በኩል የቀረበውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ውድቅ ከአደረገው በኋላ የስራ ውል የሚሻሻልበትን የሕግ ምክንያት በመዘርዘርና አመልካች የስራ መደቡን ሲቀይር የስራ ውል የማሻሻል ውጤት የሚኖረው መሆኑን በመግለጽ የአመልካችን እርምጃ ሕገ ወጥ ነው በማለት ተጠሪን የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ቀድሞ የስራ መደብ እንዲመልሳቸው ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የስር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚልባቸውን ምክንያቶች ሚያዝያ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ጉዳዩ መታየት የነበረበት በአስማሚ መሆኑን፣ ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ማጉደላቸው ተረጋግጦ እያለ ወደ ቀድሞ ስራቸው ይመለስ መባሉ ስህተት መሆኑን፣ ላልሠሩበትና ታግደው ለቆዩበት ጊዜ የአራት ወር ደመወዝ እንዲከፈል መወሰኑ አግባብነት የሌለው መሆኑና የአመልካች ምስክሮች አለመስማታቸውን ተገቢነት ያለው አለመሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ

ይገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 27 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሐምሌ 03 ቀን 2000 በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሱን አቅርቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጭብጥ ተጠሪ የአራት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለሱ ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ ከ1983 ዓ.ም. ጀምሮ በአመልካች ድርጅት በገንዘብ ያዣነት የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሠሩ መቆየታቸው በስራው አጋጣሚ ወደ እጃቸው ከገባው የአመልካች ገንዘብ ውስጥም ብር 4219.00 /አራት ሺህ ሁለት መቶ አስራ ዘጠኝ ብር/ አጉድለው ብር 1950.00 /አንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ብር/ መልሰው ቀሪውን ለመመለስ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ከስራቸው ታግደው መቆታቸውና በዚህም ወቅት በዓቃቤ ሕግ በኩል ክስ ተመስርቶባቸው የነበረ ቢሆንም ክሱ ተዘግቶ በነፃ የተሠናበቱ መሆኑ የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከዚህም የምንገነዘበው ተጠሪ ገንዘብ ማጉደላቸውን ሣይክዱ በዓቃቤ ሕግ በኩል መዝገቡ ተዘግቶ በነፃ ተሠናብቼአለሁ በማለት ብቻ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ከሆነ ምላሽ የሚያስፈልገው ጥያቄ ተጠሪ በዓቃቤ ሕግ በኩል በተመሠረተው የወንጀል ክስ ነፃ ወጥቻለሁና ወደቀድሞ ሥራ ልመለስ ይገባል ሲሉ ያቀረቡት ጉዳይ በሕግ በኩል ድጋፍ አለውን? የሚል ነው፡፡

በመሠረቱ የወንጀል ክስና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት አድርጎ የሚቀርብ ክስ የተለያየ ይዘትና ዓላማ ያላቸው ከመሆኑም በላይ በማስረጃ አመዛዘን ረገድም የተለያዩ መርሆዎችን መሠረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ በሌላ አገላለጽ የወንጀል ክስ ለጠቅላላው ማኀበረሰብ ጥቅም ሲባል የሚወሰድ መንግሥታዊና ማኀበረሰባዊ እርምጃ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርግ ክስ ግን እንደ ወንጀሉ ስፋት ያለው ይዘት የውስጥ ድርጅት እርምጃ ነው፡፡ የወንጀል ክስ እርምጃ ሊያሣካ የሚያልመው ዓላማ በማኀበረሰቡ ሠላምና ደህንነት አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሣድሩ ባሕርያትን ማረምና ማደስ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርጉ ክሶች እርምጃቸው ኢንዱስትሪያላዊ ሠላምን ማስፈንና የሥራ ዋስትናን ማስከበር መሆኑ ይታመናል፡፡ በመሆኑም ሁለቱም ክሶች የተለያየ ይዘትና ዓላማ ያላቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የወንጀል ክስ የማስረጃ ምዘና መርህ ከምክንያታዊ ጥርጣሬ የፀዳ /Beyond reasonable doubt/ የሚል ሲሆን በዚህ የማስረጃ አመዛዘን መርህ መሠረት በወንጀል ጥፋተኛ ለማሰኘት ጠንካራና የማያሻማ ማስረጃ የሚፈለግ ሲሆን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት የሚያደርግ ክስ በባሕሪይው ከዲሲፕሊን እርምጃ ጋር እጅጉን የተቆራኘ በመሆኑ እንደማንኛውም የዲሲፕሊን ክስ ተፈፃሚነት የሚኖረው የማስረጃ ምዘና መርህ ከወንጀል ክስ የማስረጃ ምዘና ላላ ያለ ነው፡፡ በመሆኑም በወንጀል ተከሶ ነፃ የሚወጣ ሠራተኛ በዲፕሊን ቢከሠስ አጥፊ ሆኖ የመገኘት ዕድሉ ሠፊ ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት የወንጀል ክስ ነፃ በማውጣት ብቻ አንድ ሠራተኛ ወደ ቀድሞ ሥራ ልመለስ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ጥያቄ የሕግ ድጋፍ አይኖረውም፡፡ ስለሆነም የሠራተኛው ጥያቄ ሊስተናገድ የሚገባው ላላ ያለ የማስረጃ ምዘና መሠረት ተደርጎ ለአድራጎቱ ተጠያቂ ሆኖ መገኘት አለመገኘቱን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እጃችን ወደአለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ የአመልካችን ገንዘብ ማጉደላቸውን አምነው ተመላሽ ማድረጋቸውን በመግለጽ መከራከራቸውን የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ አመልካች ተጠሪን ወደቀድሞው ሥራ ባይመልሣቸውም በሌላ የሥራ መደብ በመመደብ እንዲሠሩ ፈቅዷል፡፡ የበታች ፍ/ቤቶች ይህንኑ የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሱት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 15 ሥር የተመለከቱትን የሥራ ውል ማሻሻያ ምክንያቶችን መሠረት በማድረግ እና በእነዚህ ምክንያቶች የተፈፀመ ስለመሆኑ አላስረዳም በሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ አመልካች የተጠሪ የስራ መደብ ለውጥ ያደረገው ተጠሪ የገንዘብ ጉድለት ስለአስከተሉ መሆኑ ሲታይ እርምጃው ይህንን አጠቃላይ መንፈስ የሚጋጭ ነው ሊባል የሚገባው አይደለም ለሠራተኛ አግባብነት ያለውን የሥራ መደብ በመስጠት የማሠራት ኃላፊነትም ከአሠሪው የአስተዳደር ስራ ነፃነት /managerial prerogative power/ ጋር ተያያዥነት ያለው ነው፡፡ አሠሪው በንብረቱ ላይ ጉዳት ያደረሰ ሠራተኛን ከስራው ያለማስጠንቀቂያ ለማባረር የሚችል ስለመሆኑም የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1ሸ) ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ተጠሪ ከወንጀሉ ክስ ነፃ ወጥቻለሁ ከማለት ውጪ የገንዘብ ጉድለት አልተከሠተም በማለት አልተከራከሩም፡፡ በመሆኑም የገንዘብ ጉድለቱ መከሰቱ አከራካሪ አይደለም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪ ወደቀድሞ የስራ ገበታቸው የሚመለሱበት ሕጋዊ ምክንያት አይኖርም፡፡ አዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/(ሐ),(መ) እና (ሸ)

ድንጋጌዎች መሠረት አሰሪው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ የሚያቋርጥበትን ሁኔታ ያስቀመጠበት ዓላማ ሲታይም ሠራተኛው ስራውን በታማኝነት እንዲያከናውን ለማድረግ መሆኑ ይታመናል፡፡ አንድ ሠራተኛ ታማኝነት የሌለው መሆኑ ከታወቀ በኂላ ደግሞ አሠሪው ወደ ቀድሞ ሥራ እንዲመልሰው ማድረግ ሕጉን ለማሣካት ያለውን ግብ የሚፃረርም ጭምር ነው፡፡

በአጠቃላይ የሥር ፍ/ቤት የአመልካች እምርጃ ሕገወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደሰረሰው በግራ ቀኙ የቀረበውን ክርክር ባላገናዘበና የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 15"ን" ያለቦታው በመጥቀስ ከመሆኑም በተጨማሪ የሕጉንም አጠቃላይ መንፈስ መሠረት ያላደረገ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23401 የካቲት 21 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 64770 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ወደ ገንዘብ ያዥነት ሥራ ሊመለሱ አይገባም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 37402

ህዳር 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**:- የንኮማድ ኃ.የተ.የግል ማህበር - አልቀረበም

**ተጠሪ**:- አቶ ቡሽራ በቀለ - አልቀረበም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዮ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ በተከሣሽ ድርጅት ውስጥ በሎደር ኦፐሬተርነት ሙያ ከሚያዝያ 05 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ሲያገለግሉ መቆየታቸውንና በወቅቱም ይከፈላቸው የነበረው ወርሃዊ ደመወዝ ብር 1800.00(አንድ ሺህ ስምንት መቶ) መሆኑን ዘርዝረው ከጥር 22 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የተቋረጠው የስራ ውል ያላግባብ መቋረጡን ጠቅሰው ውዝፊ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ከስራ እንዲያሰናብት ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ አመልካች ላይ ሠኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው ፍ/ቤቱም የአሁኑ አመልካች እንዲቀርብ ጥሪ አድርጎ አመልካች መልስ በሚሠጥበት ቀነ ቀጠሮ መልሱን ይዞ ባለመቅረቡ በቂ ምክንያት የሌለው መሆኑን በመጥቀስ ይህንኑ መብቱን ከአለፈ በኋላ ግራ ቀኙን በቃል አከራክሮ አመልካች ተጠሪ ከአምስት ቀን በላይ ከስራ የቀረ ስለመሆኑ አላስረዳም ተጠሪም ማስረጃ ላቀርብ ስል ተከለከልኩ በማለት ክደው ተከራክረዋል የሚል ምክንያት በመያዝ ተጠሪ ከስራ የተሠናበቱት ያላግባብ ነው ሆኖም ወደ ሥራ ቢመለሱ መልካም የሆነ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ስለማይፈጥር የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለው ተጠሪ ከስራ ይሠናበቱ በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚልባቸውን ምክንያቶች ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሠበር አቤቱታ ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ በስር ፍ/ቤት መልሱን በጽሑፍ የማቅረብ መብት ያለፈበትን ምክንያት ያላግባብ መሆኑ ተጠቅሶ በቀረበው የይግባኝ ቅሬታ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ውሣኔ ሣይሠጥበት ማለፉ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ተጠሪ ከስራ ላይ ከአምስት ቀን በላይ መቅረታቸውን በቃል ክርክር ወቅት አምነው እያሉ እና የህክምና ማስረጃ ለማቅረብ ስሄድ የድርጅቱ ዘበኛ ከለከለኝ በማለት ተጠሪ የገለፁት ፍሬ ነገር በተጨባጭ ማስረጃ ተደግፎ ባልቀረበበት ሁኔታ ይህንኑ የማስረዳት ሸክም ወደ አመልካች የማዞር ውሳኔ መሠጠቱ ስህተት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም ለሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሠኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን የሠበር አቤቱታ ቅሬታ ነጥቦችን ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር መልስ ሠጥተዋል፡፡ አመልካች በበኩሉ ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታውን በማጠናከር የመልስ መልሱን ሠጥቷል፡፡

የጉዳዮ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሁፍ ክርክር የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ ከአምስት ቀናት በላይ በተከታታይ ከሥራ መቅረታቸውን ሣይክዱ በሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ የሐኪም ማስረጃውን ለአመልካች ላቀርብ ስል ዘበኛው ከልክሎኛል በማለት ያቀረቡትን ክርክር መሠረት በማድረግ ተጠሪ የተሰናበቱት ያለአግባብ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከሥራ እንዲሰናበቱ የወሰኑት ውሳኔ በአግባቡ መሆኑን ያለመሆኑን ምላሽ የሚያስፈልገው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ በስራ ገበታቸው አለመገኘታቸውን በመግለጽ ያልተገኙበት ምክንያት በህመም ሆኖ ይህንኑ ማስረጃ ለአመልካች በወቅቱ ያላቀረቡ መሆኑንና ማስረጃውን ለማቅረብ ያልቻሉበት ምክንያትም የአመልካች ድርጅት ዘበኛ ወደ ግቢው ሊያስገባቸው ፈቃደኛ ባለመሆኑ ስለመሆኑ በመግለጽ ተጠሪ የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ የበታች ፍ/ቶችም ይህንኑ የተጠሪ ክርክር በቃል ክርክር ወቅት ያረጋገጡት መሆኑን ውሣኔው ያሣያል፡፡ ተጠሪ የሀኪም ማስረጃውን ለአመልካች ያላቀረቡበት ምክንያት በዘብ ጥበቃ ግቢ እንዳይገቡ በተደረገው ድርጊት ነው ይበሉ እንጂ ይህንኑ ፍሬ ጉዳይ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቸው ስለመሆኑ ገልፀው ያልተከራከሩ መሆኑን የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ግልባጭ ይዘት የሚይሣይ ከመሆኑም በላይ ለዚህ ችሎት በሠጡት መልስም በዚህ ረገድ ማስረጃ የነበራቸው መሆኑን በመግለጽ አልተከራከሩም፡፡

እንግዲህ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮች ከላይ የተገለፁት ከሆኑ የአመልካችን ተግባር ህገ ወጥ ሊያሠኙ የሚችሉት ህጋዊ ምክንያቶች ከአዋጁ ጋር አገናዝቦ መመልከትን የግድ ይሏል፡፡

በመሠረቱ ያለበቂ ምክንያት ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ገበታው ያልተገኘን ሠራተኛ አሠሪው ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ማሠናበት መብት ያለው ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ለ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ይህንኑ የአሠሪን ህጋዊ መብት ሠራተኛው ሊቃወመው የሚችለው በቂ ምክንያት ኖሮት ተቀባይነት ሲያጣ ብቻ ነው ከስራ ገበታው መቅረት አከራካሪ ባልሆነበት ሁኔታ በቂ ምክንያት ስለመኖሩ የማስረዳት ሸክም ከስራ ገበታው መቅረቱን ያልካደው ሠራተኛ እንጂ አሠሪ ሊሆን አይችልም እንደሚታወቀው ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ የክሱን ፍሬ ነገር እንዲረጋገጥለት ዳኝነት የሚጠይቅ ወገን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ከሣሽ ክሱን የሚያስረዳ ማስረጃ (Prima facie evidence) የማቅረብ ግዴታ አለበት ይኸው ግዴታ ወደ ሌላው ተከራካሪ ወገን ሊተላለፍ የሚችለው ክሱን ለማስረዳት የቀረበው ማስረጃ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ብቃት ነው፡፡

በእጃችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ቀረሁ የሚሉበትን ምክንያት ለማስረዳት የህክምና ማስረጃ አለኝ ቢሉም ይህኑ ማስረጃ ለአመልካች አላቀረቡም፡፡ ለአመልካች የህክምና ማስረጃውን አለማቅረባቸውን ገልፀው ማስረጃውን ለማቅረብ የተቸገሩበትን ምክንያት በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ ይኸው ፍሬ ነገር በማስረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ ግን አይገልፅም፡፡ የህክምና ማስረጃውን በወቅቱ ይዘው ለአመልካች ያላቀረቡት ምክንያት በአመልካች ዘብ ጥበቃ በተደረገባቸው ክልከላ መሆኑ የማስረዳት ገዴታ ደግሞ የተጠሪ ነው፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ተጠሪ ክደው ተከራክረዋል በሚል ምክንያት ብቻ የማስረዳት ሸክሙን ወደ አመልካች በማዞር ውሣኔ መስጠቱ የማስረጃ አቀራረብ ግዴታ መርህንና የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መንፈስ ባላገናዘበ መልኩ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ተጠሪ ተገቢውን ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ደግሞ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ሊባል ሚችልበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ መቅረታቸውን በግልጽ አምነው ተከራክረው እያለና ለዚህ ከስራ ለቀሩበት ጊዜም በቂ ምክንያት ያላቸው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ባልተወጡበት ሁኔታ የማስረዳት ሸክሙ ወደ አመልካች በማዞር እርምጃው ህገ ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

<u>**ው ሳ ኔ**</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 27785 ህዳር 04 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 60853 መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም የፀና ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሠናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል
4. መዝገቡ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰበር መ/ቁ. 37573

ህዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት - ነ/ፈጅ አለምፀሐይ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ መሐመድ አደን - በሌሉበት

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ሠራተኛው መብቱን የሚጠይቅበትን የጊዜ ገደብ የሚመለከት ነው፡፡

በዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት ተጠሪ ባቀረቡት ክስ አመልካች ያለአግባብ ከስራ ስላሰናበታቸው ወደ ስራ ለመመለስ ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪ በፈፀሙት ጥፋት ከስራ መሠናበታቸው በሕጉ መሠረት መሆኑን ጠቅሶ ተከራክሯል፡፡ የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤትም ስንብቱ ሕገ- ወጥ ነው በማለት ተጠሪ ወደስራቸው እንዲመለሱ አልያም ካሣ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ የይግባኝ ቅሬታ ለዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ክሱ በይርጋ አይታገድም፣ ስንብቱም ሕገወጥ ነው፣ ተጠሪም ወደ ስራ ቢመለሱ መልካም ግንኙነት አይኖርም ተብሎ የሚገመትበት ምክንያት ስለሌለ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ ይመለሱ በማለት የወረዳውን ፍ/ቤት ውሣኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ቅሬታውም ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ሲሆን ክስ የመሠረቱት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም በመሆኑ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ ይቋረጣል የሚል ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች የይርጋውን ጥያቄ ያልተቀበሉት በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል የሠበር አቤቱታ ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ የተደረገ ሲሆን ተጠሪ ቀርበው መልስ እንዲሰጡ መጥሪያ ደርሷቸው ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት ታይቷል፡፡

እኛም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበባቸው ውሣኔዎች እና ከሕጉ አኳያ መርምረናል፡፡

ከመዝገቡ ላይ እንደተመለከትነው ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ሐምሌ 1/1999 ዓ.ም ነው በማለት አመልካች ባቀረበው መከራከሪያ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት ተቃውሞ የለም እንደዚሁም ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ ያቀረቡት ጥቅምት 14/2000 ዓ.ም መሆኑንም ግራ ቀኙ አልተካካዱበትም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከስራ ከተሰናበቱበት ቀን ጀምሮ ወደ ስራ ለመመለስ ክስ እስከመሠረቱበት ጊዜ ድረስ ሲታሰብ ከ3 ወር በላይ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 162/2/ መሠረት ደግሞ ሠራተኛው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ተቋርጦብኛል በማለት ወደ ስራው ለመመለስ የሚያቀርበው ክስ ውሉ በተቋረጠ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ እንደሚቋረጥ ተመልክቷል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ተጠሪ ፈጽመዋል በተባሉት ጥፋት ክስ ተመስርቶባቸው ሲጣራ ቆይቶ ፖሊስ ከወንጀሉ ነፃ መሆናቸውን ያረጋገጠው መስከረም 18/2000 በመሆኑ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ከዚሁ ቀን ነው በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች በአዋጁ አንቀጽ

164 ሥር የተዘረዘሩ ሲሆኑ ፍ/ቤቱ የገለፀው ሁኔታ ይርጋን ያቋርጣሉ ተብለው ከተመለከቱት ሁኔታዎች ስር የሚካተት አይደለም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪ በወንጀል ድርጊት ተጠርጥረው ጉዳዩ በፖሊስ ተጣርቶ ነፃ መሆናቸው እስኪረጋገጥ ድረስ የነበረውን ጊዜ በይርጋ አቆጣጠር ጊዜ ውስጥ አይካተትም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ከዚህም አልፎ አመልካች ባቀረበው የይግባኝ ቅሬታ ላይ ተጠሪ ያቀረቡት መስቀለኛ ይግባኝ እንኳን ሣይኖር ተጠሪውን በሚጠቅም መልኩ የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ማሻሻሉ የዳኝነት አሠራር ስርዓት አለመከተሉን ያመለክታል፡፡ በአጠቃላይ የተጠሪ ወደ ስራ የመመለስ ጥያቄ ከ3 ወር በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ውድቅ ሊደረግ ሲገባ ይህ ታልፎ በዋናው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መሠጠቱ መሠረታዊ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የዱብቲ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0/21/200 በ28/2/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. በአፋር ክልል የዞን አንድ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 0993 በ18/4/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. ተጠሪ ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ክስ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 162/2/ በይርጋ ውድቅ ሆኗል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37575

ኀዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ቃሊቲ ባሌስትራ ማምረቻ - ገ/እግዚአብሔር ተስፋዬ ጠበቃ

**ተጠሪ**፡- ብርሃኑ ልደት ወልዴ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተጀመረ ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በጥበቃ ሙያ እያገለገሉ ቆይተው የሰራተኛ አበል እና ገንዘብ ሰብሳቢ በመሆናቸው በሕገ ወጥ መንገድ እንደተሰናበቱ ገልፀው ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ ልመለስ ወይም ተገቢው ክፍያ እንዲፈፀምልኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለቀረበበት ክስ መልሱን ሲሰጥ ተጠሪ እንደሚለው በጥላቻ ውላቸው አልተቋረጠም የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው፡፡ የሚገባቸውን ክፍያ ወስደው ነው የስራ ውላቸው የተቋረጠው የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቅያ ወስዷል፡፡ በማለት ተከራክረዋል፡፡

የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን የግራ ቀኙን ክርክር ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል በመሆኑም አመልካች ተጠሪ የተሰናበቱት የድርጅቱ ስራ ስለቀዘቀዘ ነው ይበል እንጂ ይህ ለመሆኑ አላስረዱም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስምምነት የአገልግሎትና የ"2" ወር የማስጠንቀቂያ ተከፍሎት ይገልፃል ይሁን እንጂ የተደረገው ስምምነት በአዋጁ ቁጥር 24 መሰረት በጽሁፍ ለመደረጉ አላስረዱም ሕጉ በሥምምነት የስራ ውሉን ማቋረጥ በጽሁፍ መሆን አለበት ይላል በእርግጥ ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ወስዷል፡፡ የተቀረውን መብታቸውን መተዋቸው በሕግ ፊት ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ ተጠሪ ውዝፍ ተከፍሎኝ ወደ ስራ ልመለስ ያለውን ፍ/ቤቱ ተቀብሎታል ምክንያቱም ተጠሪ ውላቸውን በጽሁፍ አላቋረጠም በማለት ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው የ6 ወር ውዝፍ ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሣቸው ሲል ወሰነ፡፡

አመልካችም በዚሁ ውሣኔ ባለመስማማት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የስር ውሣኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት አሻሽሎ ተጠሪ በአዋጁ ቁጥር 43/5/ መሰረት የአንድ አመት ደመወዝ ይከፈላቸው ሲል ወስኗል፡፡

የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2000 ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሰረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረም ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሰረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተደረገው የሥራ ውል በጽሁፍ አልተቋረጠም ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረት ይህን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ እንዳየነው ተጠሪ ከአመልካች ድርጅት ሲሰራ ቆይቶ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ክፍያ በመቀበል ከሄደ በኂላ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ ካልሆነም ክፍያ እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ምንም እንኳ አመልካችም በስምምነት የሚጠበቅብኝን ክፍያ ፈጽሜ አሰናብቸዋለሁ ቢልም የሥራ ውልን በስምምነት ማቋረጥ የሚቻለው በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 25/2/ መሰረት በጽሁፍ የተደረገ ሥምምነት ሲኖር ነው በተያያዘነው ጉዳይ ግን ይህ አልተፈፀመም ስለሆነም ስንብቱ ሕጋዊ ነው ለማለት አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ ከመዝገቡና ከቀረበው አቤቱታ ለመረዳት እንደቻልነው ተጠሪ የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ ስለመቀበሉ የሥር መዝገብ ይገልፃል፡፡ ይህ ሆኖ እያለ

በሥር ፍ/ቤት ስንብቱን ተከትሎ ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው ተብሎ ተወስኗል፡፡

ተጠሪ ወደ ሥራው ይመለስ የሚለውን ነጥብ ስናየው ፍ/ቤት በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 43/3/ መሰረት ሰራተኛው ወደ ቀድሞ ስራቸው ቢመለሱ በስራቸው ግንኙነት ላይ ሊከሰት የሚችለውን ችግር በማጤን ሰራተኛው ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማድረግ እንደሚችሉ ሕግ ይደነግጋል ይህ ሆኖ ሳለ ወደ ስራው ተጠሪ ይመለስ መባሉ አግባብ አይደለም፡፡ በተጨማሪም የውዝፍ ደሞዝን አስመልክቶ ተጠሪ ክፍያዎች (የአገልግሎትና የማስጠንቀቂያ) ተከፍሎት እያለ ተጨማሪ ውዝፍ ደሞዝ ይከፈለው መባሉ አግባብ ያለው ሆኖ አላገኘነም ይሁን እንጂ ተጠሪ ካሣ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

ስለዚህ በሥር ፍ/ቤት ተጠሪ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራው ይመለስ መባሉ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 23061 በሐምሌ 20 ቀን 1999 እና በፌ/ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58532 በመጋቢት 22 ቀን 2000 የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሰረት ተሻሽሎአል፡፡
2. ተጠሪ ወደ ስራው ሊመለስም ሆነ ውዝፍ ደሞዝ ሊከፍለው አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ቀደም ሲል የተከፈለው ስለሆነ ያልተከፈለው ካሣ በሕጉ መሰረት ተከፍሎት ይሰናበት ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭ እና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37778

ኀዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አዲስ መለዋወጫ እቃዎች አስመጪና አከፋፋይ አ.ማ - ጠ/ብስራት መኮንን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ካሣሁን ከበደ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በተከሣሽ ድርጅት ከታህሳስ 1 ቀን 1979 ዓ.ም ጀምሮ እስከ የካቲት 15 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ማገልገላቸውን፣በመጨረሻ የነበረው የስራ መደብ ደረጃም ግምጃ ቤት ትራንዚት አምስት መሆኑን ከሕብረት ስምምነቱ ውጪ ዝውውር መፈፀሙንና የስራ ውሉም ያላግባብ መቋረጡን በመዘርዘር ዝውውሩ እንዲሻር ወደ ስራ እንዲመለሱም ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ አመልካች ላይ መጋቢት 17 ቀን 1999 ዓ.ም የተፃፈ ክስ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ስለመሰረቱ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በፍ/ቤቱ ጥሪ መሰረት ቀርቦ በሰጠው የመከላከያ መልስ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ያለበቂ ምክንያት ከስራ ስለቀሩ በአዋጁና በህብረት ስምምነቱ መሰረት መሆኑን፣ ተጠሪ በደረሰባቸው አደጋ በጊዜአዊነት ደመወዝና የውሎ አበል እየተከፈላቸው በሕብረት ስምምነቱ መሰረት ተመድበው ሣሉ በእምቢተኛነት ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ መደባቸው ላይ ባለመገኘታቸው በገዛ ፈቃዳቸው ስራውን የለቀቁና የሄዱ መሆናቸውን በመዘርዘር ስንብቱ ባግባቡ ስለሆነ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከሣሽ ዝውውሩ አላግባብ ነው የሚል ተቃወሞ ሲኖራቸው ክስ መመስረት ያለባቸው ወደ የተዛወሩበት ቦታ ሂደው ስራቸውን እየሰሩ መሆን አለበት እንጂ ስራቸውን አቋርጠው መሆን አልነበረበትም በሚል ምክንያት ከሣሽ ከስራ የተሰናበቱት ባግባቡ ነው በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ሰራተኛው የተፈፀመበትን ዝውውር ሕገ ወጥ ነው የሚል ቅሬታ ካለው የግድ ወደ ተዛወረበት የስራ ቦታ በመሄድ ጥያቄውን ማቅረብ የለበትም፡፡ ዝውውሩም በህብረት ስምምነቱ መሰረት የተፈፀመ አይደለም፡፡ የሚሉትን ምክንያቶችን በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ያሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የህብረት ስምምነቱንና የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔን መሻሩንና ዝውውሩ ትክክል አይደለም የሚባል ቢሆን እንኳ ጉዳዩን የማየት ስልጣን ሣይኖረው ተመልክቶ መወሰኑ ያላግባብ ስለሆነ ውሣኔው ሊሻር ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርበው ሐምሌ 17 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን የሰጡ ሲሆን የአመልካች ነ/ፍጅም በበኩላቸው መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ ወደተዛወሩበት ቦታ ሳይሔዱ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት መቅረታቸውን መሰረት በማድረግ መሆኑንና ተጠሪ በበኩላቸው የሚከራከሩት ወደተዛወሩበት ቦታ ያልሄዱት ዝውውሩ በስራ ላይ ያለውን የህብረት ስምምነት እና አዋጁን ያላገናዘበ በመሆኑ የዝውውር ደብዳቤው ከደረሣቸው ጊዜ ጀምሮ ከስራ ቦታቸው ሣይቀሩ ቅሬታ እያሰሙ ባለበት ሁኔታ በስራህ ላይ አልተገኘህም በሚል ሕጋዊ  ሽፋን የስራ ውል ማቋረጥ ሕገ ወጥ ድርጊት ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡ እንግዲህ አመልካች ተጠሪን ከአዲስ አበባ ወደ ጐንደር አዛውሮ ተጠሪ የዝውውሩ ደብዳቤ ከተሰጣቸው በኋላ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ ሣይጀምሩ አምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ያለፉባቸው፣ ለዚህም በቂ ምክንያት ብለው የሚከራከሩት የዝውውሩን ሕገ ወጥነት በመቃወም ቅሬታ በማሰማት ምላሹን እየተጠባበቁ የነበሩበትን ሁኔታ ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ወደ ተዛወሩበት ቦታ አለመሄዳቸውንና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ላይ አለመገኘታቸውን  በማመን የተከራከሩ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ነው፡፡

በመሰረቱ በቂ ምክንያት ሣይኖረው በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ገበታው ያልተገኘ ሰራተኛን ማስጠንቀቂያ መስጠት ሣያስፈልግ ከስራ እንዲያባርረው ለአሰሪው ሕጉ ፈቃድ የሰጠው መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ ሰራተኛው የአሰሪውን አድራጐት ሊቃወመው የሚችለው ለመቅረቱ በቂ ምክንያት መኖሩን በማስረዳት ነው፡፡ ከስራ ለመቅረት በቂ ምክንያት ሊሰጥ የሚችሉት ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ግን ሕጉ አመልካች ወይም ዝርዝር ሁኔታዎች አላስቀመጠም፡፡ ሆኖም በቂ ምክንያት የሚለው ሐረግ መመዘኛቸው ሰራተኛው ከስራ ቦታው ሊገኝ በማይችልበት ደረጃ ላይ አድረሰውት ነበር ተብሎ ሊታመንበት የሚገባ ስለመሆኑ ከአዋጁ አጠቃላይ አላማና ከተጠቃሹ ድንጋጌ መንፈስ ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡ በመሆኑም ከስራ የቀረ ሰራተኛ በቂ ምክንያት ኑሮት ቀርቷል ለመባል የሚቀርበው ማስረጃ ሰራተኛውን በስራ ቦታ ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል የነበረ መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ሰራተኛው በማይረባ ምክንያት ሁሉ ከስራ ገበታው ባለመገኘት በአሰሪው ምርትና ምርታማነት ላይ የራሱን አሉታዊ ተጽእኖ ማሣደሩ አይቀሬ ነው፡፡

እኛችን ወደ አለው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ያልተገኙበት ምክንያት የአመልካችን ዝውውር በመቃወም ቅሬታ አቅርበው ምላሽ እየተጠባበቁ ስለመሆኑ ከላይ ተገልጿል፡፡ አንድ ሰራተኛ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መዛወር ደግሞ ሰራተኛው ወደ ተዛወረበት ቦታ በመሄድ በስራው ላይ ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል ነው ተብሎ በበቂ ምክንያት መመዘኛ ስር የሚወድቅ አይደለም፡፡ ሰራተኛው በዝውውሩ ቅሬታ ካለውም ወደ ተዛወረበት ቦታ በመሄድና ስራውን በተገቢው መንገድ እያከናወነ ስልጣን ላለው አካል አቅርቦ ተገቢውን መፍትሔ ከመጠየቅ በስተቀር ከስራ ቦታው ሣይገኝ ቅሬታውን በማቅረቡ ብቻ ከስራ ገበታው በበቂ ምክንያት ቀርቷል ሊባል አይገባም፡፡ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የደረሰበት ድምዳሜ ተቀባይነት ከሌለው የመነሻ ሐሣብ የመነጨ ከመሆኑም በላይ በስረ-ነገር ስልጣኑም የሚወድቅ አይደለም፡፡

ሲጠቃለልም ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታቸው አለመገኘታቸው እና ያቀረቡት ምክንያትም በቂ ነው ተብሎ የሚወሰድ አለመሆኑ በአግባቡ ተረጋግጦ እያለ የከፍተኛው ፍ/ቤት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ መሻሩ ተቀባይነት ባለው ምክንያት ሆኖ ስላላገኘነው ውሣኔው የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ለ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው በሚል ምክንያት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58518 ሚያዝያ 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 26458 ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ በማቅረብ ምላሽ እየተጠባበቁ የነበሩ መሆኑ ከስራ ለመቅረት በቂ ምክንያት ነው ተብሎ ሊወሰድ የማይገባ በመሆኑ ተጠሪ ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት ከስራ ገበታቸው ቀርተዋል በማለት አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ማቋረጡ በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
5. መዝገቡ ያለቀለት ስለሆነ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 03171

ኀዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የኢት/ኤሌክትሪክ ኃ/ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ዝግአለ አሰፋ

**ተጠሪ**፡- ወ/ት ትርሲት ደገፉ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የስራ ውል አመሰራረትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ አመልካች ድርጅት የምስ/ሪጅን ጽ/ቤት ለክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ደመወዝ ብር 453.00(አራት መቶ ሃምሳ ሶስት) በድርጅቱ ስኬል መሰረት ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ አውጥቶ ተጠሪ ተወዳድረው ማለፋቸው በጥቅምት 27 ቀን 1999 ዓ.ም ተገልፆላቸዋል፡፡ ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምረው የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸው ከአሻራ ምርመራ በተፃፈ ደብዳቤና በጡረታ ቅጽ ላይ ተገልጿል፡፡ ምድብ ቦታቸው ደደር መሆኑ ተገልፆላቸዋል የመጀመሪያ ስራቸውን ለቀው ለመሄድ ሲዘጋጁ ያለበቂ ምክንያት የስራ ውላቸው መሰረዙ በታሕሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ተገልፆላቸዋል፡፡ ስለዚህ የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለአግባብ በመሆኑ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ፣ ከሕዳር 1 ቀን 1999 - ታህስስ 25 ቀን 1999 ያለው ደመወዛቸው እንዲከፈላቸው፣ የስራ ውላቸው ያለአግባብ ስለተቋረጠ የ6 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ፤በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የፀና የስራ ውል የለም፣በድርጅቱ አሰራር መሰረት የተፈፀመ የቅጥር ውል የለም፣ አሻራ ምርመራ እንዲያደርጉ መላክ የስራ ውል መፈፀም ማለት አይደለም፣በቅጥር ውል ለሙከራ ጊዜ የተቀጠረ ሰራተኛን እንኳን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ማሰናበት ይቻላል፡፡ ከስራ ተሰናበትኩ ይበሉ እንጂ የስንብት ደብዳቤ አላያያዙም፣የቅጥር ውል አለ ቢባል እንኳን ወደ ስራ ለመመለስ ያቀረቡት ጥያቄ በ3 ወር ጊዜ በይርጋ ይታገዳል፣የውል ድርድር አለ ቢባል እንኳን በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1693/1/ እና /2/ መሰረት ድርድሩ እንዳልተደረገ ይቆጠራል፣ከክሣቸው ጋር ያቀረቧቸው ማስረጃዎች የአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት መኖሩን አያስረዱም፣ ስለሆነም ክስ የማቅረብ መብት የላቸውም፣ላልተሰራ ስራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣ የመብት ጥያቄ ማንሣት የሚችለው 45 ቀናት ያገለገለ ሰራተኛ ነው፣የአሻራ ምርመራ ደብዳቤው የአሻራ ውጤት ለመውሰድ በመጠባበቅ ላይ ያለ መሆኑን ስለሆነ ውጤቱ ሣይደረስ ቅጥር ሊፈጸም አይችልም በማለት የቀረበበትን ክስ አስተባብሎ ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙ ክርክር ከመረመረ በኋላ በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የቅጥር ውል አለ፣ተጠሪ የ6 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው ይመለሱ፣ እንዲሁም ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው ደመወዝ ይከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የስራ ውል የለም፣ላልተሰራ ስራ ደመወዝ ሊከፈል አይገባም፣የሚሉ ናቸው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪ የስራ ውል

የተቋረጠው ያለአግባብ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ተጠሪም ቀርበው ተከራክረዋል፡፡

ከላይ የተመለከተው የግራ ቀኙ ክርክርና የፍ/ቤቶቹ ውሣኔ ሲሆን ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታውን አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በዚህም መዝገብ ውሣኔ ማግኘት የሚያሻቸው ነጥቦች 1. በአመልካችና በተጠሪ መሃከል የስራ ውል አለ? የለም? 2. አለ ከተባለ ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ ሊመለሱ ይገባል? አይገባም የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ፣ተጠሪ በክሣቸው በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የስራ ውል አለ በማለት ተከራክረዋል፡፡ ለዚህም መሰረት ያደረጉት የአመልካች ድርጅት ምስ/ሪጅን ጽ/ቤት ለክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ደመወዝ ብር 453.00 ማስታወቂያ ወጥቶ ተወዳድረው ማለፋቸውን፣ከዚህ በኋላ አመልካች መስሪያ ቤት ከኀዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የመ/ቤቱ ሰራተኛ መሆናቸውን ገልፆ የአሻራ ምርመራ ደብዳቤ መፃፉንና በጡረታ ቅጽ ላይ ማረጋገጡን፣ምድብ ቦታቸውም ደደር መሆኑን ማሣወቁን ነው፡፡ አመልካች በበኩሉ ከፍ ሲል በተጠሪ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች ክዶ አልተከራከረም፡፡ ነገር ግን ፈተናውን ማለፋቸውም ሆነ ለአሻራ ምርመራ የተፃፈው ደብዳቤ የስራ ውል አይመሰርትም፡፡ በመ/ቤቱ አሰራር መሰረት የተፈፀመ የስራ ውል ስለሌለ ከተጠሪ ጋር ውል አለ ሊባል አይችልም በማለት ተከራክሯል፡፡ በመሆኑም የስራ ውል አመስራረትን በተመለከተ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 የሚደነግገውን መመልከት ተገቢ ይሆናል፡፡ በዚህ አዋጅ በቅጥር ላይ የተመሰረተ የስራ ግንኙነትን በሚመለከተው ክፍል ስር የሚገኘው ምእራፍ አንድ ዘርፍ አንድ የስራ ውል በምን መልኩ መመስረት እንደሚገባው ይናገራል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 4/1/

> “ ማንኛውም ሰው ደመወዝ እየተከፈለው፤በአሰሪው መሪነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለተወሰነ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ ወይም የተወሰነ ስራ ለአሰሪው ለመስራት ቢስማማ በሁለቱ ማሐከል የስራ ውል ይመሰረታል፡፡”

በማለት ያስቀምጠዋል፡፡ በመሆኑም የስራ ውል ማለት አንድ ሰራተኛ በአሰሪው መሪነት የአሰሪውን ስራ፤ በውሉ ላይ ለተመለከተው የስራ ጊዜ፤ለመስራት የሚያደርገው ስምምነት መሆኑ በዚህ አንቀጽ ትርጓሜ ተሰጥቶበታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የስራ ውሉ እንዴት መደረግ እንዳለበትና ሊይዛቸው ስለሚገባው ነገሮች በንኡስ ቁጥር 2 እና 3 ሥር ተመልክተዋል፡፡ በዚህም መሰረት የስራ ውል ተዋዋይ ወገኖች በውሉ መሰረት የሚኖራቸው መብትና ግዴታ በማያጠራጥር አኳኋን በሚያውቁበት ሁኔታ በግልጽ መደረግ ያለበት ሲሆን ውሉም የስራውን አይነትና ቦታ፣ ለስራው የሚከፈለውን ደመወዝ መጠን፣ የስሌቱን ዘዴ፣ የአከፋፈሉን ሁኔታና ጊዜ እና ውሉ ፀንቶ የሚቆይበትን ጊዜ መያዝ እንደሚኖርበት ተገልፆል፡፡ የስራ ውሉ በዚህ መልክ መደረግ የሚኖርበት ቢሆንም ግን በሕግ በተለየ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር የተለየ ፎርም የሌለው መሆኑ፣ በአንቀጽ አምስት ስር ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም የስራ ውል፤ሕግ ካላስገደደ በቀር፤በማንኛውም አይነት ሊቋቋም እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከነዚህ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎች አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር አመልካች ለክለርክ ታይፒስት ጸሐፊ ቦታ በወር ብር 453.00 ደመወዝ ለመቅጠር ማስታወቂያ በማውጣቱ ተጠሪ በማስታወቂያው መሰረት ለመቀጠር ቀርበው ፈተናውን ተፈትነው አልፈዋል፡፡ ፈተናውን ማለፍ ብቻ ሣይሆን ከኀዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ የድርጅቱ ሰራተኛ መሆናቸው ተገልፆ የአሻራ ምርመራ እንዲደርግላቸው ደብዳቤ ተጽፎ እና የጡረታ ቅጽ ተሞልቶ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላልፏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ምድብ የሥራ ቦታቸው ደደር መሆኑም ተገልፆላቸዋል፡፡ የስራ ውል የተለየ ፎርም የሌለው በመሆኑ አመልካች የክለርክ ታይፒስት ፀሐፊ ለመቅጠር የውል ድርድር ማቅረቡ ተጠሪ ደግሞ ድርድሩን ተቀብለው ፈተና ተፈትነው ማለፋቸው በቀጣይነትም አመልካች ተጠሪ የድርጅቱ ሰራተኛ ሆነው መቀጠራችን በመግለጽ ለተለያዩ መ/ቤቶች በላከው ደብዳቤና የጡረታ ቅጽ ማረጋገጡ በሁለቱ በሐከል የውል አቀራረብና አቀባበል መኖሩን ያመለክታል፡፡ የተጠሪዋ የምድብ ስራቸው ደደር መሆኑ፣የስራው አይነት የክለርክ ታይፒስት ጸሐፊ መሆኑ የተጠሪዋ ደመወዝ በወር ብር 453.00 እና በድርጅቱ ስኬል መቀጠራቸው ሁሉ ግራ ቀኙ አውቀውት የተስማሙበት በመሆኑ በአዋጁ የስራ ውል አመሰራረት የሚጠይቀውን የሚያሟላ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ጋር የስራ ውል የለንም በማለት ያቀረበው መከራከሪያ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ አመልካቹ ተጠሪ በመ/ቤቱ የአሰራር ደንብ መሰረት አልተቀጠርኩም በማለት የሚከራከር ሲሆን ይህ ደንብ መኖሩንና በዛ ደንብ መሰረት አለመቀጠራቸውን

ለማስረዳት አለመቻሉን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የቅጥር ውል አለ በማለት የስር ፍርድ ቤት የደረሱበት መደምደሚያ የህግ ስህተት አለው ለማለት አልተቻለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ የሥራ ውል አለ ከተባለ ውሉ የተቋረጠ ነው? አይደለም? አይደለም የሚባል ከሆነ ውጤቱ ምንድነው የሚለው ነው፡፡

አመልካች በስር ፍ/ቤት በነበረው ክርክር ከተጠሪ ጋር የስራ ውል አልመሰረትንም ከማለት በቀር የስራ ውሉ የተቋረጠበትን ምክንያት አልገለፀም፡፡ በእርግጥ በሰበር ችሎት በቀረበው አቤቱታ ላይ ለውስጥ ሰራተኞች የእድገት ማስታወቂያ ሣይወጣ ክፍት የስራ ቦታ ማስታወቂያ መውጣቱ ተገቢ ባለመሆኑ ውሉ መሰረዙን ገልጿል፡፡ ይህ ክርክሩ በስር ፍ/ቤት ያልተነሣ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክንያቱም የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂ አልነበረም፡፡ የስራ ውል ያለአግባብ ከተቋረጠም ሰራተኛው ወደ ስራው ሊመለስ የሚገባው መሆኑና ወደ ስራ መመለስ ካልፈለገ ግን ካሣ ተከፍሎት ሊሰናበት እንደሚችል በአዋጁ አንቀጽ 43/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በእርግጥ የስራ ግንኙነቱ ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ ሰራተኛውን ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት መወሰን እንደሚቻል የዚሁ አንቀጽ ንኡስ ቁጥር 3 ያመለክታል፡፡ በተያዘው ጉዳዩ ተጠሪ ወደ ስራ መመለስ የፈለጉ በመሆኑና ወደ ስራ መመለሣቸው በስራ ግንኙነቱ ላይ የሚፈጥረው ችግር ስለመኖር በአመልካች በኩል የተነሣ ክርክር ስለሌለ ተጠሪ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ማለት አልተቻለም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ያላግባብ የስራ ውሉ የተቋረጠበት ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ሲወሰን በተጨማሪ ከስድስት ወር የማይበልጥ ውዝፍ ደመወዝ እንደሚወሰንለት ከአዋጁ አንቀጽ 43/5/ መረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚሁ መሰረት ተጠሪ ወደ ስራ ሲመለሱ የ6 ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ በአግባቡ ነው፡፡

በሌላ በኩል ከክርክሩ ሂደት ተጠሪ ገና ስራ ሣይጀምሩ ውሉ መቋረጡን መረዳት ችለናል፡፡ ነገር ግን በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 54/1/ መሰረት በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ ደመወዝ የሚከፈለው ለተሰራ ስራ ብቻ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም አመልካች ስራ ሣይሰሩ ከሕዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው የአንድ ወር ከ25 ቀናት ደመወዝ እንዲከፈላቸው መወሰኑ ተገቢነት የሌለው መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለዚህ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19067 በሰኔ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03174 በጥር 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ከኀዳር 1 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ታህሣስ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ያለው የአንድ ወር ከ25 ቀናት ደመወዝ ሊከፈላቸው አይገባም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ
4. ይህ ችሎት በመጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው እግድ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከተው ክፍል ይተላለፍ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36210

ኀዳር 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች:-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች:-** አቃቂ መለዋወጫ እቃዎችና መሣሪያዎች አ/ማ - አልቀረበም፡፡

**ተጠሪ:-** አቶ ኃይለ ሳልቫልቶር - ቀርቧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት የሥራ ድልድል አብረውኝ እንደሚሠሩት ሠራተኞች ከደረጃ 6 ወደ 8 ላይ እንድመደብ ይወሰንልኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ደረጃ 8 ላይ የተመደቡት 19 ዓመት እና በላይ ልምድ ያላቸውና በራሳቸው መስራት የሚችሉትን ነው፡፡ ተጠሪ ልምድም የላቸውም፣ መዋቅሩ መሠረት ያደረገው የሥራ ፍላጎትና ፍቅር፣ ውጤታማነት ታይቶ ነው፤ ስለዚህ ተጠሪ ለቦታው አይገቡም ብሎ ተከራክሯል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን የግራ ቀኙን ክርክር ካለው ሕግ ጋር በመመርመር አመልካች የሥራ ምድቡን ለመስጠት መሠረት ያደረገው ልምድና የትምህርት ደረጃ ብቻ አይደለም የታየው፣ ነገር ግን ታማኝነት የስራ አፈፃፀም እና ውጤታማነትም ታይቶ ስለሆነ በአግባቡ ነው ብሎአል፤ ነገር ግን ቦታው ለምን እንደማይገባቸው ከመናገር ውጪ ቦታው እንደማይገባቸው ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡

ተጠሪ አብረውኝ ለነበሩት ደረጃ 8 ሰጥቷል የሚለውን ቅሬታ አመልካች አላስተባበለም በማለት ተጠሪ በደረጃ 8 ላይ እንዲመደብ እና በደረጃ 8 የሚከፈለው ክፍያ እንዲከፈለው ወስኗል፡፡

አመልካችም በዚህ ፍ/ቤት በተሰጠው ውሣኔ ባለመስማማት ቅሬታውን ቢያቀርብም ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ውሣኔው ጉድለት የሌለበት መሆኑን ገልፆ ሰርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚህ ላይ ነው፡፡

አመልካች መጋቢት 1 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነውም ተጠሪ በአመልካች መ/ቤት መዋቅር መሠረት ወደ ደረጃ 8 ከፍ ብሎ እንዲመደብ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረት ይህንን ነጥብ ግራ ቀኙ ወገኖች ካሰሙት ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ለክርክሩ ዋናው ነጥብ የሆነው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በደረጃ 6 ላይ ሲሰራ ቆይቶ ወደ ደረጃ 8 መመደብ ሲገባው የተከለከለ መሆኑን ገልፆ በማመልከቱ ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም በማከራከር ተጠሪ ወደ ደረጃ 8 እንዲመደብ እና ክፍያውም እንድፈጽምለት ወስኗል፡፡

የአመልካች ድርጅት አዲስ መዋቅር መዘርጋቱን ሳይክድ በዚሁ አዲስ አሰራር ከደረጃ 6 ወደ 8 ሊያድጉ የሚችሉትን /የሚገባቸውን/ ሠራተኞች ራሱ ባወጣው መስፈርት መሠረት እንደለየ እና ተጠሪ ለዚህ ቦታ እንደማይመጥኑ ከምክንያቱ ጋር ገልጿል፡፡ ተጠሪም በዚሁ መሠረት በደረጃ 7 ላይ እንዳሉም መዝገቡ ያስረዳል፡፡ ይህ የሚያመለክተው ተጠሪ ሊመጥን በሚችልበት የተመደበ መሆኑን መገመት ይቻላል፡፡ አሠሪ የራሱን ሥራ ለማቀላጠፍ እና ምርታማ ለመሆን ሰራተኞችን እንደየችሎታቸውና እውቀታቸው ይጠቅሙኛል ባለው ቦታ በሕጋዊ መንገድ መደልደልም ሆነ መመደብ የሚከለክለው ሕግ የለም፡፡ ከሱ /ከድርጅቱ/ በላይ ስለሠራተኞቹ የሚያውቅ ሊኖር አይችልምና፡፡

ስለዚህ የአመልካች ድርጅት ተጠሪን ወደ ደረጃ 8 /ስምንት/ የማታሳድግበትን ምክንያት አላስረዳህም እና ወደ ደረጃ 8 አሳድገህ የመደቡን ክፍያም ፈጽም ተብሎ መወሰኑ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 28621 በቀን 11/4/2000 ዓ.ም. የፌ/ከ/ፍ/በመ/ቁ. 62/09 በቀን 16/5/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ፍ/ቤቶች በድርጅቱ /በአመልካች/ ሥራ ገብተው ሠራተኛን አሳድግ በማለት መወሰን አይችሉም ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 34669

ታህሳስ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አድማስ ኮሌጅ - ጠበቃ አበበ ኃይሌ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ሠለሞን ሙሉዓለም - በሌለበት የሚታይ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዮ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 ን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 08 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ከታህሳስ 01 ቀን 1995 ዓ.ም እስከ የካቲት 29 ቀን 1998 ዓ.ም ድረስ በወር ብር 1800.00 /አንድ ሺህ ስምንት መቶ ብር/ እየተከፈላቸው በመምህርነት ስራ ከአመልካች ድርጅት ጋር መስራታቸውን ሆኖም ያላንዳች ጥፋትና ማስጠንቀቂያ አሠሪው ድርጅት ከሥራ ያሠናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው የሥራ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሠናበቱ የስራ ማስረጃ እንዲሠጣቸው ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም የተጠሪን የስራ ስንብት አግባብነት በመጥቀስ ተከራክሯል፡፡ የተጠሪ የስራ ስንብት አግባብ ነው በማለት በምክንያትነት ያቀረባቸው ነጥቦችም ተጠሪን በመደጋገም የስራ ሰዓት አለማክበር የተማሪዎችን ውጤት ከአንድ ወር በላይ በእጁ ማቆየቱና ውጤቱን ሣይመልስ መቅረቱ እንዲሁም ተማሪዎች ያላገኙትን ውጤት መስጠታቸው በኮሚቴ ተጣርቶ መረጋገጡን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካችን ምስክሮች ከሠማ በኋላ የተጠሪን ከስራ መሠናበት አግባብነት በጭብጥነት ይዞ ጉዳዮን ከመረመረ በኋላ በስንብት ደብዳቤው ላይ የተገለፀው ጥፋት ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ የሚያሠናብት አይደለም በማለት የስራ ስንብቱ ያላግባብ ነው ካለ በኋላ የተጠሪ ወደ ስራ ልመለስ ጥያቄ ተቀባይነት ስለሌለው በአማራጭ የጠየቋቸው የስንብትና የካሣ ክፍያዎች እንዲከፈሉ የምስክር ወረቀትም እንዲሠጣቸው ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይሄው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ታህሳስ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የተማሪዎችን የፈተና ወረቀት ሣይመልስ መቅረቱ ለተማሪዎች ድጋሚ ፈተና መሰጠቱን ይህን ለማድረግም ከፍተኛ ገንዘብና ጊዜ ማወጣታቸውን ይህም በኮሌጁ ንብረት ላይ ጉዳት መድረሱን የሚያረጋግጥና በአዋጅ ቀጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ስር የሚወድቅ ሆኖ እያለ የታለፈው ያላግባብ በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባል ተብሎ ተጠሪ በጋዜጣ ጥሪ ቢደረግላቸውም ባለመቅረባቸው ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ታዝዟል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የአመልካችን የሠበር አቤቱታ አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ

መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ነው ተብሎ መወሰኑ በአግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ ይሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአሁኑ ተጠሪ ከስራ እንዲሰናበቱ የተደረገው በአመልካች ድርጅት በሚሠሩት የመምህርነት ሙያ የተማሪዎችን ውጤት በወቅቱ ሣያስገቡ በመቅረታቸው ስለመሆኑ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ፈተናውን በድጋሚ እንዲወስዱ መደረጉንና እንዲህ ሲደረግም ለተማሪዎቹ ለአንድ ሣምንት ‹‹ቲቶሪያል›› ተሰጥቶ ስለመሆኑ የአመልካች የሠው ምስክሮች መመስከራቸውን ከስር ፍ/ቤት ዋና መዝገብ ተመልክተናል፡፡ ተጠሪ የተማሪዎችን ውጤት እንዲያስገቡም በስልክና በተለያዩ መንገዶች ተጠይቀው ሊመልሱ ያልቻሉ ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡

እንዲህ ለስራ ስንብቱ በምክንያትነት የተጠቀሰው የተጠሪ የተማሪዎችን ውጤት በወቅቱ አለመመለስና ይህንኑ አላፊነታቸውን ባግባቡ አለመወጣት ስለመሆኑ የአመልካችን ማስረጃዎች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ይኸው ፍሬ ጉዳይ በማስረጃ የተደገፈ መሆኑን ተገንዝቦ ምክንያቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27 ስር የሚወድቅ አይደለም ሲል ነው የሥራ ሥንብቱን ሕገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ የደረሰው፡፡ በእርግጥ የስር ፍ/ቤት በስራ ስንብቱ ላይ የተመለከተውን የተጠሪን ጥፋት ይዘቱን በተፃፈው መልክ ከተመለከተው ጥፋቱ በአዋጁ መሠረት ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሠናበት ከሚያስችሉ ምክንያቶች ውስጥ ሊካተት የማይችል መሆኑን መገንዘብ ይችል ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በተጠቃሹ አዋጅ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች በክርክሩ ወቅት የሚረጋገጡ ፍሬ ጉዳዮችንና የአዋጁን አጠቃላይ ዓላማ በመመርመር ሊተረጐሙ የሚችሉ ስለመሆናቸው መገንዘብ አያዳግትም፡፡ አመልካች የሚከራከረው ተጠሪ በንብረት ላይ ጉዳት አድርሷል በማለት ነው፡፡ ጉዳት ደረሰ የተባለውም ተማሪዎች እንደገና ሊፈተኑ ሲደረግ የጊዜ፣ የጉልበት፣ የወረቀት ወጪ ከመደረጉም በላይ የኮሌጁ መልካም ስም ጠፍቷል በሚልም ጭምር ነው አመልካች ለዋቢነት የሚጠቅሰው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(1)(ሸ) ስር የተመለከተውን ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነ ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛን ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ለማሠናበት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት ነው፡፡ ንብረት ለሚለው ቃል በአዋጁ ሥር የተመለከተ ትርጓሜ የለም፡፡ ይሁን እንጂ ከአዋጁ ዓላማና ከአሠሪው ድርጅት ባህርይ እንዲሁም ከንብረት ህግ ጽንሰ ሀሣቦች ጋር በማዛመድ ለቃሉ ትርጉም መሰጠት ፍትሐዊነት ይኖረዋል ምክንያቱም ንብረት ለሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ትርጉም መስጠት የሚችል አይደለምና፡፡ በመሆኑም የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን አጠቃላይ ዓላማም ሆነ የንብረት ህግ ጽንሰ ሀሣቦች ባህርያት ግንዛቤ ውስጥ ስናስገባ ንብረት ማለት ዋጋና ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታ ያለው እንዲሁም በአብዛኛው ሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር መሆኑን ለመገንዘብ አስቸጋሪ አይሆንም ዋጋና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ በባለሀብትነት ሊያዝ የሚችል ነገር ላይ ሆን ብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ያደረሰ ሰራተኛ ከሆነ በአሠሪው ንብረት ላይ በህጉ አነጋገር ጉዳት አድርሷል ለማለት የማይቻልበት ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም የተጠሪ አድራጐት ለአመልካች ዋጋና ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታ ባለው ነገር ጉዳት አላደረሰም የሚል አይደለም በመሆኑም የስር ፍ/ቤት በተጠሪ የስንብት ደብዳቤ ላይ የተገፀውን ምክንያት እንዳለ በመውሰድ የደረሰበት ድምዳሜ አግባብነት ያለውን ድንጋጌ ባለመምረጥና አጠቃላይ ይዘቱንና መንፈሱን ባለማገናዘብ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22051 ሰኔ 06 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 57644 ታህሳስ 09 ቀን 2000 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ወጪና ኪሣራ የራሱን ይቻል ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ.39118

ታህሳስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-**ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ደሣለኝና ቤተሰቡ ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ወ/ሥላሴ ብርቱ -ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ፈቃዱ በላይ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መስከረም 23 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፉት የክስ ማመልከቻ በአመልካች መ/ቤት ከመጋቢት 16 ቀን 1994 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባሉበት ሁኔታ አመልካች ያለጥፋትና ማስጠንቀቂያ ከስራ ያሰናበታቸው መሆኑን በመግለጽና ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎችን በመዘርዘር በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ አመልካች በፍ/ቤቱ ጥሪ መሠረት ቀርቦ ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱት ለስራ ሊገለገሉበት የተሰጣቸውን ብረጅ ስቶን ጉማ ተረኛ በነበሩበት ጊዜ መውሰዳቸውን ወይም እንዲወሰድ በማድረጋቸው በመሆኑና ይህም አድራጐት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/,/ቀ/ እና 14/2/ለ/ መሠረት የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት በመሆኑ የተጠሪ ክስ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ከመከራከሩም በተጨማሪ ክፍያዎችን በተመለከተም ተገቢነት የላቸውም የሚላቸውን ምክንያቶችን በማንሳት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በአመልካች በኩል የቀረቡት የሰነድ ማስረጃዎች ሐምሌ 04 ቀን 1998 ዓ.ም ብረጅ ስቶን ጉማ የጠፋ መሆኑን እና ጠፋ በተባለ ጊዜ ተጠሪ ተረኛ የነበሩ መሆኑን ከሚያስረዱ በቀር ተጠሪ ለእራሱ ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት የአመልካችን ንብረት የሆነውን ጉማ ላይ አላግባብ የተጠቀሙ መሆኑን፣ አመልካች በግልጽ ሳይፈቅድ ከስራ ቦታ ጉማውን የመውሰድ ህገ ወጥ ተግባር ተጠሪ የፈፀሙ መሆኑን አያስረዱም፣ አመልካች የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም የሚሉትን ምክንያቶችን በመዘርዘር የስራ ውል ማቋረጥ እርምጃ አግባብ አይደለም ሲል ከወሰነ በኂላ ክፍያዎችን በተመለከተም ተገቢ ነው ያለውን ወስኗል፡፡ በዚህ የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ አግባባ አይደለም ተብሎ በተሰጠው የውሣኔ ክፍል የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ ጉዳዩን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ መሠረት የአሠሪው ንብረት ወይም ገንዘብ መጥፋት ብቻውን ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት የተፈፀመ መሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ የስራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ በቂ አይደለም የሚል ምክንያት በመያዝ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቷል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሐምሌ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ተጠሪ የተረከቡት የስኮርት ጉማ እንደጠፋ ራሳቸው በፃፏቸው የተለያዩ ፁሑፎች ተረጋግጦ እያለ እና ለጠፋው ጉማ ኃላፊ የማይሆኑበትን ምክንያት ማስረዳት ሲገባቸው ሳያስረዱ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/,/ቀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርቡ ተደርጐ መስከረም 22 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ጠፋ የተባለውን

ጉማ በተመለከተ አመልካች ለዓ/ህግ አመልክቶ ክስ ካቀረበ በኂላ ተጠሪ ለስራ ክርክር ችሎት ክስ መስርተው በክርክር ላይ ያሉ መሆኑን አመልካች እያወቀ በዓ/ህግ በኩል የቀረበውን ክስ ማንሳቱ የአመልካችን ንብረት ተጠሪ ያልወሰዱና ለግል ጥቅም አለማዋላቸውን በራሱ የሚያስረዳ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው የወንጀል ክሱ የተነሳበት ምክንያት ለተጠሪ ትብብር ለማድረግ የተደረገ መሆኑንና ይህም አመልካች ጠፋብኝ የሚለውን ተለዋጭ ጉማ አልጠፋም የሚል ማረጋገጫ ያልሰጣቸው መሆኑን እንደሚያሳይ ገልፀው ህዳር 05 ቀን 2001 ዓ.ም መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የስራ ውል የማቋረጥ እርምጃ አግባብ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

በክርክሩ ሂደት ተጠሪ የተረከቡትን የአመልካች መ/ቤት ንብረት የሆነው ብሪጅ ስቶን ጉማ በእጃቸው አለመገኘቱ እና በኂላም ለአመልካች መ/ቤት ያልመለሱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ተጠሪም እስከዚህ ችሎት ባደረጉት ክርክር የአከራካሪው ጉማ መጥፋትን ክደው የማይከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ የሚከራከሩበት የአመልካችን ጉማ ያልወሰዱና ለግል ጥቅማቸው ያላዋሉ መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ የበታች ፍ/ቤቶችም ተጠሪ የተረከቡት የአመልካች ጉማ መጥፋቱን አመልካች ማስረዳቱን እያመኑ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ወደ ሚለው ድምዳሜ የደረሱት አመልካች ጉማው መጥፋቱን ከማስረዳት በተጨማሪ ተጠሪ ድርጊቱን የፈፀሙት ለራሳቸው ወይም ለሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት መሆኑን የማስረዳት ሸክም አለበት፣ ይህንኑ ግዴታም አልተወጣም በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/መ/ እና /ቀ/ ስር የተመለከቱት ምክንያቶች የስራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችሉ ሕጋዊ ምክንያቶች ናቸው፡፡ አመልካች የሚከራከረውም እነዚህን ምክንያቶችን በመጥቀስ ነው፡፡ የሰጠው ምክንያትም ተጠሪ ለስራ ሊገለገሉበት የተሰጣቸውን የብሪጅ ስቶን ጉማ አጥፍተዋል በሚል ነው፡፡ ይኸው ጉማ የጠፋው ተጠሪ ተረኛ በነበሩበት ወቅት ስለመሆኑ እና መጥፋቱም በስር ፍ/ቤቶች የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ በሹፌርነት ሙያ የተቀጠሩ የአመልካች ድርጅት ሰራተኛ ከመሆናቸውም በላይ ጉማው ተረኛ ከነበረው ሌላ ሹፌር አልተረከብኩም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ በመሆኑም ከተረኛ ሹፌር መኪናውን ተጠሪ ከተረከቡ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ ስር እንደተመለከተው ለስራው የሚሰጡትን መሣሪያዎች በጥንቃቄ የመጠበቅ አላፊነት አለባቸው፡፡ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ግን ተጠሪ ይህንኑ ግዴታ አለመወጣታቸውን ነው፡፡ ይልቁንም ተጠሪ መኪናውን ተረክበው በራሣቸው ቁጥጥር ስር ባደረጉበት ወቅት ጉማው አለመጥፋቱና ይኸው ጉማው በምን ሁኔታና ምክንያት ሊጠፋ እንደቻለ ተጠሪ ማስረዳት ያልቻሉ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በዚህም ምክንያት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 14/2/ለ/ ስር እንደተመለከተው የጉማው በህገ ወጥ መንገድ የመጥፋቱ ሁኔታ ከተጠሪው ጋር በቀጥታ ግንኙነት የለውም ለማለት የሚያስችል ህጋዊ ምክንያት የለም ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ የተረከቡት ብሪጅ ስቶን ጉማ በእጃቸው አለመገኘቱ ከተረጋገጠ ድርጊቱ የተፈፀመው የራስን ወይም የሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት ጭምር ስለመሆኑ ሊረጋገጥ የሚገባው ነው ተብሎ በህጉ በመስፈርትነት ያልተቀመጠ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ይኸው ነጥብ ንብረቱ መጥፋቱ ከተረጋገጠ ግምት የሚወስድበት ስለመሆኑ ከአሠሪና ሠራተኛ እና ማስረጃ ህግ አጠቃላይ መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነውና፡፡ በመሆኑም ከፍ ሲል እንደተገለፀው የጉማው መጥፋት ከተጠሪ ጋር ግንኙነት የለውም የሚባልበት የህግ ምክንያት ካለመኖሩም በላይ ድርጊቱ የተፈፀመው የራስን ወይም የሌላ ሰው ብልጽግና በመሻት ስለመሆኑ አመልካች እንዲያስረዳ የሚገደድበት የማስረጃ ሸክም የሌለበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ተጠሪ የአመልካችን ንብረት ያልወሰድኩና ለግል ጥቅም አለማዋሌን የሚያረጋግጠው ጉዳይ አመልካች በዓ/ህግ በኩል መስርቶት የነበረውን የወንጀል ክስ ማንሣቱ ነው በሚል ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም የወንጀል ክሱን መተው በፍትሐብሔር ረገድ ያለውን ክርክር ሊያቋርጥ የሚችልበት የህግ ምክንያት እና ሥነ ሥርዓት የሌለ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች በአመልካች በኩል የቀረቡትን መከራከሪያ ነጥቦች ውድቅ ያደረጉት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ እና /ቀ/ ስር የተመለከተውን ድንጋጌ መንፈስ ባግባቡ ባለማገናዘብ በመሆኑ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለው ተወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 32262 ታህሳስ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63030 ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በህጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 36591

ታህሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

አልማው ወሌ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ማታዶር አዲስ ጎማ አ/ማ - ጠበቃ ደረጀ ታፈሰወርቅ ቀረበ

**ተጠሪ**፡- ደረጀ ኡመታ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 መሠረት የሚታይ የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው የስራ ውሌ ከሕግ ውጪ አቋርጦብኛል በማለት ነው፡፡ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው እንዲመለስ እንዲወሰንለትም ጠይቆአል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ የተቋረጠው ተጠሪ በፈፀመው ጥፋት ምክንያት ነው፡፡ የተፈፀመውም በሕጉ እና በሕብረት ስምምነታችን መሠረት ነው በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስተናገደው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኂላ፣ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው፡፡ ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት  ወደስራው ይመለስ በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ተጠሪ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደስራው ይመለስ በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 10 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ጥፋት ስለመፈፀሙ በሥር ፍ/ቤቶች ታምኖበት እያለ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በሚል የመወሰኑን አግባብነት ለመመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው በሁለት ምክንያቶች ነው፡፡ እነዚህም ተጠሪ ቀደም ሲል በፈፀመው ጥፋት በገንዘብ /በደመወዙ/ ቅጣትና በማስጠንቀቂያ ታልፎ ነበር የተባለው የማጭበርበር ተግባር እና በምርት ማምረት ሂደት በፈፀመው ጥፋት የጎማ ምርት ከጥቅም ውጪ እንዲሆን አድርጎአል የተባለው ናቸው፡፡ እነዚህ ድርጊቶች በእርግጥም በተጠሪ የተፈፀሙ ለመሆናቸው የስር ፍ/ቤቶች አረጋግጠዋል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ለማለት የበቃው ተጠሪ የፈፀመው ጥፋት ከስራ ለማሰናበት "የሚችል በቂ ኃይል" የለውም፡፡ አመልካች ተመጣጣኝ እርምጃ መውሰድ ሲችል ተጠሪን ከስራ ያናበተው አላግባብ ነው የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት ነው፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም የራሱ የተገለፀ ምክንያት የሰጠ ሲሆን፣ ይህም ለሥራ ውሉ መቋረጥ መሠረት የተደረገው ጥፋት በህብረት ስምምነቱ እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 27 የተመለከተ አይደለም የሚል እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ተገንዝበናል፡፡

ተጠሪ ቀደም ሲል ፈጽሞት ነበር የተባለው ጥፋት እንዳየነው በአንድ ወቅት ሞተዋል በማለት የሐዘን ፈቃድ የወሰደባቸውን አክስቱን ለሁለተኛ ጊዜ ሞተዋል በማለት የሐዘን ፈቃድ መጠየቁ ስለተረጋገጠበት ነው፡፡ ይህን መሰል ጥፋት የፈፀመ ሠራተኛ ለመጀመሪያ ጊዜ የአስር /10/ ቀን ደመወዝ ከመጨረሻ ደረጃ ማስጠንቀቂያ ጋር እንደሚቀጣና በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ጥፋት ላይ ቢገኝ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከስራ እንደሚሰናበት በህብረት ስምምነቱ ተደንግጎአል፡፡ በእርግጥ ይህ ጥፋት ከሥራ ያሰናብታል ተብሎ በአዋጁ አንቀጽ 27 አልተመለከተም፡፡ አንቀጽ 27 ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ምክንያቶች በተመለከተ የተደነገገ ሲሆን፣ በንዑስ አንቀጽ /1/ እንደተመለከተው በህብረት ስምምነት በሌላ አኳኋን የተወሰነ የሥራ ውል የሚቋረጥበት ምክንያት ካለ በአዋጁ ባይመለከትም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ሕጉ ግልጽ ነው፡፡ በህብረት ስምምነቱ ከሥራ ውል መቋረጥ በቂ ምክንያት ነው ተብሎ የሚቀመጠው ድንጋጌ ምን ዓይነት ሊሆን እንደሚገባ ሕጉ አላመለከተም፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ በተያዘው ጉዳይ እንደምናየው በሕብረት ስምምነቱ ላይ የተቀመጠው ሁኔታ ብቻውን አይደለም ለስራ ውል መቋረጥ በቂ ምክንያት የሚሆነው በህብረት ስምምነቱ የተመለከተውን ጥፋት መፈፀም ተከትሎ የሚፈፀም ጉዳት ሲኖር ነው የስራ ውሉ የሚቋረጠው፤ ይህ ደግሞ በትክክል ተሟልቶአል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጉዳዩን ከአዋጁ አንቀጽ 134/2/ ጋር አነፃጽሮ መመልከቱ ተገቢ የማይሆነውም በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ሲጠቃለል አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ሕጉንና ሕብረት ስምምነቱን መሠረት በማድረግ በመሆኑ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. አቤቱታ የቀረበባቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23162 ሰኔ 10 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 57742 መጋቢት 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ተመስርቶ የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁጥር 36894

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ/ም

**ዳኞች ፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች ፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረ ፈጅ ወ/ሮ ኮከብ ስለሺ

**ተጠሪ ፡-** አቶ ሙላት ታረቀኝ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 በመጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ መጋቢት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ስለጠየቀ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ በከሳሽነት በመቅረብ ከታህሳስ ወር 1972 ዓ.ም ጀምሮ ተቀጥሮ በአመልካች ድርጅት ውስጥ የተለያየ ስራ ሲሰራ የቆየ መሆኑን ከገለፀ በኋላ ህዳር 23 ቀን 1998 ሃላፊነትህን አልተወጣህም የሚል ምክንያት በመስጠት አላግባብ ከሥራ ያሰናበተኝ ስለሆነ ፍርድ ቤቱ የሥራ ስንብቱን ውድቅ እንዲያደርግለት ጠይቋል፡፡ አመልካች በበኩሉ በተከሳሽነት ቀርቦ የይርጋ የጊዜ ገደብ አልፏል፣ የሚልና ተጠሪ ሰራተኛ ሳይሆን የሥራ መሪ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ስልጣን የለውም የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የአመልካችን መቃወሚያ በመቀበል ተጠሪ የሥራ መሪ መሆኑን በመግለጽ ጉዳዩን የማየት ስልጣን የለኝም በማለት ዘግቶታል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ከግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ ተጠሪ ምክትል የግምጃ ቤት ሐላፊ በመሆን ያገለገለው በጊዜአዊነት ስለሆነ በቋሚነት ተመድበው ያልሰሩበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ ሊያሰኛቸው አይችልም በማለት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር የሥር ፍርድ ቤት ጉዳዩን በአሠሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት አከራክሮ እንዲወሰን በማለት መልሶለታል፡፡ አመልካች ይኸ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው፡፡ በሥራቸውም የሚመሯቸውና የሚያስተደድሯቸው ሠራተኞች አሉ፡፡ በምክትል ግምጃ ቤት ሃላፊነት የተመደቡት በጊዜያዊነት ቢሆንም ሙሉ ሃላፊነቱን እና የሚያስገኘውን መብት ተረክበው እስከሰሩ ድረስ በጊዜያዊነት በመመደባቸው ብቻ ሠራተኛ አያደርጋቸውም፡፡ ስለዚህ ከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ የአዋጅ ቁጥር 377/1993 አንቀጽ 3/2/ሐ ድንጋጌና የህብረት ስምምነቱን አንቀጽ 14 የሚተላለፍ በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ እኔ በቦታው ላይ ተመድቤ እየራ የነበረው በተጠባባቂነት ነው፡፡ የሰራተኛ ወገን እንጅ የአሰሪ ወገን አይደለሁም፡፡ አመልካች ለክርክር ያቀረበው የሥራ መዘርዝር ለእኔ ያልተሰጠኝና እኔ የማላውቀው ነው፡፡ አመልካች በመከራከሪያነት የሚጠቅሰው አስረኛውን የህብረት ስምምነት ሲሆን እኔ ሥራ ላይ በነበርኩ ጊዜ የነበረው ዘጠነኛው የህብረት ስምምነት ነው፡፡ በወቅቱ የሠራተኛ ማህበሩ ከፍተኛ ኃላፊ የነበርኩ ስለሆነ አመልካች ሥራ መሪ ነው ለማለት የሚያቀርበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፣ ስለዚህ ፍርድ ቤቱ የአመልካችን የሰበር አቤቱታ ውድቅ በማድረግ ያሰናበተኝ በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በጽሑፍ የመልስ መልስ ያቀረበ ሲሆን፣ ይህ ችሎት የአመልካችንና የተጠሪን

የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ እንደዚሁም አመልካችና ሠራተኛ ማህበሩ የተስማሙበትን ዘጠነኛውን የህብረት ስምምነትና አስረኛውን የህብረት ስምምነት በማስቀረብ ተመልክቷል፡፡

በሥርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም አመልካች የሥራ መሪ ነው ወይስ ሠራተኛ? የሚለው ነጥብ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ይሰሩበት የነበረው የሂሳብ ክፍል ረዳት ኃላፊ የሥራ ቦታ ላይ የነበረ መሆኑና ተጠሪም የክፍሉን እንቅስቃሴዎች የመቆጣጠር የዕለት ከዕለት የሒሳብ ቁልፎችን መያዝና የሒሳብ ከፋዬችን የዕለት ተዕለት የሥራ ምደባ ፕሮግራም እንደሚያዘጋጅ ተጠሪ ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መዘርዝር በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም ተጠሪ የሰራተኛነት ሳይሆን የሥራ መሪነት የሥራ ድርሻ የነበረው መሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ይሰራበት የነበረው የሥራ መደብ ተጠሪ በስራ ላይ በነበረበት ጊዜ ተፈፃሚነት በነበረው ዘጠነኛ የሕብረት ሥራ ስምምነት መሠረት የሠራተኛ የሥራ መደብ ሣይሆን የሥራ መሪ የሥራ መደብ መሆኑ በህብረት ስምምነቱ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 10 በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ከዚህም ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድቦ ሲሰራበት የነበረው ምክትል የግምጃ ቤት /የሂሳብ ክፍል/ ኃላፊ የሥራ መደብ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 ንዑስ አንቀጽ 3/2/ሐ/ መሠረት የሥራ መሪ የሥራ መደብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪ በተጠባባቂነት የሚሰራበት የነበረው የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሥራ መደብ ነው ከተባለ ተጠሪ በሥራ መደቡ ይሰራ የነበረው በቋሚነት ሳይሆን በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪን ሰራተኛ ያሰኘዋል ወይስ አያሰኘውም? የሚለውን ነጥብ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ተጠሪ በተጠባባቂነት ተመድበው ሲሰሩ ለቦታው የሚገባውን ጥቅማጥቅም የሚያገኙ እንደነበርና ለሥራው ሙሉ ሀላፊነት ወስደው ይሰሩ እንደነበር በስርና በዚህ ፍርድ ቤት የተደረገው ክርክር ያሳያል፡፡ በአዋጅ ቁጥር 494/1998 ከተደረገው፣ ማሻሻያ መሠረት የሥራ መሪ ማለት በቋሚነት ብቻ ሣይሆን በአሠሪው በተሰጠው ውክልና መሠረት በአዋጁ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ የተዘረዘሩትን ተግባራት የሚያከናውን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ በቦታው ላይ ተመድበው ይሰሩ የነበሩት በተጠባባቂነት መሆኑ ተጠሪ ሠራተኛ ናቸው ከሚለው መደምደሚያ ላይ የሚያደርስ ምክንያት ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ስለሆነም ከላይ የተገለፁትን የህግ ድንጋጌዎች ሳያገናዝብ ተጠሪ ሠራተኛ ነው የሥራ መሪ አይደለም በማለት ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 58378 መጋቢት 8 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 21891 ሰኔ 15 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ብይን ፀንቷል ይፃፍ፡፡
3. ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆኑ ጉዳዩ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ 377/1996 በአዋጅ ቁጥር 494/1998 እንደተሻሻለ የሚታይ አይደለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37201

ታህሳስ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

አሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ማታዶር አዲስ ጎማ አክሲዮን ማህበር ጠበቃ ደረጀ ታፈሰወርቅ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1. አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል

2. አቶ ዲባባ ዎርዶፋ ቀርበዋል

3. አቶ ፍቅረሰላም ቦጋለ ቀርበዋል

4. አቶ ፍቃዱ ይመኑ አልቀረቡም

5. አቶ ዓለሙ ወነታ ወኪል አቶ ኤልያስ በቀለ ቀርበዋል

6. አቶ ዮሃንስ ንጋዬ ቀርበዋል

7. አቶ አዲሱ በቀለ ቀርበዋል

8. አቶ ካሳሁን እሸቱ አልቀረቡም

9. አቶ ደረጀ ወ/ሚካኤል ቀርበዋል

10. አቶ ሙሉነህ ካሣ ቀርበዋል

11. አቶ ዋቅቶላ በዳሳ ቀርበዋል

12. አቶ ተክለማርያም ባዩ ቀርበዋል

13. አቶ መለሰ ፋንታሁን ቀርበዋል

14. አቶ ጌትነት ቶፋ ቀርበዋል

ጉዳዩ ለምርመራ በተቀጠረው መሰረት ተመርምሮ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተንበታል፣

## ፍ ር ድ

ክርክሩ በዚህ ሰበር ችሎት ሊቀርብ የቻለው አመልካቹ ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት በመጠየቅ ነው።

በአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ከሳሾች እንዲሁም የአሁኑ አመልካች ተከሳሽ በመሆን የተከራከረ ሲሆን ስር ከሳሾቹ ጥቅምት 30/1999 ዓ.ም በተፃፈ ክስ ያቀረቡት መሰረታዊ ይዘቱ በተከሳሽ ድርጅት በተለያዩ ጊዜያት ቅጥር በመፈፀም በወር ብር 288.66 (ሁለት መቶ ሰማንያ ስምንት ብር ከስድሳ ስድስት ሣንቲም) እየተከፈለን ስንሰራ ከቆየን በኋላ ምንም አይነት ጥፋት ሳንፈፅም ጥቅምት 21/1999 ዓ.ም አላግባብ ከሥራ ስላሰናበተን ውዝፍ ደሞዛችን ከፍሎ ወደ ስራችን ይመልሰን ይህ ካልሆነ ግን የስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ክፍያ፣ ካሳ፣ ክፍያ ለዘገየበት እንዲሁም ከበቂ ወጪና ኪሳራ ጋር እንዲከፍለን ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

ስር ተከሳሹ በበኩሉ ታህሳስ 20/1999 ዓ.ም በተፃፈ መልስ የሰጠ ሲሆን፣ ይዘቱም የተጫኑ ጎማዎች እንዲያራግፉ ጥቅምት 19 ቀን 1999 ዓ.ም በቅርብ ኃላፊያቸው ሲታዘዙ በአድማ መልክ ተደራጅተው አናራግፍም እንዳሉና በማግስቱም ይህ እምቢተኝነታቸው በመቀጠሉ በህብረት ስምምነቱ አንቀፅ 4.4 ተራ ቁጥር 5 መሰረት ከስራ ሊሰናበቱ ችለዋል፤ የከሳሾቹ የስራ ውል ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ ስላልሆነ የሚከፈላቸው ክፍያ የለም ተብሎ ክሳቸው ውድቅ ይሁንልኝ የሚል ነው፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም በግራ ቀኙ ወገኞች መካከል የቃል ክርክር አካሂዷል፤ የግራ ቀኙ ወገኖች ምስክሮችም ሰምቷል፤ የተገኘው ውጤትም ከሳሾቹ ጎማውን አናራግፍም ያሉት እሁድ እለት እንደነበርና በዚሁ ጊዜም በተቋሙ ውስጥ በተፈጠረው የስራ ጫና ምክንያት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈላቸው ስራቸውን በማከናወን ላይ በነበሩበት ሁኔታ ስለነበርና ስራ በዝቶብናል በሚል ምክንያት ነው የሚል ነበር፤ ፍ/ቤቱም ይህንን ሃቅ ከተገነዘበ እና ተከሳሹም የጎማውን ማራገፍ እስከ ሰኞ ድረስ አቆይቶ አሁንም እንዲያራግፉት ከሳሾችን መጠየቁ በአዋጅ ቁ 337/1996 በአንቀፅ 67 የተመለከቱትን ምክንያቶች እንዳልነበሩ ያሳያል በማለት በአጠቃላይ ከሳሾቹ ስራ ለመሥራት አልፈለጉም ተብሎ በተከሳሽ የተወሰደው ከስራ የማሰናበት ተግባር አግባብነት ያልነበረው በመሆኑ እና ከሳሾቹ በአዋጁ አንቀፅ 10 መሠረት የተቀጠሩ መሆናቸው ማህደራቸው ስለማይገልፅ ተከሳሹ የአዋጁ አንቀፅ 43(4) (ሀ)"ን" መሰረት ያደረገ ካሳ ለከሳሾቹ ሊከፍላቸው ይገባል፤ እንዲሁም የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜም ክፍያ ጨምሮ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ከላይ በሰፈረው የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ውሳኔ ቅር በመሰኘትም ስር ተከሳሹ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙ ወገኖችን ካከራከረ በኋላ መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በኮ.መ/ቁ.60960 በሰጠው ፍርድ ስር ከሳሾቹ በስር ፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ በተከሳሹ ድርጅት ውስጥ በጉልበት ሰራተኛነት ተቀጥረው በመሥራት ላይ እያሉ የኮንትራት ጊዜያቸው ሳያልቅ የስራ ውላቸው እንዳቋረጠባቸው የሚገልፅ በመሆኑና ይህ ደግሞ የስራ ግንኙነቱ ለተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ የሚያሳይ በመሆኑ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳ በአዋጅ ቁ 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት ሳይሆን በአንቀፅ 43(4)(ለ) መሰረት ነው፤ የስንብትና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያዎች በተመለከተ ግን የስር ፍ/ቤቱ የሰጠው ፍርድ ተገቢ ነው በማለት የፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤቱ ውሳኔ አሻሽሏል፡፡

ከላይ በሰፈረው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔም አመልካቹ ቅሬታ በማሳደር ሚያዝያ 10/2000 ዓ.ም በተፃፈ ቅሬታ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም የተጠሪዎቹ የስራ ቅጥር ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ነው እስከተባለ ድረስ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በጊዜያዊ የቅጥር ውላቸው በተስማማነው መሰረት የ15 ቀናት ብቻ እንጂ አንዱ የ2 ወር ደሞዝ አይደለም ተብሎ ይታረምልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዎቹም መስከረም 27/2001 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸው ከፍተኛው ፍርድ ቤቱ ክርክራችን በአግባቡ ሳያገናዝብ የስራ ግንኙነታችን በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) ሆኖ እያለ ወደ አንቀፅ 43(4)(ለ) መቀየሩ የህግ ስህተት ነው፤ አመልካች ባቀረበው አቤቱታ የኮንትራት ሰራተኞች እንደሆንን ቢገልፅም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 35(መ) መሰረት የሙከራ ጊዜያችን ያጠናቀቅን በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው የሁለት ወራት ደሞዝ ክፍያ ሊሆን ይገባል ተብሎ በከፍተኛው እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቶቹ የተሰጠው ውሳኔ ህግን ያማከለ በመሆኑ ሊፀና ይገባዋል ብለዋል፡፡

አመልካቹም ህዳር 08/2001 ዓ.ም በተፃፈ የመልስ መልሱ ተጠሪዎች ቅጥራችን በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ሀ) እንጂ በአንቀፅ 43(4)(ለ) አይደለም በማለት እኔ በአቀረብኩት የሰበር አቤቱታ ሊከራከሩ አይችሉም የራሳቸው የሆነ አቤቱታ ሊያቀርቡበት የሚገባ ነው፤ የኮንትራት ሰራተኞች መሆናቸው አምነው የተከራከሩ በመሆናቸው እና የኮንትራት ሰራተኛ ሊከፈለው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጁ አንቀፅ 35(2) መሰረት በኮንትራት ውሉ ላይ

የተገለፀው ተብሎ በመደንገጉ በእኛ የኮንትራት ውል ላይ ደግሞ የ15 ቀናት ክፍያ ተብሎ በግልፅ የተቀመጠ በመሆኑ የተጠሪዎቹ መከራከሪያ ነጥብ የህግ ድጋፍ የለውም ብሏል፡፡

ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ በተቀመጠው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ስንት ነው የ2 ወር ደሞዝ ወይስ የ15 ቀናት ብቻ የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ እንደሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰጠው ፍርድ እንዲሁም እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከፈፀመው ስምምነት መረዳት ይቻላል፤ ሊከፈላቸው የሚገባ ካሳም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 43(4)(ለ) መሠረት ሊሰላ እንደሚገባ ነው፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልስ የስራ ግንኙነታችን ለተወሰነ ጊዜ ስላልሆነ ሊከፈለን የሚገባ ካሳም በአዋጁ አንቀፅ 43(4)(ሀ) መሰረት መሆን ይገባል ቢሉም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት ፍርድ በመቃወም ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ በሌለበት ሁኔታ ክርክራቸው ተቀባይነት የለውም፡፡ በዚህ ችሎት በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል አከራካሪው ነጥብ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ መጠን በተመለከተ ነው፤ የግራ ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት በተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያው በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 35(2) መሰረት የሚሰላ ነው፡፡ ይህ አንቀፅም ተዋዋዮቹ ወገኖች በስምምነታቸው ባስቀመጡት መልክ እንደሚከናወን ስለሚገልፅና እያንዳንዱ ተጠሪ ከአመልካች ጋር በፈፀመው ስምምነት አንቀፅ 3.3 መሠረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ እንደሆነ ነው፤ የስምምነታቸው በዚህ መልክ ተገልጾ እያለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የማስጠንቀቂያ ጊዜው ክፍያ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤቱ የወሰነውን የ2 ወር ደሞዝ ተቀብሎ ማለፉ የግራና ቀኙ ወገኖች የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ ከመሆኑ አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የህግ ስህተት የፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 60960 መጋቢት 15/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽሏል፤ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና በእያንዳንዱ ተጠሪ መካከል ያለው የስራ ግንኙነት ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ በመሆኑ ለእያንዳንዱ ተጠሪ ሊከፈል የሚገባው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀፅ 44 እና በስምምነታቸው አንቀፅ 3.3 መሰረት የ15 ቀናት ደሞዝ ብቻ ነው ብለናል፡፡
3. ሚያዝያ 20/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የተላለፈው እግድ ተነስቷል፣ ይፃፍ፡፡
4. ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ያካሄዱትን ክርክር በሚመለከት ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
   ክርክሩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

ፍርዱ በዛሬው ዕለት 07/05/2001 ዓ.ም በችሎት ተነገረ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 37454

ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዲልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡** ሰላም የቴክኒክና የሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል ነ/ፈጅ በቀለ ነዲ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ከበደ ሰይፉ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62157 ሚያዝያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝና በመዝገብ ቁጥር 32105 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሚያዝያ 28 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ በከሳሽነት ቀርበው ከሚያዚያ ወር 1993 እስከ መስከረም 25 ቀን 1999 ዓ.ም በጥበቃ ሠራተኝነት ተቀጥሮ ከአመልካች ድርጅት ከማገልገል ላይ እያለ አመልካች አላግባብ የሥራ ውሉን በማቋረጡና ከሥራ በማሰናበቱ ፍርድ ቤቱ ወደ ሥራ እንዲመለስ ይወሰንልኝ ወደ ሥራዬ የማልመለስ ከሆነ ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡ የአሁን አመልካች ሥር በከሳሽነት ቀርቦ ተጠሪ ከሥራ የተሰናበተው በየዕለቱ የዘብ ሥራውን ሲያከናውን የቅርብ አለቃውን ትእዛዝ የማይቀበል በመሆኑ የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው በኂላ በቀርብ አለቃው ላይ በመዛቱና የተለያዩ የፅሁፍና የቃል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸው ሊስተካከሉና ሥራቸውን በአግባቡ ሊያከናውኑ ባለመቻላቸው ነው፡፡ ለተጠሪው (ከሳሽ) ሊፈፀም የሚገባው ክፍያ የለም በማለት ተከራክሯል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች በየጊዜው ለተጠሪ ጽፌአቸዋለሁ ከሚላቸው የጽሑፍ ማስረጃዎች ውጭ ተጠሪ በሥራቸው ላይ አንባገር የፈጠሩ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ አላቀረቡም በማለት የተጠሪን ወደ ሥራ የመመለስ ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ተከፍለዋቸው ተጠሪ ከሥራ እንዲሰናበቱ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካችና ተጠሪ ቅር በመሰኘት ሁለቱም በየበኩላቸው ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርበዋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረበው ይግባኝ የሚያስቀርብ ህግ ወይም የፍሬ ገዳይ ምክንያት የለም በማለት በመዝገብ ቁጥር 62157 ሚያዚያ 14 ቀን 2000 ዓ.ም ትእዛዝ የሰጠ ሲሆን ተጠሪ ባቀረቡት የይግባኝ ቅሬታ ላይ አመልካች መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኂላ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ ወደ ሥራ አይመለሱም ብሎ መወሰኑ ተገቢ ባለመሆኑ የስምንት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

አመልካች የፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት የሥራ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የእኛን ይግባኝ በመሰረዝና የተጠሪን ይግባኝ በመቀጠል ተጠሪ ወደ ሥራ ቢመለስ የሚፈጠር ችግር የለም በማለት ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ መሠታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል ተጠሪ በበኩሉ የሥር ፍርድ ቤት ካሣ

ተከፍሎት ይሰናበት በማለት የሰጠው ውሣኔ ህጋዊነት የሌለው ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት እኔ ያቀረብኩትን ይግባኝ በመመርመር ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የሰበር አቤቱታው ውድቅ ይሁንልኝ በማለት ሀምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር በመልስ መልሱ ተከራክሯል፡፡ የሥር የክርክሩ አመጣጥ በዚህ ፍርድ ቤት በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ተጠሪ የስምንት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ መታየት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

አመልካች ተጠሪ ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው በቂና አሣማኝ ማስረጃ አላቀረበም በማለት የሥር ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም አመልካች አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ጉዳዩ የፍሬ ጉዳይ ክርክርና የማስረጃ የምዘና እንጂ መሠረታዊ የሆነ የህግ አተረጓጐም ሆኖ ያላገኘነው በመሆኑ አልተቀበልነውም፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ከሥራ ለማሰናበት የሚያስችል ጥፋት የፈፀመ መሆኑን የሚያሣይ ማስረጃ የለም በማለት አመልካች የፈፀመው የሥራ ስንብት ህጋዊነት የሌለው ነው በማለት ከወሰነ በኂላ የተጠሪ ወደ ሥራው መመለስ በአሠሪውና ሠራተኛው ግንኙነት ላይ የሚፈጥረውን አሉታዊና አዎንታዊ ጎን በመመዘን ተጠሪ በአሠራና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት የተለያዩ ክፍያዎችን በመክፈል ከሥራ እንዲሰናበት ወስኗል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ምክንያት አላምንበትም ከማለት ውጭ የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ ከአመልካች ጋር መልካም ግንኙነት እና ጥሩ የሥራ ሁኔታ የሚፈጥር ስለመሆኑ የሰጠው ምክንያትና ለዚህም መነሻ የሆኑትን ነባራዊ እውነታዎችና መረጃዎች በዝርዝር አልገለፁም፡፡

ተጠሪ በጥበቃ ሥራ የተሠማራና በእጁም ትጥቅ የሚይዝ ከመሆኑና ከቅርብ አለቆቹ ጋር በተለያየ ጊዜ ግጭት የሚፈጥር ስለመሆኑ ከመገለፁ አንፃር እና ከዚህም መነሻ ከሥራ ተሰናብቶ የቆየ መሆኑና አመልካች ይህንን በበቂ ማስረጃ ባለማስረዳቱና የሥራ ስንብቱን ህጉ የሚጠይቀውን ፎርሚሊቲ አሟልቶ ባለማከናወኑ ምክንያት አመልካች የፈረመው የሥራ ስንብት ህጋዊነት የጐደለው ነው እንደተባለ ከሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡ አንድ ሠራተኛ የሥራ ቅጥር አላግባብ ከተቋረጠ ፍርድ ቤቱ ወደ ሥራው እንድመለስ ወይም ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ሲወሰን እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ፍርድ ቤቱ ሠራተኛው ወደ ሥራው እዲመለስ የሚወሰነው ከሥራ ግንኙነት ጠባይ የተነሳ የሥራ ግንኙነቱ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ሊከተል ይችላል ብሎ በማያምንበት ጊዜ መሆኑንና ከሥራ ባሕሪው የተነሳ የሥራ ግንኙነቱ ቢቀጥል ከፍተኛ ችግር ያስከትላል ብሎ ካመነ ሰራተኛው ወደ ሥራ ለመመለስ ቢፈልግ እንኳን ካሣ ተከፍሎት እንዲሰናበት ማዘዝ እንደሚችል ከአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስናየው የተጠሪ የሥራ ባህሪ የአመልካች ድርጅት ጠቅላላ ንብረት ፀጥታና ደህንነት መጠበቅ ከመሆኑ አንፃርና ይኸም በአሠሪውና በሠራተኛው መካከል የሚጠይቀውን ከፍተኛ የሆነ መተማመን የሻከረውና ግንኙነቱ ቢቀጥል በአመልካች ድርጅት ላይ ከፍተኛ የሆነ ጉዳትና ችግር ሊያስከትል የሚችል በመሆኑ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ይህንን ወደ ጐን በመተው የተጠሪ ወደ ሥራ መመለስ ሊፈጥር የሚችለው ከፍተኛ ችግር ስለሌለ ወደ ሥራ እንዲመለስ በለማት የሰጠው ውሣኔ ከላይ የተገፀውን የህግ ድንጋጌ የሚቃረንና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62105 ሚያዝያ 1 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 32488 ህዳር 23 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ይፃፍ
3. በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ሰሚ ችሎት ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 38255

ታህሣሥ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር ነ/ፈጅ ምናለ በሪሁን ቀርበዋል

**ተጠሪ**፡- ዓለምሰገድ ኃይሉ አልቀረበም፡፡

ጉዳዩን በመመርመር የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታው የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62997 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲሻርለት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ ባለእዳ፣በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ደግሞ መልስ ሰጭ የነበረ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ በፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብት፣የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር ደግሞ ይግባኝ ባይ በመሆን ተከራክረዋል፡፡

የፍርድ ባለመብት የሆኑት የአሁኑ ተጠሪ ታህሳስ 29 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ለፌ/መጀ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት አቤቱታ ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 36237 ከባለ እዳው ጋር ባደረጉት የስራ ክርክር ወደ ስራቸው እንዲመለሱ፣ውዝፍ ደሞዝና ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው ተወስኖላቸው እንደነበር በማስታወስ ወደ ስራ የመመለሱ ሁኔታ እንደማይፈልጉትና በምትኩ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለዋቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ጠይቀዋል፡፡ የመጀ/ደ/ፍ/ቤቱም የፍርድ ባለመብቱ በፍርዱ እንደሰፈረው በአመራጭ የጠየቋቸው ሌሎች ክፍያዎች ያልነበሩ በመሆኑና የአራት ወር የደሞዝ ክፍያ የተከፈላቸው በመሆኑ ወደ ሥራ ለመመለስ እንዳልፈለጉ በመቁጠርና የሚከፈላቸው ሌላ ቀሪ ክፍያ የለም በማለት መዝገቡን ዘግቶ አሰናብቷቸዋል፡፡

ከላይ የሰፈረውን ትእዛዝ በመቃወምም የአሁኑ ተጠሪ ወደ ፌ/ከ/ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን መሰረታዊ ይዘቱም ደቀም ብሎ በተፈረደልኝ መሰረት መልስ ሰጭው ምክንያት እየፈጠረ ወደ ስራ ሳይመልሰኝ በመቅረቱና የስራ ግንኙነታችን በመሻከሩ ወደ ስራ መመለሴ ቀርቶ በካሳ ልሰናበት በማለት ላቀረብኩት ጥያቄ ስራውን እንዳልፈለኩት በመቁጠር ያለምንም መፍትሄ መዝገቡ መዝጋቱ ተገቢ አይደለም የሚል ነው፡፡

መልስ ሰጭ የነበሩት የአሁኑ አመልካች በሰጡት መልስም በውሳኔው መሰረት ተፈጽሟል፤የተወሰነላቸው ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሏቸዋል፤ ወደ መደበኛ ስራቸውም እንዲመለሱ የመኪናው አረካካቢ ተመድቦላቸው እያለ የተዘጋውን መዝገብ እንደገና አንቀሳቅሰው ካሳ ተከፍሎኝ ልሰናበት ማለታቸው አላግባብ ነው ብሏል፡፡

ይግባኝ ሰሚው ከፍተኛው ፍ/ቤትም በኮ/ቁ. 62997 ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይ/ባይ በስር ፍ/ቤት በዋና ክርክራቸው በአማራጭ በካሳ ልሰናበት ብለው ባይጠይቁም ውሳኔው ከተሰጠ በኋላ በአፈፃፀም መጠየቅ እንደሚችሉ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/3/ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነና የአፈፃፀም መዝገቡ ሳይዘጋ ወደ ስራ

መመለሳቸው ቀርቶ ካሳ ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ የጠየቁ ሰለሆነ ወደ ስራ ለመመለስ ፍቃደኛ አልሆኑም በማለት የስር ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሳኔ በመሻር በፍርዱ መሰረት ውዝፍ ደሞዝ እንደተከፈላቸው በማረጋገጥና ይህንን ውዝፍ ደሞዝ ይዘው ወደ ስራቸው ይመለሱ ብሏል፡፡

የአሁኑ አመልካችም ከላይ የሰፈረውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ሰኔ 03 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት አቅርቧል፤መሰረታዊ ይዘቱም በፍርዱ መሰረት የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዝና ወጪና ኪሳራ ለተጠሪው በመክፈል ስራቸውም እንዲጀምሩ ደብዳቤ ጽፈንላቸው እያለና በዚህ ደረጃም ፍርዱ የተፈፀመ መሆኑ ግልጽ ሆኖ እያለ ከዚህ በኋላ ተጠሪው ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ ካሳና ሌሎች በፍርዱ ያልተፈረዱላቸውን ክፍያዎች ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ያቀረቡት ጥያቄ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በትክክል የወሰነውን ከፍተኛ ፍ/ቤቱ በይግባኝ አከራክሮ ወደ ስራ ይመለሱ ማለቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት ነው፤በአዋጁ አንቀጽ 43/3/ መሰረት ተጠሪው ጥያቄውን ማቅረብ የሚገባው ዋናውን ፍርድ ለሰጠው ፍ/ቤት እንጂ የአፈፃፀም ክርክር ለሚያካሂደው አይደለም፤በመሆኑም የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይሻርልኝ የሚል ነው፡፡

ተጠሪዋ ሐምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ መልሳቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣ይዘቱም ያቀረብኩት ጥያቄ አዋጅ ቁ. 377/1996 አንቀጽ 43/3/ መሰረት በማድረግ በዋናው ጉዳይ ፍርድ ከተሰጠ በኋላም ቢሆን ወደ ስራ በመመለስ ፈንታ ካሳ ተከፍሎኝ ልሰናበት ማለት እችላለሁ፤ጥያቄዬ ያቀረብኩት በተዘጋ የፍርድ አፈፃፀም መዝገብ ሳይሆን በቀጠር ላይ ወይም በሂደት በነበረ የአፈፃፀም መዝገብ ውስጥ ነው፤ወደ ስራ መመለሱ ይቅርብኝ ያልኩት በመካከላችን ያለው የስራ ግንኙነት የተባላሸ መሆኑ ስለተገነዘብኩኝ ነው፤አመልካች በስር ፍ/ቤት ባደረጋቸው ክርክሮችም ካሳ ተከፍሎኝ እንድሰናበት ፍላጐቱ እንደነበር ነው፤አመልካች ያቀረበው ጥያቄ የህግ መሰረት የሌለው በመሆኑ የከፍተኛ ፍ/ቤቱ ውሳኔ ይጽናልኝ የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ እንደመጣው ሲመስል ተጠሪው ወደስራቸው እንዲመለሱ ማድረጉ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? ሊከፈላቸው የሚገባ ክፍያስ ምንድን ነው ? የሚሉትን መሰረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከክርክሩ መረዳት እንደሚቻለው የአሁኑ ተጠሪ ቀደም ብሎ ማለትም በመ/ቁ. 36237 በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በዋና ጉዳይ በቀረበው ክስ መሰረት አመልካች ወደ ስራ እንዲመልሰው፣የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዝ እንዲከፈለው እና ወጪና ኪሳራም እንዲከፈለው በተወሰነለት መሰረት የተጠቀሱት ክፍያዎች አመልካች ለተጠሪው እንደከፈለና ወደ ስራው እንዲመለስም በደብዳቤ አሳውቆት በርክክብ ደረጃ እያለ ተመልሶ ወደ ፌ/መ/ደ/ፍ/ቤቱ በመቅረብ ወደ ስራው ከመመለስ ይልቅ ካሳ የስንብት ክፍያና ሌሎች ክፍያዎች ተከፍለውት ከስራ እንዲሰናበት እንደጠየቀ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በአዋጅ ቁጥር 43/3/ ከሰፈረው አኳያ ሲታይ ልዩነት ያለው ነው፡፡ በተጠቀሰው አንቀጽ የተቀመጠው መብት ተግባራዊ የሚሆነው ተጠሪው በፍርዱ መሰረት የተወሰነለትን ውዝፍ ደሞዝና ሌሎች ክፍያዎች ሳይወስድ ቢሆን ኖሮ ነው፣በዚህ ጉዳይ ግን ተጠሪው በፍርዱ መሰረት ወደ ስራው እዲመለስ ወስኖ በፍርዱ የተወሰኑለትን ክፍያዎች ከተቀበለ በኋላ ነው፤ስለሆነም በፍርዱ መሰረት መብቱ ከተፈጸመለት በኋላ በአዋጅ አንቀጽ 43/3/ መሰረት ወደ ስራ ከመመለስ ይልቅ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፈለውት በአማራጭ እንዲሰናበት የቀረበ ጥያቄ ነው ማለት አይቻልም፤በመሆኑም ተጠሪው ስራ መስራት እንደማይፈልግ ገልጾ እያለ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወደ ስራው ይመለስ ብሎ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመሆኑም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 37264፣ጥር 08 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፣ይፃፍ፡፡
2. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በኮ/መ/ቁ. 62997፣ግንቦት 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

3. ተጠሪው ካሳና የስራ ስንብት ክፍያ ተከፍሎት በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 43/3/ መሰረት ከሥራው እንዲሰናበት የጠየቀው የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 36237 ፣ሕዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም በወሰነለት መሰረት የአራት ወራት ውዝፍ ደሞዙ ከተከፈለውና ወደ ሥራውም እንዲመለስ በአመልካቹ ደብዳቤ ከተፃፈለት እንዲሁም ከውሳኔው በኋላ ደሞዝ መብላት ከጀመረና ፍርዱ ከተፈፀመ በኋላ በመሆኑ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም፡፡
4. ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፤ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት የመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 37551

ታህሣሥ 09 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ድካምየለህ ጥበቡ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አርሾ የሕክምና ላብራቶሪ ኃላ/የተ/የግል ማኀበር - ጠበቃ ጌታቸው ብሩ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች መስከረም 30 ቀን 2000 ዓ.ም. ከሌሎች ከሣሾች ጋር ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የሥራ ውል የጡረታ ዕድሜ ደርሷል በሚል ምክንያት መቋረጡን ገልፀው በድርጅቱና በሠራተኛ ማኀበሩ መሃከል በተደረገው የሕብረት ስምምነት በፈቃዱ ሥራ የለቀቀ ሠራተኛ ፕሮቪደንት ፈንድና የሥራ ስንብት ክፍያ እንደሚያገኝ ስለሚደነግግ ተጠሪ ይህንኑ እንዲፈጽም በተደጋጋሚ ቢጠይቁም ፈቃደኛ ሣይሆን መቅረቱንና መከልከሉን ጠቅሰው የሥራ ስንብት ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ ብር 20,189.00 /ሃያ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር/ ተጠሪ እንዲከፍል ይወስንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በተጠሪ ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም አመልካች ዕድሜያቸው ለጡረታ በመድረሱ የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ ተፈጽሞላቸው በሕብረት ስምምነቱ መሠረት ከሥራ የተሠናበቱ በመሆኑ የስራ ስንብት ክፍያ ጥያቄው ሊፈፀም እንደማይገባ፣ ለአመልካቹ ተገቢው ክፍያና ጥቅማጥቅም የተፈፀመላቸው በመሆኑ ክፍያ ለዘገየበት ጥያቄ አላፊነት እንደሌለበት በመግለጽ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም አመልካች በጡረታ የተሰናበቱ መሆኑን አምነው የተከራከሩ ከመሆኑ እና በሕብረት ስምምነት መሠረት የስራ ስንብትና የፕሮቪደንት ፈንድ ክፍያ የሚፈፀመው በፈቃድ ለለቀቀ ሠራተኛ ብቻ ነው በማለት የሚደነግግ በመሆኑ እንዲሁም በተሻሻለው አዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ መሠረት የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ የሆነ በጡረታ የተገለለ ሠራተኛ የስራ ስንብት የማይፈፀምለት መሆኑን የሚደነግግ ነው የሚሉትን ምክንያቶች ጠቅሶ የአመልካችን የሥራ ስንብት ክፍያና ክፍያ ለዘገየበት ጥያቄ ውድቅ አድርጎ ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የበታች ፍ/ቤቶች ከጡረታ በኋላ ጡረተኛው ከሌላ አሠሪ ጋር የሚያደርገው ግንኙነት ሲቋረጥ ያለውን የሕግ ከለላ እና በሕብረት ስምምነት ለሠራተኛው የበለጠ መብት የሚሠጥ ከሆነ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት መፈፀም ያለበት መሆኑን ባላገናዘበ መልኩ መወሰናቸው መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በመሆኑ ታርሞ አመልካች ስራቸውን በራሣቸው ፈቃድ የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጦ

በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ከወጪና ኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰን ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሠበር ችሎቱ ሊተይ ይገባል በመባሉ ተጠሪ እንዲቀርብ ተደርጎ ሐምሌ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ጠበቃቸው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ አመልካች በሁለት መ/ቤቶች ቅጥር እንደፈጸሙ አድርገው ያቀረቡት ክርክር አዲስ በመሆኑ ሥነ ሥርዓታዊ አይደለም፣ የስራ ስንብት ክፍያም አመልካቹ በጡረታ የተገለሉና የጡረታ መብትም ተጠቃሚ በመሆናቸው ሊጠየቅ የማይገባ መሆኑን በመዘርዘር የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ተብሎ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የመልስ መልስ የማቅረብ መብት ከታለፈ በኋላም ግራ ቀኙ ማጣሪያ ጥያቄ ቀርቦላቸው መልሣቸውን እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የሥራ ስንብት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ የተረገው ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በክርክሩ ሂደት አመልካች በጥቁር አንበሣ ሆስፒታል ተቀጥረው ሲያገለግሉ ቆይተው እድሜያቸው ሃምሣ ዓመት ሲሞላ በፈቃዳቸው ስራውን ለቀው ለዚህ አገልግሎታቸው የጡረታ መብት ተጠቃሚ መሆናቸው፣ ከዚህ መስሪያ ቤት በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በተጠሪ መስሪያ ቤት ከሐምሌ 19 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ ተቀጥረው ለአስር ዓመታት ያሕል አገልግለው እድሜ ለጡረታ ደርሷል በሚል ምክንያት ከነሐሴ 25 ቀን 1999 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ መገለላቸው የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡

ተጠሪ አመልካች በሁለት መ/ቤቶች ሁለት የተለያዩ የቅጥር ውሎችን የፈፀሙ መሆኑንና በዚህ ረገድ ያለውን የሕግ ክለላ በሰበር አቤቱታቸው መጥቀሣቸው በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ አዲስ የክርክር ነጥብ ነው በማለት ያነሱትን መቃወሚያ ስንመለከተው አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚነታቸው የተጠበቀው በተጠሪ መ/ቤት ሳበረከቱት አገልግሎት መሆኑ ያልተረጋገጠ በመሆኑ፣ አመልካች በሁለት የተለያዩ መ/ቤቶች ሁለት የተለያዩ የቅጥር ውሎችን መፈፀሜ እየታወቀ በዚህ ረገድ ያለው የሕግ ከለላ ግንዛቤ ውስጥ ሣይገባ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መስጠታቸው ስህተት ነው፡፡ በማለት በሰበር አቤቱታው ላይ መግለፃቸው በይዘቱም ሲታይ በሥር ፍ/ቤት ያልተነሣ የክርክር ነጥብ ነው፡፡ ለማለት የሚያስችል ሁኖ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ጠበቃ በዚህ ረገድ ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ወደ ዋናው ጉዳይ ስንመለስም፤ አመልካች ከተጠሪ ድርጅት የተሠናበቱት የጡረታ ዕድሜ ስለደረሰ ሕጉም ስለሚያስገድዳቸው ጠይቀው ጡረታ ወጡ እንጂ ሥራ መልቀቅ ፈልገው አይደለም በማለት የተጠሪ ጠበቃ ያልቀረቡት መከራከሪያ ሲታይ አመልካች ከጥቁር አንበሣ ሆስፒታል በጡረታ የተገለሉ መሆኑ እየታወቀ በተጠሪ መስሪያ ቤት የተቀጠሩ መሆናቸው ጋር ተዳምሮ ሲታይ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም አመልካች በጡረታ ከተገለሉ በኋላ በተጠሪ መ/ቤት ተቀጥረው ሲሠሩ ቆይተው ስራውን የለቀቁትን በገዛ ፈቃዳቸው እንጂ የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ሕጉ የሚያስገድዳቸው ሆኖ አይደለም፡፡ አመልካች ከተጠሪ መ/ቤት ስራቸውን የለቀቁት ዕድሜያቸው የጡረታ ዕድሜ ደርሶ ነው ቢባልም የጡረታ ዕድሜ የደረሰ ሠራተኛ የተጠሪን ጅርጅት ለመልቀቅ ከፈለገ ሊከለከል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ ስለሆነም አመልካች ከተጠሪ ድርጅት የተሠናበቱት በገዛ ፈቃዳቸው ውጪ በሌላ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት ሁኔታ የሥር ፍ/ቤት አመልካች በጡረታ የተሰናበቱ መሆኑን አምነዋል ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አመልካች ስራቸውን የለቀቁት በገዛ ፈቃዳቸው ነው ከተባለ በተከታይ ሊታይ የሚገባው ውጤቱ ነው፡፡ አመልካች በገዛ ፈቃዱ ስራውን የሚለቅ የተጠሪ ሠራተኛ በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የመጠባበቂያ መዋጮውንና የአገልግሎት ካሣውን ወዲያውኑ የማግኘት መብት ስላለው ያልተፈፀመልኝ የአገልግሎት ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል በማለት የሚከራከሩ ሲሆን ተጠሪ በበኩሉ አመልካች የጡረታ ዕድሜ ደርሷቸው ከሥራ በሕጉ አግባብ የተለሉ ከመሆኑም በላይ የፕሮቪደንት ፈንድ ተጠቃሚ ስለሆኑ የአገልግሎት ካሣ ሊወስዱ አይገባም በማለት የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

በመሠረቱ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ የሆኑት በተጠሪ ድርጅት ባበረከቱት አገልግሎት አለመሆኑን ከላይ ተመልክተናል፡፡ በተጠሪ ድርጅት አዲስ የስራ ውል ፈጽመው ዕድሜያቸው ከስልሣ ዓመት በላይ እስኪሆናቸው ሠርተዋል፡፡ ዕድሚያቸው ስልሣ ዓመት ሲሞላቸውም በሕብረት ስምምነቱ መሠረት የጡረታ ዕድሜ ደርሷል በሚል ምክንያት ከሥራ እንዲገለሉ ሣይደረግ ከተጠሪ ጋር ያላቸው የስራ ግንኙነት እንዲቀጥል መደረጉ አመልካች ሥራውን የለቀቁት የጡረታ ሕጉ እና የሕብረት ስምምነቱ ስለማያስገድዳቸው ነው የሚለው የተጠሪ ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ተጠሪ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ በመሆናቸው በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2/2/ሰ/ መሠረት የአገልግሎት ካሣ ሊያገኙ አይገባም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ስንመለከተውም አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚነታቸው የመነጨው ለተጠሪ ባበረከቱት አገልግሎት ካለመሆኑም በላይ አዋጅ ቁጥር 494/98 ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ነሐሴ 10 ቀን 1998 ዓ.ም. በተደረገ ስምምነት የተጠሪን ድርጅት ለመልቀቅ የሚፈልግ ሠራተኛ የድርጅትን የመጠባበቂያ መዋጮውንና የአገልግሎት ካሣውን በጣምራ የማግኘት መብት እንደለው በአንቀጽ 38/1/ ስር የተመለከተ በመሆኑ እና የሕብረት ስምምነቱ ከአሠሪና ሠራተኛ ሕግ የተሻለ ሁኖ ሲገኝ ደግሞ ተፈፃሚ ሊሆን እንደሚገባ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 134/2/ ሥር የተደነገገ ስለሆነ የተጠሪ ክርክር በሕግ ፊት ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ከተጠሪ ጋር የነበራቸውን የሥራ ግንኙነት በፈቃዳቸው የለቀቁ መሆኑ ተረጋግጦ እያለና የሕብረት ስምምነቱ ደግሞ ለፕሮቪደንት ፈንዱና የአገልግሎት ካሣ በአንድነት ሊያገኙ የሚገባ መሆኑን የሚደነግግ ሆኖ እያለ የሥር ፍ/ቤት የአመልካችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉም ሆነ የከፍተኛው ፍ/ቤት ይህንኑ ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 22619 ጥር 02 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 63019 መጋቢት 23 ቀን 2000 ዓ.ም. በትዕዛዝ የፀናው እና የአመልካችን የአገልግሎት ካሣና ክፍያው ለዘገየበት ክፍያ ጥያቄ ውድቅ ያደረገው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የአገልግሎት ካሣና ክፍያ ለዘገየበት ብር 20,189.00 /ሃያ ሺህ አንድ መቶ ሠማኒያ ዘጠኝ ብር/ እንዲከፍል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 34476

ታህሳስ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድርመሐመድ

ሂሩት መለሰ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ኩመላ በጅሣ- ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ብሔራዊ አስጉብኚና ጉዞ ወኪል ድርጅት - ነ/ፈጅ በርሃኑ ከፍነው ቀረቡ

መዝገቡን መረምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ አመልካች በአሁኑ ተጠሪ ድርጅት ከሚያዚያ 29 ቀን 1975 ዓ.ም ጀምሮ በሹፌርነት ሙያ ለ24 ዓመታት ማገልገላቸውንና ያገኙት የነበረውን የደመወዝ መጠን ጠቅሰው ተጠሪ ያላግባብ የስራ ውሉን በማቋረጥ ያሠናበታቸው መሆኑን በመዘርዘር የስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የ6 ወራት ደመወዝ ካሣ ክፍያ እና ስራ ሠርተው ያልተከፈላቸው የ14 ቀን ደመወዝ እንዲከፈላቸው እንዲሁም የምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በአሁኑ ተጠሪ ላይ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ ተጠሪ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሰጠው መልስ የአመልካች የሥራ ውል የተቋረጠው በተከታታይ አምስት ቀን ከሥራ ገበታቸው በመለየታቸው በሕጉ አግባብ መሆኑን የሚገባቸው ክፍያ አለመኖሩንና በድርጅቱ ውስጥ 24 አመታት ያገለገሉ በመሆኑ የአገልግሎት ጡረታ አበል በእድሜ ልክ ስለሚከፈላቸው የአገልግሎት ካሣ ክፍያ የመጠየቅ መብት የሌላቸው ሆኑን በመዘርዘር ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው ፍ/ቤትም የተጠሪ እርምጃ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን በመጥቀስ የሥራ ስንብቱ አላግባብ መሆኑን በመግለጽ የአሁኑ አመልካች የጡረታ መብት ተጠቃሚ በመሆናቸው የስንብት ክፍያ እንደማይገባቸው የ14 ቀን ደመወዝ እንደሚገባቸው ይህ ክፍያ ለዘገየበት የሁለት ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸውና የምስክር ወረቀትም እንዲሰጣቸው ዘርዝሮ ከወሰነ በኋላ የስንብት ወይም የጡረታ መብት ለአመልካች አንዱ ካልተፈፀመ አቤቱታ የማቅረብ መብታቸውን ጠብቆላቸዋል የአሁኑ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ተቀባይነት አላገኙም የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ታህሳስ 16 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ የስር ፍ/ቤት የጡረታ መብት የመከልከል ሥልጣን ሣይኖረው በዚህ ረገድ የሠጠው ውሣኔ እርስ በራሱ የሚጋጭና ህጋዊ መሠረት የሌለው መሆኑን ስንብቱን ህገ-ወጥ ነው ብሎ ከወሰነ በኋላ በህጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገቡ ክፍያዎችን ማለፉ ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪ ቀርቦ ሐምሌ 07 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን ሠጥቷል፡፡ በመልሱ ላይም የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ተብሎ አለመወሰኑን የስር ፍ/ቤት የአመልካችን ዘላቂ የጡረታ መብት ተጠቃሚነት ከልክሎ የሰጠው ውሣኔ አለመኖሩን በመዘርዘር አመልካች የስር ፍ/ቤት ያልሰጠውን ውሣኔ እንደሰጠ በማስመሰል እንዲሁም የማይገባቸው ክፍያ ስር ፍ/ቤት ላይ ያልነበረን ጭብጥ በማንሣት እንዲከፈላቸው መጠየቃቸው ያላግባብ በመሆኑ የሠበር አቤቱታው ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ አመልካች በበኩላቸው ሐምሌ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የስር ፍ/ቤት አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት ያላግባብ ነው በማለት ከወሰነ በኋላ የካሣ ይከፈለኝ ጥያቄውን ማለፉና በስንብት ክፍያ ላይ የሠጠው ውሣኔ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊመርመር የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከመዝገቡ መገንዘብ የተቻለው የአመልካች የስራ ስንብት ያላግባብ ነው ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሰኑን ነው ተጠሪ ለዚህ ችሎት የጽሑፍ መልስ ሲያቀርብ የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው በሚል ውሣኔ አለመሰጠቱን የገለፀ ቢሆንም በመ/ቁ 26844 ሠኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም በስር ፍ/ቤት የተሰጠው የውሣኔ ግልባጭ ግን የስራ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው በሚል የተሰጠው ውሳኔ የለም የሚለው ክርክር መሠረት የሌለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በዚህ ረገድ ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡

የአመልካች የስራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው ከተባለ ጉዳዩ እልባት ሊያገኝ የሚገባው ከህግ ውጪ የሆነ የስራ ውል ማቋረጥ የሚያስከትላቸው ውጤቶችን የሚገዛውን የህጉን ዘርፍ ባገናዘበ መልኩ ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካች ከሥራ የተሰናበቱት ያላግባብ መሆኑን ገልፀው የተለያዩ ክፍያዎች በተጠሪ እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው የስራ ስንብቱ ህገ-ወጥ መሆኑ ተገልጾ ከተወሰነ በኋላ እንዲከፈላቸው የተደረገው አመልካች የጠየቋቸው ክፍያዎች ሁሉ አይደለም፡፡ በአመልካች ከተጠየቁት ክፍያዎች ውስጥ የካሣ እና ይሄው ካሣ የዘገየበት የ3/ሦስት/ ወር ደመወዝ ክፍያ በስር ፍ/ቤት በዝምታ የታለፉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የስራ ውል ከህግ ውጪ ነው የተቋረጠው እየተባለ ውጤቱ በግልጽ ዳኝነት ተጠይቆበት በዝምታ ማለፉ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን ዓላማ የሚፃረር ነው፡፡ የስራ ውል ከህግ ውጪ ሲቋረጥ የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ህጉ የደነገገው ኢንዱስትሪያላዊ ሠላምን በመጠበቅ ምርትና ምርታማነት ለማሣደግ እና ያላግባብ የሚባረርን ሠራተኛ ለመካስ ነው፡፡ በመሆኑም የስራ ውል ከህግ ውጪ መቋረጡ ከተረጋገጠ የኢንዱስትሪውን ሠላም የመጠበቅና የሠራተኛውን የመካስ መብቱን ህጉ ዓላማ ማድረጉን ግንዛቤ ውስጥ ለማስገባት ዳኝነት ሊሰጥ ይገባል በዚህ ረገድ የተቀመጡት ድንጋጌዎች ተግባራዊ የሚደረጉትም ግልጽ ዳኝነት መጠየቁን አግባብነትና ብቁነት ያለው ማስረጃ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

እኛችን ወደተያዘው ስንመለስም አመልካች ሊከፈሉኝ ይገባል የሚሏቸውን ክፍያዎች ዘርዝረው አቅርበው ተጠሪ ክፍያዎቹ አይገባም የሚልበት ምክንያት በዋናነት የስራ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ሲሆን የአመልካች የአገልግሎት ጡረታ አበል የማግኘት መብት በህጉ የተጠበቀ በመሆኑ የአገልግሎት ክፍያ ሊያገኙ አይገባም በማለትም ጭምር ነው፡፡

ይሁን እንጂ የአመልካች የስራ ስንብት ባግባቡ አይደለም ተብሎ ተወስኗል፡፡ እንዲሁም አመልካች የ24 ዓመታት አገልግሎት ያላቸው ቢሆንም በጡረታ ህግ የተመለከተውን መደበኛ የጡረታ ዕድሜ ላይ ደርሶ ከስራ የተገለሉ መሆኑ አልተረጋገጠም፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያ የማያገኙበት ህጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2(ሰ) ድንጋጌ ያገናዝባል፡፡ የስር ፍ/ቤት የስንብት ወይም የጡረታ መብት አንዱ ካልተፈፀመ አመልካች አቤቱታ የማቅረብ መብታቸው የተጠበቀ ነው በማለት መወሰኑ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገርና የተጠየቀውን ዳኝነት እንዲሁም የዳኝነት አሠጣጥ ሥርዓቱን የተከተለ አይደለም፡፡

በአጠቃላይ የአመልካች የስራ ውል የተቋረጠው በህገ-ወጥ መንገድ ነው እየተባለ በአመልካች የተጠየቁት ክፍያዎች ውስጥ የካሣ ክፍያና ይህው ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ እና የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ጥያቄዎች በዝምታ መታለፋቸውና የስራ ስንብት ክፍያ በአማራጭ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 26844 ሰኔ 26 ቀን 1999 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 58367 ጥቅምት 05 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. ተጠሪ ለአመልካች የስራ ስንብት ክፍያ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የሦስት ወር ደመወዝ ክፍያው ለዘገየበት የ3(ሦስት) ወር ደመወዝ የስራ ውል ከህግ ውጪ ስለተቋረጠ የ6(ስድስት) ወር ደመወዝ ስራ ተሰርቶ የልተከፈላቸው የ14 ቀን ደመወዝ ይከፈል ብለናል የምስክር ወረቀትም ይሰጣቸው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል
   መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰ/መ/ቁ. 40305

ታህሣሥ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ኢትዮጵያ ፐልፐና ወረቀት አ/ማ - ነ/ፈጅ አብዱልቃድር

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ታመነ ጫላ

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳዩ የጀመረው በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበር፡፡

ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት በተከሣሽ /አመልካች/ ላይ ባቀረቡት ክስ፤ አመልካች ተጠሪዎችን በጥበቃ የሥራ መደብ ቀጥሮ ሲያሰራቸው ቆይቶ ያለአግባብ ከሥራ ስላሰናበታቸው የሥራ መደባቸው በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10 መሠረት መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ቋሚ ሠራተኛ አድርጎ ወደ ስራቸው እንዲመልሳቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ ጉዳዩን ለማየት ፍ/ቤቱ ስልጣን የለውም፣ የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ ስራው ሲቃለል ማሠናበቱ አግባብ ነው፤ በመሆኑም ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪዎች በዚህ ውሣኔ ላይ ለምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የወረዳ ፍ/ቤቱን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

በዚህ ውሣኔ ላይ ተጠሪዎች ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች ተጠሪዎች የተቀጠሩት ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ መሆኑን ያላረጋገጠ በመሆኑ ተጠሪዎች ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ ሠራተኞች ናቸው በማለት አመልካች የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት የተቀጠሩ ሲሆን ስራው ሲቃለል መሠናበቻው አግባብ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪዎች ስንብት ሕገ-ወጥ ነው የመባሉን አግባብነት ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረጉ ተጠሪዎች ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተደምጧል፡፡

ከመዝገቡ እና ከክርክሩ ሂደት ተጠሪዎች ክስ የመሰረቱት በጥበቃ የሥራ መደብ ሲሰሩ ቆይተው በመሰናበታቸው የተቀጠሩበት ሥራ ቀጣይነት ያለው በመሆኑ ቋሚ ሠራተኛ ሆነው ወደ ሥራ እንዲመለሱ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ከዚህም የተጠሪዎች ክስ ተጠሪዎች ቀድሞውኑ የተቀጠሩት ለተወሰነ ሥራ ወይም ጊዜ መሆኑን ነገር ግን ሥራው ቀጣይነት ስላለው በቋሚነት ለመቀጠር የጠየቁ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ከአመልካች ክርክርና ማስረጃም ተጠሪዎች በአ/ቁ. 337/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት መቀጠራቸውን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ የአንድ የሥራ ውል በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10 ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች የተደረገ መሆኑ ካልተረጋገጠ በቀር የሥራ ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደተደረገ ይቆጠራል፤ የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ስራ መደረጉን የማስረዳት ሸክም ያለበት ደግሞ አሠሪው ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ መሆኑን የፈረሙትን ውል በማቅረብ አስረድቷል፡፡ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የሰጠው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው የሥራ ውሉ ለተወሰነ ጊዜ አልተደረገም በሚል ሣይሆን በእርግጥም አመልካች ተጠሪዎችን ሥራ ለማቃለል የቀጠራቸው ለመሆኑና ያሠናበታቸውም ሥራው በመቃለሉ መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ ነገር ግን ተጠሪዎች ለተወሰነ ጊዜ ሥራ ለማቃለል መቀጠራቸው ውሉ በሚገባ የሚያረጋግጥ ከመሆኑም በተጨማሪ ተጠሪዎች ባቀረቡት ክስ የሥራ ውላቸው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሆኑ ቀርቶ በአንቀጽ 9 መሠረት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲሆን መጠየቃቸው የተቀጠሩት አመልካች እንዳለው ሥራ ለማቃለል መሆኑን ያውቁ እንደነበርና በወቅቱ አመልካችና ተጠሪዎች የነበራቸው ሃሣብ ይኸው መሆኑን በሚገባ ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪዎች ሥራ ለማቃለል የተቀጠሩ ላለመሆኑ ያስረዱት ነገር የለም፡፡

ተጠሪዎች ሥራው ቀጣይነት አለው በማለት ያቀረቡትን ክርክር በተመለከተ ምንም እንኳን ስራው የአሠሪው ቋሚ ስራ ቢሆንም እንኳን መብዛት የሚኖርበት ጊዜ ሥራን ለማቃለል ለተወሰነ ጊዜ የሥራ ውል መፈፀም የሚቻል መሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 10/1/ሐ/ የሚፈቅድ በመሆኑ የተጠሪዎች ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች የተቀጠሩት ለተወሰነ ጊዜ በመሆኑ የአንድ ዓመት ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ ይመለሱ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 67773 በ14/11/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የምስ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 13061 በ05/02/2000 የሰጠውና የአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 16081 በ17/08/99 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. ተጠሪዎች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 10/1/ሐ/ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠሩ በመሆኑ ጊዜው ሲያልቅ መሠናበታቸው ሕጋዊ በመሆኑ ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 40804

ጥር 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዳንዲቦሩ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ - ጠበቃ እስክንድር ዘውዴ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች**፡-1/ ተክሉ ኡርጋ ኢደኤ - ቀረቡ፡፡

2/ ቶሎሳ መገርሳ ባልቻ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የአሠሪና ሠራተኛ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት የአሁኖች ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረቱት የስራ ውላችን ከህግ ውጭ አቋርጦብናል በማለት ነው ፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የሥራ ውሉ የተቋረጠው የትምህርት ሚኒስቴር ባወጣው መመሪያ መሠረት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ባለመቻሉ ነው በመሆኑም ከሕግ ውጪ የተፈፀመ ነገር የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ እንደ ክርክሩ ያስረዳል ያለውን ማስረጃ አያይዞ ስለማቅረቡ ክሱን ባስተናገደው ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ ተገልጾአል፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክርም ከሰማ በኋላ የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ በማለት ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ከዚህ ውሳኔ በመነሳትም አመልካች የስራ ውል ከሕግ ውጪ ሲቋረጥ ሊከፍሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ለተጠሪዎች ይከፈል ብሎአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔው ጉድለት የለበትም በማለት ይግባኙን ውድቅ አድርጐአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መስከረም 15 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት መገንዘብ እንደቻልነው ተጠሪዎች በአመልካች ኮሌጅ በመምህርነት ተቀጥረው ሲሠሩ የነበረ ሲሆን፣ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ተቀጥረው ሲሰሩበት የነበረው የስራ ክፍል በበቂ ምክንያት ተሰርዞአል፡፡ ሥራው የለም በማለት ነው ፡፡ተጠሪዎችም ክሱን የመሠረቱት ሥራው ስላለ ወደ ስራችን እንመለስ በማለት ሳይሆን ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነውና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ይከፈሉን በማለት ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኞች ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28(1)(መ) እንደተመለከተው ሠራተኛው ጉዳይ የያዘው የስራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲቀርብና ሠራተኛውን ወደ ስራ ቦታ ማዛወር የማይቻል ሆኖ ሲገኝ የሥራ ውሉ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ /የማስተማር ስራ/ መንግስት ባወጣው መመሪያ መሠረት መሠረዙን በማስመልከት አመልካች ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪዎችም ይሄንኑ አልካዱም መንግስት ያወጣው መመሪያ ከመስከረም ወር 2000 ዓ.ም ጀምሮ ከግል ትምህርት ተቋሞች የሚመረቁ ዕጩ መምህራን በመንግስት

የትምህርት ተቋ
ሞች እንደማይቀጠሩ መታዘዙን የሚያመለክት ነው፡፡ ተጠሪዎች ተቀጥረው ይሠሩ የነበሩትም እጩ መምራንን ማሰልጠን ነው፡፡ መመሪያው ከወጣ በኋላ ግን ለመሠልጠን ተማሪ ሊመዘገብ አልቻለም፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ የለም ማለት ነው፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች እንደመልሱ ያስረዳልኛል ያለውን ማስረጃ ከመልስ ማመልከቻው ጋር አያይዘን እንዳቀረበለት በውሳኔው ላይ ገልጿል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ መዝገቡ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ አልቀረበም፤ የሚል ምክንያት በመስጠትና ማስረጃ እንደሌለው በመግለጽ አቤቱታ የቀረበበትን ውሳኔ ሰጥቶአል፡፡ ቀደል ሲል እንደተመለከተው አመልካች በዋነኛነት የጠቀሰው ማስረጃ የመንግስት መመሪያ ነው፡፡ በመንግስት የሚወጡ ሕጐች እና መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ወዘተ በግልጽ የሚታወቁ እንደመሆናቸው ፍ/ቤቶች (ዳኞች) ግንዛቤ የሚወሰዱባቸው ናቸው፡፡ ተከራካሪ ወገን ለክርክሩ የሚጠቅመውን ሕግ ከአስረጅነት አላቀረበም በሚል ክርክሩን በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ደግሞ አመልካች ለሥራ ውሉ ማስረጃ ስለማቅረቡ ፍ/ቤቱ በሚገባ መዝግቦለታል፡፡ ጉዳዩ ለቃል ክርክር በተቀጠረበት ዕለት ነገረ ፈጁ ባለመቅረቡ ማስረጃው እንደሌለ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ ሲጠቃለል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 30239 ግንቦት 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 68312 ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ ሕግ ቁ 348 (1) መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕጋዊ መንገድ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

የሰ/መ/ቁ 36194

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-**ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ በራሳቸው እና ሞግዚት ለሆኑላት ለህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ጠበቃ አዳሙ ሽፈራው ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪ፡-** ፍሬድሪክ ኤቨርት ሲቲፍቱንግ- ጠበቃ መሐሪ ዓለማየሁ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ፡ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሆኖ የጉዳት ካሣንና ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎችን የሚመለከት ነው ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ አመልካች የካቲት 02 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ የአመልካች ህጋዊ ባለቤት እና የህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ወላጅ እናት የሆኑት ሟች ዶ/ር ሠብለ ደምሰው በተጠሪ መ/ቤት ከሚያዝያ 25 ቀን 1996 ዓ.ም ጀምሮ በፕሮጀክት ስራ አስተባባሪነት የሥራ መደብ በወር ደመወዝ ብር 4500.00/አራት ሺህ አምስት መቶ ብር/ በሠራተኛነት ተቀጥረውና ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም ከደመወዛቸው በተጨማሪ እየተከፈላቸው በማገልግል ላይ እያሉ ተጠሪ ለመስክ ስራ ወደ አዋሣ ልኳቸው ወደ አዲስ አበባ በመመለስ ላይ እንዳሉ ተጠሪ ለመስክ ስራ በግልፅ የመደበው መኪና ነሐሴ 09 ቀን 1997 ዓ.ም ተገልብጦ ዶ/ር ሠብለ ደምሠው ህይወታቸው በአደጋው ወዲያውኑ ማለፍን በመጥቀስ የጉዳት ካሣ፣ የቀብር ማስፈፀሚያ፣ የስንበት ክፍያ እንዲሁም የዓመት ፈቃድ ክፍያ እና ክፍያው ለዘገየበት ከበቂ ኪሣራ ጋር እንዲከፈላቸው ይወሰንላቸው ዘንድ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በተጠሪ ላይ በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው ፡፡ የአሁኑ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርቦ የሟች የስራ ቅጥር ውል ባለመሆኑ በስራ ክርክር ችሎት ሊታይ እንደማይገባውና ሟች የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቅጥር ሆነው በተከሣሽ ድርጅት የነበራቸው የአገልግሎት ውል መሆኑን በመግለፅ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የተከራከረ ሲሆን በፍሬ ነገር ረገድም ሟች ህይወታቸው ባሉ ጊዜ ከተከሣሽ ጋራ ውል ያልነበራቸው መሆኑን ፣ ህይወታቸው ባለፈበት ጊዜም ወደ መስክ የሄዱት ከተከሣሽ ድርጅት ጋራ ለስራ ውል ግንኙነት ሣይኖራቸው አንደኛ አመልካች ባለቤታቸው በመሆናቸው አንድ ላይ ለመሄድ ፈልገው መሆኑን፣ የመኪና መገልበጥ አደጋው የደረሠውም በተከሣሽ ድርጅት የተመደበ ሹፌር እያለ የስር አንደኛ ከሣሽ አላግባብ መኪናውን ከሹፌሩ በመቀበል በማሽከርከራቸው በመሆኑ ተከሣሽ ድርጅት ለአደጋው ኃላፊ ሊባል እንደማይገባና የተጠየቁትን ክፍያዎችም የስራ ውል ግንኙነት ሣይኖር የሚከፍሉበት ህጋዊ ምክንያት አለመኖሩን ሚያዝያ 04 ቀን 1998 ዓ.ም በፃፈው የመከላከያ መልስ ማመልከቻ ዘርዝሮ ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር እና ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ በተጠሪ በኩል በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት የቀረቡትን የክርክር ነጥቦች ውድቅ በማድረግ በሟችና በተጠሪ መካከል የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የነበረ መሆኑን ተረጋግጧል በማለት ድምዳሜ ከደረሠ በኋላ የጉዳት ካሣውን በተመለከተ አደጋው በደረሠ ጊዜ መኪናውን የሟች ባለቤት የሆኑት አንደኛ አመልካች ሲያሽከረክሩ ስለነበር በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ነው ሊባል አይችልም በማለት በዚህ ረገድ የቀረውን የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ አድርጐ ተከሣሽ ድርጅት የስንብት ክፍያ ብቻ ሊከፈል እንደሚገባ በመግለፅ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ይግባኛቸው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ተሠርዞባቸዋል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ መጋቢት 02 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- የጉዳት ካሣውም ሆነ የቀብር ማስፈፀሚያ ክፍያ እንዳይከፈል የተባለው በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 96(1) ስርና ተከታዩቹ ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ መሆኑን አንደኛ የሠበር አመልካች ጥፋት የለባቸውም አለባቸው ቢባል እንኳ የሁለተኛ አመልካች የካሣ ጥያቄ ውድቅ የሚሆንበት አግባብ አለመኖሩን፣ የሟች የቀብር ማስፈፀሚያ የተከላከለውም ህጋዊ መሠረት ሣይጠቀስ መሆኑንና ፣ ሟች ያልወሠዱት የዓመት እረፍት ክፍያ ውድቅ የተደረገውም የሠበር ተጠሪ ባልተከራከርንበትና ባላስረዳ ሁኔታ መሆኑን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ የሞት ጉዳት ካሣ ብር 270,000.00(ሁለት መቶ ሰባ ሺህ) ፣ የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ የሟችን የሁለት ወር ደመወዝ፣ ያልተወሰደ የዓመት እረፍት የሟች የሁለት ወር ደመወዝ እና ተጠሪው ክፍያ ላዘገየበት የሟች የሶስት ወር ደመወዝ ለሠበር አመልካቾች ተከፍሎ እስከ ሚጠናቀቅ ድረስ ከሚታሠብ ወለድ ጋር እንዲከፈል ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ በሠበር ችሎት ሊታይ ይገባዋል ተብሎ በመታዘዙም፤ የተጠሪ ጠበቃ ሰኔ 19 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሱን አቅርበዋል፡፡ በመልሣቸውም የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ማየቱ ተገቢ ያልነበረ ስለመሆኑና ሟች የተጠሪ መደበኛ የቅጥር ሠራተኛ ያልነበሩ ስለመሆናቸው፣ የስር ፍርድ ቤት ጉዳዩን ካየም ሟች ዶ/ር ሠብለ ደምሰው ከተጠሪ ጋር ባደረጉት የአገልግሎት ውልም መሠረት መወሠን የነበረበት ስለመሆኑ፣ የሟች የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መደበኛ ተቀጣሪ ሆነው ከተጠሪ ዘንድ በተወሠነ ጊዜ በተደራቢነት አገልግሎት መስጠታቸው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት ከተጠሪ ጋር የቅጥር ውል ነበራቸው ሊባል የማይገባ ስለመሆኑ፣ ሟች የአገልግሎት ውልም ቢሆን ሟች በ09/12/1997 ከመሞታቸው አንድ ወር ተኩል ቀደም ብሎ በ23/10/97 ያበቃ ስለመሆኑ፣ ሟች የሞቱት በስራ ላይ ባልነበሩበትና መኪናውን ለማሽከርከር ከተጠሪ ፈቃድ ባልተሠጣቸው  በአንደኛ አመልካች አላግባብ ሲሽከረከር ስለመሆኑ ተጠያቂነትም ቢኖር ክስ አልቀረበበትም እንጂ ከውል ውጪ ባለ ኃላፊነት ስለመሆኑ ይህንን ዓይነት አደጋ ሲያደርስ ሟች ሊካሱ እንዲችሉ ተጠሪ በአገልግሎት ውሉ መሠረት በየወሩ ለሟች ብር 200 የመድን ሂሣብ ለራሣቸው ይከፈል የነበረ ስለመሆኑ፣ የቀረቡት የክፍያ ጥያቄዎች የህግ መሠረት የሌላቸው ስለመሆኑ በመዘርዘር የአመልካቾች የሠበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ በቂ ወጪና ኪሣራ እንዲከፈል ይወሰን ዘንድ ተከራክረዋል፡፡ የአመልካቾች የተጠሪ ጠበቃ መከራከሪያ ነጥቦች ሥነ ሥርዓቱን ጠበቃው ያልቀረቡ መሆኑን በመለየትና ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን በመዘርዘር የሠበር አቤቱታቸውን አጠናክረው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ የቃል ክርክር እንዲያደርጉ ታዝዞ ክርክራቸው ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ እና የቃል ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ከላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝቦ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም አደጋው የደረሠው አንደኛ የሠበር አመልካች ያላግባብ መኪናውን ከሾፌሩ በመቀበል ሲያከራክሩ ነው ተብሎ ተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት የለበትም መባሉ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ? በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ህይወታቸው ያለፈው የተጠሪ መስሪያ ቤት ንብረት የሆነው መኪና ለመስክ ስራ ከሄደበት ቦታ በመመለስና በአንደኛ የሠበር አመልካች በመሽከርከር እያለ በመገልበጡ ምክንያት መሆኑን፣ በሟችና በተጠሪ መካከልም የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙት መኖሩ ተረጋግጧል ተብሎ በስር ፍ/ቤት መወሠኑን፣ አንደኛ አመልካች በተጠሪ መስሪያ ቤት የስራ ግንኙነት ያላቸው መሆኑንና ሁለተኛ ተጠሪ አካለ መጠን ያላደረሠች የሟች ተወላጅ መሆናቸውን ነው የስር ፍ/ቤት የሟችና የተጠሪ ግንኙነት በአሠሪና ሠራተኛ የሚፈረጅ መሆኑን በመደምደምም ተጠሪ የስራ ስንብት ክፍያ ሊከፍል እንደሚገባ በውሣኔው ላይ መግለፁን ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የሟችና የተጠሪ ግንኙነት በሚያዝያ 25 ቀን 1996 ዓ.ም በተደረገ ውል መቋቋሙን፣ በዚህ ውል መሠረት ግንኙነታቸው እስከ ጥቅምት 21 ቀን 1997 ዓ.ም ቆይቶ ከጥቅምት 22 ቀን 1997 ዓ.ም በኋላ ግን የስራ ቅጥር ስምምነት ለመዋዋል እንደሚያቅዱ መስማማታቸውን፣ ከዚህ በኋላ ተደረገ በተባለ ማሻሻያም የውል ግንኙነት እስከ ሠኔ 23 ቀን 1997 ዓ.ም ድረስ መራዘሙን እንዲሁም ከሚያዝያ - ነሐሴ ወር 1997 ዓ.ም ላሉት ጊዜያት በውሉ ላይ የተመለከቱት ክፍያዎች በሟች ስም ተሠርተው ለአንደኛ አመልካች መከፈላቸው በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮችም ሟች ለመስክ ስራ የሚያስፈልጋቸው የውሎ አበል ክፍያ ተከፍሏቸው ለስራው የሄዱ መሆኑ መመስከራቸውን ነው፡፡ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡት ጉዳዬች እነዚህ ሆነው የሰበር ተጠሪ ሟች ጋር የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የለንም በማለት

ለሠበር ችሎቱ በሠጠው የጽሁፍና የቃል ክርክር ያቀረበውን ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ መሆን ያለመሆኑን መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡

የተጠሪ ጠበቃ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሚችንና የተጠሪን ግንኙነት አስመልክቶ በቀረበው ክርክር የተጠሪን ክርክር ባለመቀበል በመካከላቸው የነበረው ውል ከአሠሪና ሠራተኛ የሚመነጭ ዓይነት ውል ስለመሆኑ በመጥቀስ ውሣኔ መስጠቱን አምነው በዚህ ነጥብ ላይ ለበላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያላቀረቡት ለሟቹ ይከፈል የተባለው የስራ ስንብት አነስተኛና የተጠሪን መብት የማይጉዳ ስለሆነ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ በአንድ የፍ/ቤት ውሣኔ ይግባኝ ለበላይ ፍ/ቤት የሚቀርበው ውሣኔው ወይም ትዕዛዙ የይግባኝ አቅራቢውን መብት ወይም ጥቅም የነካ ፣ አሊያም ግዴታው ከፍ እንዲል ያደረገ ሆኖ ሲገኝ ስለመሆኑ ስለ ይግባኝ አቀራረብ የተደነገጉት የፍትሐብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎች የሚያስገነዝቡት ጉዳይ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የሚችንና የተጠሪ ግንኙነት የስራ ቅጥር ግንኙነት ስለመሆኑ በመቀበል የስራ ስንብት ክፍያ እንዲከፍል መወሠኑ የተጠሪን መብት ወይም ጥቅም የነካ አይደለም ሊባል የማይችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ የተጠሪ ጠበቃ በሥርዓቱ መሠረት በጉዳዩ ላይ ቅሬታ ሣያቀርቡ በተጠሪና በሚች መካከል የስራ ቅጥር ግንኙነት የለም በማለት በሠበር ደረጃ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በዚህ ረገድ የቀረበው ክርክር ሥነ-ሥርዓታዊ ካለመሆኑም በላይ ሟች አደጋው በደረሠባቸው ወቅት ለመስክ ስራ የሄዱት ከተጠሪ መስሪያ ቤት አበል ተከፍሏቸው ነው ተብሎ ከተረጋገጠው ፍሬ ጉዳይ አኳያ ተቀባይነት የለውም ሟች በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቋሚ ሠራተኛ መሆናቸውም ከተጠሪ ጋር የስራ ቅጥር ግንኙነት ለማድረግ የሚከለክላቸው አለመሆኑን የአዋጅ ቁጥር 351/1995 አንቀጽ 24 ድንጋጌ በግልፅ ያሣያል፡፡ በመሆኑም በሚችና በተጠሪ መካከል ነበረ የተባለውን ግንኙነት በተመለከተ የተጠሪ ጠበቃ ያነሡት መከራከሪያ ሥነ-ሥርዓቱን ያልጠበቀና የግራ ቀኙን የማስረጃዎች ይዘት እንዲሁም ስለከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የወጣውን አዋጅ ያላገናዘበ በመሆኑ አልፈነዋል፡፡

ወደ ዋናው ጭብጥ ስንመለስም ሟች ህይወታቸው ያለፈው ተጠሪ ለመስክ ስራ የመደበውን መኪና ከተጠሪ ሹፌር አንደኛ አመልካች በመቀበል ሲያሽከረክሩ መሆኑ በግራ ቀኙ ያልተካደ ጉዳይ ነው፡፡ አንደኛ አመልካች በወቅቱ ወደ መስክ የሄዱት ከተጠሪ ፍላጐት ውጪ ነው ከመባሉ በስተቀር የተጠሪ ሠራተኛ መሆናቸው አልተካደም፡፡

እንግዲህ ሟች የሞቱት 1ኛ አመልካች መኪናውን ሲያሽከረክሩ መሆኑ አሠሪ የሆነውን ተጠሪ ከአላፊነት ያድንዋል ወይ? የሚለው ጥያቄ ሊመረመር የሚገባው ነው፡፡

በመሠረቱ በስራ ምክንያት ለሚመጡ ጉዳቶች አሠሪው አላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ በስራ ምክንያት የሚመጣ ጉዳት ከሆነ አሠሪው አላፊነቱን እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን በአዋጁም በስራ ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት በስራ ላይ የሚደርስ አደጋ ወይም በስራ ምክንያት የሚመጣ በሽታ መሆኑን በቁጥር 95(2) ደንግጓል በአዋጅ አንቀጽ 96(1) "አሠሪው ጥፋት ባይኖረውም….." ተብሎ መመልከቱ የአሠሪው የአላፊነት ዓይነት ጥፋት ሣይኖር አላፊነት /Strict Liability or Liability in the absence of Fault/ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ አሠሪው ከዚህ ዓይነት አላፊነት የሚድነው ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ ሆነ ብሎ በራሡ ላይ ያደረሠው ጉዳት መሆኑን ማስረዳት ሲችል ስለመሆኑ አንቀጽ 98(2) ያስገነዝባል፡፡ሆነ ብሎ ያደረሠው ጉዳት የሚባሉት ሁኔታዎችም ሠራተኛው አስቀድሞ በግል የተሠጡትን የደህንነት መጠበቂያ መመሪያዎችን መጣስ ወይም የአደጋ መከላከያ ደንቦችን መተላለፍ ወይም አካሉን ወይም አእምሮውን በሚገባ ለመቆጣጠር በማይችልበት ሁኔታ በመጠጥ ወይም በአደንዛዥ እፅ ሠክሮ በሥራ ላይ መገኘት መሆናቸውን ህጉ በቁጥር 96(2(ሀ እና ለ)) ስር አመላክቷል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 97(1) ድንጋጌ ሲታይም አንድን አደጋ በስራ ላይ የደረሠ ነው ለማለት ሠራተኛው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ ወይም ከስራው ጋር ግንኙነት ባለው ሁኔታ ከራሡ ውጭ በሆነ ምክንያት ወይም ስራውን ለማከናወን ባደረገው ጥረት ምክንያት በአካሉ ወይም በአካሉ በማንኛውም ክፍል ተፈጥሮአዊ እንቅስቃሴ ላይ በድንገት የደረሠበት ጉዳት ስለመሆኑ መርሁን ያስቀመጠ ሲሆን ይኸው ድንጋጌ ከፊደል (ሀ) እስከ ፊደል (መ) በተመለከቱት ንዑስ ድንጋጌዎች የተመለከቱት ምክንያቶች በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ተብለው የሚጨመሩ ስለመሆኑ ያሣያል፡፡ ስለሆነም በመርሁ መሠረት ሠራተኛው የጉዳት ካሣ ለማግኘት ማሣየት የሚጠበቅበት አደጋው ስራውን በማከናወን ላይ እያለ

የደረሠ መሆኑን፣ ወይም ደግሞ በራሡ ባልሆነ ምክንያት ግን ከሥራው ጋር ግንኙነት ባለው መልኩ የደረሠበት አደጋ መሆኑን ነው ።ከላይ እንደተገለፀው ከስራ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሁኔታዎች ምን እንደሆኑ ህጉ አስቀምጧል። ለዚህ ጉዳይ ቀጥተኛ አግባብነት ያለው ድንጋጌ በአንቀጽ 97(1(ሐ)) ስር የተመለከተው ሲሆን በዚህ ድንጋጌ መሠረት አሠሪው በመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት ሠራተኛው ሲጠቀም ጉዳት ከደረሠ አደጋው በስራ ላይ እንደደረሠ ተቆጥሮ ኣላፊነቱን ከአሠሪው ሲወሰድ የሚገባ መሆኑ ተመልክቷል። ይኸው ድንጋጌ አሠሪው የመደበው የመጓጓዣ አገልግሎት አደጋው ከደረሠበት በአሰሪው ስር ባለው ሌላ ሠራተኛ ወይም 3ኛ ወገን ከሆነ አሰሪው ለተጐጂው ሠራተኛ የጉዳት ካሣ ኣላፊነት የሌለበት ስለመሆኑ አያሣይም ይልቁንም ድንጋጌው በአዋጁ አንቀጽ 96(1) ስር ከተመለከተው የአሠሪ ኣላፊነት ዓይነት ጋር ተዳምሮ ሲታይ አሠሪው ኣላፊነት ያለበት መሆኑን የሚያጠናክር ነው በሌላ አገላለፅ በሠራተኛው ላይ ጉዳት ያደረሠው ሠራተኛው ወደ ስራ ሲሄድና ከስራ ወጥቶ ወደ ቤቱ ሲመለስ አሠሪው በመደበው የመጓጓዠ አገልግሎት ሲጠቀም አደጋ የደረሠበት መሆኑ ከተረጋገጠ 3ኛ ወገኖች ለአደጋው ያደረጉት አስተዋጽኦ ለአሰሪው መከላከያ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም አንደኛ አመልካች የተጠሪን መኪና በወቅቱ ሲያሽከረክሩ የነበሩ መሆኑ መረጋገጡ ተጠሪን ነፃ ሊያደርገው የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የስር ፍ/ቤቶች አደጋው የደረሠው በስራ ምክንያት አይደለም ሲሉ የደረሠበት ድምዳሜ ከላይ የተመለከተቱን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል።

ተጠሪ ለጉዳቱ ኣላፊነት አለበት ከተባለ የጉዳት ካሣ መክፈል ያለበት ለየትኞቹ የተጐጂ ጥገኞች? የሚለው ጥያቄም በህጉ አግባብ መታየት ያለበት ነው። ለዚህ ጥያቄ ምላሽ የሚሠጠው ድንጋጌም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107(1(ሐ) ስር ተመልክቷል። በዚህ ድንጋጌ መሠረት ማንኛውም በስራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሠበት ሠራተኛ የሞተ እንደሆነ ለጥገኞች የጡረታ አበል ወይም ዳረጐት ወይም ካሣ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ ተመልክቷል።የአዋጁ አንቀጽ 110 ድንጋጌ ሲታይም ለሟች ሠራተኛ ጥገኞች የሚከፍሉትን የክፍያ ዓይነቶቹንና ጥገኛ የሚባሉትን ወገኖች በንዑስ ቁጥር አንድና ሁለት በግልፅ ዘርዝሯል። በዚህም መሠረት ማንኛውም ሠራተኛ ወይም ለማጅ ሠራተኛ በስራ ምክንያት በደረሠበት ጉዳት የተነሣ የሞተ እንደሆነ የጉዳት ካሣ ለጥገኞች፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት ወጪ እንደሚከፈልና ጥገኞች የሚባሉትም የሟች ህጋዊ ባል ወይም ሚስት፣ ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች የሆኑ የሟች ልጆችና በሟች ሠራተኛ ድጋፍ ይረዱ የነበሩ የሟች ወላጆች ስለመሆናቸው ተመልክቷል። ይሁን እንጂ ህጉ ጥገኝነት ማለት ምን እንደሆነ ትርጓሜ ያልሠጠበት ሲሆን ከህጉ አቀራረፅና ይዘት በመነሣት ግን የቃሉን ትርጉም ለመገንዘብ አያዳግትም። በመሆኑም በህጉ የተመለከተው ጥገኞች የሚለው ቃል ከሟች የምግብ፣ የመጠለያ፣የልብስና ለጤናው አጠባበቅ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን እንዲሟላላቸው የሚጠይቁትን ወገኖችን የሚመለከት ስለመሆኑ ተገንዝበናል ሥራ ሠርቶ እራሡን ለማስተዳደር የሚችልና ችግረኛ መሆኑ በቅድሚያ ያልተረጋገጠበት ወገን የሟች ሠራተኛ ባል ወይም ሚስት በመሆኑ ብቻ የጉዳት ካሣ የሚያገኝበት ምክንያት አይኖርም። ከጉዳት ካሣ ዓላማ ጋርም አንድ ላይ ይሄዳል ተብሎ አይታሠብም። ስለሆነም የሟች ሠራተኛ ባል ወይም ሚስት መተዳደሪያ የሚሆነው በቂ ሀብት ካለው ጥገኛ ሊባል አይችልም። ከዚህም በተጨማሪ በአንቀጽ 110(1) እና (2) የተመለከቱት ድንጋጌዎች አቀራረፅና ይዘት እንዲሁም በዘርፍ መሠረት የሚደረጉ ክፍያዎች ከገቢ ግብር ነፃ መሆናቸው፣ ሊተላለፍ፣ ሊከበር ወይም በዕዳ ማቻቻያነት ሊያዝ አለመቻሉ በአዋጁ አንቀጽ 112 ስር መመልከቱ የጉዳት ካሣ ዓላማው መተዳደሪያ የሚሆነው በቂ ሀብት የሌለውን የሟች ሠራተኛ ለመደገፍ የታሠበ ነው የሚለውን ክርክር የሚያጠናክር ነው ።

ወደ ተያዘው ጉዳይ ስንመለስም አንደኛ አመልካች የሟች ባል ቢሆኑም በቂ የሆነ መተዳደሪያ ሀብት ያላቸው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት ያሣያል። ስለሆነም አንደኛ አመልካች የሟች ጥገኛ ባለመሆናቸው የጉዳት ካሣ የሚያገኙበት ህጋዊ ምክንያት የለም።

ሁለተኛ አመልካችን በተመለተ ግን የሟች ልጅና በህጉ አግባብም የሟች ጥገኛ መሆኗ ስለተረጋገጠ የጉዳት ካሣ የሚገባት ሆኖ ተገኝቷል።

የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ ክፍያ የስር ፍ/ቤት ያለው አደጋው የደረሠው በስራ ምክንያት አይደለም። በሚል ነው። ሆኖም ከላይ እንደተመለከትነው ተጠሪ በአሠሪነቱ ኣላፊነት አለበት ተብሏል። ስለሆነም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(1(ለ) መሠረት የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈፀሚያ የመክፈል ኣላፊነት ያለበት ሆኖ ተገኝቷል። የዓመት ፈቃድ ክፍያን በተመለከተ በበታች ፍ/ቤቶች የተሠጠ ውሣኔ የሚነቅፍ ሆኖ አልተገኘም።

በሌላ በኩል የስር ፍርድ ቤት ውሣኔ የሠጠው አላፊነትን መሠረት በማድረግ በመሆኑ የጉዳት ካሣ መጠኑን አልወሠነም ከላይ እንደተመከለተው ተጠሪ ለጉዳቱ አላፊነት ያለበት የሟች ልጅ ለሆነችው ሁለተኛ አመልካች የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት ያለበት መሆኑን ተገልጿል፡፡ ለጥገኞች የሚከፈል የጉዳት ካሣ መጠን በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 110(3) እና (4) ስር ተመልክቷል ፡፡ ስለሆነም የካሣ መጠኑን በተመለከተ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን እንደገና ተመልክቶ እንዲወሰን ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

**<u>ውሣኔ</u>**

1/ አላፊነትን በተመለተ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ 21716 ሠኔ 25 ቀን 1999 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌዴራሉ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 58497 ታህሣሥ 30 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው የውሣኔው ክፍል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የስር ፍርድ ቤት የዓመት እረፍት እና የስንብት ክፍያን በተመለከተ የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ ሟች የሞቱት በስራ ላይ የደረሠ አደጋ ነው ሊባል በሚችል ምክንያት በመሆኑ ተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል አላፊነት አለበት ብለናል፡፡

4/ ተጠሪ የሟች የቀብር ሥርዓት ማስፈፀሚያ የመክፈል አላፊነት አለበት ብለናል፡፡

5/ አንደኛ አመልካች፤ ዶ/ር ማንደፍሮ እሸቴ የሟች ጥገኛ ባለመሆናቸው የጉዳት ካሣ አይገባቸውም ብለናል፡፡

6/ ሁለተኛ አመልካች ህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ የሟች ጥገኛ በመሆኗ የጉዳት ካሣ ሊከፈላት ይገባል ብለናል፡፡

7/ ለህፃን ጀሲካ ማንደፍሮ ሊከፈላት የሚገባትን የካሣ መጠንና የሟች የቀብር ሥነ ሥርዓት ማስፈፀሚያ መጠንን በተመለከተ የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን በመመርመር ተገቢውን ይወስን ዘንድ ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

8/ በዚህ ችሎት በተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

የሰ/መ/ቁ 38811

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ርሆቦት ሆሊሴቪየር ኃ/የተ/የግ/ማ ጠ/ተስፋዬ ክትላ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ አማረ አድማሱ ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሥራ ክርክር ችሎት የጀመረ ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ በዚሁ ፍ/ቤት በቀረቡት ክስ አመልካች በህገ-ወጥ መንገድ የሥራ ውላቸውን ስላቋረጠው ወደ ስራ እንዲመልሣቸው የማይመልሳቸው ከሆነ ግን የተያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸውና የስራ ም/ወረቀት እንዲሠጣቸው ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪ ላቀረበበት ክስ የስራ መሪ በመሆናቸው ክሱ በዚህ ፍ/ቤት ሊቀርብ አይገባም በማለት ከተቃወሙ በኂላ በድርጅቱ በደተረገው የመዋቅር በውስጥ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙና ተጠሪን ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛውሮ ማሠራት ባለመቻሉ ማሠናበቱንና ይህም ስንብት ህጋዊ እርምጃ በመሆን የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም አመልካች የማስጠንቀቂያና የስራ ስንብት ክፍያ ለተጠሪ ፈጽሟል የም/ወረቅትም ሠጥቷል በማለት ለፍሬ ጉዳዩ መልስ ሰጥቷል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ተጠሪ የሥራ መሪ የሚያከናውነው ተግባር ላይ የተሠማሩ ስለመሆናቸው ማስረጃ ስላላቀረበ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም የድርጅቱን ወጪ በመቀነስ የአመልካች የመደበኛ ት/ቤቶች ሀላፊነት የስራ መደብ መሠረዙን ያስረዳ ቢሆንም ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ አዛውሮ ማስረዳት አለመቻሉን የሚያስረዳ ማስረጃ ስላላቀረበ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ስለሆነም የ2 ወር ደመወዝ ከፍሎ ተጠሪን ወደ ስራቸው ይመልሣቸው በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይርባኝ ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኂላ ስንብቱ ህገ-ወጥ በመሆኑ የ2 ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ ይመለሱ የሚለውን ውሣኔ ያፀና ሲሆን ነገር ግን አመልካች ለተጠሪ የ2 ወር የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የስንብት ክፍያ የከፈለ ለመሆኑ በማስረጃ ስለተረጋገጠ ተጠሪ ወደ ስራ ከተመለሱ የተቀበሉትን ክፍያ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል በማለት ወስኗል፡፡

የአሁኑ የአመልካች አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን ተጠሪ የስራ መሪ ናቸው በተደረገው የመዋቅር መሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ የተሠረዘና ወደ ሌላ የስራ መደብ አዛወሮ ማሰራት ባለመቻሉ የስራ ውሉ መቋረጡ በአግባቡ ነው በማለት ቅሬታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የአመልካች አቤቱታ ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ተጠሪ ጥቅምት 18/2001 የተፃፈ መልስ አቅርበዋል ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና ከህጉ ጋር አገናዝቦ መርምሯል፡፡

በመጀመሪያ አመልካች ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው በማለት ያቀረበውን ቅሬታ ስንመለከት የተጠሪ የስራ ኃላፊነት የስራ መሪ የሚሠኛቸው ነው ወይስ አይደለም የሚለው በማስረጃ የሚረጋገጥ የፍሬ ነገር ጉዳይ እንደመሆኑ አመልካች ይህንኑ የማስረዳት ሸክም አለበት ነገር ግን ከመዝገቡ እንደተረዳነው በስር ፍ/ቤት አመልካች ይህንን ለማስረዳት ያቀረበው ማስረጃ የለም በመሆኑም በዚህ በኩል ያቀረበው የሠበር አቤቱታ ተቀባይነት የለውም፡፡

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንገባ አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን እንመለከታለን ተጠሪ ከስራ የተሠናበትኩት በህገ-ወጥ መንገድ ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ በተደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ በመሠረዙ በመሆኑ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ከመዝገቡ እንደተረዳነው አመልካች የድርጅቱን ወጪ ለመቀነስ ባደረገው የመዋቅር ማሻሻያ የተጠሪ የስራ መደብ መሠረዙን አመልካች አስረድቷል የሥር ፍ/ቤቶች ይህንን ካረጋገጡ በኋላ የሥራ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው ያሉት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል መሆኑን አላስረዳም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት አንድ ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ከስራ የሚሠናበተው የያዘው የሥራ መደብ በበቂ ምክንያት ሲሠረዝና ሠራተኛውን ወደ ሌላ ሥራ ማዛወር የማይችል ሆኖ ሲገኝ ነው በተያዘው ጉዳይ የተጠሪ የሥራ መደብ በመዋቅር ማሻሻል ምክንያት የተሠረዘ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የሥራ መደብ የተሠረዘው በበቂ ምክንያት ነው በሌላ በኩል ግን አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ የሥራ መደብ መዛወር አለመቻሉን የገለፁ ሲሆን ተጠሪ በቃራኒው አመልካች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ሊያሠራቸው የሚችል መሆኑን ገልፀው አልተከራከሩም በዚህ  በሠበር ችሎት በሠጡት መልካም ቢሆን በአንቀፅ 28/1/መ/ መሠረት የሥራ ውሉ ሲቋረጥ ማስጠንቀቂያ ሊሠጣቸው ሲገባ አመልካች ማስጠንቀቂያ አለመሰጠቱ ስንብቱን ህገ-ወጥ ያደረገዋል በማለት ከሚከራከሩ በቀር በአመልካች ድርጅት ውስጥ ተዛውረው ሊሠሩበት የሚችሉበት የሥራ መደብ እያለ የሥራ ውላቸው ሊቋረጥ እንደማይገባ ገልፀው አልተከራከሩም በመሆኑም ተጠሪው ይህንን ክርክር አንስተው ሣይከራከሩ የሥር ፍ/ቤት አመልካች ተጠሪን ወደ ሌላ ቦታ ማዛወር አለመቻሉን አላስረዳም በሚል ምክንያት ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የደረሠበት መደምደሚያ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 22889 በ26/05/2000 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 63104 በ4/10/2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

3/ የተጠሪ የሥራ ውል የተቋረጠው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28/1/ መሠረት በመሆኑ ህጋዊ ነው

4/ ተጠሪ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት ከአመልካች የተቀበሉትን የማስጠንቀኪያ ጊዜ ክፍያ እና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልካቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ መልሠው ከሆነ አመልዛቹ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያና የሥራ ስንብት ክፍያ ይከፈላቸው የሥራ ምስክር ወረቀት ያልሠጣቸው ከሆነም እንዲሠጣቸው ተወስኗል፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

የሰ/መ/ቁ 38435

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ኤስ ኦ-ኤስ የህፃናት መንደር - ጠበቃ አቶ አይሸሽም መድፍ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-**
1. አቶ ከበደ ኩምሳ
2. አቶ ሚደቅሳ ተክሌ
3. አቶ ወልደጊዮርጊስ ሙለታ
4. አቶ ፋሲል ገ/ሕይወት
5. አቶ አበራ ታፈሰ
6. አቶ ጌታሁን በላቸው

} ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ክርክር የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው የአሁኑ ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበር፡፡ ከሳሾች ያቀረቡት ክስ በድርጅቱ በጥበቃ ሠራተኛነት ለበርካታ አመታት ስናገለግል የቆየን ሲሆን ስራውን በሌላ ድርጅት ላሠራ ወስኛለሁ በሚል ሰበብ ያለአግባብ ከስራ ውጪ የሥራ ውላችንን ያቋረጠ በመሆኑ ወደ ሥራችን እንድንመለስ፣ የማይመልሰን ከሆነ ካሳና ጥቅማጥቅም እንዲከፈል ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አመልካችም መጋቢት 5 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው መልሱ የድርጅቱን አሰራር ለማሻሻል ከሳሾች ይሠሩበት የነበረውን የጥበቃ ሥራ የጥበቃ አገልግሎት ለሚሠጥ "ትረስት የጥበቃና የሰው ኃይል አገልግሎት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር" ከተሰኘው ድርጅት ጋር ውል በማድረግ ሥራውን ያስተላለፈ መሆኑን በመግለጽ የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 11314 በ13/9/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እና የእረፍት ጊዜ ክፍያ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በዚህ በፍ/ቁጥር 67186 ሰኔ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሰናበቱ ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ ለማጣራት ያስቀርባል እንደገና ተመልሶ እና ትዕዛዙ የ6 ወር ካሳ ክፍያን አይመለከትም ሌሎች ውሳኔዎችን አጽንቼአለሁ ሲል ትዕዛዝ በመስጠቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው ዋና ቅሬታ ስንብቱ የድርጅቱን ምርታማነት ለማሳደግ የአሠራር ዘዴ ለመለወጥ የተደረገ በመሆኑ ከሕግ ውጪ ነው መባሉና የ6 ወር ደመወዝ ካሳ እንዲከፈል የተሠጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ እንዲሻርልን የሚል ነው፡፡

በዚህ ፍ/ቤትም የተጠሪዎች ስንብት ያለአግባብ ነው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ በአግባቡ መሆኑ አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ ተጠሪዎች ሐምሌ 22 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ መልስ በማቅረብ ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል፡፡እኛም የግራ ቀኙን ክርክር በሕግ ረገድ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

የሥራ ውል ሊቋረጥ የቻለው ተጠሪዎች ይሠሩብት የነበረው የጥበቃ ሥራ ለሌላ የጥበቃ አገልግሎት ለሚሠጠው ድርጅት በመተላለፍ ምክንያት እንደሆነ በተጠሪዎችም አልተካደም ። ይህ ከታመነ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 28 መሠረት አሠሪው አዲስ አሰራርን ለመከተል የድርጅቱን ምርታማነት ለማሻሻልና የአሠራር ዘዴዎች በመለወጡ ምክንያት ሠራተኞቹ ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ ቢሠረዝ አሠሪው ማስጠንቀቂያ በመስጠት የሥራ ውል ለማቋረጥ እንደሚችል በግልጽ ተደንግጓል፡፡ የበታች ፍ/ቤት ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው ለማለት መሠረት ያደረገው አመልካች የጥበቃ ሥራ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን ተደርጓል ከሚል በስተቀር የሥራ መደቡ ተሠርዟል የሚል ባለመሆኑ በአዋጅ አንቀጽ 28 ትርጉም ሊሠጠው የሚችል አይደለም የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት ነው፡፡ በመሠረቱ አመልካች የሥራ መደቡን ለሌላ ድርጅት ሲሠጥ የጥበቃዎቹ ቅጥር፣ዕድገት፣ዝውውር፣ስንብትና ክፍያ የሚፈፀመው በዚያው ድርጅት ነው ። አመልካች የሥራ መደቡን ሠርዞ ያስተላለፈ በመሆኑ በቃል የክፍያ ስምምነት በማድረግ ለድርጅቱ የሚከፍል ስለሆነ ሥራው የሚያከናውነው በሌላ ድርጅት ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ በተያዘው ጉዳይ ለውሳኔው መሠረት መሆን የሚገባው የሥራ መደቡ መሠረዝ ወይም አለመሠረዝ ብቻ ሳይሆን ስንብቱ ሕጋዊ ነው ወይንስ ከሕግ ውጪ ነው የሚለው ጭብጥ ሆኖ አመልካች የመልስ ሰጭዎችን/የተጠሪዎችን/ የሥራ ውል ለማቋረጥ ሕጋዊና በቂ ምክንያት መኖሩን ማስረዳት ነው፡፡ አመልካች አከራካሪ የሆነውን የሥራ መደብ ለሌላ አካል ማስተላለፍን ተጠሪዎች በክስ ማመልከቻቸውም ላይ የጠቀሱትና ያልተካደ በመሆኑ ሥራን ለሌላ ማስተላለፍ /0ut sourcing/ ሕጋዊ ነው፡፡ ይህ ከሕግ ወጪ ነው የሚል ወገን አለመተላለፍን ማስረዳት ብቻ ነው፡፡ ይህ ክርክር የለም ምናልባት አመልካች ለተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሳይሰጣቸው ማሰናበቱ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ ሳይሆን ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውል ማቋረጥ ውጤቱ ለሠራተኛው ሊከፈለው የሚገባውን የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እንዲከፈላቸው ሕጉ ከሚያስገድድ በስተቀር የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደ ሚለው የተለጠጠ የሕግ ትርጉም ላይ የሚያደርስ አይሆንም፡፡

ለማጠቃለል የሥራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናውን አሳልፎ መስጠት/0ut sourcing/ በውጫዊ እይታ ሲታይ የሠራተኛውን መብት የሚነካ ቢመስልም በአሠሪና ሠራተኛ ሕግ ረገድ ሕጋዊ አሠራር ነው፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በማለት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሠናበቱ በማለት የተሠጠው ውሳኔ ከላይ በተመለከቱ ምክንያቶች መሠረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት የሚከተለውን ውሳኔ ሠጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 11314 በ 13/9/2000 ዓ.ም ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው በማለት የ6 ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሎአቸው ይሠናበቱ ሲል የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ይፃፍ፡፡
2. ስንብቱ በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 35 መሠረት የማስጠንቀቂያ ሊከፈላቸው ይገባ የነበረውን እንደየአገልግሎት ዘመናቸው አንፃር ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4. ተጠሪዎች ከ9/12/98/ እስከ ጥር 25 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ያለው የእረፍት ቅጣት ክፍያ እንዲከፈል በተሠጠው ውሳኔ ላይ የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ ፀንቷል፡፡
5. ወጪና ኪሳራ የዚህ ፍ/ቤትን ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

መ/ት

የሰ/መ/ቁ. 38023

የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - መሠረት የማነ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ብርሃኑ ደስዬ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቤት ኪራይ ውልን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው በወር ብር 8.00 /ስምንት ብር/ ኪራይ እየከፈለ ለመኖር የተከራየው ሰርቪስ ቤት ለዋናው ቤት አገልግሎት እንዲውል የተሠራ በመሆኑ እንዲለቅ ቢጠየቅ ፈቃደኛ ስላልሆነ ተገዶ ይወጣ ዘንድ ይወሰንበት በማለት ነው፡፡ ፍ/ቤቱ ከተጠሪ የቀረበውን መልስ ከሰማ በኋላ ክርክሩን መርምሮ የአመልካችን ክስ ውድቅ አድርጎአል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በበኩሉ ክርክሩን የሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ይግባኝ የተባለበትን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 19 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ያቀረበው ክስ የተሰረዘበት አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከተደረገው ክርክር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ቀደም ሲል እንደተገለፀው የግራ ቀኝ ወገኖች ግንኙነት የተመሠረተው በመሐከላቸው ተደርጎ በነበረው የቤት ኪራይ ውል ላይ ነው የቤት ኪራይ ውሉ የተደረገው ለአንድ ዓመት እንዲቆይ ታስቦ ቢሆንም፤ ለብዙ ዓመታት እንደቆየ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ አመልካችም ውሉ ላልተወሰነ ጊዜ እንደታደሰ በመቁጥር በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2966/1/ በተመለከተው መሠረት ቤቱ ይለቀቅለት ዘንድ ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ ሰጥቶአል፡፡ ተጠሪ ደግሞ ማስጠንቀቂያ ቢሰጠኝም ሌላ ተለዋጭ ቤት እስካልተሰጠኝ ድረስ ቤቱን እንድለቅ አልገደድም፡፡ በመሐከላችን የተፈረመው ውልም የሚለው ይኸው ነው በማለት የተከራከረ ሲሆን፣ የስር ፍ/ቤቶችም ይህን ክርክር በመቀበል ነው የአመልካችን ክስ የሰረዙት፡፡

ከመዝገቡ እንዳየነው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት እራሱን የቻለ የመኖሪያ ቤት ሣይሆን፤ ለአፖርታማ ተከራዮች አገልግሎት ይውል ዘንድ የተሠራ ሰርቪስ ክፍል ነው፡፡ አመልካች ሰርቪስ ቤቱ እንዲለቀቅለት እንዲሁም ውሉ ቀሪ እንዲሆን የጠየቀውም በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል የሚያበቃው ውሉ እንዲያበቃ የሚፈልገው ተዋዋይ ወገን /አከራይ ወይም ተከራይ/ አስቀድሞ በሚሰጠው ማስታወቂያ እንደሆነ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 2966/1/ ተደንግጓል፡፡ በያዝነው ጉዳይ አከራዩ አመልካች ሲሆን የቤቱም ባለቤት ነው፡፡ ተጠሪ ከአመልካች ጋር ሲነፃፀር በቤቱ ላይ የሚኖረው መብት በኪራይ የመጠቀም እንደመሆኑ ከባለሐብትነት ያነሰ ነው፡፡ ስለማይንቀሣቀስ ንብረት ኪራይ ትርጉም በያዘው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2896/1/ እንደተመለከተው ተከራይ የሆነው ወገን በጥሬ ገንዘብ ወይም በሌላ ነገር ለአከራዩ እየከፈለ

ለተወሰነ ጊዜ የሚኖርበትን ግንኙነት የሚፈጥር ነው፡፡ ይህ ግንኙነት ደግሞ ዘለዓለማዊ ወይም ማብቂያ የሌለው ነው የሚባል አይደለም፡፡ ተለዋጭ ቤት ካልተሰጠኝ አልለቅም የሚለው የተጠሪ ክርክርም ከዚህ አንፃር ሲታይ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ አመልካች ሌላ ቤት መስጠት አልቻለም በሚልም የባለቤትነት መብቱን ማሣጣት በሕግ የሚደገፍ አይደለም፡፡ ተጠሪ ቤቱን የያዘው ከሰኔ 1 ቀን 1974 ዓ.ም ጀምሮ ሲሆን፣ ከዚህ በኋላ ግን የባለቤቱን ፈቃድ እስካላገኘ ድረስ ቤቱን ይዞ የሚቆይበት ምክንያት የለም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ ትክክል ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 61614 ታህሣሥ 18 ቀን 99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 53067 መጋቢት 2 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ለአመልካች ያስረክብ ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 40921

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቢሲኒያ ባንክ (አ.ማ) - ነ/ፈጅ ዱላ መራራ

**ተጠሪ**፡- እነ አብዱ አህመድ (266 ሰዎች) - ጠበቃ ምትኩ

በዚህ መዝገብ የቀረበው አቤቱታ በመ/ቁጥር 42132 ከቀረበው አቤቱታ ጋር በስረ ነገርም ሆነ በጭብጥ ረገድ ተመሳሳይ በመሆኑ ሁለቱም መዛግብት ጐን ለጐን ተመርምረው ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበውም ሆነ በመዝገብ ቁጥር 42132 የቀረበው የሰበር አቤቱታ ከፍርድ አፈፃፀም ጋር የተያያዘ ሲሆን በዚህ መዝገብ የፍርድ ባለመብቶች የሆኑት የአሁን ተሰጠሪዎች በፍርድ ባለእዳ ጣና ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላይ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የፍርድ ባለእዳው ንብረት ተሽጦ በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለን ይታዘዝልን በማለት ጠይቀው የአሁን አመልካችም ቀርቦ በፍ/ቤት የእግድ ትእዛዝ የተሰጠባቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች ለብድር አከፋፈል በዋስትና የያዛቸው ስለሆነ በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857 መሰረት ከማናቸውም ገንዘብ ጠያቂ በፊት በተሽከርካሪዎቹ ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በእነዚህ ተሽከርካሪዎች ላይ የፍርድ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት መቃወሚያ ማቅረቡን ተገንዝበናል፡፡ በተመሳሳይም በመ/ቁ. 42832 ተጠሪዎች የሆኑት እነ አቶ አበራ መለሰ በፍርድ ባለእዳው አበባው ደስታ የግል ትራንስፖርት ላይ የፍርድ አፈፃፀም ማመልከቻ አቅርበው የባለእዳው ተሽከርካሪዎች ተሽጠው በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ እንዲከፈለን ይታዘዝልን በማለት አመልክተው በዚህ መዝገብም አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 እና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857 መሰረት ከማናቸውም ገንዘብ ጥያቂ በፊት የቅድሚያ መብት እንዳለው መቃወሚያውን አቅርቦ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 መሰረት በቅጥር ላይ ከተመሰረተ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውም የሰራተኛ ክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው ስለተመለከተ የአመልካች አቤቱታ ተቀባይነት የሌለው ስለሆነ በአመልካች ባንክ በዝግ ሂሳብ እንዲቀመጥ የተደረገው ገንዘብ ወጭ ሆኖ ለፍርድ ባለመብቶች እንዲከፈል በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበው ቢሆንም የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች በዋስትና በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቅድሚያ መብት ሳያገኝ መቅረቱ ከአዋጅ ቁጥር 97/90 እና ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/ 2857 እንደዚሁም ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አኳያ አግባብነቱ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ በሁለቱም መዛግብት ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍና በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተሰጠው ሲሆን በበኩላችንም የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ መርምረነዋል፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የፍርድ አፈፃፀሙ ሲቀጥል ለፍርድ ባለመብቶች የአሁን

ተጠሪዎች ፍርድ ማስፈጸሚያነት እንዲሸጡ ትእዛዝ የተሰጠባቸው የተለያዩ ተሽከርካሪዎች አመልካች በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሰረት ለብድር በዋስትና የያዛቸው ተሽከርካሪዎች እንደሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ባንክ መያዣ የያዛቸውን ንብረቶች እዳው ሳይከፈለው በቀረ ጊዜ የ30 ቀን ማስጠንቀቂያ ለተበዳሪው በመስጠት ያለማንም ጣልቃ ገብነት በመያዣ የያዘውን ንብረት በመሸጥ ገንዘቡን ገቢ ማድረግ እንደሚችል በአዋጅ ቁጥር 97/90 አንቀጽ 3 ላይ ተመልክቷል፡፡ ከዚህም ሌላ መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ከመያዣው ሽያጭ ዋጋ ከሌሎች ባለገንዘቦች ቀድሞ የመቀበል መብት እንዳለውም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2857/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር አመልካች ከብድር አከፋፈል በመያዣነት በያዛቸው ንብረቶች ላይ የቀደምትነት መብት እንዳለው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳዩ በሚመለከተው በአዋጅ ቁጥር 377/96 መሰረት በቅጥር ላይ ከተመሰረተ የስራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውም የሰራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚኖረው በአንቀጽ 167 ላይ ተመልክቷል፡፡ አመልካች የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት በአሰሪው ላይ ሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ክስ አቅርበው ያስፈረዱ ባለ ገንዘቦች በሚኖሩበት ጊዜ በፍርዱ መሰረት ለነዚህ ባለገንዘቦች ክፍያ ከመፈጸሙ በፊት ሰራተኖች በአሰሪያቸው ላይ ክስ መስርተው ካስፈረዱ ለሰራተኞቹ ቅድሚያ ክፍያ እንደሚፈጽም የሚያመለክት እንጂ ከዚህ አልፎ ባንኩ ለሰጠው ብድር በመያዣ የያዘውን ንብረት ሕጉ በሰጠው ስልጣን መሰረት ሸጦ ለብድሩ እዳ እንዲውል ከሚያደርግ በስተቀር ከተቀበለው የመያዣ ንብረት ሽያጭ ላይ ለባለእዳው ሰራተኞች በቅድሚያ እንዲከፈል ተደርጐ ሊተረጐም የሚገባው አይደለም በማለት ተከራክሯል፡፡

ይሁንና በሕጉ ላይ ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በቅጥር  ላይ ከተመሰረተ የስራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውንም የሰራተኛ የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው የተደነገገ እንደመሆኑ መጠን የሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች አቋም ተራ ገንዘብ ጠያቂዎች/ordinary creditors/ ወይንም እንደ አመልካች በመያዣ ብድር የሰጠ ባለገንዘብ /secured creditors/ ሆኑም አልሆኑ፤ የሰራተኛው የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ እንደሚሰጠው ስለተደነገገ ይህ ሁኔታ ግምት ውስጥ ሊገባ እንደማይችል መገንዘብ እያዳግትም፡፡ ሕግ አውጭው የባንክ የክፍያ ጥያቄ ከሰራተኛም የክፍያ ጥያቄ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ ሐሳብ ቢኖረው በአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80 ላይ እንደተመለከተው ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ የግብር ሰብሳቢው መብት ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሐብት ላይ ከማናቸውም ሌሎች እዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል በማለት እንደተደነገገው በአሰሪና ሰራተኛ አዋጅም ላይ ይህንኑ ያንጸባርቀው እንደበር ይታመናል፡፡

ሲጠቃለልም ለሰራተኞች የሚከፈል የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይንም የእዳ ጥያቄ ቅድሚያ ሊሰጠው እንደሚገባ የተደነገገው በመያዣ በተያዘም ንብረት ላይ ተፈፃሚነት እንዳለው መገንዘብ ስሚቻል አመልካች በመያዣ በተያዙ ንብረቶች ላይ የቅድሚያ መብት ስላለኝ በእነዚህ ንብረቶች ላይ አፈፃፀሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት ያቀረበውን አቤቱታ የስር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉት መቅረታቸው በአግባቡ ስለሆነ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33588 በ20/10/2000 እንደዚሁም በመ/ቁ. 33941 በ26/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 69727 በ3/2/2001 እና በመ/ቁ. 74069 በ16/4/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በአግባቡ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አጽንተነዋል፡፡
2. በዚህ መዝገብ የተሰጠው ፍርድ በመ/ቁ. 42132 ላይ ተፈፃሚነት ስላለው የፍርዱ ግልባጭ ከመ/ቁጥር 42132 ጋር እንዲያያዝ ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 41115

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ሜድሮክ ኮንስትራክሽን ኃላ.የተ.የግል ማህበር - የቀረበ የለም

**ተጠሪ**፡- አቶ ሞገስ ሽፈራው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ መጋቢት 18 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ክስ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ሁኔታ ያላግባብ ከስራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የካሣ፣ የስራ ስንብት፣ የ65 ሣዓት ትርፍ ሣዓት፣ የ16 ቀን የእረፍት ቀን፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜና ክፍያ ለዘገየበት ክፍያ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አመልካች ላይ በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ተጠሪ የድርጅቱን መኪና ባግባቡ የመጠበቅ ኃላፊነታቸውን ባለመጠበቅ ቁልፉን መኪና ላይ ትተው በመሄዳቸው ረዳታቸው መኪናውን አንቀሣቅሶ ግጭት በማድረስ ግምቱ ብር 5,867.24 /አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሣ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሣንቲም/ የሆነ የንብረት ጉዳት ማስከተሉንና ጥፋቱም ሁለተኛ በመሆኑ ስንብቱ በደንቡና በሕግ አግባብ መከናወኑን ዘርዝሮ የተጠሪ ወደ ስራ ልመለስና የክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እንዲሁም የትርፍ ሰዓት ክፍያ በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ የስራ ስንብቱ ሕገወጥ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪ የ4 /አራት/ ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ጥያቄ ደግሞ በማስረጃ አለመደገፉን ጠቅሶ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ//ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የሠበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ጥቅምት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የተጠሪ ድርጊት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ስር የሚሸፈን ሆኖ እያለ ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ተብሎ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው መባሉ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ለተጠሪ ጥሪ ተደርጎላቸው ጠበቃቸው ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የካቲት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ስንብቱ ሕገወጥ ነው ተብሎ አመልካች ለተጠሪ የአራት ወር ደመወዝ ከፍሎ ወደ ስራ ይመልሰው መባሉ ባግባቡ መሆን አለመሆኑ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በሹፌርነት ተቀጥረው እየሠሩ ባለበት ወቅት በተረከቡት መኪና ላይ ቁልፍ ትተው በመውረዳቸው ረዳታቸው ቁልፉን በማንሣት መኪናውን ሲያንቀሣቅሱ ሌላ መኪና በመግጨት በብር 5,867.24 (አምስት ሺህ ስምንት መቶ ስልሳ ሰባት ብር ከሃያ አራት ሣንቲም)የተገመተ የንብረት ጉዳት መድረሱንና በሌላ ወቅትም ተመሣሣይ ጥፋት ፈጽመው በድርጅቱ የዲሲፕሊን ቅጣት ደንብ የአምስት ቀን ደመወዝ ተጠሪ የተቀጡ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ የመኪናውን ቁልፍ በመኪናው ላይ ትተው መውረዳቸውን አረጋግጦ ይህ ጥፋት ተጠሪን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት ከባድ ቸልተኝነት ነው ለማለት የማያስችል ነው በሚል ደምድሟል፡፡ በመሆኑም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ የተጠሪ አድራጎት በከባድ ቸልተኝነት ስር ሊወድቅ ይችላልን? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ አንድ ሠራተኛ ለስራው የተሰጡትን መሣሪያዎችና እቃዎች ሁሉ በጥንቃቄ የመጠበቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 13/3/ ስር የተመለከተ ሲሆን በአሠሪው ንብረት ወይም ከድርጅቱ ስራ ጋር በቀጥታ ግንኙነት ባለው ማናቸውም ንብረት ላይ ሆነብሎ ወይም በከባድ ቸልተኝነት ጉዳት ማድረስ ሠራተኛውን ያለማስጠንቀቂያ ከስራ ለማሰናበት የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 27/1/ሸ/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሆኖም ከባድ ቸልተኝነት የሚለውን ቃል መለኪያ በተመለከተ ሕጉ በግልጽ አያሣይም፡፡ ይሁን እንጂ ቸልተኝነት የጥንቃቄ ጉድለት እንደመሆኑ መጠን የጥንቃቄ ዓይነትና ደረጃ እንደየ ድርጊቱና አድራጊው የስራ ድርሻ አኳያ በመመልከት ምላሽ ለማግኘት አያዳግትም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ የጥፋት ደረጃ "ከባድ ቸልተኝነትን" ሊያቋቁም የሚችል መሆን አለመሆኑን ከስራቸው ባህርይ አንፃር መመልከቱ የግድ የሚል ነው፡፡ ተጠሪ ስራቸው ሹፌር ሲሆን ከስራቸው በተያያዘ ሁኔታ ጥንቃቄ ማድረግ ከሚገባቸው ነገሮች አንዱ የመኪናውን ቁልፍ አያያዝ በተመለከተ ነው፡፡ የመኪናውን ቁልፍ በመኪናው ላይ በማናቸውም ጊዜና ቦታ ትተው ሊወርዱ እንደማይገባ የስራቸው ድርሻ የግድ የሚለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተያዘው ጉዳይ መኪናው ቁሞ የነበረበት ቦታ በአመልካች ድርጅት ግቢ ውስጥ ከመሆኑ እና ቁልፉን አንስተው መኪናውን በማንቀሣቀስ በሌላ መኪና ላይ ጉዳት እንዲደርስ በቀጥታ አስተዋጽኦ ያደገው የመኪናው ረዳት መሆኑ መረጋገጡ ከረዳቱ አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ የተጠሪ የጥንቃቄ ጉድለት የከባድ ቸልተኝነት መለኪያ ሊያሟላ ይችላል ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ተጠሪ ቁልፉን በመኪናው ውስጥ ረዳቱ ባለበት ሁኔታ ትቶ መውረዱ ትክክለኛ አእምሮ ባለው ሰውና በተጠሪ የግል ሁኔታ መመዘኛ መሠረት ከባድ ቸልተኝነትን ሊያሣይ የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤት የተጠሪ ጥፋት ከባድ ቸልተኝነት አይደለም ማለቱ ስህተት ሁኖ አልተገኘም፡፡ የተጠሪ ጥፋት ሁለተኛ ጊዜ ነው ቢባልም ጥፋቱ ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ተ/ መሠረት የተደረገ ስምምነት ስለመኖሩ አመልካች አላስረዳም፤ ስለሆነም የስራ ውሉ የተቋረጠበትን መንገድ የስር ፍ/ቤት ከሕግ ውጪ ነው ማለቱ የሚነቀፍ ሆኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ የቀረበውን የሰበር አቤቱታ የምንቀበልበትን ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡

ይሁንና የስራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ከተባለ ውጤቱን በተመለከተ በአዋጁ ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት ምላሽ መስጠቱ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ የግድ የሚለው ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 43/2/ ድንጋጌ ሲታይም በዚህ ቁጥር በንዑስ ቁጥር አንድ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ አዋጅ ቁጥር 24፣25፣27፣28 እና 29 ከተደነገገው ውጪ የቅጥር ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ ወደስራው እንዲመለስ ወይም ካሣ ተከፍሎት የስራ ክርክር ሰሚ አካል ሊወስን እንደሚችል አስቀምጧል፡፡ ስለሆነም ሕገወጥነቱ እነዚህን የተጠቀሱትን ድንጋጌዎች በመጣስ የተፈፀመ ዓይነት መሆኑ ከተረጋገጠ ሠራተኛው ወደ ስራ የመመለስ ወይም ካሣ ተቀብሎ የመሰናበቱ ምርጫ ለሠራተኛው ሣይሆን ለፍ/ቤቱ የተተወ ስለመሆኑ የአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/1/ እና /2/ ድንጋጌዎችን በአንድነት በማንበብ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ ፍ/ቤቱ በምን ላይ ተመስርቶ ተገቢውን ውሣኔ መወሰን እንደአለበት ደግሞ የአዋጁ አንቀጽ 43/3/ ድንጋጌ ያሣያል፡፡ በመሆኑም ሠራተኛውና አሠሪው አብሮ እንዲቀጥሉ ማድረጉ ለምርታማነትና እንዱስትሪያዊ ሠላም አመቺ ከሆነ ብቻ ግንኙነት እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻል ሆኖ የዚህ ተቃራኒ ሁኔታ የሚያጋጥም መሆኑ ከታመነ ግን ፍ/ቤቱ ሠራተኛው የስራ ስንብትና ሌላ ካሣ ተከፍሎት የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ለመወሰን ሕጉ የሰጠው ሥልጣን ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ግን በአመልካችና በተጠሪ መካከል የስራ ግንኙነቱ እንዲቀጥል ማድረጉ ለምርታማነትና ኢንዱስትሪያዊ ሠላም መሰናክል ሊሆን የማይችል ነው ብሎ ለመደምደም አስቸጋሪ ስለመሆኑ ተጠሪ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመሣሣይ ጥፋት ሁለት ጊዜ ማጥፋታቸው መረጋገጡ አመላካች ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የስር ፍ/ቤትም በተጠሪ የተጠየቀውን ዳኝነት በክርክሩ ሂደት ከተረጋገጡት ጉዳዮችና በሕጉ ለፍ/ቤቱ ከተተወው ስልጣን አኳያ በመመልከት ተጠሪ ተገቢ

ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ መወሰን እየተገባው ወደ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 43/3/ ስር የተመለከተውን ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ ካሣ ተከፍሏቸው ከስራ እንዲሰናበቱ ማዘዙ ሕጋዊ ሆኖ ስለተገኘ የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 24603 ሰኔ 23 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 61665 ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካች ለተጠሪ በሕጉ አግባብ ካሣ ከፍሏቸው ያሰናብቷቸው ብለናል፡፡

3. በዚህ ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

4. ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 40938

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሙገር ሲሚንቶ ኢንተርፕራይዝ - ነ/ፈጅ ሰይፉ በቀለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ኃይሉ መንግስቱ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ህዳር 03 ቀን 2000 ዓ.ም የፃፉት ማመልከቻ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከጥቅምት 22 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ በቅጥር ላይ በተመሰረተ ግንኙነት በጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመድበው እየሰሩ ባሉበት ሁኔታ ከህብረት ስምምነቱ ውጪ ከጥቅምት 22 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ድርጅት በፃፈው ደብዳቤ የስራ መደቡን ወደ ማይገለጽ በቅርብ ኃላፊ በሚሰጥ ትእዛዝ መሰረት ብቻ እንዲሰሩ ገልፆ ያዛወራቸው መሆኑን በመዘርዘር የስራ መደብ ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ወደ ጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ ተመልሰው እንዲሰሩ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአመልካች ድርጅት ላይ በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሰረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች ድርጅትም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ ተጠሪ የጥበቃ የኃላፊነት ስራ ባግባቡ ስላልተወጡና ጉዳዩ ተጣርቶ ለሕግ እስኪቀርብ ድረስ ከስራ ደረጃቸውና ከደመወዛቸው ሣይቀንስ ወደ አቻ ሌላ የስራ ቦታ ማዛወሩ ህጋዊ መሆኑን ዘርዝሮ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር ከመረመረ በኋላ የተጠሪ የስራ መደብ ዝውውር ከህጉ አግባብ ውጪ ነው በማለት ተጠሪ በፊት ይሰሩበት የነበረውን የጥበቃ ኃላፊ ይዘው እንዲሰሩ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት ሰርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ተወካይ ጥቅምት 07 ቀን 2001 ዓ.ም ከፃፉት 3/ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ የግራ ቀኙ የቃል ክርክርም መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሰምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበትና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸውን ማይቀንስ የስራ መደቡን ዝውውር መፈፀሙ ሕገ ወጥ ነው ተብሎ ተጠሪ በቀድሞ የስራ መደብ ተመድበው እንዲሰሩ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪ የስራ ደረጃና ደመወዛቸው ሣይቀንስ አመልካች ተጠሪን ከጥበቃ ኃላፊነት የስራ መደብ በማንሣት እያሰራ የሚገኝ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በጥበቃ ኃላፊነት ያገኙ የነበሩትን ደመወዝ

አሁንም እያገኙ ያሉ መሆኑን ሣይክዱ አጥብቀው የሚከራከሩት የሚሰሩበት የስራ መደብ በመዋቅሩ የማይቃወቅ መሆኑን በመግለጽ ነው፡፡

በመሰረቱ አሰሪ የሰራተኛውን ደረጃ ደመወዝና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ሣይነካ ከአንዱ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሳሳይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ከተቋሙ አደረጃጀትና ከአሰሪነት መብቱ የሚመነጭ መብት ነው፡፡ የአሰሪ መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛን መብት በማይነካ ሁኔታ ሰራተኛን ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ በተመሣሣይ የስራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ህገ ወጥ የሚባልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ የስራ መደብ ዝውውር ስራና ሰራተኛን ለማገናኘት ወይም ስራው እንዳይበደል ታስቦና ተረጋግጦ ከተፈጸመ ህገ ወጥ ሊባል አይችልም፡፡ ይልቁንም የኢንዱስትሪ ሰላምን ይፈጥራል፣ ለሐገር ሁለንተናዊ እድገትና ልማት አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል፡፡ የአሰሪን ድርጅት መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን ጥቅም የጠበቀ ትእዛዝ የመፈጸምና የማክበር ግዴታ ይኖረዋል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 13/2/ እና /7/ ድንጋጌዎች ይዘት የሚያስገነዝበውም ይህንኑ ነው፡፡ በመሆኑም የበታች ፍ/ቤቶች አመልካች ተጠሪን ያዛወረው ከድርጅቱ መዋቅርና አደረጃጀት ውጪ እንዲሁም የተጠሪን ጥቅም ባልጠበቀ ሁኔታ ስለመሆኑ ሣይረጋገጥ አመልካች ተጠሪን በፊት ይሰሩበት በነበረው በደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ ይመልሰው በማለት መወሰናቸውን መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 29948 ሚያዝያ 29 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 67189 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች የድርጅቱን መዋቅርና አደረጃጀት እንዲሁም የሰራተኛውን መብት በጠበቀ ሁኔታ አንድን ሰራተኛ ከአንድ የስራ መደብ ወደ ሌላ ተመሣሣይ የስራ መደብ የማዛወር ሕጋዊ መብት ስላለው በተጠሪ ላይ የፈፀመው ተግባር ሕገ ወጥ አይደለም ብለናል፡፡
3. ተጠሪን ወደ ደረጃ 10 የጥበቃ ኃላፊ የስራ መደብ አመልካች እንዲመልሰው የሚገደድበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 42292

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢ.ት/ያ መብራት ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ሠረቀብርሃን ተክሌ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ከበደ አቡነቴ - ጠበቃ አበበ አሣመረ- ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ በአሁኑ አመልካች ላይ ያላግባብ ከስራ ስላገደኝ ያልተከፈለኝ ጠቅላላ ደመወዝ ብር 6569.96 ከፍሎኝ ወደ ስራ እንድመልስ ይወሰንልኝ በማለት በደ/ብ/ብ/ሕ/ብ/ክ/መንግሥት በሀዲያ ዞን የሆሣዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስም የተጠሪ የስራ ውል የተቋረጠው በኦዲት ምርመራ ጉድለት ተገኝቶባቸው መሆኑን፣የደመወዝ ይከፈለኝ ጥያቄም ላልተሠራ ስራ ሊቀርብ የማይገባ መሆኑን ተጠሪ በተከሰተባቸው የገንዘብ ጉድለት በፍ/ቤት በፍትሐብሔር ክስ የተመሠረተባቸው መሆኑንና በወንጀልም ምርመራው እየተካሄደ ስለመሆኑ ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ታግደው መቆየታቸው በግል እና በቤተሰባቸው ህይወት ጉዳት ማድረሱን እና የገንዘብ ጉድለት ቢኖር እንኳን በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን እንጂ ያለውሣኔ ማቆየት ያላግባብ መሆኑን በምክንያትነት በመያዝ የተጠሪን ክስ ተቀብሎ የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም ካለ ተከፍሏቸው ወደ መደበኛ ስራ እንዲመለሱ ሲል ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ነ/ፈጅ ታኅሣሥ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ተጠሪ የመንግሥትን ገንዘብ ብር 182,845.43 /አንድ መቶ ሠማኒያ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ አርባ አምስት ብር ከአርባ ሦስት ሣንቲም/ ሆነ ብለው ለግል ጥቅማቸው ለማዋልና ለመበልፀግ ሲሉ በስራ አጋጣሚ በእጃቸው ላይ የገባውን ገንዘብ ማጉደላቸው በድርጅቱ ኦዲተሮች ምርመራ ተረጋግጦ እያለ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደስራ እንዲመለሱ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27(/1/ሐ/መ/) ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊታረም ይገባል በማለት ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ይህንኑ ከሕጉ ጋር አገናዝበን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም ተጠሪ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ተከፍሏቸው ወደ መደበኛ ስራ እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ ከስራ ታግደው የቆዩት በስራቸው አጋጣሚ ከእጃቸው ከገባው የአመልካች ድርጅት ገንዘብ ውስጥ ብር 182,845.43 ማጉደላቸው በአመልካች ድርጅት ኦዲተሮች የኦዲት ምርመራ ውጤት ከተረጋገጠ በኋላ የድርጅቱ የዲሲፕሊን ኮሚቴም ጉዳዩን መርምሮ ውሣኔ በማሣለፉ መሆኑን ነው፡፡ የስር ፍ/ቤትም የአመልካችን እርምጃ ሕገወጥ ነው ያለው ተጠሪን ከስራ ከአገደው በኋላ ለበርካታ ጊዜያት ውሣኔ ሣያስተላለፍ ቆይቷል፣ ጎደለ የተባለ ገንዘብ ካለም በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ማስወሰን አለበት በሚል ምክንያት ነው፡፡ ከዚህ የግራ ቀኙ ክርክር እና የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ማስተዋል የሚቻለው ተጠሪ የአመልካች ገንዘብ የጎደለባቸው መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በስራቸው አጋጣሚ እጃቸው የገባው ገንዘብ ስለመጉደሉ በአመልካች ኦዲተሮች መረጋገጡን ሣይክዱ ይኸው የምርመራ ውጤት የማስረጃነት ብቃት የለውም ተብሎ በፍትሐብሔር ክርክር ችሎት መወሰኑን ጠቅሰው ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የፍትሐብሔር ክርክሩ የመጨረሻ ውሣኔ ያላገኘ በይግባኝ ደረጃ እየተከራከሩበት ያለ ጉዳይ ከመሆኑም በላይ የአዋጅ ቁጥር 377/96 መሠረት የሚቀርቡ ክርክሮች ውጤታቸው ከፍትሐብሔር ክርክሮች የተለዩ በመሆናቸው የተጠሪ ክርክር ሕጋዊ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ ፈፀሙ የተባሉት ጥፋት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ መሠረት ከስራ እንዲሰናበቱ ሊያስወሰን የሚችል መሆን ያለመሆኑን መመርመር ሲገባው አመልካች ገንዘቡ ጎድሏል የሚል ቢሆን እንኳ በፍ/ቤት ክስ መሥርቶ ማስወሰን ይገባው ነበር ማለቱ የስር ክርክሮችና የፍትሐብሔር ክርክሮች ውጤታቸው የተለያየ መሆኑን ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባቱን የሚያሣይ ነው በመሆኑም የስር ፍ/ቤት ለፍርዱ መደምደሚያ የሰጠው ትንታኔ በበቂ የሕግ ምክንያት ያልተደገፈ ነው፡፡

በእኛ በኩል ተጠሪ ከስራ የተሰናበቱበትን ምክንያት ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ አኳያ መርመረናል፡፡ ተጠሪ ብር 182,845.43 ማጉደላቸው በድርጅቱ ኦዲተሮች የሂሣብ ምርመራ ውጤት ተረጋግጧል፡፡ ይህ የሂሣብ ምርመራ ውጤት ተቀባይነት የማያገኝበት ሕጋዊ ምክንያት አልተገኘም፡፡ ተጠሪ የአሥሪ ንብረት የሆነውን ብር 182,845.43 ማጉደላቸው ከተረጋገጠ ደግሞ ከስራቸው ያለማስጠንቀቂያ ሊሰናበቱ የሚችሉበት ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/መ/ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያሣያል፡፡ በመሆኑም የአመልካች እርምጃ ሕጋዊ ነው ከሚባል በስተቀር የሚነቀፍበት የሕግ ምክንያት አልተገኘም፡፡

በአጠቃለይ አመልካች በስር ፍ/ቤት ተጠሪ የተሰናበቱት የድርጅቱን ገንዘብ ስላጎደሉና ይህም በድርጅቱ ኦዲተሮች ኦዲት ምርመራ ተረጋግጦና በዲሲፕሊን ኮሚቴ ተቀባይነት አግኝቶ ነው ሲል ያቀረበው ክርክር ታልፎ የገንዘብ ጉድለት ቢኖር እንኳን አመልካች በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ያስወስን እንጂ ማሠናበቱ በአግባቡ አይደለም በማለት ተጠሪን ወደመደበኛ ስራቸው ይመልስ፣ ያልተከፈላቸው ደመወዝና ጥቅማጥቅም ካለም ይከፈላቸው ሲል መወሰኑ በበቂ የሕግ ምክንያት ያልተገደፈና በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 27/1/መ/ ስር የተመለከተውን ያላገናዘበ በመሆኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ በሆሣዕና ከተማ አስተዳደር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 02087 ጥቅምት 19 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በሀድያ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ.04777 ታኅሣሥ 15 ቀን 2001 በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ 41623

መጋቢት 8 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አበባ ትራንስፖርት ኃ/የተ/የግል ማህበር - ነ/ፈጅ ቀርቧል

**ተጠሪ፡-** አቶ ሣሙኤል ኪዳኔ - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**<u>ፍ ር ድ</u>**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት በመካኒክነት ተቀጥሬ እየሰራሁ ሳለ ሳላውቅ የዝውውር ኮሚቴ ሳይሰማ ጥገና ክፍል ለማጠናከር በሚል ሰበብ ወደ ሎግያ ቅርንጫፍ አዛውሮኛል እንድታከም ጠይቄ ከሥራ አግዶኛል እርምጃው ያለ አግባብ ስለሆነ ዝውውሩም እገዳውም አግባብ አይደለም ይባልልኝ ውዝፍ ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደሥራዬ እንዲመልሰኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም መልስ እንዲሰጥ ታዞ ሲመልስ አመልካች ተጠሪን ያሰናበተው የሕብረት ሥምምነቱ ከመውጣቱ በፊት ስለሆነ አዛውሮ ማሰራት ይችላል፣ በወቅቱም ዝውውሩን አልተቃወሙም፣ በሥራቸው ቦታ ላይም አልተገኙም በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበለትን ጉዳይ ከቀረቡት ማስረጃ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል በውሣኔውም አመልካች ተጠሪን እንዳዛወረው የታመነ ሲሆን ሰራተኛውን የማዛወር ሥልጣን አለኝ ያዛወርኩት የሕብረት ስምምነቱ ከመውጣቱ በፊት ነው የሕብረት ሥምምነቱን መከተል አያስፈልገኝም ሲል ተከራክሯል አመልካች ሠራተኛን (ተጠሪን) የማዛወር መብቱ ከሕብረት ሥምምነት የመነጨ አለመሆኑ ግልፅ ነው በግራ ቀኙ ያለው የሥራ ውል የማዛወር ስልጣን የሰጠው መሆኑን አመልካች በማስረጃ አላስረዳም ተጠሪ ዝውውሩ ሲገለፅላቸው ጊዜ ይሠጠኝ አሉ ማለት ዝውውሩን ሕጋዊ ያደርገዋል ማለት ባለመሆኑ ዝውውሩ ሕገወጥ ነው ዕግዱም ያለአግባብ ስለሆነ የዝውውር ውሣኔው ተሰርዞ ተጠሪ በቀድሞ የሥራ ቦታቸው ይመለሱ ዕግዱ የተላለፈበት ቀን አንስቶ ፍርድ እስከተሰጠበት ያለው ደሞዝ ተከፍሎት ስራቸውን ያስቀጥል ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች ይህንኑ ውሣኔ ባለመስማማት ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በማስቀረብ ከአከራከረ በኂላ ግድፈት የለውም ሲል የሥር ውሣኔን በፍ/ብ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት አፅንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች በ24/3/2001 ፅፈው ባቀረቡት ማመልከቻ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ሲል አቤቱታውን አቅርቧል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቷል ጉዳዩ ለሠበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የማህበር አባል ስለሆነ ዝውውሩ ተገቢ አይደለም በማለት መወሰኑ ሰራተኛን አዛውሮ የማሰራት መብቴ ነው፣ ይህን ማድረግ ያልፈለገን ሰራተኛ ማሰናበት ሕግ ይፈቅዳል የሚለውን ቅሬታ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህም መሠረት ይህን ነጥብ የግራ ቀኙ ወገኖች ባሰሙት ክርክር አቤቱታ ካቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ መርምረናል፡፡

በእኛ በኩል ባጠቃላይ የጉዳዩን አመጣጥ ስናይ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በመካኒክነት ሙያ እያገለገሉ ቆይተው የጥገና ክፍልን ለመጠናከር ሲባል ወደ ሎጊያ ቅርንጫፍ እንዲዛወሩ ተደርገው በቦታው ባለመገኘታቸው ከሥራቸው በመታገዳቸው ምክንያት ዝውውሩ አግባብ አይደለም ደሞዝ ተከፍሎኝ ወደ ሥራዬ ልመለስ ብለው ጠይቀዋል፡፡ ከመዝገቡና ካቀረበው ክርክር መረዳት እንደተቻለው የሥር ፍ/ቤት አመልካች ሰራተኛውን (ተጠሪን) ለማዛወር ያበቃውን ምክንያት ከሕብረት ሥምምነት ወይም ከውል መሆኑን አላስረዳህም በማለትና የቀረቡትን የተጠሪን ማስረጃ ለማስተባበል አልቻልክም በማለት ዝውውሩና እግዱ ሕገወጥ ነው ሰራተኛው ወደ ሥራው ይመለስ የተቋረጠበት ደሞዝ ይከፈለው ሲል ወስኗል፡፡

ቀድሞውንም ቢሆን ተጠሪ ከሥራዬ ታግጃለሁ ወደ ሥራዬ ልመለስ ብሎ እስከጠየቀ ድረስ የሥር ፍ/ቤት ጭብጥ የዞ ሊያከራክር የሚገባው ስንብቱ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም የሚል መሆን ነበረበት፡፡

ይህ ሆኖ ሳለ ፍ/ቤቱ ዝውውሩ ሕገወጥ ነው ሲል የሰጠውን ሐሳብ ስናይ አመልካች ተጠሪን የሕብረት ሥምምነት ወይም ከውል ባልመነጨ ምክንያት ስላዛወረው ዝውውሩ ሕገ ወጥ ነው ያለው አባባል አሣማኝ አይሆንም ምክንያቱም የአሠሪና የሠራተኛ ሕጉ በሁለቱም ወገን መብትና ግዴታን በማስቀመጥ የሚያገለግል ሕግ ነውና፡፡

ባጠቃላይ ሲታይ የግራ ቀኙ ባደረጉት ክርክር እንዳስተዋልነው ተጠሪ ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወሙ ከሥራቸው ቦታ ከ5 ቀናት በላይ እንዳልተገኙ በቃል ክርክር ጊዜ ፍ/ቤቱ ተረድቷል፡፡ ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ከሥራው ከ5 ቀናት በላይ የቀረ ሠራተኛ ደግሞ በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1)(ለ) መሠረት ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውሉ ይቋረጣል፡፡ በዚህም ጉዳይ ተጠሪ በቃል ክርክሩ አልቀረሁም ሲል አልተከራከረም፡፡ በመሆኑም ዝውውሩን በወቅቱ ሣይቃወም ከሥራው ገበታ ላይ መቅረቱ ስለተረጋገጠ ተጠሪውን ወደ ሥራው የሚመለስበት ምንም ምክንያት ሣይኖር የሥር ፍ/ቤት የተጠሪ ዝውውር ሕገ ወጥ ነው የተቋረጠው ደሞዝ ይከፈለው በማለት የሰጡት ውሣኔ የፌ.ከ.ፍ/ቤትም ጉዳዩን አይቶ ማረም ሲገባው ማፅናቱ መሠታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ.የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 32594 ቀን 9/11/2000 እና የፌ.ከፍተኛ ፍ/ቤት በመቁ 69715 በቀን 12-3-2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች በሥራው ቦታ ላይ ከ5 ቀናት በላይ ስላልተገኘ መሰናበት አለበት ብለናል የሚከፈለውም የደሞዝ ክፍያ አይገባውም፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 41411

ግንቦት 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሙልሙል ዳቦ መጋገሪያ ድርጅት - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ በለጠ ተገኝ - ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው ተጠሪ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ በክሣቸው አመልካች ያለማስጠንቀቂያ ከሥራ ስላገዳቸው በመሆኑ ከታገዱበት ጊዜ ጀምሮ ያለው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራቸው እንዲመለሱ ይህ ካልሆነ ግን የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች ለቀረበበት ክስ በሰጠው መልስ በተለያየ ጊዜ ሠራተኛ በመደብደብ እና ዛቻ በመፈፀማቸው ሁኔታውን ለማጣራት ከሥራ አገዳቸው እንጂ ከሥራ ስላላሠናበታቸው ከሣሽ የጠየቁት ዳኝነት አግባብ አለመሆኑን ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሥራ ታገዱ እንጂ ከሥራ ስላልተሠናበቱ ያለአግባብ ከሥራ የተሠናበተ ሠራተኛ የሚጠይቀውን የመብት ጥያቄ መጠየቃቸው አግባብ አይደለም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጓል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ ያየው የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ግን አንድ ሠራተኛ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ መሠረት የሚታገደው ለ30 ቀናት ብቻ ስለሆነ ከዚያ በላይ ማገድ ከሥራ ማሠናበት ተደርጎ ይቆጠራል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አቤቱታው በአጭሩ ተጠሪ ያላግባብ ከሥራ ተሠናብቻለሁ የሚል ክስ አላቀረቡም የእገዳው ጊዜ በማብቃቱ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የማስታወቂያ ጥሪ ተደርጎ ስላልቀረቡ አመልካች ለክሱ መልስ ከሰጠ በኋላ ከሥራ አሰናብቷቸዋል፡፡ ከ30 ቀናት በላይ ማገድ እንደ ስንብት ይቆጠራል የሚል ሕግ የለም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርበው ግራ ቀኙ የቃል ክርክር አሠምተዋል፡፡ ፍ/ቤቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ እንደመረመረውም ሊወሰኑ የሚገባቸው ጭብጦች፡-

1. ከ30 ቀናት በላይ ማገድ ከሥራ እንደመሠናበት ይቆጠራል ወይ?
2. በክርክሩ ሂደት ተጠሪ ከሥራ መሠናበታቸው በክርክሩ ሂደት ላይ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚሉት ናቸው፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው ተጠሪ በመጀመሪያ ክስ የመሠረቱት ያለአግባብ ከሥራ ታግጃለሁ በማለት ወደ ስራ ለመመለስ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች እንዲከፈላቸው በመጠየቅ ነው፡፡ አመልካች ደግሞ ተጠሪን ከሥራ አገድኩ እንጂ ስላላሰናበትኩ ጥያቄው ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክሯል፡፡ በእርግጥ ተጠሪ ክስ ሲመሠርቱ ከሥራ ታግደው እንጂ ከሥራ ተሠናብተው አልነበረም፡፡ ነገር ግን በክርክር ላይ እያሉ አመልካች ተጠሪን ከሥራ ማሠናበቱን ከመዝገቡ ሂደት የተረዳን ሲሆን አመልካችም ይህንን አልካደም፡፡

ይህ አዲስ ክስተትም ክስ የቀረበበትን ከሥራ የመታገድ ጉዳይ የክስ ምክንያት የሚያሳጣውና የክርክሩን ጭብጥ እንዲለወጥ የሚያደርገው ነው፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 251/1/ ሥር እንደተደነገገው ፍ/ቤቱ ነገሩን በፍርድ ከመወሰኑ በፊት በተከራካሪዎቹ ወገኖች የተያዘው ጭብጥ እንዲሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጥ እንዲያዝ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን የገመተ እንደሆነና ይህን ማድረግ ለጉዳዩ መልካም አፈፃፀም ቀና መንገድ የሚያስገኝ መሆኑን ሲረዳው ፍ/ቤቱ ጭብጡ እንዲሻሻል ወይም ተጨማሪ ጭብጦች እንዲያዙ ለማድረግ ይችላል፡፡

በተያዘውም ጉዳይ የተጠሪ ከሥራ መታገድ ጉዳይ በተጠሪ ከሥራ መሠናበት ምክንያት የክሱ ምክንያት ተቋርጧል፡፡ የክስ ምክንያት በሌለው ጉዳይ ላይ ደግሞ ፍ/ቤቱ ሊሠጥ የሚችለው ውሣኔ የለም፡፡ ይልቁንም ከክሱ በኂላ ተጠሪ ከሥራ በመሰናበታቸው ተጠሪ ክሣቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ወይም ደግሞ ለጉዳዩ መልካም አፈፃፀም ቀና መንገድ ለማስገኘት ሲል ጭብጡን በመለወጥ የተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ መሆን አመሆኑን አከራክሮ ተገቢውን ውሣኔ ሲሠጥ ተጠሪ ያለአግባብ ተሠናብቻለሁ የሚሉ ከሆነ በሌላ ክስ ይጠይቁ በማለት መወሰኑ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይግባኙ ሲቀርብለት መጀመሪያ ክስ የቀረበበት ጉዳይ የክስ ምክንያቱ በተጠሪ ከሥራ መሠናበት የተቋረጠ በመሆኑ ጭብጡን አስተካክሎ መወሰን ሲገባው በአመልካች የተወሰደውን የሥራ ማገድ እርምጃ መሠረት አድርጎ ውሣኔ መስጠቱ የሥር ፍ/ቤት የፈጸመውን ስህተት መድገሙን ያሣያል፡፡

በእርግጥ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ያለአግባብ ከሥራ ተሠናብተዋል የሚል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ እዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰውም ተጠሪ ከ30 ቀናት ከሥራ መታገዳቸው እንደስንብት ይቆጠራል በማለት ነው፡፡ ነገር ግን አ/ቁ 377/96 አንቀጽ 27/4/ አንድ ሠራተኛ ሊታገድ የሚችልበትን ከፍተኛውን የጊዜ ገደብ ከማስቀመጥ በቀር ከ30 ቀናት በላይ መታገድ ከሥራ እንደማሰናበት ይቆጠራል የሚል እንድምታ የለውም፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ተጠሪ ከ30 ቀን በላይ ከሥራ ስለታገዱ ከሥራ እንደተሰናበቱ ይቆጠራል በማለት ለድንጋጌው የሰጠው ትርጉም ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቱ ከ30 ቀን በላይ መታገዳቸው መሠናበታቸውን ያሣያል በማለት ያለአግባብ ከሥራ ለማሠናበት ሠራተኛ የሚገባውን ክፍያዎች እንዲያገኙ መወሰኑ ስህተት ነው፡፡ ይልቁኑ ተጠሪ በክርክሩ ሂደት ከሥራ መሰናበታቸው ስለታወቀ ይህ የሥራ ስንብት ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን ጭብጥ ይዞ ግራ ቀኙን በማከራከርና አስፈላጊም ከሆነ ተጨማሪ ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥ ይገባው ነበር፡፡

በሌላ በኩል ግን ከክሱ በኂላ ተጠሪ ከሥራ መሠናበታቸውን አመልካችም ስላልካደ የክሱ ምክንያት የተቋረጠውን ከሥራ የመታገዱ ጉዳይ የተወሰደው ይህ የሥራ ስንብት እርምጃ ሕጋዊ ነው አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ውሣኔ ሊሠጥ ይገባ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤትም ሆነ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ተጠሪ ክስ የመሠረቱበት ሥራ የመታገድ ጉዳይ ተጠሪ በመሰናበታቸው የክስ ምክንያቱ በመቋረጡ ክሱ እንዲሻሻል እና ጭብጡ እንዲስተካከል በማድረግ ውሣኔ ሊሰጡ ሲገባ የክስ ምክንያቱ በተቋረጠ ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠታቸው ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ ውጪ ግን በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ መሠረት አንድ ሠራተኛ ከሥራ ለማሠናበት የሚያበቃ ጥፋት ከፈፀመ ከሥራ ከማሠናበቱ በፊት አሠሪው ሠራተኛውን እስከ 30 ቀናት ሊያግድ ይችላል፡፡ ከ30 ቀናት በላይ የሚደረግ ከሥራ የማገድ እርምጃ አዋጁን የሚቃረንና ሕጋዊ ያልሆነ ተግባር በመሆኑ አመልካች ተጠሪን ከ30 ቀናት በላይ አግዶ ማቆየቱ ሕገወጥ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ከታገዱበት ከ31ኛው ቀን ጀምሮ አመልካች ተጠሪን ከሥራ እስካሠናበቱበት ጊዜ ድረስ ለተጠሪ ደመወዛቸውን ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ አግኝተንዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37427 ግንቦት 25/2000 የሰጠው ውሣኔ እና በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 68297 በጥቅምት 12 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለውን ጭብጥ የግራ ቀኙን ክርክርና ሌላ የሚያቀረቡት ማስረጃም ካለ ማስጃቸውን ከመረመረ በኂላ ተገቢ ነው የሚለውን ውሣኔ ይስጥ ብለናል፡፡

3. አመልካች ተጠሪን ከ30 ቀናት በላይ ከሥራ ማገዱ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 27/4/ የተፈቀደ ባለመሆኑ ተጠሪን ከሥራ ካገደበት ከ31ኛው ቀን ጀምሮ ተጠሪን ከሥራ እስካሠናበተበት ያለውን ደመወዛቸውን ይክፈላቸው ብለናል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43370

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ግብርና ምርት ማሣደጊያዎች አቅራቢ ድርጅት - ነ/ፈጅ ዳንኤል ያሬድ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጌታቸው ገድሌ - ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው በሥራ ላይ ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ የሚከፈልን የጉዳት ካሣ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

ጉዳዩ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ በመሠረቱት ክስ በሥራ ላይ በደረሰባቸው አደጋ የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ለክሱ በሠጠው መልስ ደመወዛቸው ሣይቋረጥ አሣክሞ መዳናቸው ሲረጋገጥ ወደ ሥራ መልሷቸው እየሠሩ በመሆኑ በተጨማሪ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ተከራክሯል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ከጉዳቱ አገግሞ ሥራ መጀመሩ በራሱ የጉዳት ካሣን የሚያስከለክለው ባለመሆኑ አመልካች ለተጠሪ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት የጉዳት ካሣ እንዲከፈላቸው ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ላይ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ መ/ሰጪን መጥራት ሣያስፈልገው ይግባኙን ሠርዞታል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ ውሣኔ ላይ ሲሆን አመልካች በቅሬታው ተጠሪ በደረሰባቸው አደጋ ታክመው ወደ ሥራቸው የተመለሱና የመስራት ችሎታቸው የቀነሰ ወይም ችሎታቸውን ያጡ ወይም ገቢያቸው ያልቀነሰ በመሆኑ፣ የተጠሪ ሁኔታ የተሻሻለ ወይም የተባባሠ ለመሆኑ በድጋሚ እንዲታከሙ ጠይቀን ዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታል በድጋሚ ለማከም ፈቃደኛ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የሕክምና ምርመራው እንዲካሄድ ትዕዛዝ መስጠት ሲገባው ይህንን አለማድረጉ አመልካች የመንግሥት ልማት ድርጅት በመሆኑና ለደረሰው ጉዳት በገባው የመድን ሽፋን ባለመኖሩ ጉዳት ካሣው ሊከፈል የሚገባው በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ሆኖ ሣለ በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት እንዲከፈል መወሰኑ እንዲሁም ጉዳት ካሣው መጠን ሊሠላ የሚገባው ጉዳቱ በደረሰበት ጊዜ ተጠሪ በሚያገኙት ገንዘብ እንጂ ከረጅም ዓመት በኋላ በእድገት ባገኙት የደመወዝ መጠን በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ሊሻር ይገባል በማለት አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎትም ተጠሪ ከደረሰባቸው ጉዳት ታክመው ተሽሏቸው ወደ ሥራ የተመለሱና የቀድሞ ስራቸውን እያከናወኑ በመሆኑ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 103/3/4/ መሠረት የተጠሪ ሁኔታ መሻሻሉ ወይም መባባሱ በሕክምና ሣይረጋገጥ ጉዳት ካሣ አመልካች ሊከፍል አይገባም የሚለውንና የአመልካች ቅሬታና ሌሎች ነጥቦችን ለመመርመር ሲባል አቤቱታው ለሠበር ችሎት እንዲቀርብ ለማድረግ ተጠሪም ቀርበው ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በቃል አሠምተዋል፡፡ ችሎቱም የሠበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አኳያ እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪ በስራቸው ላይ እያሉ ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑ በግራ ቀኙ አልተካደም፡፡ ተጠሪም ለዚህ አደጋ የጉዳት ካሣ ሊከፈለኝ ይገባል ሲሉ አመልካች ሊከፈላቸው አይገባም ይከፈል ቢባል እንኳን ሊከፈላቸው የሚገባው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት ሣይሆን በመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ መሠረት ሲሆን መጠኑም ሊሠላ የሚገባው ጉዳቱ በደረሰ ጊዜ ያገኙ በነበረው ደመወዝ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

ስለሆነም በዚህ ችሎት መልስ ማግኘት የሚያስፈልጋቸው ጭብጦች

1. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ ሊከፍል ይገደዳል ወይ?
2. ይገደዳል የሚባል ከሆነ በየትኛው ሕግ መሠረት ነው ጉዳት ካሣው ሊከፈል የሚገባው?
3. መጠኑስ የሚሠላው እንዴት ነው? የሚሉት ሆነው አግኝተነዋል፡፡

1ኛውን ጭብጥ በተመለከተ በተጠሪ ላይ ጉዳት የደረሰ መሆኑ አመልካችም አልተከራከረም ከክርክሩ ሂደትም በተጠሪ ላይ የደረሰው የጉዳት መጠን 20% ቋሚ የአካል ጉዳት መሆኑ በሃኪሞች ቦርድ መረጋገጡን ተረድተናል በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 107 መሠረት ማንኛውም በሥራ ላይ የሚመጣ ጉዳት የደረሰበት ሠራተኛ እንደ ጉዳቱ አይነትና መጠን ክፍያ እንደሚደረግለት ይደነግጋል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለተጠሪ ካሣ ሊከፍል አይገባም በማለት የሚከራከረው የአካል ጉዳት ማለት የመስራት ችሎታ መቀነስን ወይም ማጣትን የሚያስከትል ሁኔታ በሥራ ላይ የሚደርስ ጉዳት መሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 99/1/ ሥር የተመለከተ በመሆኑና ተጠሪ ግን አደጋ የደረሰባቸው ቢሆንም ታክመው ስለተሻላቸው የቀድሞ ስራቸውን ያለምንም ችግር እየሠሩ በመሆኑ የመስራት ችሎታቸው ሣይቀንስ ወይም ችሎታቸውን ሳያጡ ወይም ገቢያቸው ሣይቀነስ ካሣ ሊከፈላቸው አይገባም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ በአዋጁ አንቀጽ 99/1/ ሥር "የአካል ጉዳት" ማለት የሠራተኛውን የመስራት ችሎታ መቀነስ የሚያስከትል ወይም ጭራሹንም ችሎታውን የሚያሣጣ ጉዳት ነው ተብሎ ተተርጉሟል፡፡

እዚህ ላይም መነሣት ያለበት ጉዳይ "የመስራት ችሎታ" በማለት በድንጋጌው የተመለከተው ሠራተኛው ጉዳት በደረሰበት ጊዜ ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን ችሎታ ብቻ ነው ወይስ ሠራተኛው ከአደጋው በኋላም ቢሆን ሊሠራ የሚችለውን ማንኛውንም ሥራ የመስራት ችሎታ ነው? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ይህን ነጥብ ግልጽ ለማድረግ የአዋጁ አንቀጽ 99/1/ የእንግሊዝኛውን ትርጉም ማየቱ ጠቃሚ ይሆናል፡፡

"Disablement" means any employment injury as a consequence of which there is a decrease or loss <u>of capacity to work</u> /ስርዝ የተጨመረ/

ከዚህ የእንግሊዝኛ ትርጉም በግልጽ መረዳት እንደሚቻለው የአካል ጉዳት ሠራተኛው ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመሥራት የሚያስችለውን የተወሰነ ችሎታውን ብቻ የሚመለከት ሣይሆን በአጠቃላይ ወደፊትም ሠራተኛው በሌሎች የሥራ መስኮች ተሠማርቶ ሌሎች ሥራዎችንም ለመስራት የሚያስችለውን ችሎታ /capacity to work/ የሚመለከት ነው አንድ ሠራተኛ እስከመጨረሻው በመጀመሪያ የተቀጠረበትን ሥራ በመስራት ሣይገደብ ወደፊትም የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት የሚችል መሆኑ ይገመታል፡፡ ሕጉም የአካል ጉዳትን ለማያያዝ የፈለገው ሠራተኛው አደጋ በደረሰበት ጊዜ ይሠራ የነበረውን ሥራ ለመስራት የሚያስችለው ውሱን ችሎታ ጋር ብቻ ሣይሆን ይልቁንም የሠራተኛው ወደፊት በተለያየ የሥራ መስክ ተሠማርቶ ለመስራት ከሚያስችለው አጠቃላይ የመስራት ችሎት ጋር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ በአደጋው ምክንያት 20% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ለመሆኑ በሀኪሞች ቦርድ ተረጋግጧል፡፡ ይህንንም አመልካች አልካደም ይህ የደረሰባቸው ጉዳት ደግሞ ምንም እንኳን አሁን የሚሠሩትን ሥራ በአግባቡ መስራት ቢያስችላቸውም ጉዳቱ ወደፊት የተለያዩ ሥራዎችን ለመስራት ከሚያስችላቸው ችሎታ አኳያ ሊመዘን ይገባል፡፡ በመሆኑም አመልካች ተጠሪው አደጋ በደረሰባቸው ጊዜ ሲሰሩ የነበረውን ሥራ ያለችግር በመስራታቸው ብቻ ችሎታቸው አልቀነሰምና ካሣ ሊከፍል አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሌላው አመልካች የሚከራከርበት ነጥብ የሠራተኛው ሁኔታ የተባባሰ ወይም የተሻሻለ ወይም ትክክል ያልሆነ ምርመራ ተደርጎለት ከሆነ ሠራተኛው በድጋሚ እንዲመረመር ሊደረግ ስለሚችል በዚሁ መሠረት በድጋሚ ተመርምረው ውጤቱ ሣይታወቅ ካሣ ልከፍል አይገባም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ አመልካች እንዳለው የሠራተኛው ሁኔታ ተሻሽሏል ወይም ተባብሷል የሚባል ከሆነ በአዋጁ አንቀጽ 102/3/ መሠረት ሲጠየቅ ድጋሚ ሕክምና ሊደረግ እንደሚችል አዋጁ ይፈቅዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች የተጠሪ ሁኔታ ተሻሽሏል የሚል ከሆነ ይህንን የማስረዳት ሸክም አለበት፡፡ ይህንን የማስረዳት ሸክም ግን በቂ ማስረጃ በማቅረብ አልተወጣም፡፡ ድጋሚ ምርመራ እንዲደረግ የዳግማዊ ምኒሊክ ሆስፒታልን ጠይቆ ሆስፒታሉ ፈቃደኛ አለመሆኑን ከመግለጽ በቀር ሌላ ያቀረበው ማስረጃ የለም፡፡ ወይም ተጠሪን በድጋሚ እንዲመረመሩ ጠይቆ ተጠሪው ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ምርመራው ያልተደረገ መሆኑን አልገለፀም፡፡ በመሆኑም ቀደም ሲል ተጠሪ ተመርምረው 20% ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን በሐኪሞች ቦርድ የተረጋገጠው ሁኔታ ስለመሻሻሉ ያቀረበው ማስረጃ ሣይኖር ተጠሪ የቀድሞ ሥራቸውን መስራት በመቀጠላቸው ብቻ የጉዳት ካሣ ልከፍል

አይገባም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት ስለሌለው የሥር ፍ/ቤቶች የጉዳት ካሣ ሊከፍል ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለውም፡፡

2ኛውን ጭብጥ በተመለከተ አመልካች የመንግሥት የልማት ድርጅት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 109/1/ ሥርም በሕ/ስምምነቱ በሌላ አኳኋን ካልተመለከተ በቀር በአዋጁ ለሚሸፈኑ የመንግሥት ድርጅቶች ሠራተኞች የሚሠጠው የጉዳት ካሣ አሠሪው በገባበት የመድኀን ዋስትና ወይም በመንግሥት የጡረታ ሕግ መሠረት ካሣው እንደሚከፈል ያመለክታል፡፡ ድርጅቱ መድን ያልገባ ከሆነ በመንግሥት የጡረታ ሕግ ለሚሸፈኑ ሠራተኞች የመንግሥት የጡረታ ሕግ ተፈፃሚ እንደሚሆን ንዑስ ቁጥር 2 አስቀምጧል፡፡

የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 ጉዳት ለደረሰበት ሠራተኛ የሚከፈለው ካሣ መጠን የመንግሥት ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው በነበረው መደበኛ የወር ደመወዙ 45% በአምስት ዓመት ተባዝቶ የሚኘው ሂሣብ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ በደረሰው ጉዳት መቶኛ ተባዝቶ እንደሆነ አንቀጽ 33 ያመለክታል፡፡

ተጠሪ አመልካች የደረሰውን የጉዳት ዓይነት አመልካች የመድን ዋስትና ገብተው በማለት ያቀረቡት ክርክር ስለሌለ ጉዳቱ መድን ያልተገባለት መሆኑን አምነው እንደተቀበሉት ያስቆጥራቸዋል፡፡ አመልካችም የመንግሥት የልማት ድርጅት በመሆኑና ለጉዳቱ መድን ሽፋን ያልገባ በመሆኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው የመንግሥት ሠራተኞች የጡረታ አዋጅ ላይ የተመለከተው የካሣ መጠን ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በአ/ቁ. 377/96 አንቀጽ 109/3/ መሠረት ካሣው እንዲከፈል የተሠጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

የመጨረሻውን ጭብጥ በተመለከተ ከፍ ሲል በተገለፀው የመንግሥት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 33 የካሣው መጠን የሚሠላው ሠራተኛው ጉዳት ከደረሰበት ወር በፊት ይከፈለው በነበረው መደበኛ የወር ደሞዙ መሠረት ነው፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ለተጠሪ የሚከፈለው የካሣ መጠን ሊሠላ የሚገባው በተጠሪ ላይ ጉዳቱ ከደረሰበት ከሠኔ 20/1999 ዓ.ም. በፊት በነበረው ወር ይከፈላቸው በነበረው መደበኛ የወር ደመወዝ መሠረት እንጂ ከጉዳቱ በኋላ በእድገት ባገኙት ደመወዝ መሠረት ሊሆን አይገባም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. ፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 36135 በ01/05/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 75693 በ28/05/2001 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች ለተጠሪ የጉዳት ካሣ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
3. የጉዳት ካሣውም ሊሠላ የሚገባው በአ/ቁ. 345/95 አንቀጽ 33 መሠረት ተጠሪ ከሠኔ 20/1999 ዓ.ም. በፊት በነበረው ወር ይከፈላቸው በነበረው የወር ደመወዝ መሠረት ነው ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 42752

ግንቦት 12 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሀይ ታደሠ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** እነ ወ/ት ማሜ አሠፋ (36 ሠዎች) - ወኪል ትዕግስት ድንቁና

ተሾመ ሃይሌ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ብሔራዊ አስጎብኚ የጉዞ ወኪል (NTO) - ጠ/ብርሃኑ ክፍያለው

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው የሠራተኞችን ቅነሣ የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ ድርጅት ከስሯል በሚል አዲስ መዋቅር አስጠንቶ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 29(3) ሥር ከተመለከተው ውጪ ቅነሣ በማድረግ የሠጠው ማስጠንቀቂያ ህጋዊ ባለመሆኑ ይታገድልን ብለዋል፡፡

ተጠሪ ድርጅት ለቀረበበት ክስ በሠጠው መልስ በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28(1) መሠረት ምርታማነትን ለማሣደግ እና የአሠራር ዘዴዎችን ለመለወጥ በተዘጋጀው መዋቅር መሠረት መመዘኛውን ባለሟሟላታቸው ቅነሣውን እንዳካሄደ ተከራክሯል፡፡

ክሱ የቀረበለት የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ምርታማነትን ለማሣደግና የአሠራር ዘዴን ለመለወጥ አዲስ መዋቅር ማዘጋጀት መብት ያለው ቢሆንም ከጠቅላላ ሠራተኛ ውስጥ የሚቀነሠው ሠራተኛ 10% እና ከዚያ በላይ ሲሆን በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 29(2) የተከተለ ቅነሣ ማድረግ አለበት፡፡ ተጠሪ ግን ሥርዓቱን ያልተከተለ በመሆኑ በአንቀፅ 29(3) ከሀ-ረ ድረስ ባለው ቅደም ተከተል መሠረት ቅነሣውን አከናውኖ እስከሚያቀርብ ጊዜ ድረስ ለአመልካቾች የአንድ ወር ደመወዝ ይክፈል በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሠኘት ይግባኙን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ ቅነሣው በአ/ቁ 377/96 አንቀጽ 28(2)(ሐ) መሠረት በተጠናው አዲስ መዋቅር አንድ በአንቀፅ 28(3) ስር እንደተመለከተው የሥራ መደቡ በመሠረዙ አይደለም፡፡ በመሆኑም በአንቀጽ 29(3) ሥር የተመለከተውን መከተል አያስፈልግም በማለት የቦርዱን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ቅነሣው በአንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት ስለተደረገ በአዋጁ አንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተውን ቅደም ተከተል መከተል አያስፈልግም በማለት የተሠጠውን የህግ ትርጉም አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ቀርቦ ክርክሩን በቃል አሠምቷል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተመለከተው በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ነጥብ በአ/ቁ 377/96 አንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት ቅነሣ ሲደረግ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተል መከተል ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? የሚለው ነው፡፡

በሥር የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድም ሆነ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አመልካች ቅነሣውን ያደረገው ምርታማነትን ለማሣደግና የአሠራር ዘዴን ለመለወጥ አዲስ መዋቅር በማዘጋጀቱ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በመሆኑም ቅነሣው በአዋጁ አንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት መደረጉን ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪም አጥብቆ የሚከራከረው አንቀፅ 29(3) ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(1) እና 28(3) መሠረት በሚደረግ ቅነሣ እንጂ በአንቀፅ 28(2)(ሐ) የሚመለከት አይደለም የሚል ነው፡፡ በመሆኑም አንቀጽ 29(3) ተፈፃሚነቱ ለማነው የሚለውን ነጥብ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 29 ርዕስ እንደምንረዳው ድንጋጌው የሚመለከተው የሠራተኞችን ቅነሣ ጉዳይ ነው፡፡ የዚሁ አንቀፅ ንዑስ ቁጥር አንድም የሠራተኞች ቅነሣ ምን ማለት እንደሆነ ትርጓሜውን አስቀምጧል፡፡ በዚህም መሠረት የሠራተኞች ቅነሣ ማለት በአንቀፅ 28(2) በተጠቀሱት ምክንያቶች ቁጥራቸው ከድርጅቱ ሠራተኞች ቢያንስ 10% የሚያህለውን ወይም የሠራተኞች ቁጥር ከ20 እስከ 50 በሆነው ድርጅት 5 ሠራተኞችን የሚመለከት ከ10 ተከታታይ ቀናት ያላነሠ ጊዜ የሚቆይ ቅነሣ ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 28(2) ሥር በተመለከቱት ሠራተኞቹ የተሠማሩበት ስራ በከፊል ወይም በሙሉ ለዘለቄታው በመዘጋቱ ወይም የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ በመቀዝቀዝ ወይም ደግሞ ምርታማነትን ለማሣደግና አዲስ የአሠራር ለውጥ ለመጠቀም ሲባል በርካታ ሠራተኞች መቀነስ ሲኖርባቸው ቅነሣው በምን ዓይነት ሥርዓት ሊከናወን እንደሚገባ አንቀፅ 29(3) ያመለክታል፡፡ በእርግጥ የዚህ ድንጋጌ መግቢያ በአንቀፅ 28(1) መሠረት የሠራተኞች ቅነሣ ሲደረግ ቅነሣው ከሥር የተቀመጡትን ቅደም ተከተል መከተል አስፈላጊ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ነገር ግን የድንጋጌው መግቢያ "አንቀፅ 28(1)" በማለት የተገለፀው በአፃፃፍ ግድፈት እንጂ ሊጠቀስ የሚገባው "አንቀፅ 28(2)" መሆኑን ችሎቱ ያምናል፡፡ ለዚህም የሚከተሉት ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል፡፡ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተው ስርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(1) በተመለከተው መሠረት ለሚሠናበት ሠራተኛ ነው ማለቱ ትርጉም አይሠጥም፡፡ ምክንያቱም በአንቀፅ 28(1) የሚናገረው አንድን ሠራተኛ በማስጠንቀቂያ ከስራ በማሠናበት ስለሚቻልበት ሁኔታ እንጂ ስለ በርካታ ሠራተኞች ቅነሣ አይደለም አንድ ሠራተኛ የተመደበበትን ሥራ ለመስራት ችሎታው የሌለው በሆነ ጊዜ ወይም በደረሠበት የጤና መታወክ ወይም የአካል ጉዳት ሥራውን ለመስራት ያልቻለ ከሆነ ወይም ድርጅቱ ወደሌላ ቦታ ሲዛወር ሠራተኛው ተዛውሮ ለመስራት ፈቃደኛ ሣይሆን ሲቀር ወይም ሠራተኛው የያዘው የሥራ መደብ ሲሠረዝና ወደ ሌላ ሥራ መደብ ማዛወር ሣይቻል ሲቀር ሠራተኛውን ማስጠንቀቂያ ሠጥቶ የስራ ውሉን ማቋረጥ ይቻላል፡፡ እነዚህ በአንቀፅ 28(1) ሥር የተዘረዘሩትን ምክንያቶች የሚመለከቱት ችግር አለበት የተባለውን ሠራተኛ ብቻ እንጂ ሌሎችን ሠራተኞች ባለመሆኑ ሊሠናበት የሚችለውም ይኸው ሠራተኛ ብቻ ነው፡፡ በመሆኑም አንድን ሠራተኛ ለመሠናበት በአንቀጽ 29(3) ሥር የተመለከቱት በርካታ ሠራተኞች የሚቀነሱበትን ሥርዓት መከተል ተገቢ ነው ማለቱ ትርጉም የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 28(1) ሥር የተመለከቱት ምክንያቶች ሲያጋጥሙ ከስራ ለማሠናበት መከተል የሚያስፈልግ ስርዓት ሣይኖር ችግር አለበት የተባለውን አንድ ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ሠራተኞች በማስጠንቀቂያ ማሠናበት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል ግን አንቀፅ 28(2) ሥር የተመለከቱት የስራ ውል ማቋረጫ ምክንያቶች ሠራተኞቹ የሚሠናበቱት የተመደቡበትን ስራ ለመስራት ችሎታ ሣይኖራቸው ቀርቶ ወይም ሥራውን ለመስራት ፈቃደኝነት ጎድሏቸው ሣይሆን ድርጅቱ ባጋጠመው ችግር ምክንያት ብዛት ያላቸውን ሠራተኞች መቀነስ በመገደዱ ነው፡፡ ብዛት ያላቸው ሠራተኞች ከእነሱ አቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከሥራ መሠናበት ካለባቸው ሥንብቱ እንዴት መከናወን አለበት የሚለው ቀጥሎ መፍትሄ ማግኘት የሚገባው ነጥብ ነው፡፡ ስለዚህም ህጉ መፍትሔ ማስቀመጥ አስፈልጎታል፡፡ ህጉ ከፍተኛ የምርት ውጤት የሚያሣዩና ችሎታ ያላቸው በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ ቅድሚያ ሲሠጣቸው ተመሣሣይ የሥራ ችሎታና ተመሣሣይ የምርት ውጤት የሚያሣዩ ሠራተኞች በሚመለከት ደግሞ በአንቀፅ 29/3/ (ሀ-ረ) በተዘረዘሩት መሠረት ቅነሣው እንዲካሄድ ያዛል፡፡ በመሆኑም በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተው የቅነሣ ስርዓት ተፈፃሚነት የሚኖረው በአንቀፅ 28(2) እና (3) ሥር በተመለከቱት ሁኔታዎች ላይ እንጂ በአንቀፅ 28(1) ሥር ለተመለከቱት ሁኔታዎች አይደለም፡፡ በአጠቃላይ አንቀፅ 28 እና 29 በአንድነት ተገናዝበው ሲታዩ በአንቀፅ 29(3) ሥር የተቀመጠው የቅነሣ ሥርዓት ተፈፃሚ የሚሆነው በአንቀፅ 28(2) መሠረት ለሚደረግ ቅነሣ እንጂ በአንቀፅ 28(1) ሥር ለሚደረግ የሥራ ውል ማቋረጥ አይደለም፡፡

በእርግጥ በአንቀፅ 28(2)(ሐ) ሥር የድርጅት ምርታማነት ለማሣደግ የአሠራር ዘዴዎችን ለመለወጥ ወይም በአዲስ ቴክኖሎጂ ለመጠቀም የሠራተኛ ቅነሣ ማድረግ የሚቻለው በአንቀፅ 29(3) ሥር በተቀመጠው ቅደም ተከተል ቢሆንም ይህን ቅደም ተከተል መከተል ግድ የሚለው ግን የተቀነሱት ሠራተኞች ብዛት ቢያንስ 10% የሚያህለው ወይም የሠራተኞች ቁጥር ከ20-50 በሆነበት ድርጅት ቢያንስ 5 ሠራተኞች ሲቀነሱ ነው፡፡ በመሆኑም አሠሪው የቅነሣ ቅደም ተከተል አይገባም የሚል ከሆነ የሚቀነሱት ሠራተኞች ብዛት ከላይ ከተመለከተው ቁጥር በታች መሆኑን ማስረዳት መቻል ይኖርበታል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይም ስንመለስ ተጠሪ ሠራተኞቹን በአንቀፅ 28(2)(ሐ) መሠረት የቀነሣቸው ለመሆኑ በቦርድም ሆነ በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በተደረጉት ክርክሮች ተረጋግጧል፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ከፍ ሲል በተብራራው ምክንያት የቅነሣ ስርዓቱ ሊከናወን የሚገባው በአዋጁ አንቀፅ 29(3) መሠረት ነው፡፡ ተጠሪ ይህንን የቅነሣ ሥርዓት ልከተል አይገባም ማለት የሚችለው የተቀነሱት ሠራተኞች ቁጥር በአንቀፅ 29(1) ሥር ቅነሣ ነው ለማለት እንዲችል በመስፈርትነት ከተቀመጠው የሠራተኞች ቁጥር በታች ነው የሚለውን ፍሬ ነገር በማስረዳት ብቻ ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ከሥር ጀምሮ የተሠናበቱት የሠራተኞች ቁጥር በህጉ ከተመለከተው በታች ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የለም፡፡ እንደውም አመልካቾች የተቀነሱት ሠራተኞች 30% የሚያህሉ ናቸው በማለት በሠበር ችሎት ባቀረቡት አቤቱታ የገለፁትን በማስተባበል መልስ አልሠጠም፡፡ ይህም በአመልካቾች የተነገረውን ፍሬ ነገር እንዳመነ የሚያስቆጥረው ነው፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ የሠራተኞችን ቅነሣ ያደረገው በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀፅ 28(2)(ሐ) በመሆኑ ቅነሣው ሊደረግ የሚገባው በአንቀፅ 29(3) ሥር የተመለከተውን የቅነሣ ሥርዓት በመከተል በመሆኑ የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት ተጠሪ በህጉ የተመለከተውን የቅነሣ ቅደም ተከተል መከተል አይገባውም በማለት ለድንጋጌው የሠጠው ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70811 ታህሣስ 5/2001 የሠጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ 350/ቀወ1/2000 22/12/2000 ዓ.ም

የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39464

ግንቦት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሐረር ቢራ አክሲዮን ማኀበር - ነ/ፈ ሬድዋን አህመድ

**ተጠሪ፡-** አቶ አብዱልቃድር አብዱረዛቅ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ተወስኗል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በሐረሪ ሕ/ብ/ክ/መ/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪ የሥር ከሳሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ በመልካች ድርጅት በሠራተኝነት ከ1974 ዓ.ም. ጀምሮ ስሠራ ቆይቼ በራሴ ፍቃድ ውሌን አቋርጫለው በአዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 39/2/ሸ/ መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያ ሊከፍለኝ ሲገባ ቤት ከለቀቅክ በሚል ምክንያት ፈቃደኛ አልሆነም፡፡ ስለዚህ የተለያዩ ክፍያዎችን እንዲከፈለኝ በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ ባቀረበው መልስ ተጠሪ በአዋጅ ቁ 494/98 39/2/ሸ መሠረት የጠየቁት የስንብት ክፍያ የሕግ ድጋፍ የለውም ምክንያቱም ተጠሪ ኃላፊ ሆነው ሲሰሩ ስለነበረ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ሊፃፍ አይገባም በተጨማሪም ተጠሪ የጡረታ መብት ተጠቃሚ ስለሆኑ የስንብት ሊከፈላቸው አይገባም፣ የአመልካችን /የድርጅቱን/ ንብረት ሳያስረክቡ ክፍያ ሊጠይቁ አይችሉም ሲል ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት የሐረሪ ክልላዊ መንግሥት የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን በማከራከር ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በውሣኔውም አመልካች ላቀረቡት መቃወሚያ በመመርመር ውድቅ በማድረግ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ሲወስን ተጠሪ በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ መሠረት ሊዳኙ እንደሚገባ በማመልከት በዚሁ አዋጅ መሠረት ተጠሪ በፈቃዳቸው ስራቸውን በመልቀቃቸው በሕጉ አግባብ ሊከፈላቸው የሚገባውን ክፍያ በጥያቄያቸው መሠረት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንድከፍል በመወሰን አመልካች በክስ መልሱ ላይ ንብረቴን ሳያስረክበኝ ክፍያ ሊጠይቅ አይገባውም ያለውን ነጥብ አልፎ ንብረቱን /ቤት/ አስመልክቶ አመልካች ቤቱ በራሱ ስም ተመዝግቦ መኖሩን አላረጋገጠም፤ የተከሣሽ ከሣሽነትን ማቅረብ ሲገባው ክርክር ማቅረቡ ሕጋዊ አይደለም ሲል ጥያቄውን ውድቅ አድርጎታል፡፡

አመልካችም በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ለክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኙን ቢያቀርብም ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሥር ውሣኔ ጉድለት የለውም በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች በሰበር አቤቱታቸው ላይ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው በማለት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

በዚህ መሠረት የሰበር ችሎቱ ተጠሪ በአመልካች በኩል ላቀረበው አቤቱታ ቀርቦ መልሱን እንዲሠጥ መጥሪያ ብልክለትም ተጠሪ መጥሪያ ቢደርሰውም ክርክሩ ሊሰማ በተወሰነበት ቀን ሊቀርብ ባለመቻሉና አመልካችም ይህንኑ በማረጋገጡ ተጠሪ በሌሉበት ጉዳዩ እንዲታይ በማድረግ መዝገቡን መርምረናል መዝገቡ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ የተባለውም በሥር ፍ/ቤት ለተጠሪ ሊከፈለው ይገባል ያሉት የስንብት እና የቦነስ ክፍያን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም አቤቱታ የቀረበለትን ውሣኔ የአመልካችን አቤቱታ፣ አግባብነት ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡-

እኛም የጉዳዩን አመጣጥ ጠቅላል ባለ መልኩ ስናየው ተጠሪ በአመልካች ድርጅት በማገልገል ቆይተው በራሳቸው ፍቃድ የሥራ ውላቸውን በማቋረጣቸው አመልካች ቤት /ንብረት/ ካላስረከብከኝ በማለት በሕጉ የሚፈቀድልኝን ሊከፍለኝ ፈቃደኛ አልሆነም ብለው በመክሰሳቸው አመልካችም ተጠሪ በእጃቸው የሚገኘውን ንብረት ሣያስረክቡኝ ክፍያ ሊጠይቁኝ አይችልም በማለት በመከራከራቸው ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የተጠሪን የክፍያ ጥያቄ በመቀበል እንዲከፈለው በመወሰን ንብረትን አስመልክቶ በተከሣሽ ከሣሽነት ያልቀረበ ነው በማለት ውድቅ ሲያደርገው የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ጉድለት የለበትም ሲል የሥር ውሣኔን አጽድቆታል፡፡

እንግዲህ ከቀረበው ውሣኔና የአመልካችን አቤቱታ እንደመረመርነው ምንም እንኳ ክፍያን አስመልክቶ ለማጣራት ጭብጥ ቢያዝም በተንዳኝ አመልካች ተጠሪ ሊያስረክቡኝ ይገባል የሚለውን ቤት በዋናነት ሊታይ የሚገባው ነጥብ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሠረቱ ተጠሪ በሥር ክሣቸው ተጠሪ ንብረቴን ካላስረከብከኝ በማለት ክፍያ ሊከፍለኝ ፍቃደኛ አልሆነም ሲሉ ክስ መስክረዋል፤ ከዚህ በመነሣት ተጠሪ ከጠየቁት ክፍያ ውስጥ በአዋጁ አንቀጽ 36 መሠረት ሊከፈላቸው የሚገባውን ጠይቋል ይህ አንቀጽም አስፈላጊ ክፍያዎች አሰሪው በሰባት /7/ ቀን ውስጥ ለሰራተኛው ሊከፍል እንደሚገባ ይደነግጋል፡፡ ይህን ካልፈፀመ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 38 መሠረት አሠሪ በራሱ ጥፋት ካልከፈለ ለሠራተኛ ክፍያ የዘገየበትን እንዲከፍል ያዛል፡፡ ለእነዚህ አንቀጾች አግባብ ያለውን ትርጉም ለመስጠት /ክፍያ ዘገየ ወይም አልዘገየም/ ለማለት የንብረቱ ባለይዞታነትና ተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል ወይ? ወይስ አይገባም? የሚለው ነጥብ ሊጣራ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ምክንያቱም የተጠሪን የክፍያ ጥያቄ ምላሽ ለመሰጠት ስለሚረዳ ነው፡፡ በተጨማሪም አመልካች ተጠሪ ንብረቱን ሣያስረክበኝ ክፍያ ፈጽምልኝ ሊለኝ አይገባም የሚል ክርክር ስላለው ነው በመሠረቱ በአመልካች አቤቱታ ላይ ለመረዳት እንደቻልነው አመልካች የተባለውን ቤት ለሰራተኞቹ ማረፊያነት በማሰብ ከክልሉ የኪራይ ቤቶች አስተዳደር በራሱ ስም እንደተረከባቸው እየገለፀ ነው ይህ ባለበት የሥር ፍ/ቤቶች ቤቱንም ቢሆን የማን ንብረት /በማን ስም/ እንዳለ በራሱ ጊዜ ሊያጣራውና ውሣኔ ሊያሳርፍበት ሲገባ የአመልካች ቤት መሆኑ አልተረጋገጠም የተከሣሽ ከሣሽነት ሊቀርብበት ይገባል በማለት ጥያቄውን ማለፉ አግባብነት የለውም ምክንያቱም ተጠሪም ቢሆን የኔ ንብረት ነው ሲል ያቀረበው ማሳመኛ ነጥብ የለምና ነው፡፡ ባጠቃላይ የንብረት ጥያቄው ምላሽ ሣያገኝ የተጠየቀውን ክፍያ ነጥሎ ውሣኔ መስጠቱ የተጠየቀውን ዳኝነት በአግባቡ ምላሽ ተሰጥቶታል ለማለት አዳጋች ነው፡፡ በመሆኑም ከላይ የተጠቀሱት ነጥቦች ተጣርቶ ሣይጠናቀቁ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ እና በከፍተኛውም ፍ/ቤት ሣይታረም መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የሐረሪ ሕዝብ ብ/ክ/መ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27167 ግንቦት 21/2000 እና የክልሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የመ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ በያዙት ቤት ላይ በማከራከር ውሣኔ በሕጉ መሠረት ይስጥ ብለን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343 መሠረት መዝገቡን መልሰናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 41786

ግንቦት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ አየር መንገድ - ነ/ፈ ሰለሞን ተክሌ ቀርቧል፡፡

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ አሰፋ አቤቦ - ክፍለ ታደሰ ጠበቃ

2. አቶ ዋዶ ቱሣ

3. አቶ አክሊሉ ጌታሁን

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች የሥር ተከሣሽ ተጠሪዎች የሥር ከሣሾች ነበሩ ተጠሪዎች በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ባመልካች ድርጅት በማቴሪያልስ ማኔጅመንት ዲቪዢን አጣዳፊ የአውሮፕላን መለዋወጫ ዕቃ አቅራቢነት የሥራ መደብ እና በኋላም የዕቃ ግዢ በመሆን ተመድበን እየሰራን ወደ አዲሱ የሥራ መደብ ስንዛወር ደሞዝና ጥቅም ተቀንሶብናል፡፡ ስለዚህ ቀደም ሲል የምናገኘው ደሞዝ ይከፈለን፣ ወደ ነበርንበት እንድንመለስ ከደሞዝ ጋር የሚከፈል ክፍያ እንዲመለስልን የነዳጅ አበል እና የበረራ የቅድሚያ ትኬት መብታችን እንዲጠበቅልን በማለት ጠይቋል፡፡

አመልካች በበኩሉ ባቀረበው መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ውድቅ አድርጎታል፡፡ በዋናው ነገር ግን ተጠሪዎች ሲሰሩበት የነበረው የሥራ መደብ ለተቀላጠፈ የሥራ ውጤት ሲባል እንደገና ሲዋቀር የተጠሪዎች አገልግሎት አስፈላጊ በመሆኑ ከሥራ ከሚሰናበቱ በድርጅቱ የደመወዝ ፖሊሲ መሠረት በአዲሱ የሥራ መደብ ለመሥራት የሚስማሙ ከሆነ እንዲሠሩ ተጠይቀው በፍቃደኝነት በመቀበላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን ያየው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የቀረበውን ክርክር አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ ውሣኔ ሲሰጥ ተጠሪዎች ይዘውት የነበረው የሥራ መደብ በመዋቅር ለውጥ ምክንያት ተዘግቷል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎችን ከማሰናበት ይልቅ ደሞዛቸው ተቀንሶ ወደ አዲሱ የሥራ መደብ እንዲሰሩ ተጠይቀው የቀድሞ የሥራ መደባቸው /የማቴሪያልስ ማኔጅመንት ዲቪዥን አጣዳፊ የአውሮርላን መለዋወጫ ዕቃ አቅርቦት/ መሠረዙን ሳይክዱ በአዲሱ የሥራ መደብ /የዕቃ ግዢ/ ቦታ ላይ ስምምነት ያደረግነው በማስፈራራትና ተገደን ነው የሚለው መከራከሪያ እና ከተደረገው ስምምነት መረዳት እንደተቻለው በፍቃደኝነት የተመደቡበት የሥራ መደብ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ስለዚህ ጥያቄው ውድቅ ነው በማለት ተጠሪዎች ይሠሩበት የነበረው የሥራ መደብ ስለተሰረዘ በፊት ይከፍለን የነበረው ደሞዝ እንዳይቀነስብን፣ የተቀነሰው ይመለስልን ጥቅማ ጥቅማችን ይጠበቅልን ሲሉ ያቀረቡት ክርክር ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም ሲል ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች በዚሁ ውሣኔ ባለመሥማማት ይግባኛቸውን ለከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቧል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለትም የከፍተኛው ፍ/ቤት የግራ ቀኙን በማከራከር ሲወስን የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ 377/96 አንቀጽ 28/1/መ በአሰራር ለውጥ

የአንድ ሥራ መደብ ሲታጠፍ አሰሪው ሠራተኛውን ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ካልቻለ በማስጠንቀቂያ ሠራተኛውን ማሰናበት እንደሚችል ይደነግጋል፡፡

የአዋጁ አንቀጽ 59/1/"ም" በሕግ /በሕ. ስምምነት/ በሥራ ደንብ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በቀር አሰሪው የሠራተኛውን ደሞዝ መቀነስ እንደማይችል ተቀምጧል፡፡ በሌላም በኩል ተጠሪዎች ይሠሩበት ከነበረው የሥራ መደብ አሁን ወደ ተመደቡበት መምጣታቸው ደሞዛቸው እንዲቀንስ መስማማታቸውን አይደለም፡፡ የቀረበውም ሰነድ እንዲህ አይልም፡፡ በተጨማሪም የአዋጁ አንቀጽ 25/1/ መሠረት ሠራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ዋጋ የለውም፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያው ደረጃ ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ጥያቄ ውድቅ ማድረጉ አግባብ አይደለም በማለት የሥር ውሣኔን በመሻር አመልካች ከተጠሪዎች የቆረጠውን ገንዘብ ተመላሽ ያድርግ ደሞዛቸውን ያስተካክል በማለት ሲወስን የጥቅማጥቅም ጥያቄን አስመልክቶ ግን ተጠሪዎች አሁን ለሚሠሩበት ቦታ የሚገባ መሆኑን አላስረዱም ሲል ጥያቄያቸውን ሣይቀበል ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው በዚሁ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ አመልካች ታህሣሥ 2/2001 ጽፈው ባቀረቡት አቤቱታ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረምልን ይገባል ሲል ጠይቋል፡፡

እኛም በዚህ መሠረት ተጠሪዎችን በማስቀረብ ግራ ቀኙ የካሄዱትን የቃል ክርክር ሰምተናቸዋል፡፡ ጉዳዩም ለሰበር ቀርቦ ሊታይ ይገባል የተባለውም መልስ ሰጪዎች ከአመልካች ጋር ባደረጉት ስምምነት ወደ አዲሱ የሥራ መደብ ለሚያስገኘው የደሞዝ መጠን መመደባቸውን የሥር ፍ/ቤት የውሣኔ ግልባጭ ያስረዳል ይህ መሆኑ ከተረጋገጠ በዚሁ ፍሬ ነገር የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 25 እና 59 ላይ አስመልክቶ የሰጠውን ትርጓሜ አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሠረት አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ የግራ ቀኙ ካደረጉት ክርክር እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

በመሆኑም የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ ተጠሪዎች በሥር ፍ/ቤት ክሳቸውን ሲመሠርቱ በአመልካች ድርጅት ውስጥ በማቴሪያል ማኔጅመንት ድቪዢን አጣዳፊ የአውሮፕላን መለዋወጫ ዕቃ አቅራቢነት ሲሰሩ ቆይተው ወደ አዲሱ የሥራ መደብ "ዕቃ ግዢ" የሥራ መደብ ላይ በመመደባቸው ምክንያት በፊት ሲያገኙት የነበረው የደሞዝ መጠንና የሚያገኙት ልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም እንደቀነሰባቸው በመግለጽ ወደነበሩበት ቦታ እንመለስ፣ ቀደም ሲል ሲከፈለን የነበረው ደሞዝ ይከፈለን ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ይሠጠን በማለት በመጠየቃቸው አመልካችም ተጠሪዎች ሲሰሩበት የነበረው የሥራ መደብ በመዋቅር መሻሻል /ለውጥ/ ምክንያት ስለተሰረዘ ተጠሪን ከማሰናበት ይልቅ በነሱ ፍቃድ ወደ አዲስ የስራ መደብ እንዲመደቡ የተደረገ ነው፡፡ ለአዲሱ ቦታ የተያዘውን ደሞዝ እየከፈልናቸው ነው፤ በተዘጋ የሥራ መደብ ክፍያ ልንጠየቅ አይገባም በማለቱ ጉዳዩ የቀረበለትም የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ ተጠሪዎች የድሮው ቦታ /የነበሩበት የሥራ መደብ እንደተሰረዘ ሣይክዱ በፍቃዳቸው በአዲሱ የሥራ መደብ ላይ ሆነው ወደ ነበርንበት እንመለስ የተቀነሰው ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም ይከፈለን በማለት የጠየቁት ጥያቄን ውድቅ አድርጎታል፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በዚህ በተቃራኒው የአዋጁን አንቀጽ 25/1/ በመጥቀስ የቀረበው ሰነድና ተጠሪዎች ከነበረው የሥራ መደብ አሁን ወደ ተመደቡበት መምጣታቸውን እንጂ ደሞዛቸውን እንዲቀነስ መስማማታቸውን አያሣይም፡፡ ስለዚህ የተቆረጠባቸው ደሞዝ ይከፈል በዚሁም ልክ ይስተካከል ሲል የስር ፍ/ቤት ውሣኔን ሽሮታል፡፡

በመሠረቱ የከፍተኛው ፍ/ቤት የሥር ውሣኔን ለመሻር ሲል የሰጠውን የሕግ ትንተና የአዋጁን አንቀጾች አተረጓጎም አንፃር ስናይ የሥር ውሣኔ የሚነቀፍ አልነበረም፡፡ የሰበር ችሎቱም ቢሆን አጽኖት ሰጥቶ በጭብጥነት የያዛቸው ነጥብም ቢሆን ይህንኑ ለመመርመር ነው፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ተጠሪዎችና አመልካች በሰበር ችሎት ቀርበው ባደረጉት የቃል ክርክርና ከሥር መዝገብ ለመገንዘብ እንደተቻለው ተጠሪ የነበሩበት የሥራ መደብ የሥራ መሪ የሚያሰኛቸውና እነሱም /ተጠሪዎች/ ያልካዱት ጉዳይ ነው፡፡ ታዲያ ይህ አዲሱ ቦታ /የሥራ መደብ/ በድርጅቱ የመዋቅር ለውጥ ምክንያት መዘጋቱን የተካካዱበት በሌለበት አመልካች ለማሰናበት ያለውን መብት በመተው ከተጠሪዎች አገልግሎት አንፃር የእነርሱን ፍቃድ በመጠየቅ በጽሑፍ ተስማምተው ተጠሪዎችም ይህ አዲሱ የሥራ መደብ የደሞዝ መጠን ምን ያሕል እንደሆነ እያወቁ ሥራቸውን

የጀመሩ መሆኑ በሰበር ችሎት የግራ ቀኙ ስምምነት በግልጽ ተሰምቷል፡፡ ተገደን ነው የፈረምነው የሚሉት ቢሆን በዚህ ደረጃ ላይ ሊታመን የሚችል አይደለም፡፡

ይህ ሆኖ ሣለ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 28/መ/"ን" በመጥቀስ የሥራ መደብ ሲታጠፍ አመልካች ወደ ሌላ የሥራ መደብ አዛውሮ ማሰራት ካልቻለ ተጠሪን ሊያሰናብት ይችል ነበር በማለት ተችቷል፡፡

በመሠረቱ የተጠሪ ጥያቄም ቢሆን ዝውውርን አይመለከትም፡፡ ሌላው እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት አባባል /አተረጓጎም/ አመልካች የመጀመሪያው የስራ መደብ ሲሰረዝ /ሲዘጋ/ የተጠሪዎችን መሰናበት የሚያበረታታ ነው፤ ድርጅቱ ግን የተጠሪዎችን አገልግሎት ከግምት በማስገባት ከማሰናበት ይልቅ በሌላ የሥራ መደብ በፍቃዳቸው ላይ ተንተርሶ እያሰራቸው ነው፡፡ ይህ ድርጊት ፈጽሞ ሊነቀፍ የሚገባው አልነበረም፡፡

ሌላው የአዋጁን አንቀጽ 59/1/ አስመልክቶ በይግባኝ ሰሚው የተሰጠውን ትርጉም ስናይ ሰራተኛው በጽሑፍ ካልተስማማ አሰሪው የሰራተኛውን ደሞዝ ሊቀንስ አይችልም ነው የሚለው በያዝነው ጉዳይ ግን የአመልካች ድርጊት በዚህ መልኩ የሚተረጎም አይሆንም፡፡ ምክንያቱም አመልካች የተጠሪዎች የመጀመሪያው የሥራ መደብ በመሠረዙ ምክንያት አዲስ የሥራ መደብ ላይ በአዲስ መልኩ በመደራደር ወይም /በውል ሰነድ/ በመፈቃቀድ የፈፀሙት ስለሆነ የአንቀጹን መንፈስ የሳተ ትርጉም ነው፡፡ በመጨረሻም የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአዋጁን አንቀጽ 25/1/ በመጥቀስ ሠራተኛው መብቱን ለመተው የሚያደርገው ስምምነት ዋጋ የለውም ሲል ነው የሥር ውሣኔን የተቸው፡፡ ይህም ነጥብ ቢሆን ተጠሪዎችም ቢሆኑ የመጀመሪያው የሥራ መደብ ከተሰረዘ በኋላ ነው በሌለ መብት መብትን የሚጠይቁት፡፡ ይህም ማለት መብትን ፈጥሮ የነበረው የሥራ መደብ ራሱ የለምና ነው፡፡

ስለዚህ የከፍተኛው ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ከግምት ሣያስገባ በሌለ የሥራ መደብ ልክ የተጠሪዎች ደሞዝ ይስተካከል ያልተከፈላቸው ተመላሽ ይሁን በማለት የሥር ውሣኔን መሻሩ መሠረታዊ የሕግ ሥህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1- የፌዴራል የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 65973 ነሐሴ 26/2001 የተሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2- የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34902 በ26/6/2000 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3- ተጠሪዎች አሁን በሚሠሩበት የሥራ መደብ በተያዘው የደሞዝ ልክ ሊከፈላቸው ይገባል ብለናል፡፡
4- በመ/ቁ. 47676 ላይ ተሰጥቶ የነበረው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል፡፡
5- የግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 39650

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** የየረር በር ምስራቅ ፀሐይ ቅዱስ ዑራኤል ቤ/ክርስቲያን የደብሩ ዋና አስተዳደር - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** እነ ቄስ ሰፊነው ደሣለኝ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪዎች በየግላቸው በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ የክሣቸው ይዘትም በአመልካች ቤተክርስቲያን በጥበቃ ሥራ ተቀጥረው በማገልገል ላይ እያሉ ጥፋት ሣይፈጽሙ ከሥራ መሰናበታቸውን ገልፀው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ መደባቸው እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካችም በተከሣሽነቷ ቀርባ በሠጠችው መልስ ተጠሪዎች ከሥራ የተሰናበቱት የጥበቃ ተግባርና ኃላፊነት ባለማክበርና ባለመወጣት ብር 15,000.00 /አሥራ አምስት ሺህ ብር/ የያዘ ሙዳየ ምጽዋት እንዲሠረቅ በማድረጋቸው በመሆኑ የሥራ ስንብቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 ከአንቀጽ 13፣ 27/1/ሸ/ ድንጋጌዎች አኳያ ሕጋዊ ነው በማለት ተከራክራለች ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ምስክሮችን ከሠማ በኋላ አመልካች የተጠሪዎችን አላስረዳችም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር የአመልካችን ክርክር ውድቅ በማድረግ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው ድምዳሜ በመድረስ ተጠሪዎች የ6/ስድስት/ ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ስራቸው አመልካች እንድትመልስ ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም የአመልካችን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም በዚሁ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ወኪል ሐምሌ 28 ቀን 2000 ዓ.ም. 4/አራት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ ተጠሪዎች ኀዳር 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በጋራ በፃፉት የመልስ ማመልከቻ የአመልካችን የሰበር ቅሬታ ነጥቦች በመንቀፍ እና የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ተገቢነት በመዘርዘር ውሣኔው ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው ዓቢይ ጭብጥ የተጠሪዎች የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ተብሎ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ምድብ ሥራቸው እንዲመለሱ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የሚቻለው ተጠሪዎች በአመልካች ድርጅት ለጥበቃ ሥራ የተቀጠሩ፣ ይህንኑ ስራውን በዕለቱ ሲያከናውኑም ብር 15,000.00 የያዘ ሙዳየ ምስዋት መጥፋቱ መረጋገጡን ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤትም ይህንኑ ፍሬ

ጉዳይ ያረጋገጠው ሲሆን የአመልካችን ክርክር ውደቅ ያደረገው ተጠሪዎች ለገንዘብ መጥፋት ቀጥተኛ ወይም በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ ያደረጉት ስለመሆኑ አልተረጋገጠም የሚል ምክንያት ይዞ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ገንዘቡ ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራቸው ላይ በነበሩበት ሰዓት አለመጥፋቱን የሚያረጋግጥ ክርክር አልቀረበም፤ የተጠሪዎች ሥራም የቤተክርስቲያኗን ንብረት መጠበቅ ነው፡፡ ገንዘቡ የጠፋው ገንዘቡ ተቀምጦበት የነበረው ሙዳየ ምስዋት ቁልፍ ሣይሰበር ስለመሆኑና ተመሣሣይ ቁልፍም በሌሎች ሰዎች እጅ እንደሚገኝም ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን የዚህ ፍሬ ነገር መረጋገጥ የተጠሪዎችን ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አስተዋጽኦ ለገንዘቡ መጥፋት በምክንያት በመያዝ ኃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ ገንዘቡ የጠፋበት ሰዓት ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራ ላይ የሚገኙበት ከሆነ የስራቸው ኃላፊነት የለባቸውም ወደሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ ዋናው ነጥብ ገንዘቡ በሚጠፋበት ሰዓት ተጠሪዎች በጥበቃ ሥራ ላይ የሚገኙበት ከሆነ ከሥራቸው ኃላፊነት እና ተግባር ጋር ተያይዞ መታየቱ ላይ ነው፡፡ እንግዲህ የአመልካች ገንዘብ የጠፋው ተጠሪዎች በጥበቃ ላይ በነበሩበት ወቅት መሆኑ ከተረጋገጠ የአመልካች እርምጃ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ እና 27/1/ሸ/ አንፃር ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ ተጠሪዎች የሥራ ተግባራቸው ጥበቃ እስከሆነ ድረስ ስራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ እንዲያደርጉና እንዲወጡ የሥራ ደንቡ የግድ ይላል፡፡ ሥራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ ባለማድረግ ለሚደርሰው ጉዳት ደግሞ በሕጉ አግባብ ኃላፊነት ይከተላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች በጥበቃ ላይ ባሉበት ወቅት የአመልካች ንብረት መገኘቱ ስራው የሚጠይቀውን ጥንቃቄ አለማድረጋቸውን የሚያሣይ ነው፡፡

በዚህ ተግባራቸው ደግሞ በአሠሪው ንብረት ላይ ጉዳት አድርሰዋል፡፡ ይህም በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሸ/ መሠረት የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ የሚያስችል ሕጋዊ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በትዕዛዝ በማጽናት ተጠሪዎች ውዝፍ ደመወዝ ከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ማድረጉ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር፣ የተጠሪዎች የሥራ ዓይነት የሚያስፈልገውን ጥንቃቄ ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 13/3/ እና 27/1/ሸ/ ድንጋጌዎች ጋር ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በማለት ተከታዩን ውሣኔ ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 37446፣ 37456፣ 37452 የቀረቡት ጉዳዮች ተጣምረው ታይተው ሐምሌ 02 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሰጠው ውሣኔ እና ይህንኑ ውሣኔ በመ/ቁ. 69644 ሐምሌ 25 ቀን 2000 ዓ.ም. ያፀናው የፌ/ከ/ፍ/ቤት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች የሥራ ውሉን ያቋረጠው በሕጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 39543

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የፍልውሃ አገልግሎት ድርጅት ነ/ፈጅ ካሣሁን ወርቁ - ቀረበ

**ተጠሪ፡-** አቶ በረከት ተ/ማሪያም - ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ የሥር ከሣሽ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ተጠሪ ባቀረቡት ክስ በአመልካች ድርጅት ሰራተኛ መሆናቸውን ጠቅሰው አመልካች የሥራ ውሌን ያለአግባብ ስላቋረጠብኝ ወደ ሥራዬ ይመልሰኝ ካልሆነ በሕጉ የተቀመጡትን ክፍያዎች ይክፈለኝ ሲል ጠይቋል፡፡

አመልካችም ለክሱ በሰጠው መልስ ተጠሪ ሊሰናበቱ የቻሉት አድራሻ የሌለውና ለማስረጃነት ብቁ ያልሆነ የሥራ ልምድ ማቅረባቸው በመረጋገጡ ነው፡፡ ስለዚህ ስንብቱ ሕጋዊ ነው በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም የቀረበለትን ክስ ግራ ቀኙ ባቀረቡት ክርክር አግባብነት ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሮታል፡፡ በዚህም መሠረት አመልካች በ26/5/2000 በፃፈው ደብዳቤ ተጠሪ ያቀረቡትን የምስክር ወረቀትን አስመልክቶ ድርጅቱ ተጠይቆ የአይስክሬም ሽያጭ በድርጅቱ እንደማይካሄድ ቢገልፅም፤ አመልካች ተገቢውን አካል መጠየቁንና ሰርቷል የተባለበትን ጊዜ አይገልፅም፣ ማስረጃው ትክክል አልነበረም እንኳ ቢባል በአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁ 377/96 አንቀጽ 27(1)(ሐ) መሠረት በሥራ ላይ ተፈፀመ የተባለው ማጭበርበር ድርጊት ሊባል የሚችለው ከቅጥር በኋላ ሰራተኛው ስራውን በሚያከናውንበት ወቅት የሚፈፅማቸውን የማጭበርበር ድርጊቶችን ነው፡፡ በመሆኑም የተፈፀመው ድርጊት በዚህ አንቀፅ ሥር የሚወድቅ ስላልሆነ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፡፡ በአዋጅ አንቀፅ 43(2)(5) መሠረት የሁለት ወር ደሞዙ ተከፍሎት ተጠሪ ወደ ሥራቸው ይመለሱ ሲል ወስኗል፡፡

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለትም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡ አመልካች ሐምሌ 22/2000 ዓ.ም ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እና በከፍተኛው ፍ/ቤት የተሰጡት ውሣኔዎች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሲል እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክራቸውን ሰምቷል ጉዳዩ በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የተጠሪ ስንብት ሕገ ወጥ ነው የሁለት ወር ደሞዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ ይመለስ መባሉን አግባብነት ለመመርመር ሲባል ነው፡፡ በዚህም መሠረት የግራ ቀኙ ካሰሙት ክርክር አቤቱታው የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው ሕግ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የጉዳዩን አመጣጥ ባጭሩ ስናይ የአመልካች ድርጅት ተጠሪን ሲያሰናብት መሠረት ያደረገው በሀሠተኛና ብቃት በሌለው ማስረጃ (የምስክር ወረቀት) በማቅረብ የተቀጠረ መሆኑን ባደረገው ማጣራት ደረስኩበት ሲል በማሰናበቱ ምክንያት የሥር ፍ/ቤቶችም ጉዳዩን በማከራከር ተጠሪ ፈፅመዋል የሚባል ድርጊት እንኳ ቢኖር በአዋጅ 377/96 አንቀጽ 27(1/ሐ) ሥር ሊወድቅ አይችልም በሥራ ላይ እያሉ የፈፀሙት ማጭበርበር አይደለም፣ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው፣ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝና ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ሲል ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቱ ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ሲል መሠረት ያደረገው የአዋጁን አንቀፅ 27(1/ሐ) በመጥቀስ ትርጉም በመስጠት የተጠሪ ድርጊት በሥራ ላይ እያሉ የተፈጠረ አይደለም ሲል ነው፡፡ የአዋጁ አንቀፅ 27(1/ሐ)"ን" ሙሉቃል ስናነብ "የሥራ ውልን ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚቻለው ሠራተኛው በሥራው ላይ የማታለል ወይም የማጭበርበር ተግባር ሲፈፀም ነው" ይላል፡፡ በመሆኑም የዚህን አንቀፅ ትርጉምና ተጠሪ የፈፀሙትን ማጤኑ አስፈላጊ ነው፡፡ ከመጀመሪያው አመልካች የስንብቱን ምክንያት ሲገለፅ ተጠሪ ባቀረቡት የሐሰት ማስረጃ መቀጠራቸውን የተጠራጠረው ተጠሪ በተቀጠሩበት የአይስክሬም ስራ ብቃት ስላጡና ደንበኛም እየቀነሰ በመምጣቱ እና ባደረገው የማጣራት ሥራ ማስረጃው ለተጠሪ ሰጠ ያለውን ድርጅት በግንባር በመሄድ በድርጅቱ አይስክሬም እንደማይሠራ በማረጋገጥ ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተጠሪ ያቀረቡት ማስረጃ በጥርጣሬ ውስጥ የወደቀ መሆኑን ነው፡፡

ባጠቃላይ ተጠሪ ከመጀመሪያውኑ ሲቀጠሩ በሐሰት ማስረጃ እስከሆነና በዚህም ማስረጃ ሥራቸውን መስራት ከጀመሩ በኋላ በመሀከሉ የማጭበርበር ድርጊት መፈፀማቸው እስከተደረሠባቸው ድረስ ይህ ድርጊት ተጠሪ በሥራቸው ላይ (ስራቸውን በማከናወን) እያሉ የፈፀሙት ነው ተብሎ ከመተርጐም ውጪ እንደ የሥር ፍ/ቤት አባባል በተቃራኒው ሊተረጐም የሚገባው አይደለም፡፡ በመጨረሻም ከግራ ቀኙ ክርክር ልንገነዘብ እንደቻልነው ማስረጃ ሰጠ የተባለው ድርጅት የአይስክሬም ሥራ (ሽያጭ) የማይከናወንበት መሆኑ ስለተረጋገጠ የተጠሪ ማስረጃ የተጭበረበረ ለመሆኑ በጥያቄ የሚገባ አይደለም፡፡

ስለዚህ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች ሣያገናዝብ ለአንቀጽ 27(1/ሐ) አግባብ ያልሆነ ትርጉም በመስጠት ስንብቱ ህገወጥ ነው ሲል፤ የከፍተኛው ፍ/ቤትም ይግባኙን መዝጋቱ መሠረታዊ የህግ ሥህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 24723 ቀን 4/10/2000 እና የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ.ቁ 68331 በቀን 17/11/2000 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ስንብቱ ሕጋዊ ነው፡፡ ተጠሪ የሁለት ወር ደሞዝ መከፈሉም ሆነ ወደ ሥራ ሊመለሱ አይገባም ብለናል፡፡
3. የግራ ቀኙ ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39042

ግንቦት 26 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዩቴክ ኮንስትራክሽን ኃ/የተ/የግል ማኅበር - የቀረበ የለም፡፡

**ተጠሪ፡-** ጀማል መሐመድ - ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳይ በአሠሪና ሠራተኛ መካከል የተነሣን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሠረተው በአናጺነት በቀን ብር 32.00 እየተከፈለኝ እንድሠራ ተቀጥሬ ስሠራ ቆይቻለሁ፡፡ በኋላ ግን ሥራው እያለ ያለአንዳች ጥፋት ምንም ዓይነት የቃልም ሆነ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ሳይሰጠኝ ከሥራ ተሰናብቻለሁ፡፡ ሥራውን በፈቃዱ ለቆአል የሚለውን ደብዳቤ የተቀበልኩት ደብዳቤውን ካልተቀበልክ ደመወዝ አትወስድም ስለተባልኩ እንጂ ፈቅጄ አይደለም፡፡ ስለዚህ በሕጉ የተፈቀዱትን ክፍያዎች በሙሉ ተከፍሎኝ እንድሰናበት ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽን የቀጠርኩት በቋሚነት ወይም በጊዜአዊነት ሳይሆን፣ በቁርጥ ሥራ ነበር፡፡ ሥራውን የለቀቀው በራሱ ፈቃድ ነው፡፡ ሥራውን ሲለቅ ሊከፈለው የሚገባ ክፍያ ሁሉ ወስዶአል፡፡ የቀረበት ክፍያ የለም በማለት እንደተከራከረ ከስር ፍ/ቤት ውሣኔ ይዘት መገንዘብ ችለናል፡፡

ክሱን የሰማው ፍ/ቤት ከሣሽ /የአሁን ተጠሪ/ የቁርጥ ሥራ ሠራተኛ ለመሆኑ ተከሣሽ አላስረዳም፡፡ ሥራው ከሣሹ በራሱ ፈቃድ ነው የለቀቀው በሚለው ነጥብ ላይም ከተከሳሽ ማስረጃ ይልቅ የከሣሽ ማስረጃ የሚያመዝን ሆኖ ተገኝቶአል፡፡ ከሣሽ ሥራውን ስለመልቀቁ የሚያሳይ ማስረጃም ተከሣሽ አላቀረበም የሚሉትን ምክንያቶች በመስጠት የሥራ ሙሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመቀጠልም አመልካች የስንብት፣ የማስጠንቀቂያ ጊዜ የአንድ ወር ደመወዝ የካሣ ክፍያ የ6 ወር ደመወዝ እና የዓመት ዕረፍት እንደ አገልግሎቱ መጠን ታስቦ ለከሣሽ /ለተጠሪ/ ይክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሣኔው ጉድለት የለበትም ብሎአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

የሰበር ችሎቱ አመልካች ሐምሌ 2 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕግ ውጪ ነው በሚል የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

ተጠሪ ለፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በፃፈው የክስ ማመልከቻ እንዳረጋገጠው የስንብት ደብዳቤ ተቀብሎ ሥራውን ከለቀቀ በኋላ ነው ወደ ክስ ያመራው፡፡ አመልካች በመከራከሪያነት ካነሳቸው ነጥቦች አንዱም ይህኛው ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ ሥራውን ስለመልቀቁ ማስረጃ አልቀረበም በማለት በውሣኔው ላይ ያሰፈረው ትችት ከዚህ አንፃር ሲታይ ስህተት ነው፡፡ በፍሬ ነገር በግልጽ የታመነን ሁኔታ እንደሌለ አድርጎ ማለፍ አይቻልምና፡፡

ሌላው ከሥር ጀምሮ ከተደረገው ክርክር ይዘት የተመለከትነው ተጠሪ ይሠራበት የነበረው ሥራ የኮንስትራክሽን /ፕሮጀክት/ ሥራ ነው፡፡ የሥራ መደቡም አናጺነት ነው፡፡ በፕሮጀክት የተያዘ የኮንስትራክሽን ሥራ በተወሰነ ጊዜ የሚያልቅ በመሆኑ በዚህ ሥራ የተቀጠሩት ሠራተኞችም እንደቅደም ተከተሉ የሚሠናበቱ ናቸው፡፡ የተጠሪን የሥራ መደብ ስንመለከት የአናጺነት ሥራ ስለሆነ ምናልባትም ከሌሎቹ ሥራዎች ቀድሞ የሚያልቅ ነው፡፡ ተጠሪ በክሱ እንዳረጋገጠው በአናጺነት ሥራ ልምድ ያለው /ያገኘ/ መሆኑ ተገልጾ ማስረጃ እንዲሰጠው ጠይቆ ከተሰጠው በኂላ የተሰናበተውም በዚህ ምክንያት እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 30/1/ እንደተመለከተው የኮንስትራክሽን ሥራው እያለቀ ሲሄድ የሥራው መጠን በመቀነሱ ምክንያት በሥራ ተቀጥረው በሚሠሩ ሠራተኞች ላይ ቅነሣ ሊደረግ ይችላል፡፡ ቅነሳው ሲደረግም አሠሪው በአዋጁ የተመለከቱትን የሠራተኞች ቅነሳ ሥነ ሥርዓት መከተል አይኖርበትም፡፡ በያዝነው ጉዳይ የሆነውም ይኸው ነው፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን ይህን ሁኔታ አገናዝበው ውሣኔ አልሰጡም፡፡ ከዚህ የተነሣም አቤቱታ የቀረበበት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 29019 ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 67143 ሰኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የሥራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 38189

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

**አመልካች፡-** ሮፓክ ኢንተርናሽናል ኃላ.የተ.የግል ማህበር - ጠበቃ ያለለት ተሾመ ቀረበ

**ተጠሪ፡-** ይደርሣል አእምሮ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ህዳር 08 ቀን 1999 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከሚያዝያ 15 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ በወር ብር 1200.00 ደመወዝ እየተከፈላቸው በአመልካች መ/ቤት በዕቃ ግምጃ ቤትነት እስከ 03/13/98 ዓ.ም ድረስ መስራታቸውን ሆኖም ከዚሁ ከተቀጠሩበት የስራ መደብ አመልካች መ/ቤት አንስቷቸው በወር ብር 650.00 በሚከፈልበት የሠዓት ተቆጣጣሪነት የስራ መደብ አዛውሯቸው ቅሬታ ቢያሰሙም ተገቢው ምላሽ በወቅቱ አመልካች ሣይሠጣቸው መቅረቱንና ከስራ ያሠናበታቸው ያላግባብ መሆኑን ዘርዝረው የካሣ፣ የአምስት ዓመት አገልግሎት፣ የዓመት ፈቃድ፣ የህዝብ በዓላት የ14 ቀናት ክፍያ፣ ለዘገየበት ክፍያ እንዲከፍልና የስራ ምስክር ወረቀት እንዲሠጣቸው ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው፡፡ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦም ተጠሪ የተሠናበቱት ከ22/12/1998 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 04/13/1998 ዓ.ም ድረስ በስራ ቦታቸው ላይ ስላልተገኙ መሆኑን ገልፆ ስንብቱ ህጋዊ ነው በማለት ተከራክሯል፡፡ የስር ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ ጉዳዩን መርምሮ ተጠሪ ከተቀጠሩበት የስራ መደብ ወደ ሌላ ተዛውረው ቅሬታ እያሠሙ ባሉበት ሁኔታ በስራ ቦታቸው አልተገኙም ማለት ተገቢነት የሌለው ነው የሚለውን ነጥብ በምክንያትነት ይዞ የአመልካችን እርምጃ ከህግ ውጪ ነው በማለት የተለያዩ ክፍያዎች ለተጠሪ እንዲከፈሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ቢያቀርብም ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ጠበቃ ግንቦት 29 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ከስራ ገበታቸው ከ10 ቀናት በላይ ስለመቅረታቸው ተረጋግጦ እያለ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1/ለ) ስር ከተመለከተው ውጪ በተሣሣተ ትርጉም ተጠሪ ከስራ የቀሩት በበቂ ምክንያት ነው ማለታቸው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው መልሣቸውን መስከረም 27 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ወደተዛወሩበት የስራ መደብ ያልተገኙት የአመልካች ዘበኞች ያረጋገጡት ፍሬ ጉዳይ መሆኑንና የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔም የትርጉም ስህተት ያልተፈፀመበት መሆኑን ዘርዝረው ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች ጠበቃ በበኩላቸው ህዳር 04 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የመልስ ማመልከቻ ተጠሪ ወደ አመልካች ግቢ ለመግባት በዘበኛ ተከልክያለሁ የሚሉት ክርክር አዲስ መሆኑን ገልፀው የሠበር አቤቱታቸውን በማጠናከር ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ተጠሪ የተመደቡበት የስራ መደብ ካለሙያ ነው በማለት ከስራ ገበታው ላይ ለ10 ተከታታይ ቀናት በላይ በመቅረቱ አመልካች ከስራ ሲያሰናብተው የስራ ውሉ የተቋረጠው ያለበቂ ምክንያት ነው ተብሎ የአመልካች እርምጃ ህገ ወጥ ነው ሲባል መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሁኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካች የተጠሪን የስራ ውል ያቋረጠው ተጠሪ በተዛወሩበት የስራ መደብ ሣያገኙ ከ10/አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ መቅረታቸውን መሠረት በማድረግ መሆኑንና ተጠሪ በበኩላቸው የሚከራከሩት በተዛወሩበት የስራ መደብ ያልተገኙት የአመልካች ዘበኞች ግቢ እንዳይገቡ ስለከለከሏቸው እና የስራ መደብ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ አሰምተው ውጤቱን እየተጠባበቁ ስለነበር መሆኑን በመግለፅ ነው፡፡

እንግዲህ አመልካች ተጠሪን ከተቀጠሩበት የስራ መደብ ወደ ሌላ የስራ መደብ በማዛወር ተጠሪ ተገቢው ደብዳቤ ከተሠጣቸው በኂላ በተዛወሩበት የስራ መደብ ሣይገኙ ከ10/አስር/ ተከታታይ ቀናት በላይ የቀሩት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ ስለመሆኑ በመጥቀስ ይኸው ተግባር በቂ ምክንያት ነው ሲሉ ተጠሪ የሚከራከሩ ሲሆን የአመልካች ጠበቃ ይህንኑ የክርክር ነጥብ በስር ያልተነሣ ስለመሆኑ ጠቅሰው የመልስ መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍ/ቤትን ዋና መዝገብ በማስቀረብ ጉዳዩን ሲያጣራው በስር ፍ/ቤት ክሱ በተሠማበት ወቅት ተጠሪ ይህንኑ የክርክር ነጥብ አንስተው ምስክሮቻቸውም የሚያስረዱት ጭብጥ መሆኑን ገልፀው ምስክሮቻቸው መስማታቸውን አረጋግጧል፡፡ በመሆኑም የአመልካች ጠበቃ አዲስ ክርክር ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ ከላይ የተጠቀሠውን የክርክር ነጥብ በስር ፍ/ቤት ያነሡት ቢሆንም ጉዳዩን ለማስረዳት የተሠሙት ምስክሮች ግን የአመልካች ጠበቃ ተጠሪን ግቢ እንዳይገቡ የከለከሏቸው ስለመሆኑ የሠጡት የምስክርነት ቃል የለም፡፡ የስር ፍ/ቤትም ተጠሪ በስራ ቦታቸው ላይ ያልተገኙት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ አለመሆኑን በመገንዘብ ተጠሪ በስራ መደቡ ለውጥ ምክንያት ቅሬታ እያሰሙ ባሉበት ሁኔታ በስራ ገበታቸው ላይ አልተገኙም ሊባል አይገባም በማለት ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ በተዛወሩበት የስራ መደብ ከአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ ያልተገኙት በአመልካች ጥበቃ ክልከላ ምክንያት አለመሆኑን ስለተገነዘብን በዚህ ረገድ ያቀረቡትን ክርክር ውድቅ አድርገናል፡፡

የስር ፍ/ቤት ተጠሪ በስራ ላይ ያልተገኙት ዝውውሩን ተቃውመው ቅሬታ ሲያሠሙ በነበረበት ወቅት መሆኑን ጠቅሶ ተጠሪ ያለበቂ ምክንያት ከስራ ቀርተዋል ሊያስብላቸው አይችልም፡፡ ሲል የደረሠበትን ድምዳሜ ህጋዊነቱን ተመልክተናል፡፡

በመሠረቱ በቂ ምክንያት ሣይኖረው በተከታታይ ለአምስት የስራ ቀናት በስራ ገበታው ያልተገኘ ሠራተኛን ማስጠንቀቂያ መስጠት ሣያስፈልግ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ለአሠሪው ህጉ የሠጠው ስልጣን መሆኑን የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27(1/ለ) ድንጋጌ ያሣያል፡፡ ሠራተኛው የአሠሪውን እርምጃ ሊቃወመው የሚችለው በቂ ምክንያት ያለው ስለመሆኑ በማስረዳት ነው፡፡ በቂ ምክንያት የሚለው ሀረግ መመዘኛው ደግሞ ሠራተኛው ከስራ ቦታው ሊገኝ የማይችልበት ሁኔታ ስለመኖሩ ሊያመላክቱ የሚችሉ ምክንያቶች ስለመሆኑ ከአዋጁ አጠቃላይ ዓላማና ከተጠቃሹ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ለመገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም ከስራ የቀረ ሠራተኛ በቂ ምክንያት ኑሮት ከስራው ቀርቷል ለማለት የሚቀርበው ማስረጃ ሠራተኛው በስራ ቦታው ለመገኘት የሚያስችል መሰናክል የነበረ መሆኑን የሚያስረዳ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህም ሠራተኛው ባልተገባ ምክንያት ከስራው በመቅረት በምርትና ምርታማነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳያሳድር ሊያደርግ የሚችል ነው፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስም ተጠሪ በስራ ገበታቸው ያልተገኙት ምክንያት የስራ መደብ ዝውውሩን በመቃወም ቅሬታ እያሰሙ በነበሩበት ወቅት ስለመሆኑ የስር ፍ/ቤት ገልጿል፡፡ ሆኖም የስራ መደብ ዝውውር መደረግና ሠራተኛው ቅሬታውን በማሠማት ላይ መሆኑ በስራ ቦታ ላለመገኘት እንደ በቂ ህጋዊነት ምክንያት የሚወሠድ አይደለም፡፡ የስራ መደብ ዝውውሩ ሠራተኛው በስራው ቦታ እንዳይገኝ መሠናክል የሚሆንበት ሁኔታ የለምና፡፡ ሠራተኛው በዝውውሩ ላይ ቅሬታ ካለውም ስራውን እየሠራ በህጉ በተዘረጋው ሥርዓት መሠረት መብቱን ማስጠበቅ አለበት እንጂ ከስራው ሊቀር

አይገባም፡፡ ስለሆነም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሠረት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 32745 ጥር 05 ቀን 2000 ዓ.ም ተሠጥቶ በፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 62988 መጋቢት 01 ቀን 2000 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው በህጉ መሠረት ነው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 37982

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- አቶ ታደሰ ዘነበ - ጠበቃ ደርበው ተመስገን

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ ጉዳይ የሥራ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ከመጋቢት 26 ቀን 1995 ዓ.ም. በተከሣሽ ድርጅት የሥራ መሪ በመሆን በመስራት ላይ እንዳለሁ የአሠሪና አመራር ድክመት አሳይተሀል በሚል ከነሐሴ 1997 ዓ.ም. ጀምሮ በተከታታይ የሶስት ዓመት እረፍት እንድወስድ የተደረገ ሲሆን ከጥር 22 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ከመምሪያ ሥራ አስኪያጅነትና ከማናጅመንት አባልነት ተከሣሽ እንድነሳ ካደረገ በኂላ ከመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ ደግሞ ከሥራና ከደመወዝ ታግጃለሁ፡፡ በድርጅቱ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ መሠረት ዕገዳ ከአንድ ወር ሊበልጥ እንደማይችል የተመለከተ ሲሆን ይህንን መመሪያ በመጣስ ተከሣሽን በዕግድ ያቆየው አላግባብ መሆኑ ተገልፆ ወደ ሥራ እንዲመለስና ውዝፍ ደመወዝም እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽም በሰጠው መልስ የከሣሽ የክፍያ ጥያቄ በ6 ወር ይርጋ ይታገዳል፡፡ ከሣሽ ከሥራ የተነሱት ከባድ የሥራ ጉድለት በመፈፀማቸው ሲሆን የሥራ መሪም ስለሆኑ ወደ ቀድሞ ሥራቸውም ሆነ ወደ ሌላ ተመጣጣኝ ሥራ ለመመለስ ግዴታ የለብንም፡፡ ከሣሽ ላልሰሩበት ጊዜ ደመወዝና አበል እንዲከፈላቸው መጠየቅ አይችሉም፡፡ ስለሆነም ክሱ ተሰርዞ ልንሰናበት ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

የግራ ቀኙ ክርክር በዚህ መልኩ የቀረበለት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ጉዳዩን መርምሮ ከሐምሌ 1997 ዓ.ም. በሥራ ላይ በዋለው የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 35/2/ መሠረት በጥፋት ምክንያት አንድ የሥራ መሪ ከሥራ ሲታገድ ታግዶ የሚቆየው ከአንድ ወር ለማይበልጥ ጊዜ እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት በዚህ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለዕገዳው ምክንያት በሆነው ጉዳይ ላይ ተከሣሽ በዲስፒሊን ውሣኔ መስጠት አለበት ማለት ነው፡፡ ይህን ውሣኔ ካልሰጠ በከሣሽ ላይ የሰጠው ዕገዳ ተፈፃሚነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም ተከሣሽ ከመጋቢት 15 ቀን 1998 ዓ.ም. ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያለውሣኔ አግዷቸው የሚገኙትን ተከሣሽን ወደ ሥራቸው ወይም ከቀድሞ ሥራቸው ጋር ተመጣጣኝ በሆነ ሥራ ላይ የመመደብ ግዴታ አለበት፡፡ የደመወዝ ክፍያን በተመለከተ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ከሣሽ በሥራ ላይ ያልተገኙት ተከሣሽ ያለአግባብ እንዳይሰሩ ስለከለከላቸው በመሆኑ ክሱ ያቀረቡበትን የደመወዝ መጠን እና ተያይዞ የተደረገውን ጭማሪ እንደዚሁም ከሣሽ ሥራ ላይ በነበሩበት የ1997 ዓ.ም. የሥራ ዘመን የተከፈለውን ቦነስ ጨምሮ እንዲከፈላቸው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚህ ውሣኔ ቅሬታ አድሮበት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌደራል ከፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው ያቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪ አመልካችን ወደ ሥራ ሊመልሳቸው ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 እና 2574 አኳያ አግባብነቱ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡-

ተጠሪ ወደ ሥራ እንዲመለሱ የተወሰነው በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? በአግባቡ አይደለም ቢባል ካሣ ሊከፈላቸው ይገባል ወይስ አይገባም? ውዝፍ ደመወዝስ? የሚሉት ናቸው፡፡

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል ያለው ከላይ እንደተመለከተው በሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ ላይ እንደተመለከተው ዕገዳው የሚቆየው ለ1 ወር ጊዜ ብቻ ሆኖ ሳለ ከዚህ ጊዜ በላይ አግዶ ማቆየት ዕገዳው ተፈፃሚ እንደማይሆን ያደርገዋል በሚል ነው፡፡ በተጠቀሰው የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 35/2/ መሠረት አንድ የሥራ መሪ በዲስፒሊን ጉድለት ምክንያት ታግዶ የሚቆየው ለአንድ ወር ጊዜ እንደሆነ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

ነገር ግን አንድ የሥራ መሪ በዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ ታገዶ እንዳለ በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልተሰጠው ዕገዳው ተፈፃሚ የማይሆን ስለመሆኑ በደንቡ ላይ አልተመለከተም፡፡ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ዕገዳው ተፈፃሚ አይሆንም ወደሚል መደምደሚያ የደረሰው የደንቡን ድንጋጌ በመጥቀስ ሳይሆን የእራሱን ግንዛቤ በመውሰድ ነው፡፡

ስለሆነም የሥራ መሪው ከሥራ ታግዶ የሚቆይበት ጊዜ ከአንድ ወር ከበለጠ ዕገዳው ተፈፃሚ አይሆንም ማለት በደንቡ ባልተሸፈነበት ሁኔታ ነው፡፡

ይልቁንም ይህንኑ በሚያጠናክር ሁኔታ ሥራ መሪው በዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት ከሥራ ታግዶ በሚቆይበት ጊዜ ጥፋቱ ተጣርቶ ውሣኔ እስከሚያገኝ ደመወዝ አይከፈለውም ተብሎ በዚሁ የሥራ መሪዎች መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 35/3/ ላይ መደንገጉ ሲታይ ዕገዳው ከዚህ ጊዜ ከረዘመ ለሥራ መሪው ደመወዝ ሊከፈለው እንደሚገባ ከድንጋጌው ተቃራኒ ንባብ /A contraire Reading/ መረዳት ስለሚቻል የዕገዳው ጊዜ መራዘም ዕገዳውን ሕገ ወጥ ሊያደርገው የሚችል አለመሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘም በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 መሠረት አሠሪ የሥራ ውሉን ቀሪ ለማድረግ በቂ ምክንያት ባይኖረውም እንኳን ለሠራተኛው ተገቢ የሆነ ካሣ ለመክፈል ከሚገደድ በሥተቀር ሠራተኛውን ወደ ሥራ ለመመለስ ግዴታ እንደሌለበት መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም ተጠሪ ከሥራ የተሰናበቱት በበቂ ምክንያት አይደለም ቢባል እንኳን ከፍ ብለው በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 መሠረት አመልካች ወደ ሥራ የመመለስ ግዴታ የሌለበት ስለሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል በማለት የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተም ተጠሪ ከሥራ የታገዱት በፈፀሙት የዲስኘሊን ጉድለት ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ አመልካች አጥብቆ የተከራከረ ቢሆንም የተወሰደባቸው የዲስኘሊን ዕርምጃ ስለመኖሩ ወይንም ደግሞ ጥፋት የፈፀሙ ስለመሆናቸው አላስረዳም፡፡ ምንም እንኳን የተጠሪ ጥያቄ ወደ ሥራ የመመለስ ቢሆንም ስንብቱ ሕገ ወጥ ነው ከተባለ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2573 ደንጋጌ መሠረት ካሣ የማግኘት መብት ያላቸው በመሆኑ ካሳ ሊከፈላቸው የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመጨረሻም ተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው ይገባል ወይንስ አይገባም የሚለውን በተመለከተም ተጠሪ በክስ የጠየቁት ከመጋቢት ወር 1998 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ መስከረም 1999 ዓ.ም. ድረስ የተቋረጠ ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት ነው፡፡

የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤትም ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈላቸው ይገባል ያለው ከሣሽ በሥራ ላይ ያልተገኙት ተከሣሽ ያለአግባብ ሥራ እንዳይሰሩ ስለከለከላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ለመክፈል ይገደዳል በማለት ነው፡፡

ከላይ እንደተመለከተው አመልካች ተጠሪን ከሥራ ካገደ በኂላ በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለዕገዳው ምክንያት በሆነው ጉዳይ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይጠበቅበት ነበር፡፡ በዚህ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ ደመወዝ ለመክፈል እንደሚገደድ መተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 35/3/ ድንጋጌ ተቃራኒ ንባብ መገንዘብ እንደሚችል ከላይ ተመልክተናል፡፡ እንደዚሁም አመልካች ይህንኑ የዕገዳ ጊዜ አራዝሞ መገኘቱ ሠራተኛው ለሥራ ዝግጁ ሆኖ ሳለ በዕገዳው ምክንያት ሥራ እንዳይሠራ ማድረጉን የሚያሳይ እንደመሆኑ  መጠን በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/2541/1/ መሠረት ዕገዳው ጸንቶ ከሚቆይበት ጊዜ በላይ ላለው ጊዜ አመልካች በተጠሪ ደመወዝ ለመክፈል ስለሚገደድ ይህም የደንቡን ድንጋጌ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም አመልካች ዕገዳው ከሚያበቃበት ቀን ጀምሮ ውዝፍ ደመወዝና ከደመወዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ክፍያዎች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 70391 በ8/8/99 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 54707 በ10/8/2000 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/348/1/ መሠረት በማሻሻል ተጠሪ ወደ ሥራ ሊመለሱ ይገባል የተባለውን ሽረን የ3 /ሶስት/ ወር ደመወዝ ካሳ ተከፍሏቸው ይሰናበቱ ብለናል፡፡ ለተጠሪ ውዝፍ ደመወዝ የደመወዝ ጭማሪና ቦነስ ይከፈላቸው ተብሎ የተወሰነውን አጽንተናል፡፡
2. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 41720

ሰኔ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

**አመልካች**፡- የእንጨት መሰንጠቂያና መገጣጠሚያ ድርጅት - ከበደ መኰንን ቀረበ፡፡

**ተጠሪ**፡- ረዲ እንዳለ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተነሳውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ያኔ ከሣሽ የነበረው ተጠሪ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው የስራ ውሌን ከሕግ ውጪ ስላቋረጠብኝ ውዝፍ ደመወዜን በመክፈል ወደስራዬ እንዲመልሰኝ ይገደድልኝ፤ይህ ካልተቻለም የስራ ውል ከሕግ ውጪ በሚቋረጥበት ጊዜ ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ከፍሎ ያሰናብተኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ የስራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው ከሣሽ ለስራ የተሰጠውን ገንዘብ አጉድሎ በመገኘቱ ነው፤ ከዚህ በተጨማሪም የድርጅቱን ንብረት ያለአግባብ ወጪ እንዲሆን አድርጓል፤ በመሆኑም ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው በማለት ስለመከራከሩ መዝገቡ ያመለክታል፡፡ ክሱን የሰማው ፍ/ቤትም ክርክሩን ከመረመረ በኋላ ከሣሽ የተከሣሽን ገንዘብ ስለማጉደሉ በማስረጃ የተረጋገጠ እና በከሣሽም ያልተካደ ስለሆነ የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ መሰረት ነው በማለት ወስኗል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን፣በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ በመሻር ተጠሪ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ስራው ይመለስ በማለት ወስኗል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 1 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ ገንዘቡን ስለማጉደሉ እና ለቤተሰቦቹ መንቀሳቀሻ እንደተጠቀመበት በችሎት አምኖ እያለ የስራ ውሉ ከሕግ ውጪ ነው የተቋረጠው በማለት ውሳኔ የመስጠቱን አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ተጠሪ ለስራ ማስኬጃ እንዲውል ተብሎ ከተሰጠው የድርጅቱ ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን አጉድሎ ስለመገኘቱ በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጦአል፡፡ አመልካች የስራ ውሉን ያቋረጠው ይህን መሰረት በማድረግ እንደሆነም አላከራከረም፡፡ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል ተመስርቶ የነበረውን የስራ ውል ስለሚቋረጥባቸው ሕጋዊያን ምክንያቶች በሚመለከት በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 በዝርዝር ተመልክቶአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አወሳሰን ተገቢነት የአዋጁ አንቀጽ 27 ሲሆን፣ይህም ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል የሚቋረጥባቸውን ምክንያቶች በዝርዝር አስቀምጦአል፡፡ ተጠሪ በአሰሪው (በአመልካች) ገንዘብ ያለአግባብ ስለመጠቀሙ ተረጋግጦአል፡፡ ይህ ድርጊት ያለማስጠንቀቂያ የስራ ውል ከሚያቋርጡ ምክንያቶች አንዱ እንደሆነ በተጠቀሰው አንቀጽ 27(1)(መ) ተመልክቶአል፡፡

እንግዲህ ሕጉ ይህን ያሕል ግልጽ ከሆነ ከዚህ በተቃራኒ መወሰን የሚቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ሲጠቃለል የስራ ውሉ የተቋረጠው በሕግ አግባብ መሆኑ ግልጽ ሆኖ ሳለ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተቃራኒው መወሰኑ ትክክል አይደለም፡፡ ውሳኔው በሕጉ አተረጓጎም ረገድ መሰረታዊ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 69766 ኀዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው በሕግ አግባብ ነው ብለናል፡፡ ስለዚህም የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 25280 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ ፀንቶአል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39861

ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** የኢት/ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን - የቀረበ የለም።

**ተጠሪ:-** አቶ ሣምሶን በለጥካቸው - ቀረቡ።

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም የአሁኑ ተጠሪ ታኅሣሥ 14 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት የክስ ማመልከቻ አመልካች ከሕግ ውጭ የሥራ ውሉን በማቋረጥ ያሠናበታቸው መሆኑን ዘርዝረው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአመልካች ላይ በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ መነሻ ነው። የአሁኑ አመልካችም በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መከላከያ መልስ የተጠሪ ስንብት ሕጉን የተከተለ ስለመሆኑና ለዚህም ምክንያቱ ተጠሪ ለቢሮ እቃዎች ጥገና ወጪ የተደረገበት ሰነድ ቀደም ሲል የተፃፈው 20 /ሃያ/ ብር ተደልዞ 100.00 /መቶ ብር/ እንዲሆን የተደረገና ተጠሪ የክፍያ ሰነዱን ራሣቸው ያዘጋጁትና የደለዙት መሆናቸውን፣ ከዚህም በተጨማሪ ተጠሪ ለሥራ አዲስ አበባ ሄጃለሁ በማለት አበል በወሰዱባቸው ቀናት ደብረ ብርሃን ሥራ ላይ የነበሩ መሆኑ በአግባቡ በሰነድ ማስረጃ በመረጋገጡና እርምጃውም በሕጉ የተመለከተውን ቀነ ገደብ ውስጥ የተፈፀመ መሆኑን ገልፆ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል። ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የወረዳው ፍ/ቤትም አመልካች ተጠሪን ከሥራ ያሠናበተበት ምክንያት ተገቢ በሆነ የጊዜ ገደብ ባለመሆኑ ሕግን የተከተለ የሥራ ስንብት ሊባል የሚችል አይደለም በማለት የተጠሪን ደመወዝ አመልካች መክፈል ካቋረጠበት ጊዜ ጀምሮ ለተጠሪ ከፍሎ ወደ ስራው እንዲመልስ በማለት ወስኗል። አመልካች በዚህ ውሣኔ ባለመስማማት ይግባኙን ለዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ አመልካች የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ያቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ካለ በኋላ አመልካች ለተጠሪ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 39 እና 40 መሠረት የሥራ ስንብት ክፍያና ካሣ ይከፈለው በማለት ውሣኔ ሠጥቷል። የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው።

የአመልካች ነ/ፈጅ ነሐሴ 06 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፉት 3 /ሦስት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል። ይዘቱም ባጭሩ:- ተጠሪ ከሥራ የተሠናበተው በጥፋቱ ስለሆነ ስንብቱ ሕጋዊ ነው ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ካሣና የስንብት ክፍያ አመልካች ይክፈለው ተብሎ መወሰኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 39 እና 40 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው። የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ግንቦት 24 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ 2 /ሁለት/ ገጽ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል። በመልሣቸውም የተፈፀመ ጥፋት ሣይኖር በሕጉ አግባብ ያለበቂ ማስረጃ ከሥራ የተሠናበትኩ ሆኖ እያለ ካሣና የስንብት ክፍያ ሊከፈል አይገባውም ተብሎ የሰበር ቅሬታ መቅረቡ ተገቢ አይደለም በማለት ተከራክረዋል።

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለ መልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው ከተባለ የካሣና የስንብት ክፍያ እንዲከፈል መወሰን ሕጋዊነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው በአመልካችና በተጠሪ መካከል በቅጥር ላይ የተመሠረተ የሥራ ውል ግንኙነት የነበረ መሆኑን፣ አመልካች የሥራ ውሉን ማቋረጡንና ያቋረጠበት ምክንያትም ተጠሪ ሠነድ በመደለዝ በሰነዱ ላይ ያለውን የገንዘብ መጠን አበላልጠው በመገኘታቸውና የውሎ አበል ያላግባብ ተጠቅመው መገኘታቸው በመረጋገጡ ስለመሆኑ ነው፡፡ ይኸው የተጠሪ አድራጎት በተገቢው ማስረጃ መረጋገጡንና የሥራ ውሉ የተቋረጠበት መንገድም በሕጉ አግባብ ስለመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ የተመለከተው የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤት ያረጋገጠው ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ስንብቱ ከመነሻው ያላግባብ ስለመሆኑ በመግለጽ ለዚህ ችሎት መልስ ሠጥተዋል፡፡ ይሁን እንጂ ክርክራቸው ሥርዓቱን ተከትሎ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ወይም መስቀለኛ የሰበር መቃወሚያ ሊባል የማይችል በመሆኑ ተቀባይነት ስለሌለው በዚህ የክርክር ደረጃ ሊታይ የሚገባው አይደለም በማለት አልፈነዋል፡፡

በዚህ መዝገብ ወደተያዘው አቢይ ጭብጥ ስንመለስም የቅጥር ውል ሕጋዊ ወይም ሕጋዊ ባልሆኑ ምክንያቶች ሊቋረጥ እንደሚችል፣ ውጤቱም የተለያየ መሆኑን ሕጉ ያስገነዝባል፡፡

የሥራ ውል በሕጋዊ መልኩ ተቋረጠ የሚባውም በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 24፣ 25፣ 27፣ 28፣ 29፣ 31 እና 32 ድንጋጌዎች መሠረት የቅጥር ውሉ ውጤት እንዳይኖረው ሲደረግ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ የሚደረግ የሥራ ውል ማቋረጥ እርምጃ ከሕግ ውጪ ነው፡፡ በእያንዳንዱ የሥራ ውል መቋረጥ ጊዜ አሠሪው በአዋጁ አንቀጽ 12/7/ ላይ በተደነገገው መሠረት የሥራ ልምዱን የሚገልጽ ደብዳቤ የመስጠት ግዴታውን መወጣት ይኖርበታል፡፡ ከክፍያዎች ጋር በተያያዘ ግን የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ሆኖ መገኘት አሠሪው ለሠራተኛው ለመክፈል እንደማይገደድ የአዋጁ አንቀጽ 39 እና 42 እንዲሁም ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ቅርጽና ይዘት ያስገነዝባል፡፡ የሥራ ስንብት ክፍያ አሠሪ ለሠራተኛ ለመክፈል የሚገደደው የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ ሲያቋርጥ ስለመሆኑ የአዋጁ አንቀጽ 39/1/ለ/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡ ሌላው ሕጋዊ ያልሆነ የሥራ ውል ማቋረጥ ሊያስከትለው የሚችለው ውጤት ካሣ ሲሆን ይህም ሊፈፀም የሚችለው በአዋጁ አንቀጽ 42 ሥር የተመለከተው መመዘኛ ተሟልቶ የሥራ ውሉ የተቋረጠው ከሕጉ አግባብ ውጪ ስለመሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የካሣ ክፍያ ዓላማም ሕገወጥ እርምጃን መከላከልና የሥራ ውሉ ከሕግ ውጪ የተቋረጠበት ሠራተኛ በተቻለ መጠን ወደነበረበት ቦታ እንዲመለስ ማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ የሆነ የሥራ ውሉ የማቋረጥ እርምጃ ካሣን የማስከፈል ውጤት የለውም፡፡ ሲጠቃለልም የሥራ ውሉ የተቋረጠው በሕጉ አግባብ ነው እየተባለ የሥራ ስንብትና የካሣ ክፍያ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት ባለመኖሩ የሰሜን ሸዋ አስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በጉዳዩ ላይ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በደብረብርሃን ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07034 ጥር 26 ቀን 2000 ዓ.ም. ተሰጥቶ በሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18364 ግንቦት 22 ቀን 2000 ዓ.ም. የተሻሻለው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡

2/ የተጠሪ የሥራ ስንብት በሕጉ አግባብ የተደረገ ስለመሆኑ ከተረጋገጠ የሥራ ስንብት እና የካሣ ክፍያ የሚከፈልበት ሕጋዊ ምክንያት የለም ብለናል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 43610

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ናይኮን ኃ/የተ/የግ/ማ - ጠ/ማስተዋል ሐብታሙ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሠለሞን ተሠማ - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሠበር አቤቱታ ምክንያት የሆነው ጉዳይ የጀመረው ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ያቀረቡት ክስ ነው፡፡ በክሣቸውም ያለአግባብ ከስራ ስለተሠናበቱ ወደ ስራቸው እንዲመለሱ ካልሆነ ህጉ የሚፈቅደው ክፍያዎች እንዲከፈሏቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ድርጅቱ ሣይሆን ከስራ ያሠናበታቸው በራሣቸው ፈቃድ ከሥራ በመቅረታቸው ነው ውሉ የተቋረጠው በማለት የተከራከረ ሲሆን ፍ/ቤቱ ተጠሪ በራሳቸው ፍቃድ ነው ስራውን የለቀቁት በማለት ክሱን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሠኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ስንብቱ ህገ-ወጥ ነው በማለት የ7 ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ሥራ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አቤቱታው ለሠበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ቀርበው የቃል ክርክራቸው ተሠምቷል፡፡ መዝገቡም እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በመሠረቱት ክስ የአመልካች ድርጅት ባለቤት ስልክ ደውለው ከስራ ያሠናበቷቸው መሆኑን ነው የገለፁት በመሆኑም በዚህ መልኩ የስራ ውላቸው መቋረጡን በቅድሚያ የማስረዳት ሸክም ያለባቸው ተጠሪ ናቸው፡፡ ይህንንም ለማስረዳት ተጠሪ ምስክሮች ቆጥረዋል፡፡ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ምስክሮች ግን በተጠሪ የክስ አቀራረብ መሰረት እንዳላስረዱ የሥር ፍ/ቤት አረጋግጧል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ በስልክ የስራ ውላቸው መቋረጡን አላስረዱም ማለት ነው፡፡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤትም ቢሆን ስልክ ተደውሎ የተጠሪ የሥራ ውል መቋረጡን ተጠሪ አስረድተዋል አላለም፡፡ ይህም ተጠሪ ክስ የመሠረቱበትን ጉዳይ አለማስረዳታቸውን ያረጋግጣል፡፡ ይልቁንም ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ያቀረቧቸው 3ኛ ምስክር የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪ ስልክ ላይ ደውለው የስራ ቦታቸው በመቀየሩ ወደ ተቀየሩበት ቦታ እንዲሄዱና ወደ ቀድሞ ስራ ቦታቸው እንዳይገቡ መከልከላቸውን ነው ያስረዱት፤ ይህ ደግሞ የሚያስረዳው ለተጠሪ በስልክ የተነገራቸው የስራ ቦታቸው መቀየሩን እንጂ የሥራ ውላቸው መቋረጡን አይደለም፡፡ በሌላ በኩል ተጠሪ በስልክ የተገለፀላቸው የሥራ ቦታ ሄደው እንዳይገቡ ወይም እንዳይሠሩ መከልከላቸውን ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ የለም፡፡ በአጠቃላይ ተጠሪ አመልካች ከሥራ ያሠናበታቸው መሆኑን ያለባቸውን የማስረዳት ሸክም ሣይወጡ ይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የተጠሪ የሥራ ስንብት ህገ-ወጥ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 70728 ታህሣስ 28/2001 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 31913 ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም የሠጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. የተጠሪ የሥራ ውላቸው በህገ-ወጥ መንገድ የተቋረጠ መሆኑን ገልፀው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 44033

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- መንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ጽ/ቤት ነ/ፈጅ ወንድሙ መልኬ

**ተጠሪ**፡- አቶ ይበልጣል አጥናፉ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

በስር ፍ/ቤት ተጠሪ ከሣሽ ነበሩ፡፡ በክሣቸውም አመልካች ያለአግባብ ያዛወሯቸው በመሆኑ ቀደም ብሎ ወደነበሩበት የስራ መደብ እንዲመለሱ እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካችም ዝውውሩ ህጋዊ በመሆኑ ክሱ ተቀባይነት የለውም ብሎ ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት የተደረገው ዝውውር ህገ ወጥ ነው በማለት ወደ ነበሩበት የስራ መደብና የስራ ቦታ እንዲመለሱ ወስኗል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ይግባኙ ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ችሎቱም አመልካች ያደረገው ዝውውር ሕገ ወጥ ነው ተብሎ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታውን ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጐ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር አድምጧል፡፡ አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔም ከተገቢው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ተጠሪ በክሣቸው በመ/ቤቱ ውስጥ በደረሰብኝ ድብደባ እንድታረቅ ተጠይቄ ፈቃደኛ ባለመሆኔ ያለአግባብ ወደ ሌላ ሥራ ተዛውሬአለሁ በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካችም ተጠሪን ማዛወሩን አልካደም አመልካች የተጠሪ አሰሪ ነው፡፡ አሰሪ ማለት አንድን ወይም ብዙ ሰዎችን ደመወዝ እየከፈለ በእርሱ መሪነት ስራውን እንዲሰሩለት ቀጥሮ የሚያሰራ ግለሰብ መሆኑን ከአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 2/1/ እና 4 ስር መመልከት ይቻላል፡፡ በመሆኑም አሰሪው ስራውን የሚመራ እንደመሆኑ መጠን አንድ ሰራተኛ የት ቦታ ተመድቦ ቢሰራ ለስራው ይጠቅማል የሚለውን የመወሰን አስተዳደራዊ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ የአሰሪው ስራውን ቅልጥፍና፣ ውጤታማነት፣የኢንዱስትሪ ሰላም ወይም ሌሎች በተለያዩ ሁኔታዎች ከግምት ውስጥ በማስገባት አንድን ሰራተኛ ከአንድ የሰራ መደብ ወደ ሌላ ወይም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ የማዛወር መብቱ ስራ መሪነቱ ወይም አሰሪነቱ የሚመነጭ ነው፡፡ በእርግጥ አሰሪው ይህን የዝውውር እርምጃ ሲወስድ የሰራተኛውን መብትና ጥቅም ሊጠብቅ ይገባል፡፡

በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ወደ ሌላ ቦታ የተዛወሩት ደመወዛቸውን ይዘው_ለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት ተገንዝበናል፡፡ ተጠሪ በመ/ቤት ውስጥ በደረሰብኝ ድብደባ ለመታረቅ ባለመፍቀዴ ብቻ ልዛወር አይገባም በማለት ነው የሚከራከሩት ከላይ እንደተመለከተው ግን አሰሪው ለኢንዱስትሪ ሰላም ሲል ወይም ለስራው ይጠቅማሉ ብሎ በሚያምነው ቦታ ላይ የተጠሪን መብት ሣያጓድል ለማዘወር አስተዳደራዊ መብት አለው፡፡ ይህም በአዋጁ የተከለከለ ጉዳይ አይደለም፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቶች የተጠሪ ዝውውር ሕገ-ወጥ ነው ሲሉ የሰጡት ውሣኔ በአሰሪና ሰራተኛ ግንኙነት ውስጥ አሰሪው ሊኖረው የሚገባውን አስተዳደራዊ መብቶች ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 27010 በ27/05/2001 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 76626 በ20/06/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪ በአመልካች የተወሰደው ዝውውር ሕገ-ወጥ ነው በማለት እንዲነሣላቸው ያቀረቡት ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 42906

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢትዮ-ጃፓን ጨርቃ ጨርቅ አ/ማ - ጠበቃ ቴዎድሮስ ኃ/ስላሴ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** እነ ትዕግስት ማሞ (81 ሰዎች) - ወኪል አበበ መገርሳ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የሥራ ውል መቋረጥን ተከትሎ የቀረበ የልዩ ልዩ ክፍያዎች ጥያቄ የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው የሥራ ውሉ ሊቋረጥ የቻለው የጨርቃጨርቅ ፋብሪካው ከመንግሥት እጅ ወጥቶ ወደግል በመዛወሩ ነው፡፡ ተጠሪዎች ከሥራ የተሰናበቱት መንግስት ከ20 ዓመት በላይ ያገለገሉና ዕድሜአቸው 45 ዓመት የሆኑ ሠራተኞች በጡረታ እንዲገለሉ በመወሰኑ ነው፡፡ ተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥ አስቀድሞ ማስጠንቀቂያ ስላልተሰጠን የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ይገባናል፤ ሠርተን ያልተከፈለን ደመወዝ ስላለና ይህም በጊዜው ስላልተከፈለን ከነመቀጫው ይከፈለን፣ ሠራተኛ በጡረታ ሲገለል የሚሰጡ ጥቅማጥቅሞች ይሰጡን፣ ላልተጠቀምንበት የዓመት ፈቃድ እረፍት ጊዜ ገንዘብ ይከፈለን በማለት ነው፡፡

አመልካች በበኩሉ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሾች በመንግስት በጡረታ እንዲገለሉ እንደተወሰነ ሁሉንም በአንድነት ሰብስበን ከማስታወቃችንም በላይ፤ እያንዳንዱን ፎርም በማስሞላትም ከደጋፊ ሰነድ እና ፎቶግራፍ ጋር አያይዘን ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ልከናል፡፡ የመጨረሻው ውሰኔ(ውጤት) እስኪደርሰን ድረስም ከሣሾች በሥራቸው ላይ እንዲቆዩ አድርገናል፡፡ በዚሁ መሠረት እየሠሩና እየተጠባበቁ ሳለ ከአንድ ዓመት በኋላ የመጨረሻው ውሳኔ ስለደረሰ ይህንኑ በፋብሪካው የማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ አሳውቀናል፡፡ የሠራተኛ ማህበሩም ይህንኑ አረጋግጦ ገልጾአል፡፡ በመሆኑም አላሳወቃችሁም የምንባልበት ምክንያት የለም፡፡ ቀሪ ደመወዝ እና በሕጉ መሠረት ሊከፈሉ የሚገባቸውን ክፍያዎች ፔይሮል አዘጋጅተን እንዲወስዱ ብንጠይቅም ከሣሾች ለመቀበል ፈቃደኛ ስላልሆኑ ሳይከፈሉ ቀርተዋል፡፡ ሌሎች ጥቅማጥቅሞች (በጡረታ በመገለል ምክንያት) ሊከፈሉ የሚችሉት በፋብሪካው የህብረት ስምምነት መሠረት ሠራተኛው 60 ዓመት ሞልቶት ጡረታ ሲወጣ ነው፡፡ ከሣሾች በጡረታ የተገለሉት በመንግስት ውሳኔ በልዩ ሁኔታ በመሆኑና ይህም የህብረት ስምምነቱ ሥራ ላይ ሲውል አሠሪውና ሠራተኛው ያላዩት ያልተደራደሩበትና ያልተስማሙበት በመሆኑ ልንገደድበት አንችልም፡፡ በማለት ተከራክሮአል፡፡

ክሱ የቀረበለት በምስራቅ ሸዋ ዞን የሎሜ ወረዳ ፍ/ቤትም የግራቀኝ ወገኖችን ክርክር ከሰማ በኋላ የተጠሪዎችን ጥያቄ በሙሉ በመቀበል ወስኖአል፡፡ ከዚህ በመቀጠል አመልካች ለምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ደረጃም ክርክሩ የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ አፅንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ጥር 15 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ የሥር ፍ/ቤቶች በሰጡት ውሳኔ ላይ ተፈጽሞአል የሚለውን የሕግ ስህተት በመግለጽ እንዲታረምለት ጠይቆአል፡፡ በበኩላችንም አቤቱታውን መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን

አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች ላይ የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን የግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም እንደተገነዘብነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል የነበረው ውል የተቋረጠው ተጠሪዎች በመንግስት ውሳኔ መሠረት በልዩ ሁኔታ በጡረታ በመገለላቸው መሆኑን፣ ይህም ውሳኔ ከአንድ ዓመት በፊት ተጠሪዎች እንዲያውቁት ተደርጎ የጡረታ ፎርም ሞልተውና ፎቶግራፋቸውን ሰጥተው ውጤቱን ሲጠባበቁ የቆዩ መሆኑን በመጨረሻም ተጠናቆ በመድረሱ አመልካች ይህንኑ በማስታወቂያ ሰሌዳ መለጠፉንና የሠራተኛ ማህበሩም ይህን ያረጋገጠ ስለመሆኑ አላከራከረም፡፡ ተጠሪዎች ጥቅማ ጥቅሞችን ለመጠየቅ በዋቢነት የጠቀሱት የህብረት ስምምነት ድንጋጌም ጥቅማጥቅሞቹ ሊሰጡ የሚችሉት ሠራተኛው 60(ስድሳ) ዓመት ሞልቶት ጡረታ ሲወጣ ነው በሚል የተደነገገ ስለመሆኑም አከራካሪ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አከራካሪ ሆነው የተገኙት አልተከፈለም የተባለውን የስምንት ቀን ደመወዝ አከፋፈል፣ ስለማስጠንቀቂያ አሰጣጥ እና ጥቅማጥቅሞቹ የሚከፈሉበትን አግባብ የሚመለከቱ ነጥቦች ናቸው፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው የሥራ ውሉ ከመቃረቡ ከአንድ ዓመት በፊት ተጠሪዎች በጡረታ እንደሚገለሉ (የስራ ውሉ በዚህ ምክንያት እንደሚቋረጥ) አውቀው ፍጻሜውን ሲጠባበቁ ቆይተዋል፡፡ በሥር ፍ/ቤቶችም እንደተገለጸው ማስጠንቀቂያ አስፈላጊ የሚሆነው ሠራተኛው የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥ አውቆ በራሱ በኩል አስፈላጊውን ዝግጅት ለማድረግ እንዲችል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የተጠሪዎችን ሁኔታ ሲታይ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ ከተቀመጠው ጊዜ በላይ አግኝተዋል፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 35 እንደተመለከተው የማስጠንቀቂያ ጊዜ ከሦስት ወር በላይ የሚረዝምበት ሁኔታ የለም፡፡ ማስጠንቀቂያው ለእያንዳንዱ ሠራተኛ በእጁ ሊሰጠው ይገባ ነበር የሚለው የሥር ፍ/ቤቶች አካሄድም እንዲሁ በደፈናው ትክክል ነው የሚባል አይደለም፡፡ ዋናው መታየት ያለበት ሠራተኛው የሥራ ውሉ እንደሚቋረጥበት በትክክል እንዲያውቅ መደረግ አለመደረጉን ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪዎች የሥራ ውላቸው እንደሚቋረጥ በሚገባ እንዲያውቁ ተደርጎአል ብቻ ሳይሆን ፍጻሜውንም ሲጠባበቁ ቆይተዋል፡፡ ውጤቱ እንደመጣም ይኸው ተገልጾላቸው እንዲሰናበቱ ተደርጎአል፡፡ በመሆኑም የማስጠንቀቂያ ስርዓት አልተፈጸመም በሚል በስር ፍ/ቤቶች የተደረሰው መደምደሚያ ሕጉን የተከተለ አይደለም፡፡

ቀጥለን ያየነው አከራካሪ ነጥብ ከቀሪ ደመወዝ(የሳምንት ቀን) እና የተወሰኑ ሠራተኞች የዓመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ አከፋፈል የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ገንዘብ በእርግጥም ሊከፈል እንደሚገባ አመልካችም ያምናል፡፡ ክፍያዎቹን አዘጋጅቶ እንዲወስዱ ጠይቆ እንደነበር፤ ነገር ግን ተጠሪዎች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ሌሎች ጥቅሞች አብረው ካልተከፈሉን ይህን ብቻ አንወስድም በማለታቸው ሳይከፈል መቅረቱን በመግለጽም ተከራክሯል፡፡ በበኩላችንም ከአጠቃላይ የክርክሩ ሂደት መገንዘብ እንደቻልነው ገንዘቡ ሳይከፈል የቀረው ተጠሪዎች ለመውሰድ ባለመፈለጋቸው ነው፡፡ የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ እና ሌሎች ጥቅሞችም አብረው እንዲከፈሉዋቸው ተጠሪዎች ፍላጎት ቢሆንም አመልካች እነዚህን ክፍያዎች የመክፈል ግዴታ የሉብኝም የሚል ክርክር ስላነሳ ተጠሪዎች ስለፈለጉ ብቻ መክፈል ነበረበት ሊባል አይችልም፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች ግን የተጠሪዎችን ጥያቄ በመቀጠል በአዋጁ አንቀጽ 38 መሠረት ክፍያው ለዘገየበት በሚል ለእያንዳንዱ ተጠሪ የ3(ሦስት) ወር ደመወዝ በተጨማሪ እንዲከፈል ወስነዋል፡፡ በእኛ እምነት ይህ አካሄድ የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ተጠሪዎች ሌሎቹን ክፍያዎችም የምናገኝበት የሕግ ምክንያት አለ ካሉ አሁን እንደሚያደርጉት መከራከር ሲገባቸው ሌላውን አንወስድም ማለታቸውም አግባብ ነው አንልም፡፡ በመሆኑም አመልካች ለገንዘቡ በጊዜው አለመከፈል ተጠያቂ የሚሆንበት ምክንያት የለም፡፡

በመጨረሻ የተመለከትነው በጡረታ ስለተገለልን በህብረት ስምምነቱ መሠረት የሚሰጡ ጥቅሞች እና ክፍያዎች ሊሰጡን ይገባል በማለት ተጠሪዎች ያነሱት ክርክር ነው፡፡ በዚህ ረገድ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጠው ህብረት ስምምነቱ የሚናገረው 60(ስድሳ) ዓመት ሞልቶት በጡረታ ስለሚገለል ሠራተኛ እንደሆነ ነው፡፡ 60 ዓመት ከመሙላቱ በፊት በመንግስት ውሳኔ መሠረት (በልዩ ሁኔታ) በጡረታ ስለሚገለል ሠራተኛ በሚመለከት የሚለው ነገር የለም፡፡ ይሁንና የተጠሪዎች ክርክር በጡረታ ከመገለል ጋር ተያይዞ የተነሳ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች ይህንኑ ብቻ በመመልከት የተጠሪዎችን ጥያቄ ተቀብለዋል፡፡ አመልካች ግን በዚህ አይስማሙም፡፡ ያነሳው ክርክርም ቀደም ሲል ተገልጾአል፡፡ በመሆኑም እዚህ ላይ ሊመለስ የሚገባው ጥያቄ ተጠሪዎች ይጠቅመናል በማለት የጠቀሱት የህብረት ስምምነት ለተያዘው ክርክር አወሳሰን አግባብነት አለው ወይስ የለውም? የሚለው እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡

የህብረት ስምምነት በአሠሪና ሠራተኛ(ኞች) መካከል ድርድር ከተካሄደ በኂላ የተደረሰውን የሁለቱ ወገኖች ስምምነት የሚይዝ ሰነድ ነው፡፡ ይህ ሰነድ የሁለቱም ስምምነት የያዘ እና ያፀደቁትም በመሆኑ የሚገዙበትና የሚተዳደሩበት ውላቸው ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ በአመልካች ክርክር እንደተመለከተው የህብረት ስምምነቱ ሠራተኛው 60 ዓመት ሳይሞላው በመንግስት ውሳኔ መሠረት (በልዩ ሁኔታ) በጡረታ ሲገለል የሚያገኘውን ጥቅም በሚመለከት ስምምነት የተደረገበት አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ተጠሪዎች አመልካችን የሚያስገድዱበት የህብረት ስምምነት ወይም ውል የለም ማለት ነው፡፡ በክርክሩ እንደተገለጸው በልዩ ሁኔታ (የ60 ዓመት መሙላት ሳይጠበቅ) በጡረታ የተገለሉት ሠራተኞች ወደ 145 የሚጠጉ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ በህብረት ስምምነቱ ያልታየ እና አመልካችም ሆነ ሠራተኞቹ ይሆናል ብለው ያልጠበቁት ነው፡፡ በአመልካች ላይ ሚያስከትለው ወጪም ከፍተኛ ነው፡፡ በህብረት ስምምነቱ አስቀድሞ ስምምነት ተደርጎበት ቢሆን ኖሮ አመልካችም ከዚህ አንጻር ተዘጋጅቶ ይጠብቅ ነበር፡፡ ይህ እንግዲህ በአፈጻጸም ረገድ የሚታይ ችግር ሲሆን ዋናው ግን ሁለቱን ወገኖች የሚገዛ በህብረት ስምምነቱ የተቀመጠ ድንጋጌ ስለሌለ አመልካች የተጠየቀውን ክፍያ እና ጥቅማጥቅሞች እንዲሰጥ የሚገደድበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሲጠቃለል አመልካች ሊከፍል የሚገባው የሥራ ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለተሠራ ሥራ ያልተከፈለ ቀሪ ደመወዝ ካለ እና የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ላላቸው ሠራተኞች (ተጠሪዎች) ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ ብቻ ነው፡፡ ስለዚህም የሚከተለውን ውሳኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በምስራቅ ሸዋ ዞን የሉሜ ወረዳ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 11855 ግንቦት 15 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እና የምስራቅ ሸዋዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 16691 ታሕሣሥ 14 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አመልካች የማስጠንቀቂያ ጊዜ ክፍያ ለዘገየበት ጊዜ እና በጡረታ መገለልን መሠረት በማድረግ የተጠያቂ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም ሊከፍል አይገባም ብለናል፡፡
3. ተጠሪዎች ሊከፈላቸው የሚገባው ውሉ ከመቋረጡ በፊት ለሠሩት ሥራ ያልተከፈለ ቀሪ ደመወዝ እና ያልተጠቀሙበት የዓመት ዕረፍት ፈቃድ ክፍያ ብቻ ነው፡፡
4. ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የሦስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 42075

ሐምሌ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አፍሪካዊት የህንፃ ስራ ተቋራጭ ኃ/የተ/የግል ማህበር - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ እንድሪስ ዓሊ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች በአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት እና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስላለበት በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

ክርክሩ የስራና ሰራተኛ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች የሚሰራው የኮንስትራክሽን ስራ በከፊል የተጠናቀቀ መሆኑን በመግለጽ ተጠሪዎች ከስራ አሰናብቷል፡፡ ተጠሪዎች የስራ ውላችን አላግባብ ተቋርጧል በሚል ክስ አቅርበዋል፡፡ የኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት የተጠሪዎች ውል አላግባብ ተቋርጧል በማለት ተጠሪዎች የጠየቁትን የተለያዩ ክፍያዎች አመልካች እንዲከፍል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በወረዳው ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረበ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የወረዳውን ፍርድ ቤት ውሣኔ አጽንቷል፡፡

አመልካች ታህሣስ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የኮንቦልቻ ወረዳና የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ተጠሪዎች የተሰናበቱት የግንባታ ስራው እየቀነሰ በመሄዱ ነው፡፡ ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበትኳቸው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 እና 30 መሰረት በመጨረሻ ጊዜ የሰሩበትን ደመወዝ የእረፍት ሰአት ክፍያና ያልተጠቀሙበት የዓመት እረፍት ወደ ገንዘብ በመለወጥ በመክፈል ነው፡፡ ስለዚህ ከአዋጁ ድንጋጌ መንፈስና ዓላማውም በአንቀጽ 38 እና አንቀጽ 40 እና ሌሎች ድንጋጌዎች መሰረት ልዩ ልዩ ክፍያ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ አመልካች የሰሩበትን ደመወዝ የትርፍ ሰአት ክፍያና የአመት እረፍት በገንዘብ በመለወጥ የከፈላቸው መሆኑን ማስረጃ አቅርበን እያለ እና ተጠሪዎችም ይህንን አምነው በክሳቸው ገለፀው እያለ ለእያንዳንዳቸው የአንድ ወር ደመወዝ እንድንከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር እንዲታረምልን በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው አመልካች ያሰናበተን ያለምንም ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ስንሰራ የነበረበት ወር ሣይጠናቀቅ የሰራንባቸውን ቀኖች እና የአመት እረፍት ፈቃድ ክፍያ ከፍሎ አሰናብቶናል፡፡ ስራውን በተመለከተ በስምንት ብሎክ ሶስቱ ተጠናቅቀው አምስቱ ገና ከግንባታ ላይ እንደሆኑ አስረድተናል ስለዚህ የስር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም፡፡ የአመልካች አቤቱታ ውድቅ ይደረግልን በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥተዋል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለጸው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች ያከናውን የነበረው የግንባታ ስራ መጠን እየቀነሰ እና እያለቀ መሄዱን ተጠሪዎች አልካዱም፡፡ አመልካች በኮንቦልቻ ለሚገነባው ወሎ ዮኒቨርሲቲ ስምንት ብሎክ መገንባት ጀምሮ ሶስቱ ብሎክ ስራቸው ሙሉ በሙሉ

የተጠናቀቀ መሆኑንና አምስቱ ብሎኮች እየተሰሩ መሆኑን ተጠሪዎች ገልጸዋል፡፡ ይኸም አመልካች ተጠሪዎችን ሲቀጥር የነበረው ስራ የቀነሰ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ተጠሪዎች ተቀጥረው ይሰሩ የነበሩት በአናጢነት በድንጋይ ጠራቢነት እና በሰአት ተቆጣጣሪነት የነበረ መሆኑን አመልካችና ተጠሪዎች አልተካካዱም፡፡ ስለዚህ ተጠሪዎች ይሰሩበት የነበረው ብሎክ ስራ ሲጠናቀቅ አመልካች ተጠሪዎችን ማሰናበቱ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 30 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የተፈጸመ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የኮንስትራክሽን ስራ የሚሰራ ድርጅት በመሆኑ ማስጠንቀቂያ የመስጠትና ሌሎች የቅነሣ ስነ ሥርአቶችን ሣይገልጽ የስራው መጠን ሲቀንስ ወይም ስራው ሲያልቅ ሰራተኞችን ማሰናበት የሚችል ስለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 አንቀጽ 30 የኮንስትራክሽን ዘርፍ የስራ ባህሪ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ሕግአውጭው በልዩ ሁኔታ ደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ተጠሪዎች ማስጠንቀቂያ ሣይሰጠን ነው ያሰናበተን በማለት ያቀረቡት ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ተጠሪዎች ከስራ ሲሰናበቱ የሰሩበትን ደመወዝ እና የአመት እረፍት በገንዘብ ተሰልቶ የተከፈላቸው መሆኑን ለሰበር በሰጡት መልስ የገለፁ ሲሆን ቅሬታቸው በአግባቡ አልተሰላም የሚል ነው፡፡ መጠኑን በተመለከተ የተነሣው ክርክር የፍሬ ጉዳዩ ክርክር በመሆኑ በዚህ ችሎት የሚስተናገድ አይለም፡፡ ተጠሪዎች ከስራ ሲሰናበቱ የሰሩባቸው ቀናቶች ደመወዝና የአመት እረፍት በገንዘብ ተለውጦ የተከፈላቸው መሆኑን አምነው በሚከራከሩበት ሁኔታ አመልካች ለተጠሪዎች የአንድ ወር ደመወዛቸውን እንዲከፍል መወሰኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ የወረዳውና የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካች በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 24 ንኡስ አንቀጽ 1 እና በአንቀጽ 30 መሰረት ያከናወነውን የስራ ስንብት ህገ ወጥ የስራ ስንብት ነው በማለት ለተጠሪዎች ልዩ ልዩ ክፍያዎችን እንዲከፍል መወሰናቸው መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. በአማራ ክልል የደቡብ ወሎ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና የኮንቦልቻ ወረዳ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪዎችን ከስራ ያሰናበተው በአግባቡ ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ለተጠሪዎች ምንም አይነት ክፍያ የመፈጸም ግዴታ የለበትም ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39808

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ናዝሬት ሳሙና ፋብሪካ

**ተጠሪ**፡- ዘውዴ ኃ/ማሪያም /አቶ/

መዝገቡን መርምረን የሚተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ በአሰሪና ሰራተኛ መካከል የተደረገውን የስራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት በአዳማ ወረዳ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረው ተጠሪ ነው፡፡ በአመልካች ላይ ክስ የመሰረተው ስራዬን በገዛ ፈቅዴ ለቅቄ ስራ ያቋረጥኩ ስለሆነ በሕጉ መሰረት የስንብት ክፍያና የአገልግሎት ክፍያ ይከፈለኝ ዘንድ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ከሣሽ በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለና በፈቃዱ ስራውን የለቀቀ በመሆኑ እድሜው ለጡረታ ሲደርስ የጡረታ አገልግሎት አበል ለእድሜልክ ማግኘት ይችላል፡፡ ስለዚህ የአገልግሎት ክፍያ የማግኘት መብት የለውም በማለት ተከራክሮአል፡፡ ክሱን ያስሰተናገደው ፍ/ቤትም የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከሰማ በኂላ፣የአመልካች ክርክር በመቀበል ተጠሪ የጠየቀውን ክፍያ ማግኘት አይችልም በማለት ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በወረዳው ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሳኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ነሐሴ 5 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሰረት ባለመቅረቡ ክርክሩ የተሰማው እሱ በሌለበት ነው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው ተጠሪ የጡረታ የተጠበቀ ቢሆንም፣የስንብት ክፍያም ይከፈለው በሚል የተሰጠው ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣አቤቱታው ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው በአመልካች እና በተጠሪ መካከል የነበረው የስራ ውል የተቋረጠው ተጠሪ በራሱ ፈቃድ ስራውን በመልቀቁ ምክንያት ነው፡፡ ተጠሪ ወደ ክስ ያመራውም በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀጽ 39 መሰረት የስራ ስንብት ክፍያ ለመክፈል አመልካች ፈቃደኛ ሆኖ ባለመገኘቱ ነው፡፡ አመልካች የስራ ስንብት ክፍያው መክፈል የለበኝም የሚለው ተጠሪ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ያገለገለ በመሆኑ በጡረታው ሕግ መሰረት የጡረታ አገልግሎት አበል የማግኘት መብት አለው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ በማንሳት ነው፡፡ በእርግጥም የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን ወይም የጡረታ መብት የሌለውና በጡረታ ሕግ የተመለከተው መደበኛ የጡረታ እድሜ ደርሶ ከስራ የተገለለ ሰራተኛ የስራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት እንዳለው በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ(ማሻሻያ) አዋጅ ቁ. 494/98 አንቀጽ 2(2)(ሰ) ተመልክቶአል፡፡ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥበት የስራ ስንበት ክፍያ የሚፈጸምለት ሊቋቋመው የማይችል ድንገተኛ የገንዘብ ችግር እንዳይገጥመው ነው፡፡ ይህ ከሕጉ በስተጀርባ ያለው አስተሳስብ ወይም ምክንያት ሲሆን በሕጉ

እንደተመለከተው ሰራተኛው የፕሮቪደንት ፈንድ ሽፋን የጡረታ መብት ካለው ግን የስራ ውሉ ቢቋረጥም፤ ገንዘብ ማግኘቱን ስለሚቀጥል (ስለቀጠለ) የስራ ስንብት ክፍያው አይከፈለውም፡፡

ወደያዝነው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪ የስራ ውሉን ያቋረጠው በፋብሪካው ውስጥ ከ20/ሃያ/ ዓመት በላይ ካገለገለ በኋላ ነው ቢባልም፤በጡረታ ሕጉ መሰረት የጡረታ እድሜ ላይ ስለመድረሱና የጡረታ አበል የሚያገኝ ለመሆኑ አመልካች አላስረዳም፡፡ ተጠሪ የስራ ውሉን እንዳቋረጠ የጡረታ አበል ማግኘቱን ይቀጥላል የሚል ክርክርም ሆነ ማስረጃ ከሌለ ደግሞ ለስራ ስንብት መክፈል መሰረት የሆነውን በሕጉ በስተጀርባ ያለውን ምክንያት መሰረት በማድረግ የስራ ስንብቱን ክፍያ ማስከፈል የግድ ይሆናል፡፡ ሕጉ በዚህ መልክ ካልተተረጐመም ሰራተኛው ለድንገተኛ የገንዘብ ችግር ማጋለጥ ይሆናል፡፡ በመሆኑም ለወደፊት የጡረታ አበል ያገኛል በሚል መነሻነት አመልካች ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ከላይ እንዳመለከትነው የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ባለመቀበል የስራ ስንብት ክፍያው እንዲከፈል ወስኖአል፡፡ ይህ ውሳኔ በበኩላችንም የምንደግፈው ነው፡፡ ውሳኔውን የደገፍነው ሕጉ ከላይ በተገለጸም አይነት መተርጐም ያለበት መሆኑን ስለምናምን ነው፡፡ ስለዚህም የከፍተኛው ፍ/ቤት  የሕጉን ትርጉም በሚፈለገው መጠን ባያስቀምጥም፣የደረሰበት መደምደሚያ ግን ትክክል ስለሆነ ውሳኔው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው ለማለት አልቻልንም፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 06414 ሐምሌ 14 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቶአል፡፡
2. ተጠሪ የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በሰጠው ውሳኔ መሰረት ክፍያው ይፈጸምለት ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

## ት እ ዛ ዝ

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ የነበረው የእግድ ትእዛዝ ተነስቷል፡፡ ለሚመለከታቸው ይፃፍ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 42901

ሐምሌ 21 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

**አመልካች፡-** የትምህርት መሣሪያዎች ማምረቻና ማከፋፈያ ድርጅት - ነገረ ፈጅ አቶ ጌታሁን ተስፋዬ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ንግሥት ለጥይበሉ - ጠበቃ አቶ አበራ ታደሰ ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

የክርክሩ ምክንያት የሥራ ክርክር ጉዳይ ሆኖ ተጠሪ ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረበችው ክስ ያለአግባብ የሥራ ውል የተቋረጠ በመሆኑ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ሥራ እንድመለስ አሊያም ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሎ እንድሰናበት ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

አመልካች ከሳሽ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደለችም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና የፍሬ ነገር ክርክር በማቅረብ መልስ በመስጠት ተከራክሯል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሥራ ውል የተቋረጠው ከሕግ ወጪ ነው ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎአት ወደ ሥራ ትመለስ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ጥር 20 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበውን ቅሬታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ሰምተናል፡፡ ጉዳዩ በሰበር ሰሚ ችሎት እንዲታይ የቀረበው ተጠሪ የሥራ መሪ ናቸው ወይንስ አይደሉም? የሚለውን ነጥብ ለመመርመር በመሆኑ ይህንኑ ከግራ ቀኙ ክርክርና ከሕጉ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር መረዳት የተቻለው ተጠሪ የድርጅቱ የሀገር ውስጥ ዕቃ ግዥ ዋና ክፍል ኃላፊ በመሆን እንዲሁም በተጨማሪነት የውጪ ሀገር ዕቃ ግዥ ዋና ክፍልና የሽያጭ ዋና ክፍልን የሚያካትተውን የንግድ መምሪያ ኃላፊነትን ደርበው ይሠሩ የነበረ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በእነዚህ መደቦች በኃላፊነት ስለመሥራታቸው አልተካደም፡፡ የሥራ መደቡ ዋና ተግባራት ምንድናቸው የሚለው ከተጠሪ የሥራ መዘርዝር /job description/ ሲታይ በአጠቃላይ በድርጅቱ መመሪያ መሠረት ማስተባበር፣ መምራት፣ ማደራጀት እና መቆጣጣር እንዲሁም ዕቅድና በጀት ዝግጅት ላይ መሳተፍ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን በድርጅቱ ኅብረት ስምምነት አንቀጽ 3 ንዑስ ቁጥር 3.3 እንደተመለከተው ስምምነቱ የዋና ክፍሎችንና የማምረቻ ኃላፊዎችን እንደማይጨምር በግልጽ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪም ከሌሎች ሠራተኞች በተለየ ሁኔታ ከፍተኛ የድርጅቱ ኃላፊነት የተሠጠች መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር ተጠሪ ሥራን የማቀድ፣ የመምራት፣ የመቆጣጠር፣ የማደራጀትና የማስተባበር ተግባራትን የሚያከናውኑ መሆኑን ከክርክሩም ሆነ ከቀረቡ ሰነዶች መረዳት ተችሏል፡፡ ስለዚህ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 3 በአዋጅ ቁጥር 494/98 አንቀጽ 2 እንደተሻሻለው ተጠሪ ከሥራ ተግባራቸው አንፃር የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ በአዋጁ ለሥራ መሪ የተሠጠው ትርጉም "የሥራ መሪ የሚባለው በሕግ ወይም እንደ ድርጅቱ የሥራ ፀባይ በአሠሪው በተሠጠው ውክልና ሥልጣን

መሠረት የሥራ አመራር ፖሊሲዎችን የማውጣትና የማስፈፀም ከዚህ በተጨማሪ ወይም እነዚህኑ ሳይጨምር ሠራተኛን መቅጠር ማዛወር የማገድ የማሰናበት የመመደብ ወይም የሥነ ሥርዓት እርምጃ የመውሰድ ተግባሮችን የሚያከናውንና የሚወስን ግለሰብ ነው ይላል፡፡" ከዚህ አንፃር የተጠሪ የሥራ ተግባር በፍሬ ነገር ረገድ የተረጋገጠው የድርጅቱን ዋና ክፍል ሥራ በኃላፊነት መምራት፣ ማደራጀት መቆጣጠርና ማስተባበር ከመሆኑ አንፃር በሕጉ ትርጉም ከተሠጠው የሥራ ዘርፍ የሚመደቡ በመሆናቸው የሥራ መሪ ናቸው እንጅ፤ ሠራተኛ አይደሉም፡፡ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የቦርድም፣ የማናጅመንት አባላት ክፍያ አፈፃፀም መመሪያ እኔን አይጨምርም በማለት ከተጠሪ የቀረበውን ክርክር በተመለከተ መመሪያው ለቦርድና ማናጅመንት አባላት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ አስመልክቶ የወጣ የአፈፃፀም መመሪያ እንጅ ለተያዘው ጉዳይ ተፈፃሚ ስለማይሆን ክርክሩ አግባብነት የሌለው ነው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተጠቀሱ ምክንያቶች እና በሰበር መ/ቁጥር 40055 በተመሳሳይ ጉዳይ ትርጉም የተሠጠበት በመሆኑ ተጠሪ የሥራ መሪ እንጅ ሠራተኛ ባለመሆናቸው ጉዳያቸው በሥራ ክርክር ችሎት ክስ ለማቅረብም ሆነ ክርክር ለማካሄድና ዳኝነት ለማግኘት የሚችሉበት የሕግ አግባብ ስለሌለ የመጀመሪያ ደረጃ እና ከፍተኛ ፍ/ቤቶች የሠጡት ውሳኔ በሕግ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ውሳኔ ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 13197 በ18/12/2000 ዓ.ም እንዲሁም ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 73934 በ18/5/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ የሥራ መሪ በመሆናቸው ጉዳያቸው በሌላ ሕግ ከሚታይ በቀር በሥራ ክርክር ችሎት ሊታይ አይችልም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 39471

ሐምሌ 29 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች** ፡- ኤርሚያስ ሙሉጌታ - አልቀረቡም

**ተጠሪ** ፡- በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማ - ይልማ ገመቹ ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የሰበር አቤቱታ አመልካች በተጠሪ ተቀጥሮ በሾፌርነት ሲሠራ በነበረበት ጊዜ ከጅቡቲ አስጭኖ ከመጣው የአርማታብረት ውስጥ 20 ጥቅል ወይም 305 ኩንታል አጉድሎ ተገኝቶአል በሚል ተጠሪ የመሠረተውን ክስ መነሻ በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ የብረቱን ዋጋ በማስላት እንዲከፈለው አመልካችንና ዋሱ ነች የተባለችውን ሰው አጣምሮ የከሰሰ ሲሆን፣ ተከሣሾችም የመከላከያ ክርክራቸውን አቅርበዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሁለቱን ወገኖች ክርክር ከመረመረ በኋላ፣ አመልካች ብር 11,250(አስራ አንድ ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ከወለድ እንዲሁም ከዳኝነትና ከብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) ኪሣራ ጋር ይከፈል፤ እሱ ባይከፍል ዋሱ ትክፈል በማለት ወስኖአል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ እንደአግባቡ ይግባኝ እና አቤቱታ የቀረበላቸው የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት መደበኛ ችሎት እና የሰበር ችሎትም ውሣኔውን አፅንተዋል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ በሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ ላይ ተፈፅሞአል የሚለውን የሕግ ስህተት በመግለጽ አቤቱታውን አቅርቦአል፡፡ በበኩላችንም ይህን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ክርክሩ የተሰማው አመልካች ደረሰ ለተባለው ጉድለት ተጠያቂ ነው መባሉ አግባብ ነው ወይ? በሚለው ነጥብ ላይ በመመስረት ነው፡፡

ከሥር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ በዚህ ሰበር ችሎት ከተደረገው ክርክር በተለይ መገንዘብ እንደቻልነው አመልካች በሥር ፍ/ቤቶች የተሰጠውን ውሣኔ የሚቃወምበት ዋናው ምክንያት ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር በኔ በኩል ጉድለት እንዳልተገኘ ተረጋግጦ ውሣኔ ተሰጥቶአል፡፡ ክርክሩ የተካሄደው ተጠሪ ጉድለቱን መሠረት በማድረግ የሥራ ውሌ በማቋረጡ ወደ ሥራዬ እንድመለስ በሥራ ክርክር ችሎት ክስ በመመሥረቴ ሲሆን፣ ፍ/ቤቱም የስራ ውሉን ለማቋረጥ የሚያስችል ጥፋት እንዳልተፈፀመ አረጋግጦ ውሣኔ ሰጥቶአል፡፡ በመሆኑም በተመሣሣይ ጉዳይ በድጋሚ ክርክር ሊደረግ አይችልም፡፡ በማለት ነው፡፡ ተጠሪ ደግሞ ቀደም ሲል ቀርቦ ክርክር የተደረገበት ጉዳይ የሥራ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ በዚህ ክርክር ተይዞ የነበረው ጭብጥ አመልካች የሥራ ውል ሊያቋርጥ የሚችል ጥፋት ፈፅሞአል ወይስ አልፈፀመም የሚል ነው፡፡ በአሁኑ ጉዳይ የተያዘው ጭብጥ ግን አመልካች በክሱ የተመለከተውን ገንዘብ ለመክፈል ይገደዳል ወይስ አይገደድም? የሚለው ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩቹ ተመሣሣይ አይደሉም በማለት ተከራክሮአል፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ሰበር ችሎት ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባው ጭብጥ ተጠሪ በአመልካች ላይ የመሠርተው የገንዘብ ይከፈለኝ ክስ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ከተቀመጠው ድንጋጌ አንፃር ታይቶ ውድቅ መሆን የሚገባው ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

በፍሬ ነገር ረገድ የቀረበው ክርክር እንደሚያመለክተው ለሁለቱም ክርክሮች መነሻ የሆነው አመልካች ያሽከረክረው በነበረው መኪና ላይ ተጭኖ የነበረው የአርማታ ብረት ጎድሎ ተገኝቶአል የሚለው ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን የመጀመሪያው የሥራ ክርክር በመሆኑም የታየው፤ በስራ ክርክር ችሎት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በፍታብሔር ችሎት ነው የታየው ይህ በመሆኑም ነው በአመልካች የተነሣው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ላይ የተመሠረተው መቃወሚያ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚል አከራካሪ ጭብጥ ሊያዝ የተቻለው፡፡

ይህ የሰበር ችሎት በሰበር መ.ቁ. 36710 ተመሣሣይ ክርክር ቀርቦለት በሕጉ አተገባበር ረገድ ትርጉም ሰጥቶአል፡፡ በዚህም በአሠሪና ሠራተኛ መካከል በሚካሄደው የሥራ ክርክር የሚያዘው ጭብጥ አሠሪው የገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ /ክስ/ በሠራተኛው ላይ ባቀረበ ጊዜ ከሚያዘው ጭብጥ ጋር አንድ አይነት አይደለም እሚል መደምደሚያ ላይ ደርሶአል፡፡ በመጨረሻም እንደአሁኑ አመልካች በአሠሪው በጉድለት ይፈለጋል የተባለውን ገንዘብ እንዲከፍል ክስ የቀረበበት ሠራተኛ ቀደም ሲል ተካሂዶ የነበረውን የሥራ ክርክር መሠረት በማድረግ ያቀረበው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 5 ላይ የተመሠረተው መቃወሚያ ውድቅ አድርጎአል፡፡

የሰበር ችሎቱ ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም በተመሣሣይ ሁኔታ በተሰየመው ችሎት እስካልተለወጠ ድረስ በየትኛውም ደረጃ ላይ በሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍ/ቤት ላይ አስገዳጅነት እንደሚኖረው የፌዴራል ፍ/ቤቶችን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁ. 454/97 አንቀጽ 2/1/ ተደንግጎአል፡፡ በሰበር መ.ቁ. 36710 የተሰጠው የሕግ ትርጉም አልተለወጠም፡፡ በመሆኑም በዚህ መዝገብ በቀረበው ክርክርም የተለየ የሕግ ትርጉም የሚሰጥበት አግባብ የለም፡፡ አመልካች ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት ምክንያት የለም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የአዳማ ልዩ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 04076 ሚያዝያ 5 ቀን 99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ፣ የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 53326 ህዳር 17 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ እና የኦሮሚያ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. 61371 ሚያዝያ 20 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቶዋል፡፡
2. አመልካች በዚህ ሰበር ችሎት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሚያገኝበት የሕግ ምክንያት የለም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ጽ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 18419

ይንቦት 4 ቀን 1998 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረ□ሐ□ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ደ□ታች□□ ምህረቱ

መስፍን እቁበዮናስ

□/ት ሃ□ት መለሠ

**አመልካች፡-** ሐመረ□ርቅ ቅ/ማርያም ቤ/ክርስቲያን ሰበካ ጉባዔ ጽ/ቤት

**መልስ ሰጭዎች፡-** 1. □□ቆን ምህረት ብርሃን

2. አጋፋሪ አብርሃም ታደሰ

3. ዲያቆን አስራት □/ትንሣ□

4. ዲያቆን ገዛኸኝ ከበደ

5. □□ቆን ስመኘ□□ ደርማ□

6. ዲያቆን ዓለማየሁ ሞገስ

<u>□ ር □</u>

ጉዳዩ ለዚህ ችሎት የቀረበ□□ □ፀ□ራል □መደመሪ□ ደረየ □/በ□ት መ/ሰጭዎች በአመልካች ቤተክርስቲያን □□ስጨ መንፈሣዊ አገልግሎት ተቀጥረን ስናገለግል ከቆየን በኋላ አመልካች ሕገ-□ጨ በሆነ መንገድ ከስራ ያሰናበተን በመሆኑ□□ድ ስራ እንድንመለስ ይ□ሰንልን በሚል ባቀረቡት ክስ የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎችን ተፈፃሚ በማድረግ ስንብቱ ሕገ-□ጨ ነ□□ በማለት መ/ሰጭዎች ወደስራ እንዲመለሰ□ □ሰ□ውና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያፀናው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በሚል አመልካች የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነ□□፡፡ ጴ□ዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በተሰ□ው ትእዛዝ መሠረት መ/ሰጭዎች የአመልካች አቤቱታ ደርሷቸ□□ መልስ □ሰ□□ሲሆን አመልካችም የመልስ መልስ እንዲያቀርብ ተደርጓል፡፡

በጉዳዩ በዚህ ችሎት መታየት ያለበት የሕግ ነጥብ በአዋጅ ቁ.42/85 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት የሚኒስትሮች ምክር በ□ት ለ□□□ው የሚችለው ደንብ የኃይማኖት ተቋማት መንፈሣዊ አገልግሎት ከሚሰ□□ ሰራተኞቻቸ□□ ጋር □ላቸ□□ን □ስራ ይንኙ□ቶችም ለ□ ምር □ችላል? □ይስ አይችልም? የሚለው በመሆኑ ችሎቱም ነጥቡን መርምሯል፡፡ አዋጅ ቁ.42/85 በአዋጅ ቁጥር 377/96 የተሻረ ቢሆንም ነጥቡን በሚመለከት ሁለቱ አዋጆች አንድ ዓይነት ድንጋጌዎች የያዙ በመሆኑ ችሎቱ የአዋጅ ቁ. 42/85 ድንጋጌዎች መሠረት አድርጎ በተጠቀሰ□□ ነጨብ ላ□ □ማ□□ው የሕግ ትርጉም ለአዋጅ ቁ. 377/96 □ንጋጌዎችም አግባብነት ያለ□□ነ□□፡፡

ይህ ችሎት በዚህ ጉዳይ የሕግ ትርጉም ለሚሰጥበት ከላይ ለተመለከተ□□ ነጨብ ቀጨተኛ አግባብነት ያለው የአዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 3 ነው፡፡ ይኸው አንቀጽ አዋጁ በንዑስ አንቀጽ 2 ከተመለከቱት በቅጥር ላይ ከተመሠረቱት የስራ ይንኙ□ቶች □□ በሰራተኛና በአሰሪ መካከል በሚደረግ በቅጥር ላይ በተመሠረተ የስራ ግንኙነት ላይ ተፈፃሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ የኃይማኖት ተቋማት መንፈሣዊ ተግባር ከሚያከና□□ሰ□ ሰራተኞች ጋር ያላቸ□□ □ስራ ይንኙነት አዋጁ ተፈፃሚ እንደማይሆንባቸ□- በአንቀጽ 3(2) ከተዘረዘሩት የስራ ግንኙ□ቶች □-ስጥ ያልተካተተ ሲሆን ይልቁንም የአዋጁ አንቀጽ 3(3)(ለ) □ኃ□ማኖት □ይም የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በሚመሠርቱት የስራ ግንኙነቶች ላይ አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በደንብ ለ□ስን ይችላል በሚል ይደነግጋል፡፡ የስር ፍ/ቤት ጉዳዩን በአዋጅ ቁ. 42/85 መሠረት ለማ□ት □□ሣ□□ሰ□ው በአንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት የተጠቀሰ□ት □ር□ቶች በማ□መሠረቱት □ስራ ይንኙነት አዋጁ ተፈፃሚ እንዳይሆን የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ እስካላ□□ □ረስ □ር□ቶቹ በማ□መሠረቱት □ስራ ይንኙነቶች ላይም አዋጁ ተፈፃሚ

ይሆናል በማለት ነው፡፡ ይህም በስር ፍ/ቤት ለአንቀጽ 3(3)(ለ) የተሰጠው ትርጓሜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኃይማኖት ድርጅቶች መንፈሣዊ አገልግሎት ከሚሰጡ ሰራተኞቻቸው ጋር ባላቸው የስራ ይንኙነቶች ላይ የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ እንዳይሆን በደንብ ሊወስን ይችላል የሚል ድምዳሜን መሠረት ያደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ አተረጓጎም የሕጉን መንፈስ ተከትሎ የተሰጠ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የማይሸፍናቸውን የስራ ይንኙነት ዴንጋጌዎች መመልከት የግድ ይላል፡፡

የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ የስራ ውል ስለማይመሰረትበት ሁኔታ የስራ ውሉ ስለሚቆይበት ጊዜ፤ የሰራተኛውና የአሰሪው መብትና ይዴታ የስራ ይንኙነት ስለማይረጨቆቸው ውስን ሁኔታዎች፣ የስራ ውሉ ሕጋዊ ወይም ሕገ-ወጪ በሆነ መንገድ በሚቋረጥበት ጊዜ ስለሚከተሉ ውጤቶች የሚያነግጉ ድንጋጌዎች የያዘ ሆኖ ይታያል፡፡ በአጠቃላይ ሕጉ ከአሰሪና ሰራተኛ ይንኙነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮችን በአንዳንድ ሁኔታዎች ከሚያጋጥሙ ልዩ ጉዳዮች በቀር አካቶ የያዘ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ከላይ የተመለከቱት ከአሠሪና ሠራተኛ ይነኘነት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች መንፈሣዊ አገልግሎትን በሚመለከት የኃይማኖት ተቋማት በማመሠርተቸው የሥራ ይንኙነቶች ላይስጨም የማይሰጡ በሆንም በሌሎች የስራ ይንኙነቶች ከሚያጋጥሙበት አኳኋን ለየት ባለ መንገድ የሚያጋጥሙ ሁኔታዎችም አሉ፡፡ ምክንያቱም በአንድ የኃይማኖት ተቋም ላይስጨ ለመሠረት የማይችል የተለየ የሥራ ይንኙት በመኖሩ ነው፡፡ በአንድ በኩል የሚሠጡት አገልግሎት ድርጅቱ ከሚከተለው እምነት ጋር ቀጥተኛ ይንኙነት ያለውና ከእምነቱ ጋር ተነጥሎ ሊታይ የማይችል ሠራተኛን፤ እንደ ቄስ፣ ካህን፣ ዲያቆን ወዘተ ያሉ ሰሆን በሌላ በኩል ደግሞ የሚሠጡት አገልግሎት ከእምነቱ ጋር ያልተቆራኘ እንደ ሂሣብ ሠራተኛ፣ የንብረት ክፍል ሠራተኛ፣ የስታትስቲክስ ሠራተኛ ወዘተ አሉ፡፡ በመሆኑም የሃይማኖት ሥራውን ከሚሠሩት ሠራተኞች ጋር የሚነሣው የአሠሪና ሠራተኛ ሁኔታ ከሌሎቹ ሠራተኞች ጋር ከሚነሣው የተለየ ነው፡፡ ቀጥተኛ የሃይማኖቱን ወይም መንፈሣዊ ስራ የሚሠሩትን ሠራተኞች ስንመለከት የስራቸው ፀባይ የኃይማኖት ተቋሙ ከሚከተለው እምነት የሚመነጭና ከእምነቱ ጋር ጥብቅ ትስስር ያለው በመሆኑ መንፈሣዊ አገልግሎቱን ለመስጠት ብቁ ሆኖ ለመገኘት መማሟላት የማይጠበቅባቸው ነጻዎች፣ ለምን ያህል ጊዜ አገልግሎቱ ላይ መቆየት እንደሚችል፣ የኃይማኖቱ እና የመንፈሣዊ አገልግሎት ሠጪው መብትና ግዴታ አገልጋዩ መንፈሣዊ አገልግሎቱን እየሠጠ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ሁኔታዎች አገልጋዩ አግባብ ባልሆነ መንገድ አገልግሎቱን እንዳይሠጥ በተደረገ ጊዜ የሚከተሉት ሁኔታዎች እና ሌሎች በስራ ግንኙነቱ ለሳሱ የሚችሉ ጉዳዮች እያንዳንዱ የኃይማኖት ተቋም ከሚከተለው እምነት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የመንፈሣዳዊ ስራ ግንኙነቱ የሚያስነሣቸው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች ከእምነቱ ተነጥለው የሚታዩ ባለመሆናቸው በስራ ይንኙቱ ላይስጨ ልቃ መግባቱ በእምነት ውስጥ ጣልቃ መግባትን ያስከትላል፡፡

በሌላ በኩል ግን ከእምነቱ ጋር ተያያዥነት ያለውን ሥራ የሚሠሩ ሠራተኞች ከድርጅቱ ጋር የሚኖራቸው ይንኙነት ሊያስነሣ የማይችለው ጉዳዩ ከእምነቱ ጋር የማይያያዝና ይልቁንም በማንኛውም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ከሚነሱ ሁኔታዎች የተለየ አይደለም፡፡

ከላይ እንደተመለከተው የመንፈሣዊ የስራ ግንኙነቱ የሚያስነሣቸው ሁኔታዎች ከኃይማኖቱ ተነጣጥለው ሊታዩ የማይችሉ በመሆናቸው የሥር ፍ/ቤት ለተሰጠው አንቀፅ በሰጠው ትርጉም የሚኒስትሮች ምክር ቤት የመንፈሣዊ ስራ ይንኙነትን በሚመለከት ሕግ የሚያወጣ ከሆነ በኃይማኖት ጉዳዮችም ጣልቃ መግባቱ ይሆናል ይህ ደግሞ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀት 11 "መንይሥትና

ኃይማኖት የተለያዩ ናቸው፤ መንግሥት በኃይማኖት ጉዳዮች ጣልቃ አይገባም" በማለት ከተደነገገው ጋር የሚጋጭ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የሃይማኖቱን ሥራ ከሚሠሩት ሠራተኞች ውጪ ያሉና በሃይማኖት ተቋም ከሚሰሩ ሰራተኞች ጋር ያለው የሥራ ይንኙነት የሚያስነሳቸው ጉዳዮች ለሌላው የአሠሪና ሠራተኛ ይንኙነት ከሚያስነሳው ጋር ተመሣሣይ በመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአ.ቁ.42/85 አንቀጽ 3(3)(ለ) መሠረት ሊያወጣ የሚችለው ደንብ እነዚህን ሠራተኛን በተመለከተ እንጂ መንፈሣዊ አገልግሎት ለመስጠት ከኃይማኖት ተቋማት ጋር የሚያደርጉትን ግንኙነቶች የሚጨምር ሊሆን አይችልም፡፡

በመሆኑም ደንቡ እስካልወጣ ድረስ የአዋጅ ቁጥር 42/85 በመንፈሣዊ የሥራ ግንኙነቶች ላይም ተፈፃሚ ይሆናል የማለቱ ትርጉም ሕይ መሠረት የለውም ይሆናል፡፡

ከፍ ሲል በተዘረዘሩት ምክንያቶችም ማንኛውም የሥራ ክርክር ሰሚ አካላት መንፈሣዊ የሥራ ግንኙነቶች ተመስርቶ የሚነሱ ክርክሮች በአ/ቁ. 42/85 መሠረት አይቶ ለመወሰን ሥልጣን የላቸውም ሲሆን ክርክሮቹ የኃይማኖት ተቋማቱ በማቸራቸው አለመግባባቶች በሚፈቱበት መንገድ የሚታዩ ናቸው፡፡ ይህ ችሎትም የስር ፍ/ቤት በዚህ ጉዳይ በታየው የሕይ ነጨብ የሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡

**<u>□□ሣ ኔ</u>**

1/ □ፀ/መ/ድረየ □/በ□ት በመ/ቁ. 13549 ህ□ር 24 ቀን 1997 □ሰ□□□ ውሣኔና የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35562 ጥር 17 ቀን 1997 ዓ.ም የሰ□ው ትእዛዝ ተሽሯል፡፡

2/ ይራ ቀኙ □ጨና ኪሣራቸ□□ን □□ራሣቸ□□ን □ቻለ□፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ አምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.□

# ቤተሰብ

የሰ/መ/ቁ. 34703

ጥቅምት 11 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች**:- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**:- እንደሻው ፍቃዱ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪዎች**:- እነ ወንድማገኝ ፍቃዱ /ሰባት ሰዎች/

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የውርስ ንብረት ክፍፍል ጥያቄን መነሻ ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን ከሣሽ የነበረው የአሁኑ አመልካች ነው፡፡ አመልካቹ በተጠሪዎች ላይ ክስ የመሠረተው ይዘውት ከሚገኘው የውርስ ንብረት ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ ከተጠሪዎች መሃል ስድስቱ ለክሱ በሰጡት መልስ ከሣሹ ልክ እንደኛው ወራሽ ነው፤ ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ ነን፤ በእርግጥ የጠየቀው የውርስ ሃብት ግምት የተጋነነ ነው በማለት ሲከራከሩ አንዱ ደግሞ ጉዳዩ በሽምግልና እየታየ ነው የሚል መቃወሚያ አቅርቧል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኝ ወገኖችን ክርክር ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ ውርስን የሚመለከት በመሆኑ ከሣሽ የውርስ ሃብቱ ይጣራልኝ የሚል ክስ በቅድሚያ ሊያቀርብ ይገባል የሚል ምክንያት በመስጠት ክሱን ሰርዟል፡፡ በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠው ብይን ጉድለት የለበትም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ታሕሣሥ 29 ቀን 2000 ዓ.ም. በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም በሚል ምክንያት አመልካች ያቀረበው የውርስ ሃብት ልካፈል ክስ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ብይን እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው በአመልካች የቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ግልጽ ነው፡፡ ክሱን የመሠረተው በወንድሞቹ እና እህቶቹ ላይ ሆኖ በወራሾች መካከል ካልተከፋፈለው የሁሉም አባት ንብረት ላይ የውርስ ድርሻውን እንዲያካፍሉት ነው፡፡ የክፍያ ጥያቄ ያቀረበባቸውን የውርስ ሃብቶችም /ንብረቶች/ በክስ ማመልከቻው ላይ ዘርዝሮ ስለማቅረቡ አቤቱታ በቀረበበት ብይን ላይ ተመልክቶአል፡፡ አመልካች ተጠሪዎችን የከሰሰበት ምክንያትም ግልጽ ነው፡፡ ይኸውም የውርስ ሃብቶቹን በእጃቸው ይዘው ስለሚገኙ ነው፡፡ ተጠሪዎች ለስር ፍ/ቤትም ሆነ ለዚህ ሰበር ችሎት ባቀረቡት መልሳቸው ንብረቶቹን አልያዝንም /በእጃችን አይገኙም/ የሚል ክርክር አላነሱም፡፡ አመልካች ወራሽ አይደለም ወይም ከተባሉት ንብረቶች የሚያገኘው መብት የለም የሚል ክርክርም የላቸውም፡፡ ይልቁንም በክሱ የተጠየቀውን በመቀበል ለአመልካች ድርሻውን ለማካፈል ዝግጁ መሆናቸውን ነው የገለጹት፡፡

እንደምንመለከተው በዚህ ጉዳይ ወራሾቹም ሆኑ የውርስ ሃብቶቹ በግልጽ ተለይተው ታውቀዋል፡፡ ሳይከናወን የቀረው ንብረቶቹን በወራሾቹ መካከል የመከፋፈሉ ጉዳይ ነው፡፡ በእርግጥ ከውርሱ ሃብት የሚከፈል ዕዳ እንዳለና በአመልካች ክስ የተመለከተው የንብረት ግምት የተጋነነ እንደሆነ በተጠሪዎች ክርክር ተገልጾአል፡፡ እንደተባለው ከውርስ

ሃብቱ ላይ የሚፈለግ ዕዳ ካለ ክሱ በቀረበበት ፍ/ቤት መሪነት በማስረጃ ተጣርቶ ሊታወቅ የሚችል ነው፡፡ ተጠሪዎችም በእርግጥ ያልተከፈለ እና በትክክልም ከውርስ ሃብቱ ላይ የሚከፈል ዕዳ አለ ካሉ ይህንኑ በማስረጃ አስረግጠው ለፍ/ቤቱ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ ውጪ ግን ዕዳ አለ በመባሉ ምክንያት ሕግና ስርዓት ተከትሎ የቀረበው ክስ የሚዘጋበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡

አመልካች ክስ በመሠረተበት /ለክሱ መነሻ በሆነው/ ሃብት ላይ ጥቅም ወይም መብት እንዳለው አረጋግጦ ነው /የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 33/፡፡ ክሱ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በጉዳዩ ላይ የስረ-ነገር የዳኝነት ስልጣን የለውም አልተባለም፡፡ ፍ/ቤቱ ክሱን የሰረዘው የዳኝነት ስልጣን የለኝም በሚል ቢሆንም፤ ለዚህ የሰጠው ምክንያት ግን የውርስ ማጣራት ስርዓት አልተካሄደም የሚል ነው፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው የውርስ ሃብት ክፍፍልን መነሻ የሚያደርግ ክስ በውርስ አጣሪ በኩል ካላለፈ በቀጥታ ወደ ፍ/ቤት አይቀርብም የሚል አስተሳሰብ ወይም አካሄድ የተያዘ መሆኑን ነው፡፡ በእርግጥ በወራሾች በራሳቸው ወይም በተመረጠ በሌላ ሰው አማካይነት ውርስ እንደሚጣራ በሕጉ ተመልክቶአል፡፡ ከውርስ ማጣራት ተግባራት አንዱ የውርስ ሃብቱን መከፋፈል እንደሆነም ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ይህ እንግዲህ አንዱ የውርስ ሃብት የሚከፋፈልበት መንገድ ነው ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ድርሻዬን አላገኘሁም የሚል ወራሽ የውርስ ሃብቱን በያዘው ሰው ላይ በቀጥታ ክስ የመመስረት መብት የለውም ወይም ሕጉ ከልክሎአል ለማለት የሚቻል እንዳልሆነ መገንዘቡ ተገቢ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው የውርስ ሃብቶቹ በተጠሪዎች እጅ ተይዘው እንደሚገኙ አላከራከረም፡፡ አመልካችም ከእነዚህ ሃብቶች ላይ ድርሻውን እንዲያገኝ ነው የጠየቀው፡፡ በመሆኑም እንደማንኛውም የፍትሐብሔር ክርክር ታይቶ እና በማስረጃ የሚጣራ ካለም ተጣርቶ ሊወሰን ሲገባ የውርስ ማጣራት ቅድመ ሁኔታ እንደሆነ ተደርጎ መወሰዱ ትክክል አይደለም፡፡ ፍ/ቤቱ የዳኝነት ስልጣን የለኝም በማለት የሰጠው ብይን መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው ለማለት ችለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 49517 ሐምሌ 10 ቀን 99 ዓ.ም. ተሰጥቶ የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 32508 ጥቅምት 11 ቀን 2000 ዓ.ም. በሰጠው ትዕዛዝ የፀናው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በተከፈተው መዝገብ በመቀጠል በግራ ቀኝ ወገኖች የሚቀርብለትን ክርክር እና ማስረጃ ከሰማ በኋላ የመሰለውን ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 341/1/ መሠረት ይመለስለት ብለናል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኙ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 36604

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጽጌ መንግሥቱ - ጠበቃ ሰሎሞን ገ/ሚካኤል ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወንድይራድ መንግሥቱ - ቀረበ

2. ሠይፉ ተረፈ - ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ ለቀረበው ይግባኝ መነሻ የሆነው ጉዳይ ኑዛዜን መሠረት በማድረግ የቀረበውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተጠሪዎች በአመልካች አቤቱታ አቅራቢነት ተሰጥቶ የነበረው የወራሽነት ማስረጃ እንዲሰረዝላቸው መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡ ለመቃወሚያቸው መሠረት አድርገው የጠቀሱት አመልካች የወራሽነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጣት በአስረጂነት ያቀረበችው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት አያሟላም፤ ኑዛዜው ሕጋዊ አይደለም፤ የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱ አመልካችን አስቀርቦ ክርክሩን ከሰማ በኋላ ኑዛዜው የኑዛዜ አድራጊዋ ወራሾች የሆኑትን ተቃዋሚዎችን ያለምንም ምክንያት ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ ቀደም ሲል ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ ተሰርዟል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ይህን ውሣኔ በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ በዚህ ይግባኝ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቷል፡፡ ፍ/ቤቱም ኑዛዜው የሕጉን መስፈርት ያሟላ ሕጋዊ ነው የሚል ምክንያት በመስጠት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን /ይግባኝ የተባለበትን/ ውሣኔ የሻረ ሲሆን በመቀጠልም ተጠሪዎችም እንደአመልካች ወራሾች ስለሆኑ የኑዛዜ አድራጊዋን ሐብት እኩል ይካፈሉ በማለት ወስኖአል፡፡ በመጨረሻም ይህን ውሣኔ በመቃወም ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ኑዛዜው ተጠሪዎች በዝምታ ከውርስ የሚነቅል በመሆኑ የሚፀናበት የሕግ ምክንያት የለም፤ የውርስ ሃብቱን ግራ ቀኝ ወገኖች እኩል ይካፈሉት መባሉ ግን ትክክል ነው በማለት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች መጋቢት 15 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ከስር ጀምራ አቅርባ ስትከራከርበት የቆየችው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ የተደረገበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሰጠው ውሣኔ እንደተመለከተው ተጠሪዎች ኑዛዜውን በመቃወም አቤቱታ ያቀረቡት ኑዛዜ ከተደረገ ከ16 /አስራ ስድስት/ ዓመት በኋላ ነው፡፡ ኑዛዜው ሟች ከሞቱ /ኑዛዜ አድራጊዋ ከሞቱ/ በኋላ በ80ኛው ቀን ሲፈስ ተጠሪዎች ተገኝተው እንደሰሙ በምስክር ስለመረጋገጡ በውሣኔው ላይ ተገልጿል፡፡ እንደምንመለከተው ተጠሪዎች የኑዛዜውን መደረግ /መኖር/ ብቻ ሣይሆን አመልካች በኑዛዜው መሠረት ተጠቃሚ ሆና

መቆየትዋን ጭምር አውቀው ለብዙ ዓመታት በዝምታ ማለትም ሣይቃወሙ ቆይተዋል፡፡ አመልካች መቃወሚያው በይርጋ ቀሪ ሆኗል የምትልበት ዋናው ምክንያትም ይኸው ነው፡፡

ኑዛዜን በመቃወም የሚቀርበው ማናቸውም መቃወሚያ መታየት ያለበት አግባብነት ካላቸው የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች አንፃር ነው፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ክርክር አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 የተመለከተው ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ ኑዛዜው ፈራሽ ነው የሚል መቃወሚያ ያላቸው ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ የነበሩትን ሰዎች የሚመለከት ነው፡፡ ይህም ኑዛዜው ሲነበብ የነበሩ ወይም የተወከሉ ሰዎች ኑዛዜው አይፀናም ወይም በኑዛዜው የተነገረ ቃል አይፀናም የሚሉትንና የመሳሰሉትን በመቃወም ክስ የሚያቀርቡ ቢሆን ይህን ማድረግ ያለባቸው ኑዛዜው ከተነበበበት አንስቶ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ እንደሆነ ያመለክታል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ክስን የማቅረብ ሃሣብ መግለጫው በጽሑፍ ካልሆነና ለአጣሪው ወይም ለዳኞች ወይም በውርስ ላይ የተነሣውን ነገር ለመጨረስ ለተመረጡት የሽምግልና ዳኞች እንዲደርስ ካልተደረገ በቀር እንደማይፀና /መቃሚያ አለ ለማለት እንደማይቻል/ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 973/2/ ተደንግጓል፡፡ በመጨረሻም መግለጫው ከተሰጠበት ቀን አንስቶ እስከ ሦስት ወር ድረስ ክስ ካልቀረበ መብቱ ከነጭራሹ እንደሚቀር በንኡስ ቁጥር /3/ ተመልክቷል፡፡

ቀደም ሲል እንዳመለከትነው ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነገር /ሲፈስ/ በቦታው እንደነበሩ /እንደሰሙ/ አላከራከረም፡፡ መቃወሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 973 በግልጽ የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ እንዳልሆነም ተረጋግጧል፡፡ በሌላም በኩል ኑዛዜው ሲነበብ አልነበሩም ተብሎም ቢሆን ኖሮ መቃወሚያውን ሣያቀርቡ የቆዩት ለ16 /አስራ ስድስት/ ዓመታት ያህል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 974 የተቀመጠው የአምስት ዓመት የጊዜ ገደብ ይከለክላቸዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 974/2/ በግልጽ እንደተመለከተው ኑዛዜው ከፈሰሰበት /ከተነበበት/ ጊዜ ከአምስት ዓመት በኋላ ስለኑዛዜው መጽናትም ሆነ ስለክፍያው ድልድል መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል ተጠሪዎች ኑዛዜው ሲነበብ /ሲፈስ/ አልነበሩም ወይም አልሰሙም አልተባለም እንጂ ተብሎም ቢሆን ኖሮ በመጨረሻ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ ከመሆን የሚድን አይደለም፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረበችው የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ መደረጉ አግባብ አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሣኔም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 24280 የካቲት 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 45325 ሚያዝያ 12 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 31177 የካቲት 27 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. ተጠሪዎች በኑዛዜው ላይ ያቀረቡት መቃወሚያ በይርጋ ቀሪ የሆነ በመሆኑ መቃወም አይችሉም በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 37275

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ሻ/ባሻ ገዛኸኝ ድልነሣው - ቀረበ

**መልስ ሰጭ፡-** ወ/ሮ ተዋበች ደመቀ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን በአብላጫ ድምጽ ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር ጉዳይ ሊቀርብ የቻለው በግራ ቀኙ መካከል የተነሣውን የንብረት ክፍፍል በሚመለከት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት የአሁን አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን አመልካች በሥር የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከፍቺ ውሣኔ ቀጥሎ የንብረት ክፍፍል ይደረግለት ዘንድ የንብረት ዝርዝር አቅርቧል፡፡ ከቀረበውም የንብረት ዝርዝር መካከል ለዚህ ጉዳይ መነሻ የሆነው በወረዳ 28 በቀበሌ 01 በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የጋራ በመሆኑ እኩል እንካፈል ዘንድ ውሣኔ ይሰጥልኝ በማለት ዳኝነት በመጠየቁ ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም በተጠሪነታቸው ቀርበው ይኸው ንብረት ከጋብቻ በፊት ከመጀመሪያ ባለቤታቸው ጋራ ያፈሩትና የግል ንብረታቸው የሆነውን በወረዳ 28 ቀበሌ 01 በቤት ቁጥር 419 በካርታ ቁጥር ኮ/01/152/73 የተመዘገበውን ቤት በመሸጥ በምትኩ ይኸው ክርክር ያስነሣው ቤት በግዥ የተገኘ በመሆኑ የግል ሀብቴ እንጅ የጋራ ሀብት ባለመሆኑ የቀረበው የክፍፍል ጥያቄ ተቀባይነት የለውም በማለት ተከራክረዋል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም በኮ/መ/ቁ. 12164 ታህሣሥ 24 ቀን 1998 ዓ.ም በዋለው ችሎት የቤት ቁጥር 610 የተሰራው አመልካችና ተጠሪ ጋብቻ መሥርተው አብረው ሲኖሩ የነበሩበትና በቤት ቁጥር 419 የተመዘገበውን ቤት በመሸጥ ስለመሆኑ በግራ ቀኙ የተካደ ነጥብ አይደለም፤ በተጠሪ በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች እንዳረጋገጡት የቤት ቁጥር 610 መኖሪያ ቤት የተሰራው በቤት ቁጥር 419 በተመዘገበው ቤት የሽያጭ ገንዘብ ሲሆን ፤ የቤት ቁጥር 419 የአሁኑ ተጠሪ የግል ንብረት የነበረ መሆኑ ተረጋግጧል፤ አመልካችም ይኸው በሽያጭ ገንዘብ የተሰራው የቤት ቁጥር 610 ባልና ሚስቱ በጋብቻ አብረው በሚኖሩበት ጊዜ በግል ጥረታቸው ባገኙት ገቢ የተሰራ እና የተገዛ ስለመሆኑ አላስረዳም፤ ስለሆነም አመልካች የጋራ ሀብት እንደሆነ በመቁጠር የንብረት ክፍፍል ያቀረቡበት የቤት ቁጥር 610 የተጠሪ የግል ሀብት በመሆኑ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/1/ መሠረት የግል ሀብት እንጅ የጋራ ባለመሆኑ ይህንኑ ቤት አስመልክቶ ያቀረበው ክሱ ውድቅ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን በይግባኝ ደረጃ ካከራከረ በኋላ በኮ.ቁ. 44232 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም በዋለው ችሎት ምንም እንኳን የአሁን መልስ ሰጭ ክርክር ያስነሣውንና በቤት ቁጥር 610 የሚታወቀውን ቤት የገዙት የቀድሞ ቁጥሩ 419 የሆነውን መኖሪያ ቤታቸውን ሸጠው መሆኑን በተሻለ ሁኔታ ቢያስረዱም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ መሠረት በግዥ የተገኘው ቤት የግላቸው እንዲሆን በፍ/ቤት ወይም በወቅቱ እንደሚቻለው በቤተዘመድ ሽምግልና ጉባዔ አላስወሰኑም፤ ስለሆነም ተጠቃሹ ቤት የመልስ ሰጭ የግል ሀብት ነው ሲል የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ላይ መድረሱ ውሣኔው ሕጉን በአግባቡ ያላገናዘበ ነው፤ ስለሆነም በአሁኑ አጠራር በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ በቤት ቁጥር 610 ተመዝግቦ የሚገኘው ቤት የጋራ ሀብት ነው፤ ከተቻለ ግራ ቀኙ በዓይነት እኩል ይካፈሉ፣ ይህ የማይቻል ለመሆኑ ከተረጋገጠ ግን ከተስማሙ አንዱ ለአንዱ የግምቱን አጋማሽ ሰጥቶ ያስቀር፤ በዚህ ባይስማሙ ግን ከተስማሙ በጋራ ሸጠው፤ ካልተስማሙ በሐራጅ ተሸጦ ገንዘቡን እኩል ይካፈሉ በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው የአሁን መልስ ሰጭ የይግባኝ አቤቱታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ባቀረቡት መሠረት ጠ/ፍ/ቤት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎትም በጋብቻ ጊዜ በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ሀብት ይባልልኝ ብሎ ለፍ/ቤት ጥያቄ አቅርቦ እንዲፀድቅ ያስፈለገበት ምክንያት የጋራ ሀብትን እንደግል ሀብት በማስመሰል 3ኛ ወገኖችን የሚጎዳ ሁኔታ እንዳይፈጠር ለማድረግ ስለመሆኑ ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 ረቂቅ - በ1992 ከታተመው የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ረቂቅ ማብራሪያ ላይ ለመረዳት ችለናል፡፡ ስለሆነም በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ የተደነገገው የ3ኛ ወገኖችን መብት ለመጠበቅ ሲባል እንጅ በሁለቱ ተጋቢዎች መካከል ለሚነሣ ክርክር አግባብነት የለውም፡፡ በመሆኑም ለክርክሩ መነሻ የሆነው በቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የይግባኝ ባይዋ የአሁን መልስ ሰጭ የግል ሀብት እንጂ ከመልስ ሰጭው ጋር ሊካፈሉት የሚገባ የጋራ ሀብት አይደለም በማለት ወስኖ አሰናብቷል፡፡

ይህ የሰበር ጉዳይም የቀረበው በዚህ አኳኋን የፌ.ጠ.ፍ/ቤት የሰጠው የሕግ ትርጓሜ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉበትን ክርክር በማቅረብ በሰበር ሰሚው ችሎት እንዲታረምላቸው አመልካች ዳኝነት በመጠየቃቸው ነው፡፡

መልስ ሰጭም ጠ/ፍ/ቤቱ በይግባኝ አይቶ የሰጠው ውሣኔ ትክክለኛውን የሕግ ትርጉም መሠረት በማድረግ ስለሆነ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ጉዳዩን አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በዚህ ጉዳይ ክርክር ያስነሣው በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት በፊት የአሁን መልስ ሰጭ የወ/ሮ ተዋበች ደመቀ የግል ሀብት የነበረው የቤት ቁጥር 419 ተሸጦ በግዥ የተገኘ ስለመሆኑ የማያከራክር የፍሬ ጉዳይ ስለመሆኑ በየደረጃቸው የተሰጡት የውሣኔ ግልባጮች አስረጂ ናቸው፡፡ በዚህ ጉዳይ አከራካሪ ነጥብ ሆኖ የተገኘውና በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ትርጉም የሚያሰጥ ሆኖ የተገኘው ከጋብቻ በፊት የነበረ ሀብት በመሆኑ የተነሣ የነበረን የግል ሀብት በመሸጥ ሌላ ቤት በግብይት በግዥ በተገኘ ጊዜ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ በተደነገገው መሠረት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? የሚለው ነው፡፡

በመሠረቱ ባል ወይም ሚስት ጋብቻቸውን በሚፈጽሙበት ጊዜ በየግል የነበሯቸው ንብረቶች የግል ንብረቶቻቸው ሆነው እንደሚቀጥሉ በዚሁ ሕግ አንቀጽ 57 ተደንግጓል፡፡ በዚህ አኳኋን የግል የነበረ ንብረት በግብይት የተነሣ ዓይነቱን ለውጦ በተገኘ ጊዜ የግል ሆኖ እንዲቆይ ለማድረግ በአንቀጽ 58 የተመለከተውን በመረዳት አስቀድሞ ሊፈፀም እንደሚገባ የሕጉ አደራደር ቅደም ተከተል ያስገነዝባል፡፡ በመርህ ደረጃ በአንቀጽ 58/1/ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ይሆናል በሚል ከተቀመጠ በኋላ በዚህ ሁኔታ የተነሣ ንብረቱ የግል ይባልልኝ ብሎ 1ኛው ወገን ጥያቄ ሲያቀርብና ፍርድ ቤት ሲያፀድቀው ብቻ ነው በማለት በተለየ ሁኔታ አስቀምጧል፡፡ ይኸው በአንቀጽ 58/2/ መሠረት በስርዓቱ አለመፈፀሙ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ አንቀጽ 58 በእራሱ ገላጭ እንጂ ለትርጉም በር የከፈተ ሆኖ አይገኝም፡፡

ድንጋጌው ግልፅነት ይጎድለዋል ከተባለም ድንጋጌዎችን እርስ በእርሣቸው አስተሳስረን ልንመለከት ይገባል ፡፡ የአንቀጽ 57 እና 58 ርዕሰ ጉዳዮች ቁጥር 1 እና 2 በሚል የተያያዙ በመሆናቸው ከጋብቻ በፊት የነበረ ሀብት የግል ሆኖ የሚቀጥለው በማናቸውም ዓይነት ምክንያት ዓይነቱን ካልለወጠ እና ለውጦ ከተገኘም የግል ሀብት እንደሆነ ሊቀጥል እንደሚገባ፣ በዚህ መሠረት የግል ሀብት ሆኖ ሊቀጥል የሚገባው ግን በልዋጭ የተገኘው ሀብት የነበረውን የግልነት አቋም ይዞ እንዲቀጥል በፍ/ቤት ቀርቦ የፀደቀ እንደሆነ ብቻ ስለመሆኑ እነዚህ ተያያዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች በግልጽ ያመለክታሉ፡፡ ይህን በአንቀጽ 58/2/ የተመለከተውን ማሚያ አለመተግበር የሚያስከትለው ሕጋዊ ውጤት ወሰን በእነማን ላይ ያተኮረ ነው የሚለውም ቢሆን አሻሚ በመሆኑ ትርጉም ያስፈልገዋል፤ ለመተርጎምም የሕግ አውጭውን ሀሣብ መፈለግ ይበጃል ወደሚል መደምደሚያ የሚያደርስ አይደለም፡፡ በመሠረቱ ከትርጉም ዘዴዎች አንዱ የሕግ አነጋገር ግልጽ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ሕጉን እንዳለ ሥራ ላይ ማዋል እንጅ በትርጉም ሽፋን ከሕጉ ይዘት መራቅ የሚያስፈልግ አይደለም፡፡ ይተርጎም እንኳ ቢባል የሕግ አውጭው ሀሣብ ምን ነበረ ከሚለው መነሻ ይልቅ የሕጉን ድንጋጌዎች እርስ በእርሣቸው አስተሳስሮ ማየቱ ለትክክለኛው ትርጓሜ የሚያደርስ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በዚሁ ሕግ አንቀጽ 62/2/ "----በዚህ ሕግ አንቀጽ 58 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የአንደኛው ተጋቢ የግል ሀብት ነው ካልተባለ በቀር ባልና ሚስቱ ከተጋቡ በኋላ በግብይት የሚያገኙት ንብረት ሁሉ የጋራ ሀብታቸው ይሆናል" በማለት የባልና ሚስትን የጋራ ሀብት በሚደነግገው ክፍል መጠቀሱ በአንቀጽ 58/2/ የተመለከተውን ሥርዓት አለመፈፀም የሚያስከትለው ውጤት የተጋቢዎች የጋራ ሀብት የቱ ነው ለሚለው ጉዳይ ተፈፃሚ መሆኑን በግልጽ የሚያመለክት ነው፡፡

ስለሆነም የአሁን መልስ ሰጭ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን የግል ሀብት በቁጥር 419 የተመዘገበውን ቤት በጋብቻ ላይ እያሉ በመሸጥ በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበውን ቤት ሲገዙ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 58/2/ ሆነ በጊዜው ለጉዳዩ ተፈፃሚነት በነበረው ሕግ መሠረት በግብይት የተገኘው ቤት የግል ሆኖ ይቀጥል ዘንድ አቅርበው በሚመለከተው ክፍል አለማፀደቃቸው እስከተረጋገጠ ድረስ ክርክር ያስነሣው እና በቁጥር 610 የተመለከተው ቤት የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ነው ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ በድሮው አጠራር በወረዳ 28 ቀበሌ 01 በአሁኑ አጠራር ደግሞ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 19 ክልል ውስጥ የሚገኘው እና በቤት ቁጥር 610 የተመዘገበው ቤት የአመልካችና የመልስ ሰጭ/ የባልና ሚስት/ የጋራ ሀብት ስለሆነ እንደ ከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ እኩል ይካፈሉ፡፡

2/ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 12164 ታህሣሥ 24 ቀን 1998 ከሰጠው ውሣኔ ይህንን ቤት በሚመለከት ብቻ የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በፍ/ብ/ይ/መ/ቁ. 27393 መጋቢት 09 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ ተሽረዋል፡፡

3/ የከፍተኛው ፍ/ቤት በኮ.ቁ. 44232 መስከረም 29 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡ ወጭና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ ተዘግቷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሐሣብ ልዩነት

ተጠሪ ከአመልካች ጋር ከመጋባታቸው በፊት የግል ቤታቸው የነበረውን የቤ.ቁ. 419 የሆነውን ቤት ከአመልካች ጋር ከተጋቡ በኋላ ሸጠው በምትኩ የቤ.ቁ. 610 መግዛታቸው ተረጋግጧል፡፡ ከፍ ብሎ በአብላጫው ውሣኔ ላይ እንደተመለከተው ባልና ሚስት ከተጋቡ በኋላ አንዱ የግል ሀብቱ በሆነ ንብረት ለውጥ ያገኘው ወይም በግል ገንዘቡ የገዛቸው ወይም የግል ንብረቱን ሸጦ የሚያገኘው ገንዘብ የግል ሀብቱ ሊሆን እንደሚችልና ይህም ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው በግብይት የተገኘው ንብረት የግል ይባልልኝ ብሎ አንደኛው ወገን ጥያቄውን ለፍ/ቤት አቅርቦ ጥያቄውን ፍ/ቤት ሲያፀድቀው እንደሆነ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በአንቀጽ 58/1/ እና /2/ ላይ ተመልክቷል፡፡

የግል ንብረት ተሸጦ በሌላ ንብረት ሲተካ ወይንም በሌላ ንብረት ሲለወጥ የኋላኛው ንብረት የግል እንዲባልለት የሚፈልገው ወገን ጥያቄውን ለፍ/ቤት ማቅረብ የሚጠበቅበት በሽያጭ ወይንም በለውጥ የተገኘው ንብረት በጋብቻ ውስጥ ከተፈራ ንብረት ጋር የመቀላቀል አጋጣሚ ሊፈጠር ስለሚችል ከጋራ ንብረት ያልተቀላቀለ መሆኑን ጭምር በማሣየት የግል ሀብት መሆኑን ማረጋገጥ እንደሚቻል ከሕጉ ዓላማ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ቤት በጋብቻ ጊዜ ሸጠው በዚያው የሽያጭ ገንዘብ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ቤት ገዝተዋል፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ቤት ሸጠው በዚያው ገንዘብ በጋብቻ ጊዜ ሌላ ቤት መግዛታቸው ሲታይ ከጋራ ንብረት ጋር ግብይቱ ተቀላቅሏል የሚያሰኝ ካለመሆኑም በላይ ስለመቀላቀሉም አመልካች አላስረዱም፡፡ በዚህ ሁኔታ የተገኘን ቤት የግል ነው እንዲባል በፍ/ቤት እንዲፀድቅ በማድረግ ተጨማሪ ማረጋገጫ ማግኘት ከሕጉ ዓላማ አኳያ ተገቢነት ያለው አይሆንም፡፡

በእርግጥ ተጠሪ የግል ቤታቸውን ሸጠው ሌላ ንብረት ገዝተው ቢሆን ኖሮ ይሄው በግብይት የተገኘ ሌላ ንብረት ጠቀሜታው /purpose/ የተለየ ከመሆኑ አንፃር ለትዳር ጥቅም አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት እንደተገዛና ከጋራ ንብረት ጋር የመቀላቀልም ዕድሉ የሰፋ እንደሚሆን ስለሚገመት በዚህ መልኩ የተገኘ ንብረት የግል እንዲባል በፍ/ቤት ካልፀደቀ በስተቀር የጋራ ንብረት እንደሚሆን ከሕጉ ዓላማ አኳያ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ነገር ግን አስቀድሞ የነበረን ቤት በትዳር ጊዜ ሸጦ በሌላ ቤት መተካት ወይንም አስቀድሞ የነበረን መኪና ሸጦ በሌላ መኪና መተካት ከጋራ ንብረት ጋር የመቀላቀል ዕድሉ ጠባብ እንደሆነ ስለሚገመት በዚህ ሁኔታ የተገኘን ንብረት የግል ነው እንዲባል ተጨማሪ ማረጋገጫ ከፍ/ቤት እንዲገኝ መጠየቅ ሕጉ ይዞት ከተነሣው ዓላማ ጋር የተጣጣመ ነው ለማለት አያስደፍርም፡፡

ሲጠቃለልም ምንም እንኳን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተጠሪ የግል ንብረት ሊሆን ይገባል ሲል የደረሰበት ድምዳሜ በአብላጫው ውሣኔ ላይ እንደተመለከተው ከተሣሣተ የመነሻ ሃሣብ /premise/ ቢሆንም ቤቱ የተጠሪ የግል ንብረት ነው በማለት የደረሰበት ድምዳሜ ግን ከውጤት አኳያ ተገቢነት ያለው ስለሆነ ይሄው ውሣኔ ምክንያቱ ተለውጦ ሊፀና ይገባል በማለት ስሜ በተራ ቁጥር 4 ላይ የተመለከተው ዳኛ በአብላጫ ድምጽ ከተሰጠው ውሣኔ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 36777

ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መሰሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ወንድምአገኝ ዘውዱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ 1/ አቶ ታፈሠ ወንድአፍራሽ

2/ ወ/ሮ በለጤ አምደመስቀ ል ሁሉም } ቀርበዋል

3/ ወ/ሮ ቆንጅት ምንዳሁን

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ጉዳይ የኑዛዜ አፃፃፍ ሥርዓትን የሚመለከት ነው፡፡

ለሠበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ አመልካች ሟች ውብዬ ምንዳሁን የተውት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለፍ/ቤቱ አመልክተው ኑዛዜው ተረጋግጦ ማስረጃ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኖቹ ተጠሪዎች ኑዛዜው ሃሰተኛ ነው፤ ተናዛዥዋ ራሣቸውን በሣቱበት ጊዜ የተደረገ ነው፤ ሟች መፃፍ የሚችሉ ሆነው ሣለ በአሻራቸው መፈረማቸው ኑዛዜውን እንዳላደረጉ ያሣያል፤ በኑዛዜው በግልጽ አልተነቀልንም በማለት ኑዛዜው ውድቅ እንዲደረግ አቤቱታቸውን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሠረት አቅርበዋል፡፡ አመልካችም ቀርበው ኑዛዜው ውል አዋዋይ ፊት የተደረገ ነው፤ ሟች በአሻራ ቢፈርሙም በውል አዋዋይ እና በምስክሮቹ ፊት ስለተደረገ ተገቢ ነው፤ ተጠሪዎች ተወላጆች ስላልሆኑ ከውርስ የተነቀሉበት ምክንያት ሊገለፅ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ኑዛዜው በታይፕ ተጽፎ በምስክሮች ፊት ተነቦ ምስክሮችም ወዲያው መፈረማቸውን፣ ምስክሮቹ ችሎታ ያላቸውና አማርኛ ቋንቋም እንደሚችሉ፣ ሟችም ፊርማቸውን እንዳኖሩበት ተረጋግጧል፤ የምስክሮቹም ብዛት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት በቂ ነው፤ የሟች የአእምሮ ሁኔታ ደህንነትን በተመለከተ ኑዛዜውን ያስፈፀሙት ኃላፊ በምስክርነት ተጠርተው አረጋግጠዋል፤ ስለዚህ ኑዛዜው የሚነቀፍበት ምክንያት ስለሌለ የቀድሞው ውሣኔ አይሻርም በማለት የተጠሪዎችን አቤቱታ ውድቅ አድርጓል፡፡

ይህንን ውሣኔ በመቃወም ተጠሪዎች ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አስቀርቦ ካከራከረ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በ2 ምስክሮች መፈረሙ በቂ የሚሆነው ከምስክሮቹ አንዱ ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው አካል ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በኑዛዜው ላይ ከፈረሙት ሁለት ምስክሮች ውስጥ አንዳቸውም የውልና ምዝገባ ጽ/ቤት ሠራተኛ ስላልሆኑ ኑዛዜው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 የተቀመጠውን መስፈርት አያሟላም ስለሆነም አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽነት መብት የላቸውም ሲል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካችም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ የአመልካች አቤቱታም ኑዛዜው የተደረገው ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት በአ/አበባ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመሆኑ በበቂ ምስክር ተረጋግጧል፤ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉትም በነፃ ፍላጎታቸው ነው የሚል ነው፡፡ ተጠሪዎችም ቀርበው ኑዛዜው በሕግ የተመለከተውን ስርዓት አልተከተለም፤ ሟች ኑዛዜውን የሰጡት ጤነኛ በነበሩበት ሰዓት አልነበረም ሟች የተማሩ ስለነበሩ በጣት መፈረማቸው በጤና መታመማቸውን ያሣያል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው ግራ ቀኙ የሚከራከሩበትና ይህም ችሎት አቤቱታው ለሰበር ችሎት ቀርቦ እንዲጣራ ያደረገበት ነጥብ ሟች ውብዬ ያደረጉት ኑዛዜ በሕጉ ላይ የተመለከተውን መስፈርት ያሟላል አያሟላም የሚለው ነው፡፡ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ ግልፅ ኑዛዜ መሆኑ ያላከራከረ ጉዳይ ነው፡፡ ግልጽ ኑዛዜ ሊያሟላ የሚገባው ስርዓቶች በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ይኸውም 1ኛው ኑዛዜው በ4 ምስክሮች ፊት መነበብ ያለበት መሆኑ፣ ይህም ስርዓት መፈፀሙና የተፃፈበት ጊዜ በኑዛዜው ላይ መመልከቱ፣ ተናዛዡና ምስክሮቹ በኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም ያውራ ጣት ምልክታቸውን ማድረጋቸው መረጋገጡ አስፈላጊ ነው፡፡ በሟች ተሰጠ የተባለው ኑዛዜም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት የተደረገ፣ ሁለት ምስክሮች የፈረሙበት፣ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ኑዛዜውን አረጋግጦ የፈረመበት፣ ኑዛዜው በምስክሮች ፊት ስለመነበቡ የሚገልጽ እና ተናዛዥዋ የጣት አሻራቸውን ምስክሮቹ ደግሞ ፊርማቸውን ያኖሩበት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 ሥር የተመለከቱትን ስርዓቶች ያሟላ ነው፡፡ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ኑዛዜው የህጉን ሥርዓት አልተከተለም ያለው በኑዛዜው ላይ የተመለከቱት ሁለት ምስክሮች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ሠዎች አይደሉም በማለት ነው፡፡ በእርግጥ ምስክሮች ተብለው የተፃፉት ሁለት ሠዎች ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጣቸው ለመሆኑ የሚያመለክት ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ኑዛዜው የተደረገው ከሁለቱ ምስክሮች በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ፊት፣ ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ነው፡፡ ምንም እንኳን እኚህ ሰው ምስክር ተብለው ባይገለፁም ሟች ኑዛዜውን በነፃ ፈቃዳቸው ሲሰጡና ኑዛዜውም ሲነበብ አይተው በኑዛዜው ላይ ፈርመዋል፡፡ የምስክሮች ዋና አስፈላጊነትም ኑዛዜ አድራጊው ኑዛዜውን በነፃ ፍላጎቱ እና በትክክለኛ አእምሮው የሰጠ መሆኑንና የኑዛዜ ቃሉም የእርሱ መሆኑን ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው አረጋግጠው ፊርማቸውን ያኖሩ በመሆኑ ምስክር ተብለው ስማቸው ባለመገለፁ ብቻ ምስክር አልነበሩም የሚባልበት ሕጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ከምስክሮቹ አንዱ ደግሞ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ከሆነና ኑዛዜው ይኸው ሰው ስራውን በሚያካሂድበት ክፍል ከሆነ ሁለት ምስክሮች ብቻ በቂ መሆናቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች ውብዬ ምንዳሁን የኑዛዜ ወራሽ አይደሉም በማለት የተሰጠው ውሣኔ ስህተት ነው፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 47307 በ01/09/99 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 31022 በ28/06/2000 የሰጠው ውሣኔ ተሽረዋል፡፡

2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08063 በ4/08/98 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፤ ሟች አደረጉት የተባለው ኑዛዜ የሕጉን መስፈርት ያሟላ በመሆኑ አመልካች የሟች የኑዛዜ ወራሽ ናቸው፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 35710

ታህሣሥ 16 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ እፀገነት እሸቱ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሰላማዊት ንጉሴ - ጠበቃ ይልማ ቻኔ - ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

መዝገቡ ለሰበር ችሎቱ ሊቀርብ የቻለው የአሁኗ አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት የሰበር ሠሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት የሠበር አቤቱታ በማቅረባቸው ነው፡፡

የአሁኗ ተጠሪ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሟች ዘነበ ንጉሴ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ንብረታቸውንና የሕፃን ናትናዔል ዘነበን አሣዳጊነትና ሞግዚትነት በተመለከተ ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ለአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዳኝነት ጠይቀው ይኸው ፍ/ቤትም የተጠሪን አቤቱታ በመቀበል ኑዛዜው የፀደቀ መሆኑን በመግለጽ ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላም የአሁኗ አመልካች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.358 መሠረት ባቀረቡት የተቃውሞ አቤቱታ ሟች ኑዛዜውን ያደረጉት በጋብቻ የጋራ ድርሻ ባለበት ንብረት መሆኑን፣ የሞግዚትነት ስልጣን ከእናት ለመውሰድም ሕጋዊ ክልከላ ያለ ስለመሆኑ፣ ኑዛዜው ግልጽነት የጎደላቸውን ቃላት የያዘ መሆኑን በመዘርዘር ሟች አደረጉ የተባለው ኑዛዜ የፀደቀው ያላግባብ በመሆኑ ሊሠረዝ ይገባዋል በማለት ዳኝነት ጠይቀው ተቃውሞ የቀረበለት ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ ኑዛዜው ከንብረት ክፍፍሉ በፊት በጋብቻ የጋራ ንብረት መደረጉን፣ የእናት ሞግዚትነትም ከሕግ የሚመነጭ ሆኖ እያለ አባት በኑዛዜ ለሕፃን አክስት እንዲሆን ማድረጋቸው ተገቢነት የሌለው መሆኑን፣ ኑዛዜው ግልጽ ያልሆነ አሻሚ ቃል ይዞ መገኘቱም ፈራሽ የሚያደርገው ስለመሆኑ የሚሉትን ነጥቦችን በምክንያትነት ጠቅሶ የአመልካችን ተቃውሞ በመቀበል ቀደም ሲል ኑዛዜውን በማጽደቅ የሰጠውን ውሣኔ ሠርዞታል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ ደረጃ የተመለከተው የከተማው ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ ጉዳዩ በሠበር የቀረበለት የከተማው አስተዳደር ፍ/ቤት ሠበር ሰሚ ችሎትም ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ መዝገቡን በመመርመር በርካታ ምክንያቶችን በፍርዱ ላይ በማስፈር የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ ከሻረ በኋላ ሟች ታኅሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ የአሁኗን ተጠሪንና ሕፃን ናትናኤል ዘነበን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የተውት በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት የሰበር አቤቱታ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም ተጠሪን ያስቀርባል ተብሎ ሠኔ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ መልሣቸውን ሲያቀርቡ አመልካች በበኩላቸው ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ በችሎት የቃል ጥያቄ ተደርጎላቸው መልስ ከሰጡ በኋላ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ በችሎት ቀርቦ ሐሣቡንና ፍላጎቱን እንዲሰጥ ተደርጎ ቃሉ ተመዝግቧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር፣ የሕፃን ናትናዔል ዘነበን አስተያየት የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የችሎቱን ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ነጥብ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሴ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ባደረጉት ግልጽ ኑዛዜ የተጠሪና የሕፃን ናትናኤል ዘነበን ጠቅላላ የኑዛዜ ወራሽ በማድረግ የተውት ኑዛዜ ፈራሽ አይደለም ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች አቶ ዘነበ ንጉሴ እና የአሁኗ አመልካች በጋብቻ ተሣስረው ሲኖሩ ቆይተው ጋብቻው በፍቺ ውሣኔ ታኅሣሥ 22 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ መፍረሱን፣ በዚህ ወቅትም ፍቺው በልጆች አስተዳደግና በንብረት ላይ የሚያስከትለውን ውጤት በተመለከተ ስምምነት እንዲያቀርቡ፣ መስማማት ካልተቻለ አንዳቸው አቤቱታ እንዲያቀርቡ ትእዛዝ ተሰጥቶ መብት ከተጠበቀ በኋላ የፍቺ ጥያቄ የተስተናገደበት መዝገብ መዘጋቱን ነው፡፡ ከዚህም በኋላ የንብረት ክርክር ተደርጎ የጋራ መሆናቸው የተረጋገጡን ዕቃዎች ግራ ቀኙ እንዲካፈሉ፣ በመኖሪያ ቤቱ ላይ የአሁኗ አመልካች ያላቸው ድርሻ 10,171.78/ አስር ሺህ አንድ መቶ ሰባ አንድ ብር ከሰባ ስምንት ሣንቲም/ መሆኑ ተረጋግጦ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሴ እንዲከፍሉ ተብሎ መጋቢት 21 ቀን 1997 ዓ.ም በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07941 ተወስኗል፡፡ ሌላው ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ሟች ኑዛዜ ያደረጉት ታኅሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ሆኖ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት ሚያዝያ 30 ቀን 1997 ዓ.ም መሆኑን፣ የአሁኗ አመልካች የሕፃን ናትናኤል ሞግዚትና አስተዳዳሪ እንዲሆኑ በፍ/ቤት የተወሰነው ግንቦት 27 ቀን 1997 መሆኑን የአሁኗ ተጠሪ ሟች ያደረጉትን ኑዛዜ በፍ/ቤት እንዲፀድቅ ግንቦት 15 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ አቅርበው ሐምሌ 07 ቀን 1997 ዓ.ም በፍ/ቤት ፀድቆ መወሰኑን፣ ይኸው ውሣኔ እንዲሠረዝ በአሁኗ አመልካች በኩል የተቃውሞ አቤቱታ የቀረበው ጥቅምት 04 ቀን 1998 ዓ.ም እና የአሁኗ አመልካች በመኖሪያ ቤቱ ላይ ያላቸው ድርሻ በውሣኔው መሠረት ያልተከፈላቸው መሆኑን ጭምር ነው፡፡

በሌላ በኩል የአዲስ አበባ ከተማነክ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ኑዛዜ በሕፃኑ ሞግዚትነትና አሣዳሪነት ላይ የተደረገ መሆኑ እየተገለፀለት የአሁኗን ተጠሪንና ሕፃን ናትናኤል ዘነበን የሟቹ ጠቅላላ ወራሾች የሚያደርገው ኑዛዜ ፈራሽ አይደለም በማለት የሞግዚትነትን ጉዳይ በተመለከተ ግልጽ ውሣኔ አለማስፈሩን ከውሣኔ አሰጣጡ ሂደት ተገንዝበናል፡፡

እንግዲህ በሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ኑዛዜ የተገለፀው የሕፃኑ ሞግዚትነትና ኑዛዜው በጠቅላላው የሟች ንብረት ላይ ያለውን ዋጋ ከሕጉ ጋር አገናዝቦ መመልከትን የግድ ይሏል፡፡ በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ነጥብ ለሕፃን ናትናኤል ዘነበ አክስቱ የሆነችው የአሁኗ ተጠሪ ሞግዚት እንዲሆኑ ሟች ዘነበ ንጉሴ በኑዛዜ መወሰናቸው ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?የሚለው ነው፡፡

እንደሚታወቀው ሕፃናት የተለየ ድጋፍና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው የህብረተሰብ አካል ናቸው፡፡ የዚህም መነሻ ሀሣብ ሕፃናቱ ከእድሜያቸው ለጋነት በተያያዘ ለአደጋ የተጋለጡ የሕብረተሰብ አካላት /vulnerable groups/ የመሆናቸው ጉዳይ ነው፡፡ ይህንኑ አደጋ ለመከላከል እና የተለየ ድጋፍና እንክብካቤ የማድረጉ ሥራ የተሣካ ይሆን ዘንድም የእነዚህን የህብረተሰብ ክፍሎች መብትና ደህንነት በሚመለከት የተለዩ ስምምነቶች በአለምና በአህጉር አቀፍ ደረጃ ተፈርሞ እየተገበሩ ይገኛሉ፡፡ ከስምምነቶቹ ውስጥም የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን እና የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ሐገራችን ኢትዮጵያ የሕፃናት መብቶች ኮንቬሽንን ህዳር 29 ቀን 1984 ዓ.ም፣ የአፍሪካ ሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተር ደግሞ እ.ኤ.አ ኦክቶበር 02 ቀን 2002 ዓ.ም አጽድቃለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሕፃናትን መብትንና ደህንነት በሚመለከት የፌዴራሉ ሕገ-መንግሥት፣ የክልል ሕግጋተ- መንግሥታት እና ሌሎች ሕጎች አሉ፡፡ በዓለም አቀፍ በአህጉርና በአገር ደረጃ ሕፃናትን አስመልክቶ በስራ ላይ ያሉ እነዚህ ሕጎች ደግሞ መሠረታዊ መርሆዎችን የያዙ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ በሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን መሠረታዊ ከሆኑት መርሆዎች ውስጥ አንዱ ሕፃናትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ለሕፃናት ጥቅምና ደህንነነት /the best interest of the child/ ቅድሚያ መስጠት የሚለው ስለመሆኑ የአንቀጽ 3.1 ድንጋጌ ሲያሣይ የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርም በአንቀጽ 4.1 ድንጋጌ ስር ይህንኑ አካትቶ ይዟል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥትም ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸውን የዓለም አቀፍ ስምምነቶችን የአገሪቱ የሕግ አካል መሆናቸውን በአንቀጽ 9/4/ ስር ከመደንገጉና በሕገ-መንግሥቱ በስፋት ሽፋን የተሰጣቸው መሠረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ሀገሪቱ ከተቀበለቻቸውና ዓለም አቀፍ የሠብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ ስምምነቶች ወይም ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ መተርጎም የግድ ስለመሆኑ በአንቀጽ 13/2/ ከማስቀመጡም በተጨማሪ

የሕፃናትን ልዩ ችግር ከግምት ያስገቡ የተለያዩ ንዑስ ድንጋጌዎችን የያዘ ድንጋጌ በአንቀጽ 36 አስፍሯል፡፡ በተለይም የአንቀፁ ንዑስ አንቀጽ ሁለት ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ ሁሉ የመንግሥታዊ ወይም የበጎ አድራጎት ተቋማት እንዲሁም ፍ/ቤቶችና የአስተዳደር ባለስልጣናት ወይም የሕግ አውጪው አካላት የሕፃናትን ደህንነት በቀድሞ ትጋት ሊያስቡበት የሚገባ ስለመሆኑ አጽንኦት ባለው መንፈስ፤ በአስገዳጅነት ደንግጓል፡፡ ሕገ-መንግሥቱንም ተከትለው የወጡ ፖሊሲዎችና ሕጎዎች አቀራረጽ ይዘትና መንፈስ ሲታይም የሕፃናትን መብትና ደህንነት የማስከበር ዓላማ ግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆኑን ለመገንዘብ አያዳግትም፡፡

የሕፃናትን ጥቅምንና ደህንነት ቀደምትነት ከሚለው መርህ በተጨማሪ በዓለም አቀፍና በአህጉራዊ ሠነዶችና ስምምነቶች ውስጥ ልዩ ትኩረት የተሰጠው ሌላው መሠረታዊ መርህ የሕፃናት ተሣትፎ መርህ ነው፡፡ የዚህ መርህ ዓይነተኛ ይዘት በዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን በአንቀጽ 12 የተመለከተ ሲሆን የአፍሪካ የሕፃናት መብቶችና ደህንነት ቻርተርም በአንቀጽ 4.2 ስር በግልጽ ሠፍሯል፡፡ አጠቃላይ የዚህ መብት አድማስ ሲታይም ሕፃናት ህይወታቸውን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በውሣኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ተሣትፎ ማድረግ እንደሚችሉ፣ በተጨማሪም ጥቅማቸውን በሚመለከቱ ውሣኔዎች ላይ የራሣቸውን ተጽእኖ የማሣረፍ መብት ያላቸው መሆኑ፣ይህም ስፋት ባላቸው የፍርድ ጉዳዮች እንዲሁም መደበኛ የውሣኔ አሰጣጥ በሚመለከቱ በጤና፣ በትምህርትና በአከባቢ ጉዳዮች ሁሉ ሊካተት የሚገባ ስለመሆኑ ተጠቃሽ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ ድንጋጌዎቹ ሕፃናት በጉዲፍቻ ወቅት፣ በወላጆች መለያየትና ፍቺን ተከትሎ የትኛው ወላጅ ጋር ማደግ እንደአለባቸው ውሣኔ ሲሰጥ እና በመሣሠሉት ጉዳዮች ላይ አስተያየት መስጠትና ሊደመጡ እንደሚገባ እንዲሁም አስተያየታቸው ከመደመጡ ባሻገር ተገቢው አፅንኦት ሊሰጠው የሚገባ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ የሕፃናቱ ሀሣብና አስተያየት ተገቢውን አፅንኦት የሚያገኘውም የሕፃኑን እድሜንና የአስተሣሠቡን የብስለት ደረጃ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት መሆኑንም የሚያጠያይቅ አይሆንም፡፡

እንግዲህ ሕፃንን የሚመለከት አንድ ጉዳይ ሲወሰን ሊታሰብባቸው የሚገባቸውን የተወሰኑ መሠረታዊ መርሆዎችን የሕግ ማቀፋቸውንና የድንጋጌዎችን ዝርዝር ይዘትና መንፈስ ምን እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል፡፡ እጃችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም የተሻሻለው የፌዴራሉ የቤተሰብ ሕግ አካለ መጠን ያልደረሰን ልጅ የሚጠብቁትን ተቋሚትንና ቅደም ተከተሉን ከአንቀጽ 219-238 ድረስ ባሉት ድንጋጌዎች አስቀምጧል፡፡ በድንጋጌዎቹ መሠረት ወላጆች ከሌላው ሰው በቅድሚያ የአስተዳዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ያላቸው መሆኑ፣ አሣዳሪ ወይም ሞግዚት በልጁ ወላጅ በኑዛዜ ቃል የሚመረጥ መሆኑ፣ ይህም በፍ/ቤት ሊሻር ወይም ሊሻሻል የሚችል መሆኑ፣ ወላጆች ወይም የወላጅ ኑዛዜ ከሌለ ሦስተኛው መንገድ ከዘመዶቹ መካከል በዝምድና ቅደም ተከተል የአሣዳሪነትና የሞግዚትነት ሥልጣን ሊሰጥ እንደሚገባ፣ በመጨረሻም በሕግ የሚመረጡ ዘመዶች ከሌሉ ይኸው ሥልጣን በፍ/ቤቱ በሚመረጥ ሰው ሊሰጥ የሚችል ስለመሆኑ ተገልጿል፡፡ ሆኖም የእነዚህ ድንጋጌዎች ቅደም ተከተል ተግባራዊ ሲደረግ ሁልጊዜ ግንዛቤ ውስጥ መግባት ያለበት ቁልፉ ነጥብ በሕገ-መንግሥቱ የተመለከተው የሕፃኑ ደህንነት መብት ቀደምትነት ስለመሆኑ ሊረሣ የማይገባው ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ የተመለከቱት ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎችም ሆነ በአንቀጽ 113/2/ ስር የተመለከተው ድንጋጌ አቀራረፅ፣ ይዘትና መንፈስ ሲታይ ፍ/ቤቶች አካለመጠን ያልደረሰን ልጅ አሣዳሪነትና ሞግዚትነት በተመለከተ ውሣኔ ሲሰጡ በሕጉ የተሰጣቸውን ሠፊ ሥልጣን መጠቀም ያለባቸው መሆኑንና የሕፃናትን መብትና ጥቅም የማስከበር ኃላፊነታቸውን መወጣት ግዴታ ያለባቸው መሆኑን ያስረዳል፡፡ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 13/1/ ስር የተመለከተው ድንጋጌም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው፡፡ የሕፃናትን ደህንነትና ጥቅም ለማስጠበቅ የሚችል ውሣኔ ይሰጥ ዘንድ ደግሞ የሕፃናቱ ሀሣብ ሊደመጥና ተገቢው ክብደት ሊሰጠው የሚገባ ነው ይህንኑ የሚቃረኑ ልማዳዊ አሠራሮችን ተቀባይነት የሌላቸው ስለመሆኑ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 9/1/ ድንጋጌ በግልጽ ያሣያል፡፡

በዚህም መሠረት የዚህ መዝገብ ጉዳይ ሲታይ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ አስተዳዳሪነትና ሞግዚትነትን በተመለከተ የሟቹ ኑዛዜ የሕፃኑን ደህንነትና ጥቅም ቀደምትነት መርህ ለማስከበር እና ተግባራዊ ለማድግ በሚያስችል መልክ የተከናወነ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ በዚህ ችሎት ሲደመጥም ከአክስቱ ጋር የመኖር ፍላጎት የሌለው መሆኑንና ከወላጅ እናቱ ተገቢው እንክብካቤ እየተደረገለት በማደግ ላይ ያለ ስለመሆኑ አስተያየት ሰጥቷል፡፡ ሕፃኑ ከአባቱ ሞት በኋላ በአክስቱ በኩል ተገቢው ክትትልና እንክብካቤ ያልተደረገለት ስለመሆኑም አረጋግጧል፡፡ የሕፃኑ እድሜ ሲታይም አስር መሆኑንና አስተሣሰቡም የበሰለ ሊባል የሚችል መሆኑ ይህ ችሎት የተገነዘበው ሲሆን ይህም ለአስተያየቱ ተገቢው ክብደት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ

ምክንያቶች መሠረት ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ስለሕፃን ናትናኤል ሞግዚትነት የተውት ኑዛዜ ፈራሽ የማይሆንበት ሕጋዊ ምክንያት ስለሌለ በዚህ ረገድ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሌላው በሟቹ ኑዛዜ የተገለፀው ነገር የሟቹን ንብረት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን በዚህ ረገድ የተሰጠውን ውሣኔ አግባብነትን ከሕጉ ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡ በዚህ እረገድ የሟቹ ኑዛዜ ሠነድ ይዘት ሲታይ ፡-

> "... በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 19 ቀበሌ 55 የቤት ቁጥር 1654 የሆነውን መኖሪያ ቤቴን ግቢ ውስጥ ያሉትን ቤቶችንና መኖሪያ ቤት ውስጥ ያለውን ንብረቴን በስሜ በባንክ ያለውን ገንዘብ ሁለት እጁን ለእህቴ ለወ/ሮ ሠላማዊት ንጉሤ ኪዳኔ በራሤ ፈቃድ ተናዝዣለሁ፣አንድ እጁን ለልጄ ለአምስት ዓመቱ ለናትናኤል ዘነበ ንጉሤ አውርሻለሁ፣ የኑዛዜ ተቀባይዋ እህቴ ወ/ሮ ሰላማዊት ንጉሤ ኪዳኔ ከላይ ስሙ የተጠቀሰውን ልጄን አቅመ አዳም እስኪደርስና እራሱን እስኪችል ድረስ በኑዛዜ የተናዘዝኩትን ንብረቴን አንድ እጁን ተንከባክባ እየጠበቀች የቤቱንም ኪራይ እየተቀበለች አስቀምጣ እራሱን ሲችል እንድታስረክበው የእሷን ድርሻ ሁለት እጁን ለራሷ እንድትጠቀምበት ላደረገችልኝ ውለታ መክፈያ መናዘዜንና ልጄን ተንከባክባ እንድታሣድግልኝ ይህንን ኑዛዜ አድርጌአለሁ ..."

የሚል እና በአራት ምስክሮች ፊት የተደረገ ግልጽ ኑዛዜ ነው፡፡

ሟች ለተጠሪ ያደረጉት ኑዛዜ ተጠሪን የሟች ንብረቶች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደረገው በአንድ በኩል ለሕፃኑ ለሚያበረክቱት መልካም አስተዳደግ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለሕፃኑ ከሚያደርጉት መልካም አስተዳደግ በተጨማሪ ለሟቹ ላደረጉት ውለታ ስለመሆኑ የሚጠቅስ ይመስላል፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው የሕፃኑ ሞግዚትነትና አስተዳዳሪነት በኑዛዜው መሠረት አይገባሽም ከተባልኩ ንብረቱን በተመለከተ ሟች 2/3ኛው ይሠጣት በማለት የተናዘዙት የሚፈርስበት የሕግ ምክንያት የለም በማለት ተከራክረዋል፡፡ ይሁን እንጂ የሟች ኑዛዜ አጠቃላይ ይዘቱና መንፈሱ በውል ሲታይ ተጠሪ የሟች ንብረት የኑዛዜ ተጠቃሚ የሚሆኑት ሕፃን ናትናኤልን ተንከባክበው ሲያሣድጉ መሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ተጠሪ ሕፃኑን ሲያሣድጉ አስፈላጊውን ወጪ የሚያደርጉበት ለራሣቸው ድርሻ ይሆናል ከተባለው ስለመሆኑም የኑዛዜው ይዘት ያሣያል፡፡ ምክንያቱም ሟች ለሕፃኑ ከተውት1/3ኛ ድርሻ ተጠሪ ተንከባክበው እንዲጠብቁ፣ የቤት ኪራዩን እየተቀበሉ እንዲያስቀምጡና ለአካለመጠን ሲደርስና ራሱን ሲችል እንዲያስረክቡ በኑዛዜው ላይ በግልጽ መቀመጡ ለሕፃኑ እንክብካቤና አስተዳደግ ወጪ የሚደረገው ከተጠሪ ድርሻ መሆኑን የሚያሣይ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ታህሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ገደብ ያለበት ኑዛዜ /Conditional legacy/ ስለመሆኑ መገንዘብ አያዳግትም፡፡ የኑዛዜ ስጦታ ጠቅላላ ወይም ልዩ ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 912 ስር የተመለከተ ሲሆን እንደዚህ ዓይነት የኑዛዜ ስጦታዎች አንድ ሁኔታ ሲደርስ የሚፀኑ ወይም የሚቀሩ ሆነው ሊደረጉ የሚችሉ ስለመሆኑም የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 916 ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ሕፃን ናትናኤልን ተንከባክበው ያሣደጉት ሁኔታ የለም፡፡ ተጠሪ ሕፃኑን ከራሣቸው የኑዛዜ ድርሻ ወጪ በማድረግ ተንከባክበው የማሣደግ ሁኔታ ካልተረጋገጠ ደግሞ ተጠሪ የንብረቱ በኑዛዜ ተጠቃሚነት የፀና ሊሆን አይችልም፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የኑዛዜው ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሕጋዊ ምክን ያት ሣይኖር የኑዛዜ ጠቅላላ ወራሽ ናቸው ተብሎ መወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ማንኛውም የሚንቀሣቀስም ሆነ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሕጋዊ መብት የሚተላለፈው ለሕፃን ናትናኤል ዘነበ ሆኖ የሕፃኑ ሞግዚትና አስተዳዳሪ አመልካች ሆነው ሊያስተዳድሩት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አመልካች የሕፃኑን የማይንቀሣቀስ ሀብት መልካም አስተዳደር በሚመለከት የሞግዚትነት ሥልጣን እንዲኖራቸውም መወሰን አለበት ብንልም ሕፃኑ ከሟቹ አባቱ የሚተላለፍለትን ሀብት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የአመልካችን ችሎታ፣የክርክሩን አጠቃላይ ይዘትንና የልጁን ጥቅም በማመዛዘን ስለሀብቱ አስተዳደር አመልካች የሚኖራቸውን ሥልጣን ከወዲህ መግለጽ ጠቃሚ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በተመለከቱት ሕጋዊ ምክንያቶች የሚከተለውን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 04273 ጥር 02 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ/ 1120/98 ሚያዝያ 24 ቀን 1998 ዓ.ም፣ በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ደግሞ በመ/ቁ/ 03383 መጋቢት 27 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጡት ውሣኔዎች በውጤት ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

3/ ሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ታኅሣሥ 23 ቀን 1996 ዓ.ም ያአደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው ብለናል፡፡

4/ ተጠሪ ከሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ንብረት በኑዛዜው ተጠቃሚ የሚሆኑበት አግባብ የለም ብለናል፡፡

5/ የሟች አቶ ዘነበ ንጉሤ ሕጋዊ ወራሽ ሕፃን ናትናኤል ዘነበ ነው ብለናል፡፡

6/ የሕፃን ናትናኤል ዘነበ አስተዳዳሪና ሞግዚት አመልካች ናቸው ብለናል፡፡

7/ አመልካች በሞግዚትነት ሥልጣናቸው ሕፃኑ ከአባቱ በውርስ ሊያገኝ የሚገባውን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሕፃኑ እድሜ አካለመጠን /18 ዓመት/ እስከሚደርስ ድረስ በማናቸውም መንገድ ለ3ኛ ወገን የማስተላለፍ መብት የተገደበ ሆኖ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ግን በፍ/ቤት ፈቃድ ተገቢውን መፈፀም ይችላሉ ብለናል፡፡

8/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37562

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሣሙኤል ፈረንጅ - ጠበቃ አበበ ታዬ ቀርበዋል

**ተጠሪዎች፡-** 1/ አቶ ግርማ ታፈሰ - ጠበቃ አብርሃም አሰፋ ቀርበዋል፡፡

2/ ወ/ሮ አሰገደች በቀለ - ጠበቃ አብርሃም አሰፋ ቀርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለዚህ የሰበር ክርክር መነሻው አመልካች ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ.33004/ የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 ይዘት ከምስክሮች አንዱ ዳኛ ወይም ውል ለማዋዋል ሥልጣን የተሰጠው ሰው ሲባል በስጦታው /ኑዛዜው ፎርም ውስጥ የተመዘገበ ምስክር ከሆነ እንጂ ኑዛዜው ወይም ስጦታው በአዋዋዩ ወይም በዳኛው ፊት መከናወኑ ብቻ የምስክሮቹን ብዛት በተለየ ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881/2 ከሚፈለጉት 4 ምስክሮች ወደ ሁለት ዝቅ ማድረግ አይቻልም በማለት የያዘው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ፍርዱ እንዲታረምላቸው ስለጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ የጀመው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች አመልካቾች፣ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተጠሪ የነበሩ ሲሆን፤ አመልካቾቹ ጥር 06/1988 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው የሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ ወራሾች መሆናቸውን በመግለጽ በወረዳ 09/ቀበሌ 06 ክልል የሚገኘው የቤት ቁጥር 579 የሆነውና በቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቁሣቁሶች እንዲሁም ግሮሰሪ የሟች አውራሻቸው ንብረቶች መሆናቸውን በመግለጽ የውርስ አጣሪ እንዲሾምላቸው የጠየቁ ሲሆን በስር ፍ/ቤቱ ተጠሪ የነበሩ የአሁኑ አመልካችም መጋቢት 05/1988 ዓ.ም በተፃፈ መልሣቸው አመልካቾቹ ያቀረቡት ጥያቄ ሐቅነት እንደሌለው በመግለፃቸው ፍ/ቤቱም የውርስ አጣሪ ሾሟል፣ ውርስ አጣሪውም ሚያዚያ 20 ቀን 1997 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ለፍ/ቤቱ ያቀረበ ሲሆን ይዘቱም አከራካሪው ቤት ተጠሪው ከሟች በስጦታ የተላለፈላቸው እንደሆነና ይህንንም የስር አመልካቾቹ እንደማይቀበሉት የሚገልፀው መሠረታዊ ነጥብ ሲሆን የስር ፍ/ቤቱም ቤቱ ለተጠሪው በሥጦታ እንደተላለፈላቸው በማረጋገጥ አመልካቾቹ በዚሁ ተቃውሞ ካላቸው የስጦታ ይፍረስልኝ ጥያቄ ከሚያቀርቡ በስተቀር ጥያቄያቸው ተቀባይነት እንደሌለው ወስኗል፡፡

አመልካቾቹም የስር ፍ/ቤቱ በኮ/ቁ. 22789፣ ጥር 12 ቀን 1998 ዓ.ም ከላይ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የግራና ቀኙን ክርክር ካኪያሄደ በኋላ በኮ/መ/ቁ. 45348፣ ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ይግባኝ ባዮቹ በተለየ መዝገብ የስጦታው ይፍረስልን ጥያቄ ማቅረብ ሣያስፈልጋቸው በውርስ አጣሪው በተደረገው የማጣራት ስራ የስጦታው ሕጋዊ ያለመሆን ክርክር ከማቅረብ የሚከለከሉበት ምክንያት እንደሌለ ካሰፈረ በኋላ አከራካሪው ስጦታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881 እና 882 እንደተገለፀው በአራት ምስክሮች ፊት ያልተደረገ እንደሆነና መጋቢት 18 ቀን 1987 ዓ.ም ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ ለመልስ ሰጭው አደረጉት በተባለው ስጦታ የሰፈሩት ሁለት ምስክሮች እንጂ በሕጉ መሠረት አራት እንዳልሆኑ፣ ስጦታው በአዋዋይ ፊት መከናወኑ

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 እንደተጠቀሰው የምስክሮቹ ብዛት ወደ ሁለት አያስቀንሰውም፤ በዚሁ ዓንቀጽ መሠረት ምስክሮቹ ሁለት ሰዎች ብቻ በቂ የሚሆኑት ከምስክሮቹ አንዱ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ዳኛ ሆነው መደበኛ ሥራቸውን እያከናወኑ በነበሩበት ሲሆን ነው፤ በዚህ የስጦታ ጽሁፍ ግን ምንም እንኳ ስጦታው የተደረገው በአዋዋይ ፊት ቢሆንም ከሁለቱ ምስክሮች አንዱ ራሱ አዋዋዩ ባለመሆኑና በሕግ የሰፈረውን አባባል ስለማያሟሉ ተደረገ የተባለው ስጦታ ተቀባይነት የለውም፤ ይግባኝ ባዮቹ በቤቱ ላይ ድርሻ አላቸው በማለት የስር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሽሮታል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎትም ከላይ የሰፈረውን የከፍተኛ ፍ/ቤቱ አተረጓጎም ተቀባይነት ያለው መሆኑና የአሁኑ አመልካች ያቀረቡለትን ይግባኝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 337 ተቀባይነት እንደሌለው በፍ/ይ/መ/ቁ. 33004 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ አረጋግጧል፡፡

አመልካቹም ግንቦት 04 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታቸው´አከራካሪው ቤት ከወ/ሮ ጥሩነሽ አበበ በስጦታ እንደተላለፈላቸውና የስጦታ ውሉም በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ቀርቦ በቁጥር 167/87 በ26/07/1987 ዓ.ም ተመዝግቦ ከ12 ዓመታት በላይ በይዞታዬ ስር ሆኖ እያለና የስር ፍ/ቤቱ ስጦታው በአግባቡ የተከናወነ ነው ብሎ እያለ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሉ በውልና ማስረጃ ፊት ቢፈፀምም በጽሁፉ ውስጥ አራት ምስክሮች አልተጠቀሱም አዋዋዩ ራሱ በውሉ ውስጥ በምስክርነት እስካልተጠቀሰ ድረስ ሁለቱ ምስክሮች በቂ አይደሉም በማለት የስጦታ ውሉን ማፍረሱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነውና ውሣኔው ይሻርልኝ ብለዋል፡፡

ተጠሪዎቹም ጥቅምት 11/2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በስጦታ ውሉ የተጠቀሱት ሁለት ተራ ሰዎች እንጂ አንዳቸውም አዋዋይ ባለመሆናቸው በሕጉ የተቀመጠው የአራት ምስክሮች መሟላት በሌለበት ሁኔታ ስጦታው ሕጋዊ ሊሆን አይችልም፤ ስለሆነም የከፍተኛው ፍ/ቤት እና የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔዎች ተገቢውን አተረጓጎም የተከተሉ በመሆናቸው ሊፀድቁ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም የግራ ቀኙ ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ መጋቢት 18 ቀን 1987 ዓ.ም ለአመልካች ያደረጉት ስጦታ ተገቢውን ፎርማሊቲ ያሟላ ነው ወይስ አያሟላም? የሚለውን መሰረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ባቀረቡት ጥያቄ በቀድሞ ወረዳ 09፣ ቀበሌ 06 የሚገኘው ቁጥሩ 579 የሆነውን ቤት የአውራሻቸው ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ እንደሆኑ በመግለጽ በውርስ አጣሪ ተጣርቶ ድርሻቸውን እንዲከፈላቸው ሲጠይቁ የአሁኑ አመልካች ደግሞ ከላይ የተጠቀሰው ቤት ሟች ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ቀርበው የሰጧቸው እንደሆነና የውርስ መጣራቱ አካል ሊሆን እንደማይገባው የሚጠቁም መልስ ሰጥተዋል፡፡ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱ የተሾመው ውርስ አጣሪ አካል ባደረገው ማጣራት አከራካሪው ቤት ለአመልካቹ በስጦታ የተላለፈ እንደሆነና በውርስ ክፍፍሉ መካተት የለበትም የሚል የውሣኔ ሃሣብ ያቀረበ ሲሆን የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤቱም ይህንን የማጣራት ውጤት ተቀብሎ አጽድቆታል፡፡ በአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ የስጦታው ሕጋዊነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881/2/ እና 882 አኳያ ከሚፈለገው ፎርማሊቲ አንፃር ጉዳዩን በማጤን ምንም እንኳ ስጦታው በውልና ማስረጃ ጽ/ቤት የተከናወነ ቢሆንም ውል አዋዋዩ በስጦታው ጽሁፍ እንደ አንድ ምስክር ሆኖ እስካልተጠቀሰ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 የተጠቀሰው የሁለት ምስክሮች ልዩ ሁኔታ ተሟልቷል ሊባል አይችልም፤ በፍ/ብ/ህ/ቁ.881/2/ በተጠቀሰው መሠረት በስጦታ ውሉ አራት ምስክሮች መጠቀስ ሲገባቸው ሁለት ምስክሮች ብቻ መዘርዘራቸው በቂ ባለመሆኑ ስጦታው በሕግ አስገዳጅነት ያለውን ፎርማሊቲ አላሟላም በማለት ተቀባይነት የለውም ብሏል፤ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎትም የከፍተኛውን ፍርድ ቤት አተረጓጎም በመቀበል አመልካቹ ያቀረበለትን ይግባኝ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 አተረጓጎም በሚመለከት ይህ የሰበር ችሎት ካሁን በፊት በሰ/መ/ቁ. 36777 ጥቅምት 25/2001 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ትርጉም የሰጠበት ጉዳይ ሲሆን ይኸውም የኑዛዜ ወይም የስጦታ ውል የተፈፀመው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ፊት ከሆነ አዋዋዩ በኑዛዜው ወይም በስጦታ ውሉ ውስጥ እንደ ምስክር ሆኖ ባይፃፍም ምስክር አይደለም ተብሎ ሊተረጎም እንደማይገባ ነው፤ የኑዛዜው ወይም የስጦታው ሂደት ያለምንም ተጽእኖ በነፃነት እንዲከናወን በማድረግ የምዝገባውን ሂደት የመራ እስከሆነ ድረስ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 መሠረት ኑዛዜው ወይም ስጦታው ተቀባይነት እንዲኖረው ሁለት ምስክሮች በቂ ናቸው፤ በተያዘው ጉዳይም ወ/ሮ ጥሩነሽ ቦጋለ አከራካሪውን ቤት በውልና ማስረጃ ጽህፈት ቤት ማለትም ስራውን በማከናወን በነበረ አዋዋይ

ፊት ቀርበው ለአመልካች መስጠታቸውን ሁሉም የስር ፍርድ ቤቶች ያረጋገጡት ነው፤ ስለሆነም አዋዋዩ በስጦታው ሰነድ ስሙ በምስክርነት ባይፃፍም የስጦታ ሂደቱ ሲከናወን የነበረ ምስክር ነው፡፡ በመሆኑም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ሆነ ጠቅላይ ፍ/ቤቱ የስጦታ ውሉ አራት ምስክሮች ያልፈረሙበት ወይም ደግሞ ከምስክሮቹ አንዱ ውል ለማዋዋል ስልጣን የተሰጠው ሰው ወይም ዳኛ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 45348፣ ሐምሌ 17 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

2/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ችሎት በፍ/ይ/መ/ቁ 33004 የካቲት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ ተሽሯል፤ ይፃፍ፡፡

3/ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በኮ.መ.ቁ. 22789፣ ጥር 12 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ 348/1/ መሠረት ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

4/ አከራካሪው የስጦታ ውል ስራውን ሲያከናውን በነበረ ውል አዋዋይ ፊት በመቅረብ የተከናወነ በመሆኑ ምንም እንኳ አዋዋዩ በስጦታ ውሉ ውስጥ በምስክርነት ባይጠቀስም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 882 በተጠቀሰው መንገድ እንደ ምስክር ስለሚቆጠር ስጦታው ተገቢውን የምስክሮች ብዛት /ፎርማሊቲ/ ያሟላ ነው ብለናል፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወገኖች ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 41896

የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ታደለች ዋለልኝ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ሮ አዲስ አለም ፀጋው በሌሉበት

2. ወ/ሮ ማስተዋል አስማረ አልቀረቡም

3. አቶ እሸቴ ዓለምገና አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሰረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን በአሁን አንደኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል የነበረውን የጋብቻ ክርክር ፍ/ቤቱ ተመልክቶ በአዲስ አበባ ከተማ በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 01/05 ክልል የሚገኝ ቁጥር 242 የሆነው ቤት የሁለቱ የጋራ ሐብት ነው በማለት ውሳኔ ከሰጠ በኋላ ይህ ውሳኔ መብቴን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው መዝገቡ ከተከፈተ በኋላ የአሁን አመልካችም በበኩላቸው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 41 መሰረት መቃወሚያ አቅርበው ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ/ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ጋር በትዳር እያለን በጋራ ያፈራነው መኖሪያ ቤት የመቃወም ተጠሪዎች ነው ተብሎ መወሰኑ መብቴን ስለነካ ይህ ውሳኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ጣልቃ ገብ ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር ጋብቻ የፈጸሙት በ26/3/2000 ዓ.ም እንደሆነ በማስረጃነት ያቀረቡት የጋብቻ የምስክር ወረቀት የሚገልጽ ሲሆን ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የመቃወም ተጠሪዎች የጋራ ሐብት ነው ተብሎ የተወሰነው ደግሞ ጣልቃገብና ሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት በ29/10/99 ዓ.ም ስለሆነ ጣልቃገብ ከሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ ጋር ጋብቻ ከመፈጸማቸው በፊት የመቃወም ተጠሪዎች የጋራ ሐብት ነው ተብሎ በዚህ ፍ/ቤት ውሳኔ የተሰጠበት ንብረት የጣልቃገብ እና የሁለተኛ የመቃወም ተጠሪ የጋራ ሐብት የሚሆንበት የሕግ አግባብ የለውም፡፡ በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

አመልካች በዚሁ ውሳኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሰረት ይግባኙን ሰርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ከሦስተኛ ተጠሪ ጋር በባህል የተጋባነው በ1992 ዓ.ም ነው እያሉ የስር ፍ/ቤት ክርክር የተነሳበት ንብረት የተፈራው

አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት ነው በማለት የአመልካችን አቤቱታ ሳይቀበል መቅረቱ ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን ጠርቷል፡፡

ይሁንና አንደኛ ተጠሪ የፍ/ቤቱን መጥሪያ አልቀበልም ስለማለታቸው በአመልካች ቃለ መሐላ በመረጋገጡ ሁለተኛ ተጠሪም በምትክ መጥሪያ ተጠርተው ባለመቅረባቸው ክርክሩ በሌሉበት እንዲታይ ትእዛዝ የተሰጠ ሲሆን ሦስተኛ ተጠሪ ቀርበው ከአመልካች ጋር በባህል የተጋቡት በ1992 ዓ.ም እንደሆነ ገልጸው በአቤቱታው መሰረት ቢወሰን ተቃውሞ የለኝም ብለዋል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

እንደመረመርነውም አመልካች ከሦስተኛ ተጠሪ ጋር በ1992 ዓ.ም በባህል መጋባታቸውን የሚያረጋግጥ ሰነድ በአስረጅነት ለስር ፍ/ቤት ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡ የስር ፍ/ቤት አቤቱታቸውን ሳይቀበለው የቀረው ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ክርክር የተነሳበት ንብረት የተፈራው አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ ከመጋባታቸው በፊት ስለሆነ በንብረቱ ላይ መብት የላቸውም በማለት ነው፡፡ ለዚህም ውሳኔ መሰረት ያደረገው አመልካችና ሦስተኛ ተጠሪ የፈጸሙት ጋብቻ በ26/3/2000 ዓ.ም በክብር መዝገብ ሹም የተመዘገበ መሆኑን የሚያረጋግጠውን የጋብቻ የምስክር ወረቀት በመመልከት ነው፡፡

በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 28/1/ ላይ ጋብቻው የተፈጸመው በማንኛውም የጋብቻ አፈጻጸም ስርአት ቢሆንም አግባብ ባለው የክብር ሹም መመዝገብ እንዳለበት የተደነገገ ሲሆን ጋብቻው ሕጋዊ ውጤት የሚኖረው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ሳይሆን ጋብቻው ከተፈጸመበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ በዚህ አንቀጽ 28/3/ ላይ ተመልክቷል፡፡

በአመልካችና በሦስተኛ ተጠሪ መካከል የተፈጸመው ጋብቻ ተመዝገበው በ26/3/2000 ዓ.ም ቢሆንም ከዚህ ቀን በፊት ጋብቻው የተፈጸመ መሆኑ ከተረጋገጠ ሕጋዊ ውጤት ሊኖረው ስለሚችል በዚሁ መሰረት ላይ ግራ ቀኙን አከራክሮ ውሳኔ መስጠት ሲገባው ጋብቻው የተመዘገበበትን ቀን መሰረት በማድረግ ከዚህ በፊት ጋብቻ ስለሌለ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት የደረሰበት ድምዳሜ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም ይህንኑ ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19258 በ7/1/2001 ዓ.ም የሰጠው ከፊል ውሳኔና የፌደራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 73407 በ23/3/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካችና በሦስተኛ ተጠሪ መካከል የባህል ጋብቻ መፈጸሙን በማጣራት ክርክር በተነሳበት ንብረት ላይ እንዲወሰን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 343/1/ መሰረት ጉዳዩ ተመልሶለታል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38691

የካቲት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ለገሰ ቢራቱ - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ደረጀ ጅማ ገርግሶ - ቀረቡ፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ጉዳዩ የጀመረው በሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪ አባት አቶ ጅማ ጌርጎሶ አመልካች ላይ በነበረባቸው እዳ ምክንያት እሣቸው በመሞታቸው ተጠሪን ጨምሮ በሚች ባለቤትና ወራሾች ላይ ክስ ተመስርቶ ተፈርዶባቸዋል፡፡ ይህንንም ፍርድ ለማስፈፀም አመልካች በባለእዳዎቹ ላይ የአፈፃፀም ክስ አቅርበዋል፡፡ ለውሣኔው ማስፈጸሚያም እንዲሆን አሁን ክርክር የተነሣበት ቤት በ25/04/98 በተደረገ ጨረታ በብር 38,200 (ሰላሣ ስምንት ሺህ ሁለት መቶ ብር) አሸናፊ የተገኘ ቢሆንም አሸናፊው ገንዘቡን ባለመክፈላቸው አመልካች ቤቱ በድጋሚ ጨረታ እንዲሸጥ አመልክተዋል፡፡ በዚህን ጊዜ የአሁኑ ተጠሪ በ28/04/98 በተፃፈ አቤቱታ በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የግል ቤታቸው በመሆኑ ጨረታው እንዲቆም ሲሉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ አቅርበዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የተጠሪን ጥያቄ መርምሮ ተጠሪ አቤቱታውን ያቀረቡት ቤቱ በጨረታ በ25/04/98 ተሸጦ በ03/05/98 ስለሆነና የዘገዩበትን ምክንያትም ስላልገለፁ እንዲሁም የባለንብረትነት ማስረጃም ስላላቀረቡ አቤቱታው ተቀባይነት የለውም በማለት ጥያቄውን ውድቅ አድርጐታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ መርምሮ ቤቱ በሐራጅ እንዲሸጥ ጥያቄ ያቀረቡት አመልካች በመሆናቸው ቤቱ የተጠሪ አባት መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ያለባቸው አመልካች ናቸው፤ነገር ግን ቤቱ የተጠሪ አባት መሆኑን አላረጋገጡም፣ተጠሪም የወራሽነት መብታቸውን ተጠቅመው አባታቸውን የወረሱ ለመሆኑም አልተረጋገጠም፣ተጠሪ የግብር ደረሰኝና የቀበሌ ማ/ፍ/ቤት ውሣኔ በማስረጃነት አቅረበዋል በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

አመልካች በተራቸው በዚህ ውሣኔ ላይ አቤቱታ ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅረበዋል፡፡ ችሎቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፣ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት መቃወሚያ ያቀረቡት የመጀመሪያው ጨረታ ከመደረጉ በፊት ነው፣በመሆኑም አቤቱታቸው ሊስተናገድ ይገባል፣ክርክር የተነሣበት ቤት የተጠሪ አባት ቤት ለመሆኑ ተገቢው ማስረጃ ቀርቦ በአግባቡ ተጣርቷል ወይ? የሚለው ከመታየቱ በፊት ግን ዋናው ውሣኔ የተሰጠው በአቶ ጅማ ጊርጐሶ ወራሾች ላይ በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚገባው በወራሾች ንብረት ላይ ነው፡፡ የሚች ንብረት ለወራሾች ከተላለፈ የሚች ንብረት ተብሎ ሊቀርብ የሚችል የለም፡፡ አመልካችም በተጠሪ ንብረት ላይ አፈፃፀሙ እንዲቀጥል ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ የቀረበው ክርክር ከሚች ንብረት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በሚች ንብረት ደግሞ አፈፃፀም ሊቀጥል

ስለማይችል የአመልካች ክርክር ተቀባይነት የለውም በሌላ በኩል ግን ተጠሪ የሟች ወራሽ ለመሆናቸው አልተረጋገጠም የተባለው ዋናውን ውሣኔ የሚቃረን በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትን ውሣኔ አሻሽሏል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የተጠሪ አቤቱታ ተቀባይነት አግኝቶ የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በስር ፍ/ቤት አቤቱታ ያቀረቡት በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የግል ንብረታቸው በመሆኑ ሐራጁ እንዲቆምላቸው ሲሆን መሰረት ያደረጉትም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 ድንጋጌ ነው፡፡ ይህ ድንጋጌ በአፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዲያዝ ሲታዘዝ በዚሁ ንብረት ላይ ተቀዳሚ መብት አለኝ የሚል ተቃዋሚ ሲቀርብ የሚያገለግል ነው፡፡ በመጀመሪያ ክርክር ላይ ተካፋይ ባይሆኑም በሚያዘው ንብረት ላይ መብት አለን የሚሉ ወገኖች የሚያቀርቡትን መቃወሚያ ፍ/ቤቱ ሊመረምር የሚገባው ቢሆንም ተቃዋሚዎቹ መቃወሚያውን በቂ ባልሆነ ምክንያት አዘግይተው ከሆነ ግን መቃወሚያው ላይመረመር እንደሚችል ድንጋጌው ያመለክታል፡፡ የአመልካችም አቤቱታ ቢሆን ተጠሪ ተቃውሞውን አዘግይተው ያቀረቡ በመሆኑ ፍ/ቤቱ ሊመረምረው አይገባም ነበር፡፡ የሚል ነው፡፡ ጉዳዩ በመጀመሪያ የቀረበለት የሰ/ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ጨረታው የወጣው በ25/04/98 ሲሆን መቃወሚያው የቀረበው በ03/05/98 በመሆኑ አላግባብ ዘግይቶ የቀረበ ሲሆን ለመዘግየቱም በቂ ምክንያት መኖሩን ተጠሪ አላስረዱም በሚል የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ቢያደርገውም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤትም ሰበር ችሎት ጥያቄው የቀረበው ከጨረታው በፊት ነው በማለት አረጋግጧል፡፡ መቃወሚያው መቼ ቀረበ? የሚለው ነጥብ ደግሞ በማስረጃ የሚረጋገጥ ፍሬ ነገር በመሆኑ በዚህ ችሎት ሊስተናገድ የሚችል አልደለም፡፡

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 በሚጠይቀው መሰረት ተቀባይነት ያለው መቃወሚያ ለማቅረባቸው የስር ፍ/ቤቶች በአግባቡ መርምረዋል ወይ? የሚለው መታየት የኖርበታል፡፡

የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰ/ሸዋ ከፍተኛ ፍ/ቤትን ውሣኔ ለመሻር መሰረት ያደረገው በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው ቤት የተጠሪ አባት ቤት ነው ያሉት አመልካች ስለሆኑ ይህንኑ በቅድሚያ የማረዳት ሸክም ያለባቸው አመልካች ናቸው፡፡ ነገር ግን አላስረዱም በማለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418/3/ ተቃዋሚው ወይም መብት አለኝ ባዩ ከመቃወሚያ ማመልከቻ ጋር በንብረቱ ላይ ያለውን ተቀዳሚነት መብት ወይም ባለይዞታነቱን የሚያረጋግጥ የጽሁፍ ማስረጃ አያይዞ በማቅረብ በቅድሚያ መብቱን የማስረዳት ሸክም ያለበት ለመሆኑ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ፍ/ቤቱ ግን በቅድሚያ ሊመረምር የሚገባው የአመልካች ማስረጃ ነው በማለት የደረሰበት መደምደሚያ የተጠቀሰውን የሥነ-ሥርአት ህጉን የተከተለ አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ተጠሪ ክርክር የተነሣበት ቤት የራሣቸው እንጂ የአባታቸው ያለመሆኑን በቂ ማስረጃ ያቀረቡ መሆን አለመሆኑን በአግባቡ ሣያጣራ አልፎታል፡፡

በሌላ በኩል ተጠሪ በዋናው መዝገብ የተከሰሱት የአባታቸው ወራሽ በመሆናቸው ሲሆን በዚህ መዝገብም ተወስኖባቸዋል፡፡ ይህንን ውሣኔ አባታቸውን የወረሱ ባለመሆኑ ውሣኔው ሊሻር ይገባል፡፡ ብለው በይግባኝ ውሣኔ የኦሮሚያ ጠቅላይ ሰበር ችሎት በዋናው መዝገብ ከተሰጠው ውሣኔ ጋር ይቃረናል በማለት ሽሮታል፡፡ ይህን በተመለከተ ተጠሪ ያቀረቡት አቤቱታ የለም፡፡ በመሆኑም ተጠሪ የሟች አባታቸው ወራሽ መሆናቸውን ይህ ችሎት ተገንዝቧል፡፡ ነገር ግን የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በአንድ በኩል ተጠሪ የአባታቸው ወራሽ በመሆናቸው በአባታቸው እዳ ተከሰው የተፈረደባቸው ለመሆኑ እያመነ በሌላ በኩል ግን የተወሰነው በወራሾች ላይ በመሆኑ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚገባው በወራሾች ንብረት ላይ እንጂ በሟች ንብረት ላይ አይደለም በማለት ወስኗል፡፡

በመሰረቱ በሟች መሞት ምክንያት የሚቋረጡ ካለሆነ በቀር የሟቹ መብትና ግዴታዎች ለወራሾቹና ለኑዛዜ ባለስጦታዎች እንደሚተላለፍ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 826/2/ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑ ወራሾች የአውራሻቸውን ግዴታ በወረሱት የሟቹ ንብረት ወይም ሐብት መጠን እንዲወጡ ይገደዳሉ፡፡ በተያዘውም ጉዳይ ተጠሪ እና ሌሎቹ የሟች ወራሾች ተከሰው የተፈረደባቸው በአባታቸው እዳ ምክንያት ነው፡፡ በመሆኑም እዳውን እንዲከፈሉ የሚጠየቁት ከአባታቸው በወረሱት ሐብት መጠን ነው፡፡ ስለሆነም ለእዳው መክፈያ በአፈፃፀም ሊያዝ የሚገባው ከአባታቸው በውርስ ያገኙት ንብረትና ሐብት እንጂ የወራሾቹ የግል ሐብት ሊሆን አይገባም፡፡ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን የተወሰነው በወራሾች ላይ በመሆኑ ብቻ አፈፃፀሙ ሊቀጥል የሚችለው በወራሾች ንብረት ላይ እንጅ በሟች ንብረት ላይ አይደለም የደረሰበት

መደምደሚያ የተሣሣተ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ እዚህ የተሣሣተ መደምደሚያ ላይ በመድረሱም ክርክር የተነሣበት ቤት ተጠሪ አባት ለመሆኑ በቂ ማስረጃ ቀርቦ በአግባቡ መጣራቱን በተመለከተ የያዘውን ጭብጥ ውሣኔ ሣይሰጥበት አልፎታል፡፡

በአጠቃላይ የኦሮሚያ የጠቅላይ ፍ/ቤትም ሆነ የሰበር ችሎቱ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 በሚያዘው መሰረት በቂ የጽሁፍ ማስረጃ መቅረብ አለመቀረቡን ሳያጣሩ የተጠሪን መቃወሚያ ተቀብለው የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ ካደረገበት ምክንያት አንዱ ተጠሪ መብታቸው ለማረጋገጥ ማስረጃ አላቀረቡም የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ከግራ ቀኙ በቃል እንዳጣራውም ቢሆን ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418/1/ መሰረት መቃወሚያ ሲያቀርቡ በቤቱ ላይ ባለመብት ለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ የግብር ደረሰኝና የቱሉ ሚልኪ ከተማ 01 ቀበሌ ቤቱ የተጠሪ ለመሆኑ የሰጠው ማረጋገጫ ነው፡፡ እነዚህ ደረሰኞች ደግሞ ክርክር የተነሣበት ቤት ባለቤት ተጠሪ ለመሆናቸው ማስረዳት የሚችሉ በቂ ማስረጃዎች እንዳልሆኑ ተገንዝበናል፡፡ በዚህም ምክንያት ነው የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪን መቃወሚያ ውድቅ ያደረገው፡፡ ስለሆነም ተጠሪ የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን የሚያስርዳ በቂ ማስረጃ ባላቀረቡበት ሁኔታ ቤቱ በሃራጅ እንዳይሸጥ መከልከሉ አግባብ ሆኖ አላገኘውም፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38529 በ09/02/2000 ዓ.ም እና የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 45292 በ04/09/2000 ዓ.ም ክርክር የተነሣበት ቤት በሐራጅ እንዳይሸጥ የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የሰሜን ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 07488 በ18/05/98 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ጸንቷል፡፡
3. ተጠሪ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 418 መሰረት ያቀረቡት መቃወሚያ ተቀባይነት የለውም፡፡ ቤቱ በሐራጅ ሊሸጥ ይገባል ብለናል፡፡
4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38126

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ዲያቆን ኃ/ጊዮርጊስ ወንድም ሲያምረኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ ወ/ሮ የሺ ተፈሪ (2 ሰዎች) - ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚህ ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ናቸው፡፡ በክሣቸው ከአሁኑ ሁለተኛ ተጠሪ ጋር ባልና ሚስት ሆነው በጋራ የሰሩት የእሣቸው ፈቃድ ሣይኖር ሁለተኛ ተጠሪ ለአመልካች መስጠታቸውን በመግለጽ የሽያጩ ውል ከተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ ጋር የሚቃረንና ሕጉ የሚጠይቀውን ፎርማሊቲ ያልተከተለ በመሆኑ ፈራሽ ነው እንዲባልላቸው ጠይቀዋል፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723(1) መሰረት በህግ የሚጠይቀውን የአፃፃፍ ስርአት አልተከተለም በማለት ውሉ እንዲፈረስ ውሣኔ ሰጠ፡፡ አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ መልስ ሰጪን መጥራት ሣያስፈልግ ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታ የስር ከሣሽ ያቀረቡት ክስ በተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አ/ቁ. 213/92 አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ የታገደ ነው የሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊታይ ይገባል በማለቱ ተጠሪዎች ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብ ካለው የህግ ድንጋጌ ጋር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለጸው በስር ፍ/ቤት ከሳሽ የነበሩት አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር በጋብቻ ውስጥ ያፈሩት የጋራ ቤታቸውን ሁለተኛ ተጠሪ ያለ እሳቸው ፈቃድ ለአመልካች ከመሸጣቸውም በላይ ውሉ በሕግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ስርአት ስለማያሟላ እንዲፈርስላቸው ነው፡፡ አመልካች የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል የሚልና ሌላም መቃወሚያ እንዲሁም ለዋናው ጉዳይ በአማራጭ ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡ በመሆኑም አመልካች ያቀረቡት የይርጋ መቃወሚያ በቅድሚያ ሊታይ ይገባል፡፡

ከመዝገቡ ላይ በአመልካችና በሁለተኛ ተጠሪ መሐከል የሽያጭ ውል የተደረገው ኅዳር 1 ቀን 1995 መሆኑና የስር ከሣሽ ወይም የአሁኗ አንደኛ ተጠሪ ክስ የመሰረቱት በ09/08/1999 ዓ.ም መሆኑን ተረድተናል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ክሱን የተቃወሙት ውል የተደረገበት ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር ያፈሩት የጋራ ንብረት በመሆኑ ነው፡፡ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 68 ፊደል “ሀ” ስር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት ለመሸጥ የሁለቱም ተጋቢዎች ስምምነት አስፈላጊ ነው፡፡ ይህ ስምምነት ሣይኖር የተደረገ ሽያጭ ውጤቱ ምን እንደሆነ በዚህ ህግ አንቀጽ 69 ስር ተቀምጧል አንደኛው ተጋቢ በሌላኛው ተጋቢ ስምምነት ሣይኖር የጋራ የሆነውን የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ እንደሆነ ስምምነቱን ያልሰጠው ተጋቢ ውሉ እንዲፈርስ ሲጠይቅ እንደሚችልና ፍ/ቤቱ ውሉን ማፍረስ እንደሚችል ተገልጾአል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ በጋብቻ ጊዜ ያፈሩት የጋራ ቤት የአንደኛ ተጠሪ ፈቃድ ሣይኖር ተሸጦ ከሆነ ተጠሪዋ ውሉ እንዲፈረስ ጥያቄ ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ግን ግዴታው እንዲፈርስ የሚቀርበው

ጥያቄ ጠያቂው ወገን ግጼታው መገባቱን ከአወቀበት ቀን ጀምሮ ከ6 ወር በኂላ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ግጼታው ከተገባ ከሁለት ዓመት በኂላ ሊቀርብ እንደማይችል በቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 69/2/ ስር ተደንግጓል፡፡ ከፍ ሲል እንደተገለፀው በሁለተኛ ተጠሪና በአመልካች መሐከል የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው 01/03/95 ሲሆን አንደኛ ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ በ09/08/99 ከአራት አመት በኂላ ነው፡፡ የስር ፍ/ቤት የአመልካችን የይርጋ ክርክር ውድቅ ያደረገው የስር አንደኛ ተከሣሽ ከሣሽ በሆኑበት መዝገብ አንደኛ ተጠሪ ተከሣሽ ሆነው ቀርበው ተከራክረው ከተወሰነ በኂላ ፍ/ቤቱ የአንደኛ ተጠሪን ክስ የማቅረብ መብት የጠበቀላቸው በመሆኑና ይህም ውሣኔ ከተሰጠ ጀምሮ አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ክሱ በመቅረቡ ይርጋው ተቀባይነት የለውም በማለት ነው፡፡ አንድ ክስ ለማቅረብ በህጉ የተመለከተው በይርጋ ጊዜ ካለፈ በኂላ ክስ ማቅረብ የማይቻል ቢሆንም ነገር ግን አሁንም ህጉ ለይቶ ባስቀመጣቸው ምክንያቶች የይርጋው ጊዜ ሊቋረጥ እንደሚችልና አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር እንደሚጀምር የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1852/1/ ያመለክታል፡፡ ወይም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1853 ስር የተመለከተው ሁኔታ ሲያጋጥም ፍ/ቤቱ የይርጋን መቃወሚያ አልቀበልም ለማለት ይችላል፡፡ ይርጋ የሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚባሉት የባለእዳው እዳው ማመኑ፣ ወለድ ወይም ከእዳው ላይ ከፊሉን መክፈሉ፣ መያዣ ወይም ዋስ መስጠቱ ወይም ደግሞ ባለገንዘቡ መብቱ እንዲታወቅለት በፍ/ቤት ክስ አቅርቦ ባለእዳውን ማሣወቁ መሆናቸው ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851(1)(2) መረዳት ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የሽያጭ ውሉ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ አንደኛ ተጠሪ ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ 4 አመት ያለፈው በመሆኑ ክሣቸው በተሻሻለው ቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 69/2/ መሰረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ በዚህ አራት አመት ውስጥ ይርጋውን የሚያቋርጡ ሁኔታዎች (በህጉ በተመለከቱት አይነት) ስለማጋጠማቸው የቀረበ ነገር የለም፡፡ ፍ/ቤቱ በጠቀሰው መዝገብ ላይ የአንደኛ ተጠሪ ክስ የማቅረብ መብት ያላቸው መሆኑ መገለጽ የይርጋውን ጊዜ ለማቋረጥ የሚበቃ ምክንያት አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል በተጠቀሰው መዝገብ አንደኛ ተጠሪ ተከሣሽ እንጂ ከሣሽ ለመሆናቸው መብታቸው እንዲታወቅላቸው በፍ/ቤት ክስ አቅርበዋል ሊባል የሚችሉ ባለመሆናቸው በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1851/ለ/ መሰረት የይርጋው ጊዜ ተቋርጧል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም ውሉ ከተደረገ ከ4 አመት በኂላ የቀረበው ክስ በይርጋ ሊቋረጥ ሲገባ የአመልካችን የይርጋ መቃወሚያ ውድቅ ማደረጉ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58635 በ12/09/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ እና የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44809 በ27/11/99 የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የከሣሽ የዳኝነት ጥያቄ በተሻሻለው የቤተሰብ ህግ ቁጥር 69/2/ መሰረት በይርጋ ይቋረጣል ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 38152

ሚያዝያ 29 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች:-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች:-** የወ/ሮ ገነት ዳምጤ ወራሾች - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ:-** እነ አቶ ይስማ አስፋው - ጠበቃ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የውርስ ሀብት ክፍፍልን የሚመለከት ሲሆን ተጠሪዎች በአመልካች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 11 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 847 የሆነውን ቤት ጥቅምት 19 ቀን 1962 ዓ.ም. ሟች ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ባደረጉት ኑዛዜ ለከሣሾችና የተከሣሽ ባለቤት ለሆነው ወንድማችን ሠጥተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አውራሻችን ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ በባንክ ያስቀመጡትን ብር 4,666(አራት ሺህ ስድስት መቶ ስልሳ ስድስት) ወንድማችንና የተከሳሽ ባለቤት የሆኑት ወስደው አላካፈሉንም፡፡

ስለዚህ ተከሣሽ ከላይ የተጠቀሰውን ቤትና አብረውት ያሉትን ቤቶች እንደዚሁም ከገንዘቡ እንዲያካፍሉን ይወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተከሣሽ /የአሁን አመልካቾች አውራሽ/ ቀርበው በሰጡት መልስ ከሳሾች አውራሻችን የሚሏቸው ወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ከሞቱ በኋላ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ላይ እንደተቀመጠው በ3 ዓመት ጊዜ የውርስ ሀብት ይገባናል በማለት ጥያቄ ያላቀረቡ ስለሆነ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የተከራከሩ ሲሆን ለፍሬ ጉዳዩም ሙሉ መልስ ሰጥተዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤትም የይርጋ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም ካለ በኋላ ክስ የቀረበበት ቤት የግራ ቀኙ የጋራ ሀብት ስለሆነ 2/3ኛውን ከሣሾች ቀሪውን 1/3 ደግሞ ተከሣሽ እንዲወስዱ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ተከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከ/ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ባለመቀበል ውሣኔውን አጽንቷል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ በሥር ፍ/ቤት በአመልካቾች አውራሽ በኩል የተነሳው የይርጋ መቃወሚያ ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ተጠሪዎች ባሉበት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ እንደተቻለው ለክሱ ምክንያት የሆነው ቤት ተጠሪዎች ሟች ወ/ሮ ተካበች ሀ/ወልድ በኑዛዜ ሠጥተውናል የሚሉት በ1962 ዓ.ም. ሲሆን ወ/ሮ ተካበች ሀ/ወልድ ደግሞ ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በ1968 ዓ.ም.

ነው፡፡ የውርስ ንብረቱ ድርሻችንን የአመልካቾች አውራሽ ሊያካፍሉን ይገባል በማለት ክስ የመሠረቱት በ1994 ዓ.ም. ነው፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የአመልካቾች አውራሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ላይ የተመለከተውን በመጥቀስ ነው፡፡ የዚህ ድንጋጌ ተፈፃሚነት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው አንድ እውነተኛ የሆነ ወራሽ ትክክለኛው ወራሽ መሆኑ ታውቆለት ዋጋ ያለው የወራሽነት ማስረጃ ሳይኖረው የውርሱን ንብረት በእጁ ያደረገው ሰው የውርሱን ንብረት እንዲለቅ ክስ በሚያቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች አውራሽ ላይ ክስ ቀርቦ የነበረው ምንም ዓይነት መብት ሳይኖራቸው ይዘውት የሚገኘውን የውርስ ሀብት ድርሻችንን ትልቀቅልን በማለት ስለሆነ የተጠቀሰው ድንጋጌ ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም፡፡

ተጠሪዎች በዚህ መልኩ ያቀረቡት አቤቱታ በምን ያሕል ጊዜ መቅረብ እንዳለበት በውርስ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ የውርስ ሕጉ በዚህ ረገድ ክፍተት ካለበት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ ለጉዳዩ እልባት መስጠት በሕግ አተረጓጎም መርህ /principles of legal interpretation/ የተፈቀደ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለውሎች ከተደነገገው አንፃር ተመልክተነዋል፡፡ በዚህ ክፍልም ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆንም በውል ሕግ ላይ የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት እንዳላቸው በቁጥር 1677/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ በውል ሕግ ደግሞ ዋናው የይርጋ ድንጋጌ በቁጥር 1845 ላይ የተመለከተው የ10 ዓመት የይርጋ ጊዜ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪዎች በውርስ የተላለፈልንን ድርሻ ንብረታችንን ሊለቁልን ይገባል በማለት በአመልካቾች አውራሽ ላይ ክስ የመሠረቱት ከላይ እንደተመለከተው በ1994 ዓ.ም. ሲሆን ኑዛዜውን አድርገዋል የተባሉት ግለሰብ በሞት የተለዩት ደግሞ በ1968 ዓ.ም. ነው፡፡ ኑዛዜው ከሟች ሞት በኋላ ውጤት የሚኖረው እንደመሆኑ መጠን ሟች ከሞቱበት ጊዜ ጀምሮ በ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠሪዎች አቤቱታውን ማቅረብ ሲገባቸው ከ26 ዓመት በኋላ ጥያቄውን ማቅረባቸው በይርጋ የማይታገድበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍ/ቤቶች የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1000 ለዚህ ጉዳይ አግባብነት አይኖረውም ማለታቸው ተገቢ ቢሆንም ነገር ግን ከ26 ዓመት በኋላ የቀረበን የውርስ ንብረት ክፍያ ጥያቄ ከጠቅላላ ሕግ አኳያ በይርጋ የታገደ ሆኖ ሳለ ከዚህ አንፃር የይርጋ ክርክሩን ሳይመለከቱት መቅረታቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18669 በ24/01/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 61155 በ21/9/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ተጠሪዎች ያቀረቡት ክስ በይርጋ ቀሪ ሆኗል ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## የሃሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ፣ ተጠሪዎች የወ/ሮ ተካበች ሀብተወልድ ወራሽ መሆናቸውን በማረጋገጥ ንብረቱን ከሟች መካሽ ጌታነህ የአመልካች ባል ጋር በጋራ የያዙትና የባለቤትነት ደብተር በጋራ ያወጡ መሆኑን ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ የተገለፀ በመሆኑ ይህም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1053 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የወራሾቹ የጋራ ንብረት እንደሆነ ስለሚቆጠርና ተጠሪዎች ይህንን የጋራ ሀብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1272 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በማንኛውም ጊዜ ለመከፋፈል ጥያቄ ማቅረብ የሚችሉ በመሆኑ ተጠሪዎች ንብረት ለመካፈል ያቀረቡት ጥያቄ በይርጋ አይቋረጥም በማለት የልዩነት ሀሳቤን አስፍሬያለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 37313

ግንቦት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ መሐሪ ተክለማርያም
2. ወ/ሮ መድህን ወልዱ } ጠበቃ ቀረቡ

**ተጠሪዎች፡-** የወ/ሮ ገነት መኮንን ወራሾች

1. ወ/ት ሜሮን ብርሃኑ - ቀረበች
2. ወ/ት ህሊና ብርሃኑ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሆኖ ተጠሪዎች ከሳሾች ሲሆኑ አመልካቾች ተከሳሾች ነበሩ፡፡ ክሱም የሟች ብርሃኑ ጫላና የእኔ የባልና ሚስት የጋራ ሀብት የሞግዚት አድራጊዎቼ የውርስ ንብረት የሆነውን በወረዳ 25 ቀበሌ 01 ቁጥሩ 714 የሆነውን መኖሪያ ቤት ከሕግ ውጪ የያዙበት ውል ፈራሽ ሆኖ ቤቱን እንዲያስረክቡ ይወሰንልን የሚል ነው፡፡

አመልካቾችም የባልና ሚስት የጋራ ሀብት መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ አላቀረቡም፡፡ ክርክር በተነሳበት ቤት ላይ ኖረው አያውቁም፣ ሚስት ወ/ሮ ዘቢደር አናውጤ እንጅ ከሳሽ አይደሉም ተጠቃሹ ቤት ወ/ሮ ገነት መኮንን ጋብቻ መሠረትን ከሚሉት ከ1973 ዓ.ም በፊት አቶ ብርሃኑ ጫላና ባለቤታቸው ወ/ሮ ዘቢደር አናውጤ 1966 ዓ.ም የገዙት ለመሆኑ ማስረጃ አለ፡፡ ስለዚህ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) መሠረት ለመክሰስ ስለማይችሉ ክሱ ይሠረዝ በማለት መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 06185 በ8/2/2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት ወ/ሮ ገነት መኮንን የሟች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት መሆናቸው በፍ/ቤት በመ/ቁጥር 01783 ከተወሰነ በኂላ ወ/ሮ ዘብይደሩ አናውጤ ተቃዋሚ ሆነው ገብተው ተከራክረው ፍ/ቤቱ ወ/ሮ ገነትን ሚስትነት ስላፀናው ይግባኝ ቀርቦ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 17437 ላይ በ30/5/98 ዓ.ም በዋለው ችሎት የወ/ሮ ዘቢደሩ ምሥክሮች ተሰምተው እንደገና በመቃወሚያ አቤቱታው ላይ ውሳኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን ለታች ፍ/ቤት የላከው ሲሆን ወ/ሮ ዘብይደሩ በክርክሩ ሳይቀጥሉ ቀርተዋል፡፡ በመሆኑም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ወ/ሮ ገነት መኮንን የሟች ብርሃኑ ጫላ ሚስት ናቸው፣ሟች ወ/ሮ ገነት እና ሟች አቶ ብርሃኑ ሲጋቡ በ6-10-73 ዓ.ም ባደረጉት የጋብቻ ውል ላይ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ቤት የጋራ እንዲሆን ብለዋል፡፡ የእሳቸው ድርሻ ላይ ፈቃድ ሳይጠየቅ የተደረገ ውል ሊሠረዝ ይገባል በማለት የሽያጩ ውል ተሠርዞ ቤቱን ያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ/ቁጥር 59947 በሆነው መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት

በሚስትነት ዙሪያ ያለው ክርክር ሁለቱም ተከራካሪዎች በሕይወት የሌሉ በመሆኑ አመልካቾች ወ/ሮ ገነት ሚስት አይደሉም፣ ወ/ሮ ዘቢደር ሚስት ናቸው የሚል ክርክር የሕግ መሠረት የለም። ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 መሠረት በሕግ ፊት የሚፀና አይደለም በማለት ውሳኔውን በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው።

አመልካቾች ሚያዝያ 10 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ አቤቱታ ያቀረቡት ቅሬታ፡-

- ተጠሪዎች የሟች ብርሃኑ ጫላ ልጆችና ወራሾች መሆናቸው እና የወ/ሮ ገነት መኮንን ሚስትነት የተረጋገጠበት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ተሰርዞ ጉዳዩ እንደገና ታይቶ እንዲወሰን ተብሎ የታዘዘ ቢሆንም ለሥር ፍ/ቤት እንዲያቀርቡ የታዘዘውን ማስረጃዎች ሳያቀርቡ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በሕግ ፊት የሚፀና የሚስትነት ውሳኔ አልተሠጠም።
- ተጠሪዎችም የሟች ብርሃኑ ጫላ ልጆች ብሎም ሕጋዊ ወራሾች መሆን የሚመሠረተው ሟች እናታቸው የሟች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት ናቸው ከሚል ከተረጋገጠ ፍሬነገር በመነሳትና በጋብቻ ውስጥ የተወለዱ ልጆች አባት የእናታቸው ባል ነው በሚለው የሕግ ግምት መሠረት ነው። ሆኖም የእናታቸው ሚስትነት ሳይረጋገጥ የተጠሪዎች ወራሽነት ተረጋግጧል ለማለት ስለማይቻል የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ፈጽሟል በማለት ውሳኔው እንዲሻር የሚጠይቅ ነው።

ቅሬታውን መሠረት በማድረግ የተጠሪዎች እናት የሟች አቶ ብርሃኑ ጫላ ሚስት መሆናቸውና የተጠሪዎች ወራሽነት አልተረጋገጠም እየተባለ ለክርክሩ መንስኤ የሆነው ቤት ያለተጠሪዎች እናት ፈቃድ በሟች የተሸጠው በሕግ አግባብ አይደለም፣ ውሉም በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 ላይ የተቀመጠውን መስፈርት አያሟሉም ተብሎ አመልካቾች ቤቱን ያስረክቡ የመባሉን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎት እንዲቀርብ ታዞ ግራ ቀኙ በዚህ ፍ/ቤት የጽሑፍና የቃል ክርክር አካሂደዋል። በተጠሪዎች በኩል የቀረበው ክርክር በአጭሩ በምሥክሮች መስማት ረገድ ለወ/ሮ ዘቢደር መስቀለኛ ጥያቄ የመጠየቁ አጋጣሚ ስለሚፈጠር ምስክሮች ቃል ይሰማ ተብሎ የተሠጠውን ውሳኔ አመልካቾች መከራከሪያ ሊያደርጉ አይችሉም። እንደገና እንዲታይ መመለስ የመክሰስ መብትንና ጥቅምን አያሳጣም። በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት የጋብቻ ውል ላይ ተለይቶ የተሠጠ ውሳኔ የለም በማለት ውሳኔው እንዲፀና ተከራክረዋል።

እኛም የግራ ቀኙን ክርክር እንደሚከተለው መርምረናል።

በቀዳሚነት ሊታይ የሚገባው የሕግ ነጥብ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ጉዳዩን መጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት እንደገና መልሶ እንዲያይ ጭብጥ ይዞ መመለስ የቀድሞውን ውሳኔ የመሻር ውጤት ይኖረዋል ወይንስ አይኖረውም? የሚለው ነጥብ መታየት የሚገባ ነው። የተጠሪዎች ክርክር በጥቅሉ ሲታይ ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ቢመለስም የሚስትነትን ውሳኔ አልሻረውም የሚል ነው። የአመልካቾች ክርክር ደግሞ የቀድሞ ሚስትነት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ክርክር ተካሂዶ ውሳኔው ተሠርዞ ጉዳዩ እንደገና ታይቶና ማስረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን በተባለው መሠረት እንዲያቀርቡ የታዘዙትን ምስክሮች ሳያቀርቡ ከዚህ ዓለም በሞት በመለየታቸው በሕግ ፊት የሚፀና የሚስትነት ውሳኔ የለም በማለት ነው። እንግዲህ አንድ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት ክርክር ተሰምቶ ጉዳዩ እንደገና መጀመሪያ ያየው ፍ/ቤት መልሶ እንዲያየው ከተደረገ የቀድሞ ውሳኔ እንዳልተወሰነ ወይም በውሳኔው የተገኘው መብት እንደሌለ ወይም እንደተሻረ የሚቆጠር ነው። በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች እናት ሚስት ናቸው ተብሎ የተሠጠው ውሳኔ ማስረጃ ተሰምቶ እንዲወሰን ታች ወደ ወሰነው ፍ/ቤት ተመልሷል። በተመለሰው ውሳኔ መሠረት ክርክር ሳይደረግና የተባለው ምሥክሮች ክርክርም ሳይካሄድ የሚስትነታቸው ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ ቀርቷል። በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁኑ ተጠሪዎች እናት ሞግዚትነት የተገኘው የሟች ሚስት ነበሩ ልጆችም የተወለዱት ከሚስትነታቸው ነው ተብሎ በፍ/ቤት በተረጋገጠው ውሳኔ መሠረት ነው። ይህ ውሳኔ ደግሞ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዳልተወሰነ ተደርጐ እንደገና ምሥክሮች ተሰምቶ እንዲወሰን ከተደረገና ክርክር ተካሂዶበት ውሳኔ ካልተሠጠ በስተቀር በእንጥልጥል ላይ ያለ ጉዳይ ከሚሆን በስተቀር በሕግ ፊት የሚፀና ሚስትነትን የሚያረጋግጥ ውሳኔ አለ ለማለት አይቻልም። የጽሑፍ የጋብቻ ውልን ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት ለይቶ አልወሰነውም የሚለውን ክርክር በተመለከተ የውሳኔው ይዘት ሲታይ በጽሑፍ ውል ላይ ብቻ ተንተርሶ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የሠጠው ውሳኔ ያለአግባብ በመሆኑ የምሥክሮች ቃል በመስማት እንዲወሰን መባሉ የጽሑፍና የሰው ማስረጃዎች ሁለቱም ተመዝኖ ሊወሰን የሚገባ መሆኑን የሚያመለክት እንጅ ውሉን አልነካውም የሚያስብል የሕግ መሠረት አይኖርም። የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ለውሳኔው መሠረት ያደረገው በከፍተኛ ፍ/ቤት የሚስትነት ውሳኔ አልተሻረም በማለት ነው። ለሽያጩም ውል መፍረስ ምክንያት የሆነው ያለሚስት ፈቃድ የተደረገው የሽያጭ ውል

ሊሠረዝ ይገባል በማለት የውሳኔው መሠረት ሚስትነት ነው፡፡ የሚስትነት ውሳኔ አልተሻረም የተባለው ውሳኔ ከፍ ሲል እንደተመለከተው እንዳልተወሰነ ወይም እንደሌለ የሚቆጠር ውሳኔ ነው፡፡ ውሳኔው እንደሌለ ወይም እንዳልተወሰነ የሚቆጠር ከሆነ ደግሞ ከዚህ የሚመነጭ መብትም ሆነ ጥቅም ሊኖር አይችልም፡፡ የሽያጩ ውል እንዲሠረዝ ለመቃወም መብት የተገኘው ከሚስትነት ነው፡፡ ሚስትነት ከሌለ ደግሞ መቃወሚያ ማቅረብ አይቻልም፡፡ በመሆኑም አመልካቾች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 33(2) መሠረት ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የላቸውም በማለት ያቀረቡትን ክርክር ፍ/ቤቱ ባለመቀበል የሠጠው ውሳኔ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ይህን ማረም ሲገባው በማጽናት የሠጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 06185 በ8/2/2000 ዓ.ም እንዲሁም የከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 59947 መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሠጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡ የፃፍ፡፡
2. ተጠሪዎች የመክሰስ መብት የላቸውም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኝ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 42525

ግንቦት 27 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** እነ አቶ ዓብዱልዋሲቅ አርጋው - ጠበቃ ተስፋዬ ተገኝወርቅ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ አለውያ አባበሊስ - ወኪል ኑርአዲስ አርጋው ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ህግን መሠረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረውም በውርስ ማጣራት ሂደት ነው፡፡ የውርስ ማጣራቱን ሥራ የውርስ አጣሪው እንዲያከናውንና ሪፖርቱን ለፍ/ቤቱ እንዲያቀርብ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሠጥቶ የውርስ አጣሪው የሚች አቶ አራጋው ከድር የውርስ ንብረት አጣርቶ ጥቅምት 26 ቀን 2001 ዓ.ም የተፃፈ ሪፖርት ለፍ/ቤቱ አቅርቦ ሪፖርቱ በፍ/ቤቱ ፀድቆ ተመዝግቧል፡፡

ለዚህ የሠበር ክርክር መነሻ የሆነው የሪፖርቱ ክፍል ደግሞ የውርስ አጣሪው በአ/ከ/ክ/ከተማ ቀበሌ 02 የቤት ቁጥር 270 የሆነ የንግድ ሱቅ ድርጅት ተጠሪ ከመንግስት በ1986 ዓ.ም የተከራዩት ነው እንጂ ከሟች አቶ አራጋው ከድር ጋር በጋራ የተከራዩት ንብረት አይደለም በማለት ያቀረበው ነጥብ በፍ/ቤት መፅደቁ ተገቢነት የለውም የሚል ነው፡፡ አመልካቾች የበታች ፍ/ቤቶች ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈፅሞበታል የሚሉበትን ምክንያት ጥር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 5/አምስት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ አመልካቾች ክርክራችን ለማስረዳት ያቀረብናቸው ማስረጃዎች ሣይሰሙ ውሣኔ መስጠቱ ያላግባብ ስለሆነ የበታች ፍ/ቤቶች ትዛዞች ተሽረው ማስረጃዎቻችን ተሰምተው ተገቢው ውሣኔ እንዲሠጠን ይደረግልን የሚል ነው፡፡ የአመልካቾች አቤቱታ ተመርምሮም በሠበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሚያዝያ 03 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት 4/አራት/ ገፅ ማመልከቻ መልሣቸውን ሠጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ የስር ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ ውሣኔ የሠጡት ማጣራት አድርገውና ከህጉ ጋር አገናዝበው በመሆኑ ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የለበትም ተብሎ ከውጪና ኪሣራ ጋር ሊፀና ይገባዋል በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው የተጠሪ መልስ የሱቅ ድርጅቱ የተገኘበትን ህጋዊ መንገድ የማይገልፅ እና ተቀባይነት የሌለው በመሆኑ ውድቅ ሊሆን ይገባል ሲሉ ሚያዝያ 28 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የመልስ መልስ ተከራክረዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የገለፀው ሲሆን ችሎቱም የግራ ቀኙን የፁሑፍ ክርክር የሠበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሱቅ ድርጅት በአመልካቾች የተቆጠሩት የሠው ምስክሮች ሣይሠሙ የተጠሪ የግል ንብረት ነው ተብሎ መወሠኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው አመልካቾች የሱቅ ድርጅቱ የንብረት ድርሻ ጥያቄ ያቀረቡት አውራሽ የሆኑት ሟች አባታቸው አቶ አራጋው ከድር የንግድ ድርጅት ነበር በማለት መሆናቸውን፣ የንግድ ድርጅቱ ወደ ተጠሪ የተላለፈው ተጠሪ የአመልካቾች ሞግዚትና ንብረት አስተዳዳሪ የነበሩ በመሆኑና ይህንንም በሠውና በሠነድ ማስረጃ ለማረጋገጥ

አቤቱታ ማቅረባቸውን ቀድሞ የነበረው የሱቅ ንግድ ድርጅት በእሣት ቃጠሎ በ1980 ዓ.ም ወድሞም በተቃጠለው ሱቅ ምትክ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን የንግድ ሱቅ ተጠሪ በዕጣ የወሠዱ መሆኑንና ይህም ሊሆን የቻለው ተጠሪ በወቅቱ በአቀረቡት የሞግዚትነትና የሚስትነት የፍርድ ውሣኔ መነሻ ስለመሆኑ አመልካቾች ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ በበኩላቸው ሱቁ የግል ንብረታቸው መሆኑ በአግባቡ ተጣርቶ መወሠኑን ጠቅሰው የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ እንዲሁም የውርስ አጣሪው ለክርክሩ መነሻ የሆነው የሱቅ ድርጅት ማህደር ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ንግድና ኢንዱስትሪ ልማት ጽ/ቤት ቀርበው በመመልከት የቤት ቁጥር 270 የሆነው የሱቅ ድርጅት ከመንግስት የተከራዩት ተጠሪ ወ/ሮ አለውያ አባቢለስ መሆናቸውን፣ ጊዜውም በ1986 ዓ.ም ሟች አቶ አራጋው ከድር ከሞቱ ከሠባት ዓመት በኋላ መሆኑን ጠቅሰው ለስር ፍ/ቤት የውርስ ማጣራት ሪፖርቱን ማቅረባቸውን ተረድተናል፡፡

በመሠረቱ የውርስ ማጣራት ስራ ተገቢው ሥርዓት ተጠብቆ የወራሾች ክርክርና ማስረጃ ተሠብስቦና ታይቶ የሚከናወን ስራ ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ 942 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መንፈስ የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ የውርስ ማጣራት ስራ እንዲከናወን ትዕዛዝ የሠጠው ፍ/ቤትም የአጣሪውን ሪፖርት የሚያፀድቀው የማጣራቱ ተግባር በህጉ አግባብ መከናወኑን ከአረጋገጠ በኋላ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የውርስ ማጣራቱ ስራ የተከናወነው በፍ/ብ/ህ/ቁ 950(1) መሠረት በፍ/ቤት በተሾመ አጣሪ ሁኖ አጣሪው ስራውን ያከናወኑት ግራ ቀኙ ወገኖች ባሉበትና ተገቢው የማስረጃ ማሠባሠብ ስራ አከናውኜአለሁ ካሉ በኋላ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ሱቅ በተመለከተ በአመልካቾች በኩል የቀረቡት ማስረጃዎች ያልተሠሙበትን ምክንያት የውርስ አጣሪውም ሆነ የአጣሪውን ሪፖርት ያፀደቀው ፍ/ቤት በግልፅ አላስቀመጡትም፡፡ በአንድ ተከራካሪ ወገን የተቆጠረ ማስረጃ የማይሠማው ደግሞ ህጋዊ ምክንያት ሲኖር ብቻ ነው፡፡ የአመልካቾች ማስረጃዎች በውርስ አጣሪው ያልተሠሙት በህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ አልተገለፀም፡፡ የአመልካቾች ክርክር በአባታቸው ስም ይታወቅ የነበረ ቁጥሩ 398 የሆነ የሱቅ ድርጅት እንደነበር፣ ይህ ሱቅ በቃጠሎ መውደሙንና በምትክ ደግሞ አሁን ክርክር ያስነሣውን ሱቅ ቁጥሩ 270 የሆነውን ተጠሪ ከመንግስት መረከባቸውን የሚያሣይና ይህንንም ፍሬ ጉዳይ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን ስለመቆጠራቸው የሚያሣይ ነው፡፡ ለክርክሩ መነሻ የሆነው ሱቅ የተያዘበት መንገድ ከላይ የተገለፀው ስለመሆኑ አመልካቾች እየጠቀሡ የሱቁን ማህደር ብቻ በመመልከት ፍትሐዊ ወደሆነው ውሣኔ ለመድረስ አይቻልም፡፡ የውርስ አጣሪው የአመልካቾችን ማስረጃዎች አለመስማቱ የማጣራቱን ሂደት የተሟላ ነበር ለማለት የማያስችል፣ የአመልካቾችን የመከራከር መብት ያጣበበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የውርስ አጣሪውን ሪፖርት ያፀደቀው ፍ/ቤትም ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት የአመልካቾችን የማስረጃ ማሰማት መብታቸውን ሣያስተካክሉ ማለፋቸው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 241 እስከ 270 እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ቁ 345 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሠጠው ውሣኔ ተሽሮ የአመልካቾች ማስረጃዎች ተሠምተው ተገቢ ውሣኔ ይሠጥበት ዘንድ ለስር ፍ/ቤት ጉዳዩን መመለሱ አስፈላጊ ሁኖ በመገኘቱ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራሉ መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 114932 ህዳር 19 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ፣ የፌ/ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 74285 ታኅሣስ 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሠጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሠረት ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በአመልካቾች የተቆጠሩትን ማስረጃዎችን ከሠማ በኋላ በጉዳዩ ላይ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሠጥበት ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343(1) መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ. 32817

ሰኔ 11 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ ወኪል ጌታቸው ታደሰ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ እቴቱ ዘውዴ

2. ወ/ሮ መሰረት አድማሱ } ቀረቡ

3. አቶ ደረሰ ዘውዴ አልቀረበም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች መጋቢት 25 ቀን 1992 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ማመልከቻ ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ መኖሩን ገልፀው ይኸው ኑዛዜ በፍ/ቤት ፀድቆላቸው የኑዛዜ ወራሽነታቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው በፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ መነሻ ሲሆን፣ የአሁኑ ተጠሪዎችም በተቃዋሚነት ቀርበው አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ጥር 22 ቀን 1993 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ ሟች መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም እና ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጓቸው ኑዛዜዎች ሟች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ የተሻሩና የተተኩ በመሆኑ ኑዛዜው ሊፀድቅ አይገባም በማለት የተከራከሩ ሲሆን፣ የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ ግን መጋቢት 08 ቀን 1996 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አመልካች እንዲፀድቅላቸው የጠየቁት ኑዛዜ ቢፀድቅ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

የስር ፍ/ቤትም ሟች ከመስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም በኋላ ሁለት የተለያዩ ኑዛዜዎች ማድረጋቸውን፤አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ደግሞ ሟች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ እንዲፀድቅላቸው ጥያቄ አቅርበው የአሁኗ አመልካች እና የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ በተቃዋሚነት ቀርበው ይኸው ኑዛዜ በመ/ቁ. 1169 የካቲት 10 ቀን 1997 ዓ.ም በፍ/ቤቱ መጽደቁን፣ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም በተደረገው ኑዛዜ ሟች በወረዳ 3 ቀበሌ 44 የቤት ቁጥር 220 የሆነውን ቤታቸውን ለወ/ሮ የውብዳር እና ለወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ መስጠታቸውን፣ በሙከጡሪ ከተማ ያለውንም ቤት ወ/ሮ አልማዝ ዘውዴ በራሷ ገንዘብ የገዛችው መሆኑን ገልፀው ማንም እንዳይጠይቃት የተናዘዙ መሆኑን፣ ሆኖም እነዚህን ንብረቶች ወ/ሮ እቴቱ ዘውዴ እንዲወስዱ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ መናዘዛቸውን ዘርዝሮ መስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 859/2/ መሰረት በሟች ተለውጧል፤ የሚል ምክንያት በመያዝ የአመልካችን የኑዛዜ ይጽደቅልኝ ጥያቄ ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኗ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበውም ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም በዚሁ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች ወኪል ጥር 04 ቀን 2000 ዓ.ም አሻሽለው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ሟች የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ በግልጽ ቀኑን ጭምር ጠቅሰው የሻሩት ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉትን ብቻ እንጂ አስቀድሞ በ26/1/1984 ዓ.ም የተፃፈውን ኑዛዜ አለመሆኑን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ሟች ኑዛዜ ሲያደርጉ የእድሜ ባለጠጋ እንደነበሩና ኑዛዜ ያደረጉበት ንብረትም የግላቸው ባልሆነው መሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 865/2/ መሰረት ኑዛዜው ሊፈፀም

የማይችል መሆኑን እንደሚያሣይ፤ አመልካች ከሟች ውርስ ያላግባብ መነቀላቸውን በመዘርዘር የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ተሽሮ ሟች በ26/1/84 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ ፀድቆ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪዎች ቀርበው መልሣቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ጥቅምት 03 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት የመልስ ማመልከቻ ሟች አመልካችን ከውርስ በምክንያት የነቀሏቸው መሆኑን፤ ሟች ኑዛዜ ባደረጉበት ወቅት አእምሯቸው ጤነኛ እንደነበርና የአመልካች ቅሬታ በማስረጃ ያልተደገፈ መሆኑን፤ ቤቱም በሟች የግል ገንዘብ የተገዛ መሆኑን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም የተደረገውን ኑዛዜ የተቀበሉት መሆኑን በኮ/መ/ቁ. 463 የተደረገው ክርክር እንደሚያሣይና ይኸው ኑዛዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.895/3/ መሰረት ተቀባይነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ሆኖ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ከበቂ ወጪና ኪሣራ ጋር ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡ ሦስተኛ ተጠሪ በበኩላቸው ሟች አመልካችን ከውርስ የሚነቅሉበት አንዳችም ምክንያት ሣይኖር መንቀላቸውና በአመልካች ስም የሚታወቀውን ቤታቸውን የሟች አስመስለው በኑዛዜ ለሌላ አሣልፈው መስጠታቸው ያላግባብ መሆኑን በመዘርዘር የመስከረም 26 ቀን 1984 ዓ.ም ኑዛዜ ቢፀድቅ ተቃውሞ የሌላቸው መሆኑን ገለፀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች ኀዳር 05 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎችን መልስ በመንቀፍ፣የሦስተኛ ተጠሪን መልስ ደግሞ ተቀባይነት ያለው መሆኑን በመዘርዘር የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሣቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመረውም ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ይገኛል በተባለው ቁጥሩ 139 በሆነው ቤት አደረጉ የተባለው ኑዛዜ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ መስከረም 26 ቀን 1984፣ ግንቦት 05 ቀን 1988 እና የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ኑዛዜ ማድረጋቸውን፤ በኑዛዜዎቹም የንብረቶችን ምንጭ ከዓይነታቸውና ብዛታቸው ጋር መግለፃቸውን፤ የውርስ ንብረቶቹ ሊተላለፉለት የሚገባውን ወራሽ፣ ለአሁኗ አመልካች ከውርስ ድርሻ ሣይሰጡ ያለፉበትን ምክንያት እንዲሁም በኋላኛው ኑዛዜ የትኛውን ኑዛዜ እንደሻሩ መጥቀሣቸውን፤ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ በፍ/ቤት መጽደቁንና ከዚህ በኋላም የአሁኗ አመልካች በ26/01/1984 ዓ.ም ተደረገ የተባለው ኑዛዜ እንዲጸድቅላቸው ለፍ/ቤት ጥያቄ ማቅረባቸውን ተገንዝበናል፡፡

ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ የካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ የመጨረሻው ሲሆን በዚህ ኑዛዜ ለአመልካች የሰጡት የውርስ ድርሻ ካለመኖሩም በላይ ግንቦት 05 ቀን 1988 ዓ.ም ያደረጉትን ኑዛዜ በዚሁ በየካቲት 12 ቀን 1989 የሻሩት መሆኑን፤ ለአመልካች በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ የሚገኘውን ቤት የተናዘዙላት ቢሆንም አመልካቿ ልትንከባከባቸውና ልትጦራቸው ባለመቻሏና ከኑዛዜው በኋላ በቤቱ ውስጥ እንዳይኖሩ ያባረረቻቸው ከመሆኑም በላይ በቤት ውስጥ የነበራቸውን ሐብትና ንብረት ሁሉ የእለት ልብስ ሣይቀራቸው ቀምታ በችግር ላይ እንዳሉ በመግለጽ ያለፉ ስለመሆኑ የኑዛዜ መሻሪያ ሰነዱ ያሣያል፡፡ እንግዲህ የየካቲት 12 ቀን 1989 ዓ.ም ኑዛዜ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ በሆኑበት ሂደት በፍ/ቤት የፀደቀ ከመሆኑም በላይ በሕግ ረገድ ፎርማሊቲውን ያልጠበቀ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው ሕጋዊ ፎርማሊቲውን የጠበቀ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ሕጋዊ ፎርማሊቲው አጠያየቂ ካልሆነ መታየት ያለበት የኑዛዜው ይዘት ነው፡፡ አመልካች የኑዛዜውን ይዘት

በተመለከተ ያቀረቡት ክርክር ከውርስ የሚነቅላቸው መሆኑን በመጥቀስ ነው፡፡ በእርግጥ ሟቹ ለአመልካች በኑዛዜው የሰጧቸው የውርስ ድርሻ የለም፡፡ ይህንኑ ሊያደርጉ የቻሉበትን ምክንያት በኑዛዜው መሻሪያ በግልጽ አስፍረዋል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 838/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ስር እንደተመለከተው ተናዛዡ ልጆቹን ወይም ወደታች የሚቆጠሩ ተወላጆቹን ሲነቅል ከውርስ የነቀለበትን ምክንያት በግልጽ ማስፈር እንደሚገባውና ዳኞች የምክንያቱን እውነትነት በመያዝ ተናዛዡ ተወላጆቹን ለመንቀል የሰጠው ምክንያት ከውርስ ለመንቀል የሚያበቃ ነው ወይስ አይደለም በማለት ለመመርመር እንደሚችሉ ተገልጿል፡፡ በመሆኑም ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ አመልካችን ከውርስ ሐብት ድርሻ እንዳያገኙ ያደረጉበት ምክንያት በኑዛዜው መሻሪያ ላይ በግልጽ የተቀመጠና ተወላጅን ለመንቀልም የሚያበቃ ምክንያት ሆኖ ስለተገኘ በዚህ ረገድ አመልካች ያቀረቡት ጥያቄ ሕጋዊ መሰረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ ባደረጉት ኑዛዜ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ ይገኛል የተባለውንና ቁጥሩ 139 የሆነው ቤት ከአመልካች ውጪ ላሉት ወራሾች እንደሚገባ ዘርዝረው የማከፋፈላቸውን ሕጋዊነት ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 865/2/ እና ተዛማጅነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር አገናዝበን ተመልክተናል፡፡

በመሰረቱ ኑዛዜ በባህርይው ተራ የሐሣብ መግለጫ ቢሆንም በተናዛዡ በግሉ ብቻ ሊፈፀም የሚገባው ተግባር ነው፡፡ ኑዛዜ በይዘቱ ንብረትን ከማስተላለፍ ተግባር ጋር የተያያዘ ሲሆን ህጋዊ ጥበቃ የሚደረገውም ተናዛዡ የራሱ የሆነውን ህጋዊ ንብረት ለማስተላለፍ ህጋዊ ኑዛዜ አድርጐ ሲገኝ ስለመሆኑ የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ ተናዛዡ ህጋዊ ንብረቱ ባልሆነው ላይ ኑዛዜ ቢያደርግና ይኸው ኑዛዜ በፍ/ቤት ቢፀድቅ የኑዛዜ ሰነዱ ዋጋ የሚያገኝበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

እኛችን ወዳለው ጉዳይ ስንመለስም ሟች ባደረጓቸው የተለያዩ ኑዛዜዎች ሙከጡሪ ከተማ ውስጥ ይገኛል የተባለውን ቤት በተመለከተ በማን ገንዘብና ለማን

እንደተገዛ የተለያየ ሐሣብ እንደነበራቸው የኑዛዜ ሰነዶቹ ያሣያሉ፡፡ በ26/01/84 ዓ.ም ተደረገ በተባለው ኑዛዜ ቤቱ በአመልካች ገንዘብ መገዛቱን ጠቅሰዋል፡፡ በሌሎች የኑዛዜ ሰነዶች ግን ቤቱ የተገዛው በሟች ገንዘብ ስለመሆኑ ገልጸዋል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሁኖ በ02/01/84 ዓ.ም ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በውጫሌ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ. G/F/4028/89 በቀን 07/04/90 ዓ.ም ተረጋግጧል፡፡ ቤቱን የገዙትም አመልካች ስለመሆናቸው ይኸው የፍ/ቤቱ ሰነድ ያሣያል፡፡ ከዚህ ሁሉ መገንዘብ የሚቻለው በሙከጡሪ ከተማ ውስጥ ይገኛል የተባለው አከራካሪው ቤት ህጋዊ ባለቤት አመልካች እንጂ ተናዛዡ አለመሆናቸውን ነው፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪዎች ቤቱ የሟች ነው የሚሉበት ምክንያት አመልካች በወቅቱ የነበራቸውን እድሜ መሰረት በማድረግ ገቢ ስላልነበራቸው ቤቱን ሊገዙ አይችሉም በሚል ነው፡፡ ሆኖም ምክንያታቸው ህጋዊ ተቀባይነት የሌለው ነው፡፡ በመሆኑም አከራካሪውን ቤት በተመለከተ ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ ያደረጉት የኑዛዜ ሰነድ ዋጋ ሊሰጠው የሚገባው ሆኖ ስላልተገኘ በዚህ ረገድ ኑዛዜው የፀደቀበት አግባብ ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 01183 የካቲት 03 ቀን 1997 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 38849 ግንቦት 09 ቀን 1999 ዓ.ም የፀናውን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት አሻሽለናል፡፡
2. ሟች ባላምባራስ ዘውዴ ደምሴ በሙከጡሪ ከተማ 01 ቀበሌ ውስጥ በሚገኘው ቁጥሩ 139 በሆነው ቤት ላይ ያደረጉት ኑዛዜ ፈራሽ ነው፤ቤቱን አመልካች የገዙት በመሆኑ የግል ንብረታቸው ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ከሟች ውርስ ያላግባብ ተነቅያለሁ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
4. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 40510

ሰኔ 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መሰሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ቴዎድሮስ መንበሩ

**ተጠሪ፡-** ገ/ሕይወት ታደሰ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የውርስ ንብረት ይገባኛል በሚል የቀረበውን ክስ መሠረት በማድረግ የተደረገውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን፣ ከሣሽ የነበረው አመልካች ነው፡፡ አመልካቹ በተጠሪ ላይ ክስ የመሠረተው ከሟች እናቴ ድርሻ ላይ በውርስ የማገኘውን ንብረት አካፍለኝ በማለት ነው፡፡ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤትም የንብረቱ ግምት ለመሬት ልማት አስተዳደር የላኩለት መሆኑን በመግለጽ ከዚሁ ላይ አመልካች ድርሻውን 1/4ኛ ይሰጠው በማለት አዞአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ባለመስማማት ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረቡ ክርክሩ እንደገና የተሰማ ሲሆን፣ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ንብረቱን እንደገና በመሬት ልማት አስተዳደር በማስገመት አመልካች ከዚሁ ላይ ድርሻውን ¼ኛ እንዲወስድ ወስኖአል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መስከረም 5 ቀን 2001 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ስምምነቱን ሳይገልጽ በባለሙያ የቀረበው የንብረቱ (ቤት) ዋጋ መነሻ ተደርጎ ከዋጋው ግምት ¼ኛው አመልካች ይውሰድ በሚል የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በእናቱ በኩል የሚገኘውን የውርስ ድርሻ እንዲሰጠው ነው የጠየቀው፡፡ የውርስ ክፍያ የተጠየቀበት ሃብት የከተማ ቤት ሲሆን፣ ቤቱ የአመልካች እናት እና ተጠሪ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ ያፈሩት የጋራ ሃብት እንደሆነ በክርክሩ ተገልጾአል፡፡ የአመልካች እናት ከተጠሪ ሦስት ልጆች እንደወለዱና አመልካችን ግን ከሌላ ሰው የወለዱት እንደሆነ አመልካች አረጋግጦአል፡፡ በመሆኑም ለውርስ ክፍፍል የሚቀርበው ቤቱ እንዳለ በሙሉ ሳይሆን፣ ተጠሪ ግማሽ ድርሻውን ካነሳ በኋላ በሚቀረው የቤቱ ግማሽ ላይ ነው፡፡ ይህም ከሟች በተወለዱ አራቱ ልጆች መካከል የሚከፋፈል ነው፡፡ በዚህ ምክንያትም ነው የአመልካች የውርስ ድርሻ ¼ ነው የተባለው፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር እንዳየነው አመልካች ተቃውሞ ያነሳው በቤቱ ግምት ላይ ብቻ ነው፡፡ በሰበር አቤቱታው ግን ድርሻዬን መውሰድ ያለብኝ ቤቱ በሐራጅ ተሽጦ ነው የሚል የመከራከሪያ ነጥብ አንስቶአል፡፡ ይሁንና ከፍ ሲል እንደተገለጸው ቤቱ የመኖሪያ ከመሆኑም በላይ፣ ግማሹ የተጠሪ የግማሽ ¾ኛው ደግሞ የሌሎቹ ሦስት ልጆች ስለሚሆን፣ የ1/4 ድርሻ ላለው አመልካች ሲባል ቤቱን በሐራጅ እንዲሸጥ በማድረግ ተጠሪና ልጆቹን ቤት አልባ ማድረግ የሚመረጥ አይደለም፡፡ ከፍትሕ አኳያ ሲታይም ተገቢ አይሆንም፡፡ በመሆኑም ቤቱ በሃራጅ ሊሸጥ ይገባል የሚለው

የአመልካች ክርክር ከጅምሩም ቢሆን ያልተነሳ እና ከፍትሕ አንፃር ሲታይም ተቀባይነት ሊኖረው ስለማይገባ ውድቅ አድርገዋል፡፡ በሌላ በኩል ግን በመሬት ልማት አስተዳደር ቀረበ የተባለው የቤቱ ግምት የገበያ ዋጋን መሠረት ያደረገ ሳይሆን፣ የግንባታ ዋጋን መሠረት በማድረግ የተሰላ በመሆኑ ይህን ግምት መሠረት ተደርጎ የሚፈጸመው የውርስ ሃብት ክፍፍል ፍትሐዊ ሊባል ይችላል ወይ? የሚለውን ነጥብ ማየቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአከራካሪው ቤት ላይ አመልካችም መብት እንዳለው አላከራከረም፡፡ ከዚህ ንብረት ላይ የውርስ ድርሻውን ማግኘት አለበት ከተባለ ደግሞ በክፍፍል ወቅት ሊጠበቅ የሚገባውን ሁኔታ በጥንቃቄ የሚታይ ነው የሚሆነው፡፡ የአመልካች እናት ድርሻ የሆነው የቤቱ ግማሽ በአራቱም ልጆች መካከል ሲከፋፈል አራቱም ልጆች እኩል ነው የሚታዩት በሌላ አነጋገር ክፍፍሉ የአራቱም ልጆች የእኩልነት መብት ያረጋገጠ መሆን ይገባዋል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም የእኩልነት መብቱ የሚረጋገጠው ክፍፍሉ በምን አይነት መንገድ ቢፈጸም ነው የሚለውን ጥያቄ መመለስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ከላይ እንደተገለጸው አከራካሪው ቤት የተገመተው የገበያን ዋጋ (የወቅቱን የገበያ ዋጋ) መሠረት በማድረግ ሳይሆን የወቅቱን የግንባታ ዋጋ መሠረት በማድረግ ነው፡፡ የግንባታ ዋጋ ማለትም ቤቱን ለመስራት ለሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች መግዣ የሚወጣው እና ለሠራተኞች የሚከፈለው ገንዘብ ብቻ የሚያጠቃልል ነው የሚሆነው፡፡ የገበያን ዋጋ ስንመለከት ግን ከዚህም ያለፈ እንደሆነ ነው መገንዘብ የሚቻለው፡፡ የገበያ ዋጋ ከስሙ እንደምንረዳው ቤቱ ለገበያ /ለሽያጭ/ ቢቀርብ የሚያስገኘውን ዋጋ ነው የሚያመለክተው፡፡ የገበያ ዋጋ ለመገመትም ቤቱ የሚገኝበትን አካባቢ፣ በወቅቱ ክፍፍሉ በሚደረግበት ወቅት ያለውን የገበያ ሁኔታ ወዘተ በተጨማሪነት እግምት ውስጥ ይገባሉ፡፡ ይህ ደግሞ የቤቱን የወቅቱ ዋጋ በማስላት ረገድ የግንባታን ዋጋ ከሚሰላበት ዘዴ የተሻለ /የሰፋ/ መሠረት ያለው አካሄድ ነው፡፡ ሲጠቃለል ንብረቱን የሚከፋፈሉ ወገኖች የእኩልነት መብት በተሻለ ሁኔታ ማረጋገጥ የሚቻለው ንብረቱ(ቤቱ) በገበያ ዋጋ ግምቱ ቢሰላ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በያዝነው ጉዳይ የግንባታን ዋጋ መሠረት በማድረግ ክፍፍሉ እንዲፈጸም በስር ፍ/ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ ሊታረም የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሳ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ.ቁ 01411/99 ጥር 23 ቀን 2001 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 0172/2000 በ3/13/2000 የተሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ 348(1) መሠረት ተሻሽለዋል፡፡
2. አከራካሪው ቤት ለክፍፍል በሚቀርብበት ወቅት በሚኖረው የገበያ ዋጋ መሠረት ግምቱ ከቀረበ በኋላ አመልካች ድርሻውን ¼ኛ ይሰጠው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በሚመለከት ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
4. በዚህ ሰበር ችሎት ውሳኔ መሠረት ይፈጸም ዘንድ ለሥር ፍ/ቤቶች ይጻፍ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የመ/ቁ. 40781

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሒሩት መለሠ

ታፈሠ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ፍቅረሥላሴ ካህሳይ - ጠ/ዳኛቸው ተስፋዬ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ሮማን ታደሰ - ጠ/መንበረስላሴ በዛብህ ቀረቡ፡፡

**ፍ ር ድ**

በዚህ መዝገብ የቀረበው የፍቺ ጥያቄን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪ ለዚህ የሰበር አቤቱታ ምክንያት የሆነውን ክስ ከማቅረባቸው በፊት በግራ ቀኙ መሐከል የነበረው ጋብቻ አውስትራሊያ አገር በሚገኝ ፍርድ ቤት በፍቺ በመፍረሱ የፍቺ ውጤት እንዲሰጥላቸው ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱ የፍቺ ውጤት ለመወሰን በቅድሚያ በኢትዮጵያ ውስጥ የተደረገው ጋብቻ ሊፈርስ ይገባል በማለት አመልካችን ሳይጠራ የተጠሪዋን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል፡፡ ይህን ውሣኔ በመቃወም ተጠሪዋ ያቀረቡት ይግባኝም ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በኂላ ነው ተጠሪ ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ከአመልካች ጋር ጥር 16 ቀን 1984 ዓ.ም. የመሠረቱት ጋብቻ እንዲፈርስ ጥያቄ ያቀረቡት፡፡ አመልካች የተጠሪ አቤቱታ ደርሷቸው የተለያዩ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ መቃወሚያቸውን ውድቅ አድርጎ በአመልካች እና በተጠሪ መሃከል የነበረው ጋብቻ በፍቺ ይፍረስ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ አመልካች ያቀረቧቸው ቅሬታዎች ቀደም ብለው በውሣኔ ያለቁ ናቸው በማለት ሳይቀበላቸው ቀርቷል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ የአመልካች ቅሬታ በአጭሩ፣ የኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ጉዳዩን ለማየት የዳኝነት ስልጣን የላቸውም፣ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የስረ-ነገር ስልጣን የለውም፤ ጉዳዩ ሊዳኝ የሚገባው በአውስትራሊያ ሕግ ነው፣ የኢትዮጵያ ፍ/ቤት ስልጣን አለው ቢባል እንኳን ጋብቻው በፍቺ ፈርሷል፤ የሚል ነው፡፡

ይህ ችሎትም ግራ ቀኙ በአውስትራሊያ አገር ሲኖሩ በዚያው አገር መፋታታቸውን ግራ ቀኙ ሳይክዱ በድጋሚ ፍቺ የመወሰኑ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው በቃል ባደረጉት ክርክር የአመልካች ቅሬታ ቀደም ሲል በውሣኔ ያለቀ ጉዳይ ነው በማለት ተከራክረዋል፡፡ ችሎቱም ጉዳዩን ከያዘው ጭብጥ አኳያ መርምሯል፡፡

አመልካች በግራ ቀኙ መሃከል የነበረው ጋብቻ በአውስትራሊያ አገር በፍቺ ፈርሷል ስለዚህ ድጋሚ ፍቺ የሚወሰንበት ምክንያት የለም ሲሉ ተጠሪ ደግሞ ይህ ክርክር ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኂላ በይግባኝ የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ያፀናው ስለሆነ በውሣኔው ያለቀ ጉዳይ በመሆኑ ድጋሚ ሊታይ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

እኛም ወደ ፍሬ ጉዳዩ ከመግባታችን በፊት በቅድሚያ ተጠሪ አመልካች የሰበር አቤቱታ ያቀረቡበት ጉዳይ ቀደም ሲል በፍርድ አልቋል በማለት ያቀረቡትን መቃወሚያ መመልከቱ ተገቢ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር እንደተደረዳነው ተጠሪ ቀደም ሲል የግራ ቀኙ ጋብቻ በአውስትራሊያ አገር በፍቺ በመፍረሱ የፍቺ ውጤት እንዲወሰንላቸው ጥያቄ አቅርበው ነበር፡፡ ፍ/ቤቱ ደግሞ የአውስትራሊያ ፍ/ቤት በፍቺ እንዲፈርስ የወሰነው

ግራ ቀኙ በዛው አገር ያደረጉት ጋብቻ እንጂ አስቀድሞ በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻ ስላልሆነ የመጀመሪያው ጋብቻ ሳይፈርስ የፍቺ ውጤት ሊጠየቅ አይገባም በማለት የተጠሪን ጥያቄ ውድቅ አድርጓል። ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኝ ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ይግባኛቸው ውድቅ ተደርጓል። ከክርክሩ ሂደት እንደተረዳነው ፍ/ቤቱ ይህንን ውሣኔ የሰጠው አመልካችን ሳይጠራ ነው። በመሆኑም በዚህ ክርክር አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ስላልነበሩ አሁን አመልካች በሚያቀረቡት ክርክር ላይ ፍ/ቤት የመጨረሻ ውሣኔ እንደሰጠ የሚያስቆጥረው አይሆንም። ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት በድጋሚ ክስ እንዳያቀርብ ወይም ክርክር እንዳያቀርብ የሚከለከለው በክርክሩ ተካፋይ የሆነን ወገን ነው።

በሌላ በኩል ግን ተጠሪ በኢትዮጵያ አገር የተደረገው ጋብቻ እንዲፈርስ ባቀረቡት ክስ አመልካች እነዚህን መቃወሚያዎች አቅርበው ፍርድ ቤቱ መቃወሚያዎቹን በብይን አልፎባቸዋል። አመልካች በብይኑ ላይ ይግባኝ ጠይቀው ይግባኙ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀርቷል። በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻ ሊፈርስ ይገባል አይገባም የሚለው ጭብጥ ላይ ፍ/ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው በዚህ ሁኔታ የቀረበው መቃወሚያ ላይ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ነው። ምንም እንኳን አመልካች ባቀረቧቸው መቃወሚያዎች ላይ ብይን የተሰጠና ይህም ብይን በይግባኝ የፀና ቢሆን የፍቺ ጥያቄን አስመልክቶ የተሰጠ ውሣኔ ስለሌለ በዚህ ላይ አመልካች ያቀረቡት ክርክር የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘና በድጋሚ ሊታይ አይገባም ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም። ስለሆነም ተጠሪ አመልካች ያነሱት ክርክር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5 መሠረት ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ያቀረቡት ተቃውሞ ተቀባይነት የለውም።

ወደ ፍሬ ጉዳዩ ስንመለስ ከክርክሩ ሂደት አመልካችና ተጠሪ ጥር 16 ቀን 1984 ዓ.ም. በባሕል ጋብቻ ኢትዮጵያ ውስጥ የተጋቡ መሆኑን እንዲሁም የካቲት 5 ቀን 1985 ዓ.ም. በአውስትራሊያ አገር የብሔራዊ ጋብቻ መፈጸማቸውን ተረድተናል። እንዲሁም የግራ ቀኙ ጋብቻ አውስትራሊያ አገር በሚገኘው የማጅስትሬት ፍ/ቤት በፍቺ መፍረሱንም ግራ ቀኙ አልተካካዱም። እንደውም ተጠሪ ከአመልካች ጋራ ያላቸው ጋብቻ በፍቺ መፍረሱን ተቀብለው የፍቺ ውጤት እንዲወሰንላቸው አቤቱታቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው የነበረ መሆኑን ተገንዝበናል። በእርግጥ የከፍተኛ ፍ/ቤት በአውስትራሊያ አገር የፈረሰው ጋብቻ በዛው አገር የተደረገው እንጂ በአ/አበባ የተደረገው ጋብቻ ባለመሆኑ ይህ ጋብቻ ሳይፈርስ የፍቺ ውጤት ሊወሰን አይችልም በማለት የተጠሪን አቤቱታ ሳይቀበል አልፎታል።

ጋብቻ ማለት አንድ ወንድና ሴት ባልና ሚስት ሆነው አንድ ላይ ለመኖር የሚያደርጉት ሕጋዊ ስምምነት ነው። በኢትዮጵያ ጋብቻ በሶስት ዓይነት መንገድ ሊፈፀም እንደሚችል የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አንቀጽ 1 ያመለክታል። በእነዚህ ስርዓቶች በአንደኛው ጋብቻ ከተፈፀመ በድጋሚ በሌላኛው ስርአት ሊፈጸም የሚገባበት የሕግ ምክንያት አይኖርም። ድጋሚ ተደርጎ እንኳን ቢገኝ ጋብቻው ፀንቶ የሚቆየው የመጀመሪያው ጋብቻ ከተደረገበት ጊዜ ጀምሮ ነው። በአንድ ወንድና ሴት መሃከል የሚደረግ ጋብቻ ፈርሶ እንደገና ካልተፈፀመ በቀር ጋብቻ አንድ እንጂ ሁለትና ከዚያ በላይ ሊሆን አይችልም። በተያዘው ጉዳይ ግራ ቀኙ በኢትዮጵያ ውስጥ በባሕል ከተጋቡ በኋላ በድጋሚ በአውስትራሊያ ጋብቻ ማድረጋቸውን ከክርክር ሂደት ተገንዝበናል። በእርግጥ የሥር ፍ/ቤት እንዳለው አንድ ጊዜ ጋብቻ ከተመሰረተ ሁለተኛ ጋብቻ የሚፈፀምበት የሕግ መሠረት የለም። ተፈጽሞ እንኳን ቢገኝ ጋብቻው ውጤት የሚኖረው የመጀመሪያው ጋብቻ ከተፈፀመበት ጊዜ ጀምሮ ነው። አንድ ጋብቻ ከሚፈርስባቸው ምክንያቶች ውስጥ አንደኛው የፍቺ ውሣኔ ሲሰጥ መሆኑ የቤተሰብ ሕጉ አንቀጽ 75/ሐ/ ያመለክታል። ጋብቻ አንድ እንደሆነ ሁሉ ጋብቻው በፍቺ ሊፈርስ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው። ሁለት የጋብቻ ስርአቶች መከናወናቸውም ሁለት ጊዜ የፍቺ ውሣኔ እንዲሰጥ ምክንያት ሊሆን አይችልም። በመሠረቱ ፍቺ ማለት የሁለት ተጋቢዎችን የትዳር ግንኙት በሕግ መሠረት ማቋረጥ ማለት ነው። በመሆኑም ተጋቢዎቹ ግንኙታቸውን ማቋረጥ ከፈለጉ ጋብቻው በሁለት አይነት ስርአት ስለተፈፀመ ግንኙቱን ለማቋረጥ እያንዳንዱን ጋብቻ አስመልክቶ የፍቺ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው አይሆንም። የሕጉም አላማ ይህ አይደለም። በተያዘው ጉዳይ የሥር ፍርድ ቤቶች ሁለተኛ ፍቺ ለመስጠት ምክንያት ያደረጉት በአውስትራሊያ የሚገኘው ፍ/ቤት ያፈረሰው ሁለተኛው እና በዛው አገር የተደረገውን ጋብቻ እንጂ በኢትዮጵያ የተደረገው ጋብቻን አይደለም። ሁለተኛው ጋብቻ ደግሞ አላስፈላጊና ውጤት የሌለው ጋብቻ ነው በማለት ነው። በመሠረቱ ግራ ቀኙ ጋብቻቸውን መቀጠል ባለመፈለጋቸው ፍ/ቤት ቀርበው ጋብቻቸው በፍቺ እንዲፈርስ ጠይቀው አስወስነዋል። በግራ ቀኙ መሐከል የነበረው ጋብቻ አንድ ብቻ በመሆኑ አውስትራሊያ የተሰጠው የፍቺ ውሣኔ ይህን በመካከላቸው የነበረውን አንድ ጋብቻ እንደፈረሰ ተደርጎ ሊቆጠር ይገባል። ከላይ እንደተደገለፀው ግራ ቀኙ አውስትራሊያ አገር ከሄዱ በኋላ ሌላ የጋብቻ ሥነ ሥርዓት መፈፀማቸው ሁለት ትይዩ /Parallel/ ትዳር ውስጥ ነበሩ ሊያሰኛቸው አይችልም። በመሆኑም በመካከላቸው የነበረው የጋብቻ ግንኙነት አንድ

የመሆኑን ያሕል የሚፈርሰውም በአንድ የፍቺ ውሣኔ ነው፡፡ ለፍ/ቤቱ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት ግራ ቀኙ አውስትራሊያ አገር ሄደው ሁለተኛ ሥነ-ሥርዓት በመፈፀማቸው ብቻ ሁለት የፍቺ ሥነ-ሥርዓት እንዲያከናውኑ ማድረጉ የቤተሰብ ሕግን አላማና መንፈስ የሚከተል አይደለም፡፡ ሁለተኛ ጊዜ የተደረገው ጋብቻ መፍረሱ ምናልባት በፍቺ ውጤት ላይ ክርክር የሚያስነሳ ካልሆነ በቀር የመጀመሪያው የጋብቻ ሥርዓት ባለመፍረሱ የግራ ቀኙ የጋብቻ ግንኙነት አልተቋረጠም ወደሚለው መደምደሚያ አይወስድም፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ጋብቻው በሁለት አይነት ሥርዓት ተፈጽሞ ቢሆን እንኳን ጋብቻው በፍቺ ሊፈርስ የሚችለው አንድ ጊዜ ብቻ እንጂ ሁለት የጋብቻ ሥርዓት በመፈፀሙ ሁለት አይነት ፍቺ ሊኖር አይችልም፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያው ጋብቻ ሥርአት ሳይሆን ሁለተኛ የተደረገው ሥርዓት-በፍቺ መፍረሱ ተጋቢዎቹ እንደተፋቱ አያስቆጥርም በሚል ሁለተኛ የፍቺ ውሣኔ መስጠቱ የሕጉን አላማ የሳተና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካችና ተጠሪ አ/አበባ እና አውስትራሊያ ጋብቻ የፈፀሙ ቢሆንም ግራ ቀኙ የትዳር ግንኙነታቸውን በፍቺ ማቋረጥ ስለፈለጉ በአውስትራሊያ ፍርድ ቤት የፍቺ ውሣኔ አሰጥተዋል፡፡ ይህንንም ፍቺ ሁለቱም ተቀብለውት የራሳቸውን ሕይወት መኖር ቀጥለዋል፡፡ ተጠሪም ቢሆኑ የፍቺ ውጤት ውሣኔ እንዲሰጣቸው ለፍ/ቤት አቤቱታ ማቅረባቸው በግራ ቀኙ መሃከል የነበረው ግንኙነት በፍቺ የተቋረጠ መሆኑን አምነው መቀበላቸውን ያሳያል፡፡ ግንኙነቱ ከተቋጠ ደግሞ አ/አበባ የተደረገው ጋብቻ ለሁለተኛ ጊዜ በፍቺ ሊፈርስ ይገባል የሚባልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ፍ/ቤት አውስትራሊያ አገር በተደረገ የፍቺ ውሣኔ ሕልውና ያጣውን ጋብቻ ፍርድ ቤቱ ውሣኔ እስከሰጠበት ዕለት ድረስ እንደቀጠለ በማሰብ በ12/06/2000 ፈርሷል ማለቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰው የአውስትራሊያው ፍ/ቤት በመካከላቸው የመጨረሻ ውሣኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ ሊሆን ይገባዋል ብለናል፡፡ ከማንደሩ ጋር ተያይዘው ከቀረቡት ሰነዶች በመካከላቸው የነበረው ጋብቻ የፈረሰው ሴፕቴምበር 20/2004 /መስከረም 10 ቀን 1997 ዓ.ም/ መሆኑን ተረድተናል፡፡ በመካከላቸው የሚነሳ የንብረት ክርክር ካለም ይህን ቀን ታሳቢ ማድረግ አለበት ብለናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍ/ቤት በመ/ቁ 53555 የካቲት 12 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሻሽሏል፡፡
2. በአመልካችና በመልስ ሰጪ መካከል የነበረው ጋብቻ ከመስከረም 10 ቀን 1997 ዓ.ም. ጀምሮ ፈርሷል፡፡
3. የፍቺ ውጤትን በተመለከተ ከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ይቀጥላል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 18394

መጋቢት 21 ቀን 1999 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ፍስሀ ወርቅነህ

አብዱልቃድር መሐመድ

አሰግድ ጋሻው

ተሻገር ገ/ሥላሴ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ዝናሽ በቀለ ማንደፍሮ - አልቀረቡም፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** ወ/ሮ ሐረገወይን በቀለ - ቀርበዋል፡፡

በዚህ መዝገብ የተደረገውን የሰበር አቤቱታና ክርክር መሠረት አድርገን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የቀረበው ክርክር የውርስ ሕግ ድንጋጌዎችን አተረጓጎም የሚመለከት ነው፡፡ ለጉዳዩ መነሻ የሆነው ነገር ሟች አቶ በቀለ ማንደፍሮ ለአሁንዋ አመልካች በአርሲ ነገሌ የሚገኘውና በ1967 ዓ.ም. በወጣው አዋጅ ቁ. 47/67 የተወረሰውን ቤት በኑዛዜ መስጠታቸው ኑዛዜውን ፈራሽ ማድረግ አለማድረጉን የሚመለከት ነው፡፡ የአሁን አመልካች ኑዛዜው ሊፈፀም የማይችልና ከሌሎች ወራሾች ጋር እኩል የመካፈል መብቴን የሚነካ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን ይገባል በማለት ከሥር ጀምሮ የተከራከረች ሲሆን መልስ ሰጪ ደግሞ በቤቱ ላይ ሟች አበል ይቀበሉበት ስለነበር ኑዛዜው ፈራሽ የሚሆንበት ምክንያት የለም በማለት ተከራክራለች፡፡ የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ነጥብ ላይ የተለያየ ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ ጉዳዩን መጀመሪያ የተመለከተው የወረዳ ፍ/ቤት ኑዛዜው ይፀናል ሲል ይግባኙ የቀረበላቸው የከፍተኛና የጠቅላይ ፍ/ቤቶች ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባል በማለት ውሣኔ ሰጥተዋል፡፡ የይግባኝ ፍ/ቤቶቹ ኑዛዜው ሊፈርስ ይገባዋል በማለት ውሣኔ ለመስጠት የቻሉት በኑዛዜው የተጠቀሰውና በአርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት የከተማ ትርፍ ቤት ለመንግሥት እንዲሆን በወጣው አዋጅ የተወረሠ በመሆኑ የኑዛዜው ውጤት የአመልካች ከውርስ መነቀልን የሚያስከትል ነው፤ ይህ ደግሞ አመልካች ከወራሾች እኩል እንዳትካፈል የሚያደርግ ነው በማለት ነው፡፡ ጉዳዩን መጨረሻ ላይ ያየው የደቡብ ሕዝቦች ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ችሎት በሌላ በኩል ኑዛዜው የሚፈርስበት ምክንያት የለም በማለት የክልሉን ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ ሽሮአል፡፡ የሰበር ችሎት ኑዛዜው ይጸናል የሚል ውሣኔ ለመስጠት ኑዛዜው የሚመለከተው አርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት የተወረሰ ቢሆንም ሟች አበል ይቀበሉበት ስለነበር ኑዛዜው አበሉን አስመልክቶ ተፈፃሚ ሊሆን ይችላል፤ ከዚህም ሌላ ቤቱ የተወረሰ ቢሆንም ሊመለስ የሚችልበት እድል የለም ሊባል ስለማይችል ኑዛዜው ሊፈፀም በማይችል ጉዳይ ላይ የተረገ ነው ሊባል አይችልም፤ የአመልካች ሕጋዊ ወራሽ መሆን የኑዛዜውን ፈራሽነት የሚያስከትል አይደለም፤ የሚሉትን ምክንያቶች ሰጥቷል የሰበር ችሎቱ አመልካች ኑዛዜው ይፍረስልኝ የሚል አቤቱታ ሳታቀርብ ከፍተኛውና ጠቅላይ ፍ/ቤቶች ኑዛዜው እንዲፈርስ ውሣኔ መስጠታቸው ባልቀረበላቸው ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠታቸውን ስለሚያመለክት ሂደቱ ግድፈት የነበረበት መሆኑንም በፍርዱ አትቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህን የጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ችሎት ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ዝርዝር ሃሣቦችን ያጠቃለለ ሲሆን በዚህን ፍርድ ቤቱ ከያዘው ዋነኛው ነጥብ ጋር ግንኙነት ያለው ቅሬታ በተወረሰ ቤቱ ላይ የተሰጠው ኑዛዜ እንዲፀና መደረጉ የአመልካችን የወራሽነት መብት የሚጎዳ በመሆኑ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡ ለቀረበው የሰበር አቤቱታ የጽሁፍ መልስ ቀርቦ ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል፡፡ የመልሱ ዋነኛ ፍሬ ሃሣብ ኑዛዜው የፀና ነው መባሉ የሕግ ስህተት አይደለም በመሆኑም የሰበር ችሎት የሰጠው ውሣኔ ሊፀና ይገባዋል የሚል ነው፡፡ የመልስ መልሱ የሰበር ማመልከቻውን የሚያጠናክር ነው፡፡

ይህ ችሎት የቀረበለትን ጉዳይ ከውርስ ሕጉ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማያያዝ መርምሮአል፡፡ የሚከተሉትን ጭብጦች አስመልክቶ ሕጉ የሚለውን መመልከት ለውሣኔ አስፈላጊ ሆኖም አግኝቶታል፡፡

1/ ሟች ያደረጉት ኑዛዜ በመንግሥት የተወረሰን ቤት የሚመለከት መሆኑ በኑዛዜው የሚያስከትለው የሕግ ውጤት ምንድነው?

2/ ኑዛዜው ይፀናል ከተባለ በክፍፍሉ ላይ የሚኖረው ውጤት ምንድነው?

እነዚህን ሁለት ነጥቦችና ሌሎች ተጓዳኝ ጥያቄዎች በቅደም ተከተል ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን፡፡

ከሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔዎች ለመገንዘብ እንደቻልነው አርሲ ነገሌ የሚገኘውና ለአሁን አመልካች በኑዛዜ የተተወው ቤት በመንግሥት የተወረሰ መሆኑ አላከራከረም፡፡ በመሆኑም ሟቹ የተናዘዙት የራሳቸው ባልሆነ ንብረት ነው ማለት ነው፡፡ አንድ ሰው በራሱ ባልሆነና ሊያዝበት በማይችል ንብረቱ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚኖረው ሕጋዊ ሁኔታ ምንድነው? የሚለው ጥያቄ በውርስ ሕግ በግልጽ ምላሹ ያገኘ ነው፡፡ የውርስ ሕግ ውስጥ ይህንን ጉዳይ የሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 1047 እንዲህ ይነበባል፡፡

1/ "በኑዛዜው የተደረገው ስጦታ በተለየ ነገር እንደሆነና ሟቹ በሞተበት ቀን በዚህ ነገር ላይ አንዳችም መብት የሌለው እንደሆነ የኑዛዜው ስጦታ ፍርስ ነው፡፡

2/ ስለሆነም ሟቹ ይህን ሁኔታ እያወቀ በኑዛዜው ሰጥቶ እንደሆነ ስጦታው ዋጋ ያለው ይሆናል፡፡

3/ እንደዚህ በሆነ ጊዜ አጣሪው በኑዛዜ የተሰጠውን እቃ ዋጋ መስጠት አለበት"

ከዚህ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው በመርህ ደረጃ ማንም ሰው ምንም መብት በሌለው ንብረት ላይ የተናዘዘ እንደሆነ የተሰጠው ኑዛዜ ዋጋ አይኖረውም፡፡ በሕግ ፊት የሚፀና ኑዛዜ ለመስጠት ሟቹ ኑዛዜ በተደረገበት ንብረት ላይ መብት ሊኖረው ይገባል በሌላ በኩል በንዑስ አንቀጽ /2/ በግልጽ እንደሰፈረው ሟቹ ኑዛዜ በሚያደርጉበት ንብረት ላይ ምንም መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ ስጦታ የሰጠው እንደሆነ በስጦታው ሕጋዊነት የፀና ይሆናል፡፡ በመሆኑም ኑዛዜ አድራጊው መብት ያለው መሆን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ስለዚህ ጉዳይ የነበረው ግንዛቤ በኑዛዜው ፍርስ መሆን አለመሆን ላይ ውጤት ይኖረዋል፡፡ ኑዛዜው ፍርስ የሚሆነው ተናዛዡ ስጦታ ባደረገበት ንብረት ላይ መብት እንደሌለውና ይህም ያውቅ እንዳልነበረ ሲታወቅ ብቻ ነው፡፡ ይህ መደምደሚያ የሚገኘው ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ ሁለት ንዑስ ቁጥሮችን አጣምሮ በማንበብ ነው፡፡

አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተናዛዥ አርሲ ነገሌ በነበረውና ለአሁን አመልካች በስጦታ በሰጡት ቤት ላይ የባቤትነት መብት አልነበራቸውም፡፡ ቤቱ በአዋጅ የተወረሰ በመሆኑና አበልም ይቀበሉበት ስለነበር ሟቹ ቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው እያወቁ ኑዛዜ ማድረጋቸው ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም ኑዛዜው የተሰጠበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ 1047 /2/"ን" መስፈርት የሚያሟላ ነው፡፡ በመሆኑም ምንም እንኳ ቤቱ የተወረሰ በመሆኑ ምክንያት ሟቹ በቤቱ ላይ መብት ባይኖራቸው የኑዛዜ ስጦታውን ያደረጉት ይህ መብት እንደሌላቸው እያወቁ በመሆኑ ኑዛዜው ሊፈርስ የሚባው አይደለም፡፡ ኑዛዜው ፍርስ ሊሆን ይችል የነበረው ሟቹ በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው የማያውቁ መሆኑ ማስረጃ ቢቀርብ ነበር፡፡

በመሆኑም የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልላዊ መንግሥት ጠቅላይ ፍ/ቤት የኑዛዜ ስጦታው ይፀናል በማለት ያቀረበው ምክንያት ትክክል ባይሆንም ውጤቱ ግን ይህም ችሎት የሚስማማበት ነው፡፡ ስለዚህ የአሁን አመልካች በተወረሰ ቤት ላይ የተደረገ ኑዛዜ በመሆኑ ብቻ ኑዛዜ ፍርስ ሊሆን ይገባል በማለት ያቀረበችው ጥያቄ ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ጉዳዩን የተመለከቱት የሥር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው በተወረሰ ሀብት ላይ የተሰጠ በመሆኑ የአመልካችን ከውርስ መነቀል ያስከትላል በማለት የኑዛዜ ስጦታውን ፍስር ማድረጋቸው የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ መሻሩ አግባብ ነው፡፡ አንድ ወራሽ አለአግባብ ተነቀለ የሚባል ቢሆን በውርሱ አከፋፈል ላይ የሚታይ እንጂ በአግባቡ የተሰጠን ኑዛዜ ፈራሽነት የሚያስከትል አይደለም፡፡

ቀጥሎ መታየት ያለበት ግን የኑዛዜ ስጦታው የፀና መሆን በወርስ ክፍፍሉ የሚያስከትለው ውጤት ምንድነው? የሚለው ጥያቄ ነው። ይህን ጥያቄ በአግባቡ ለመመለስ ተያያዥነት ያላቸውን የውርስ ሕግ ድንጋጌዎች መዳሰስ ያስፈልጋል። በቅድሚያ ከላይ የጠቀስነው የአንቀጽ 1047/3/ ይዘት መመርመር ተገቢ ነው። የዚህ ድንጋጌ መልእክት አንድ ሰው በአንድ ንብረት ላይ መብት የሌለው መሆኑን እያወቀ የተናዘዘ እንደሆነ ኑዛዜው የሚፀና ከመሆኑም ባሻገር የውርስ አጣሪው የዚህ ንብረት ግምት መስጠት እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው። በዚህ ደንብ መሠረት ተናዛዥ በስጦታ የሰጠው ንብረት በውርሱ ሀብት እንኳን ባይኖር ከውርሱ ሀብት በዋጋ ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት ወይም ገንዘብ ለስጦታ ተጠቃሚው መስጠት ሕጉ ያስቀመጠው ሥርዓት ነው። ሆኖም ይህ ደንብ ተፈፃሚ የሚሆነው ለውርስ ስጦታ /legacy/ ብቻ ነው። በመሆኑም አንድ ኑዛዜ ውስጥ ያለው የተናዛዡ ቃል የውርስ ስጦት /legacy/ መሆን አለመሆኑን መለየት ለዚሁ ድንጋጌ አፈፃፀም መሠረታዊ ነው። አንድ የኑዛዜ ቃል የውርስ ስጦታ መሆን አለመሆኑን ለመለየት ሌሎች የውርስ ሕጉን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል። አሁን ከያዝነው ጉዳይ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀጽ 913 ነው።

<u>913 የኑዛዜ ስጦታና የክፍያ ደንብ</u>

የኑዛዜው ቃል የተናዛዥን ተቃራኒ ሐሣብ የሚገልጽ ካልሆነ በቀር ከውርስ ሃብት አንድ ድርሻን ወይም አንድ ንብረትን ሚቹ ለወራሾች መስጠቱ ተራ የሆነ የክፍያ ደንብ እንጂ እንደ ኑዛዜ ስጦታ ነው ተብሎ አይቆጠርም።

የዚሁ አንቀጽ የእንግሊዝኛ ትርጉም እንደሚከተለው ይነበባል።

<u>913 Legacies and rules of partition</u>

An Assignment of a portion of the succession or of property forming part of such succession made by the testator to one of her heirs shall not be deemed to be a legacy but a mere rule for partition, unless the contrary in tension of the testator emerges from the disposition.

ከዚህ ድንጋጌ ለመገንዘብ የሚቻለው በኑዛዜው የሚከናወኑ ተግባሮች <u>የኑዛዜ ስጦታ</u> /legacy/ ወይም <u>የክፍያ ደንብ</u> /Rule of Partition/ ሊሆኑ እንደሚችሉ ነው። በመርህ ደረጃ አንድ ሰው ከውርስ ሀብቱ መካከል አንድን ንብረት ለወራሾቹ መስጠቱ የኑዛዜ ስጦታ አያሰኘውም። ይልቁንም ይህ አይነት ኑዛዜ ሕጉ የሚቀበለው እንደ አንድ የክፍያ ደንብ ነው። በመሆኑም አንድ አውራሽ ለወራሹ አንድን ንብረት ቢናዘዝለት የኑዛዜው አፈፃፀም የስጦታ /legacy/ አፈፃፀምን በመከተል ሳይሆን የክፍያ ደንብ /Partition/ በመከተል የሚከናወን ይሆናል።

ኑዛዜው ስጦታን /legacy/ የሚመለከት ከሆነ በፍትሀብሔር ሕጉ አንቀጽ 942 ጀምሮ ባሉ አንቀፆች መሠረት በማጣራት /liquidation/ ሥርዓት የሚከናወን ሲሆን ክፍያ ግን ክፍፍልን /partition/ በሚመለከቱና ከአንቀጽ 1060 ጀምሮ ባሉ ድንጋጌዎች መሠረት የሚስተናገድ ነው።

አሁን በቀረበልን ጉዳይ በአርሲ ነገሌ የሚገኘው ቤት በኑዛዜው ይሰጥልኝ የተባለው የሟች ልጅ መሆንዋ ለተረጋገጠው ለአሁንዋ አመልካች ነው። አመልካች ወራሽ በመሆንዋ ከላይ በተጠቀሰው አንቀጽ 913 መሠረት ኑዛዜው የስጦታ ውል ሳይሆን የክፍያ ሥርዓት የያዘ ነው ማለት ነው ኑዛዜው የስጦታ ነው የሚባል ቢሆን ኖሮ በፍትሀብሔር ሕግ ቁጥሮች 1037-1051 መሠረት እንዲሁም 1047/3/ መሠረት የተጠቀሰው ንብረት ወይም ግምቱ ለስጦታ ተጠቃሚው በቅድሚያ ይሰጣል። ሆኖም ከላይ እንደተጠቀሰው የአሁን አመልካች ወራሽ በመሆንዋ የኑዛዜው ቃል ክፍፍልን በሚያመለክቱ ድንጋጌዎች መሠረት የሚስተናገድ ነው። በዚህ ረገድ ከአንቀጽ 1117 ጀምሮ ያሉት ድንጋጌዎች አግባብነት አላቸው አንቀጽ 1017 አባትና እናት ወይም ሌሎች ወደላይ የሚቆጠሩ ወላጆች ለልጆቻቸውና ለሌሎች ተወላጆች ሀብታቸውን ለመስጠትና ለማከፋፈል እንደሚችሉ ይደነግጋል። ይህ ክፍፍል ሥርዓት አንድን ተወላጅ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር ጥያቄ ማቅረብ እንደማይችል በአንቀጽ 1123 ተደንግጓል። አንቀጽ 1123/1/ እና በስጦታ አከፋፈል ውስጥ ተቃራኒ ቃል ከሌለ በቀር ወደታች ከሚቆጠሩ ተወላጆች አንዱ ከሚደርሰው ከሩብ የበለጠ ጉዳት ደርሶበት እንደሆነ የስጦታ አከፋፈሉ እንዲቀር ለመጠየቅ ይችላል" ይላል።

ከቀረበልን ጉዳይ ለመገንዘብ እንደቻልነው ሟቹ ኑዛዜአቸው ላይ ያሉዋቸውን ቤቶች ለልጆቻቸው አከፋፍለዋል፡፡ የዚህ ዓይነት ክፍፍል ሕጉ የሚደግፈው ቢሆንም ማንኛውም ልጅ ከአንድ አራተኛ በላይ ጉዳት የሚያደርስ ከሆነ የክፍፍል ሥርዓቱ እንዲፈርስ መጠየቅም ሆነ በዚህ መሠረት ውሣኔ መስጠት ይቻላል፡፡ ከመዝገቡ ጋር ከተያያዘው የኑዛዜ ኮፒ ለመገንዘብ እንደቻልነው አውራሹ የነበሯቸውን ቤቶች ሲያከፋፍሉ ለአሁንዋ አመልካች የሰጡት አርሲ ነገሌ የሚገኘውና ተወረሰ የተባለውን ቤት ሲሆን ለመልስ ሰጪ የሰጡት ሌላ በሆሳዕና የሚገኘውን ቦታና ሲኖሩበት የነበረውን ቤት ነው፡፡ ለአመልካች የተሰጠው ቤት የተወረሰ መሆኑ በመረጋገጡ ለአመልካቿ በንብረት ክፍፍል የሚደርሳት ሀብት ከአንድ አራተኛ በላይ የሚጎዳት ከሆነ ክፍፍሉ በአንቀጽ በ1123 መሠረት መስተካከል ይኖርበታል፡፡ አመልካች ይህን አንቀጽ ባትጠቅስም ኑዛዜው እንዲፈርስላት የጠየች በመሆኑና ትክክለኛውን አንቀጽ መጥቀስ የማይጠበቅባት በመሆኑ ያቀረበችው ጥያቄ ከዚህ ድንጋጌ አንፃር መስተናገድ ነበረበት፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ይህን አላደረጉም፣ በመሆኑም ውሣኔአቸው ከላይ በተሰጠው ዝርዝር ምክንያት ሊለወጥ የሚገባው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የደረሰባት ጉዳት ምን ያሕል መሆኑ በሥር ፍርድ ቤቶች ያልተጣራ በመሆኑ ለወራሾች የተከፈለው ንብረት ግምት አስልተው ለአሁን አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ እንዲሰጡ መደረጉ አግባብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ለማጠቃለል የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ኑዛዜው ይፀናል በማለት የሰጠው ውሣኔ ከላይ በተሰጠው ዝርዝር ምክንያት ሊሻሻል የሚገባው ነው፡፡ ኑዛዜው የአሁንዋን አመልካች ከአንድ አራተኛ በላይ ስለሚጎዳት ጠቅላይ ፍ/ቤቱ ይህን የጉዳት መጠን የሚያስተካክል የአከፋፈል ሥርዓት ሊከተል ይገባል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ጠቅላይፍ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 5017 ጥቅምት 25 ቀን 1997 የተጠሰው ውሣኔ የፍትሐብሔር ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡

2/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ለአሁንዋ አመልካችና መልስ ሰጪ የተሰጠውን ንብረት ግምት እንዲሰላ አድርጎ የአሁንዋ አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ እንድታገኝ ያድርግ፡፡

3/ ኑዛዜው በአጠቃላይ ፍርስ ባይሆንም ከላይ በተራ ቁጥር 2 በተጠቀሰው መሠረት ሟቹ የሰጡት የክፍፍል ሥርዓት አመልካች የንብረቱ አንድ አራተኛ ታግኝ በሚል ተሻሽሏል፡፡

4/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ውሣኔው መሻሻሉን እንዲያውቀው የውሣኔ ኮፒ ይላክለት፡፡

5/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# ውል

የሰ/መ/ቁ. 35472

ጥቅምት 6 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ መሐመድ ካሣሁን - ጠበቃ አረጋኸኝ መርዕድ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሣልሀዲን ኑር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በሰሜን ጎንደር መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን ተጠሪ በአመልካችና በሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ ባቀረቡት ክስ አቶ ኑር ሁሴን ካሴ ከተባሉት ሽሪኬ ጋር በመሆን በደንቢያ ወረዳ ልዩ ስሙ "ዋዋ" በተባለ ቦታ መሬት ለማልማት በነበረን ፍላጎት 17 ሄክታር መሬት በኪራይ ተሰጥቶን የኢንቨስትመንት ፈቃድ አውጥተን ከሽሪኬ ከአቶ ኑርሁሴን ካሴ ጋርም ሰኔ 5 ቀን 1988 ዓ.ም የህብረት ሽርክና ውል ተፈራርመን ከዚያም በተፈቀደልን መሬት ላይ አስፈላጊ የሆነውን የማለስለስና የማዘጋጀት ሥራ ሠርቼ በተዘጋጀው መሬት ላይ የተለያየ እህል ዘርቼበት እንዳለ ያለምንም ማስጠንቀቂያ የውሉ ጊዜ ሣይደርስ መሬቱን ከተዘራው እህልና ከተለያዩ የግብርና መሣሪያዎች ጋር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት በመውሰድ ለሁለተኛ ተከሣሽ አሣልፎ ሰጥቷል፤ በማለት፣ ይገባናል ያሉትን የእህልና የጉልበት ዋጋ በመዘርዘር በድምሩ ብር 71.990 እንዲከፈላቸውና መሬቱም እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡

የዞኑ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ በአንደኛ ተከሣሽና በአቶ ኑርሁሴን ካሴ መካከል በተደረገው የመሬት ኪራይ ውል መሠረት ውሉ ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች አንዱና ዋናው በኪራይ ውሉ አንቀጽ 11/ለ/ መሠረት ተከራዩ ለአከራዩ መክፈል የሚገባውን የመሬት ኪራይ ለሁለት ተከታታይ ዓመታት ሣይከፈል በሚቀርበት ጊዜ እንደሆነ የተመለከተ ሲሆን ተከራዩም በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የመሬት ኪራዩን መክፈል ሲገባቸው ባለመክፈላቸው አንደኛ ተከሣሽ ውሉን እንዳቋረጠ ፍ/ቤቱ ስለተገነዘበ በተቋረጠ ውል ላይ በመመስረት ከሣሽ ያቀረቡት ክስ አግባብነት የለውም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ፣ በተደረገው የመሬት ኪራይ ውል መሠረት ተከራዩ መክፈል የሚገባውን የመሬት ኪራይ በየጊዜው ሲከፍል እንደነበር በአስረጂነት የቀረቡት ሰነዶች የሚያረጋግጡ ሆኖ ሣለ የሥር ፍ/ቤት ውሉን ሊያቋርጥ የሚችል ነገር መኖሩን ሣያረጋግጥ በአንደኛ መ/ሰጭ /የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት/ የቀረበውን መከራከሪያ ብቻ በመቀበል በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ተቋርጧል በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ነው በማለት ሽሮ ለክሱ ምክንያት የሆነው መሬት ለይግባኝ ባይ /ለአሁን ተጠሪ/ እንዲመለስለት በማለት ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ ግን የሥር ፍ/ቤት በማስረጃ አጣርቶ እንዲወስን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መልሷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ አመልካች /የሥር ሁለተኛ ተከሳሽ/ ከወረዳው ገጠር ልማት ጽ/ቤት ጋር ባደረገው ውል ያገኘውን መሬት ለተጠሪ

እንዲያስረክብ መወሰኑ ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡ ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ከሥር አንደኛ ተከሣሽ ከደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ጋር ባደረጉት ውል መሠረት የያዙትን መሬት ለተጠሪ እንዲያስረክቡ በአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት መወሰኑ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው ተጠሪ በአመልካችና በሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ ክስ ያቀረቡት በኪራይ ውል መነሻነት የተያዘውን 17 ሄክታር መሬት አንደኛ ተከሣሽ ለሁለተኛ ተከሣሽ /የአሁን አመልካች/ ያለአግባብ አሣልፎ የሰጠ ስለሆነ መሬቱን መልሰው ያስረክቡኝ ኪሣራም እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ነው፡፡

የመሬት ኪራይ ውሉ ተደርጎ የነበረው በአቶ ኑርሁሴን ካሴና በወረዳው ግብርና ልማት ጽ/ቤት በኩል የነበረ ቢሆንም እስከ 1994 ዓ.ም ድረስ በየዓመቱ ውሉ ሲታደስ የነበረው በተጠሪ በአቶ ሣልሀዲን ኑር ስም ስለነበር ይህ ሁኔታ ተጠሪን ተዋዋይ ወገን እንዳደረጋቸው ስለሚያስገነዝብ ውሉ በተጠሪ ላይ የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ሊሆን ስለሚችል ይህንኑ ውል መሠረት በማድረግ ክስ ማቅረባቸው ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅምት /vested interest/ እንዳላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

ተጠሪ ክስ ባቀረቡበት ነገር መብትና ጥቅም አላቸው ከተባለ ውሉን አስገድዶ ለማስፈፀም /forced performance/ ያቀረቡት ክስ ከሕጉ አኳያ ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ መርምረናል፡፡

የሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የውሉ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ከተጠሪ ላይ በመውሰድ ለአመልካች ስለማከራየቱ ግራ ቀኙን አላከራከረም፡፡

የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት የመሬት ኪራይ ውሉን በተናጠል መሠረዙ /unilateral cancellation/ አግባብነት የለውም ቢባል ውሉ የተሰረዘበት ወገን በውሉ መሠረዝ ምክንያት የደረሰበት ኪሣራ ቢኖር ይህን ከመጠየቅ አልፎ የውሉን ቃል በመፃረር የሠራውን ሥራ እንዲያፈርስና እንደ ውሉ ተገዶ እንዲፈጽም መጠየቅ ስለመቻሉ ከሕጉ አንፃር ተመልክተነዋል፡፡

በዚህም መሠረት ውልን አስገድዶ ለማስፈፀም በሚቀርብ አቤቱታ በውሉ አለመከበር የተነሣ በባለገንዘቡ ላይ የደረሰው ወይም ይደርሣል ተብሎ የሚገመተው ኪሣራ ከባለእዳው ቀጥተኛ የውል አፈፃፀም በስተቀር በጉዳት ኪሣራ መልክ ፈጽሞ ሊካስ የማይችል በሚሆንበት ጊዜ እንደሆነ እንደዚሁም እንደ ውሉ ይፈፀምልኝ ብሎ ለሚጠይቀው ተዋዋይ ወገን የተለየ ጥቅም በሚሰጠው ጊዜና አፈፃፀሙም የባለእዳውን የግል ነፃነት የማይነካ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ መሆኑን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 ድንጋጌ መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የውሉ ጊዜ ከመጠናቀቁ በፊት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ይኼው 17 ሄክታር መሬት ከተጠሪ ያለአግባብ ተነጥቆ ለአመልካች ተሰጥቷል ቢባል እንኳን በተጠሪ ላይ የደረሰው ወይንም ወደፊት ይደርሣል ተብሎ የሚጠበቀው ኪሣራ በጉዳት ኪሣራ መልክ ሊካስ የሚችል በመሆኑ ተጠሪ ኪሣራ ከመጠየቅ አልፈው መሬቱን ተከሣሾች ተገደው ሊያስረክቡኝ ይገባል በማለት ያቀረቡት ክስ በውል አፈፃፀም የተለየ ጥቅም /special interest/ ሣይኖራቸውና በአጠቃላይም ሕጉ ውልን አስገድዶ ስለማስፈፀም ከደነገገው መርህ ጋር የማይጣጣም በመሆኑ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሥር ተከሣሾች መሬቱን ለሥር ከሣሹ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

**<u>ው ሣ ኔ</u>**

1/ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 08167 ታህሣሥ 24 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት የሥር ተከሣሾች ለሥር ከሣሽ ሊያስረክቡ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመበት ይህንኑ የውሣኔውን ክፍል በመሻር የኪሣራ ክፍያ ጥያቄውን በተመለከተ በሰሜን ጎንደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በኩል ታይቶ እንዲወሰን ጉዳዩን ወደ ሥር ፍ/ቤት መመለሱ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

2/ አመልካችም ሆነ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን መሬት ለተጠሪ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡ ይፃፍ፡፡

3/ ይህ ፍርድ የሰበር አቤቱታ ባላቀረበው የደንቢያ ወረዳ ግብርና ልማት ጽ/ቤት ላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 331 መሠረት ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 34803

ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** መ/ር መኳንንት ወረደ- ወኪል ጌታቸው ወረደ - ቀርበዋል፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1/ መስከረም ዳኛው

2/ ሃይለየሱስ ዳኛው

3/ አዳነች ዳኛው

4/ ዙሪያሽወርቅ ዳኛው

ሞግዚት አቶ ጥጋቡ መኮንን - ቀርበዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኂላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው የደቡብ ጎንደር መስተደድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ. 11282 ሰኔ 04/1999 ዓ.ም. የሰጠውን ፍርድ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114 ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ በመሻሩ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው በሚል ነው፡፡

የአሁኑ አመልካች በስር ፍርድ ቤቶች ተከሣሽና መልስ ሰጭ እንዲሁም የአሁን ተጠሪዎች በስር ፍርድ ቤቶች ከሳሾችና ይግባኝ ባዮች በመሆን እየተከራከሩ የመጡ ሲሆን የአሁን ተጠሪዎች በሥር ፍርድ ቤት ያቀረቡት ክስ መሠረታዊ ይዘቱ ደግሞ በደቡብ ጎንደር መስተደድር ዞን በእብናት ከተማ ቀበሌ 01 የሚገኘውን የአውራሽ አባታችን አቶ ዳኛው አስፋው የሆነውን አዋሳኞቹ በምስራቅ የወ/ሮ እንዬ ጥጋቡ ቤትና ቦታ፣ በምዕራብ የአቶ አስማረ አየለ ቤትና ቦታ፣ በሰሜን የሊቀ ትጉሃን ፍስሃ እርቂዬ ቤትና ቦታ እንዲሁም በደቡብ የመልዛ አውራ መንገድ የሆነ ቤትና ቦታ ተከሣሽ በኪራይ እየተጠቀመበት ከቆየ በኂላ አባታችን ሲሞት ሊያስረክበን ስላልቻለ ቤቱን ያስረክበን ያልተከፈለ የቤቱ ኪራይም ይከፈለን የሚል ነው፡፡

ስር ተከሣሹም በሰጡት መልስ የተጠቀሰውን ቤት ከሟች ዳኛው አስፋው ሃምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተፃፈ የሽያጭ ውል በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ ሸጠውልኝ ስሙን ሳያዞሩልኝ በስራ ምክንያት ወደ ሰሜን ጎንደር ተዛውረው እንደሞቱ በመግለጽ የከሳሾች ክስ ሕጋዊ ያልሆነ ጥቅምን ለማግኘት ታስቦ የቀረበ ስለሆነ በቂ ኪሣራ ተቆርጦልኝ በነፃ ልሰናበት ይገባል ብለዋል፡፡

የስር ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን ወገኖች ክርክር በሰውና በጽሁፍ ማስረጃዎች አጠናክሮ ከመረመረ በኂላ የደረሰበት ማጠቃለያ ስር ተከሣሽ ከከሳሾቹ አውራሽ አከራካሪውን ቤት ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተፃፈ ውል በሕጋዊ መንገድ በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ እንደገዛና ገገርም ብር 4000 /አራት ሺህ/ ወዲያውኑ ለሻጭ

ማለትም ለአቶ ዳኘው አስፋው እንደከፈሉና ቀሪው ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ሻጭ የቤቱን ስም በገዢ ሲያዛውሩ እንደሚሰጥ እንደተዋዋሉ ከገለፀ በኋላ ውሉ በሕጋዊ መንገድ የተፈፀመ በመሆኑ ተከሳሹ ቤቱን ለከሣሾች የሚመልሱበት ምክንያት እንደሌለ ነገር ግን ሳይከፍሉ የቀሩትን ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ለከሣሾቹ እንዲከፍሉና ቤቱ በተከሣሹ ስም መዛወር እንዳለበት ወሰነ።

የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ የቀረበውን ክርክርና ውሣኔ በይግባኝ ቀርቦለት ካከራከረ በኋላ በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114፣ ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ የግራ ቀኙ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል በሚመለከተው ውል አዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ያልተደረገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሠረት ውል ነበር ማለት እንደማይቻል በአጠቃላይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 21448 በሰጠው ውሣኔ ያስቀመጠውን የሕጉን አተረጓጎም የሚፃረር የቤት ሽያጭ ውል በመሆኑ ውድቅ እንደሆነ በመግለጽ የሥር ፍ/ቤቱን ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በመሻር ቤቱ ለስር ከሳሾች /ይግባኝ ባዮች/ ሊመለስላቸው ይገባል ብሏል።

ከላይ የሰፈረው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት አመልካች ጥቅምት 23/2000 ዓ.ም. የተፃፈ አቤቱታ ወደ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም በአመልካቹና በተጠሪዎቹ አውራሽ /አባት/ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል በተዋዋዮቹ ወገኖች መካከል እንደ ሕግ ስለሚቆጠር የምዝገባ አስፈላጊነት በ3ኛ ወገኖች ዘንድ ውጤትን እንዲያስገኝ ሲባል እንጂ የተደረገውን የሽያጭ ውል ሊያፈርስ አይገባም፣ ይህ ሃሣብም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 ተመልክቷል፣ በስር ፍርድ ቤት የቀረበው ክስ አመልካች ቤቱን በኪራይ መልክ እንደያዝኩ በማስመሰል እንድለቅላቸው የሚጠይቅ ሆኖ እያለ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ግን ከተያዘው ጭብጥ በመውጣት ውሉ ዋጋ እንደሌለው ለፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 ትርጉም ሰጥቶ ማለፉ አግባብነት የለውም፣ ውሉ ይፈርሳል እንኳ ቢባል አመልካች ለተጠሪዎቹ አውራሽ ማለትም ለሻጭ የከፈልኩት ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በምን ሁኔታ መተርጎም እንዳለበት ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ በዝምታ ማለፉ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው።

ተጠሪዎችም በሞግዚታቸው በኩል የካቲት 14/2000 ዓ.ም. የተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን አጭር ይዘቱም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ፍርድ የሚነቀፍበት አንዳችም ምክንያት ባለመኖሩ እንዲፀናላቸው፣ አመልካች ለሟች አቶ ዳኘው አስፋው ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በቤቱ ሽያጭ ምክንያት ከፍለው እንደነበር ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ይህ ገንዘብ እንዲመለስላቸው መጠየቃቸው አግባብነት የለውም፣ ይልቁንስ አመልካች በኪራይ መልክ የያዙትን ቤት የ4 ዓመት ኪራዩን ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ ስላልከፈሉ እንዲከፍሉ ሆኖ ፍርድ ይሰጠን፣ ወጪና ኪሣራችንም ይታሰብልን የሚል ነው።

አመልካችም መጋቢት 12/2000 ዓም በሰጡት የመልስ መልስ ተጠሪዎች እርስ በርሱ የሚምታታ የኪራይ ጥያቄ ሊያቀርቡብኝ አይችሉም ያሉ ሲሆን ቀሪው በአቤቱታቸው ውስጥ የዘረዘሯቸውን ሃሣቦች የሚያጠናክሩ በመሆናቸው ደግሞ መዘርዘር ሳያስፈልግ ታልፏል።

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የግራ ቀኙን ወገኖች የክርክር አመጣጥ ከላይ እንደተቀመጠው ከተገነዘበ በኋላ፡-

1. በአመልካችና የተጠሪዎች ወላጅ አባት በሆኑት በአቶ ዳኛው አስፋው መካከል ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ሕጋዊ ነው ወይስ አይደለም?
2. ውሉ በሕግ መሠረት ያልተደረገ ነው የሚባል ከሆነ አመልካች በውሉ መፈፀም ምክንያት ለተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ የከፈሉት ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ሊመለስላቸው ይገባል ወይስ አይገባም?
3. ተጠሪዎች በመልሳቸው አመልካች እንዲፍላቸው የጠየቁት የ4 ዓመታት የአከራካሪው ቤት ኪራይ ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ/ የሕግ መሠረት አለው ወይስ የለውም? የሚሉትን ጭብጦች በመመስረት ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሯል።

የመጀመሪያውን ጭብጥ በተመለከተ የግራ ቀኙን ወገኖች እያከራከረ ያለው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውል በመካከላቸው መኖር ወይም ያለመኖር ሲሆን አመልካች ከተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. በተደረገ ውል በብር 7250 /ሰባት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሣ ብር/ ቤት እንደገዙ የሚያመለክተው ጽሁፍ ወደሚመለከተው ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው አካል ወይም ወደ ፍርድ ቤት ቀርቦ የተመዘገበ አይደለም። ምንም እንኳ ሻጭና ገዢ እንዲሁም ምስክሮች

በውሉ የፈረሙ ቢሆንም ይህ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ሕጋዊ ለመሆን ከላይ የተጠቀሱት አካላት ዘንድ ቀርቦ የመመዝገቡን አስገዳጅነት የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አስቀምጦታል፡፡ የምዝገባው ሂደት ባልተሟላበት ሁኔታ ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረቱ ሽያጭ ሕጋዊ ሊባል እንደማይችል የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ሚያዝያ 30/1999 ዓ.ም. በሰጠው ፍርድ ግልጽ ትርጉም እንደሰጠበት ነው፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጣቸው የመጨረሻ ፍርዶችም በፌዴራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤቶች ወይም የተለያዩ እርከኖቻቸው ተቀባይነት ሊያገኙ እንደሚገባ አዋጅ ቁጥር 454/1997 አስፍሯል፡፡ ከላይ የተጠቀሰው የሰበር ችሎት ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ እና 2878 ያላቸውን ልዩነት አስፍሯል፡፡ ይኸውም የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት እንዲደረግ የማድረጉ አስፈላጊነት በተዋዋይ ወገኖቹ መካከል የሚፀና ውል መኖሩን ለማረጋገጥ ሲሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2878 የተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረት ምዝገባ ዓላማ ደግሞ ውሉ በሦስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት ለማምጣት ሲባል ነው፡፡ ከዚህ የሕግ ይዘትና አተረጓጐም አኳያ የአሁኑ አመልካች የሽያጭ ውሉ በአዋዋይ አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት አለመፈፀሙ ከተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ የገዛሁትን አከራካሪውን ቤት ውጤት የሌለው አያደርግብኝም በማለት ያቀረቡት መከራከሪያ ነጥብ ተቀባይነት የለውም፡፡ ስለሆነም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን ጭብጥ በሚመለከት የሰጠው ትንታኔ ትክክለኛ በመሆኑ በአመልካች ጥያቄ ላይ የፈፀመው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም፡፡

ሁለተኛውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ከላይ እየተጠቀሰ የመጣውን አከራካሪ ውል መሠረት በማድረግ አመልካች የተጠሪዎች አባት ለሆኑት ለአቶ ዳኛው አስፋው ብር 4000 /አራት ሺህ/ እንደሰጧቸውና ብር 3250 /ሦስት ሺህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር/ ቀርቷቸው እንደነበር የደቡብ ጎንደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሰነድና በሰው ምስክር እንዳረጋገጠው ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት አከራካሪው ውል ሕጋዊ አይደለም የሚል ውሣኔ ሲሰጥ አመልካች ለተጠሪዎች አባት የከፈሉት ከላይ የተጠቀሰው ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ እንዲመለስላቸው አብሮ መወሰን አልነበረበትም ወይ? የሚለውን ነጥብ በተመለተ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 እንዳስቀመጠው ተዋዋይ ወገኖቹን ወደ ነበሩበት የመመለስ ተግባር መከናወን እንዳለበት ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አኳያ የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አመልካች ለተጠሪዎች አባት በአከራካሪው ውል ምክንያት የከፈሉትን ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ተጠሪዎች እንዲመልሱላቸው አለመወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡

በመጨረሻም የተቀመጠውን ጭብጥ በተመለከተ ደግሞ ተጠሪዎች በዚህ ሰበር ችሎት በሰጡት መልስ አመልካች ያልከፈሉትን የ4 ዓመት የቤት ኪራይ በጠቅላላ ብር 4800 /አራት ሺህ ስምንት መቶ ብር/ ሕጋዊ አግባብነቱ ሲታይ ተጠሪዎቹ ይህንን ነጥብ በተመለከተ የስር ፍርድ ቤቱ የሰጠውን ውሣኔ በመቃወም ያቀረቡት ይግባኝ የለም፡፡ ይህንን ጥያቄ እያቀረቡ ያሉት አመልካች ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ መነሻነት እየተካሄደ ባለው ክርክር ነው፡፡ ይግባኝ ወይም አቤቱታ ባላቀረቡበት ሁኔታ የቤቱ ኪራይ እንዲከፈላቸው ተጠሪዎች መጠየቃቸው ሕጋዊ አካሄድን የተከተለ ባለመሆኑ ከዚህ አኳያ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለም ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 13114 ጥቅምት 20/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት በአብላጫ ድምጽ ተሻሽሏል፤ ይፃፍ፡፡
2. በአመልካችና የተጠሪዎች አባት /አውራሽ/ በሆኑት በአቶ ዳኛው አስፋው መካከል ሐምሌ 04/1996 ዓ.ም. የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 አኳያ ሲታይ ውል ለማዋዋል ስልጣን ከተሰጠው አካል ያልተመዘገበ ወይም በፍርድ ቤት ፊት ያልተፈፀመ በመሆኑ አመልካች ውሉ እንዲጸናላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ ነገር ግን በሽያጭ ውሉ ምክንያት አመልካች ለተጠሪዎች አባት የከፈሉትን ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815 መሠረት ተጠሪዎች ሊመልሱላቸው ይገባል፡፡
3. ተጠሪዎች ይግባኝ ወይም አቤቱታ ሳያቀርቡ በመልሳቸው የጠየቁት የቤት ኪራይ ጥያቄ አግባብ ያለው የክርክር ሂደት ያልተከተለ በመሆኑ ውድቅ ሆኗል፡፡ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
   መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

## <u>የልዩነት ሀሣብ</u>

እኔ ስሜ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔና በተከተለው የሕግ ትርጓሜ ባለመስማማት እንደሚከተለው የልዩነት ሀሣቤን አስፍሬያለሁ፡፡

አብላጫው ድምጽ በሰጠው ውሣኔ በዝርዝር እንደተገለፀው በሥር ፍርድ ቤት ከሣሽ በዚህ ፍርድ ቤት ተጠሪ በሆኑት የእነ መስከረም ዳኘው አውራሽና አባት አቶ ዳኘው አስፋውና በአመልካች ሐምሌ 4 ቀን 1996 ዓ.ም. በጽሑፍ በተደረገ የቤት ሽያጭ ውል፣ አመልካች ቤቱን በብር 7250 /ሰባት ሺ ሁለት መቶ ሀምሳ ብር/ ገዝተዋል፡፡ በዚህ የውል ስምምነት መሠረት አመልካች ለተጠሪዎች አባት ብር 4000 /አራት ሺ ብር/ በመክፈል ቤቱን ተረክበው በይዞታቸው አድርገው እየተጠቀሙበት የሚገኙ ሲሆን በውላቸው መሠረት ቀሪውን ብር 3250 /ሶስት ሺ ሁለት መቶ ሀምሣ ብር/ የቤቱ ስመ ንብረት ሲዛወር አመልካች ለተጠሪዎች አውራሽ ለመክፈል ተስማምተዋል፡፡ ስለሆነም በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በጽሁፍ የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገ በመሆኑ በሽያጭ ውሉ መሠረት አመልካች የበኩላቸውን ግዴታ በመፈፀም ቤቱን ከተጠሪዎች አውራሽ ተረክበዋል፡፡ በውሉ መሠረት ያልተፈፀመውና ሊፈፀም የሚገባው የቤቱን ስመንብረት በአመልካች ስም ለማዛወር የሚያስፈልጉ ተግባራትን መፈፀምና ቀሪውን ክፍያ ለተጠሪዎች መክፈል ብቻ ነው፡፡

አብላጫው ድምጽ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል በሕግ የሚጸና ውል የለም በማለት የወሰነው ከዚህ በፊት አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 የሰጠው የሕግ ትርጉም በዚህም ጉዳይ ለተያዘው ጭብጥ ያገለግላል የሚል መደምደሚያ ላይ በመድረሱ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አብላጫው ድምጽ የተከተለውን የሕግ ትርጓሜ ትክክለኛነት የማላምንበት በመሆኑና በዚህ መዝገብ ያለው ሁኔታ ራሱን የቻለ ልዩ ባሕሪ አለው ብዬ ስለማምን ከሙያ ባልደረቦቼ ተለይቻለሁ፡፡ አብላጫው ድምጽ የሚከተሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ አግባብነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አተረጓጎምን ማስተካከልና ውሣኔ መስጠት ነበረበት ብዬ አስባለሁ፡፡

በእኔ እምነት መሠረታዊው ችግር ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1፣ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2878 የተሰጠው የሕግ ትርጓሜ በመሆኑ በሕጉ ድንጋጌዎች የተሰጠውን ትርጓሜ

1. ከጠቅላላው የውል ሕግ ድንጋጌዎች መሠረታዊ ግብና ዓላማ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረታዊ ባሕሪ ጋር በመመርመር ድንጋጌው በምን መልኩ መተርጎም እና ተግባራዊ መሆን እንዳለበት መወሰን፤
2. ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ከሽያጭ የውል ድንጋጌዎች ጋር የሚኖራቸው ግንኙነትና በተለይም የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና 2578 ጋር ያለው አንድነትና ልዩነት እንደዚሁም ልንከተለው ስለሚገባው የአተረጓጎም ስልት መወሰን፤
3. በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በውል አዋዋይ ባለሥልጣን ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ፊት ያልተደረገ ውል በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት እንደ ረቂቅ ይቆጠራል በሚል መልክ የተሰጠውን የሕግ ትርጓሜ ተገቢነት መመርመር፤
4. በተራ ቁጥር 3 በተገለፀው መንገድ የተሰጠው የሕግ አተረጓጎም የውሎችን ተፈፃሚነት ወይም ፈራሽነት መርምሮ በመወሰን ሂደት የፈጠረው የተዛባ ግንዛቤና ችግር የፍትህ መዛባት ስለመኖሩና ችግሩን ለመቅረፍ ልንከተለው ስለሚገባው የአተረጓጎም ስልት መወሰን፤
5. ውሎች በጽሁፍ በመደረግ ብቻ ሣይወሰኑ በግማሽ ወይም በሙሉ በተፈፀሙበት ሁኔታ በተራ በቁጥር 3 የተገለጸው የሕግ አተረጓጎም ተገቢ ስለመሆኑና በአጠቃላይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 አተረጓጎምን አስመልክቶ ልንከተለው የሚገባውን የአተረጓጎም ስልት በስፋትና በዝርዝር አይቶ መወሰን አስፈላጊ ነው የሚል ዕምነት አለኝ፡፡ እነዚህና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ነጥቦች በጥልቀት ሣይታዩ ሶስትና አራት የሚሆኑ የሕግ ድንጋጌዎች በማገጣጠም የሚሰጥ ውሣኔ ከችግር ፈችነቱ ይልቅ ችግር ፈጣሪነቱ የሚያመዝን እንደሚሆን ለመገንዘብ ይኸ የህግ አተረጓጎም ከተሰጠ በኋላ እየተፈጠረ ያለውን የተመሠቃቀለ ሁኔታ በማየት በቂ ትምህርት ለመውሰድ ይቻላል ብዬ አስባለሁ፡፡

1. በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 2877 መካከል ያለውን ልዩነት ለመረዳት ህግ አውጭው በ1952 ዓ.ም የፍታብሔር ህጉን ሲያውጅ በተለይም ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችንና የልዩ የውል ህግ ድንጌጋዎችን ሲያውጅ ሊያሣካው የፈለገውን መሠረታዊ ግብ በዝርዝር ማየትና መመርመር ያስፈልጋል፡፡ ህግ አውጭው የፍትሀብሔር ህጉን በተጠቃለለ መንገድ ሲያውጅ፡-
   - ማንኛውም በአገሪቱ ውስጥ ነዋሪ የሆነ ወይም ለዕለቱ በእንግድነት በአገሪቱ ግዛት ውስጥ የሚገኝ ሰው ያለውን የሲቪል መብትና ግዴታ አውቆ መብቱን ለማስከበርና ግዴታውን ለመወጣት የዕለት ከዕለት የኑሮ መመሪያው አድርጐ እንዲጠቀምበት፤
   - ህብረተሰቡ የፍትሀብሔር ህጉ ከመታወጁ በፊት ይሠራባቸውና ይተዳደርባቸው በነበሩ ልማዳዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ደንቦች መሠረት የፈጠራቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ግንኙነቶች የህብረተሰቡን ልማድ ባህልና ሀይማኖታዊ እሴት ከግምት ውስጥ በማስገባት ታውጇል ብሎ በሚያስበው የፍትሀብሔር ህግ ድንጋጌዎች ግልጽ የሆነ ዕውቅና እንዲያገኙ ማድረግና ህጋዊ ጥበቃ መስጠት፤
   - እያደገ ከመጣው የዓለም የንግድ ልውውጥና ዘመናዊ አሠራር ጋር የማይራመደውን በአገሪቱ የሚከናወን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት ወደዳበረና ያደገ ዘመናዊ አሠራር የማሸጋገር ግብ የነበረው መሆኑን ከፍትሀብሔር ህጉ የማጽደቂያ አዋጅና ንጉሰ ነገስቱ በፍታብሔር ህጉ በመግቢያነት ከገለጿቸው ፍሬ ሀሳቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡

ህግ አውጭው የውልን ህግ አስመልክቶ ጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችንና ልዩ የውል ህግ ድንጌጋጌዎችን ሲደነግግ እነዚህን መሠረታዊ ግቦች የማሣካት ሀሳብና ፍላጐት ነበረው ብዬ አስባለሁ፡፡ ህግ አውጭው የልዩና የጠቅላላ የውል ህግ ድንጋጌዎችን ሲደነግግ ህብረተሰቡ ሲፈጽማቸው ለነበረው የውል ግንኙነቶች በተለይም ባህላዊና ልማዳዊ እሴቶችን መሠረት አድርጐ ሲፈጽማቸው ለነበሩ የውል ግንኙነቶች ህጋዊ ዕውቅና እና ጥበቃ መሥጠት አንደኛው ዓላማው እንደነበር የፍትሐብሔር ህጉን መግቢያ ብቻ ሣይሆን ስለቀብድ የተደነገጉ የውል ድንጋጌዎችን በመመርመር ለመረዳት የሚቻል ሲሆን በአገሪቱ የሚደረጉ ውሎች እና የውል ፈቃድ አሰጣጥ ሥርዓት ከውል የሚመነጩ ጉዳዮች አስተደደርና የችግር አፈታት እንደዚሁም የውሎች ተፈፃሚነት ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው መርሆች መሠረት እንዲከናወኑ የማድረግና የውል ግንኙነቶችን ወደ ዘመናዊነት የማሸጋገር ዓላማና ግብ እንደነበረው የውሉን ድንጋጌዎች ዝርዝር ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡

ህግ አውጭው እነዚህን መሠረታዊ ግቦች ለማሣካት በዋነኛነት ሶስት አይነት ባህሪ ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች አውጇል የሚል ዕምነት አለኝ፡፡

(i) የመጀመሪያው ፈቃጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች "Permissive provisions of law of contract" ሲሆኑ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች ሰፊ ነፃነት ለተዋዋይ ወገኖች የሚሰጡ ናቸው፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ህግ አውጭው በፈቃጅነት የደነጋገቸውን የውል ድንጋጌዎች መከተል ካልፈለጉ ደግሞ የመተው ነፃነት አላቸው፡፡ የፈቃጅ የህግ ድንጋጌዎች አለመሟላት የውሉ ህጋዊነት ላይ የሚያስከትለው ምንም አይነት ተጽዕኖ የለም፡፡ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በተዋዋይ ወገኖች ፍላጐትና ፈቃድ ተጠቃሽና ተፈፃሚ የሚሆኑ ሲሆኑ ተዋዋይ ወገኖች በዝምታ ያለፉት ነገር ሲኖርና በዚያም ምክንያት ክፍተት ሲፈጠር ክፍተቱን ለመሸፈን ሊጠቀሱና ሊፈፀሙ የሚችሉ የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ፈቃጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች የተዋዋዮቹን የመዋዋል ነፃነት (Freedom of contract) በማክበር ህግ አውጭው በአስገዳጅነት ሣይሆን በአማራጭነት የደነገጋቸው ናቸው፡፡

(ii) በሁለተኛ ደረጃ የሚፈረጁት አስገዳጅነት ያላቸው የውል ህግ ድንጋጌዎች (Mandatory provisions of the law of contract) ናቸው፡፡ እነዚህ የህግ ድንጋጌዎች በባህሪያቸው ተዋዋይ ወገኖች ውል የመዋዋል ነፃነታቸውን ተጠቅመው የውል ስምምነት ሲያደርጉ በግዴታ ሊከተሉት የሚገባውንና ሊያሟሉ የሚገባቸውን መሥፈርቶች የሚደነግጉ ናቸው፡፡ እነዚህ ድንጌጋዎች ህግ አውጭው ተዋዋይ ወገኖች ምን ማድረግ እንዳለባቸው ትእዛዝ የሚሰጥባቸው ብቻ ሣይሆኑ ህግ አውጭው በድንጋጌዎቹ የሰጠውን ጥብቅ ትእዛዝ አለመፈፀም ወይም አለማሟላት ውሉን ህጋዊ ህልውና እንዳይኖረው የሚያደርግ ውጤት አልባ (Void) ወይም ውሉ እንከን ያለበትና ፈራሽ (voidable) እንዲሆን የማድረግ ሀይልና ጉልበት ያላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም ተዋዋይ ወገኖች ውላቸው በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከፈለጉ አስገዳጅ የሆኑ የውል ህግ ድንጌጋዎች መከተልና ማሟላት አለባቸው፡፡ የአስገዳጅነት ባህሪ ያላቸውን የውል ህግ ድንጌጋዎች አለማሟላት ውሉን ለማፍረስ የሚያስችል እንከን ያለበት ውል የሚያደርግ ወይም ውሉን ውጤት አልባና ህጋዊ ህልውና የሌለው የሚያደርግ ነው፡፡

(iii) አብዛኛውን ጊዜ በህግ ትምህርት ቤቶች የሚሰጡ ትምህርቶች እና ስለ ህግ የሚፃፉ ጽሁፎች የአገራችንን የውል ህግ ድንጋጌዎች ፈቃጅ የሆኑ የህግ ድንጋጌዎች እና አስገዳጅነት ያላቸው የህግ ድንጌዎች በማለት የሚፈርጁ ናቸው፡፡ አብላጫው ድምጽም ሆነ በሰበር መዝገብ ቁጥር 21448 ለፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ትርጓሜ የሰጠው ችሎት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በባህሪው አስገዳጅነት ያለው የህግ ድንጋጌ ነው የሚል አቋም አላቸው፡፡ በእኔ በኩል አንድ መታየት ያለበት የውል ህጋችን ባህሪ ሣይዳሰስና ሣይታይ ታልፏል የሚል እምነት አለኝ፡፡ የውል ህግ ድንጋጌዎችን ስንመረምር ህግ አውጭው በትእዛዝ መልክ የደነገጋቸው ነገር ግን የአስገዳጅነት ባህሪ የሌላቸው ድንጌጋዎችን እናገኛለን፡፡ የዚህ አይነት የህግ ድንጋጌዎች አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጋጌዎች (Directory provisions of the law of contract) በሚል መንገድ ይገለፃሉ፡፡ የአዛዥነት ወይም የመምራት ባህሪ የተላበሱ የውል ህግ ድንጌዎች በወቅቱ የነበረውን ህግ አውጭ ፍላጎት የሚያንፀባርቁ ናቸው፡፡ በተለይም የፍትሐብሔር ህጉን ሲያውጅ ህግ አውጭው በአገሪቱ ግዛት ክልል የሚፈፀሙ የውል ግንኙነቶችን ወደ ዘመናዊ የውል አሠራርና አስተዳደር ለማሸጋገር በማሰብ የተደነገጉ ናቸው፡፡ አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጌዎች ህግ አውጭው የውል ግንኙነት ሲቋቋም ወይም ሲፈፀም እንዲሆን የሚፈልገውን ነገር በትእዛዝ መልክ በመደንገግ ህብረተሰቡን ወደሚፈልገው ግብ የሚመራባቸው የህግ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የውል ድንጋጌዎች ህብረተሰቡን ወደሚፈለገው ግብ ለመምራት ሚና ያላቸው ሲሆን በተለያዩ ምክንያቶች አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጌዎች ሣይከበሩና ሣይሟሉ ቢቀሩ መሠረታዊ የሆኑና በውል የተቋቋሙ መብትና ግዴታዎችን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማድረግ ባህሪ የሌላቸው ናቸው፡፡

የህግ መዝገበ ቃላት የአዛዥነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያላቸውን ድንጋጌዎች "the observance of which is not necessary to the validity of the proceeding to which it relates. Statutory provisions which do not relate to the essence of things to be done, and as to which compliance is of convenience rather than substance are directory" በማለት ይገልፃቸዋል፡፡

ከዚህ በመነሣት የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌን ባህሪ ስመረምረው ድንጌጋው አዛዥ ወይም መሪ የህግ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ለዚህም ከአንድ በላይ የሆኑ ምክንያቶች መስጠት ይቻላል፡፡ የመጀመሪያው የድንጋጌው አቀራረጽና የቃላት አሰካክ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቃል በቃል ሲነበብ "የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ባለቤትነት ወይም የማይንቀሣቀሥ ንብረት ላይ አላባ ጥቅም መብት ወይም መያዥያ ወይም ሌላ አገልግሎት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች ሁሉ በጽሑፍና በሚገባ አኳኋን በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው" በሚል መንገድ የተደነገገ ነው፡፡

የዚህ ድንጋጌ አቀራረጽ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ስለመሆኑ ከማያከራክረው የፍትሐብሄር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ጋር በማነፃፀር ብንመለከተው የፍትሐብሐር ህግ ቁጥር 1723 የንዑስ አንቀጽ 1 "በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን አለባቸው" ከማለት ውጭ ውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት አለመደረጉ ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የሚያደርገው ስለመሆኑ አይደነግግም፡፡

ሁለተኛው ምክንያት ህግ አውጭው የፍ/ሕ/ቁ 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገበት ሁኔታ ነው፡፡ ህግ አውጭው በአገሪቱ ግዛት ክልል ውስጥ የማይንቀሣቀሥ ንብረትን አስመልክቶ የሚከናወኑ ውሎች በባለሥልጣን ተረጋግጠው ተመዝግበውና በመንግሥት ጥበቃ ሥር እንዲቀመጡ ፍላጎት ያለው መሆኑን ለማግለጽና ህብረተሰቡ በዚህ መንገድ ውሎችን እንዲፈጽም ለመምራት አስቦ የደነገገው ድንጋጌ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ህግ አውጭው የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በአስገዳጅ የህግ ድንጋጌነት የመደንገግ ሀሳብ ነበረው ብሎ ለመከራከር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም በ1952 ዓ.ም የፍትሐብሔር ህጉን ያወጀው ህግ አውጭ በአገሪቱ መልካምድራዊ ግዛት ውስጥ የሚደረጉ የማይንቀሣቀሥ ንብረትን የሚመለከቱ የሽያጭ፣ የመያዥያ፣ የአላባ ጥቅም ማስተላለፊያና የሌሎች አገልግሎት ውሎችን የሚመዘግብና ህብረተሰቡ በቀላሉ ሊደርስባቸውና ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ተቋሞችን ገና ያላደራጀ መሆኑና ተቋማቱም በነበሩባቸው ውስን ሥፍራዎች የህጉን ይዘት መንፈስና ዓላማ በአግባቡ ተገንዝቦ ሥራ ላይ ሊያውል የሚችል የሰው ሀይል ገና ያላፈራ መሆኑን ጠንቅቆ የሚያውቅና የሚገነዘብ ነበር ብዬ አስባለሁ፡፡ በህግ አተረጓጐም ሥርዓት ውስጥ ምን ጊዜም ህግ አውጭው ምክንያታዊና የአገሪቱን ነባራዊ ዕውነታዎች በአግባቡ በመመርመርና በመመዘን ህጐችን ይደነግጋል ተብሎ

ይገመታል። ስለዚህ ውሉን ለመመዝገብ የሚችሉ ተቋማትና የሰው ሀይል ባልነበረበት ሁኔታ በአገሪቱ ውስጥ ሲከናወኑ የነበሩ የቤትና የመሬት ሽያጭ፣ የመያዥያ ውልና ሌሎች ውሎች ካልተመዘገቡ በስተቀር ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ መሆን አለባቸው የሚል ሀሳብ ይዞ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1ን ደንግጓል ብሎ መተርጎም ምንም አይነት ማነሻና መሠረት የሌለው አተረጓጎም ነው የሚል እምነት አለኝ።

በአንፃሩ ህግ አውጭው ለደህነትና ለጥንቃቄ "to convenience" በማይንቀሳቀሥ ንብረት ላይ የሚደረጉ ውሎች በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ቢደረጉ የሚመረጥ መሆኑን ለማሣወቅና ህብረተሰቡም በዚህ መልክ ውሎችን እንዲዋዋል ለመምራት በማሰብ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1723 የንዑስ አንቀጽ 1ን በመደንገግ ይህ ባይሟላ ግን ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማያደርግ መሆኑን በሚያሣይ መልኩ ድንጋጌውን የቀረፀ መሆኑን ሌሎች የህግ ድንጋጌዎችን መመልከት ሣያስፈልግ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በፍትሀብሔር ህግ ቁጥር 1728 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አቀራረጽ መካከል ያለውን ልዩነት በማነፃፀርና ድንጋጌው ሲታወጅ በአገሪቱ የነበረውን ነባራዊ ዕውነታና ህግ አውጭው ሲያሣካው ከሚፈልገው ግብና አላማ አንፃር  በመመዘን ለመረዳት ይቻላል የሚል ዕምነት አለኝ።

ከዚህ በተጨማሪ በእኛ የህግ ሥርዓት ውስጥ የትኞቹ የህግ ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች ናቸው? የትኞች አስገዳጅነት ያላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ናቸው? የትኞቹ ድንጋጌዎች ደግሞ የአዛዥነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያላቸው ናቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስና የድንጌዎቹን ባህሪ ለመለየት የምንጠቀምባቸውን ዘዴዎች ተገቢነት በመመርመር የችግሩን መንስኤና ምክንያት ለመረዳት ጥረት ማድረግ ይገባናል ብዬ አስባለሁ። እንደሚታወቀው በአገራችን የህግ ሥርዓት ውስጥ በአማርኛው ቅጅ "ሊሆን ይችላል፣ ሊፈፀም ይችላል፣ የተፈቀደ ነው፣...." የሚሉ ቃሎችን በመጠቀም ህግ አውጭው የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው የህግ ድንጌጋዎች ናቸው በማለት የምንፈርጅ ሲሆን በእንግሊዘኛው ቅጅ "May, possible, permissible ………" የሚሉና የመሳሰሉ ቃላቶችን የተጠቀመባቸውን ድንጋጌዎች ፈቃጅነት ያላቸው (permissive provisions of law) በማለት እንፈርጃለን።

በሌላ በኩል ህግ አውጭው በአማርኛው ቅጅ "መሆን አለበት፣ ሊፈፀም ይገባዋል፣ ማድረግ አለባቸው ………." የመሳሰሉ ትእዛዝ አዘሎች በመጠቀም የደነገጋቸውንና በእንግሊዘኛው ቅጅ "Shall, ought to be, must, may not…" የሚሉ ቃላትን በመጠቀም የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ሁሉ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌዎች  /mandatory provisions of law/ ናቸው የሚል የአብዛኛው የሕግ ባለሙያዎች መደምደሚያ አለ። ሆኖም እነዚህን ትዕዛዝ አዘል ቃሎች ሕግ አውጪው በአንድ ድንጋጌ ውስጥ መጠቀሙን በማየት ብቻ የድንጋጌዎችን ባህሪ ለመለየት የምንጠቀምበት ዘዴ አሣሣችና አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን አዛዥ ወይም መሪ ከሆኑ የሕግ ድንጋጌዎች ለመለየት የማያስችል የአፈራረጅ ዘዴ ነው።

ስለሆነም አስገዳጅ የህግ ድንጋጌዎችን አዛዥና መሪ ከሆኑ የህግ ድንጋጌዎች ለመለየት ህግ አውጭው ትእዛዝ አዘል ቃላት የተጠቀመ መሆኑን ማየት ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ ህግ አውጭው በትእዛዝ መልክ ያስቀመጣቸውን ደንቦች መጣስ ወይም ሣያከብሩ መቅረት የሚያስከትለውን ውጤት በመመርመር ድንጋጌዎችን መለየት ያስፈልጋል የሚል እምነት አለኝ።

የዚህ አይነት ዘዴ መጠቀም አዲስ አይደለም በህግ መዝገበ ቃላት ውስጥ "Mandatory provisions, they prescribe, in addition to requiring the doing of the thing specified, the result will follow if they are not done where as directory provisions, their terms are limited to what is required to be done" በሚል መንገድ ልዮነታቸው ተገልጾ እናገኛለን።

ህግ አውጭው ከተጠቀመባቸው ቃላት ባሻገር ከላይ የተገለፀውን መሠረተ ሀሳብ አስገዳጅ የህግ ድንጌጋዎችን አዛዥ ወይም መሪ ከሆኑ የህግ ድንጌጋዎች ለመለየት ጥቅም ላይ ማዋል ይገባናል የሚል እምነት አለኝ። ስለሆነም በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 በአማርኛው ቅጅ ‹‹በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ፊት መሆን አለባቸው›› የሚል ቃል መኖሩንና በእንግሊዘኛው ቅጅ ‹‹Shall be in writing  and registered with a court or notary>> የሚል ቃል መኖሩን በመመልከት ብቻ ድንጋጌው አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ነው በማለት የተደረሰበት መደምደሚያና የህግ ትርጉም ከላይ ከገለጽኩት የህግ ድንጌጋዎችን ባህሪ መለያ አሠራርና ዘዴ አንፃር እንደገና መታየትና መመርመር አለበት የሚል ሀሳብ አለኝ።

ስለሆነም ከላይ በዘረዘርኳቸው ምክንያቶች የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው (Directory provision of low) የሕግ ድንጋጌ እንጂ አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ እንጂ አብገዳጅ የሕግ ድንጋጌ /mandatory provision of low/ አይደለም የሚል ሀሳብ አለኝ፡፡ አብላጫው ድምጽ ይህንን ድንጋጌ  አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ ነው በሚል እምነት አመልካች ከተጠሪዎች አውራሽ ጋር ያደረገው የቤት ሽያጭ ውል  በፍርድ ቤት መዝገብ ቤት ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት የተደረገ ባለመሆኑ ህጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጠው ውሳኔ ህግ አውጭው ህጉን ሲያውጅ የነበረውን ሀሳብ ሊያሣካው የሚፈልገውን ግብና ዓላማ ግምት ውስጥ የማያስገባ ከመሆኑም በላይ ውሳኔው ከህግ መተርጐም ያለፈና አዲስ ህግ የማውጣት ያህል ውጤት ያለው በመሆኑ ከሙያ አጋሮቼ ተለይቻለሁ፡፡ 2. የፍታብሔር ህግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከማይንቀሣቀሥ ንብረት ሽያጭ ውል ድንጋጌዎች በተለይም ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2877 እና ከፍታብሔር ህግ ቁጥር 2878 ጋር ያለውን ግንኙነት መመርመር የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን አስፈላጊ ነው፡፡ የፍታብሐር ህግ ቁጥር 1723 ሁለት መሠረታዊ ደንቦችን በአንድ ላይ አጣምሮ የያዘ ድንጋጌ ነው፡፡ የመጀመሪያው የማይንቀሣቀሥ ንብረት ባለቤትነት የአላባ ጥቅም መብት፣ ወይም መያዣና ሌላ አገልግሎት መብት ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ የሚደረጉ ውሎች ሁሉ በጽሑፍ መደረግ እንዳለባቸው የሚደነግገው ሲሆን፦ ሁለተኛው ውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ፊት መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ነው፡፡ ይኸ ድንጋጌ በጥቅሉ ሲታይ አሐዝ ወይም መሪ ድንጋጌ ነው የምልበትን ምክንያት ከላይ በዝርዝር ገልጫአለሁ፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ደንቦች ውስጥ የትኛው ክፍል ለቤት ሽያጭ ውል አስገዳጅ የትኛው ክፍል ደግሞ አሐዝ ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ልዩ ድንጋጌ ነው፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ የሚደረግ የቤት ሽያጭ ውል በጽሁፍ ካልተደረገ በስተቀር ፈራሽ እንደሚሆን የፍ/ሕግ ቁጥር 2877 በግልጽ ይደነግጋል፡፡  ይኸ ድንጋጌ ውሉ በጽሑፍ መደረግ አለበት በሚል መንገድ ብቻ የተቀመጠ ሣይሆን ውሉ በጽሑፍ አለመደረጉ የሚያስከትለውን ውጤት ግልጽ የሚያደርግ ድንጋጌ ነው፡፡ ስለሆነም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ በአሃዝነት ወይንም በመሪነት ካስቀመጣቸው ሁለት ደንቦት ውስጥ "የውሉ በጽሑፍ መሆን" የሚደነግገው ደንብ የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማስተላለፍ የግድ መፈፀም ያለበትና አስገዳጅ የሕግ ሁኔታ መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ነው ስለሆነም ድንጋጌዎቹ ጐን በጐን ሊፈፀሙ የሚችሉ ድንጋጌዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንዑስ አንቀጽ 1 ከያዛቸው ደንቦች ውስጥ ሁለተኛው ክፍል ማለትም "የውሉ በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል በተሰጠው አካል ፊት" መደረግ አለመሟላት ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ የማያደርግ በሌላ አነጋገር አስገዳጅ ሣይሆን አሐዥ ወይም መሪ የሕግ ድንጋጌ መሆኑን ግልጽ የሚያደርግ ድንግጌ ነው፡፡ ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ከተደረገ በውል አዋዋይ ፊት ባለመደረጉ ብቻ ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ እንደማይሆንና በተዋዋዮቹ መካከል አስገዳጅነት ያለው የፀና ውል መሆኑን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 ድንጋጌ ግልጽ የሚደረግ ነው፡፡ ስለሆነም በእኔ እምነት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ሲሆን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለው የሕግ ድንጋጌ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡

ስለሆነም የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ የተደረገ ሆኖ እያለ አስገዳጅነት በሌለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በውል አዋዋይ ፊት የመደረግ መስፈርት አላሟላም ተብሎ ውጤት የለውም መባሉና የአመልካች ውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ውድቅ መደረጉ አግባብነት የለውም የሚል እምነት አለኝ፡፡

ሌላው በዚህ መዝገብ በጭብጥነት ያልተያዘ ነገር ግን ግልጽ መሆን ያለበት ውል ለማማዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ ወይም የማይንቀሣቀስ ንብረት መመዝገቢያ መዝገብ ያልተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል ውጤት የማይኖረው በተዋዋዮቹ መካከል ሣይሆን በሌሎች ሶስተኛ ወገኖች ላይ መሆኑን ከላይ በሰፊው በዘረዘርኩት የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረታዊ ይዘትና ባህሪና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2878 አስገዳጅ የሕግ ድንግጌ ከመሆኑ አንፃር በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 እና 2878 አስገዳጅ የሕግ ድንግጌዎች በመሆናቸው የአሃዝነት ወይም የመሪነት ባህሪ ካለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 በላይ ተፈፃሚነት ያላቸው ናቸው የሚል ሐሳብ ያለኝ ሲሆን አብላጫው ድምጽ የእነዚህን ድንጋጌዎች ባህሪ የተፈፃሚነት ወሰን አስመልክቶ የሰጠው ትርጓሜ ተገቢነት የሌለውና በጥልቀት መታየት አለበት በሚል መነሻ ይህንን የልዩነት ሐሳብ ጽፌአለሁ፡፡

3. አብላጫው ድምጽ እና ከዚያ ቀደም ብሎ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ነው በማለት ትርጉም የሰጡት ዳኞች የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 "በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው ፊት መሆን አለባቸው" ከማለት ውጪ ውሉ በዚህ መንገድ ሣይፈፀም ቢቀር ውጤቱ ምን ይሆናል? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ምላሽ እንደማይሰጥ በውል ተገንዝበዋል፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በውል አዋዋይ ፊት ባይፈፀም ውሉን ውጤት አልባ ወይም ፈራሽ እንደማይሆን ለማሳየት ሕግ አውጭው ሆን ብሎ ያለፈውና ድንጋጌው አስገዳጅ የሕግ ድንጋጌ ሳይሆን አሃዝ ወይም በመሪ የሕግ ድንጋጌነት የደነገገው መሆኑን ባለመገንዘብ አብላጫው ድምጽ የተከተለው ትርጓሜ ሕግ አውጭው ሕጉን ካሰበው ሐሳብ ያፈነገጠ እና አዳናጋሪና አፍራሽ ውጤት ያለው ነው፡፡ አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን ባለው አካል ፊት ያልተደረገ የቤት ሽያጭ ውል እንደረቂቅ እንደሚቆጠር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንዑስ አንቀጽ 1 ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ጋር በማጣመር በመተርጐም ወስኗል፡፡

በመሰረቱ ይኸ አተረጓጐም መሰረታዊ ስህተት ያለበት ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ የቤት ሽያጭ ውል የሚፈፀምበት ፎርም ምን መሆን እንዳለበት ሕግ አውጭው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በግልጽና አስገዳጅ ደንጋጌ ደንግጐ እያለ ፍርድ ቤቱ በትርጉም ሌላ ተጨማሪ የውል ፎርም ለመፍጠር የሰጠው ውሣኔ ከሕግ አተረጓጐም መርህ የወጣና ያፈነገጠ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረት አንድን ውል እንደረቂቅ የሚያስቆጥረው የውሉ በሚገባ አኳኋን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1726 መሰረት የተስማሙበትን ሞልተው አለመፃፋቸው፣

በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727/1/ መሰረት ተዋዋዮች ያልፈረሙበት ሲሆንና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1728 ንኡስ አንቀጽ 1 እና ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት ተዋዋዮቹ ፊርማቸውን ያላስቀመጡ ሲሆን ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ውሉ የተዋዋዮቹ ስምምነት በሚገልጽ መንገድ በጽሑፍ ተዘጋጅቶ ተዋዋዮቹ ከፈረሙበት በኋላ ምስክሮች ሣይፈርሙበት ቢቀሩ የውሉን ሰነድ እንደረቂቅ የሚያስቆጥር ጉድለት እንዳልሆነ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በተዋዋዮቹ የተፈረመው ውል ላይ ምስክሮች ሣይፈራረሙ ቢቀሩ ውሉ እንደረቂቅ የሚታይ ሣይሆን ውሉን ውጤት አልባ የሚያደርግ ጉድለት ስለመሆኑ ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727/2/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል በልዩ ሁኔታ የቤት ሽያጭ ውል በጽሑፍ ሳይደረግ ቢቀር እንኳን እንደረቂቅ የሚታይ ሣይሆን ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተደነገገው በፍርድ ቤት መዝገብ ሹም ወይም ውል አዋዋይ ፊት አለመደረግ አብላጫው ድምጽ እንደሚለው የውል ፎርም አለመሟላት አይደለም፡፡ አንድ ውል በውል አዋዋይ ፊት ሲደረግ የሚፈፀሙ ተግባራት ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የመጀመሪያው የተዋዋዮቹን ፈቃደኝነት እና የውሉን ለሕግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ያለመሆን በማረጋገጥ ውሉን መመዝገብ ሲሆን ሁለተኛው ተዋዋዮቹ አስፈላጊውን የቴንብር ቀረጥና ሌሎች ሕጋዊ ክፍያዎችን እንዲከፍሉ ማድረግ ነው፡፡ ሶስተኛው ውሉን አንድ ኮፒ የማስቀመጥና የመጠበቅ ሥራ መሥራት ነው፡፡

ውልን የመመዝገብ እና የቴንብር ቀረጥ የመክፈል ግዴታን አለመወጣት ውሉን ፈራሽ እንደማያደርገው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 2 ተደንግጓል፡፡ ይሕም የሚያሣየው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 በውል አዋዋይ ፊት አለመደረጉ ውሉን ፈራሽ የማያደርገው መሆኑን ነው፡፡ ሆኖም አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 የተቀመጠውን የመመዝገብ የቴንብር ቀረጥ የመክፈልና በመጨረሻም ኮፒ የማስቀመጥ መስፈርት አለመሟላት ውሉን ፈራሽ ወይም ውጤት አልባ በማድረግ የሚወሰን ሣይሆን ከጅምሩ እንዳልተደረገና እንደረቂቅ ሰነድ ያስቆጥረዋል በማለት የሰጠው ትርጓሜ ተገቢ ነው ብየ አላስብም፡፡ ስለሆነም አብላጫው ድምጽ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ ድንጋጌ አስገዳጅ ሣይሆን አሃዝ ወይም መሪ የሕግ ድንጋጌ መሆኑን ባለመገንዘብ በሕጉ ድንጋጌ የተቀመጠው መስፈርት ሳይሟላ ውጤቱ ምን ይሆናል? የሚለውን ሕግ አውጭው ሆን ብሎ በክፍትነት የተወውን በትርጉም በማሟላት ውሉ እንደረቂቅ የሚቆጠር ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያውጅ ከነበረው ሐሳብ እና ሊደርስበት ካሰበው ግብና ዓላማ ያፈነገጠ የሕግ አተረጓጐም መርሆችን ያልተከተለ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡

4. አብላጫው ድምጽ የተከተለውና የተቀበለው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አለመከበር ወይም አለመሟላት ውጤት ውሉን በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1720 ንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት እንደረቂቅ ያስቆጥረዋል የሚለው አተረጓጐም ተግባራዊ ምላሽ የሚሹ የበርካታ ችግሮች መንስኤና ምክንያት ሆኗል ብየ አስባለሁ፡፡ የመጀመሪያው ቤት ሽያጭና ቤት ገዥ የፈረሙበትና ምስክሮችም በፊርማቸው ያረጋገጡት የጽሑፍ ውል እንደርቂቅ ሰነድ የሚታይ ነው ተብሎ በመወሰኑ ይህንን የውል ሰነድ የመብትና ግዴታ ማረጋገጫ ሰነድነት በመጠቀም ክስ ለማቅረብ ሲሞክሩ ክስ ለማቅረብ የማያስችልህ መብትና ጥቅም የለህም፡፡ ያቀረብከው የውል ሰነድ እንደ ውል ሣይሆን እንደ ረቂቅ የሚታይ ነው በማለት ጥያቄያቸው በፍታብሔር ስነ ስርአት ሕግ ቁጥር 33/2/ መሰረት የሚሰረዝባቸው ቢያንስ በውሉ መሰረት የከፈሉትን ገንዘብ የማስመለስ መብታቸውን እንዳይጠይቁ መዝገባቸው በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 231 መሰረት እየተዘጋባቸው ያሉ ሰዎች መኖራቸውን በዚህ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 32226 የተደረገውን ክርክርና የተሰጠውን ውሣኔ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ሰነዱ ረቂቅ ነው ውል አይደለም የሚለው አተረጓጐም ውሉ ሕግ የተደነገገውን ፎርም አያሟላም በሚል ምክንያት ፈራሽ እንዲሆን ለመጠየቅ እና ጥያቄውን ለማቅረብ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1810 ንኡስ አንቀጽ 1 እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1845 የተደነገገው ጊዜ አልፏል የሚለውን የመከራከሪያ ሐሳብ አንስቶ የመከራከር መብትን አጠያያቂ የሚያደርግ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰነድ ከጅምሩ ረቂቅ ነው ከተባለ ተዋዋዮች ያደረጉት ምንም አይነት የውል ግኑኝነት የለም ማለት ነው፡፡ የሌላ የውል ግኑኝነት እንዲፈርስ በሁለት ዓመት ወይም በአስር አመት ውስጥ መጠየቅ ነበር ብሎ ለመከራከርም ሆነ ውሣኔ መስጠት የሚቻል አይሆንም፡፡ ስለሆነም የዚህ አይነት አደናጋሪ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑና ይኸም ጉዳዮችን በእንጥልጥል የሚያስቀር አተረጓጐም መሆኑን በዚህ ችሎት መዝገብ ቁጥር 24515 ከተደረገው ክርክርና ከተሰጠው ውሣኔ ለመረዳት ይቻላል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ይኸ አተረጓጐም ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ከመፈፀማቸው በፊት ወደ ነበሩበት ሁኔታ ለማስመለስ የሚያስችል ነው፡፡ ተከራካሪዎች ውል ከመዋዋላቸው በፊት እንዲመለሱ ለማድረግ በመጀመሪያ ውል አለ ውሉ ግን ግድፈት ያለበት ስለሆነ ውጤት አልባ (void) ነው ወይም ፈራሽ (avoidable) ነው የሚለውን መነሻ ይዛ መወሰን ይጠይቃል፡፡ ውሉ ረቂቅ ነው ከተባለ ከውል በፊት የተደረገ ምንም አይነት መብትና ግዴታ የማያቋቁም ተዋዋዮቹም ፈቃዳቸውን ያልገለፁበት ሰነድ ነው የሚል እንድምታና ትርጉም አለው፡፡ ስለዚህ በውል በፊት በጅምር ረቂቅነት ያለን ነገር “void” ውጤት አልባት ወይም (avoidable) ፈራሽ ነው ብሎ ለመፈረጅና ለመወሰን አይቻልም፡፡ በዚህ ምክንያት የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ ረቂቅ ነው የሚለውን የሰበር ትርጉም ተከትለው ውሣኔ ከሰጡ በኂላ ተከራካሪዎች ወደ ነበሩበት ሁኔታ ይመለሱ ብለው እንደማይወስኑ አብላጫው ድምጽ በዚህ መዝገብ ያደረገው ማሻሻያ በቂ ማስረጃ ነው፡፡

በአጠቃላይ ተዋዋይ ወገኖች ፈቅደውና ወደው በፊርማቸው ያረጋገጡትንና በምስክሮች ፊርማ የተረጋገጠ የቤት ሽያጭ ውል ጉድለት ያለበት ስለሆነ ውጤት አልባ ነው ወይም ፈራሽ ነው ከማለት አልፎ እንደረቂቅ ይቆጠራል ተብሎ የተሰጠው ትርጓሜ መነሻ እየተፈጠሩ ያሉትን በርካታ ውስብስብ ችግሮችና ለመፍታት የሚያስችል መንገድ ለማስተካከል ጥረት መደረግ ሲገባው ከዚህ በፊት የተሰጠው የአህግ ትርጉም ባለበት ሁኔታ በችግር ፈጣሪነቱ እንዲቀጥልና ተፈሚ እንዲሆን መደረጉ ተገቢነት የለውም የሚል ሐሳብ አለኝ፡፡

5. በዚህ መዝገብ ያለው ልዩ ሁኔታ የቤት ሽያጭ ውል በመፈራረም ብቻ የቆመ አይደለም፡፡ አመልካችና የተጠሪዎች አውራሽ ባደረጉት የቤት ሽያጭ ውል መሰረት የየበኩላቸውን ግዴታ ከግማሽ በላይ ፈጽመዋል፡፡ አመልካች ብር 4000 /አራት ሺህ ብር/ ለተጠሪዎች አውራሽ የከለፈሉ ሲሆን የተጠሪዎች አውራሽ የቤቱን ይዞታ ከአምስት አመት በፊት ለአመልካች አስረክበዋል፡፡ ተዋዋይ ወገኖች ውሉን ከመፈራረም አልፈው በውሉ መሰረት የግዴታቸውን በፈፀሙበት ሁኔት በመካከላቸው ያለው ግኑኝነት ውል ሣይሆን የውል ረቂቅ ነው የሚለው አተረጋጐም ተዋዋዮች የውል ግኑኝነት ከመፍጠር አልፈው ለውላቸው ተገዥ ሆነው በሚታይና በሚጨበጥ መልኩ የውሉን ኃይለ ቃል ለመፈፀም የወሰዱትን እርምጃ ከግንዛቤ ውስጥ የማያስገባ አተረጓጐም ነው ይኸ አይነት የሕግ አተረጋጐም ደግሞ የውልና የኢኮኖሚያዊ ግኑኝነት እርግጠኝነትን ለውል ሐይለ ቃለ ማክበርና ተገዥ መሆኑን ሣይሆን እብለትን ክህደትን ተሸላሚ የሚያደርግ በመሆኑ ሊስተካከልና ሊታረም ይገባዋል የሚል አምነት አለኝ፡፡

ሕግ አውጭው ጠቅላላና ልዩ የውል ሕግ ድንግጌዎችን ሲያውጅ በአገሪቱ የሚፈፀሙ የውል ግኑኝነቶች ገዥነት እንዲኖራቸው ውሎች በተወዋይ ወገኖች መካከል እንደ ሕግ ሆነው እንዲያገለግሉና የሕግ ያሕግ ከበሬታና ተፈፃሚነት

እንዲኖራቸው በማሰብ ነው፡፡ የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሰረታዊ ባህሪ ጠቀሜታና ውጤት ሕጉ ሲታወጅ ከነበረው የሕግ አውጭው ሐሳብ ዓላማና ግብ ጋር በተጣጣመ መንገድ ሊተረጎምና ሥራ ላይ ሊውል ይገባዋል፡፡ ሕግ ተራ የቃላት ስብስብና ሕግ አውጭው በዘፈቀደ የሰራው አረፍተ ነገር አይደለም፡፡ ሕግ ታስቦበት የአንድን ማህበረሰብ ኢኮኖማያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግር መፍታትና ወደ እድገት ጉዳና የመምሪያ መሣሪያ ነው፡፡

የውል ሕግ ድንጋጌዎች ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ እየተከናወኑ ያሉ የውል ግኑኝነቶች የፈፃሚነት የንግድ ሥራና ልውውጥ እርግጠኝነት እና ማህበራዊ መረጋጋት በሚፈጥር መንገድ መተርጐምና ሥራ ላይ ማዋል አለባቸው፡፡ የውል ሕግ ድንጋጌዎች ሰዎች ወደውና ፈቅደው ለገቡት ግዴታ ተገዥ እንዲሆኑና የውል ግዴታቸውን እንዲያከብሩ በሚያደርግና በተዋዋዮች ነፃ ፈቃድ የተመሰረተ ለሕግና ለሞራል ተቃራኒ ያልሆነ ውል ከውሉ መሰረታዊ ይዘትና ባህሪ ጋር ግኙኝነት በሌላቸው ጥቃቅን ምክንያቶች ለማፍረስ እና ለማሰረዝ በክፉ ልቦና የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን ለመግታት ለመከላከልና ለመቆጣጠር በሚያስችል መልኩ መተርጐምና ሥራ ላይ መዋል አለባቸው፡፡ ከዚህ አንፃር በመዝገብ ቁጥር 21448 የተለየ ትርጉምና ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት ለፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ይዘት የድንጋጌው ባህሪና የሚያስከትለውን ውጤት አስመልክቶ ፍርድ ቤቶች ሲከተሉት የነበሩት የሕግ አተረጓጉም ሕብረተሰቡ በጽሑፍ የተደረገ ተዋዋይ ወገኖችና ምስክሮች የፈረሙበት የቤት ሽያጭ የመያዥያና ሌሎች አገልግሎቶች ምስክሮች የፈረሙበት የቤት ሽያጭ የመያዥያና ሌሎች አገልግሎቶች ለማቋቋም ወይም ለማስተላለፍ ያደረጉ ውሎች ህጋዊ ውጤት ያላቸውና በፍርድ ሐይል ተፈፃሚነት አላቸው ብሎ እንዲያምን የሚያደርጉ ነበሩ፡፡ ይህንን አተረጋጉም ለመቀየር የተሰጠው ምክንያትም ሆነ ሕጉ የተተረጐመበት አግባብ አንድ ብቻ ሣይሆን በርካታ ስህተቶች ያሉበት ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ በመሆኑም አብላጫው ድምጽ፡-

- ሕግ አውጭው ሕጉን ሲያውጅ የነበረውን ሐሳብ ሕጉን በማወጅ ሊያሣካው ከሚፈልገው ግብና ዓለማ ግንዛቤ ውስጥ ሣያስገባና ትክክለኛ የሕግ ድንጋጌዎች ባህሪያት መለያ ዘዴ ሣይከተል የአዛዣነት ወይም የመሪነት ባህሪ ያለውን የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723 ንኡስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ አስገዳጅ የሕግ ድንግጌ ነው የሚል ትርጉም መስጠቱ፡-
- በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መካከል የተደረገው የቤት ሽያጭ ውል አስገዳጅና ልዩ የሕግ ድንጋጌ በሆነው በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2877 በተቀመጠው ፎርም የሚያሟላ ሆኖ እያለ አላግባብ የፍታብሐር ሕግ ቁጥር 1723/1/ የተቀመጠውን ፎርም ስለማያሟላ የሽያጭ ወሉ ውጤት የሌለው ረቂቅ ብሎ በመወሰን፡-
- የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1723/1/ መሰረታዊ ጥቅም ዓላማና ውጤት አስመልክቶ ሌላው የሰበር ችሎት በመዝገብ ቁጥር 21448 ሚያዝያ 30 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትርጉም ከላይ የዘረዘርኳቸው ችግሮችና የሕግ አተረጓጉም ነው ብሎ ከውሣኔ ውስጥ በመጥቀስና በመከተል የሰጠው ውሣኔ የተሣሣተ መደምደሚያና ውሣኔ ነው ብዬ ስለማስብ በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መካከል በሕግ ፊት የሚፀናና አስገዳጅነት ያለው የቤት ሽያጭ ውል አለ፡፡ ተጠሪዎች በውሉ መሰረት ግዴታቸውን ሊፈጽሙ ይገባል በማለት በልዩነት ወስኛለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 32854

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ት ማርታ አድማሱ - ጠበቃ ወርቅዬ ዓባይነህ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ በረከት ሰብስቤ - ቀረቡ፡፡

2. የኢትዮጵያ መድን ድርጅት - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች በ1ኛ ተጠሪና በሥር በአንደኛ ተከሣሽ አቶ ዳዊት ጌታሁን ላይ ባቀረቡት ክስ ንብረትነቱ የሁለተኛ ተከሣሽ /የአሁን አንደኛ ተጠሪ/ በሆነና በአንደኛ ተከሣሽ ሹፌርነት ሲሽከረከር በነበረው "ካቻማሊ" የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ ተሳፍሬ ከድሬዳዋ ወደ አዲስ አበባ በመጓዝ ላይ ሳለሁ ሹፌሩ በፈጸመው ጥፋት መኪናው በመገልበጡ የአካል ጉዳት የደረሰብኝ ስለሆነ ይህንኑ ጉዳት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ለመታከም፣ የተቋረጠ ደመወዝ፣ ለሕክምና እና ለመድኃኒት መግዣ ወጭ የሆነ፣ ለትራንስፖርት ለአልሚ ምግብና እንደዚሁም በእጄ ላይ በደረሰብኝ ጉዳት ምክንያት ወደፊት መሥራት ስለማልችል ይሄው ሊከፈለኝ ይገባል በማለት ዘርዝረው በድምሩ ብር 581,402.25(አምስት መቶ ሰማንያ አንድ ሺህ አራት መቶ ሁለት ብር ከሃያ አምስት ሣንቲም) ተከሣሾች በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ንብረትነቱ የሁለተኛ ተከሣሽ የሆነው አውቶቡስ መኪና በኢትዮጵያ መድን ድርጅት /የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ/ በኩል የመድን ሽፋን የተገባለት መሆኑን በማረጋገጡ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 43 መሠረት የኢትዮጵያ መድን ድርጅትን ወደ ክርክሩ በማስገባት ግራ ቀኙን አከራክሮ በከሣሽና የመኪናው ባለንብረት በሆኑት ሁለተኛ ተከሣሽ መካከል የአጓዥነት ውል መኖሩ የተረጋገጠ ስለሆነና በን/ሕ/ቁ. 595 መሠረት በተሳፋሪ ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ የሚሆነው አጓዡ እንደሆነ ስለተመለከተ አንደኛ ተከሣሽ የመኪናው አሽከርካሪ እንጂ አጓዥ ስላልሆነ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት የለበትም በማለት አንደኛ ተከሣሽን ከክሱ አስወጥቷል፡፡

ሁለተኛ ተከሣሽን በተመለከተም የመኪናው ባለንብረት ስለሆነ በከሣሽ ላይ ለደረሰው ጉዳት ኃላፊነት አለበት ካለ በኋላ በንግድ ሕግ ቁጥር 597/1/ መሠረት በጉዞ ላይ ጉዳት ለደረሰበት መንገደኛ የሚከፈለው ካሣ ከብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የማይበልጥ ሲሆን እስከ ብር 40,000 (አርባ ሺህ ብር) የካሣ ክፍያ ለማግኘትም ቢሆን በአደጋው የደረሰው ጉዳትና የጉዳት መጠን በማስረጃ ተደግፎ መቅረብ እንዳለበት በውሣኔው ላይ አስፍሮ ነገር ግን ከሣሽ በግራ እጄ ላይ በደረሰው የነርቭ ጉዳት በውጭ አገር ለመታከም ብር 200,000( ሁለት መቶ ሺህ) ያስፈልጋል፣ እንደዚሁም በሰውነቴ ላይ ለደረሰ ጉዳት ለሕክምና ብር 25,000(ሃያ አምስት ሺህ ብር) ያስፈልጋል በማለት የጠየቁትና የኮምፒዩተር ሙያ ለመማር የተከፈለ ክፍያና ወደፊት በኮምፒዩተር ሙያ አገልግሎት ሊገኝ የሚችል በማለት የጠየቁት የካሣ ክፍያ በማስረጃ ተደግፎ ያልቀረበ ስለሆነ ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ከሣሽ በአደጋው ምክንያት ለ4 ወር የመምህርነት ሥራዬ የተቋረጠ ስለሆነ የ4 ወር ደመወዝ ይከፈለኝ በማለት የጠየቁትንም በተመሣሣይ ከሣሽ በመምህርነት

ሙያ የምታገለግል ስለመሆኗና በአደጋው ምክንያት ደመወዝ የተቋረጠባት ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጠችም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

ለጥርስ ማስተከያና ለሕክምና፣ ለመድኃኒት ለአልሚ ምግብና ለትራንስፖርት የተጠየቀውን የካሣ ክፍያ በተመለከተም መጠኑ የተጋነነ መሆኑን በውሣኔው ላይ አመላክቶ ለጥርስ ሕክምናና ማስተከያ ብር 6,000(ስድስት ሺ.ህ) ፤ ለሕክምና፣ ለመድኃኒት፣ ለአልሚ ምግብና ለትራንስፖርት ብር 2,000(ሁለት ሺ.ህ) በድምሩ ብር 8,000(ስምንት ሺ.ህ ) ሊከፈላት ስለሚገባ ይህንኑ ገንዘብ ሁለተኛ ተከሣሽና ለሁለተኛ ተከሣሽ መኪና የመድን ሽፋን የሰጠው የኢትዮጵያ መድን ድርጅት /3ኛ ወገን ተከሣሽ/ በአንድነትና በነጠላ ለከሣሽ ይክፈሉ በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ከሣሽ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 337 መሠረት ፍ/ቤቱ ይግባኙን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው የሥር ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ተፈጽሞበታል በማለት ሲሆን ይህ ሰበር ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች ደርሶብኛል ለሚሉት የአካል ጉዳት ያቀረቡት የካሣ ክፍያ ጥያቄ የማስረጃ ድጋፍ የሌለው ነው በሚል በሥር ፍ/ቤቶች ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ ከሕጉ አኳያ አግባብነት አለውን? የሚለው ነው በዚሁ ጭብጥ መሠረት የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አመልካች የአካል ጉዳት የደረሰባቸው ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ በሆነ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡስ በመጓዝ ላይ እያሉ ስለሆነ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንዳሰፈረው በግራ ቀኙ መካከል የአጓዥነት ውል /Contract of carriage/ ስላለ ይህንኑ የግራ ቀኙን ግንኙነት የሚገዛው የንግድ ሕጉ ስለሆነ ጉዳዩን ከዚሁ የንግድ ሕጉ አኳያ መመልከቱ አግባብነት ይኖረዋል፡፡

በዚህም መሠረት መንገደኞች ከአንድ ሥፍራ ወደ ሌላ ሥፍራ በሚጓዙበት ጊዜ በጉዞ ላይ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት አደጋ ቢደርስባቸው አጓዡ ኃላፊነት እንዳለበት በንግድ ሕግ ቁጥር 595 ላይ የተደነገገ ሲሆን አጓዡ ከኃላፊነት ነፃ ሊሆን የሚችለው ጉዳቱ ሊደርስ የቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ /force majeure/ በሚሆንበት ጊዜ ወይንም በ3ኛ ወገን ድርጊት ወይም በእራሱ በተሳፋሪው ጥፋት መሆኑን ካሣየ እንደሆነ በቁጥር 596 ላይ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ጉዳቱ በዚህ መልኩ የደረሰ መሆኑን አጓዡ /አንደኛ ተጠሪ/ ያላሳዩ በመሆኑ በሥር ፍ/ቤት የኃላፊነት ውሣኔ መሰጠቱ አግባብነት ነበረው፡፡

በሌላ በኩልም አንድ ተሳፋሪ በጉዞ ላይ እያለ የሞት ወይንም የአካል ጉዳት አደጋ ቢደርስበት ሊከፈለው የሚችለው የካሣ ክፍያ መጠን ከብር 40,000(አርባ ሺ.ህ) እንደማይበልጥ በዚሁ የንግድ ሕግ በቁጥር 597/1/ ላይ ተመልክቷል፡፡ ይሁንና በአንድ ተሳፋሪ ላይ ለደረሰው የሞት አደጋም ይሁን የአካል ጉዳት የሚከፈለው የካሣ መጠን ከብር 40,000(አርባ ሺ.ህ) ሊበልጥ እንደማይችል በንግድ ሕጉ ላይ ከመመልከቱ በስተቀር የካሣው መጠን የሚሰላው በደረሰው ጉዳት ልክ ብቻ ወይንም ወደፊት በእርግጠኛነት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚታመን ጉዳትን ጨምሮ ስለመሆኑና በአጠቃላይ የካሣ መጠን አወሳሰን /Damage Assessments/ በንግድ ሕጉ ላይ አልተመለከተም፡፡ ይህ ሁኔታ በልዩ ሕጉ ካልተሸፈነ ደግሞ የጠቅላላ ሕግ ድንጋጌዎችን መፈተሽና በዚሁ ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ እልባት መስጠት እንደሚገባ ከሕግ አተረጓጎም መርህ መገንዘብ ስለሚቻል በዚሁ መሠረት በፍትሐብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለ ውሎች የሚለውን ክፍል ተመልክተናል፡፡

እንደተመለከትነውም በውል ግዴታ ውስጥ ባለዕዳ የጉዳት ኪሣራ ከፋይ የሚሆነው ውሉን አሟልቶ ባለመፈጸሙ ወይም ውሉን ከስምምነቱ ውጭ አዘግይቶ በመፈጸሙ በባለገንዘቡ ወይም በሌላው ተዋዋይ ወገን ላይ በገንዘብ የሚተመን ኪሣራ የደረሰበት መሆኑ ሲታወቅ እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1790 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህም

ሌላ ሊከፈል የሚችለው የኪሣራው መጠን ልኩ ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት በተደነገገው የፍትሐብሔሩ ምዕራፍ ሥር ባሉ ድንጋጌዎች እንደሚመራም በፍ/ብሔር ሕግ ቀጥር 1790/2/ ላይ ተመልክቷል፡፡

ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት የጉዳት ኪሣራ አከፋፈልና ልኩ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2090 ጀምሮ ባሉት ድንጋጌዎች በዝርዝር የተቀመጠ ሲሆን ለደረሰው ጉዳት ኃላፊ መሆኑ በሕግ የታወቀው ሰው የሚከፍለው የጉዳት ካሣ ኃላፊነቱን ያመጣው ጉዳይ በተበዳዩ ላይ ካደረሰው ጉዳት ጋር እኩል ሆኖ መመዛዘን እንዳለበት፣ ለወደፊት ሊደርስ ይችላል ተብሎ የሚገመተው ጉዳት የተረጋገጠ ሲሆን እስኪፈጸም ድረስ ሳይጠበቅ ካሣ ሊከፈለው እንደሚገባም በቁጥር 2091 እና 2092 ላይ ተቀምጧል፡፡

በሌላ በኩልም ጉዳት የደረሰበት ወገን የደረሰበትን ጉዳት ልክና ጉዳት አድራሹ ካሣ በመክፈል ረገድ ያለበትን ግዴታ ማስረዳት እንዳለበት በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2141 ላይ የተመለከተ ቢሆንም ተጎጂው ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ነገር ግን የካሳውን መጠን ለመገመት አስቸጋሪ ሁኔታ በሚያጋጥም ጊዜ በቁጥር 2102 መሠረት ዳኞች የካሣውን መጠን በርትዕ ለመወሰን ሥልጣን የተሰጣቸው በመሆኑ በተያዘው ጉዳይ አመልካች በመኪናው መገልበጥ ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ባቀረቡት ማስረጃ መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡

ሲጠቃለልም አመልካች ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ በሆነ የሕዝብ ማመላለሻ መኪና ተሳፍረው ሲጓዙ መኪናው በመገልበጡ ምክንያት በግራ እጃቸው ላይ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑና በአጠቃላይም በሰውነታቸው ላይ የተለያየ ጉዳት ስለመድረሱ በማስረጃ የተረጋገጠ እንደመሆኑ መጠን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይህንኑ ጉዳት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው በንግድ ሕጉ ያለውን ክፍተት ወደ ጠቅላላ ሕግ በመሄድ በፍ/ብሔር ሕጉ ጠቅላላ ስለ ውሎች ከሚለውና ከውል ውጭ ስለሚደርስ ኃላፊነት ድንጋጌዎች ጋር አያይዞ በመመልከት የካሣውን መጠን በርትዕ መወሰን ሲገባው የካሣ ክፍያ ጥያቄው የማስረጃ ድጋፍ የለውም በማለት በተወሰነ ደረጃ ሳይቀበለው መቅረቱና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ስህተት ሳያርም መቅረቱ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44932 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም. በካሣ አከፋፈል ረገድ የሰጠው ፍርድ እንደዚሁም ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30615 ሰኔ 28 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠውን ትዕዛዝ በከፊል በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ በማሻሻል በሥር ፍ/ቤት ከተወሰነው የብር 8000 /ስምንት ሺህ/ ክፍያ በተጨማሪ ብር 22,000 /ሃያ ሁለት ሺህ/ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍሉ በጠቅላላ ከተወሰነው ብር 30,000 /ሰላሳ ሺህ/ ላይ ሁለተኛ ተጠሪ ለአንደኛ ተጠሪ መኪና በሰጠው የመድን ሽፋን መሠረት ብር 10,000 /አሥር ሺህ/ ለአመልካች እንዲከፍል ቀሪውን ብር 20,000 /ሃያ ሺህ/ አንደኛ ተጠሪ ለአመልካች እንዲከፍል ተወስኗል፡፡
2. የዚህን ችሎት ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 36520

ጥቅምት 27 ቀን 2001

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ - ነገረ ፈጅ ሂሩት አስራት ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ፡-** አቶ ይብራህ ግርማይ - ጠበቃ አቶ አበበ ኃይሌ ቀረቡ፡፡

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 42765 ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ. 32556 ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት መጋቢት 17 ቀን 2000 ዓ.ም. ባቀረበው የሰበር አቤቱታ በመጠየቁ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ሲሆን፣ የአሁን አመልካች በከሳሽነት በመቅረብ በሥር በተከሣሽነት የተከራከረው ተጠሪ ንጉሴ ግርማይ ላይ ባቀረበው ክስ የአሁን ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 16 ቀበሌ 11 የቤት ቁ. 834 የሆነውን ቤት ጥር 1 ቀን 1990 ዓ.ም. በተፈረመ የኪራይ ውል በብር 175 /አንድ መቶ ሰባ አምስት ብር/ ተከራይቷል፤ ሆኖም ይህንን ቤት ከአከራዩ ፈቃድና ዕውቅና ውጭና የኪራይ ውሉን በሚጥስ ሁኔታ ለንጉሴ ግርማይ አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ቤቱን እንዲያስረክብ ትዕዛዝ ይሰጥልን በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ በቤቱ ውስጥ የምኖረው እኔ ነኝ፤ ለአቶ ንጉሴ ግርማይ አሳልፌ አልሰጠሁም፤ የሚል ክርክርና ይህንን ያስረዱልኛል የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡ የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካች ያቀረባቸውን ሁለት ምስክሮች ከሰማና በተከሳሽ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ከመዘነ በኋላ የኪራይ ውሉ ፈርሶ ተጠሪ ቤቱን ለአመልካች እንዲያስረክቡ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ተጠሪ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የኪራይ ውሉ የሚቋረጠው /ይግባኝ ባይ/ ተጠሪ ቤቱን ለመኖሪያ ቤት ሣይሆን ለንግድ ቢጠቀምበት ነበር፤ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔ ተገቢነት የለውም በማለት ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን ሽሯል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሣኔ የሚነቀፍበት የሕግ ወይም የፍሬ ጉዳይ ስህተት የለም በማለት ይግባኙን ሰርዞታል፡፡

አመልካች በኪራይ ውሉ አንቀጽ 6/2/ መሠረት ተጠሪ ቤቱን ራሱ ሊገለገልበት እንጂ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለማከራየት ወይም ለመስጠት እንደማይችል ተመልክቷል፤ ተጠሪ ቤቱን ለሌላ ሰው አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ በኪራይ ውሉ አንቀጽ 11/3/ መሠረት ውሉ ይቋረጣል፤ ይህ ሆኖ እያለ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለኪራይ ውሉ አንቀፆች ያልሆነ ትርጉም በመስጠት መወሰኑና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኛችንን መሠረዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ውሣኔ የሰጠው ከቀበሌ የተፃፈለትን ማስረጃና የሁለት ምስክሮች ቃል ሰምቶ ነው፤ ማስረጃው ቀጥተኛ ማስረጃ ሣይሆን የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ነው፤ የሰሚ ሰሚ ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው ማስረጃ ነው፤ በተቃራኒው እኔ በቤቱ ውስጥ እንደምኖር የቀበሌ መታወቂያ ደብተርና ደብዳቤ በማቅረብ አስረድቻለሁ፤ ከዚህ በተጨማሪ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ለኪራይ ውሉ አንቀጽ 6/1/ የሰጠው ትርጉም ተገቢነት ያለው ነው፤ ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሣኔና ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ትዕዛዝ ምንም አይነት የሕግ ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ በማድረግ እንዲያሰናብተኝ በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ተጠሪ የማስረጃ ተዓማኒነትና ተቀባይነትን አስመልክቶ ያቀረበው ክርክር ተገቢነት የሌለው ነው፤ የውሉን አተረጓጎም በተመለከተ ያቀረበው ክርክር የሕግ መሠረት የለውም በማለት የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በሰበር ያደረጉት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የከፍተኛው ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪ ላደረጉት የኪራይ ውል የሰጠው ትርጉም ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ መጣራት ያለበት ሆኖ አግኝተዋል፡፡ ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት ስለውል ድንጋጌዎች አተረጓጎም በፍትሐብሔር ሕግ የተደነገጉትን ድንጋጌዎች መመልከት ያስፈልጋል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የውል ድንጋጌዎች መተርጎም ያለባቸው በተዋዋዮቹ መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅንነትና የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግና በጉዳዮቹ ውስጥ ያለውን ልማዳዊ ሥርዓት በመከተል በቅን ልቦና መተርጎም ያለባቸው ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 የተደነገገ ሲሆን የውል ቃል የሚያሻማ ሆኖ በተገኘ ጊዜ የተዋዋዮች ሃሣብ ምን እንደነበረ በመፈለግና መሠረት በማድረግ ሊተረጎም እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 ንዑስ አንቀጽ 1 ይደነግጋል፡፡ አመልካች የመንግሥት የልማት ድርጅት ነው፡፡ አመልካች የተቋቋመው የነዋሪዎችን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመቅረፍና በተመጣጣኝ ዋጋ ለሕብረተሰቡ አገልግሎት ለመስጠት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር የአመልካችን አገልግሎት ያገኘና የኪራይ ውል የተዋዋለ ሰው ቤቱን በኪራይ ውሉ ከተገለፀው አገልግሎት ውጭ እየተገለገለበት ከተገኘ ውሉ ፈራሽ እንደሚሆን ከኪራይ ውሉ አንቀጽ 6 እና አንቀጽ 11/3/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቤቱን እራሱ በመኖሪያ ቤትነት ለመገልገል ተስማምቶ የተከራየ ተከራይ በተከራይ አከራይነት ቤቱን ሌላ ሰው ለመኖሪያ ቤትነት እንዲገለገልበት አከራይቶ ቢገኝ ወይም ከአከራይ ስምምነትና ፈቃድ ውጭ በሌላ በማናቸውም መንገድ ቤቱን ለሌላ ሦስተኛ ወገን አሳልፎ ሰጥቶ ቢገኝ ቤቱን አከራይ በውሉ ከገለፀው አገልግሎት ውጭ እንደተጠቀመበት ተደርጎ መተርጎም ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም አመልካች የመኖሪያ ቤት የተከራይ አከራይነት መብት በመጠበቅ ውል ያልተዋዋለ በመሆኑ፣ ይህም የአመልካች ሀሣብ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1734 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መታየት ያለበት ነው፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት ከላይ የተገለጹትን መሠረታዊ የውል ሀይለቃል አተረጓጎም ድንጋጌዎች በመተላለፍና ውሉን አመልካች ከነበረው ሀሣብ በላይ በማስፋት አመልካች የኪራይ ውሉን ለማፍረስ የሚችለው ተጠሪ ቤቱን ከተገለፀው ተግባር ውጭ ለንግድ ድርጅትነት ሲጠቀምበት ብቻ ነው በማለት የሰጠው ትርጉምና ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ ይግባኝ ሰሚው ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንን ስህተት አለማረሙ በአመልካችና በተጠሪ መካከል ያለውን የኪራይ ውል በመተርጎም በኩል የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአተረጓጎም ስህተት የተጋራ መሆኑን ያመለክታል በማለት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግንቦት 22 ቀን 1999 ዓ.ም. እና የፌ/ጠቅላይ ፍርድ ቤት ታህሣሥ 16 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፣ ይፃፍ፡፡
2. ተጠሪ ከአመልካች ጋር የገቡትን የኪራይ ውል ያላከበሩ በመሆኑ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ቤቱን ለአመልካች ያስረክቡ በማለት ጥቅምት 2 ቀን 1998 ዓ.ም. በመዝገብ ቁጥር 44194 የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፤ ይፃፍ፡፡

3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ጥቅምት 27 ቀን 2001 ዓ.ም. በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ.ቁ. 29363

ኅዳር 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ወርቅነሽ አምዴ - ጠበቃ አስናቀ ከፋለ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ጥላሁን አርምዴ ከጠበቃ ሰብስቤ ባልቻ ጋር ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ሲሆን ተጠሪ በአመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ተጠሪ የወንድሜ ልጅ በመሆኑ ከባለቤቴ ሞት በኋላ አብሮኝ እንዲኖር በወረዳ 23 ቀበሌ 10 በሚገኘው ቁጥር 190 በሆነው ቤት አስጠግቼው ሲኖር የግል ሀብቴን ለመውሰድና ለመጠቀም አስቦ ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም አሞኝ በነበረበት ወቅት እንደማላነብና መሐይም መሆኔን በማወቅ የስጦታ ውል አዘጋጅቶ አስፈርሞኛል፡፡ ከዚያም በጥር ወር 1991 ዓ.ም ቤተክርስትያን ሄጄ ስመለስ ወደ ቤቴ እንዳልገባ ከልክሎኛል ስለሆነም ነሐሴ 9/1984 ዓ.ም የተደረገው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ተብሎ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀዋል፡፡

ተጠሪም ቀርበው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያና ሙሉ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት ያነሱት ክርክርም በዚህ ጉዳይ አስቀድመው በከተማ ነክ ፍ/ቤት ክስ አቅርበው ተቀባይነት ሣያገኝ የቀረ ሲሆን በዚያው ጉዳይ በድጋሚ ክስ ማቅረባቸው ተገቢ አይደለም፡፡ የስጦታ ውሉ ይሻርልኝ ተብሎ የቀረበው አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት በይርጋ ቀሪ ሆኗል የሚሉ ናቸው፡፡ በፍሬ ጉዳይ ክርክር ረገድም የስጦታ ውሉ በሕግ አግባብነትና በአመልካች ሙሉ ፈቃደኛነት እንደተደረገ ጠቅሰው ሊሻር ይገባል ተብሎ የቀረበ አቤቱታ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ ተጠሪ አስቀድሞ ጉዳዩ ውሣኔ አግኝቷል በማለት ያቀረቡትን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በተመለከተ አስቀድሞ ለከተማ ነክ ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረው አቤቱታ ሁከት ይወገድልኝ በማለት እንጂ የስጦታ ውሉ ይፍረስልኝ በማለት ስላልሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 5 መሠረት መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም ብሏል፡፡

ይርጋን አስመልክቶ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያ በተመለከተም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 መሠረት የይርጋ መቃወሚያ ማቅረብ የሚቻለው ውሉ ሲመሰረት የችሎታና የፈቃድ ጉድለት አለበት በሚባልበት ጊዜ ሲሆን ተጠሪ ደግሞ ውሉ እንዲፈርስ የጠየቁት ችሎታና ፈቃድ መሠረት አድርገው ሣይሆን መሐይም ነኝ በማለት ስለሆነ የዚህ ዓይነቱ ጥያቄ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ሥር ስለማይሸፈን አቤቱታው በይርጋ ቀሪ አይሆንም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የፍሬ ጉዳይ ክርክሩን መርምሮ የማይንቀሣቀስ ንብረት ስጦታ በሚደረግበት ጊዜ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 881 መሠረት ግልጽ ኑዛዜ በሚደረግበት ሥርዓት ሊደረግ እንደሚገባ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 ላይ የተመለከተ ሲሆን ነገር ግን በማስረጃነት

የቀረበው የስጦታ ውል ሲታይ ግን ስጦታ አድራጊውና ምስክሮች ባሉበት ከተነበበ በኋላ የተፈረመ ስለመሆኑ ስለማያስረዳ ፈራሽ ነው በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ጉዳዩን በይግባኝ የተመለተውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ ይግባኝ ባይ የስጦታ ውሉ እንዲፈረስ ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1810 ላይ የተመለከተው የ2 ዓመት የይርጋ ጊዜ ካለፈ በኋላ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ አልሆነም ማለቱ ተገቢነት በሌለው ሁኔታ ነው በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም በአመልካች በኩል የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ ግራቀኙን በማከራከር የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙ አከራክሯል፡፡

ምላሽ ማግኘት የሚገባውም የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች በተጠሪ ላይ ያቀረቡት የስጦታ ውል ይፍረስልኝ አቤቱታ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በይርጋ ቀሪ ሆኗል መባሉ በአግባቡ ነው ወይንስ አይደለም? የሚለው ነው፡፡

ከዚሁ ጭብጥ አኳያም አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አመልካች በተጠሪ ላይ ክስ ያቀረቡት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ታምሜ በነበረበትና መሐይም መሆኔንም በማወቅ የመኖሪያ ቤት የስጦታ ውል ያስፈረመኝ ስለሆነ ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ነው፡፡

ስጦታ እንዲቀነስ ወይም እንዲሻር የሚቀርብ አቤቱታ ስጦታው ከተደረገበት ቀን አንስቶ እስከ 2 ዓመት ባለው ጊዜ ለዳኞች ካልቀረበ ዋጋ እንደሌለው / በይርጋ እንደሚቋረጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ ላይ ተደንግጓል፡፡

አመልካች የስጦታ ውሉ ተፈርሟል የሚሉት ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም ሲሆን ይሄው የስጦታ ውል ፈራሽ ነው ይባልልኝ በማለት ክስ ያቀረቡት ደግሞ ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ዘጠኝ ዓመት ሊሞላው ጥቂት ወራት ሲቀር ነው፡፡ አመልካች ነሐሴ 9 ቀን 1984 ዓ.ም የተፈረመው ሰነድ የስጦታ ውል መሆኑን ያወቅሁት የካቲት 8 ቀን 1991 ዓ.ም ለሚመለከታቸው ክፍሎች አቤቱታ ሣቀርብ ነው ያሉትን በመውሰድ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንኳ ክስ እስካልቀረቡበት ሰኔ 1 ቀን 1993 ዓ.ም ያለው ሲታሰብም 2 ዓመት እንዳለፈው መገንዘብ ይቻላል፡፡

በሌላ በኩልም የፌዴራል ከፍ/ቤት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል ያለው በፍ/ብ/ቁ. 1810 ላይ እንደተመለከተው በ2 ዓመት ጊዜ አልቀረበም በማለት ነው፡፡

በግራ ቀኙ መካከል ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል እንደመሆኑ መጠን ይህንኑ ግንኙነት በተለይ የሚገዛው በፍ/ብሔር ሕጉ ስጦታን አስመልክቶ በተደነገጉት ድንጋጌች መሠረት ሲሆን ወደ ጠቅላላ የውሎች ሕግ ድንጋጌዎች መሄድ የሚቻለው በልዩ ሕግ ላይ ተመስርቶ ለጉዳዩ ዕልባት ለመስጠት ካልተቻለ ነው፡፡ በዚሁ መሠረትም የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት ጉዳዩን ከስጦታ ውል ድንጋጌዎች አኳያ መርምሮ ለይርጋ ክርክሩ እልባት መስጠት ሲገባው ስለ ውሎች በጠቅላላው በሚለው ምዕራፍ ሥር የተደነገገውን የይርጋ ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ውሣኔ መስጠቱ ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር ተገቢነት የሌለው ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ.1810 ላይ የተመለከተውና ውሉ የማይረጋበት ምክንያት ከቀረበት ጊዜ ጀምሮ ከ2 ዓመት በኋላ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ አይቀርብም ተብሎ የተመለከተውም ውሉ በችሎታና በፈቃድ ረገድ ጉድለት በሚኖረው ጊዜ ነው፡፡ መሐይምነትን ወይንም ዓይነስውርነትን አስመልክቶ የሚቀርብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ከውሉ የአፃፃፍ ሥርዓት /ፎርም/ ጋር ተያይዞ እንደሚነሣ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1719 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች መገንዘብ የሚቻል እንደመሆኑ መጠን የዚህ ዓይነቱ ጥያቄም በይርጋ የሚታገደው በቁጥር 1845 እንጂ በቁጥር 1810 ላይ እንደተደነገገው ስላልሆነ በዚህ ድንጋጌ መሠረት አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ ለድንጋጌው የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት መሆኑን ተገንዝበናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 64 በ17/6/95 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ተሽሯል፡፡

2/ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 18957 ጥር 23 ቀን 1998 ዓ.ም አቤቱታው በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የሰጠው ውሣኔ ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ሲሆን ከውጤት አኳያ የሚነቀፍ ስላልሆነ እንደዚሁም የፌዴራል ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 23712 ጥር 29 ቀን 1999 ዓ.ም ይህንኑ ውሣኔ ማጽናቱ ከውጤት አኳያ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡

3/ አመልካች የስጦታ ውል ይፍረስልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2441/1/ መሠረት በ2 ዓመት ጊዜ ስላልቀረበ በይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት ወስነናል፡፡

4/ ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

5/ መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአራት ዳኞች ፊርማ አለበት

## የሀሣብ ልዩነት

እኔ በአምስተኛው ተራ ቁጥር የተሰየምኩት ዳኛ አመልካች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2434 ድንጋጌዎች መሠረት ጥብቅና በግሏ ብቻ አመልካች ሆነ ብላና አስባበት ልትፈጽመው የሚገባው ተግባር /ስጦታ/ አልፈፀምኩም እያለች ተከራክራለች፡፡ አመልካች ተጠሪ አሳስቶ የስጦታ ውል ያስፈረምኩኝ መሆኑን ያወቅሁት በጥር ወር 1991 ዓ.ም ነው በማለት ተከራክራለች፡፡ እንደዚህ ከሆነ የይርጋው ጊዜ መቆጠር ያለበት ከጥር ወር 1991 ጀምሮ መሆን ይገባዋል፡፡ ውሉ በተንኮል ተቀነባብሮ አመልካች ሣታውቅ የተፈረመ ነው የሚል ክርክር ያለበት በመሆኑ የይርጋ የጊዜ ገደቡም በተንኮል የተዘጋጀ ውል ይታወቅ መፈረሙን ካወቀችበት ከጥር ወር 1991 ዓ.ም ጀምሮ ባለው አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ መሆን አለበት፡፡ ምክንያቱም ለእንደዚህ ዓይነት ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንጅ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2441 አይደለም የሚል አምነት አለኝ፡፡ ስለሆነም ወደ ዋናው ጉዳይ ተገብቶ የስጦታው ሕጋዊነት መመርመር አለበት፡፡ የይርጋ ጊዜ አልፎበታል ተብሎ መዘጋቱ ተገቢ አይደለም የሚል እምነት ስላለኝ ከሙያ አጋሮቸ በሃሣብ ተለይቻለሁ፡፡

የማይነበብ የአንድ ዳኛ ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 36740

ህዳር 23 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

አልማው ወሌ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** አቶ ዓብዱል ዋሀብ ኢብራሂም - ጠ/ ገ/ማርያም ገ/እግዚአብሔር

**ተጠሪ፡-** 1. ወ/ት መሰለች ከፍያለው
2. አቶ ሰለሞን ከፍያለው } ቀረቡ ጠበቃ መኰንን አምበ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች በስር ፍ/ቤት ከሣሾች ሲሆኑ አመልካች ተከሣሽ ነበሩ፡፡ ከሣሾች ባቀረቡት ክስም የከሣሾች አባት በከፍተኛ 24 ቀበሌ 13 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 2011 የሆነውን ቤት በ3/13/1980 ዓ.ም በተፃፈ የወለድ አገድ ውል በብር 29,000 (ሃያ ዘጠኝ ሺ.ህ) ለ10 አመት ለአመልካች/ተከሣሽ ያስያዙት ሲሆን የከሣሾች አባት በ21/6/89 ዓ.ም ከሞቱ በኋላ አመልካች ገንዘባቸውን ወስደው ቤቱን እንዲያስረክቡን ብንጠይቃው ፈቃደኛ ስላልሆኑ ገንዘቡን ተቀብለው ቤቱን ያስረክቡን፣ ማስጠንቀቂያ ከደረሣቸው ጊዜ ጀምሮ የቤቱን ኪራይ እንዲከፍሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡

የሥር ተከሣሽ የአሁኑ አመልካች ለክሱ በሰጡት መልስ፤ በ3/13/1980 የተደገውን ውል መሠረት በማድረግ የቀረበው ክስ በይርጋ ይታገዳል፣ 8 ዓመት ያለፈ የቤት ኪራይ ጥያቄም ቢሆን በይርጋ ቀሪ የሚሆን ነው፡፡ ይህ ቢታለፍ ግን በ3/13/1980 የወለድ አገድ ውል ተደርጎ ቤቱንና ቤቱን የሚመለከቱ ሠነዶች ተረክቤአለሁ፡፡ ከዚህ በኋላም ለግለሰብ ቤት እንዲሸጥ ስለፈቀደ የተጠሪዎች ወላጅ አባትና ባለቤታቸው ነሐሴ 06/1988 በተፃፈ ውል በአ.አ ከተማ መስተዳድር የውልና ማስረጃ ጽ/ቤት ተፈራርመን የቤት ሽያጭ ውል ፈጽመናል፣ ስለሆነም የወለድ አገድ ውሉ በሽያጭ ውል ስለተተካ ሊከሱኝ አይችሉም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የሽያጭ ውሉ በ6/12/88 መደረጉን ቢገልፁም የተመዘገበው ግን 17/03/1991 ነው፡፡ ውሉ በተመዘገበበት ቀን ደግሞ የከሣሾች አውራሽ በህይወት አልነበሩም በመሆኑም አመልካች ባቀረቡት የሽያጭ ውል ላይ የተጠሪዎች አባት ሊፈርሙ የማይችሉ በመሆኑ የሽያጭ ውል ፈርመናል የሚለው ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ የግራ ቀኙ ግንኙነት በ3/13/80 ዓ.ም የተደረገው የመያዣ ውል ነው በማለት ተጠሪዎች የሚፈለግባቸውን ብር 29,000(ሃያ ዘጠኝ ሺ.ህ) ለአመልካች ሲከፍሉ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ይግባኛቸውን ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ፤ የሽያጭ ውል የተፃፈው በ6/12/1988 ሲሆን የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርቦ በኃላፊ የተመራበትና የተፈረመበት የተዋዋይ ወገኖች የምስክሮች ፊርማና መታወቂያ የተረጋገጠው በዚሁ ቀን ቢሆንም የዕዳና እገዳ እስከሚሠራ የፎርማሊቲ ስርዓቱና ክፍያ መፈፀሚያው ተቋርጦ እንደገና ማጣራት ተደርጎ በ1991 ዓ.ም ተረጋግጦ ወጭ ሆኗል ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ውል በፊቱ ሲደረግ አረጋጋጭ እንጂ ውል መዝጋቢ አካል ባለመሆኑና ውል በፊቱ

የተደረገው በ6/12/1988 ዓ.ም በመሆኑ የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ አመልካች ቤቱን በሕጋዊ ውል የያዙት በመሆኑ ሊያስረክቡ አይገባም፤ በማለት ወስኗል፡፡

ተጠሪዎች ደግሞ በዚህ ውሣኔ ላይ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ካከራከረ በኋላ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በመሻር የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሣኔ ለማስለወጥ ነው፡፡ ይህ ችሎትም የሽያጭ ውል የተደረገው መቼ ነው የሚለውን ጉዳይ ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ በማድረግ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሠበር አቤቱታውን የሠበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብ ካለው ሕግ ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው ተጠሪዎች በአመልካችና በተጠሪዎች አውራሽ መሃከል ያለው የወለድ አገድ ውል ነው ሲሉ አመልካች ደግሞ ከወለድ አገድ ውሉ በኋላ የቤት ሽያጭ ውል ተደርጓል በማለት ተከራክረዋል ተጠሪዎች የሽያጩ ውል ተደረገ የተባለው አውራሻችን ከሞቱ በኋላ በመሆኑ የሽያጭ ውል የለም ሲሉ አስተባብለዋል፡፡ ችሎቱም የሽያጭ ውሉ መቼ ነው የተደረገው የሚለውን አግባብ ካለው ሕግ ጋር አናዝቦ መርምሯል፡፡

አንድ ውል ፍፁም ነው የሚባለው ተዋዋዮቹ በተስማማ አኳኋን መፍቀዳቸውን ገልፀው ሲገኙ መሆኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1680/1/ መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም ውል አቅራቢው በቃልም ሆነ በጽሁፍ በማያጠራጥር ሁኔታ ግዴታ ለመግባት መፍቀዱን ካሣወቀና ውል ተቀባዩም በተመሣሣይ መልኩ የውል ድርድሩን መቀበሉን ካሣወቀ በሁለቱ መሐከል ስምምነት መደረጉን ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1681 መረዳት ይቻላል በእርግጥ ጉድለት የሌለበት ፈቃድ ከመስጠት በተጨማሪ ሕጉ ልዩ የሆነ የሚጠበቅ አፃፃፍ ፎርም እንዲኖር ካስገደደ ይኸው የአፃፃፍ ሥርዓት መሟላቱ ለውሉ ሕጋዊነት ሌላው መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ስለሆነም ተዋዋዮች ነፃ ፈቃዳቸውን ከመስጠታቸው በተጨማሪ ውሉን ሕጉ በሚያዘው የአፃፃፍ ሥርዓት ሊመሠርቱ ይገባል፡፡ ለምሣሌ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ውሉ በጽሁፍ ከመደረጉ በተጨማሪ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723/1/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው የቤት ሽያጭ ውል መደረግ ያለበት በጽሑፍ ብቻ ሣይሆን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው ሰው ወይም በዳኛ ፊት ጭምር ነው፡፡ ውሉ በአዋዋይ ወይም በዳኛ ፊት እንዲደረግ ያስፈለገበት ዋነኛ አላማም የተዋዋዮቹ ማንነት ያላቸው ችሎታና መብት ነፃ ፈቃዳቸውን መስጠታቸውን ውሉ የተደረገበትን ቀንም ለማረጋገጥ ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ የተጠሪዎች አውራሽ እና አመልካች ውላቸውን በ6/12/1988 ዓ.ም በተፃፈ ሰነድ አዘጋጅተው ሁለቱም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ቀርበው መፈረማቸው የምስክሮቹም ማንነትና ፊርማ በዚሁ ውሉ በተፃፈበት ቀን መረጋገጡን ከክርክሩ ሂደት ተረድተናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪ አውራሽና አመልካች የቤት ሽያጭ ውሉን ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያደረጉት በ6/12/1988 መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በእርግጥ ግራ ቀኙ ውሉን በ6/12/1988 የፈፀሙ ቢሆንም ቤቱን የሚመለከቱ ዕዳና እገዳ ለማጣራትና ክፍያ ለመፈፀም የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በውሉ ላይ ማህተም ሣያሣርፍበትና የፕሮቶኮል ቁጥር ሰጥቶ ሣያረጋግጥበት የተወሰነ ጊዜ ማለፉን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን አንዳንድ አስተዳደራዊ ጉዳዮች እስኪከናወኑ ድረስ በውሉ ላይ ማህተም ሣያርፍበት መቆየቱ ወይም የፕሮቶኮል ቁጥር ሣይሰጠው መዘግየቱ ውሉ እንዳልተደረገ የሚያስቆጥረው ነው ለማለት አያስችልም፡፡

በሌላ በኩል ሠነዱን የፃፈው ወይም የተቀበለው የመንግሥት መ/ቤት ከሆነ ሰነዱ የተፃፈበት እርግጠኛ ቀን ነው የሚባለው የፃፈበት ወይም የተቀበለበት ቀን በመሆኑ /የፍ/ብ/ህ/ቁ.2015/ሀ/"ን" ይመለከቷል/ የውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት የሽያጩን ውል ያፈራረመበትና ሰነዱን የተቀበለበት ነሐሴ 6/1988 ዓ.ም የሰነዱ ትክክለኛ ቀን ተብሎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ ሻጭና ገዢ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ቀርበው የሽያጭ ውልን የተፈራረሙበት ቀን ተረጋግጦ እያለ ውሉ ተደረገ ሊባል የሚችለው በዚህ ቀን ሣይሆን አንዳንድ የአስተዳደር ጉዳዮች ተጣርተው መ/ቤቱ ማህተም ያደረገበት ቀን ነው በማለት የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1/ የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 62466 በ22/02/99 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33198 በ3/07/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡

2/ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 50414 በ18/11/1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡

3/ አመልካች ቤቱን በ6/12/88 ዓ.ም በተደረገ የሽያጭ ውል የያዙት በመሆኑ ተጠሪዎች ቤቱን እንዲያስረክቡ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፡፡ አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡

4/ ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 36294

ህዳር 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሠናይት ገነሜ ገንታ - ሣሙኤል ደመቀ ቀረበ

**ተጠሪዎች፡-** 1. በቀለ ገመዳ ዳኖ

2. ወ/ሮ ወርቅነሽ ጀቤሣ ኤጎ } ጠበቃ ማረን ወንዴ ቀረበ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታው መነሻ የሆነው ጉዳይ የቤት ሽያጭ ውልን መሠረት ያደረገ ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ ክርክሩ በተጀመረበት የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሣሽ የነበረችው አመልካች ናት፡፡ ተጠሪዎችን የከሰሰችውም ይቻላል በተሰኘ ማህበር በሸንሻኖ ቁጥር 13 የሚታወቅ 175 ካሬ ሜትር ግቢ ያለው ጅምር ቤት ሸጠውልኝ ውሉ በተደረገበት ዕለት ቀብድ ከፍያለሁ ቀሪውን ደግሞ በማህበሩ በአባልነት ሲያስመዘግቡኝ፣ እዳና እገዳ እንደሌለበት ሲያረጋግጡ፣ ካርታውን ከአስፈላጊው ዶክመንቶች ጋር ሲያስረክቡኝ፣ ጉዳዩ ለማህበራት ማደራጃና ማስፋፊያ ቢሮ ሲቀርብ እንደዚሁም የሽያጭ ውሉ በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት ሲፈፀም ልከፍል ተስማምተናል፡፡ ሆኖም ተጠሪዎች እንደውላቸው አልፈፀሙም፡፡ ይልቁንም የጀመርኩትን ግንባታ እንዳላካሂድ ችግር ፈጥረውብኛል፡፡ ስለዚህ በውላቸው መሠረት እንዲፈጽሙ ይገደዱልኝ በውሉ የተመለከተው የመቀጫ ገንዘብ እንዲከፍሉም ይወሰንባቸው በማለት ነው፡፡ ተጠሪዎች ለክሱ በሰጡት መልስ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር ክርክር አቅርበዋል የተከሣሽ ከሣሽነት ክስ አቅርበውም ውሉን ለመተግበር ያልቻለችው አመልካች ናት በማለት መቀጫ ትከፍላቸው ዘንድ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡ በመጨረሻም ፍ/ቤቱ ክሱን ከሰማ በኂላ በሁለቱ መካከል ተደረገ የተባለው የሽያጭ ውል የሕጉን መስፈርት አያሟላም የሚል ምክንያት በመስጠት በሁለቱም ወገኖች የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ወስኖአል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ውሣኔውን በመቃወም ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረብዋ ክርክሩ በድጋሚ የተሰማ ሲሆን በመጨረሻም ፍ/ቤቱ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተሰጠውን ውሣኔ አጽንቶአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች መጋቢት 4 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈችው ማመልከቻ ያቀረበችውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ክርክር ያስነሣው ጉዳይ የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል የሚመለከት ነው ወይስ በማህበርተኝነት የመተካት መብትን የሚመለከት? የሚለውን ነጥብ ለማጣራት ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

ከስር ጀምሮ የተደረገውን ክርክር በዝርዝር ተመልክተናል፡፡ ከዚህም ግራ ቀኝ ወገኖች የቤት ሽያጭ ውል አድርገናል ብለው ያምኑ እንደነበር፤ በውሉ አፈፃፀም ረገድ ችግር ካጋጠማቸው በኂላ ግን ወደ መካሰስ እንዳመሩ፣ በመጨረሻም በተለይ ተጠሪዎች በሕጉ መሠረት የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል የለም ወደሚለው በማዘንበል እንደተከራከሩ

ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ክሱን ያስተናገደው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጨረሻ ውሣኔ የሰጠው በግራ ቀኝ ወገኖች መካከል ተደረገ የተባለው የቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ ቁ.1723 የተመለከተውን መስፈርት አያሟላም በረቂቅ ደረጃ የቀረ ነው በማለት ነው፡፡

በእርግጥ የፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 የማይንቀሣቀሱ ንብረቶችን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረጉት ውሎች ማሟላት ስለሚገባቸው መስፈርቶች ደንግጎአል፡፡ ከዚህ የተነሣም እንደውሉ ይፈፀም ዘንድ ውሣኔ እንዲሰጥ የተጠየቀው ፍ/ቤት የውሉን ሕጋዊነት በቅድሚያ ለማረጋገጥ ክርክሩ ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 አንፃር ማየቱ ተገቢ ይሆናል፡፡ በሌላ በኩል ግን ውል ነው በሚል የቀረበለት ሰነድ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 እንደተመለከተው በእርግጥም የማይንቀሣቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ለማድረግ ታስቦ የተደረገ ነው ወይስ ሌላ የሚለውን ነጥብም መመርመሩ ተገቢ የሚሆንበት አጋጣሚ እንደሚኖር ማሰቡ ተገቢ ይሆናል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደሚታየው ተጠሪዎች በእነሱ ስም ብቻ ካርታና የባለቤትነት መታወቂያ ተለይቶ የተሰጠው ቤት እንዳላቸው ክርክሩ አያመለክትም፡፡ ይልቁንም ጅምር ነው የተባለው ቤት የሚገኘው ይቻላል በተሰኘ የቤት ሥራ ማህበር አጠቃላይ ይዞታ ስር እንደሆነ ነው መዝገቡ የሚያመለክተው ተጠሪዎች የዚህ ማህበር አባላት እንደመሆናቸው መብት እንዳላቸውም የሚያከራክር አይደለም፡፡ አከራካሪ የሚሆነው ወይም ልዩ ትኩረት በመስጠት ሊታይ የሚገባው ተጠሪዎች በማህበሩ ላይ ያላቸውን መብት ለሦስተኛ ወገን ሊያስተላልፉ ይችላሉ ወይ? የሚችሉ ከሆነስ ስርዓቱ ምንድነው? የሚለው ነው፡፡

ሰዎች በመደራጀት የሕብረት ስራ ማህበር ማቋቋም እና በዚህም በጋራ የመጠቀሙ ሁኔታ በሕግ እውቅና የተሰጠው ነው፣ በዚህ መልክ የሚቋቋሙት ማህበራት በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው መብትና ግዴታቸውም በሕግ የተወሰነ ነው፡፡ የህብረት ስራ ማህበራትን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ በሥራ ላይ ያለው የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 147/91 ነው፡፡ ይህ አዋጅ ስለማህበራት ዓላማ፣ ስለማህበራት አመሠራረት፣ ስለሚመሩባቸው መርሆዎች፣ ስለሕግ ሰውነትና ኃላፊነት፣ ስለመተዳደሪያ ደንብ፣ ወዘተ በተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌዎችን አካቶአል፡፡ በዚህ መዝገብ ለተያዘው ጉዳይ አወሳሰን ቀጥተኛ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች አንዱ የአዋጁ አንቀጽ 19 ሲሆን ይህም በአንድ በኩል የማህበር አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ እንደሚችል በመርህ ደረጃ ሲደነግግ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማስተላለፉ ሁኔታም የራሱ የሆነ የተለየ ስርዓት እንዳለው ያመለክታል፡፡ የማህበሩ አባል ዕጣውን ወይም ጥቅሙን ለማስተላለፍ ቢፈልግ ከማህበሩ የሥራ አመራር ኮሚቴ ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የሚለው አንዱ ሁኔታ እንደሆነ በንኡስ አንቀጽ 1/ለ/ ተመልክቶአል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው በማህበር ተደራጅቶ የተገኘውን መብት የማስተላለፊያ ስርዓቱ በግል ከተገኘ መብት የተለየ መሆኑን ነው፡፡ መብት የሚተላለፍለት ወገንም በአስተላላፊው መብት መጠቀም የሚችለው በመተካት የማህበሩ አባል መሆን ከቻለ ብቻ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 ከተመለከተው የማይንቀሣቀስ ንብረት መብት ማስተላለፊያ ስርዓት የተለየ ነው፡፡ በመሆኑም በማህበር በመደራጀት የተሠራውን ቤት ሽያጭ ውል በፍ/ብ/ሕግ ቁ/ 1723 ከተመለከተው ድንጋጌ ጋር አያይዞ ማየቱ ትክክል አይሆንም በተያዘው ጉዳይም ተጠሪዎች ከአመልካች ጋር የተዋዋሉት በማህበሩ ያላቸውን መብት ለማስተላለፍ በመሆኑ ክርክሩ መታየት ያለበት ከአዋጅ ቁ. 147/91 አንፃር ነው፡፡ ሲጠቃለል የስር ፍ/ቤቶች ውሉ በፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 መሠረት የተደረገ አይደለም ከሚል በመነሣት የሰጡት ውሣኔ ሕጉን የተከተለ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 19000 ሐምሌ 5 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ. 49515 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽረዋል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪዎች መካከል ተፈጠረ የተባለው ግንኙነት መታየት ያለበት ከፍ/ብ/ሕግ ቁ. 1723 አንፃር ሣይሆን ከህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁ. 147/91 አንፃር ነው ብለናል፡፡
3. አመልካች ጥያቄዋን ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ታቅርብ፡፡
4. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

የሰ/መ/ቁ. 33473

ኀዳር 16 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሃርሴማ ሰሎሞን - ጠበቃ አቶ አምባቸው ዮሐንስ ቀረቡ፡፡

**መልስ ሰጪ፡-** የአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲ - ነገረ ፈጅ አቶ ግርማ ገ/ፃዲቅ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን መርምረን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ የሰበር መዝገብ ሊቀርብ የቻለው የግራ ቀኙን ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛው ፍ/ቤት በይግባኝ ተመልክቶ በኮ/መ/ቁ. 56916 ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት የሰጠው ዳኝነት ተገቢውን የሕግ ትርጉም ያልተከተለ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት በቀረበው የሰበር አቤቱታ መነሻ ነው፡፡

ጉዳዩም ባጭሩ እንደሚከተለው ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭ ከሣሽ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ በመሆን በደቡብ ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግሥት በጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ተከራክረዋል፡፡ ከሣሽ ተከሣሽን አስተምሯል፡፡ ተከሣሽም ከትምህርት ተመልሰው ከሣሽን ለማገልገል ግዴታ ገብተዋል፡፡ የማያገለግሉ ቢሆን ለማስተማር ተብሎ የወጣውን ወጭ ብር 290,961 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ ለመክፈል ተዋውለዋል፡፡ ስለሆነም እንደውሉ ለአራት ዓመት እንዲያገለግሉ ወይም ገንዘቡን እንዲከፍሉ ይወስንልን የሚል ክስ ቀርቧል፡፡

ተከሳሽም ለዚሁ ክስ የሰጡት መልስ ወጭውን የሸፈነው የኔዘርላንድ ፌሎውሺፕ ፕሮግራም ነው፤ ግዴታውም ወደ አገራቸው ተመልሰው እንዲያገለግሉ እንጂ በከሣሽ ተቋም ለማገልገል አይደለም፤ እንደገቡት ግዴታም ወደ አገራቸው ተመልሰው በማገልገል ላይ ናቸው፤ የቀረበውም ውል በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም፤ ግልጽ ነፃነትን የሚያሰናክል ስለሆነ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

የግራ ቀኙን ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ ያየው ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 03727 ግንቦት 02 ቀን 1999 ዓ.ም. በዋለው ችሎት በግራ ቀኙ መካከል የተደረገው ውል ቀርቧል፤ የትምህርት ደረጃቸውን እንዲያሻሽሉ የአንድ ዓመት ዕረፍት ተሰጥቷል፤ የትምህርት ዕድሉም የተሰጠው ባገኙት ተጨማሪ ችሎታ መሠረት እንዲያለግሉ ነው፤ ሲመለሱም ለአራት ዓመት ተኩል ለማገልገል ተዋውለዋል፤ ሰኔ 23 ቀን 1995 ዓ.ም. የተፃፈላቸው ደብዳቤ የትምህርት ዕድሉ የተገኘው በዩኒቨርሲቲው እንጂ በግላቸው አለመሆኑን ያሳያል፤ በመሆኑም እንደግዴታቸው ካላገለገሉ ከሣሽ ወይም 3ኛው ወገን የከፈለለትን ገንዘብ ለአሠሪው መክፈል እንደሚገባው በውሉ ላይ ስለተመለከተ እና መብትና ግዴታው በግልጽ ስለተጠቀሰ በገቡት ግዴታ መሠረት ያገልግሉ ወይም ገንዘቡን ብር 290,961.00 ይክፈሉ ሲል ወስኗል፡፡

በአሁን አመልካች ቅሬታ አቅራቢነት የይግባኝ ጉዳዩን የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በሥር ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት አላገኘሁበትም በማለት በመልስ ሰጭነት የተሰየመውን ሳይጠራ መዝገቡን ዘግቷል፡፡

የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ከላይ ባጭሩ በየደረጃው ባሉት ፍ/ቤቶች የተሰጠው ዳኝነት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው፤ ሊታረም ይገባል የሚለውን መሠረት በማድረግ ነው፡፡

የቅሬታው ፍሬ ቃልም፡-

የትምህርት ዕድሉ የተገኘው በግል በመፃፃፍ ሆኖ እያለ ይህ አልታየልኝም፤ ወጭውንም የሸፈነው የትምህርት ዕድሉን የሰጠኝ ድርጅት ነው፤ ስለዚህ የአሁን መልስ ሰጭ በጉዳዩ አመልካች ላይ ክስ የማቅረብ መብት የለውም፤ ትምህርቱን የተማርኩት ከሦስተኛው ወገን ጋር ባደረኩት ስምምነት መሠረት ነው፤ ስምምነቱም ወደ አገር ተመላሼ ለማገልገል ነው፤ ውሉን የፈረምኩትም ካልፈረምሽ የዕረፍት ፍቃዱ አይሰጥሽም የድጋፍ ደብዳቤም አንጽፍም ስላሉኝና አዘጋጅተው በማቅረባቸው እንቅፋት እንዳይፈጠር በመስጋት ነው፤ በግል ያገኘሁት ስለመሆኑ ወጭውንም ሦስተኛው ወገን ስለመሸፈኑ ያስባገኘም ግዴታ ምን እንደሆነ የሚያረጋግጥ ማስረጃ አቀርባለሁ፤ እንደውሉ ይፈፀም እንኳ ቢባል የግል ነፃነቴን ይነካል፤ ለትምህርት ምን ያህል ገንዘብ እንደወጣ እንኳን ሳይረጋገጥ የተሰጠ ውሣኔ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል የሚል ነው፡፡

የአሁን መልስ ሰጭም የበኩሉን ክርክር አቅርቧል፡፡ ይዘቱም በግሌ የተገኘ የትምህርት ዕድል ነው የተባለው ሀሰት ነው፤ በ1995 ዓ.ም. የኔዘርላንድስ መንግሥት በሰጠው ነፃ የትምህርት ዕድል ዩኒቨርሲቲው ተጠቃሚ እንዲሆን ከትምህርት ሚ/ር በተፃፈ ደብዳቤ መነሻ እንዲወዳደሩ ተደርጎ ያገኙት ለመሆኑ፣ የትምህርት ዕድሉ በዩኒቨርሲቲው ኮታ ለመሆኑ፣ ትምህርቱን እንዲማሩ ስፖንሰር የሆነው መልስ ሰጭ ለመሆኑ በማስረጃው ከመልሱ ጋራ አያይዘናል፤ ውሉን የፈፀሙት በገዛ ፈቃዳቸው እንጂ መገደድ ስላልተፈፀመባቸው በግራ ቀኛችን መካከል የተደረገው ውል እንደ ሕግ ያገለግላል፤ ሦስተኛ ወገን ሳይሆን ደመወዝ ከፍሎና ስፖንሰር ሆኖ ያስተማረ በመሆኑ በጉዳዩ ላይ ክስ ለማቅረብ መብት አለው የሚሉ ናቸው፡፡

አመልካችም በመልስ መልሳቸው ላይ ክርክራቸውን በማጠናከር አቅርበዋል፡፡

በሰበር ደረጃም ሆነ በሥር ፍ/ቤቶች ሁለቱም ወገኖች ያቀረቡት ክርክር ከላይ ባጭር ባጭሩ የተመለከተው ሲሆን እኛም ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

አመልካች በሥር ፍ/ቤትም ሆነ በዚህ የሰበር ችሎት የሚያቀርቡት የትምህርት ዕድሉን ያገኘሁት በግል ባደረግሁት መፃፃፍ ነው፤ በዚህም የተነሣ ወጭውን የሸፈነው ሦስተኛ ወገን ነው፤ የግዴታውም ዓይነት ወደ አገሬ ተመልሼ እንዳገለግል የሚገልጽ ሲሆን ወደ አገሬም ተመልሼ እያገለገልኩ ስለምገኝ የሚጠበቅብኝ ግዴታ የለም የሚለው የፍሬ ነገር ክርክር ይገኝበታል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አኳኋን የቀረበውን የማስተባበያ የፍሬ ነገር ክርክር ተከራካሪው ወገን በማስረጃ አስደግፎ ማስረዳት ይኖርበታል፡፡ የመዝገቡን ግልባጭ እንዳየነው ይህንኑ ክርክር ሊደግፍ የሚችል ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም አንድ ተከራካሪ ወገን በማስረጃ ያልተደገፈ የፍሬ ነገር ክርክር ስለገለፀ ብቻ የቀረበበትን ክስ አስተባብሏል ለማለት የሚቻል አይደለም፡፡ በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩል የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት ለውሣኔው መሠረት ያደረገው አመልካችና መልስ ሰጭ ያደረጉትን የጽሁፍ ስምምነት ስለመሆኑ የውሣኔው ግልባጭ ያስረዳል፡፡ ይህም የውል ስምምነት ግልባጭ ቀርቦ ከዚህ የሰበር መዝገብ ጋር በመያያዙ ተመልክተነዋል፡፡

አመልካች ይኸው የጽሁፍ ስምምነት ሊያስገድደኝ አይችልም የሚል ክርክር ሲያቀርቡ ለዚህ ክርክር በምክንያትነት የገለጹት ውሉ በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም የሚለውንና ካልፈረምሽ የዕረፍት ፈቃድ አይሰጥሽም የድጋፍ ደብዳቤም አንጽፍም ስላሉኝ እንቅፋት እንዳይፈጠር በመስጋት ነው የሚለውን በማተት ነው፡፡ ሆኖም የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ማየት እንደሚቻለው በይዘቱ የተዋዋይ ወገኖችን መብትና ግዴታ ለይቶ ያስቀመጠ፣ መብትና ግዴታውም በግልጽና በተነፃፃሪ ሁኔታ የሰፈረበት በመሆኑ በመካከላቸው ያለውን ትክክለኛ መብትና ግዴታ አያሳይም የሚለው ክርክር የሰነዱን ይዘት ያገናዘበ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ በውሉ ላይ የተመለከተውን ፊርማ ላስቀምጥ የቻልኩት በነፃ ፍቃድ አይደለም የሚለውም ክርክር ቀርቧል፡፡ እንደተባለውም በሕግ ፊት ሊፀና የሚችል ውል ለመያዝ መሟላት ከሚገባቸው ቋሚ ሁኔታዎች አንዱ ጉድለት የሌለበት የፈቃድ ሁኔታ መኖር ነው፡፡ ይኸው ፈቃድ በስህተት

በኃይል ወይም በተንኮል የተገኘ እንደሆነ ውሉ እንደማይፀና በሕግ ተመልክቷል፡፡ አመልካች ከእነዚህ በአንዱ የተነሣ የተሰጠ ፈቃድ ስለመሆኑ ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የጠቀሱት የፍሬ ነገር ክርክር ምናልባትም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1710 የተጠቀሰውን /መጉዳት/ የሚለውን ያሚላል እንዳይባል አመልካች ይህንኑ ክርክር በአባባል ደረጃ ጠቀሱት እንጂ ካልፈረሙ የዕረፍት ፈቃድ እንደማይሰጣቸው፣ የድጋፍ ደብዳቤም እንደማይፃፍላቸውና በአጠቃላይ እንቅፋት እንዳይፈጠርባቸው በመስጋት የችግራቸው ሁኔታ ገፋፍቷቸው ውሉን እንዲፈፀሙ በማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ በሕግ ምክንያቶች የሚያዝ አይደለም፡፡

በአኳያው ግራ ቀኙ ነሐሴ 02 ቀን 1995 ዓ.ም. ያደረጉት ውል አመልካች በውጪ ለመማር የተሰጣቸው ዕድል በተባለው ጊዜ እና የተባለውን የትምህርት ዘርፍ ተከታትለው ተመልሰው በመልስ ሰጭ ተቋም ለምን ያሕል ጊዜ ማገልገል እንዳለባቸው፣ ይህን ባያደርጉ በምትኩ መልስ ሰጭ አሠሪው ወይም ሦስተኛ ወገን የከፈለለትን ሙሉ ገንዘብ ብር 290,961 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ አመልካች ለመልስ ሰጭ የመክፈል ግዴታ እንዳለባቸው እና በተመለሱም ጊዜ ያላቸው ተነፃፃሪ መብት ምን እንደሆነ በግልጽ እና በማያሻማ አኳኋን ተገልጿል፡፡

ይህ ውል በይዘቱ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1678/ለ/ አንፃር ሲታይም የውሉን ጽናት ሊያስቀር የሚችል አንዳችም ምክንያት የለበትም፡፡ በሕግ ፊት የፀና ውል ያደረጉ ወገኖችም እንደ ውሉ እንዲፈጽሙ ውሉ ሕጋዊ ውጤት እንደሚያስከትል የታወቀ ነው፡፡ እንደ ውሉ ያልተፈፀመለት ወገን እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት ከውል ያገኘውን መብት ለማስፈፀም መብት ያለው በመሆኑ የመልስ ሰጭ የክስ አቤቱታ አግባብነት ያለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደ ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 እንደተመለከተው ይፈፀም የሚባለው ግዴታ የፈፃሚውን የግል ነፃነት የሚነካ ከሆነ ያለፍላጎቱ ተገዶ ሊፈፀም አይገባም፡፡ በዚህ ጉዳይ አመልካች እንደገቡት ግዴታ እንደሙያቸው ለመልስ ሰጪ እንዲያገለግሉ የሚገደዱት የፈቀዱ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ በፈቃዳቸው ለተባለው ጊዜ ያሕል ለማገልገል ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን በአማራጭ ሊከፈል የሚገባውን የገንዘብ ክፍያ ሊፈጽሙ ይገባል፡፡

ይህንን በሚመለከት ምንም እንኳን ለትምህርቱ ሲባል ሦስተኛ ወገን የከፈለለትን ሙሉ ገንዘብ ብር 290,961.00 /ሁለት መቶ ዘጠና ሺህ ዘጠኝ መቶ ስልሳ አንድ ብር/ በሚል የገንዘቡ መጠን ተለይቶ የተቀመጠ ቢሆንም ይኸው ገንዘብ ለትምህርት የተከፈለውን ማናቸውንም ወጭ ለመሸፈን ሲባል የተደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡ ለትምህርት ተብሎ የተከፈለው ወጭ ትምህርቱን ጀምረው ከማጠናቀቃቸው በፊት የታወቀ ወይም ሊታወቅ የሚችል ስለመሆኑ በክርክሩ ሂደት የታወቀ አይደለም፡፡ እንደ ውሉ አመልካች ለማገልገል ካልፈቀዱ እንደ ውሉ ምትክ ግዴታቸውን በገንዘብ ሊከፍሉ፣ እርሳቸውን ለማስተማር ተብሎ በአሠሪውም ሆነ በሦስተኛው ወገን በእርግጥም ያወጣውን ማናቸውም ወጭ ሊሆን ይገባል፡፡ ይህንን በሚመለከት መልስ ሰጭ በውሉ ላይ የተጠቀሰውን ብር 290,961.00 የሚለውን በመጥቀስ ለክሱ መሠረት አደረገ እንጂ አመልካችን ለማስተማር ሲባል በመልስ ሰጭም ሆነ በሦስተኛው ወገን በትክክል የወጣውን ወጭ በማስረጃ አላረጋገጠም፡፡ ስለሆነም የአሁን አመልካች ሊከፍሉ የሚገባውን የትምህርት፣ የትራንስፖርት እና ደመወዝ ሳይከፍሉ ለማገልገል ከፈለጉ የሥር ፍ/ቤት በውሣኔው ላይ እንደገለፀው እንዲያገለግሉ ይህንን ለመፈፀም ካልፈለጉ ግን አሠሪው ወይም ሦስተኛው ወገን በደመወዝም ሆነ በትራንስፖርት ወይም ማናቸውንም ለትምህርቱ ተብሎ የተከፈለውን ወጭ ዘርዝሮ ሲያቀርብና በማስረጃም አስደግፎ ሲያስረዳ የታወቀውን እውነተኛ ወጭ የአሁን መልስ ሰጭ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1776 መሠረት የመክፈል ግዴታ አለባቸው በማለት ፈርደናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የጋሞ አካባቢ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 03727 ግንቦት 02 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እና የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በኮ/መ/ቁ. 56916 ሐምሌ 27 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽሏል፡፡
2. አመልካች በገቡት ግዴታ መሠረት በመልስ ሰጭ ተቋም ለማገልግል ከፈለጉ የማገልገል ግዴታቸውን ይፈጽሙ፤ ለዚህ ግዴታ ፈቃደኛ ካልሆኑ ግን አሠሪው የአሁን መልስ ሰጭም ሆነ ሦስተኛው ወገን ለደመወዝ፣ ለትራንስፖርት እንዲሁም ለትምህርት ሲባል ያወጡትን ወጭ መጠን በሚመለከት በግራ ቀኙ መካከል

የሚቀርበው ክርክርና ማስረጃ ታይቶ እንዲወሰንና በውሣኔ የሚታወቀውን ገንዘብ የአሁን አመልካች ሊከፍሉ ይገባል በማለት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰናል፡፡
ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰበር መ/ቁ. 32571

ታህሣሥ 9 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

በላቸው አንሽሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ሚፍታህ ከድር - ጠበቃ አቶ ከበደ እጉማ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- የባህር ትራንዚት አገልግሎት - አቶ መላኩ መኮንን ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20608 የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ፤ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልካች በማመልከቱ ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አመልካች በከሣሽነት ቀርበው ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት በመርከብ ያስጫንኩትን የንግድ ዕቃ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ከመርከብ አራግፎና የወደብ ፎርማሊቲዎችን አጠናቅቆ ለማስረከብ ተስማምቶ ብር 2870 /የሁለት ሺህ ስምንት መቶ ሰባ ብር/ የአገልግሎት ክፍያ ተከፍሎታል፡፡ ሆኖም አስራሰባት ጥቅል ዕቃዎችን ሲያስረክብ ሁለት ጥቅል ዕቃ ያላስረከበ በመሆኑ የዕቃዎቹን ግምት ብር 37650 /ሰላሣ ሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሀምሣ ብር/ ከነወለዱ እንዲከፍል ይወሰንልኝ በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን፣ ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርቦ የእኔ ግዴታ ከመርከብ የተራገፉትን ዕቃዎች አስፈላጊ የወደብ ፎርማሊቲዎችን በማስፈፀም ዕቃውን አስጭኖ ለባለዕቃው ማስተላለፍ፣ዕቃው የተጎዳ ከሆነ በአንሹራንስ አስመርምሮ የጉዳት ማረጋገጫ መቀበልና ለዕቃው ባለቤት ማስተላለፍ፤ ወይም በእጥረት የተደገፈ ከሆነ የእጥረት ማረጋገጫ ሰርቲፊኬት መቀበልና ለባለእዳው ማስተላለፍ ብቻ ነው፡፡ ከመርከብ የተፈለገውን ዕቃ የማስቀመጥ ኃላፊነት የለበትም፡፡ በመሆኑም በግዴታችን መሠረት የተወጣን በመሆኑ ክሱ ውድቅ ይደረግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት አመልካች የማስረዳት ሸክሙን አልተወጣም በማለት ክሱን ውድቅ ያደረገበት ሲሆን፤በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት አቅርበው የከፍተኛው ፍርድ ቤት የግራ ቀኙን ማስረጃ ከሰማ በኂላ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በመሻር ተጠሪ በክሱ የተገለፀውን ገንዘብ ከነወለዱ እንዲከፍል በማለት ወስኗል፡፡ ተጠሪ ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሰጠው ውሣኔ፣ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለጠቅላይ ፍርድ ቤት አቅርቦ ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ተጠሪ ኃላፊ የሚሆንበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ የለበትም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡

አመልካች ይህ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፣ ምክንያቱም ተጠሪ አስራዘጠኝ ጥቅል ዕቃ ከመርከብ የተራገፈና ከወደብ የደረሰ መሆኑን በማረጋገጥ በራሱ ደረሰኝ የመጋዘን ክፍያ አስከፍሎኛል፡፡ ይኸ ከሆነ ዕቃውን ስላልተረከብኩ እኔ ኃላፊነት የለብኝም በማለት ያቀረበው ክርክር ተቀባይነት የሌለው ሲሆን ለጎደለው ሁለት ጥቅል ዕቃ ተጠያቂ እንደሚሆን አግባብነት ያላቸውን የሕግ ማዕቀፎች በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ ኃላፊነት ተጠሪ የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ የቅድሚያ ክፍያ የተፈፀመው ዕቃዎቹን ለማስተላለፍ እንጅ ዕቃዎቹን ስለተረከብን አይደለም፤ የወደብ ግልጋሎት የሚሰጠው በኤርትራ የወደብ ባለሥልጣን ስለነበረ እነርሱ ለሚፈጽሙት ስህተት ተጠሪ ተጠያቂ የሚሆንበት

ምክንያት የሌለ በመሆኑ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክሯል፣ አመልካች የመልስ መልስ በማቅረብ የሰበር አቤቱታውን በማጠናከር ተከራክሯል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካችና ተጠሪ በጽሑፍ ያቀረቡት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን፣ ይኸ ችሎት የሥር ፍርድ ቤት መዝገብ በማስመጣት በግራ ቀኙ በኩል የቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ተመልክቷል፡፡ የአመልካችንና የተጠሪን የቃል ክርክር አዳምጧል፡፡ ስለሆነም ተጠሪ፣ የጠፉትን ሁለት ጥቅል ዕቃ ዋጋ የመክፈል ኃላፊነት አለበት ወይስ የለበትም የሚለው ጭብጥ በአግባቡ መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት በመጀመሪያ "የዕቃ አስተላላፊነት" ተግባር ምንድን ነው? የሚለውን መመለስ ይጠይቃል፡፡ የዕቃ አስተላላፊነት ተግባር ማለት በአገር ውስጥ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ ዕቃ ተቀባይነት ወይም ዕቃ ላኪን ለመወከል የጉምሩክ ሥነ ሥርዓትና የወደብ ሥነ ሥርዓት እና ሌሎች ሥነ ሥርዓቶችን አስፈጽሞ የገቢ ወይም የወጭ ዕቃዎች ከወደብ እንዲገቡ ወይም እንዲወጡ የማድረግ ተግባር እንደሆነና ይኸም ተግባር የዕቃ ማስረከብን እና ማጓጓዝን ሥራ የሚጨምር ስለመሆኑ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ባላቸው ሰነዶች የተመለከተ ሲሆን በእኛም አገር ይህ ትርጓሜ ሕጋዊ ዕውቅና እና ተቀባይነት ያለው ስለመሆኑ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስለ ዕቃ አስተላላፊነት ከደነገጋቸው ደንቦች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም የተጠሪ የዕቃ አስተላላፊነት ግዴታና ኃላፊነት ከዚህ መሠረታዊ የሆነ ትርጓሜ አንፃር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠሪ በአመልካች የተሰጠውን የሥር ትእዛዝ በመቀበል፣ አመልካች ለአስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች የመጋዘን ኪራይ እና የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፍሉ በመጠየቅ ክፍያውን በራሱ ደረሰኝ ተቀብሏል፡፡ ተጠሪ አስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች ከመረከብ መራገፋቸውንና መጋዘን ውስጥ መግባታቸውን በመግለጽ ከኤርትራ ወደብ አስተዳደር ጋር በተፃፃፋቸው ደብዳቤዎች ግልጽ አድርጓል፡፡ እነዚህ ማስረጃዎች በተጠሪ በራሱ የተዘጋጁ ሰነዶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2018 መሠረት ሰነዶቹ በአዘጋጃቸው በተጠሪ ላይ ዕቃዎቹ ወደብ ለመድረሣቸውና ለመራገፋቸው የአስረጅነት ዋጋና ክብደት ያላቸው ሲሆኑ ተጠሪ በራሱ የተዘጋጁትን ሰነዶች ይዘትና ታዓማኒነት በመቃወም ሁለት ጥቅል ዕቃ አኔ አልተረከብኩም ስለዚህ በኃላፊነት ልጠየቅ አይገባም በማለት የሚያቀርበው ክርክር የሕግ ድጋፍና መሠረት የሌለው ነው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ተጠሪ የሥራ ትእዛዝ የተቀበለባቸው ዕቃዎች በወደብ ያልተራገፉና አጥረት የተፈጠረ ከሆነ ኃላፊነት ካለበት አካል የእጥረት ሰርቲፊኬት በማውጣት ለአመልካች የማስተላለፍ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ አጥብቆ የሚከራከርበት ነጥብ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ የሥራ ትእዛዙን እንደተቀበለ ሁለት ጥቅል እቃ እጥረት ያጋጠመ መሆኑን ለእጥረቱ በኃላፊነት ከሚጠይቀው አካል የእጥረት ሰርቲፊኬት አውጥቶ ለአመልካች አልሰጠም፡፡ በተቃራኒው ተጠሪ አስራዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች እንዳሉ በመግለጽ አመልካች ለአስራ ዘጠኝ ጥቅል ዕቃዎች የወደብና የመጋዘን ኪራይ እንደዚሁም የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው ጠይቆ ክፍያውን ተቀብሏል፡፡ ተጠሪ ሁለት ጥቅል ዕቃዎች ያጎደሉ መሆኑን ለአመልካች ያሣወቀው ዕቃው ከወደብ ወደ አዲስ አበባ በሚጫንበት ጊዜ ነው፡፡ ይኸም ተጠሪ የአስተላላፊነት ግዴታውን በአግባቡ ያልተወጣና በዚህ ምክንያት አመልካች ጉዳት የደረሰባቸው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ከላይ በዝርዝር የገለጽናቸው ምክንያቶች ተጠሪ የአስራ ዘጠኝ ጥቅል እቃዎች የወደብ መጋዘንና የአገልግሎት ክፍያ ከአመልካች የተቀበለና ለአመልካችም የእጥረት ሰርቲፊኬት ያልሰጠ በዚህም ምክንያት አመልካች ላይ ጉዳት ያደረሰ መሆኑን አመልካች የሥራ ትእዛዝ ተቀብሎ የወደብ፣ መጋዘንና የአገልግሎት ዋጋ ክፍያ የጠየቀበትንና ክፍያ የተቀበለበትን ግዴታውን በአግባቡ ባለመወጣቱ ምክንያት ለደረሰው ጉዳት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1790 መሠረት በኃላፊነት የመጠየቅና ለአመልካች ካሣ የመክፈል ኃላፊነት አለበት፡፡ ስለሆነም የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ በዝርዝር የተቀመጡት የሕግ ድንጋጌዎች እና የአመልካችና የተጠሪ ከውል የመነጨ ተነፃፃሪ ግዴታና ኃላፊነት በአግባቡ ሣይገነዘብ ተጠሪ ከሁለት ጥቅል እቃ በኃላፊነት የሚጠየቅበት ከሕግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታና ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1- የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 20608 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2- ተጠሪ የሁለት ጥቅል ዕቃ ዋጋ ብር 37650 /ሰላሣሰባት ሺህ ስድስት መቶ ሃምሣ ብር/ ከስ ካቀረበበት ነሐሴ 10 ቀን 1986 ዓ.ም ጀምሮ ከሚታሰብ ዘጠኝ ፐርሰንት ወለድ ጋር ለአመልካች ይክፈል ብለናል፡፡ ለሚመለከተው ይፃፍ፡፡
3- በዚህ ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሣቸው ይቻሉ፡፡ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ታህሣሥ 9 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማየነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 34940

ታህሳስ 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ሐጅራ አብሮ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ሐሺም ሐጂ አሊዪ - ቀረቡ

**ፍ ር ድ**

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በምስ/ሐረ/ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡

ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ በአወዳይ ከተማ የሰሩትን ቤት ለአባታቸው ትተው ከሄዱ በኋላ አባታቸው ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው ያሉ ስለሆነ እንዲለቁላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ደግሞ ቤት የተሰራበትን ቦታ ባለቤታቸው ከአቶ ዮሴፍ ኡመር ከተባለ ሰው ወስደው በ1969 ዓ.ም ቤቱን የሰሩ በመሆኑ ከ38 አመት በኋላ ሊጠይቋቸው እንደማይችሉ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡ ቤቱን ከረጅም ጊዜ በፊት የአመልካች ባለቤት ከአመልካች ጋር አብረው ሲኖሩ የሰሩት መሆኑን የግራ ቀኙ ምስክሮች አረጋግጠዋል በማለት ፍ/ቤቱ የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡ ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ላይ ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱም ክርክር የተነሣበት ቤት በከሣሽ(ተጠሪ) ስም የተመዘገ በመሆኑ አመልካች ቤቱን ለተጠሪ ይልቀቁ ሲል ውሣኔ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች ለክልሉ ሰበር ሰሚ አቤቱታ አቅርበው አቤቱታቸው ተቀባይነት ሣያገኝ ቀርቷል፡፡

አመልካችም ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት አለበት በማለት እንዲታረምላቸው አቤቱታ ለሰበር ችሎት አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም ተጠሪ የይርጋ ጥያቄ አንስተዋል ወይ? ካነሱ በየፍ/ቤቶቹ ሣይታይ መታለፉ አግባብ ነው ወይ? ተጠሪስ ያቀረቡት ማስረጃ ባለቤትነትን ለማስረዳት ሊቀርብ የሚችል ነው ወይ? የሚሉትን ነጥቦች ለማጣራት አቤቱታው ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ አድርጓል፡፡ ተጠሪም ቀርበው ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

ከፍ ሲል እንደተባለው ተጠሪ በአወዳይ ከተማ ቤት ሰርተው ለአባታቸው ሰጥተው መሄዳቸውን ገልፀው አባታቸው በ1978 ዓ.ም ሲሞቱ አመልካች ቤቱን ይዘው መቆየታቸውንና ቤቱንም ለመልቀቅ ፈቃደኛ ስላለሆኑ እንዲለቁላቸው ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካችም ቤቱን ባለቤታቸው በ1969 ዓ.ም የሰሩት መሆኑን ገልፀው ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እይኖሩበት በመሆኑ ተጠሪ አሁን ሊጠይቋቸው እንደማይገባ ተከራክረዋል፡፡ አመልካች በዚህ ክርክራቸው በግልጽ ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት አይግለፁ እንጂ ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው እየኖሩበት በመሆኑ አሁን ክስ ሊቀርብባቸው የማይችል መሆኑን መግለፃቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት መከራክራቸውን ያመለክታል፡፡ አመልካች ቤቱን ለ38 አመታት ይዘው በመቆየታቸው የገለፁትን ፍሬ ነገር ተጠሪ አላስተባበሉም፡፡ በመሆኑም የስር ፍ/ቤቶች ወደ ፍሬ ጉዳዩ ከመግባታቸው በፊት በአመልካች በኩል የቀረበውን የይርጋ መቃወሚያ መርምረው ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጡ ይገባ ነበር የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 244/1/ ይመለከቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው ትቼው ሄጃለሁ የሚሉት በ1969 ዓ.ም ነው፡፡ አባታቸው ከዚህ አለም በሞት የተለዩት በ1978 ዓ.ም ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤቱን ለአባቴ ሰጥቼ ሄጃለሁ ካሉበት ከ1969 ዓ.ም ጀምሮ ክስ

እስከተመሰረተበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 27 ዓመት ያለፈው ነው፡፡ ተጠሪ ቤቱን ለአባታቸው በአደራ ሰጥተው ለመሄዳቸው በስር ፍ/ቤት የተረጋገጠ ፍሬ ነገር የለም፡፡ ነገር ግን ይህ ተረጋግጧል ቢባል እንኳን አባታቸው በ1978 ዓ.ም ከዚህ አለም በሞት ከተለዩ አንስቶ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ድረስ 17 አመታት አልፋል፡፡ በመሆኑም ተጠሪ ቤታቸው ያለአግባብ በሌላ ሰው ተይዟል በማለት ክስ ማቅረብ የሚችሉት እስከመቼ ነው? የሚለው ነጥብ መታየት ይኖርበታል፡፡ በመሰረቱ ጉዳዩን በቀጥታ የሚመለከት በህግ ተለይቶ የተቀመጠ የይርጋ ድንጋጌ በሌለ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው የጠቅላላ ውል ህግ ድንጋጌ ነው፡፡ ምክንያቱም ምንም እንኳን ግንኙነቱ ከውል የመነጨ ባይሆንም ስለውሎች በጠቅላላው የተነገሩት ድንጋጌዎች እንደሚፈጸሙባቸው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1677/1/ ያመለክታል፡፡ በዚህም መሰረት አንድ ሰው መብቱን መጠየቅ ካለበት ጊዜ ጀምሮ በ10 አመት ውስጥ ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ መሆኑን የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ይገልፃል፡፡ በተያዘው ጉዳይም ተጠሪ ቤቱ ያለአግባብ በአመልካች ተይዟል ካሉበት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት እስከ 1997 ዓ.ም ድረስ 17 አመታት ያለፉ በመሆኑ የተጠሪ መብት በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡ አመልካች ከስር ጀምሮ ቤቱን ለብዙ ዓመታት ይዘው እየተጠቀሙ የቆዩ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ እንደሚገባ ተከራክረው እያለ ፍ/ቤቶቹ ይህንን የአመልካችን የይርጋ ክርክር ሳያስተናግዱ በማለፍ በፍሬ ጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት መፈፀሙን ያመለክታል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39769 በ29/02/2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በ/ቁ 57751 በ20/3/2000 የሰጠው ትእዛዝ በተጨማሪ በምስ/ሐረርጌ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 01899 በ08/07/98 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቤት ለመረከብ ያቀረቡት ጥያቄ /ክስ/ በይርጋ ቀሪ ሆኗል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ.መ.ቁ. 32299

ጥር 07 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** 1. አቶ ሰለሞን ከተማ
2. አል ሣልቫቶር ኃ.የተ.የግ.ማ
} ጠበቃ ጥላሁን ደስታ ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. ሴንትራል ቬኑ ኃ.የተ.የግ.ማ
2. ወ/ሮ ሸዋወንድም ተስፋዬ
3. አቶ ዳዊት ከበደ
} ጠበቃ ፍፁም ብርሃን ገ/ክርስቶስ ቀረቡ

4. ወ/ት ነጠረች ከበደ - ጠበቃ ሰለሞን ገ/ሚካኤል ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው በአመልካቾችና በሁለተኛና ሦስተኛ ተጠሪዎች መካከል ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የንግድ ድርጅት እና የንግድ ድርጅት ህንፃ ሽያጭ ውል በህግ መሰረት የተፈፀመ ውል አይደለም ተብሎ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት በመወሰኑ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል በማለት አመልካቾች ቅሬታ በማቅረባቸው ነው፡፡

ጉዳዩ በተጀመረበት በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ከሣሾች የነበሩት የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ሲሆኑ ህዳር 26 ቀን 1998 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክፍለ ከተማ በቀድሞው በቀበሌ 08 የሚገኘውን በሁለተኛ ተጠሪ ባለቤት እና በሦስተኛ ተጠሪ አባትና አውራሽ በሆኑት በሟች አቶ ከበደ ዘለቀ ስም በካርታ ቁጥር 25116 ተመዝግቦ የሚታወቀውንና በ2825 ካ.ሜ. ቦታ ላይ ሰፍሮ የሚገኘውን ሴንትራል ቬንዩ ሆቴል ከእነ መገልገያ ዕቃዎቹ ጭምር በ04/09/1997 በተፃፈ የሽያጭ ውል ከነመልካም ስሙ በንብረቶቹ ላይ ካሉት የኢትዮጵያ ልማት ባንክና ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብድር ዕዳዎች፣ የሆቴሉ ሠራተኞች ክፍያ እና የሆቴሉ የአገር ውስጥ ገቢ የግብር ዕዳዎችን ገዥዎች ሸፍነው ከእዳዎቹ ውጪ በብር 1,000.000.00 /አንድ ሚሊዮን ብር/ ከሳሾች ለተከሳሽ መሸጣቸውን፣ ውሉ በተደረገ ዕለት ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ቀብድ መቀበላቸውን ቀሪውን ስመሃብቱ ሲዛወር ተከሳሽ ለመክፈል ግዴታ ውስጥ ገብተው ሆቴሉን ከመገልገያዎቹ ዕቃዎች ጭምር መረከባቸውን፣ ተከሳሹ የሆቴሉን ሥመሃብት ለማዛወር የሚረዱትን በውሉ የተጠቀሱትን ግዴታዎችን ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ቀሪ ክፍያም ሳይከፍሉ መቅረታቸውንና ለዚህም ህዳር 23 ቀን 1998 ዓ.ም ተከሳሽ ግዴታቸውን ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆን ምክንያት ውሉ ፈራሽ እንደሚሆንና ከሳሾች መብታቸውን በህግ አግባብ ለማስከበር የሚገደዱ መሆኑን ገልፀው የመጨረሻ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠታቸውን፣ ተከሳሹ በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ ግዴታቸውን ባለመፈፀማቸው ውሉ መፍረሱንና

ክስ ማቅረባቸውን ዘርዝረው ተከሳሽ በውሉ ምክንያት የተረከቡትን ሆቴል ከእነ መገልገያ ዕቃዎቹ ለከሳሾች እንዲያስረክቡ፣ በውሉ የተመለከተውን የገደብ መቀጫ ብር 100,000.00 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ እንዲከፍሉ፣ በሆቴሉ ድርጅት መልካም ስምና ዝና ለደረሰው ጉዳትና ለተገኘው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ወደፊት ክስ የማቅረብ መብታቸው እንዲጠበቅና በክሱ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሣራ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ አንደኛ አመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ ክስና ማስረጃ ለአንደኛ አመልካች ደርሶም በ24/04/1998 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የመከላከያ መልሱን አቅርበዋል፡፡ በመከላከያ መልሳቸውም የሽያጭ ውሉ መደረጉ እውነት ሆኖ ተከሳሹ በውሉ በገቡት ግዴታ መሠረት የልማት ባንኩን ዕዳ ከፍለው ንብረቱን ከልማት ባንክ መረከባቸውን፣ ለሌሎች ዕዳዎችም ከብር 800,000.00 /ስምንት መቶ ሺህ ብር/ በላይ ከፍለው ብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ብቻ መቅረቱን፣ ሌሎች እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ያልቻሉትም ጉዳዩን ለማስፈፀም የተሰጣቸውን ውክልና በከሳሾች በመሻሩ ምክንያት ሆኖ ከዚህ በኋላም ከሣሾች እንደውሉ ለመፈፀም ምንም ዓይነት ጥረት አለማድረጋቸውንና ሌሎች ምክንያቶችን በመዘርዘር ለውሉ አለመፈፀም ምክንያት ከሳሾች መሆናቸውን በመጥቀስ ክሱ ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተከሳሽ ከሳሽነት ክስ አቅርበዋል፡፡ በዚህ ክሳቸውም በውሉ መሠረት የባንክ ዕዳዎችንና ቅድሚያ ክፍያ ጨምሮ ብር 7,470,541.10(ሰባት መቶ ሺህ አራት መቶ ሰባ ሺህ አምስት መቶ አርባ አንድ ብር ከአስር ሳንቲም) ክፍያ ፈጽመው ድርጅቱንና ህንፃውን በመረከብ ከብር 200,000.00 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ በላይ የሆነ ገንዘብ ወጪ በማድረግ ስራ እንዲጀምር ማድረጋቸውን፣ ቀሪውን የሽያጭ ገንዘብ ስመሃብቱ ሲዛወር ለመክፈል በውሉ መስማማታቸውንና የውሉን ግዴታ የከሳሽ ተከሳሾች እንዲፈጽሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመዘርዘር በውሉ ግዴታ የከሳሽ ተከሳሾች እንዲፈጽሙ ቢነገራቸውም ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በመዘርዘር በውሉ ግዴታ መሠረት ተከሳሾች ለንግድ ድርጅቱና ለህንፃው ስመ ሀብት መዛወር አስፈላጊ የሆኑትን ማንኛውንም ፎርማሊቲዎች እንዲፈጽሙና በእጃቸው የሚገኘውን ማንኛውንም ሰነዶች ለተከሳሽ ከሳሽ እንዲያስረክቡ፣ ውሉ በግድ እንዲፈፀምና ወጪና ኪሣራም ይከፈላቸው ዘንድ እንዲወሰንላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ የከሳሽ ተከሳሾችም ጥር 24 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የተከሳሽ ከሳሽ ክስ ተቀባይነት የለውም የሚሉባቸውን የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያቶችን ዘርዝረው ተከራክረዋል፡፡ ከዚህም በኋላ የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ የጣልቃ ገብነት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም በአጭሩ ለሽያጭ መሠረት የሆነው ሆቴል ያልተከፋፈለ የውርስ ሀብት በመሆኑና በንብረቱ ላይ ድርሻ ያላቸው በመሆኑ፣ ውሉ በተንኰል የተደረገና የሦስተኛ ወገንን መብት የነካ በመሆኑ ፈራሽ ሊሆን የሚገባው ህገ-ወጥ ውል ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህ የጣልቃገብ አቤቱታም አንደኛ አመልካችም ሆነ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጐ አለን ያሉትን መልስ ሰጥተዋል፡፡ በሌላ በኩል የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች መጋቢት 13 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ የጣልቃገብነት አቤቱታ ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የንግድ ድርጅትና የንግድ ድርጅቱ ህንፃ ሽያጭ ውል የተፈረመው የአበዳሪ ባንኮችንና የፋይናንስ ተቋማትን ፍላጐት ለማሟላትና ለማመቻቸት ሲባል ሆኖ ጣልቃገብ ሁለተኛ ገዥነት መዋዋሉን፣ የአሁኑን አመልካች ዕዳም ጣልቃገብ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ባገኘው የብር 6,400,000.00 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ብር/ መክፈሉን፣የሆቴሉን ህንፃ እና ጠቅላላ ድርጅቱንም ሐምሌ 01 ቀን 1997 ዓ.ም በተፈረመ የመያዣ ውል ለአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ በመያዣነት መስጠቱን፣ በጣልቃገብ ስም በወጣ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ስያሜም ሆቴሉ ንግዱ እየተመራና እየተካሄደ የሚገኝ መሆኑን፣ በገዥዎች በኩል የውል ግዴታ ተጥሷል በሚል የቀረበው ምክንያትም የማይገባ መሆኑን በመዘርዘር የሽያጭ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ የፍሬ ነገርም ሆነ የህግ ምክንያት የለም ከማለቱም በተጨማሪ ውሉ ይፈርሳል ቢባል እንኳ ገዥዎች ወደ ነበሩበት ቦታ ለመመለስ የሚያስችል ሁኔታ አለመኖሩን በመጥቀስ የውሉ ቃል ተግባራዊ ይሆን ዘንድ እንዲወሰንለት ዳኝነት ጠይቋል፡፡ በዚህ የጣልቃገብ አቤቱታም ከሣሾች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጐ ጣልቃገቡ የዳኝነት ሳይከፍሉ የሚስተናገድበት ምክንያት አለመኖሩን፣ ጉዳዩም የአሁኑ አንደኛ አመልካች የተከሳሽ ከሣሽነት ክስ ሲያቀርቡ ሳይቀርብ ቀርቶ በኋላ መቅረቡ ሥነ-ሥርዓቱን የጠበቀ አለመሆኑን፣ አንድ ድርጅት በአንድ ቀን ለተለያዩ ግለሰቦች ሊሸጥ የማይችል መሆኑንና በጣልቃገብ በኩል የቀረበው የውል ሰነድም በስህተት የተፈረመ በመሆኑ በህግ ፊት ሊፀና እንደማይገባ በመግለጽ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤትም ቀደም ሲል ይዞት የነበረውን ጭብጥ በማሻሻል ተገቢ ነው ያለውን ጭብጥ ከያዘ በኋላ አግባብነት አላቸው ያላቸውን የውርስ እና የሽያጭ ህግ ድንጋጌዎችን በመጥቀስ የሽያጭ ውሉ ህጋዊ የሚባልበት ምክንያት የለም በሚል ምክንያት የሽያጭ ውሉን ፈራሽ ነው ብሎ ከደመደመ በኋላ የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ብር 513,012.20 /አምስት መቶ አስራ ሦስት ሺህ አስራ ሁለት ብር ከሃያ ሳንቲም/ ለአሁኑ አንደኛ አመልካች እንዲከፍሉ አንደኛ አመልካችም የተረከቡትን የድርጅት ቤት ለሻጮች መልሰው

እንዲያስረክቡ እና የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች በሽያጭ ውሉ ምክንያት ለሻጮች ከፈልኩ የሚለውን በተመለከተ ደግሞ ዳኝነት ከፍሎ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀለት መሆኑን በመግለጽ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ የአሁኑ አመልካቾች ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርበው ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት የህንፃው ሽያጭ ውል በፍርድ ቤት መዝገብ ወይም ውሉ ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ በመሆኑ የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል ሊያሟላ የሚችል አለመሆኑንና በዚህ ረገድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ/መ/ቁ. 21448 ስለ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1723 ድንጋጌ የሰጠውን ትርጓሜ በመጥቀስ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔን በውጤት ደረጃ የተቀበለው መሆኑን ገልጾ አጽንቶታል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የበታች ፍ/ቤቶችን ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካቾች ጠበቃ ሐምሌ 30 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረዋል፡፡ የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ተራ ቁጥር የተጠቀሱት ተጠሪዎች ጠበቃ መጋቢት 25 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ አራተኛ ተጠሪም በተመሳሳይ ቀን ለብቻቸው በፃፉት ማመልከቻ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ በተጠሪዎች መልስ ላይም የአመልካቾች ጠበቃ የመልስ መልሳቸውን አቅርበዋል፡፡ ከዚህም በኋላ ግራ ቀኙ በቃል እንዲከራከሩ ተደርጐ ህዳር 25 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክርክራቸው ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን የጽሑፍና የቃል ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የዚህን ችሎት ምላሽ የሚያስፈልገው አቢይ ጥያቄ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት ተገቢነት ያለውን ጭብጥ በመያዝ አግባብነት ያለውን ዳኝነት ሰጥቷል ወይስ አልሰጠም? የሚለው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የሆቴል ድርጅትና ህንፃው የሟች የአቶ ከበደ ዘለቀ እና የአሁኑ ሦስተኛ ተጠሪ የጋብቻ የጋራ ሀብት መሆኑን፣ ይህንኑ የሆቴል ድርጅት እና ህንፃ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች የጋራ ባለሃብት ነን በማለት ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሽያጭ ውል ለአመልካቾች የሸጡላቸው መሆኑን ነው፡፡ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ውሉ መደረጉን አምነው ለፍ/ቤቱ ክስ መመስረት የቻሉት አንደኛ አመልካች በሽያጭ ውሉ የተቀመጠውን ግዴታቸውን ባለመወጣታቸው ተገቢውን ማስጠንቀቂያ ሰጥተን ውሉን በግላችን ስለሠረዝን ድርጅቱን አንደኛ አመልካች መልሰው ያስረክቡን በሚል ምክንያት መሆኑንም ተረድተናል፡፡ እንዲሁም አንደኛ አመልካች በስር ተከሳሽነታቸው የሰጡት መልስ የውሉን መኖር አምነው በውሉ ለተቀመጡት ግዴታዎች አለመፈፀም ምክንያት የሆኑት ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መሆናቸውን በመዘርዘር ውሉ የሚሰረዝበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም ሲሉ የሚከራከሩ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ ክርክር መሠረት ያደረገውም ለሽያጭ መሰረት የሆነው የሆቴል ድርጅት የሟች አባታቸው ያልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ሆኖ እያለ ሽያጩ በሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች መከናወኑ መብቴን ስለሚነካ ውሉ ሊፈርስ ይገባል በሚል ነው፡፡ የአሁኑ ሁለተኛ አመልካች ክርክር ደግሞ ለክርክሩ መሰረት የሆነው የሆቴል ድርጅት ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአንደኛ አመልካች ጋር በጋራ የገዛው የአበዳሪ ባንኮችንና የፋይናንስ ተቋማትን ፍላጐት ለማሟላትና ለማመቻቸት ሲባል መሆኑን፣ አንደኛ አመልካች በውሉ መሠረት በገባው ግዴታም ለሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ዕዳ ከአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ ተበድሮ ብር 6,400,000.00 /ስድስት ሚሊዮን አራት መቶ ሺህ ብር መክፈሉንና በራሱ የንግድ ስያሜም የንግድ ሥራውን እየሰራ እንደሚገኝ እንዲሁም ለፋይናንስ ተቋማትና ሌሎች የሻጭ ዕዳዎችን እና ሆቴሉን በዘመናዊ ሁኔታ ለማደራጀት በድምሩ ብር 11,285,889.00 /አስራ አንድ ሚሊዮን ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ስምንት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ ብር/ ወጪ ማድረጉን ገልጾ ውሉ የሚሰረዝበት አግባብ የለም የሚል ነው፡፡

እንግዲህ የግራ ቀኙ ክርክርና የዳኝነት ጥያቄ የሚያሳየው ግንቦት 04 ቀን 1997 ዓ.ም የተደረገው የሆቴል ድርጅት እና ህንፃ ሽያጭ ውል መኖሩ ታምኖ በውሉ በተመለከተው አኳኋን ግዴታውን ያልተወጣው የትኛው ወገን ነው በሚል አመልካቾችና ከአንደኛ እስከ ሦስተኛ ተራ የተጠቀሱት ተጠሪዎች የሚከራከሩ መሆኑን፣ አራተኛ ተጠሪ ደግሞ ሽያጩ ባልተከፋፈለ የውርስ ንብረት ላይ የተፈፀመ ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል የሚሉ መሆኑን ነው ከዚህ የክርክር ይዘት የምንገነዘበው ደግሞ በፍ/ቤቱ በጭብጥነት ተይዞ ውሣኔ ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ምን እንደሆነ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ምላሽ

የሚያገኘው የፍትሐብሔር ሙግቶች የሚመሩበትን የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ ድንጋጌዎችን መሠረት በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም የፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ህግ አንቀጽ 248 የሚያሳያው ጭብጥ የሚያዘው ከሣሽና ተከሳሽ በሥርዓቱ መሠረት የሚያቀርቡት የክስ ማመልከቻና የመከላከያ መልስ፣ ከአባሪ ሠነዶችና በቁጥር 241 መሠረት ከተደረገው ምርመራ የተገኘውን የተከራካሪ ወገኖች ቃል መሠረት በማድርግ መሆኑን ነው፡፡

በያዝነው ጉዳይም የተከራካሪ ወገኖች የክርክር ሂደት ሊያዝ እና በፍ/ቤት ሊወሰን የሚገባው ጭብጥ ምን እንደሆነ ያሳያል፡፡ ይኸውም የስር ከሣሶች ጥያቄ ግንቦት 04 ቀን 1997 የተደረገው የሽያጭ ውል ይፍረስልን ሳይሆን ውሉ በግላችን ስለተሠረዘ ድርጅቱን ገዢ ያስረክበን የሚል ነው፡፡ ገዢዎች ውሉ ሊሰረዝ አይገባም የሚሉትን ምክንያት ዘርዝረዋል፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ዳኝነት የሰጠው ውሉ ፈራሽ ነው በሚል ምክንያት ነው፡፡

በመሠረቱ ውል ማፍረስና ውል መሠረዝ በውል የተቋቋሙት ግዴታዎች ከሚቀሩባቸው መንገዶች ውስጥ የሚካተቱ ቢሆንም ምክንያታቸውና ውጤታቸው የተለያዩ መሆኑን በዚህ ረገድ የተደነገጉት የውል ማፍረስ ከውል አመሠራረት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ሲሆን ሲሆን ውሉ ከአመሰራረቱ በህጉ የተመለከቱትን ሁኔታዎች ባለማሟላቱ ግድፈት ያለበት መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡ በሌላ በኩል የውል መሰረዝ ጉዳይ ከውል አመሰራረት ችግር የሚነሳ ሳይሆን ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታውን ካለመወጣት የሚመነጭ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ውል የሚሰረዘው ከመሠረቱ ግድፈት ስላለው አይደለም፡፡ ይልቁንም የውል መሠረዝ ምክንያት ከተዋዋይ ወገኖች የውል ግዴታን ከመፈፀምና ካለመፈፀም ጋር ተያይዞ የሚከሠት ነው፡፡ የውል መሠረዝ ሥርዓትም የራሱ የሆነ አካሄድ አለው፡፡ ይኸውም ውሉን የመሠረዝ ፍላጐት ያለውን ወገን የውሉ ግዴታ ባለመፈፀሙ የተነሳ ከህግ ወይም ከውሉ ከራሱ ባገኘው መብት ተጠቅሞ ውሉን ሊሰርዝ ይችላል፡፡ ይህ መብት ተግባራዊ የሚሆንበት አጋጣሚም ግዴታው ባለመፈፀሙ የተነሳ የደረሰውን ጉዳት ከማረጋገጥ ጋር ተያይዞ የሚታይ እንጂ ጥያቄ አቅራቢው ሁል ጊዜ ተቀባይነት የሚያገኝበት አይደለም፡፡ በመሆኑም የውል ይሰረዝልኝና ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በህጉ አግባብ የሚስተናገዱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1784 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች ያስገነዝባሉ፡፡ በተያዘው ጉዳይም የስር ከሳሾች ጥያቄ ውል ይሰረዝልኝንና ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች በሚስተናገዱበት የፍትሐብሔር ህግ ክፍል ምላሽ ማግኘት ሲገባ በህጉ አግባብ የውል ይፍረስልኝ ጥያቄ ባልቀረበበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በራሱ ተነሳሽነት በፍ/ብ/ህ/ቁ 1723 ስር የተመለከተውን የፎርማሊቲ ጥያቄ በማንሳት ጉዳዩን መወሰኑ የህግ መሠረት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡ በመሠረቱ ፍ/ቤቱ በተከራካሪ ወገኖች የተጠየቀውን ዳኝነት በመተውና በተከራካሪ ወገኖች ያልተነሳለትን የፎርማሊቲ ጥያቄ በራሱ ጊዜ በማንሳት ውሣኔ እንዲሰጥ የሚያስችል የህግ አካሄድ የለም ስለሆነም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ የውል ይሰረዝልን፤ ሠርዘናል የክርክር ጭብጥ መሠረት አድርጐ የተሰጠ መሆን ያለመሆኑን በመመርመር ዳኝነት መስጠት ሲገባው የፎርማሊቲ ጥያቄን በማንሳት እና ምክንያቱን በመለወጥ ውጤቱን ማጽናቱ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት የክርክሩን ጭብጥ የውል ይሠረዝ፤ ሠርዘናል አኳያ አለመመልከቱን ከላይ ገልፀናል፡፡ እንዲህ ከሆነ ይኸው ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከተገቢው ጭብጥ አኳያ እንዲመለከትና ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በማድረግ ጉዳዩን መመለሱ ሥነ ሥርዓታዊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም፡-

1ኛ/ የስር ከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ውሉን ሰርዘናል ማለታቸው ተቀባይነት አለው ወይስ የለውም?

2ኛ. የውሉ መሠረዝ ጥያቄ በፍ/ቤት ሊወሰን የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት አለ ወይስ የለም?

3ኛ. የአሁኗ አራተኛ ተጠሪ ውሉን የመሠረዝ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ? ለክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት መብት አላቸው? መብት አላቸው ከተባለስ መብታቸው በምን መንገድ መከበር አለበት? በሚሉትና ሌሎች አስፈላጊ ናቸው ባላቸው ከውል መሰረዝ ጥያቄ ጋር ሊያያዙ የሚችሉትን ተጨማሪ ነጥቦችን በመመልከት ተገቢውን ውሣኔ ሊሰጥበት የሚገባ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/መ/ቁ. 27497 ሐምሌ 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የፍትሐብሔር ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔው የተሻረ መሆኑን አውቆ ከላይ ከተመለከቱት ጭብጦች አኳያ ጉዳዩን እንደገና በመመልከት ተገቢውን ይወስን ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 343/1/ መሠረት መልሰንለታል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሳቸውን ይቻቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 34586

ጥር 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ ያለው ድልነሳው - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- 1. ወ/ሮ ብርቅነሽ ሸዋረግ - አልቀረቡም ከተባለበኋላ ቀረቡ

2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር - ነ/ፈጅ ቀረቡ

3. ወረዳ 22 ቀበሌ 04 አስተዳደር - አልቀረበም

4. አቶ ወሰን ፀጋ - ተቋርጧል፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በአንደኛ ተጠሪ ከሳሽነትና ከሁለት እስከ አራተኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ተከሳሽነት የነበረውን ክርክር መርምሮ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ሳያገኝ በመቅረቱ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥም ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ከሁለት እስከ አራተኛ በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት መንግሥት ስለ ንግድ ቤቶች መግለጫ ካወጣም በኋላ በስሜ ውል ተዋውዬ ባለሁበት ሁኔታ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ከአራተኛ ተጠሪ ጋር በውል ላይ ውል በማድረግ የንግድ ቤቱን አሳልፈው የሰጡ ስለሆነ የተፈጠረው ሁከት ይወገድልኝ በማለት ክስ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሳሽ ንግድ ቤቶችን አስመልክቶ የመንግሥት መመሪያ ከወጣ በኋላ በስማቸው ተከራይተው በይዞታቸውም ሥር አድርገው በንግድ ቤቱ ሲጠቀሙበት የነበረ ስለሆነና ተከሳሾች መመሪያው ከወጣ በኋላ ከከሳሽ ጋር የተደረው ውል በስህተት እንደተደረገ ከማንሳት ውጭ ውሉ የጸና ሊሆን እንደማይችል ያቀረቡት ክርክርም ሆነ ማስረጃ ስለሌለ በዚህ ሁኔታ በተከሳሾች የተፈጸመው ድርጊት በሕግ የተፈቀደ መብትን ተከትሎ የተፈጸመ ባለመሆኑ አድራጎቱ ከሁከት ስለሚፈረጅ ባለይዞታ ለሆኑት ለከሳሽ ቤቱ ሊመለስላቸው ይገባል በማለት ውሳኔ ሠጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም የአሁን አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 የተመዘገበውን የንግድ መደብር የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በንግድ ቤቱ ላይ እዳና እገዳ እንደሌለበት አጣርቼ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ከሦስተኛ ተከሳሽ /ከአሁን ሦስተኛ ተጠሪ/ ላይ ገዝቼ ሽያጩም ሕጋዊ መሆኑ በቀበሌው አስተዳደር በኩል ታምኖበት የኪራይ ውሉ በስሜ ተዛውሮ ኪራይ የምከፍል ከመሆኑም በላይ የንግድ ፈቃድም አውጥቼ በመስራት ላይ እንዳለሁ የንግድ ቤቱን አስቀድሞ በተሰጠ ፍርድ መነሻነት ለከሳሽ ለአሁን አንደኛ ተጠሪ እንዳስረክብ የተገደድኩ ስለሆነ ይሄው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ይሰረዝልኝ በማለት አመልክተው ፍ/ቤቱም ከሳሽና ተከሳሾች የነበሩት በመጥራት ካከራከረ በኋ በቀድሞው ውሳኔ ክርክር ያስነሳው የንግድ ቤት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስለ ንግድ ቤቶች

መግለጫ ከማውጣቱ በፊትም ሆነ በኂላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ተከራይተው ይጠቀሙበት እንደነበርና ይዞታቸው እንደሆነ የተረጋገጠ ከመሆኑም ሌላ ከሳሽ መመሪያው ከወጣ በኂላ ከአንደኛ እና ሁለተኛ ተከሳሾች ጋር ያደረጉት ውል ፈራሽ ነው ሳይባል ከሦስተኛ ተከሳሽ ጋር ያደረጉት ውል መብትና ግዴታን ሊያቋቁም እንደማይችል ስለተወሰነና ከዚህም ውሳኔ ሦስተኛ ተከሳሽ አንዳችም መብት እንደሌላቸው መገንዘብ ስለሚቻል የመቃወም አመልካችም የንግድ ቤቱን ገዛሁ የሚሉት መብት ከሌላቸው ከሦስተኛ ተከሳሽ ላይ ስለሆነ በዚህ ሁኔታ የቀድሞው ውሳኔ ይሰረዝልኝ በማለት ያቀረቡት አቤቱታ ተገቢነት የለውም በማለት ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይሄው ውሳኔም የፍሬ ነገርም ሆነ የሕግ ጉድለት የለውም ተብሎ እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ እንደፀና ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ለዚህ ችሎት የቀረበውም የሰበር አቤቱታ ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ችሎቱም አቤቱታውን መርምሮ አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ በየደረጃው የሚገኙ የሥር ፍ/ቤቶች ሳይቀበሉ የቀሩበት ምክንያት ተጠሪዎች ባሉበት ተጣርቶ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በጽሁፍ አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን የዚህን ችሎት ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ፡-

አመልካች ባቀረቡት መቃወሚያ መነሻነት አስቀድሞ የተሰጠው ፍርድ ሊሰረዝ ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ከዚሁ ጭብጥ አኳያም የሰበር አቤቱታው እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ ፍርድ በአንድ ፍ/ቤት ከተሰጠ በኂላ ይሄው ፍርድ በዚያው ፍ/ቤት በድጋሚ ከሚታይባቸው ሥርዓቶች መካከል አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 መሠረት መቃወሚያ በሚቀርብበት ጊዜ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሠረትም በክርክሩ ውስጥ ተካፋይ መሆን የሚገባው ወይም በክርክሩ ውስጥ ለመግባት የሚችልና እንደዚሁም ተካፋይ ባልሆነበት ክርክር የተሰጠው ፍርድ መብቱን የሚነካበት ማንኛም ሰው ተካፋይ ባልሆነበት የተሰጠው ፍርድ ከመፈጸሙ በፊት መቃወሚያውን ማቅረብ እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አስቀድሞ ፍርድ ያረፈበትንና ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ ቤት አመልካች በስማቸው የንግድ ፈቃድ አውጥተው ሲሰሩበት ከነበረው የሥር ሦስተኛ ተከሳሽ የአሁን አራተኛ ተጠሪ ላይ የካቲት 16 ቀን 1992 ዓ.ም በውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ ስለመግዛታቸውና በኂላም የኪራይ ውሉን በስማቸው በማዛወርና የንግድ ፈቃድም በስማቸው በማውጣት የንግድ ሥራ ሲሰሩበት እንደነበር ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡ የቀድሞው ውሳኔም መብቱን የነካ ስለሆነ ሊሰረዝ /Set aside/ ይገባል በማለት መቃወሚያ ያቀረቡትም ይህንኑ መሠረት በማድረግ ነው፡፡

ጉዳዩን በየደረጃው የተመለከቱት የሥር ፍ/ቤቶች በዚህ ረገድ የቀረበውን የአመልካች መቃወሚያ ሳይቀበሉት የቀሩት ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው አንደኛ ተጠሪ ከሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች ጋር ያደረጉት የኪራይ ውል ቀሪ ባልሆነበት ሁኔታ ሌላ ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር መደረጉ ተገቢነት የሌለውና ውጤትም ሊኖረው ስለማይችል በዚሁ ውጤት በሌላው ውል ላይ ተመስርቶ በአራተኛ ተጠሪና በአመልካች መካከል የተቋቋመው የንግድ መደብር ሽያጭ ውል የመብትም ሆነ የግዴታ ምንጭ ስለማይሆን መቃወሚያው ተገቢነት የለውም በማለት ነው፡፡

ይሁንና አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውና የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ሲገዙ ከላይ እንደተጠቀሰው አራተኛ ተጠሪ ንግድ መደብሩን በስማቸው ባደረጉት ውል ይዘውት እንደሚገኙ እንደዚሁም በስማቸው የንግድ ፈቃድ በማውጣት እየሰሩ እንደሚገኙ በማረጋገጥ ውልና ማስረጃ ምዝገባ ጽ/ቤት በመቅረብ የሽያጩን ውል ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደረጉ እንደመሆኑ መጠን ሁለተኛ እና ሦስተኛ ተጠሪዎች አስቀድሞ ከአራተኛ ተጠሪ ጋር ያደጉት የኪራይ ውል ተገቢነት የሌለው ነው ቢባል እንኳን አመልካች ውሉን በቅን ልቦና ያደረጉት በመሆኑ ሕጉ ለቅን ልቦና ተዋዋዮች ከሰጠው ጥበቃ አኳያ ጉዳዩ የማይታይበት ምክንያት አይኖርም በዚህም መሠረት የቅን ልቦና ባለይዞታነትን አስመልክቶ በፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ላይ ግዙፍነት ያለው ተንቀሳቃሽ ነገር ባለሀብት ለመሆን በቅን ልቦና ዋጋ ሠጥቶ ውል የተዋዋለ ሰው የተባለውን ተንቀሳቃሽ ነገር በእጁ ሲያደርግ በቅን ልቦናው ምክንያት የዚህ ንብረት ባለሀብት እንደሚሆን ተደንግጎ ይገኛል፡፡ የንግድ መደብር ግዙፍነት ባይኖርም ነገር ግን ግዙፍነት የሌለው ተንቀሳቃሽ ንብረት /Incorporeal

movable/ እንደሆነ የንግድ ሕግ ቁጥር 124 ላይ ስለተመለከተ ስለቅን ልቦና ባለይዞታነት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው፡፡

አመልካች ይህንኑ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን የንግድ መደብር ይዘው የሚገኙት በቅንልቦና በተደረገ ውል መነሻነት ነው ከተባለ አስቀድሞ አንደኛ ተጠሪ ከሁለት እስከ አራት በተጠቀሱት ተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ መነሻነት የንግድ መደብሩን ለከሳሽ ለአንደኛ ተጠሪ ሊያስረክቡ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ አመልካች በክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑበት መብታቸውን የነካ ውሳኔ አንደሆነ መገንዘብ አያዳግትም፡፡

በመሆኑም አመልካች የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/358 በሚፈቅደው መሠረት ያቀረቡት አቤቱታ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ/1161 አኳያ ታይቶ አስቀድሞ የተሰጠውና የአመልካችን መብት የነካው ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት መሰረዝ ሲገባው ከአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ አዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ድረስ አቤቱታው ተቀባይነት ሳያገኝ መቅረቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመቁ 2901/91፣ ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት በመ.ቁ 414/93 እንደዚሁም ሰበር ሰሚው ችሎት በመ/ቁ 01424 በ20/3/2000 ዓ.ም የሰጡት ውሳኔ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 348 (1) መሠረት ተሽሯል፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ ነክ የመ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ 2901/91 የሰጠው ውሳኔ አመልካች የክርክሩ ተካፋይ ሳይሆኑ መብታቸው የነካ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ/360(2) መሠረት ተሰርዟል፡፡
3. አመልካች በወረዳ 22 ቀበሌ 04 ክልል በቤት ቁጥር 596 ተመዝግቦ የሚገኘውን የንግድ መደብር ከአራተኛ ተጠሪ ላይ የገዙት በቅንልቦና ስለሆነ ሊያስረክቡ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሳራ ይቻቻሉ፣፣
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ፀ/መ

የሰበር መ/ቁ. 39568

መጋቢት 24 ቀን 2001

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ሽንቁጤ ተ/ማርያም - ቀርበዋል

**ተጠሪ፡-** አቶ ገብሬ ጎንጤ - ቀርበዋል

ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ከመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡

**ፍ ር ድ**

ይህ አቤቱታ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻው የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፍ/ይ/መ/ቁ. 6833፣ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የሰሜን ሸዋ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 17074፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠውን ፍርድ ተቀብሎ ማፅናቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለቱ ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው በአማራ ክልል በሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍርድ ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ፣ የአሁኑ ተጠሪ ደግሞ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ክርክሩ የተጀመረው ስር ከሣሹ ህዳር 16 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡትን ክስ መሠረት በማድረግ ሲሆን አጭር ይዘቱ ደግሞ ወኪል አድራጊዬን በመወከል ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም በተፃፈ ውል በወኪል አድራጊዬ ተመዝግቦ የሚታወቀውን የሰሌዳ ቁጥር 3- 08106 ኦሮ የሻንሲ ቁጥሩ 15416፣ የሞተር ቁጥሩ OME 03 - 41-3000-056326 የሆነ ጣሊያን ሰራሽ ፊያት መኪና ለተከሣሹ በብር 50,000 /ሃምሣ ሺህ ብር/ ሸጨላቸው ከዚህ ገንዘብ ብር 19,000 /አስራ ዘጠኝ ሺህብር ከፍለውኝ እኔም መኪናውን ህዳር 09 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ መረካከቢያ አስረክቤአቸዋለሁ፤ ይሁን እንጂ ቀሪውን ብር 31,000 /ሰላሣ አንድ ሺህ ብር/ ከፍለው መኪናው በስማቸው እንዲያዞሩ ተከሣሹን ብጠይቃቸው ፍቃደኛ ባለመሆናቸው የተጠቀሰው ቀሪው ገንዘብ በመክፈል መኪናውን በስማቸው ተገድደው እንዲያዞሩ ይደረግልኝ፤ በተጨማሪም ታህሣሥ 18 ቀን 1999 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል ብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ተከሣሹ ተበድረው የወሰዱ ሲሆን ይህንን ብድር እንዲመልሱልኝ እንዲሁም ወለድና ወጪና ኪሣራ አክለው እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ነው፡፡

ተከሣሹም በሰጡት መልስ ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም ባደረግነው የመኪና ሽያጭ ውል ውስጥ መኪናው የካምቢዮን ጥርስ ችግር ስላለው ከሣሹ ወደፊት እስከ ህዳር 30 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ ይህንን ጉድለት እንዲስተካከል አድርገው በስሜ እንዲዛወር የማድረግ ግዴታ ገብተው ሲያበቁ ይህንን ግዴታቸው ባልተወጡበት ሁኔታ ያቀረቡት የመኪናው ሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ይስጡኝ ጥያቄ ተገቢነት የለውም፤ እንዲሁም ከመኪናው ሽያጭ ውል ጋር ምንም አይነት ዝምድና የሌለው የብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ብድር አጣምረው መክሰሣቸው ተገቢነት የለውም፤ ከፈለጉ ራሱን በቻለ ክስ መጠየቅ ይችላሉ እንጂ ከመኪና ሽያጩ ጋር አያይዘው ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም ብለዋል፡፡

የሥር ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አግባብነት አላቸው ካላቸው ህጎች ጋር በማገናዘብ በመ/ቁ. 17074 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም ፍርድ የሰጠ ሲሆን፣ የፍርዱ ይዘትም ግራ ቀኙ ወገኖች ባደረጉት የመኪናው ሽያጭ ውል መኪናው የካምቢዮ ጥርስ ችግር ያለበትና ይህንን ጉድለት ከሣሹ እስከ ህዳር 30 ቀን 1999 ዓ.ም ለማስተካከል ግዴታ

የገቡ ስለሆነ ይህንን ግዴታቸውን ባልተወጡበት ሁኔታ የመኪናው ሽያጭ ቀሪ ገንዘብ ይከፈለኝ ጥያቄ ማንሣታቸው ተቀባይነት የለውም፤ ከብር 19,000 /አስራ ዘጠኝ ሺህ ብር/ በተጨማሪ ከሣሹ ብር 10,416 / አስር ስሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከተከሣሹ መቀበላቸው በተከሣሹ የቀረበው የሰነድ ማስረጃ ስለሚያሣይና በከሣሹም ያልተካደ በመሆኑ ከሣሹ ከተከሣሹ ላይ የሚቀራቸው ገንዘብ ብር 31,000 /ሠላሣ አንድ ሺህ ብር/ ሣይሆን ብር 20,584 /ሃያ ሺህ አምስት መቶሰማኒያ አራት ብር/ እንደሆነና ተከሣሹ በቀሪው ያልከፈሉት ገንዘብ መኪናው እንዲታደስና ቀሪ ገንዘብ የመኪናውን ጉድለት ለማሣደስ የማይበቃ ከሆነ በደረሰኝ መሰረት ለሚረጋገጥ ተጨማሪ የማሣደሻ ወጪ ከሣሹ እንዲከፍሉና መኪናውን አሟልተው ለከሣሹ እንዲያስረክቡ፤ ከሣሹና ተከሣሹ ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ያደረጉት የመኪናው ርክክብ ውል በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ የተመዘገበ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፤ ከሣሹ ከመኪናው ሽያጭ ውል አለመፈፀም ጋር አያይዘው ያቀረቡት የብር 1474 /አንድ ሺህ አራት መቶ ሰባ አራት ብር/ ጥያቄ ራሱን የቻለ ክስ አቅርበው መጠየቅ እንጂ ተጣምሮ መቅረቡ ተቀባይነት የለውም የሚል ነው፡፡

ከላይ የሰፈረውን የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔ በመቃወም ስር ከሣሹ ወደ አማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ በፍ/ይ/መ/ቁ. 6833/ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሠረት ሠርዞታል፡፡

አመልካቹም በሥር ፍርድ ቤቶቹ የተሰጠውን ፍርድ በመቃወም ሐምሌ 23 ቀን 2000 ዓ.ም የተፃፈ አቤቱታ ወደዚህ ሰበር ችሎት ያቀረቡ ሲሆን መሠረታዊ ይዘቱም ስር ተከሣሽ የነበሩት የአሁኑ ተጠሪ በውሉ መሠረት መኪናው እንደተረከቡ የሚገልጽ ሰነድ ፈርመውና ይህ ሰነድም ለስር ፍ/ቤት ቀርቦለት እያለ ስሙን እንዳዞርላቸው እና ቀሪውን ገንዘብ እንዲከፍሉኝ ጥያቄ አቅርቤ እያለሁ መኪናው አሟልተህ ለተጠሪው አስረክብ ብሎ ፍርድ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው፤ ተጠሪው መኪናው ተረክበው ሲያበቁ በመኪናው ለሚደርስ ጉዳት ሻጭ አስራ መባሌ ተገቢ አይደለም፤ ፍ/ቤት ተዋዋይ ወገኖች በውላችን ካስቀመጥነው ግዴታ ውስጥ ሌላ አዲስ ግዴታ ሊፈጥር አይችልም፤ ተጠሪው በመረጡት ጋራጅ መኪናውን ስላሣደስኩላቸው የከፈልኩትን ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ የመለሱልኝን ገንዘብ የስር ፍ/ቤቱ ይህ ገንዘብ ለመኪናው ሽያጭ ተብሎ እንደተቀበልኩ በማድረግ መወሰኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው የሚል ነው፡፡

ተጠሪም የካቲት 25 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ መልስ ያቀረቡ ሲሆን ይዘቱም አመልካቹ ለተጠቀሰው መኪና ሽያጭ ተብሎ ብር 29416 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከእኔ ወስዷል፤ አመልካቹ የሸጠልኝ መኪና ጉድለት የነበረበትና በእዳ የተያዘ ነው፤መኪናው ቀደም ብሎ በሌላ ምክንያት ለነበረው ዕዳ መክፈያ እንዲሆን የሐራጅ ሽያጭ ወጥቶበት ይገኛል፤ አመልካቹ በውላችን መሠረት የነበረበትን ግዴታ ሣይወጣ መኪናው ተጠሪው ተረክቧልና እዳ የለብኝም በማለት ያቀረበው አቤቱታ ተገቢነት የለውም፣ መኪናው እንዲያሣድስልኝ አመልካችን አልወከልኩትም፣ ስለሆነም እኔ ለአመልካች የሰጠሁት ብር 10416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ለመኪናው ዋጋ ተብሎ የተሰጠው ተጨማሪ ክፍያ እንጂ ለመኪና ማሣደሻ አይደለም፤ ስለሆነም አመልካቹ የወሰደውን ጠቅላላ ገንዘቤ ብር 29416 /ሃያ ዘጠኝ ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከሕጋዊ ወለዱ ጋር ደምሮ ሊመልስልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡

ይህ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ እየተዘረዘረ በመጣው መልኩ በመገንዘብ፣

1/ አመልካቹ በመኪና ሽያጭ ውሉ መሠረት የሚጠበቅባቸውን ግዴታ ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም?

2/ አመልካቹ በስር ፍ/ቤት የመሠረቱት ክስ ተጠሪው የመኪና ሽያጭ ቀሪ ገንዘቤ ይክፈለኝና መኪናው በስሙ ይዛወርለት የሚል ሆኖ እያለ በፍርዱ የተመለከቱትን ሌሎች ግዴታዎች በአመልካቹ ላይ ሊፈረዱ ይገባል ወይስ አይገባም? በሌላ አገላለጽ የፍርዱ ገደብ እስከየት ድረስ ሊሆን ይገባል?

የሚሉትን መሠረታዊ ጭብጦች በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

ከክርክሩ መንፈስ መረዳት የሚቻለው አመልካቹ የሚሉት ከተጠሪው ጋር ባደረጉት የመኪና ሽያጭ ውል መሠረት ከእርሣቸው የሚጠበቅ ማንኛውም አይነት ግዴታ እንደተወጡና መኪናውም ለተጠሪው እንዳስረከቡ በመግለጽ ቀሪ ገንዘባቸውን ተጠሪው ከፍለው መኪናዋ በገዢው ስም እንድትተላለፍ ነው፤ የስር ፍርድ ቤቶቹም አመልካቹ ቀሪ ገንዘብ እንዲከፈላቸው ከመጠየቃቸው በፊት ሊወጡት የሚገባ መኪናውን የማስጠገን ግዴታ አለባቸው ማለታቸው

አመልካቹ ፍ/ቤቱ የፈጠረባቸው አዲስ ግዴታ አድርገው ያስቀምጡታል፡፡ ተጠሪው ደግሞ አመልካቹ የሸጡላቸው መኪና ችግር ያለበት እንደሆነና በውላቸውም መሠረት መኪናውን የማስጠገን ወይም የጎደለውን የማሟላት ግዴታ አለባቸው የሚል ነው፡፡ ግራ ቀኙ ወገኖች ሐምሌ 10 ቀን 1998 ዓ.ም አደረጉት በተባለው የመኪና ሽያጭ ውል ውስጥ የአመልካቹ ግዴታ ሆኖ መስፈሩን የስር ፍርድ ቤቱ በውሣኔው የገለፀው መኪናው የካምቢዮ ብልሽት እንዳለውና ይህንን የማሰራት ወይም የመተካት ግዴታ እንዳለባቸው ነው፡፡ የመኪናው ካቢዮን አሰርተው መኪናው ለተጠሪው ስለማስረክባቸው የሚገልጽ ማስረጃ አመልካቹ አላቀረቡም፡፡ ተጠሪው መኪናው ተረክበው በእጃቸው አስገብተዋልና የመኪናው ጉድለት አርሜ መኪናው ማስተላለፌ ያሣያል የሚለው የአመልካቹ ክርክር ሲታይም ምንም እንኳ የስር ፍ/ቤቱ ሐምሌ 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተደረገው የመኪናው ማረካከቢያ ውል በሚመለከተው አካል ፊት ቀርቦ የተመዘገበ አይደለም በማለት ውጤት እንደሌለው አስመስሎ መወሰኑ ተገቢነት ባይኖረውም በዚህ ሰነድም ቢሆን መኪናው የካምቢዮን ችግር እንዳለበት የተቀመጠ በመሆኑ አመልካቹ በውሉ መሠረት ሊወጡት የሚገባ ግዴታ ሙሉ በሙሉ ተዋጥተዋል ማለት አይቻልም፡፡ በውል የተመለከተ ግዴታቸው ሣይወጡ ደግሞ የቀሪ ገንዘብ ክፍያና የመኪናው ስም መዛወር ጥያቄ ማንሣታቸው አግባብነት የለውም፤ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1757 እንደደነገገውም ውሉ እንዲፈፀምለት የሚጠይቀው ወገን በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ ከተወጣ በኋላ መሆን እንዳለበት ነው፡፡ ስለሆነም የስር ፍ/ቤቱ አመልካቹ የመኪናው ካምቢዮን የማስተካከል ግዴታቸውን ሣይወጡ የቀሪ ገንዘብ ክፍያ ጥያቄ ማንሣት አይችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈፀመበት ነው፡፡

በሌላ በኩል የስር ፍ/ቤቱ ከላይ ከተቀመጠው ማጠቃለያ ማለትም አመልካቹ በውሉ መሠረት አስቀድሞ ሊወጣው የሚገባ ግዴታ ሣይፈጽም ክስ ማቅረብ አይችልም ከሚለው ውሣኔ አልፎ ሌሎች በአመልካቹ መብት ላይ ያስተላለፋቸው ውሣኔዎች ማለትም ተጠሪው ያቀረቡት ክስ ሣይኖር ለአመልካቹ የከፈሉት ተጨማሪ ገንዘብ ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት/ አለ ብሎ ማረጋገጡና ሌሎች ተጨማሪ ነጥቦችን መተንተኑ ከክርክር ሂደት አኳያ ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፤ አመልካቹ ግዴታውን ሣይወጣ ክስ ማቅረብ አይችልም ተብሎ ተጠቃልሎ እያለ ፍ/ቤቱ ከዚህ አልፎ ወደ ሂሣብ ስራ ገብቶ ውሣኔ መስጠቱ ተገቢነት የለውም፤ ስለሆነም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የሰሜን ሸዋ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.17074፣ ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፍ/ይ/መ.ቁ. 6833/ ሰኔ 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሻሽለዋል፤ ይፃፍ፡፡

2/ አመልካቹ በመኪና ሽያጭ ውሉ የተመለከተውን ግዴታቸው ሣይወጡ ቀሪ ገንዘብ ተጠሪው ይስጠኝ በማለት ክስ ሊያቀርቡ አይችሉም፡፡

3/ ተጠሪው ክስ ሣያቀርቡ አመልካቹ ባቀረቡት ክስ ተጠሪው ለአመልካች ከመኪናው ሽያጭ ብር 10,416 /አስር ሺህ አራት መቶ አስራ ስድስት ብር/ ከፍለዋል የተባለውና ሌሎች ትችቶች የክርክር አካሄድ ስርዓት የተከተለ ውሣኔ ባለመሆኑ ተቀባይነት የለውም፣

4/ ታህሣሥ 03/2001 ዓ.ም የተላለፈው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡

5/ ግራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍ/ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፤ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 38935

መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ወልደፃድቅ ብርሃኑ - ቀረቡ

2. ወ/ሮ ፈንታነሽ ኃይሉ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** አቶ ስንታየሁ አያሌው - ጠበቃ አቶ ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፣ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 03131 ሐምሌ 27 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው ብይንና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 48885 ሰኔ 10 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ሰኔ 27 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ ስለጠየቁ ነው፡፡

የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይ አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤት በከሣሽነት ቀርበው በሥር ተከሣሽ የሆነው ተጠሪ፣ በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 11 ቀበሌ 19 የቤት ቁጥር 671 የሆነውን የመኖሪያ ቤት ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም ሸጠውልናል፡፡ ቤቱንና ቤቱ የሚመለከቱ ሰነዶችና ማስረጃዎችም አስረክበውናል፡፡

ሆኖም ተከሣሽ /ተጠሪ/ ከቀድሞው የቤቱ ባለንብረቶች መስከረም 21 ቀን 1986 ዓ.ም ባደረገው የግዥ ውል መሠረት ስመንብረቱን ወደራሱ በማዛወር ካርታውን ለማስረከብ የተስማማ ቢሆንም ቤቱን በሸጡለት እነ አቶ መስፍን አሰፋ ስም የወጣ ቁጥሩ 39348 የሆነ ካርታ ከተረከቡ በኋላ ካርታውን ለእኛ ለማስረከብ ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ካርታውን እንዲያስረክቡና ስመንብረቱን እንዲያዛወሩ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡ ተጠሪም በተከሣሽነት ቀርበው ቤቱ በሸጡልኝ ግለሰብ ስም ያለ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ የማይረጋ ነው፡፡ ከሣሾች /አመልካቾች/ ሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እድፈጽምላቸው ማስጠንቀቂያ ሰጥተውኛል፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ እንደውሉ ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ያወቁ ስለሆነ ክሱን ያቀረቡት ማስጠንቀቂያ ከሰጡኝ ከአንድ ዓመት ከስምንት ወር በኋላ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ክሣቸው በይርጋ ይታገዳል በማለት የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረቡ ሲሆን በአማራጭ ሌሎች መከራከሪያዎችን አቅርበዋል፡፡ የተጠሪ ሚስት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው በበኩላቸው በጣልቃ ገብነት በክርክሩ ለመግባት ያመለከቱ ሲሆን የበኩላቸውን ክርክር አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪና በጉዳዩ ጣልቃ ለመግባት ባለመለከቱት ወ/ሮ ስንታየሁ ሽፈራው ወደ ቀረቡት ዝርዝር ክርክር ከመግባቱ በፊት የከሣሾች /አመልካቾች/ ክስ በይርጋ ይቋረጣል ወይስ አይቋረጥም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በአመልቾችና በተጠሪ መካከል በውልና ማስረጃ ያልተመዘገበ የቤት ሽያጭ ውል የተደረገው መስከረም 21 ቀን 1992 ዓ.ም መሆኑን ገለፆና አመልካቾች ለተከሣሹ ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ ይኸም ክሱ የቀረበው አመልካቾች ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከአንድ ዓመት ከስድስት ወር በኋላ ስለሆነ

ክሱ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይቋረጣል በማለት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 245/2/ መሠረት መዝገቡን ዘግቶታል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛው ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሣኔን አጽንቷል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ ነኝ ካርታና ፕላኑን አስጨርሼ አስረክባለሁ በማለት ጥር 10 ቀን 1993 ዓ.ም በጽሑፍ መተማመኛ የሰጠ ከመሆኑም በላይ ማስጠንቀቂያ ከፃፍንለትም በኋላ በውሉ መሠረት ግዴታውን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑንና ፕሮሰሱን እያስጨረሰ መሆኑን እያነጋገረን ነበር፡፡ በመጨረሻ ሚስቱ ቤቱን በሌለሁበት ነው የገዛችሁት ብላ በነገረችን በሶስተኛ ቀን ክስ መሥርተናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ውሉ የሚፈፀምበት የጊዜ ገደብ ያልተቀመጠለት ጅምር ቤቱን ተረክበን አሰርተን ያጠናቀቅንና ሠርቪስ ቤቶችም ያሠራን መሆኑንና ተጠሪ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኑን ሲገልፅልን የቆየ መሆኑን ከግምት ውስጥ ሣያስገቡ፣ ለፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892/3/ የተሣሣተ ትርጉም በመስጠት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ማስጠንቀቂያ ከሰጡበት ከሚያዚያ 30 ቀን 1995 ዓ.ም ጀምሮ እንደማልፈጽምላቸው የሚያውቁ መሆኑን ባቀረቡት ክስ ገልፀዋል፡፡ አመልካቾች በሥር ያላነሱትን ውሉ እንደማይፈፀም የነገረችን ሚስቱ ናት በማለት ያቀረቡት ክርክር በሕጉ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ክሱን ያላቀረቡ በመሆናቸው ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል በማለት የሥር ፍርድ ቤቶች የሰጡት ውሣኔ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት በጽሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካቾች በሰበር አቤቱታ ያቀረቡትን ክርክር በማጠናከር በጽሑፍ የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካቾችና የተጠሪ ጠበቃ የካቲት 19 ቀን 2001 ዓ.ም በቃል ክርክር አድርገዋል፡፡

የክርክሩ አመጣጥ የክርክሩ መሠረታዊ ጉዳይና አመልካቾች እና ተጠሪ ያቀረቡት ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው የሥር ፍርድ ቤቶች የአመልካቾች ክስና ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ቀሪ ሆኗል በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በመጥቀስ የሰጡት ውሣኔ በአግባቡ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት የማይንቀሣቀስ ንብረት የገዛ ሰው ሻጭ በውሉ መሠረት እንዲፈፀምለት ስለሚጠይቅበት ሁኔታና ጥያቄውን ስለሚያቀርብበት የጊዜ ገደብ የተደነገጉ ድንጋጌዎችን፣ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ አመልካቾች ተጠሪ ሐምሌ 5 ቀን 1992 ዓ.ም በገባው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ ባለመሆኑ በፍርድ ተገድዶ እንዲፈፀምልን በማለት ያቀረቡት ክስ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የቀረበ ነው፡፡

አመልካች በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1776 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች መሠረት ያቀረቡት የቤት ሽያጭ ውል ይፈጽምልኝ ክስ በሕግ የተደነገገው የይርጋ ሕግ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ነጥብ ለመወሰን በመጀመሪያ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ ይዘት መንፈስና ዓላማ እንደዚሁም ድንጋጌው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና ስለ ሽያጭ እና ጠቅላላ ውል ከተደነገጉ ድንጋጌዎች ጋር ሊኖረው የሚገባውን ተፈፃሚነት መመርመር ያስፈልጋል፡፡

1.የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2893 ንዑስ አንቀጽ 3 "ስለሆነም ሻጭ ውሉን እንደውሉ ቃል ለመፈፀም መዘግየቱን ከተረዳበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ካልጠየቀ በቀር ገዢው ውሉ በግዴታ እንዲፈፀም የማድረግ መብቱን ያጣል" በማለት ይደነግጋል፡፡ እዚህ ላይ በአማርኛው "መዘግየቱን ከተረዳበት" በሚለው ቃልና በእንግሊዘኛው "ascertained" በሚለው ቃል መካከል ልዩነት ያለመሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን፡፡ የድንጋጌው መንፈስ ገዥ በአንድ ዓመት ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምለት ለፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ያለበት ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ካረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ እንደሆነ የእንግሊዘኛውን የቃል አጠቃቀም በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሣው ጥያቄ ሻጭ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ ያለበት ማን ነው? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ መሠረታዊ ነጥብ እልባት ለመስጠት ስለውል እና ተዋዋይ ወገኖች በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጠ የሕግ ግምቶችን ማየት አስፈላጊ ነው፡፡

በሕግ አግባብ የተቋቋሙ ውሎች ባቋቋሚቸው ሰዎች ላይ ሕግ ናቸው በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1731 ንዑስ አንቀጽ 1 የደነገገ ሲሆን ውሎች በተዋዋይ ወገኖች መካከል ሊኖር የሚገባውን የቅንነት የመተማመን ግንኙነት መሠረት በማድረግ በቅን ልቦና ሊተረጎሙ እንደሚገባ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1732 ይደነግጋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው ተዋዋይ ወገኖች በተዋዋሉት የውል ቃል መሠረት ውሉን የመፈፀም ፍላጎትና ቅን ልቦና ያላቸው መሆኑ የውል ሕግ ግምት የሚወስድበት ጉዳይ በመሆኑ ገዥ ሻጭ በሽያጭ ውሉ በገባው የውል ቃል መሠረት እንደሚፈጽም የተለያዩ የተስፋ ቃሎችን ሲሰጠው የቆየ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ የለበትም፡፡

በተቃራኒው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌን ጠቅሶ የሚከራከር ሻጭ ከገዥ ጋር ባደረገው የቤት ሽያጭ ውል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ በማያሻማ ሁኔታ እንዲያውቅ እና እንዲረዳው ያደረገ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም እንደማይፈልግ በእርግጠኝነት ገዥ እንዲያውቅ ካደረገው ከአንድ ዓመት በኋላ የሽያጭ ውሉ በፍርድ ኃይል እንዲፈፀምለት የጠየቀ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ ስለሆነም የማይንቀሣቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ሻጭ የሽያጭ ውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታና የባለቤትነት ሰነዶች ለገዥ ያላስረከበ ከሆነ ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑንና በጽሑፍና በማያሻማ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዢ ካሣወቀው ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ያቀረበ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

- ሻጭ በውሉ መሠረት የቤቱን ይዞታ ለገዥ አስተላልፎ ከሆነ ገዥ ሻጭ በውሉ መሠረት ይፈጽማል የሚለውን ዕምነት የሚያጠናክርና ውሉም በከፊል መፈፀም መጀመሩን የሚያሣይ መሆኑን ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 እና ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2274 ድንጋጌዎች ለመረዳት ይቻላል፡፡ ስለሆነም ሻጭ የቤቱን ባለሀብትነት ለገዥ ለማስተላለፍ እንደማይፈልግና የቤቱን ይዞታ ሻጭ በመልቀቅ እንዲያስረክበው የከፈለውንም ገንዘብ ገዥ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡

- ሻጭ የቤቱን ሰነዶች ለገዥ አስተላልፎ የቤቱን ይዞታ ይዞ በሚገኝበት ጊዜ የቤቱን ሰነዶች ሻጭ እንዲመልስለት የከፈለውን ገንዘብ እንዲወስድ በማያሻማ ሁኔታና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1789 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚደነግገው አይነት ለገዥ ያሣወቀ መሆኑን ማስረዳት የሚጠበቅበት ሲሆን ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች በአማራጭ ሻጭ ውሉ እንዲፈርስለት ወይም እንዲሰርዝለት በፍርድ ቤት ክስ አቅርቦ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ገዥ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን ወይም በሕግ እውቅና ላለው የሽምግልና ተቋም ሻጭና ገዥ በነበራቸው ድርድር ሻጭ ውሉን ለመፈፀም እንደማይፈልግ ገዢ እንዲረዳው ከተደረገ ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረበው መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡ በአጠቃላይ ሻጭ በገባው የሽያጭ ውል ቃል መሠረት ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ለገዥ ካሣወቀውና ገዥም ይህንኑ ከተረዳና ካረጋገጠ ከአንድ ዓመት በኋላ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ገዥ ያቀረበ መሆኑን የማስረዳት ግዴታ አለበት፡፡

ሻጭ በውሉ መሠረት ለመፈፀም የማይፈልግ መሆኑን ገዥ ያረጋገጠ መሆኑን ገዥ ውሉ እንዲፈፀምለት ማስጠንቀቂያ መስጠቱንና ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ ሻጭ በውሉ መሠረት አለመፈፀሙን በማየት ብቻ ለማረጋገጥ አይችልም፡፡ ሻጭ ገዥ ማስጠንቀቂያ ከሰጠው በኋላም ቢሆን የተለያዩ ችግሮችን እያነሣ በመካከላቸው ያለውን የመተማመንና የቅን ልቦና ግንኙነት ተጠቅሞ ከአንድ ዓመት በላይ ውሉን ሣይፈፀም የሚቆይበት አጋጣሚ ያለ ሲሆን በዚህ ጉዳይም ተጠሪ በሽያጭ ውሉ መሠረት ለመፈፀም የተለያየ ፕሮሰስ እየፈፀመ መሆኑን ለአመልካቾች በመግለጽ አመልካቾች ክስ ከማቅረብ እንደዘገዩ ያደረጋቸው መሆኑን በማንሣት አመልካቾች ተከራክረዋል፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ይርጋ ተፈፃሚነት የሚኖረው ገዥ ለሻጭ ማስጠንቀቂያ የሰጠበትን ቀን መነሻ በማድረግና ጊዜውን በማስላት ሣይሆን ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ገዥ እንዲያውቀው ያደረገበትን ቀን መነሻ በማድረግ መሆን ይገባዋል፡፡ ከዚህ አንፃር ስናየው የሥር ፍርድ ቤቶች አመልካቾች በውሉ መሠረት እንዲፈፀምላቸው ለተጠሪ ማስጠንቀቂያ የሰጡበትን ቀን መነሻ ጊዜውን አስልቶ የአመልካቾች ክስ

በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. በሁለተኛ ደረጃ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚነት የሚኖረው በሻጭና በገዥ መካከል የተደረገው ውል የማይፈፀምበት የመጨረሻ ቀን በጥብቅ የተወሰነ ከሆነ በውሉ የተወሰነው ነው የጊዜ ገደብ ካለፈ ከአንድ ዓመት በኋላ ገዥ የውል ይፈፀምልኝ ክስ ማቅረቡን በማስረዳት እንደሆነ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875 መሠረታዊ መርህና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ድንጋጌዎች ጋር አጣምሮ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህም አንፃር ስናየው በአመልካቾችና በተጠሪ መካከል የተደረገው ውል፣ ውሉ የሚፈፀምበትን ጭብጥ የጊዜ ገደብ የማያስቀምጥ በመሆኑ በጉዳዩ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2875፣ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2331 ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የላቸውም፡፡

3. በሶስተኛ ደረጃ የሚነሣው ጥያቄ በዚህ ጉዳይ ተጠቃሽና ተፈፃሚ መሆን ያለበት የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የትኛው ነው? የሚለው ነው፡፡ ሻጭ በውሉ መሠረት የመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለገዥ በማያሻማ ሁኔታ ያሣወቀ መሆኑን ባላስረዳበት ሁኔታ ወይም የሽያጭ ውሉ ውሉ የሚፈፀምበትን ጥብቅ የጊዜ ገደብ ባልተገለፀበት ሁኔታ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገው የአንድ ዓመት የይርጋ የጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት የለውም፡፡ በልዩ የሕግ ድንጋጌ የተቀመጠዉ የይርጋ ጊዜ ገደብ ተፈፃሚነት በማይኖረው ጊዜ ወይም በልዩ ሁኔታ የተደነገገ የይርጋ የጊዜ ገደብ ከሌለ ውል ይፈፀምልኝ በሚል መነሻ የሚቀርቡ ክርክሮች ላይ ተፈፃሚነት ያለው የይርጋ ሕግ ድንጋጌ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 እንደሆነ የዚህን ድንጋጌ ይዘት በመመርመር ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ከአመልካቾች ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ ሁኔታ ካሣወቀችው ከአንድ ዓመት በኋላ ክሱን ያቀረቡ ስለመሆኑ አላስረዳም፡፡ ስለሆነም በዚህ ጉዳይ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ 3 ተፈፃሚነት የለውም፡፡ የሥር ፍርድ ቤቶች ከላይ በዝርዝር ያስቀመጥናቸውን ምክንያቶችና የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ የአመልካቾች ጥያቄ በአንድ ዓመት ይርጋ ይታገዳል በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች ያቀረቡት የውል ይፈፀምልኝ ክስ በይርጋ የማይታገድ በመሆኑ አመልካችና ተጠሪ ሌሎች ተከራካሪዎች የሚያቀርቡትን ክርክር በመመርመርና በመመዘን ጉዳዩን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 341/1/ መሠረት መልሰን ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት መልሰን ልከንለታል፡፡
3. የአመልካቾች ክስ በይርጋ አይታገድም ብለናል፡፡
4. በሥር ፍርድ ቤት ያወጡትን ወጭ ግራ ቀኙ ለየራሣቸው ይቻሉ ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

□ሰ/መ/ቁ.ጥ 36756

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች:-** አብዱልቃድር መሐመድ

□□ሰ □ር□

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

□ሊ መሐመ□

**አመልካች:-** አቶ ፀጋዬ ምትኩ- ጠበቃ መኮንን አምቦ ቀርበዋል::

**ተጠሪዎች:-** 1/ ወ/ሮ አበበች ምትኩ - ጠበቃ አረጋ ይ□□ሱ ቀርበ□ል::

2/ አቶ ፈለቀ አላጋው - ጠበቃ አረጋ ይታገሱ ቀርበ□ል::

ጉዳዩ ከተመረመረ በኋላ የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል::

**□ ር □**

ጉዳዩ ሊቀርብ የቻለው አመልካች መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታቸው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ. 18885 ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ. 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው::

ጉዳዩ የተጀመረው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዚሁ ፍ/ቤት የአሁኑ አመልካች ከሣሽ፣ የአሁኑ ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች በመሆን የተከራከሩ ሲሆን፣ ስር ከሣሹ ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የተሻሻለ ክስ አጭር ይዘቱ ተከሣሾች በየካ ክፍለ ከተማ በቀበሌ 16 ክልል ውስጥ የሚገኘውን ቁጥሩ 740 የሆነውን ቤታቸውን የካቲት 02 ቀን 1980 ዓ.ም በተጻፈ የሽያጭ ውል በብር 20,000 ( ሃያ ሺህ ብር ) ሸጠውልኝ ቤቱንና ከቤቱ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶች በወቅቱ አስረክበውኝ በቁጥጥሬ ስር ይገኛሉ:: ይሁን እንጂ ቤቱ ገና ካርታ ያልወጣለት ስለነበር ካርታ በወቅቱ ሊያስረክቡኝ አልቻሉም ነበር:: አሁን ግን ካርታውን አውጥተው እንዲያስረክቡኝ ወይም ደግሞ ፍርድ ቤቱ የገዛሁትን ቤት በስሜ እንዲዛወርልኝ ( በከሣሽ ስም እንዲመዘገብ ) የሚያደርግ ውሣኔ ይሰጠኝ የሚል ነው::

ተከሣሾችም ጥቅምት 18 ቀን 1997 ዓ.ም በተጻፈ መልሳቸው ከሣሽ ያቀረቡት የውል ይፈጸምልኝ ጥያቄ ውሉ ተፈጸመ ካሉበት ጊዜ ወዲህ ሲታሰብ ከ16 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ በመሆኑ ክሳቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በ□ር□ □ሚታገድ ነው:: የሽያጭ ውሉም ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በፍርድ ቤት ፊት የተፈጸመ ባለመሆኑ:: እንዲሁም እኛ መሐይማን በመሆናችን ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1728/3/ መሠረት ውድቅ ነው ሊባልልን ይገባል ብለ□ል::

□ሥር □/ቤቱም □□ራ ቀኙን ወገኖች ክርክር ከላይ በሰፈረው መልኩ ከተገነዘበ በኋላ ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ብይን ወደ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ሳይገባ የቀረበው ክስ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ ክሱ እስከቀረበው ጊዜ ያለው ሲሰላ ከ10 አመት በላይ በመሆኑ ጉዳዩ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ የሚታገድ ነው በማለት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 245/2/ መሠረት ዘግቶ□ል::

ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን ወገኖች ካከራከረ በኋላ በመ/ቁ/ 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም በሰጠው ፍርድ የስር ፍ/ቤት ውሣኔን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት አፅንቶታል::

ከላይ የሰፈረው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት:: ቤቱ ውሉ ከተፈጸመበት ጊዜ □ምሮ በ□□ □□ለ □ሱ በ□ር□ □ታገዳል ሊባል አይገባም:: ተጠሪዎቹ የቤቱን ካርታ ያወጡት በ1996 ዓ.ም መጨረሻ በመሆኑና እስከዚያ ድረስ ግን ከተጠሪዎች አቅም ውጭ በሆነ ሁኔታ መንግሥት ካርታ እንዳይዘጋጅለት አግዶት የነበር ስለሆነ አመልካች ተጠሪዎቹ

*ካርታ ያስረክቡኝ ብዬ ክስ ለመስርት አልችልም ነበር። ስለዚህ ይርጋው የሚታሰበው ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ መሆን ሲገባው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተፈራረምንበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ መሰላቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ነው። ይርጋው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1846 መሠረት መሰላት ያለበት ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ጊዜ ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ነው በማለት መጋቢት 24 ቀን 2000 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታቸው ገልጸዋል።*

*መጋቢት 10 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎትም በግራ ቀኙ ወገኖች መካከል የቃል ክርክር የተካሄደ ሲሆን አመልካች በአቤቱታቸው ከገለጹት ሃሣብ ውጭ የሆነ ክርክር አላቀረቡም። ተከሣሾቹ በሰጡት መልስ ደግሞ ቤቱን አልሸጥንም፣ ተያያዥ ሰነዶችም አላስረከብንም፣ አለኝ በማለት ያቀረቡት ውል በሐሰት የተዘጋጀ ነው። ክሱ የቀረበው ከ16 □መታት በኋላ የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑና ሰኔ 29 ቀን 1996 ዓ.ም የተሻሻለ ክስ በመቅረቡ ውሉ ተደረ□ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ ሲታሰብ በይርጋ ይታገዳል። አመልካች የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ነው □ተ□□□ ማለታቸው የይርጋ መቋጠሪያውን ጊዜ ወደኋላ ሊመልስ የሚችል ምክንያት አይደለም። አመልካች የአንደኛ ተጠሪ ወንድም በመሆናቸውና የቤት ችግር የነበረባቸው በመሆኑ በጥገኝነት እንዲኖሩበት የሰጠናቸው እንጂ አልሸጥንላቸውም። ውሉ የመንደር ውል በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1723 መሠረት የማይፀናና ረቂቅ ነው ብለዋል።*

*□ር□ ቤቱም □□ራ ቀኙ ወገኖች ክርክር አመጣጥ ከላይ ባሰፈረው መልኩ በመገንዘብ ክርክሩ በ□ር□ ሊ□□□ ይገባዋል ወይስ አይገባውም ? የሚል መሠረታዊ ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን እንደሚከተለው መርምሮታል።*

*ከክርክሩ መረዳት እንደተቻለው አመልካች ባቀረቡት ክርክር የቤቱ ሽያጭ ውል የተደረገው የካቲት 2 ቀን 198ወ ዓ.ም ሆኖ ቤቱንና ከቤቱ ካርታ ውጭ ያሉ የቤቱ ሰነዶች ወዲያው ተረክበው እስካሁን ድረስ እየኖሩበት እንደሆነና ተጠሪዎችም ካርታ በወቅቱ ያልሰጧቸው በሚመለከተው አካል ካርታ እንዳይሰራላት ታግዶ ስለነበር እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎች እንደተሰጣቸው ወዲያውኑ ይህ ክስ እንደመሰረቱባቸው እኛም በ□ር□□ □□ መታሰብ ያለበት ከ1996 ዓ.ም መ□ ረሻ □ምሮ እንጂ ውሉ ከተደረገበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አይደለም የሚል ሲሆን ተጠሪዎቹ ባቀረቡት ክርክር ደግሞ የቤቱ ካርታ በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ተሰጣቸው የሚለውን የአመልካች መከራከሪያ ነጥብ ሳይክዱ የይርጋ ጊዜው መሰላት ያለበት ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 01845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ ይታገዳል የሚል የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ተገቢ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። የሥር ፍ/ቤቶችም በሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ውሣኔ ሳይሰጡ ውሉ ተደረገ ከተባለበት ከ1980 ዓ.ም ጀምሮ አመልካች ክስ እስካቀረቡበት ጊዜ ድረስ ያለው ጊዜ ሲሰላ ከ10 ዓመታት በላይ በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በይርጋ ይታገዳል በሚል ለ□□ዩ መቋጫ ያደረጉ መሆኑ መዝገቡ ያሳያል። ይሁን እንጂ ቤቱ ካርታ እንዳይዘጋጅለት በሚመለከተው አካል ታግዶ እስከ 1996 ዓ.ም መቆየቱ እና በ1996 ዓ.ም መጨረሻ ግን ካርታ ተዘጋጅቶ ለተጠሪዎቹ እንደተሰጣቸው ግራ ቀኙ ወገኖች የሚተማመኑበት ነጥብ ነው። ይህ በሆነበት ሁኔታ ደግሞ አመልካቹ ተጠሪዎቹን የቤቱን ካርታ ስጡኝ ወይም በስሜ አዘጋጁልኝ ብለው ሊከሱ የሚችሉበት የበሰለ መብት ያለመኖሩ □ሳ□ል። □□/ብ/*

*ሕ/ቁጥር 1846 እንደደነገገ□ም □□ር□ □□ መቆ□ር □ሚ□ምረ□ □ጸ ታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነ ጊዜ ጀምሮ ነው ይላል። አመልካቹ ለተጠሪዎቹ የቤቱን ካርታ በሚመለከተው አካል ከመሰጠቱ ከ1996 ዓ.ም በፊት ቢከሱ ኖሮ ሊፈጸም የማይችል መብት ይሆን እንደነበር ከክርክሩ መረዳት ይቻላል። በመሆኑም የስር ፍርድ ቤቶቹ በዚህ ጉዳይ ይርጋው መቆጠር ያለበት ውሉ ከተደረገበት ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም □ምሮ*

*መሆን አለበት የሚል ትርጉም በመያዝ ክርክሩ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት በ10 ዓመት ይርጋ የታገደ ነው በማለት የሰጡት ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የሚከተለውን ውሣኔ ሰጥተናል።*

<u>***□ ሣ ኔ***</u>

*1/ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት በመ/ቁ/ 18885 ህዳር 22 ቀን 1998 ዓ.ም የሰጠው □ር□ እንዲሁም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 44695 ታህሣሥ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጡት ፍርድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348 /1/ መሠረት ተሽረዋል። ይጻፍ።*

*2/ በዚህ ክርክር ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው የቤቱ ሽያጭ ውል ከተደረገበት ከየካቲት 02/1980 ዓ.ም ሳይሆን የሚመለከተው አካል የቤቱን ካርታ በተጠሪዎቹ*

ስም አዘጋጅቶ ከሰጠበት ከ1996 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ በመሆኑና አመልካችም በተ ጠሪዎቹ ላይ ክስ የመሰረቱት የካቲት 30 ቀን 1996 ዓ.ም በመሆኑ በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1845 መሠረት የይርጋው ጊዜ ያለፈበት አይደለም ብለናል፡፡

3/ ከይርጋ ክርክር ውጭ ባሉ ሌሎች መከራከሪያ ነጥቦች ጉዳዩን መርምሮ የመሰለውን ውሣኔ እንዲሰጥበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 341 መሠረት ለፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት ተመልሶለ□ል፡፡ □□፡፡

4/ □ራ ቀኙ ወገኖች በዚህ ፍርድ ቤት ላካሄዱት ክርክር ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ ብለናል፡፡

5/ ጉዳዩ ያለቀ በመሆኑ መዝገቡ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 41571

ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- ማህደር አእምሮ - ጠ/ይሁን ፀሐይ ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ላእከ ገ/መድህን- ጠ/ሙሉጌታ ገብሩ ቀረቡ

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ነው፡፡ የአሁኑ ተጠሪ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አመልካች ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ) ተበድረው በተዋዋሉት ቀን ያልከፈሉዋቸው በመሆኑ ዋናውን ገንዘብ፣ወለድ እና የገደብ መቀጫ እንዲከፍሏቸው ጠይቀዋል፡፡

አመልካች በሰጡት መልስ ገንዘቡን መበደራቸውን አምነው ነገር ግን ጥር 14/1997 ዓ.ም መክፈላቸውንና በዋስትና ያስያዙትን መቆፈሪያ ማሽንና ቼክ ተጠሪ ያስረከቧቸው መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃ ሰምቶ የገንዘብ ሰነድ ለባለእዳው መመለሱ እዳው እንደተከፈለ ያስቆጥራል፤ መቆፈሪያ ማሽኑም ገንዘቡ በመከፈሉ ተመልሷል በማለት አመልካች ያቀረቡት ክርክር የማስረጃና የሕግ ድጋፍ አለው በማለት የተጠሪን ክስ ውድቅ አድርጐታል፡፡

ተጠሪ በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው ፍ/ቤቱ የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የብድር መመለስን ማስረዳት የሚቻለው በፍ/ቤት በሚሰጥ የእምነት ቃለ መሐላ ወይም በጽሁፍ ብቻ ነው፤ አመልካች ደግሞ ብድሩ ስለመመለሱ ከነዚህ በአንዱም አላስረዱም በማለት የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሮ አመልካች ዋናውን ገንዘብ ወለዱንና የገደብ መቀጫ እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር ተሰኝተው ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ፍ/ቤቱ ይግባኙን ባለመቀበል ሰርዞታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ በዚህ ውሣኔ ላይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ስለተፈፀመ ይታረምልኝ በማለት የቀረበ ነው፡፡ የአመልካች ዋነኛ ቅሬታም ለብድሩ በዋስትና የተያዘው ቼክ እና የመቆፈሪያ ማሽን መመለሱ የብድሩ ገንዘብ መመለሱን ያረጋግጣሉ፤ የስር ፍ/ቤቱ ውሣኔ የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2020 እና 2845 "ን" ያላገናዘበ ነው የሚል ነው፡፡

የሰበር ችሎቱም የአመልካች አቤቱታ ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የአመልካችን አቤቱታ የሰበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔና አግባብነት ካላቸው የሕጉ ድንጋጌዎች ጋር መርምሯል፡፡

በዚህ መዝገብ አከራካሪ የሆነው ለብድሩ በዋስትና የተሰጡት ቼክና መቆፈሪያ ማሽን ለተበዳሪው መመለሳቸው ብድሩ ስለመከፈሉ ያረጋግጣሉ ወይ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ተጠሪ ለአመልካች ብር 120,000(መቶ ሃያ ሺህ) ያበደሯቸው እና ገንዘቡን ግን አመልካች ያልከፈሉ መሆኑን በመግለጽ ክስ የመሰረቱ ሲሆን አመልካችም ብድሩን መውሰዳቸውን ሣይክዱ ነገር ግን ገንዘቡን የከፈሉ መሆኑን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ አመልካች መበደራቸውን ያልካዱና ከፍያለሁ የሚሉ ስለሆነ ገንዘቡ ስለመከፈሉ በቅድሚያ የማስረዳት ሽክም አለባቸው፡፡ አመልካች ብድሩን ለመክፈላቸው ያቀረቡት ቀጥተኛ ማስረጃ የለም፡፡ የሚከራከሩት ለብድሩ በዋስትና ያስያዙት ቼክና መቆፈሪያ ማሽን ለእርሣቸው መመለሱ ብድሩ እንደተከፈለ የሚያስቆጥረው ነው በማለት ነው፡፡ በሌላ አነጋገር ቼኩና ማሽኑ ለባለእዳው መመለሱ ገንዘቡ እንደተከፈለ የሕሊና ግምት እንዲወሰድላቸው ነው የሚጠይቁት፡፡ የይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የአመልካችን ክርክር ውድቅ ያደረገው ከ500 ብር በላይ የሆነን የብድር ውል እንዲሁም ይህንኑ የገንዘብ መጠን የመመለስ ነገር ማስረዳት የሚቻለው በጽሁፍ ወይም ፍ/ቤት በተደረገ የእምነት ቃል ወይም በቃለ መሐላ ብቻ ነው በማለት ነው፡፡

በእርግጥ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2472 ስር ይኸው በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የተገለፀው ነገር ተመልክቷል፡፡ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ሁኔታዎች ሕጉ አንድ ፍሬ ነገር ከተረጋገጠ ማስረጃ ያልቀረበበት ሌላ አዲስ ነገር እንደተረጋገጠ ግምት እንዲወሰድበት የሚያዝበት አጋጣሚ አለ፡፡ በመሆኑም በህሊና ግምት መርህ (principle) የግምቱ ተጠቃሚ የሆነው ተከራካሪ ወገን የመጀመሪያውን ፍሬ ነገር ካረጋገጠ ሌላኛውን ፍሬ ነገር ለማረጋገጥ ማስረጃ ማቅረብ ሣያስፈልግ ፍ/ቤቱ ይኸው አዲስ ነገር እንደተረጋገጠ ግምት ሊወስድ ይገባል ማለት ነው፡፡ ከነዚህ የሕሊና ግምት ሊወሰድባቸው እንደሚገባ ሕጉ ከሚያስቀምጣቸው አንዱ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2020 ስር የተመለከተው ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሰነድ ለባለእዳው መመለሱ እዳው እንደተከፈለ የሚያስቆጥር መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ባለገንዘቡ እዳውን የሚያረጋግጥ ሰነድ እዳው ካልተከፈለው በቀር ለባለእዳው አይመልስም ተብሎ ስለሚገመት ነው፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ለወሰዱት ብድር ብር 120,000(አንድ መቶ ሃያ ሺህ) የያዘ ቼክ መስጠታቸው አላከራከረም፡፡ በተጨማሪም ይህንኑ ለዋስትና የተሰጠውን ቼክ ተጠሪ ለአመልካች የመለሱላቸው መሆኑን በስር ፍ/ቤት በምስክሮች ተረጋግጧል፡፡ ቼኩ ለተጠሪው የተሰጠው እዳ መኖሩን በማረጋገጥ ለእዳው አከፋፈል ዋስትና እንዲሆን ነው፡፡ በመሆኑም ተጠሪ እዳ ካልተከፈላቸው ቼኩን ባንክ ወስደው በመመንዘር ለእዳው መክፈያ ከማዋል ፋንታ እዳው ሣይከፈላቸው ለአመልካች የሚመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ቼኩን ለተጠሪ ከመለሱ ደግሞ እዳው እንደተከፈለ እንደሚቆጠር ሕጉ ያመለክታል፡፡ በመሆኑም ለአመልካች ቼኩ መመለሱ የብድሩ ገንዘብ እንደተከፈለ የሕሊና ግምት ሊወሰድበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል አመልካች ለብድሩ በመያዣ የሰጡት የመቆፈሪያ ማሽንም ቢሆን ለአመልካች መመለሱ በመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ተረጋግጧል፡፡ በእርግጥ በክርክሩ ሂደት ማሽኑ በባንክ በመያዣ መያዙን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን በባንክ በመያዣ መያዙ ብቻ ሣይሆን ተጠሪ በፈቃዳቸው ማሽኑን ለአመልካች መመለሣቸው በፍሬ ነገር ረገድ ተረጋግጧል፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2846 መያዣ የተቀበለ ባለገንዘብ ሊከፈለው የሚገባው በሙሉ እስኪከፈለው ድረስ የመያዣውን እቃ በእጁ የማቆየት መብት ያለው መሆኑ ተመልክቷል፡፡ ተጠሪ ሊከፈላቸው የሚገባው እዳ በሙሉ ተከፍሎ ካላለቀ መያዣውን ለአመልካች የሚመልሱበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ለእዳው አከፋፈል በመያዣ የተሰጣቸውን ንብረት ዕዳው ሳይከፈላቸው ለባለዕዳው ይመልሣሉ ብሎ መገመትም ያስቸግራል፡፡ በተቃራኒው መያዣውን የተቀበለ ባለገንዘብ ለእቃ አስያዡ ዕቃውን የሚመልሰው ገንዘቡ ሲከፈለው ወይም በሌላ ምክንያት የመያዣው ውል ሲያልቅ መሆኑም በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2845/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ ተጠሪም በዋስትና የያዙትን ማሽን ለባለገንዘቡ መመለሣቸው አመልካች ያለባቸውን ገንዘብ በመክፈላቸው መሆኑን ችሎቱ ተገንዝቧል፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተመለከቱትን የሕጉን ድንጋጌዎች ሣያገናዝብ ብድሩ ስለመከፈሉ በጽሁፍ ወይም በፍ/ቤት በተሰጠ እምነት ቃል ወይም በቃለ-መሐላ ያልተረጋገጠ በመሆኑ አመልካች የብድሩን ገንዘብ ከወለድና መቀጫ ጋር ይክፈሉ በማለት ይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት የሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 58565 በ06/09/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 39461 በ04/02/2001 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 30571 በ20/10/99 የሰጠው ውሣኔ ጸንቷል፡፡

3. አመልካች ክስ የቀረበበትን የብድር ገንዘብ ሊከፍሉ አይገባም ብለናል፡፡

4. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ.መቁ. 39336

ሐምሌ 07 ቀን 2001

ዳኞች፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መሰሠ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ኒያላ ኢንሹራንስ አ/ማ - ጠ/ ተካ አስፋው ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አዱኛ እጅጉ - ጠ/ መኰንን ሽፈራው ቀረቡ

2. ጤናዬ ገለታ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሠጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በሥር ፍ/ቤት ከሣሽ የነበሩት የአሁኖቹ ተጠሪዎች ናቸው፡፡ በክሣቸውም ንብረታቸው የሆነ ህንፃ በረቂቅ የሽያጭ ውል መሠረት አመልካች ስለያዘው እንዲያስረክባቸው እና ላላግባብ ለተጠቀመበትም ኪራይ እንዲከፍላቸው ጠይቀዋል፡፡ አመልካች ለክሱ በሰጠው መልስ ውሉ በውልና ምዝገባ ጽ/ቤት ያልተደረገው በተጠሪዎች ክፉ ልቦና መሆኑን፣ ንብረቱን ፈቅደው ለአመልካች ማስረከባቸው ውሉም ረቂቅ ሣይሆን ያለቀ መሆኑን ኪራይም ሊከፈላቸው እንደማይገባ ተከራክሯል፡፡ በበኩሉም ቤቱን ገዝቶ የያዘው በመሆኑ ስም እንዲይዛወርለት ይህ ካልሆነ ለህንፃው መግዣ የከፈለው ብር 6,500,000 (ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) እንዲመለስለት የተከሣሽ ከሳሽነት ክስ አቅርቧል፡፡

ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር መርምሮ የሺያጭ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ባለመደረጉ በህግ ፊት አይፀናም በማለት ውሉ ፈርሶ አመልካች ህንፃውን ለተጠሪዎች እንዲያስረክቡና ተጠሪዎች የተቀበሉት ብር

6, 500,000 ለአመልካች እንዲመልሱ በማለት ወስኗል፡፡

በዚህ ውሣኔ አመልካች ቅር በመሠኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርብም ይግባኙ ተቀባይነት አላገኘም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታም የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡

የአመልካች አቤቱታም ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በመባሉ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ይህ ችሎትም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የህጉ ድንጋጌዎች አንፃር ተመልክቶታል፡፡

ከፍ ሲል እንደተገለፀው የተጠሪዎች ክስ የመሠረቱት አመልካች በረቂቅ የሺያጭ ውል የያዘውን ህንፃ ያስረክበን በሚል ነው ከተጠሪዎች ክስም ሆነ ከክርክሩ ሂደት በአመልካችና በተጠሪ መሐከል የህንፃ ሽያጭ ውል የተደረገ መሆኑ፣ በዚህ ውል መሠረት ተጠሪዎች ህንፃውን ለአመልካች ማስረከባቸውና የሺያጩ ገንዘብ ብር 6,500,000 መቀበላቸው አከራካሪ ያልሆኑ ነገሮች ናቸው፤ ተጠሪዎች ለመክሰስ ምክንያት የሆናችው ይህ የሺያጭ ውል ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በዳኛ ፊት ያልተደረገ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ችሎት ይህ የሺያጭ ውል ፈርሶ አመልካች ህንፃውን ለጠሪዎች ሊያስረክብና ተጠሪዎችም የሺያጩን ገንዘብ ለአመልካች ሊመልሱ ይገባል ወይ? የሚለውን ጭብጥ መስርቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት እንደተገነዘብነው ግራ ቀኙ የህንፃ የሺያጭ ውል ማድረጋቸውን እንዳልተካካዱ ሁሉ ውሉ ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው አካል ወይም በፍ/ቤት ያልተደረገ መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ የማይንቀሣቀስ ንብረትን የባለቤትነት መብት ለማስተላለፍ የሚደረግ ውል ሁሉ በፁሁፍና በሚገባ አኳኋን በፍ/ቤት መዝገብ ወይም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሠጠው ሰው ፊት መሆን እንዳለበት የፍ/ብ/ህ/ቁ 1723(1) ያመለክታል፡፡ ይህን የአፃፃፍ ሥርዓት መከተል ውሉ በህግ ፊት የፀና እንዲሆን ከሚያስፈልጉ መስፈርቶች አንደኛው ነው፡፡ ስለሆነም በህግ ፊት ውጤት እንዲኖረው የማይንቀሣቀስ ንብረት ሺያጭ በህጉ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ሊከተል ይገባል፡፡ ይህን ስርዓት ካልተከተለ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል በፍ/ብ/ህ/ቁ 1808(2) ተገልጿል፡፡ ውሉ በህግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ካልጠበቀ ከተዋዋዩቹ አንዱ ወይም ማንኛውም ጥቅም ያለው ሰው ውሉ እንዲሠረዝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡ በዚህም መሠረት ውሉ እንዲፈርስ ሊወሰን ይችላል፡፡ የውሉም መፍረስ ውጤቱ በተቻለ መጠን ውለታ ከመደረጉ በፊት ወደነበሩበት ሁኔታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው፡፡ (በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815(1)) ተዋዋዩቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሲወሰን ውለታውን ለመፈፀም የተሠራ ሥራ ሁሉ ቀሪ እና ውጤት የሌለው እንደሚሆን የተጠቀሰው አንቀፅ ንዑስ ቁጥር 2 ይገልፃል፡፡

በመርህ ደረጃ ከፍ ብለው የተጠቀሱት ጉድለቶች ሲያጋጥሙ ውሉ ፈርሶ ተዋዋዮች ወደነበሩበት ቦታ የሚመለሱ ቢሆንም የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817 ጉድለት ኖሮም ቢሆን ውሉ የሚፈጋበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ይደነግጋል፡፡ ይኸው የፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817(1) "ውለታውን ለመፈፀም የተሰራውን ሥራ ለማፍረስ የማይቻል ሲሆን ወይም አስቸጋሪ ሆኖ ሊገኝ ወይም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሲሆን እነዚህ የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ይደረጋል" በማለት ይደነግጋል፡፡ የዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ትርጉም "Acts done in performance of the contract shall not be invalidated where such invalidation is not possible or would involve serious disadvantages or inconvenience" ይላል፡፡ ከሕጉ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻለው ውለታውና (contract) ውሉን ለመፈፀም የተሰሩ ስራዎች (acts) የሚለያዩ መሆናቸው ነው፡፡ ስለሆነም ውሉ በራሱ በአንድ በኩል፣ ውሉን ለመፈፀም የተከናወኑ ተግባራትን በሌላ በኩል ለይቶ ማየት አስፈላጊ ነው፡፡ ተዋዋዮች በፈቃድ ጉድለት፣ በችሎታ ማጣት ወይም በህግ የተመለከተውን የአፃፃፍ ሥርዓት ባለመከተል የውል ስምምነት አድርገው ሊሆን ይችላል፡፡ ይህንንም ጉድለት ያለበትን ውል ለመፈፀም የተለያዩ ተግባራትን ፈፅመውም ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ውሉ የማይፀናበትን ምክንያት በመግለፅ ውል እንዲፈርስ ሲጠየቅ ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ሊመለሱ የሚገባ ቢሆንም ይህ ጉድለት ያለበትን ውል ለመፈፀም የተከናወኑትን ተግባራት (acts) ማፍረስ ፈፀሞ የማይቻል ወይም ከፍ ያለ መሰናክል ወይም አስቸጋሪ የሚሆንበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይህ በሆነ ጊዜ ደግሞ ከፍ ሲል እንደተገለፀው ዳኞች ሊወስኑ የሚገባው ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ሣይሆን የተሰሩት ሥራዎች እንደረጉ እንዲቆዩ ነው፡፡ ምናልባት ወደነበሩበት መመለስ ባለመቻሉ የደረሰ ጉዳት ካለ ጉዳቱን በካሣ መልክ ወይም ፍ/ቤቱ ተገቢ ነው የሚለውን መፍትሔ በመስጠት ሊስተካከል ይችላል (የፍ/ብ/ህ/ቁ/1817(2))፡፡ በመሆኑም ውሉ የሚፈርስበት ወይም የሚሠረዝበት ምክንያት ሲከሰት ውሉ ፈርሶ ግራቀኙ ወደነበሩበት የመመለስ ውሣኔ ሊሰጥ የሚገባው ውሉን ለመፈፀም የተሠራው ሥራ ቀሪ ለማድረግ የሚቻል ከሆነ ብቻ ነው፡፡

በዚህ መሠረት የቀረበልንን ጉዳይ ተመልክተናል፡፡ አመልካች በ1994 ዓ.ም 6,500,000(ስድስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን) ሚሊዮን ብር በመክፈል ከመልስ ሰጪ ሕንፃ መረከቡ ተረጋግጦአል፡፡ ህንፃውን ከተረከቡ በኋላ የኢንሹራንስ ሥራ ለማካሄድ እንዲያስችለው ህንፃው ላይ የተለየዩ ማስተካከያዎች የተደረጉበት ስለመሆኑም ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በሰበር ችሎት ባለጉዳዮች የቃል ክርክር ባደረጉበት ወቅት አመልካች ለመኪና ማቆምያ አገልግሎት የሚውል ሌላ ተጨማሪ ቦታ ገዝቶ የጨመረበት መሆኑንም ለማወቅ ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ይህ ችሎት በሙሉ አመሰራረት ሂደት የነበረውን ጉድለት መሠረት በማድረግ ተዋዋዮቹ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማድረግ ተገቢ መሆን አለመሆኑን አገናዝቧል፡፡ አሁን በቀረበልን ጉዳይ ተዋዋይ ወገኖችን ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስ ማለት አመልካች የከፈለውን ብር 6,500,000(ስድስት ሚሊዮን አምስት መቶ ሺህ) እንዲቀበል በማድረግ መልስ ሰጪዎች ደግሞ ቤቱን እንዲረከቡ ማድረግ ማለት ነው፡፡ ክፍያውን የመፈፀምም ሆነ ቤቱን የመረከብ ሥራ በፍትሐብሔር ሕጉ አንቀፅ 1815(2) መሠረት ውለታው ለመፈፀም የተሰሩ ሥራዎች (acts) በመሆናቸው በመርህ ደረጃ ውሉ ሲፈርስ አብረው ዋጋ የሚያጡ ናቸው፡፡ ሆኖም አሁን በቀረበልን ጉዳይ እነዚህን ሥራዎች (acts) ዋጋ እንዲያጡ ማድረግ አስቸጋሪና ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ ሆኖ (involving serious disadvantage and inconvenience) አግኝተነዋል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ በዚህ ችሎት ዕምነት የሽያጭ ዋጋውን በመመለስና ቤቱን በመረከብ ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የሚቻል አይደለም፡፡ ገንዘቡ

ከተከፈለበት ከ1994 ዓ.ም ወዲህ በመንግስትም ዕውቅና ያገኘ የገንዘብ ግሽበት (inflation) ያለ በመሆኑ የተከፈለው ገንዘብ አሁን ከሚመለሰው ገንዘብ ጋር ተመጣጣኝ ነው ሊባል አይችልም፡፡ በሌላ በኩል የሚመለሰው ቤት ደግሞ በአንፃራዊነት የዋጋ ጭማሪ እንደሚያሳይ ይገመታል፡፡ ይህ ግምት እንኳን ቢታለፍ ቤቱን ገዝቻለሁ በሚል ዕምነት አመልካች በህንፃው ላይ ለያዘው ንግድ የሚመች ለማድረግ የተለያዩ ወጪዎችን አውጥቶበታል፡፡ በመሆኑም አሁን ያለው ህንፃ መጀመሪያ ከተረከበው ህንፃ ጋር አንድ ዓይነት ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ በመሆኑም በዋጋ ግሽበት ምክንያት የሚረከበው ገንዘብ እሴት (value) በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ከሚያስረክበው ህንፃ ዋጋ በተለያዩ ምክንያቶች መጨመር ጋር ተዳምሮ ወደነበሩበት የመመለሱ ሥራ ለመልስ ሰጪ ያልተገባ ጥቅም የሚሰጥና አመልካችን የሚጐዳ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ኩባንያ ህንፃውን ለንግድ የሚጠቀምበት መሆኑ ህንፃው ከሚገኝበት ቦታ ጋር የተያያዘ መልካም ስም (good will) እንዲያጣ ስለሚያደርገው የጉዳቱም መጠን በዚያው መጠን መጨመሩ የሚቀር አይሆንም፡፡ በክርክሩ ሂደት አመልካች ቤቱን ገዝቻለሁ በሚል ዕምነት ተጨማሪ ለመኪኖች የሚሆን ቦታ ገዝቶ እየተጠቀሙበት መሆኑ ሲታከልበት ደግሞ ወደነበሩበት የመመለስ (reinstatement) አማራጭ በፍትሃብሔር ሕጉ አንቀፅ 1817 እንደተገለፀው ከሞላ ጐደል የማይቻል ያደርገዋል፡፡

በመሆኑም ግራ ቀኙ ያላቸው የሽያጭ ውል በረቂቅ ደረጃ ያለ ነው የሚለው የመልስ ሰጪ ክርክርም ሆነ የሥር ፍ/ቤቶች ድምዳሜ በመሠረቱ ትክክል ቢሆንም በዚህ ረቂቅ ውል መነሻነት የተፈፀሙ ሌሎች ድርጊቶችን ወደኋላ ተመልሶ እንዳልነበሩ መቁጠር ግን ከላይ በዘረዘርነው ምክንያት ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡ ፍርድ ቤቶች ሁለቱም ተዋዋይ ወገኖች ወደነበሩበት ይመለሱ ብለው ከመፍረዳቸው በፊት በሕጉ እንደሰፈረው የውሉ መፍረስ ወይም መሰረዝ ብቻ ሳይሆኑ ከዚህ ጋር ተያይዘው የተፈፀሙ ሌሎች ሥራዎች (acts) እንዳልተሰሩ የመቁጠር ውጤት ሊመዝኑ ይገባል አሁን በያዝነው ጉዳይ ክሱ የቀረበለት ሆነ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው ፍ/ቤት ክርክሩን ከዚህ አቅጣጫ ተመልከተው አግባብነት ያለውን የሕግ ድንጋጌ ተፈፃሚ አላደረጉም፡፡ ስለዚህ በግራ ቀኙ የተከናወኑትን ድርጊቶች ከግምት ሣያስገቡ የሥር ፍ/ቤቶች የሽያጭ ውሉ የአፃፃፍ ሥርዓትን ባለመከተሉ ብቻ ውሉ ፈራሽ ሆኖ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት ይመለስ በማለት የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 56347 በ21/6/2000 የሰጠው ውሣኔ እና የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 36804 በ3/11/2000 የሰጠው ትዕዛዝ ተሽረዋል፡፡
2. የሽያጭ ውሉ የአፃፃፍ ሥርዓትን ያልተከተለ ቢሆንም ውሉ ፈርሶ ግራ ቀኙ ወደነበሩበት እንዲመለሱ ማድረጉ አስቸጋሪና ከፍ ያለ መሰናክል የሚያመጣ በመሆኑ ውሉ ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ በፍ/ብ/ህ/ቁ 1817(1) መሠረት ወስነናል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች ክስ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39170

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ - ነ/ፈጅ ባይሳ ሸኔ ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- 1. አቶ ክንዴ አፍራሶ - ጠበቃ ዳኛቸው ተስፋዬ ቀረቡ

2. አቶ ጅብሪል ኢማም - ጠበቃ ዘውገ ተስፋዬ ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የክርክሩም አመጣጥ ባጭሩ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ ለንግድ ስራ ማከናወኛ ብር 421,612.80 (አራት መቶ ሃያ አንድ ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሁለት ብር ከሰማንያ ሣንቲም) በ24/4/83 ዓ.ም በተደረገ የብድር ውል ከአመልካች ላይ ተበድረው ገንዘቡን በውሉ መሰረት ያልከፈሉ ስለሆነ እንዲከፍሉ ይወሰንልኝ በማለት ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ በ19/11/96 ዓ.ም በዋለው ችሎት ክስ የቀረበበትን ገንዘብ ተከሳሹ ለከሳሽ ሊከፍሉ ይገባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች የፍርድ አፈጻጸም ማመልከቻ አቅርቦ ንብረትነቱ የፍርድ ባለእዳው የሆነውንና በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ አጠራር በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው የቤት 020 የሆነው ቤት በሐራጅ ተሽጦ እዳው እንዲከፈል ጠይቆ አፈጻጸሙን የያዘው የፌደራል መ/ደ/ፍ/ቤት በፍርድ አፈጻጸም መምሪያ በኩል አፈጻጸም የተጠየቀበት ይሄው ቤት በሐራጅ እንዲሸጥና ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ሰጥቶ በዚሁ መሰረት የፍርድ አፈጻጸም መምሪያ ቤቱን ለመሸጥ ሲንቀሳቀስ የአሁን ሁለተኛ ተጠሪ እንዲሸጥ የተባለው ቤት የፍርድ ባለእዳው ሳይሆን የእኔ ንብረት ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል ስለማይችል በዚህ ረገድ የተሰጠው ትእዛዝ ይነሳልን በማለት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ቤቱ በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በአመልካቹ ስም በአሁን ሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ የሚታወቅ ስለመሆኑ ሲገለጽለት በፍርድ አፈጻጸም እንዲሸጥ ትእዛዝ የተሰጠበት ቤት የፍርድ ባለእዳ ሳይሆን የአመልካች መሆኑ ስለተረጋገጠ አፈጻጸሙ ይቁም በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ ባለመብቱ የአሁን አመልካች በዚሁ ትእዛዝ ቅር በመሰኘት የይግባኝ ቅሬታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርቦ ፍ/ቤቱም በበኩሉ ግራ ቀኙን አከራክሮ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት አጽንቶታል፡፡

የሰበር አቤቱታው የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን የአመልካችም የቅሬታ ነጥብ ተጠቃሎ ሲታይ አመልካች የብድሩ ገንዘብ እንዲከፈለው በአንደኛ ተጠሪ ላይ ክሱን ካቀረበ በኋላ አንደኛ ተጠሪ ይህንኑ የአፈጻጸም ክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት ከ2ኛ ተጠሪ ባገኙት ውክልና መሰረት ለባለቤታቸው ለወይዘሮ ፀሐይ ጉልማ ገዝተው ስም እንዲዞርም ለሚመለከተው አካል አመልክተው ውሉ ከቤቱ ማኅደር ጋር ተያይዞ እንደሚገኝና እንዲታገድ ለፍ/ቤቱ ባቀረበው ጥያቄ መሰረት ፍ/ቤቱ አምኖበት ቤቱ ተከብሮ እንዲቆይ በ26/11/92 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቶ ይሄው ትእዛዝ ለሚመለከታቸው ክፍሎች ተላፍፏል፡፡ ፍ/ቤቱ ቤቱ እንዳይሸጥ እገዳ ከሰጠ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 መሰረት በፍርድ የተገኘ የመያዣ መብት

(judicial mortgage) እንደተቋቋመና በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723 መሰረትም እንደተመዘገበ ማረጋገጥ የሚቻል በመሆኑ የስር ፍ/ቤቶች ክርክሩን ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ በመመልከት ሁለተኛ ተጠሪ በቤቱ ላይ መብት እንደሌላቸው ማረጋገጥ ሲገባቸው ቤቱ የሁለተኛ ተጠሪ ስለሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል የሚል ነው፡፡

ይህም ችሎት የቀረበውን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ሁለተኛ ተጠሪ ይሄው ቤት እንዲሸጥ ውክልና ለአንደኛ ተጠሪ በሰጡበት ሁኔታ እንደዚሁም አንደኛ ተጠሪ ቤቱን ተረክበው እየኖሩ ባሉበት ሁኔታ የስር ፍ/ቤቶች ቤቱ ተመዝግቦ የሚገኘው በ2ኛ ተጠሪ ስም እንጂ በፍርድ ባለእዳው በአንደኛ ተጠሪ ስም ስላልሆነ አፈጻጸሙ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ውሳኔ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

የተጠሪዎችም ክርክር ተጠቃሎ ሲታይ አንደኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተውን አካል ጠይቆ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ ተረጋግጦለታል፡፡ ይህም ሁኔታ ቤቱ በ26/11/92 ዓ.ም በፍ/ቤት ተሰጥቷል የተባለውን እግድ የሚያፈርስና እግድ እንደሌለ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በአስተዳደር ክፍል የተሰጠ የባለሐብትነት የምስክር ወረቀት እስካልተሰረዘ ድረስ የባሐብትነት ማረጋገጫ እንደሆነ ይህ ሰበር ችሎት በመ/ቁ. 14554 የሕግ ትርጉም የሰጠበት ሲሆን በተያዘውም ጉዳይ ካርታና ደብተሩ ተመዝግቦ የሚገኘው በሁለተኛ ተጠሪ ስም ስለሆነ የስር ፍ/ቤቶች አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም በማለት የሰጡት ትእዛዝ የሰበር ችሎቱ አስቀድሞ ከያዘው አቋም ጋር የተጣጣመ ነው፡፡

ከዚህም ሌላ አመልካች በቤቱ ላይ በፍርድ የተገኘ የመያዣ መብት አግኝቻለሁ የሚለው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041"ን" በመጥቀስ ነው፡፡ ሆኖም ቤቱ ቀድሞውንም ቢሆን በአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ስም ተመዝግቦ ይታወቅ የነበረ ባለመሆኑ ቤቱ ታግዷል ለማለት የማይቻል ከመሆኑም በላይ በፍርድ የሚሰጥ የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ የሚቋቋመው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3044 መሰረት ሲሆን ይህ የመያዣ መብትም የሚቋቋመው ፍ/ቤቶች በዳኝነት በሚሰጡት ፍርድ እንጂ በእግድ ሰበብ ሊቋቋም አይችልም፡፡

ስለሆነም የበታት ፍ/ቤቶች የፍርድ አፈጻጸሙ በሁለተኛ ተጠሪ ቤት ላይ ሊቀጥል አይችልም በማለት የሰጡት ትእዛዝ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ የሰበር አቤቱታው ከኪሳራ ጋር ሊሰረዝ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ሁለተኛ ተጠሪም በይዘቱ ከአንደኛ ተጠሪ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መልስ አቅርበዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ዝርዝሩን መመዝገቡ ባለማስፈለጉ ታልፏል፡፡

በአጠቃላይ የግራ ቀኙ ክርክር ከፍ ብሎ የተመለከተው ሲሆን ምላሽ ማግኘት የሚገባው የጉዳዩ ጭብጥ አመልካች የጀመረው አፈጻጸም በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል ቁጥሩ 020 በሆነው ቤት ላይ ሊቀጥል ይገባል ወይንስ አይገባም? የሚለው ነው፡፡ ይህንኑ ጭብጥ ይዘን ጉዳዩን መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የአሁን አመልካች በብድር የተወሰደ ገንዘብ እንዲከፈለው በክናፍ የቆዳ ውጤቶች አምራችና ላኪ ድርጅት እንደዚሁም በአሁን አንደኛ ተጠሪ በአቶ ክንዴ አፍራሶ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ክሱን ካቀረበ በኋላ የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት በሆኑት በወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ስም የተመዘገበው በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘው የቤ.ቁ. 020 የሆነው ቤት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 154 መሰረት እንዲከበርለት አቤቱታ አቅርቦ ፍ/ቤቱም የቀረበውን አቤቱታ መርምሮ የተጠቀሰው ቤት ጉዳዩ እልባት ከማግኘቱ በፊት ቢሸጥ ወይም ለሌላ ሦስተኛ ወገን ቢተላለፍ ከሳሽ ወደፊት በፍርዱ ተጠቃሚ ቢሆን ፍርዱን የሚያስፈጽምበት ንብረት በማጣት ሊተካ የማይችል ጉዳት ሊደርስበት እንደሚችል ያቀረበው ቃለመሐላ ተቀባይነት አለው በማለት በትእዛዙ ላይ ካሰፈረ በኋላ የተጠቀሰው ቤት በግለሰቧ ስም ተመዝግቦ የሚገኝ ከሆነ ተለዋጭ ትእዛዝ እስከሚሰጥ ድረስ እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ በማናቸው ወገን ለሦስተኛ ወገን ሳይተላለፍ ተከብሮ ይቆይ በማለት ሐምሌ 26 ቀን 1992 ዓ.ም የእግድ ትእዛዝ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ በኋላም ቤቱን ከሁለተኛ ተጠሪ ገዝተዋል የተባሉት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት የሆኑት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ በዚህ ቤት ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 154"ን" በሚጻረር ሁኔታ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 158 መሰረት እንዲነሳልኝና ስለመነሳቱም አስቀድሞ የእግዱ ትእዛዝ ተላልፎላቸው ለነበሩት አካላት ይተላለፍልኝ ሲሉ ጥር 18 ቀን 1993 ዓ.ም አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም አቤቱታውን መርምሮ የእግዱ ትእዛዝ የተሰጠው ቤቱ የክርክሩ ምክንያት

ነው ተብሎ ሳይሆን ለፍርድ ማስፈጸሚያነት በሚል ስለሆነ አስቀድሞ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ሊነሳ አይገባም በማለት አቤቱታውን ሳይቀበለው መቅረቱንም ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይገባም የሚል መቃወሚያ በሁለተኛ ተጠሪ አማካይነት ሲቀርብለት የቤቱ ባለቤት በማን ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል እንዲያረጋግጥ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ባለሐብትነቱ በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል የገለጹለት ቢሆንም ባለሃብትነት ከሕግ ወይም ከውል የሚመነጭ እንደመሆኑ መጠን በ6/4/84 ዓ.ም በተደረገ ውል የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ ይህንኑ ቤት ከሁለተኛ ተጠሪ የገዙ እንደመሆኑ መጠን ባለሐብትነታቸው በውል እንደተቋቋመ መገንዘብ ስለሚቻል የባለቤትነት ስሙ ወደ ገዢ ሳይዛወር በሻጭ ስም ተመዝግቦ መገኘቱ ይህ የሂደት ጉዳይ እንጂ የወሉን አመሰራረት ጥያቄ ውስጥ የሚከተው አይሆንም፡፡ ሐምሌ 26 ቀን 1992 ዓ.ም ፍ/ቤቱ የሰጠው የእግድ ትእዛዝም የሚመለከተው አካል ተቀብሎ ተግባራዊ ያደረገው በዚሁ የሽያጭ ውል መሰረት ቤቱ ከሁለተኛ ተጠሪ ወደ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ መተላለፉን በማረጋገጡ ነው፡፡ ይህ ባይሆን ኖሮ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ እግዱ እንዲነሳ ማመልከት ባላስፈለጋቸው ነበር፡፡ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3041 ላይ እንደተደነገገው መያዣ ከውል ብቻ ሳይሆን በቀጥታ ከሕግ ወይንም ደግሞ በፍርድ ሊቋቋም ይችላል፡፡ በዚህም ጉዳይ ፍ/ቤቱ በዚህ ቤት ላይ የሰጠው የእግድ ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3044 ላይ እንደተመለከተው ለአመልካች ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብትን (judicial mortgage) ያጐናጽፋል፡፡ ይህ ሰበር ችሎትም በመ/ቁ. 25863 በሰጠው የሕግ ትርጉም በፍ/ቤት በንብረት ላይ የሚሰጥ የእግዳ ትእዛዝ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ተቋቁሟል ለማለት እደሚያበቃ በመጥቀስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ስለሆነም ተጠሪዎች የቤቱ ባለሐብት ሁለተኛ ተጠሪ ስለሆኑ በዚህ ንብረት ላይ የተሰጠው የእግድ ትእዛዝ ተፈፃሚ አልሆነም በማለት ያነሱት ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አልተገኘም፡፡

በሌላ በኩልም የሽያጭ ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ የሽያጭ ውል አለ ለማለት አይቻልም በማለት ተጠሪዎች ያነሱትን ክርክር በተመለከተም ሁለተኛ ተጠሪ ቤቱን ለመሸጥ የሚያበቃ ውክልና መስጠታቸውን አልካዱም፡፡ አንደኛ ተጠሪ የሽያጩን ውል ያደረጉት የሿሚውን ጥቅም በሚጐዳና የጥቅም ግጭት (conflict of interest) ባለበት ሁኔታ ነው ወይንም ደግሞ ውሉን ያደረጉት ከእራሳቸው ጋር ነው የሚሉ ከሆነ አግባብነት ያላቸውን የውክልና ድንጋጌዎችን በመጥቀስ ውሉ እንዲፈርስ መጠየቅ ይገባቸው ነበር፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ የውል ይፍረስልኝ ክስ ያላቀረቡ ሲሆን ይልቁንም በቤቱ ላይ የእግድ ትእዛዝ ሲሰጥ እግዱ እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረቡት ሁለተኛ ተጠሪ ሳይሆኑ ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ መሆናቸው ሲታይ 2ኛ ተጠሪ ቤቱን በሽያጭ ማስተላለፋቸውን ይበልጥ የሚያረጋግጥ ነው፡፡

የቤት ሽያጭ ውሉ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ውጤት የሌለው ነው በማለት ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክን በተመለከተ ይህ ጉዳይ በጭብጥነት ተይዞ ሊታይ ይችል የነበረው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1808/2/ ላይ እንደተመለከተው በተዋዋይ ወገኖች ወይንም ጥቅም ባላቸው ሦስተኛ ወገኖች የውል ይፍረስልኝ ክስ በቀረበ ጊዜ ነው፡፡ ነገር ግን በዚህ መልኩ የቀረበ አቤቱታ ስለሌለ የሚስተናገድ አይሆንም፡፡

ሲጠቃለልም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት ባለሐብትነቱ በሽያጭ ውሉ መሰረት የአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ለሆኑት ወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ የተላለፈ ስለሆነና በዚህ የሽያጭ ውልም ላይ ተመስርቶ አመልካች በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3041 እና 3044 መሰረት ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ያለው ሆኖ ሳለ የስር ፍ/ቤቶች የቤቱ ባለሐብትነት በሁለተኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የሚመለከተው አካል ያረጋገጠ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚህ ቤት ላይ ሊቀጥል አይችልም ሲሉ የደረሱበት ድምዳሜ የሽያጩን ውሉንም ሆነ ሕጉን ያላገናዘበና መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 45991 በ27/11/99 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌደራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 59710 በ9/8/2000 ዓ.ም የሰጠው ፍርድ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ.348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡

2. በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 7 ቀበሌ 17 ክልል የሚገኘውና ቁጥር 020 የሆነው ቤት ለአንደኛ ተጠሪ ባለቤት ለወ/ሮ ፀሐይ ጉልማ በሽያጭ በመተላለፉ ምክንያት አመልካች በቤቱ ላይ ከፍርድ የመነጨ የመያዣ መብት ያቋቋመ ስለሆነ አፈጻጸሙ በዚሁ ቤት ላይ እንዲቀጥል ብለናል፡፡
3. አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች እያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ ብር) በድምሩ ብር 2000(ሁለት ሺህ) ወጭና ኪሣራ ለአመልካች እንዲከፍሉ ብለናል፡፡
4. መዝገቡ ተዘገቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ 39778

ሀምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሰ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ሕብረት ባንክ(አ.ማ) - አልቀረቡም

**ተጠሪ፡-** አቢሲኒያ ባንክ (አ.ማ) - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 55790 ታህሣሥ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35179 ሀምሌ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በማቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ተጠሪ አመልካች ጣልቃ ገብ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ ተጠሪ በሥር ፍርድ ቤት በአመልካችነት ቀርቦ ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የተባለ የንግድ ድርጅት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በሥር አመልካች ከሆነው ከአቢሲኒያ ባንክ ገንዘብ ተበድሯል፡፡ ተበዳሪው የንግድ ድርጅት ለወሰደው ብድር በአዲስ አበባ ከተማ በቀድሞ ወረዳ 8 ቀበሌ 05 የሚገኘውን ቁጥሩ 343 የሆነውን ቤትና ድርጅት ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአንደኛ ደረጃ መያዣነት፣ ለአቢሲኒያ ባንክ በሁለተኛ ደረጃ መያዣነት አስይዟል፡፡ ሆኖም የአቢሲኒያ ባንክ በሁለተኛ ደረጃ በንብረቱ ላይ ያለውን የመያዣ መብትና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3081 ንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገውን በመፃረር የጉለሌ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት ንብረቱ የህብረት ባንክ አንደኛ ደረጃ እንደሆነ በማድረግ የመዘገበ ስለሆነ ይኸ ምዝገባ ተሠርዞ ንብረቱ የአቢሲኒያ ባንክ አንደኛ ደረጃ መያዣ ነው ተብሎ እንዲወሰንልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

በዚህ ክርክር ተሣታፊ ያልሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ የመሬት ልማትና አስተዳደር ጽ/ቤት በተጠሪነት ቀርቦ ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር የማይንቀሣቀሥ ንብረት የሕብረት ባንክ አንደኛ መያዣ መሆኑን የመዘገብኩት ሕብረት ባንክ የንግድ ድርጅቱ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር በመክፈል የንብረቱን የባለቤትነት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ በመረከብና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን አስፈቅዶ በመቅረቡ ነው፡፡ ስለዚህ የመያዣ ቀዳሚነት አስመልክቶ ለቀረበው ክርክር ሕብረት ባንክ (አ.ማ) ጣልቃገብቶ እንዲከራከር በማለት አመልክቷል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የሰበር አመልካች በጉዳዩ ጣልቃ ገብ ሆኖ በክርክሩ እንዲገባ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ለሥር ፍርድ ቤት ባቀረበው መልስ በንብረቱ ላይ የመያዣ ቀዳሚነት አለኝ፡፡ ምክንያቱም በባለዕዳው ጠያቂነት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተበደሩትን ብድር በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተይዘው የነበሩ ሰነዶች ተቀብያለሁ፡፡ ስለሆነም በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የተዳረኩ (የተተካሁ) በመሆኔ በንብረቱ ላይ አንደኛ ደረጃ መያዣ እንዳለኝ መመዝገቡ ትክክል ነው በማለት ተከራክሯል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ አመልካች በመሆን ያቀረበውን አቤቱታና ማስረጃ በሥር ተጠሪ የሆነው የጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር እና አመልካች በጣልቃ ግብ ተከራካሪነት ያቀረበውን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካች በንብረቱ ላይ የአንደኛ ደረጃ መያዣ መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ በመክፈልና በማስፈቀድ በዳረጎት መብቱን ያረጋገጠ ስለሆነ በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት አለው በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኝ አቅርቦ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካችን ክርክር ከሰማ በኋላ አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመዳረግ ቀድሞውንም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት ያለው መሆን ይገባዋል፡፡ አመልካች ከዚህ በፊት በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት የሌለው በመሆኑ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ የከፈለ ቢሆንም በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት የለውም በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ሽሮታል፡፡ አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ይግባኝ ሰሚ ችሎቱ ይግባኙን በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች ነሐሴ 2 ቀን 2000 ዓ.ም ባቀረበው የሰበር አቤቱታ አመልካች ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ህዳር 6 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን የብድር ዕዳ ብር 11862768.72 /አስራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሣንቲም/ በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንድንተካ በጠየቀን መሠረት ክፍያውን በሲፒኦ ቁጥር 046293 ፈፅሟል ገንዘቡ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ የተከፈለ መሆኑ በመያዥያውን ንብረት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተረክቧል፡፡ አመልካች በመያዣው ላይ የቀዳሚነት መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ በመክፈል በመብቱ የተዳረገ ሆኖ እያለ በባለ ዕዳውና በአመልካች መካከል የተደረገው የብድር ውል ገንዘቡ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ዕዳ ለመክፈል የሚውል ስለመሆኑ አይገልፅም በሚል ምክንያት ብቻ የመዳረግና በመያዣው ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት የላቸውም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ፍትሐብሔር ሕጉ ስለመዳረግና ስለመተካት የተደነገጉትን ድንጋጌዎች ያላገናዘበና መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪ በበኩሉ አመልካች ለባለዕዳው ብድር የሰጠው ለሥራ ማስኬጃ ማከናወኛ እንጅ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዕዳ ለመክፈል አለመሆኑን በአመልካችና በተበዳሪው መካከል የተደረገው ውል ያሣያል፡፡ አመልካች የቆረጠው ሲፒኦ ገንዘቡ ለተበዳሪው እንጅ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕውን ዕዳ የከፈለ መሆኑን የሚያሣይ ደረሰኝ አላቀረበም፡፡ አመልካች በባለዕዳው ፈቃድ ለመዳረግ የሚያስችሉ እነዚህን መስፈርቶች ባላሟላበት ሁኔታ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እግር ተዳርጌአለሁ በማለት የሚያቀርበው የህግ መሠረት የለውም፡፡ አመልካች በንብረቱ ላይ አንዳችም የመያዣ መብት ሣይኖረው በንብረቱ ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ያለውን ተጠሪ በመቅደም በንብረቱ ላይ የመያዣ መብት አለኝ እያለ የሚያቀርበው ክርክርም የህግ መሠረት የለውም፡፡ ስለሆነም ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት የህግ ትርጉም ምንም አይነት ስህተት የሌለበት በመሆኑ የአመልካችን አቤቱታ በመሠረዝ እንዲያሰናብተኝ በማለት በፅሑፍ መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች በበኩሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለባለዕዳው የሚፈልገውን ዕዳ በሙሉ አጠቃልዬ የከፈልኩ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ሰጥቶኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕዳውን ንብረት በቀዳሚነት በመያዣነት ሲይዝ የተረከባቸውን የንብረቱን ባለቤትነት የሚያረጋግጡ ሰነዶች ለእኛ አስረክቦናል፡፡ እኛም በንብረቶች ላይ አንደኛ የመያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመዳረግ መያዣውን አስመዝግበናል፡፡ ስለሆነም ከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት በመሆኑ በሰበር እንዲታረምልን በማለት በፅሑፍ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የተደረገው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመዳረግ የባለዕዳውን ንብረቶች በመጀመሪያ ደረጃ መያዣነት የመያዝ መብት አለው ወይስ የለውም? የሚለው የጉዳዩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ በአማርኛ ቋንቋ “መዳረግ” የምንለው እና በእንግሊዘኛ ቋንቋ “subrogation” በመባል የሚገለፀው ፅንሰ ሀሳብ ትርጉም ይዘትና ውጤት መመርመር ያስፈልጋል፡፡ መዳረግ ወይም በእንግሊዘኛ “subrogation” የሚለው ፅንሰ ሀሳብ “The substitution of one person in the place of another with reference to lawful claim, demand or right, so that he who is substituted succeeds to the rights of the

other in relation to debt or claim, and its rights, remedies, or securities" የሚል ትርጓሜ ያለው መሆኑን ለመረዳት እንችላለን፡፡ በአጭር አገላለፅ ዳርጎት ወይም subrogation "The right of one who has paid an obligation which another should have paid to be indemnified by another" የሚል ትርጉምና ይዘት ያለው መሆኑን ለፅንሰ ሀሳቡ በህግ መዝገበ ቃላት የተሰጠውን ትርጓሜ በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር አበዳሪው ከባለዕዳው የሚጠይቀውን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል የከፈለ ሶስተኛ ወገን በከፈለው ዕዳ ልክ በዋናው አበዳሪ በመተካት አበዳሪው በባለዕዳው ላይ ያሉትን ልዩ መብቶች በዋስትናዎችና ሌሎች ተጨማሪ መብቶች ሊሠራባቸው የሚቻልበትን ሁኔታ "መዳረግ" በሚል መንገድ የሚገለፅ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ አንድ ሶስተኛ ወገን አበዳሪው ከተበዳሪው የሚፈልገውን ዕዳ በመክፈል በአበዳሪው እግር የመዳረግ መብት የሚኖረው ዳረጎቱ በአበዳሪው የተፈቀደ ሲሆን ወይም በተበዳሪው የተፈቀደ ሲሆን ወይም በህግ የተፈቀደ ሲሆን እንደሆነ በዚህ ዙሪያ የተደረጉ የሥነ-ህግ ጥናቶች ይገልፃሉ፡፡ የመዳረግ መብት ምንጩና መሠረቱ የአበዳሪው ፈቃድ ወይም የተበዳሪው ፈቃድ ወይም ህግ ሊሆን እንደሚችል ለመገንዘብ ይቻላል፡፡

በአገራችንም የባለዕዳውን ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው መብት ለመዳረግ የሚቻልባቸው ሁኔታዎችና መዳረጉ ስለሚያስከትለው ውጤት ገዥነት ያላቸው ድንጋጌዎች ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 እስከ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1974 በዝርዝር ተደንግጓል፡፡ የፍትሐብሔር ህጉ የባለዕዳውን ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው ፈቃድ ስለሚዳረግበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1968፣ በተበዳሪው ፈቃድ ስለሚዳረግበት ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1970 በህግ መዳረግ የሚቻልበትን ሁኔታ በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1971 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የተበዳሪው ዕዳ ለአበዳሪው የከፈለ ሶስተኛ ወገን በአበዳሪው መብት ለመተካትና ለመዳረግ የሚቻለው ከሶስቱ የዳረጎት አይነቶች አንደኛው የተሟላ ሆኖ ሲገኝ እንደሆነና ሶስቱ የዳረጎት አይነቶች የሚጠይቁት መስፈርት የተለያየ መሆኑን ከላይ የጠቀስናቸውን የህግ ድንጋጌዎች ይዘት በማየት ለመረዳት ይቻላል፡፡

አመልካች ባለዕዳው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የነበረበትን ዕዳ እንድንከፍልለት በፅሑፍ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ባለዕዳም ስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚፈለግበትን ብር 11862768.72 /አስራ አንድ ሚሊዮን ስምንት መቶ ስልሣ ሁለት ሺ ሰባት መቶ ስልሣ ስምንት ብር ከሰባ ሁለት ሣንቲም/ በሲፒኦ የከፈለ መሆኑን ይህም በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በሰጠው ማስረጃ የተረጋገጠ መሆኑን በማንሣት ተከራክሯል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባገኘው ፈቃድ መሠረት በመብቱ የተዳረገ መሆኑንና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመብቱ ለመዳረግ የሚያስችለውን በመያዣነት የያዛቸውን የባለዕዳውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ አሳልፎ በመስጠት በንብረቶቹ ላይ ያለውን የቀዳሚነት የመያዣ መብት እንዲሠራበት እንዳደረገው በመግለፅ የተከራከረ መሆኑን ለበታች ፍርድ ቤቶች እና በሰበር ከተደረገው ክርክር ተገንዝበናል፡፡

አመልካች በባለዕዳው ንብረቶች ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ባለው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምትክ የመዳረግ መብቴን አረጋግጫለሁ የሚለው በባለዕዳው በስማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ፈቃድና ስምምነት መሠረት ሣይሆን በአበዳሪው በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፍቃድና ስምምነት መሠረት መሆኑን በመግለፅ በየደረጃው ተከራክሯል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ይህንን የአመልካች ክርክር በጭብጥነት በመያዝ ውሣኔ የሰጠ ሲሆን የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች የመዳረግ መብቴ ምንጭ ነው ብሎ ያልጠቀሰውን በተበዳሪው ፈቃድና ስምምነት ስለመዳረግ ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 የተደነገጉት ሁኔታዎች አልተሟሉም በማለት ውሣኔ መስጠታቸውን ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ከዚህ አንፃር ስንመዝነው የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አመልካች በአበዳሪው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድ የመዳረግ መብቴን አረጋግጫለሁ በማለት ያቀረበውን ክርክር በማለፍ አመልካች የመዳረግ መብቴ ምንጭና መሠረት ነው ብሎ ባልተከራከረበት በባለዕዳው ፈቃድ ስለመዳረግ የሚደነግጉትን የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1969 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ተገቢ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

2. አመልካች በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ላለው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የባለዕዳውን ዕዳ በመክፈል በአበዳሪው ፈቃድ ተዳርጌአለሁ የሚለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመብቱ እንድዳረግ ፈቅዶልኛል በማለት ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት ተዳርጓል ወይስ አልተዳረገም? የሚለው ነጥብ በዝርዝር መታየት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ አግባብነት ያላቸውን የህግ ድንጋጌዎች

አቀራረፅና ይዘት መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡ "ባለገንዘቡ ስለሚሰጠው ዳረጎት" በሚል ርዕስ የተደነገገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 1 "ሶስተኛ ወገን የከፈለውን ገንዘብ ባለገንዘቡ የተቀበለ እንደሆነ በራሱ መብቶች ተደራጊ ሊያደርገው ይችላል" በማለት በአበዳሪው ፈቃድና ስምምነት የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን ለመዳረግ የሚቻል መሆኑን የሚደነግግ ሲሆን የዚሁ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 2 "የዳረጎቱ ጉዳይ ግልፅ መሆንና የገንዘቡ መከፈል እንደተደረገ መፈፀም ይገባዋል" በማለት ይደነግጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 የእንግሊዘኛው ቅጅ ስንመለከት "subrogation shall be express and effected at the time of payment" በማለት ይደነግጋል፡፡

የመዳረጉ ሁኔታ እንዴት መፈፀም እንዳለበት የሚደነግገው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 የአማርኛው ቅጅም ሆነ የእንግሊዘኛው ቅጅ የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን አበዳሪውን በመዳረግ መብቱን እንዲሠራበት የተስማማ መሆኑን ግልፅ በሚያደርግ መንገድ ዳረጎቱ መፈፀም እንዳለበትና የመዳረግ ሁኔታው ክፍያው በተፈፀመበት ጊዜ መከናወን እንዳለበት የሚገልፁ ናቸው፡፡ እዚህ ላይ አበዳሪው የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ ሶስተኛ ወገን በእሱ መብት ተዳርጎ እንዲሠራበት መሥማማቱን በግልፅ ለማሣየት የሚቻለው እንዴት ነው? የሚለው ጥያቄ ምላሽ ሊሰጠው ይገባል፡፡ የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1968 ንዑስ አንቀፅ 2 በመስፈርትነት ያስቀመጠው የተበዳሪውን ዕዳ የከፈለው ሶስተኛ ወገን በመብቱ ተዳርጎ እንዲሠራበት አበዳሪው የተስማማ መሆኑን ለባለዕዳው እና ለሌሎች ወገኖች በግልፅ በሚያሣይ ሁኔታ ፈቃዱን መስጠቱን እንጅ አበዳሪው የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለው ሶስተኛ ወገን እንዲዳረግ የተስማማ መሆኑን በሚገልፅ ልዩ ፎርማሊቲ ባለው ፅሑፍ ወይም ስለመዳረግ በተደረገ ውል የመግለፅ ግዴታ እንዳለበት የሚደነግግ ድንጋጌ አይደለም፡፡ ስለሆነም አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ለመዳረግ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመልካች በመብቱ እንዲዳረግ ፈቃድና ስምምነቱን የሰጠ መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለማሣየት የሚችሉ የፅሑፍ ማረጋገጫዎችን ወይም የተለያዩ ተግባራትን የፈፀመ መሆኑን ማስረዳት ይጠበቅበታል፡፡ ከዚህ አንፃር የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባለዕዳው የነበረበት ዕዳ በአመልካች የተከፈለው መሆኑን በመግለፅ የሰጠው ማስረጃና በመያዣነት ይዟቸው የነበሩ የባለዕዳውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ለአመልካች አሳልፎ መስጠቱ አመልካች መያዣውን በእሱ እግር ተተክቶ (ተዳርጎ) በቀዳሚነት እንዲያስመዘግብ የተስማማ መሆኑን በግልፅ የሚያሣዩ ናቸው፡፡

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አመልካች የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለ መሆኑን በማረጋገጥ በመያዣ የያዛቸውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ለአመልካች አሳልፎ መስጠቱ አበዳሪው ዕዳውን የከፈለው ሶስተኛ ወገን በመዳረግ መብቱ ሊሠራበት እንዲችል በመያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ እና ሌሎች ማስረጃዎች አሳልፎ የመስጠት ግዴታውን በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1974 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የተወጣ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቂ ማስረጃ ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች የባለዕዳውን ዕዳ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመክፈል በአበዳሪው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት በባለዕዳው ንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ባለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ተዳርጓል በማለት የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ በተበዳሪው ፈቃድ ስለመዳረግ የሚደነግጉትንና ለጉዳዩ አግባብነት የሌላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1969 እና የፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 1970 የተደነገገው መሥፈርት አልተሟላም በማለት የከፍተኛው ፍርድ ቤት መሻሩና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ ማፅናቱ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. ተጠሪ በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ያለው መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ተጠሪ አመልካች ከዚህ በፊት በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ምንም አይነት የመያዣ መብት የሌለው በመሆኑ በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ከእኔ የሚቀድም የአንደኛ ደረጃ የመያዣ መብት ሊኖረው አይችልም በማለት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 በመጥቀስ ተከራክሯል የተጠሪ ክርክር የህግ ድጋፍ ያለው መሆኑን ለመመርመር የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 አቀራረፅ ይዘትና ተፈፃሚነት በትኩረት ማየት ያስፈልጋል፡፡ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 "ስለ መተካት" የሚል ርዕስ ያለው ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ንዑስ አንቀፅ 1 ማንኛውም የማይንቀሣቀሥ ንብረት መያዣ መብት ያለው ገንዘብ ጠያቂ ከርሱ በፊት ቀደምትነት ያለውን ገንዘብ ጠያቂ አስፈቅዶ የቀደምትነቱ ተራ መውሰድ ይችላል፡፡ በተራ ተከታይ የሆነው ገንዘብ ጠያቂ ባደረገው ጥያቄ መሠረት የመያዣ መብት የተሰጠበትን የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ እንዲያዝ አድርጎ እንደሆነ ግን ከርሱ በፊት የነበረውን ገንዘብ ጠያቂ ማስፈቀድ አስፈላጊው አይደለም በማለት ይደነግጋል፡፡

የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛው ቅጅ "Any mortgage may pay a creditor having the priority with the consent of the creditor, or where the immovable attached on the cotter's request with out such

consent" የሚል ነው፡፡ድንጋጌ በይዘቱ ሁለት ገዥ የሆኑ የተለያዩ ደንቦችን የያዘ ነው፡፡ የመጀመሪያው ድንጋጌው በመሠረታዊነት ባለዕዳው ንብረት በቀዳሚነት መያዣ ያደረገው አበዳሪ የባለዕዳውን ዕዳ የከፈለውን ሶስተኛ ወገን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 መሠረት የመዳረግ መብት ሙሉ በሙሉ የሚከላከል ወይም የሚገድብ አይደለም፡፡ ተጠሪ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከባለዕዳው የሚፈልገውን ገንዘብ በመክፈል በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ሊኖረው የሚችለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ይህንን ጥያቄውን ሲቀበለውና ሲፈቅድለት ነው፡፡ ስለሆነም ከባለዕዳው የሚፈልገውን ገንዘብ ከሌላ ሶስተኛ ወገን በመቀበል ክፍያውን የፈፀመው ሶስተኛ ወገን አመልካች በመብቱ እንዲዳረግ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1968 የመፍቀድ ወይም በንብረቶቹ ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ካለው ተጠሪ ያበደረውን ገንዘብ በመቀበል ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት እንዲኖረው የመስማማትና የመምረጫ መብቱ የተሰጠው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መሆኑን ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 የመጀመሪያው ክፍል ገዥ ደንብ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው ከእሱ የቀዳሚነት መብት ያለውን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ሣይጠይቅ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ በመክፈል ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ሊኖረው የሚችለው ተጠሪ ንብረቶቹን በፍርድ ያሣገደ ስለመሆኑ ማስረጃ ሲያቀረብ ብቻ እንደሆነ ከፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ሁለተኛው ክፍል ገዥ ደንብ ለመረዳት ይቻላል፡፡ ተጠሪ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀዳሚ መያዣነት የያዛቸውን ንብረቶች በፍርድ ያሣገደ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ያላቀረበ መሆኑ ያለ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመተካትና በመብቱ ተዳርጎ ሊሠራበት አይችልም፡፡ ስለሆነም ምርጫውን ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የሚሰጠውንና ፈቃጅ የሆነውን ፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ እንደ አስገዳጅ የህግ ድንጋጌ በመቁጠር ተጠሪ የቀዳሚነት መብት እንዲሰጠው የሚያቀርበው ክርክር የህግ መሠረትና ድጋፍ ያለው ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ተጠሪ የባለዕዳውን ንብረት በቀዳሚ መያዣነት ለመያዝ በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት ማግኘት አለበት፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ዕዳ አጠቃልሎ የከፈለ መሆን እንደሚገባው ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡ ተጠሪ አመልካች ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ ከመክፈሉ በፊት የባለዕዳውን ዕዳ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አጠቃልሎ በመክፈል በፍትሐብሔር ህግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ለመዳረግ ያቀረበው ጥያቄ የለም፡፡ ተጠሪ የባለዕዳውን ዕዳ አጠቃልሎ በመክፈል መብቱ ለመዳረግ ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጥያቄ ሣያቀርብና ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሊከፍል የሚገባውን ገንዘብ ሣይከፍል በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት ስላለው ብቻ በንብረቶቹ ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሊረጋገጥልኝ ይገባል በማለት የሚያቀርበው ክርክር የህጉን ድንጋጌ መሠረታዊ አቀራረፅ፣ ይዘት መንፈስና ዓላማ እና የድንጋጌውን ተፈፃሚነት ከግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና የህግ መሠረት የሌለው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

4. ከላይ ከሰጠናቸው የህግ ምክንያቶች በተጨማሪ አመልካች ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መክፈል የሚገባውን ገንዘብ አጠቃልሎ በመክፈል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መብት መዳረጉ ተጠሪ በአበዳሪው ንብረቶች ላይ ያለውን የሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት የሚነካ ወይም የሚያጣብብ አይደለም፡፡ ተጠሪ የባለዕዳውን ንብረቶች በሁለተኛ ደረጃ መያዣነት ለመያዝ ያደረገው ስምምነት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአመልካች በድርጎ በመተካቱ ምክንያት ብቻ የሚጣበብ ወይም የሚነካ አይደለም፡፡ ተጠሪ ባለዕዳው ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ያለበትን ዕዳ በሙሉ ወይም በከፊል ከሌሎች የገቢ ምንጮች በመክፈል ሆነ ብሎ አመልካች በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት እንዲኖረው ለማድረግ አመልካችና ከአበዳሪው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር በመመሳጠር ተግባር የፈፀመ መሆኑን አላስረዳም፡፡ በመዝገቡ የተደረገው ክርክርና ማስረጃዎች የሚያሣዩት ባለዳው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር በውሉ መሠረት ለመክፈል ባለመቻሉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በቀዳሚ መያዣነት የያዛቸውን የአበዳሪውን ንብረቶች በመሸጥ ዕዳውን ለማስከፈል በመንቀሣቀስ ላይ እያለ አመልካች ዕዳውን አጠቃልሎ የከፈለና ይህንኑ የሚያረጋግጥ ማስረጃም በመያዣነት የተያዙ የባለዕዳው ንብረቶች የባለቤትነት ሰነድ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መቀበል በአበዳሪው መብት ተዳርጎ የሠራበትና በንብረቶቹ ላይ ያለውን ቀዳሚ የመያዣ መብት በሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ያስመዘገበ መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪ ባለዕዳው ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የወሰደውን ብድር ባለመክፈሉ በንብረቶቹ ላይ የቀዳሚ የመያዣ መብት ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መያዣውን ለመሸጥ ሲንቀሣቀሥ ከባለዕዳው የሚፈለገውን ገንዘብ አጠቃልሎ ለመክፈል ሣይጠይቅና ክፍያ ሣይፈፅም

በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ መብት ለመዳረግ ያቀረበው ክርክር የህግ ድጋፍና ምክንያት የሌለው ነው፡፡ ተጠሪ በንብረቶቹ ላይ ያለው ሁለተኛ ደረጃ የመያዣ መብት አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ምትክ በመዳረጉ ምክንያት አልተሸራረፈም፡፡

በአጠቃላይ አመልካች በባለዕዳው ንብረቶች ላይ ቀዳሚ የመያዣ መብት ያለው የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከባለዕዳው የሚጠይቀውን ገንዘብ አጠቃልሎ በመክፈል በባለገንዘቡ (አበዳሪው) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ፈቃድና ስምምነት መሠረት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1968 ድንጋጌዎች መሠረት ተዳርጓል፡፡ አመልካች በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመተካት ንብረቶቹን በአንደኛ ደረጃ መያዣነት ለማስመዝገብ የሚያስፈልጉ የባለዕዳው ንብረት ሰነዶችና ማስረጃዎች የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1974 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመረከብ ንብረቶቹን በቀዳሚ መያዣነት አስመዝግቧል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ለጉዳዩ አግባብነትና ተፈፃሚነት የሌላቸውን የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1969 የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1970 እና የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 3083 ድንጋጌዎች በመጥቀስ አመልካች የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን የመዳረግ መብት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከመዝገብ ቁጥር 55790 የሰጠው ውሣኔና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 35179 የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 74358 መጋቢት 26 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ ፀንቷል፡፡
3. አመልካች የባለዕዳው የሰማቸው ደምሴ ኢንቨስትመንት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በአንደኛ ደረጃ መያዣነት አሲዟቸው በነበሩ ንብረቶች ላይ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን በመዳረግ ቀዳሚ የመያዣ መብት አለው ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል

   ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ

የሰ/መ/ቁ 41116

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሒሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ፍሊነሰቶን ኢንጂነሪንግ - ጠበቃ ብሥራት ሐመልማል - ቀረቡ፡፡

**ተጠሪ**፡- እነ ወ/ት ሃና ተስፋዬ /6 ሰዎች/ - ጠበቃ ኮ/መላኩ ካሰኝ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ለሰበር አቤቱታ መነሻ የሆነው ጉዳይ የጀመረው በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በዚሁ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ከሳሾች የነበሩ ሲሆን አመልካች ሁለተኛ ተከሣሽ ነበረ፡፡ ተጠሪዎቹ ለፍ/ቤቱ ባቀረቡት ክስ አንደኛ ተከሣሽ ወ/ሮ ወርቅይጠሩ ሰርፀመድኀን ከመሞታቸው በፊት ለክርክር ምክንያት የሆነውን ቤት በስጦታ ስለሰጡኝ ይጽደቅልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ የተጠሪዎች አባት ተቃውመው የስጦታ ውሉ በፍ/ቤቱ ፈራሽ እንዲሆን ተወስኗል፡፡ ነገር ግን ቤቱን አንደኛ ተከሣሽ ለአመልካች የሸጡ በመሆኑ ተከሣሾች ቤቱን እንዲያስረክቡና ቤቱን በቁጥጥራቸው ሥር ካዋሉበት ጊዜ ጀምሮ ተከራይቶ የተገኘው ገቢ ብር 201,000 /ሁለት መቶ አንድ ሺህ/ ይክፈሉ በማለት ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ መርምሮ ለአንደኛ ተከሣሽ በቤቱ ላይ መብት ሰጥቷቸው የነበረው የስጦታ ውል የፈረሰ በመሆኑ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በቤቱ ላይ ከመነሻው ጀምሮ የባለቤትነት መብት የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ አመልካችም ቤቱን የገዛው መብት ከሌለው ሰው ላይ በመሆኑ የሽያጭ ውሉ ለአመልካች ባለቤትነት የማስተላለፍ ውጤት ያለው ሕጋዊ ድርጊት አይደለም፡፡ አመልካች በሽያጭ ውሉ መሠረት ከአስተዳደር አካል የተሰጠው የቤት ባለቤትነት ሰነድ የሚያጎናጽፈው የባለንብረትነት የሕግ ግምት ሰነዱ የተገኘው ሕጋዊ ውጤት በሌለው ውል ላይ ተመስርቶ በመሆኑ ፈራሽ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ያስረክብ፤ ካሣውን የመክፈል ግዴታ ግን የለበትም፡፡ በሌላ በኩል የሥር አንደኛ ተከሣሽ የስጦታ ውሉ ላይ ክርክር መነሳቱን አውቀው መልስ ከሰጡ ቀን ጀምሮ ክስ እስከቀረበበት ጊዜ ያለውን በወር ብር 500 /አምስት መቶ/ እየታሰበ ከወለድ ጋር ይክፈሉ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ለፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ያቀረበ ቢሆንም ፍ/ቤቱ የስር ውሣኔ አጽንቶታል፡፡

የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ ይህ ችሎትም አመልካች ቤቱን እንዲመልስ የተሰጠው ውሣኔ አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበዋል፡፡ ችሎቱም የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች አንፃር እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚሁ መሠረት በዚህ ችሎት ሊመለስ የሚገባው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤትን አስመልክቶ የተሰጠው የስጦታ ውል በመፍረሱ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች ሊመልሱ ይገደዳሉ ወይ? የሚለው ጭብጥ ነው፡፡

ከክርክሩ ሂደት ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ወ/ሮ ወርቅይጥሩ ሰርፀመድኀን ለሥር አንደኛ ተከሣሽ በ28/02/1993 በተፃፈ የስጦታ ውል ሰጥተው የነበረ መሆኑን፤ የሥር አንደኛ ተከሣሽ በ16/04/1994 በስማቸው የቤት የባለቤትነት ማስረጃ ተሰጥቷቸው የነበረ መሆኑን፤ በ28/08/1998 በአዋዋይ ፊት በተደረገ የሽያጭ ውል ለአመልካች

መሸጡና አመልካችም የቤት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን፤ ቤቱ ለአመልካች ከተሸጠ በኋላ የስጦታ ውሉ ክርክር ቀርቦበት ስለነበር በ25/02/1997 ዓ.ም. ፈራሽ ነው ተብሎ መወሰኑን ተገንዝበናል፡፡

ከላይ እንደተመለከተው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው የሥር አንደኛ ተከሣሽን ባለቤት አድርጓቸው የነበረው የስጦታ ውል መፍረስ ነው፡፡ ስጦታ ከውል አይነቶች አንዱ ነው፡፡ የስጦታ ውል ካለው የራሱ የሆነ ባሕሪ አኳያም የስጦታ ውል ግንኙነትን የሚገዙ የተለያዩ የሕግ ድንጋጌዎች በፍ/ብሔር ሕጋችን ተካተው ይገኛሉ፡፡ ምንም እንኳን የስጦታ ውል በእነዚህ የተለያዩ ድንጋጌዎች የሚዳኝ ቢሆንም ስጦታን የሚመለከቱት እነዚህ ድንጋጌዎች የማይሸፍኗቸው ጉዳዮች ሲገጥሙ ስለ ውሎች በጠቅላላ የተመለከቱት ደንቦች ተፈፃሚ ይሆናሉ /የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1676(1) ይመለከቷል/፡፡ ስጦታን የሚመለከቱ የሕጉ ድንጋጌዎችም የስጦታ ውል ፈራሽ የሚሆንባቸው የተለያዩ ምክንያቶችን የሚዘረዝሩ ቢሆንም የስጦታ ውል ሲፈርስ ምን ውጤት ሊያስከትል እንደሚችል የሚገልጽ ድንጋጌ ግን አላካተቱም፡፡ ስለዚህ የስጦታ ውል መፍረስ የማያስከትለውን ውጤት በተመለተ ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገባቸው ስለ ውል በጠቅላላው የሚናገሩት ደንቦች ናቸው፡፡ በእነዚህ ደንቦች መሠረት አንድ ውል ሲፈርስ ወይም ሲሰረዝ ተዋዋዮች በተቻለ መጠን ውሉ ከመደረጉ በፊት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ ማድረግ ነው /ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1815/1/ ይመለከቷል፡፡/ የውል መፍረስ ወይም መሰረዝ ውጤቱ ውሉ ከጅምሩ እንዳልተደረገ መቁጠር በመሆኑ ውለታው ለመፈፀም የተሰሩ ሥራዎች ሁሉ ቀሪ ሆነው በማናቸውም አኳኋን ውጤት አይኖራቸውም /ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1815/2//፡፡ አሁን እንዳየነው በመርህ ደረጃ የውል መፍረስ ውጤት ተዋዋዮችን ወደ ነበሩበት ቦታ መመለስ ነው፡፡ በሌላ በኩል ግን ምንም እንኳን ውሉ ቢፈርስ ወይም ቢሰረዝም የተለያዩ ሁኔታዎች ባጋጠሙ ጊዜ ውሉን ተክትለው የተሰሩ ሥራዎችን ቀሪ በማድረግ ተዋዋዮችን ወደነበሩበት ቦታ ከመመለስ ይልቅ እንደረጉ መቆየቱ የተሻለ አማራጭ የሚሆንበት ጊዜ አለ፡፡ ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ሲሆን አለበለዚያም ከፍ ያለ መሰናክል የሚያስከትል ሲሆን የተሰሩ ሥራዎች እንደረጉ እንዲቀሩ ሕጉ ያዛል /ፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1817/1//፡፡ በተመሣሣይ ሁኔታ እነዚህ የተሰሩ ሥራዎች በቅን ልቦና ለተዋዋለ ሦስተኛ ወገን ጠቃሚ ሆነው ከተገኙ የተሰሩ ሥራዎች ሳይፈርሱ እንደረጉ እንዲቆዩ ማድረግ እንደሚገባ ሕጉ ያዛል /ፍ/ብ/ሕ/ቁ 1816/፡፡

ከእነዚህ ድንጋጌዎች አኳያ የተያዘውን ጉዳይ ስንመረምር ከፍ ሲል እንደተመለከትነው ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት ለሥር አንደኛ ተከሣሽ በስጦታ የተሰጣቸው በ28/3/1993 ነው፡፡ ተከሣሹም ይህንን የስጦታ ውል መሠረት አድርገው በ16/04/1996 በቤቱ ላይ የባለቤትነት ማረጋገጫ ሰነድ አግኝተዋል፡፡ የአስተዳደር ክፍል የአንድን ንብረት ባለሃብትነት በማወቅ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት የሰጠው ሰው የንብረት ባለሃብት ሆኖ እንደሚቆጠር ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1195 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በአስተዳደር መስሪያ ቤት ተረጋግጦ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት ከተሰጣቸው ቀን ጀምሮ የሥር አንደኛ ተከሣሽ የቤቱ ባለሃብት ሆነው ይቆጠራሉ ማለት ነው፡፡ ይህንንም ሰነድ ይዘው ነው ቤቱን ለአመልካች በ28/08/1996 የሸጡለት፡፡ አመልካች ቤቱን ሲገዛ የቤቱ ባለቤት የነበሩት የሥር አንደኛ ተከሣሽ ናቸው፤ የሽያጩ ውልም ውል ለማዋዋል ስልጣን በተሰጠው አካል ፊት ተደርጓል፤ ከዛም አልፎ የቤቱ ባለሃብትነት ከሥር አንደኛ ተከሣሽ ወደ አመልካች ተዛውሮ አመልካች ቤቱ የባለቤትነት ምስክር ወረቀት አውጥቶ የቤቱ ባለቤት ሆኗል፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ አመልካች ቤቱን ሲገዛ የስጦታ ውሉ አልፈረሰም፡፡ እንግዲህ አመልካች ቤቱን ሲገዛ ቤቱ የሥር አንደኛ ተከሣሽ ሳይሆን የሌላ ሰው እንደሆነ ሊያውቅ የሚችልበት ምንም አይነት ሁኔታ አልነበረም ብቻ ሳይሆን የቤቱ ባለቤት ተብለው በሕጉ ፊት ይቆጠሩ የነበረው እኚሁ የሥር አንደኛ ተከሣሽ ናቸው፡፡ ከመዝገቡ ላይ የተረጋገጡት ፍሬ ነገሮች ሁሉ አመልካች የቅን ልቦና ተዋዋይ የነበረ መሆኑን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ምንም እንኳን ለሥር አንደኛ ተከሣሽ የተደረገው የስጦታ ውል በመጨረሻ ፈራሽ ቢሆንም የስጦታውን ውል ተከትለው የተሰሩ ሥራዎች ቀሪ ማድረጉና ተዋዋዮቹን ወደነበሩበት ቦታ መመለሱ በቅን ልቦና የተዋዋለውን የአመልካችን መብት በእጅጉ የሚጎዳ በመሆኑ እነዚህ ሥራዎች እንዲረጉ ማድረጉ የተሻለና የሕግ መሠረትም ያለው ነው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍ/ቤቶች ከላይ የተመለከቱትን የሕግ ድንጋጌዎች በአግባቡ ሳያገናዝቡ የስጦታ ውሉ ፈራሽ በመሆኑ ብቻ አመልካች ቤቱን ለተጠሪዎች እንዲመልስ መወሰናቸው መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

# ው ሳ ኔ

1. የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 46947 በ25/02/2000 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ እንዲሁም የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 34278 በ07/02/2001 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ቤቱን ሊያስረክቡ አይገባም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ 39256

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

መንበረፀሐይ ታደሰ

ዓብዱልቃድር መሐመድ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ነገረፈጅ ደረጀ ባዩ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1ኛ. አቶ ሞሣ ነጋሽ አልቀረቡም

2ኛ. ጣና ትራንስፖርት ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር

ጠበቃ አቶ አምሣለፀሐይ - ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካች ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም በፅሑፍ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62713 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38688 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት በማመልከቱ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በከፍተኛው ፍርድ ቤት አንደኛ ተጠሪ ሁለተኛው ተጠሪ በፍርድ የተወሰነበትን ብር 2,957,935.30 /ሁለት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሃምሣ ሰባት ሺ ዘጠኝ መቶ ሰላሣ አምስት ብር ከሰላሣ ሣንቲም/ ከህጋዊ ወለድ ጋር እንዲከፍል የአፈፃፀም ትዕዛት ይሰጥልኝ በማለት ጠይቋል፡፡ የከፍተኛው ፍርድ ቤትም በአንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ያቀረበውን ክርክር ከመረመረ በኋላ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ በሃራጅ ተሸጦ በፍርድ ለተሰወሰነበት ዕዳ መክፈያ እንዲሆን ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በኋላ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በፍርድ ቤት የተጀመረውን የአፈፃፀም ክርክር ከፍርድ ቤት ውጭ በስምምነት ለመጨረስ ተስሣምተዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን ጠቅላላ ዋጋቸው 1,427,150 /አንድ ሚሊዩን አራት መቶ ሃያ ሰባት ሺ አንድ መቶ ሃምሣ ብር/ የሆነ የአክሲዮን ድርሻዎች በዕዳ መክፈያነት በአንደኛ ተጠሪ እንዲተላለፍ እንደዚሁም ሁለተኛው ተጠሪ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 ከአክሲዮን ድርሻ ያገኘው ዲቪደንድ በዕዳ መክፈያነት ለአንደኛው ተጠሪ እንዲተላለፍ ተስማምተዋል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ ይህንን ስምምነታቸውን ለፍርድ ቤቱ አቅርበዋል፡፡ የአፈፃፀሙን ክርክር የያዘው ፍርድ ቤትም የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በስምምነታቸው መሠረት እንዲፈፀም ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

የአፈፃፀም ክርክሩ በዚህ ሂደት ላይ እያለ አመልካች በክርክሩ ጣልቃ ገብቶ መብቱን ለማስከበር እንዲፈቀድለት አመልክቷል፡፡ አመልካች አንደኛ ተጠሪና ሁለተኛ ተጠሪ ባደረጉት ስምምነት ፍርድ ቤቱ ለሁለተኛው ተጠሪ ዕዳ መክፈያነት እንዲውል ትዕዛዝ የሰጠበት ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻና ሁለተኛ ተጠሪ ከአክሲዮን ድርሻው መሠረት እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር 2006/2007 ዓ.ም የሚከፈለው ዲቪደንድ እና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መብቶች ላይ የቅድሚያ መብት አለኝ፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር

ያለው የአክሲዮን ድርሻ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና ስታር ቢዝነስ ግሩኝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት ይዠዋለሁ። የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የተያዘ መሆኑ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ ውስጥ ተመዝግቧል። የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ሰርተፊኬትም በእጃችን ይገኛል። ስለሆነም ፍርድ ቤቱ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻና ዲቪደንድ ለአንደኛ ተጠሪ ዕዳ መክፈያነት ወደ አንደኛው ተጠሪ እንዲተላለፍ የሰጠውን የአፈፃፀም ትዕዛዝ ይሰርዝልን በማለት አመልክቷል።

አመልካች በአፈፃፀም ክርክሩ ጣልቃ ለመግባት ካቀረበው ማመልከቻ ጋር በማያያዝ የፅሑፍ ማስረጃዎች አቅርቧል። አመልካች ክርክሩን ለማስረዳት ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር እንዲፈቀድለት ላቀረበው ጥያቄ መያዣ ይሆን ዘንድ ሁለተኛ ተጠሪ አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 475,000 (አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር) የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችንና ሌሎች ስምንት ሰዎች በአቢሲኒያ ባንክ ያላቸውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ያቀረበ መሆኑን ገልፆ የፃፈው ደብዳቤ ከነ አባሪው

- አመልካች ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት ብድር ለወሰደው 40,000,000 (አርባ ሚሊዮን ብር) መያዣ እንደሆነ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 475,000 (አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር) የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችንና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻዎች በመያዣነት የያዘ በመሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎቹ አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ እንዲመዘገብለት ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የፃፈው ደብዳቤ፣
- የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር አመልካች ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዛቸው የሁለተኛው ተጠሪና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑ በአክሲዮኖች መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበና ለሶስተኛ ወገን የማይተላለፍ መሆኑን በማረጋገጥ ለአመልካች በአድራሻው የፃፈውንና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች ብር 40,000,000 (አርባ ሚሊዮን ብር) የኦቨር ድራፍት ብድር የወሰደበት የብድር ውልና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት የወሰደውን ብድር ከነ ወለዱ ያልከፈለ መሆኑን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ፣
- አመልካች ስታር ቢዝነስ ግሩኝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ብር 10,000,000 /አስር ሚሊዮን ብር/ በኦቨር ድራፍት ብድር ሲወሰድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ አክሲዮኖች በመያዣነት ያስያዘና መያዣው በመሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ እንዲመዘገብለት ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የፃፈው ደብዳቤ፣
- አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር አመልካች ለእስታር ቢዝነስ ግሩኝ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዛቸው የሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው ዋጋቸው 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎች በመያዣነት የተያዙ መሆኑ በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበ መሆኑንና ለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች እንደማይተላለፉ በማረጋገጥ ለአመልካች በአድራሻው የፃፈውና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- በአመልካች እጅ የሚገኘውን ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬትና አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት መያዙን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ የሚደርሰው ዲቪደንድ ለአመልካች ተከፋይ የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲመቻች ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በአድራሻው የፃፈውና ለሁለተኛው ተጠሪ ግልባጭ የተደረገ ደብዳቤ፣
- አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች አስረኛ መደበኛ ጠቅላላ ስብሰባ የሚካሄድ መሆኑንና ሁለተኛው ተጠሪ ያሉት አርባ ሶስት የአክሲዮን ድርሻዎች በአመልካች በመያዣነት የተያዙ በመሆኑ አመልካች ካልፈቀደለት በስብሰባው ላይ ለመገኘትና ድምፅ ለመስጠት የማይችል መሆኑ በንግድ ሕግ ቁጥር 329/1/ የተደነገገ መሆኑን ገልፆ ሁለተኛው ተጠሪ በስብሰባው ለመገኘትና ድምፅ ለመስጠት ከአመልካች ውክልና ይዞ መቅረብ እንዳለበት ለሁለተኛ ተጠሪ በአድራሻው የፃፈው እና ለአመልካች ግልባጭ ያደረገውን ደብዳቤ፣

- ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውንና ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆነ አርባ ሶስት አክሲዮኖች ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ብድር በዋስትና ያስያዘ መሆኑን በመግለፅ፣ ከባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤና ሌሎች ስብሰባዎች በመካፈል ድምፅ ለመስጠት እንዲፈቅድልንና ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ደብዳቤ እንዲፃፍልን በማለት ለአመልካች የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት አያይዞ አቅርቧል፡፡

የአመልካች ማመልከቻና ማስረጃ ለተጠሪዎች ደርሷቸው ተጠሪዎች በተናጠል የመከላከያ መልስና ማስረጃ አቅርበዋል፡፡ አንደኛ ተጠሪ ባቀረበው የፅሑፍ ክርክር ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር ሲወስድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት አላስያዘም፡፡ አመልካች ከሁለተኛ ተጠሪ ጋር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት የመያዣ ውል ያተዋዋለ መሆኑን የሚያስረዳ የፅሑፍ ማስረጃ አላቀረበም፡፡ አመልካች ከሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ጋር በተለያየ ጊዜ ያደረጋቸው መፃፃፎች በአመልካችና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የመያዣያ ውል አያቋቁሙም፡፡ አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የህጉን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት ያልያዘ መሆኑን በማመን የአመልካች የክሬዲት አገልግሎትና የሕግ አገልግሎት በተፃፃፏቸው ደብዳቤዎች አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻ ላይ የቀዳሚነት መብት አለኝ በማለት ያቀረበው ጥያቄ ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክሯል፡፡

ሁለተኛው ተጠሪ በበኩሉ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማሕበር እና ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት የኦቨር ድራፍት ብድር እኔ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለኝን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለማስያዝ ከአመልካች ጋር ያደረግሁት የመያዣ ውል የለም፡፡ እኔ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለኝን የአክሲዮን ድርሻ አመልካች በመያዣነት እንዲይዝ አልተስማማሁም፡፡ አመልካች ከእኔ ፍላጐትና ፈቃድ ውጭ የኦቨር ድራፍት ብድር ከወሰዱት የንግድ ድርጅቶችና ከአቢሲኒያ ባንክ ጋር በመፃፃፍ የአክሲዮን ድርሻዎቹን በመያዣነት ይዣለሁ በማለት የቀዳሚነት መብት እንዲረጋገጥለት የሚያቀርበው ጥያቄ ተገቢ አይደለም፡፡ በማለት ተከራክሯል፡፡ አንደኛና ሁለተኛ ተጠሪ በተናጠል ያቀረቡትን ክርክር ያስረዳልናል በማለት፡-

- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አንዋር ቅርንጫፍ ምክትል ሥራ አስኪያጅ እና ዋና ሥራ አስኪያጅ የሁለተኛው ተጠሪና የሌሎች ስምንት ሰዎች የአክሲዮን ድርሻ በመያዣ የተያዙበትን አግባብ፣ አስተያየት የተለዋወጡበት የውስጥ ሜሞ
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሕግ አማካሪ ዋና ክፍል ለባንኩ ዋና ሥራ አስኪያጅ የሰጠው የሕግ አስተያየት /የውስጥ መፃፃፊያ ሜሞ/ እና አቢሲኒያ ባንክ አክስሲዮን ማህበር አመልካች በመያዣያ የያዛቸውን፣ የአክሲዮን ድርሻዎች በሚመለከት ከአክሲዮን ባለድርሻዎቹ እያቀረቡ ያሉ ጥያቄዎችን በመግለፅ አመልካች ተገቢውን እንዲፈፅም ለመጠየቅ የፃፈውን ደብዳቤ በማስረጃነት አቅርበዋል፡፡

የሥር ፍርድ ቤት የአመልካችን ማመልከቻና ማስረጃ እንደዚሁም ተጠሪዎች ያቀረቡትን መከላከያና ማስረጃ ከመረመረ በኂላ አመልካች ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የያዘ መሆኑን ለማስረዳት ያቀረባቸው ማስረጃዎች በአመልካችና በተጠሪ መካከል በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2፣ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1725 እና በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 1727 ድንጋጌዎች መሠረት የመያዣ ውል የተደረገ መሆኑን አያስረዱም፡፡ ስለሆነም አመልካች በሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለው የአክሲዮን ድርሻ ላይ የመያዣና የቅድሚያ መብት የለውም በማለት ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ትዕዛዝ ቅር በመሰኘት ይግባኙን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፍታብሔር ችሎት አቅርቧል፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎቱም የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ የሚነቀፍበት ምክንያት የሌለ መሆኑን በግለፅ የአመልካችን ይግባኝ ሰርዞታል፡፡ አመልካች በሥር ፍርድ ቤትና በይግባኝ ሰሚው ችሎት የተሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት ያስያዘ መሆኑን በግልፅ በማመን በባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ለመሣተፍና ድምፅ ለመስጠት የውክልና ደብዳቤ እንዲፃፍለት አመልካችን የጠየቀበት ደብዳቤ በማስረጃነት ቀርቧል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት የተያዘ መሆኑንና በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የመዘገበ መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ

አቅርበናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የሚያረጋግጠው የአክሱዮን ሰርተፊኬት እስካሁን በእጃችን እንደሚገኝ አስረድተናል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት የአክሱዮን ድርሻ በመያዣነት የሚያዙበትን ልዩ ሁኔታ ሣያገናዝብ አግባብነት የሌላቸውን የፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች በመጥቀስና በመተርጐም የሰጠው ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ይግባኝ ሰሚ ችሎትም ይህንን መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበትን የሥር ፍርድ ቤት ትዕዛዝ አፅንቷል፡፡ ስለሆነም ጉዳዩ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

ተጠሪዎች በተናጠል በሰጡት መልስ አመልካች የኦቨር ድራፍት ብድር ሲሰጥ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በዋስትና ለማስያዝ ከአመልካች ጋር አልተዋዋለም፡፡ አመልካች ከሁለተኛው ተጠሪ ጋር በፍታብሔር ሕግ ድንጋጌዎች መሠረት የተዋዋለው የመያዣያ ውል በሌለበት ሁኔታ አመልካች የሚያቀርበው የቀዳሚነት ጥያቄ የሕግ ድጋፍ የለውም፡፡ አመልካች የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬቱን በእጁ ያስገባው ከሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ፍላጐት ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ አመልካች ያቀረባቸው የፅሑፍ ማስረጃዎች በአመልካችና በሁለተኛው ተጠሪ መካከል የመያዣ ውል ያለ መሆኑን ስለማያስረዱ የሥር ፍርድቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም፡፡ ሰበር ችሎት የአመልካችን አቤቱታ ውድቅ ያድርግልን በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

አመልካችና ተጠሪዎች ለሰበር በፅሑፍ ካቀረቡት ክርክር በተጨማሪ ችሎቱ የአመልካች ነገረ ፈጅና የተጠሪዎች ጠበቆች የቃል ክርክር ሰምቷል፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለወሰዱት ኦቨር ድራፍት ብድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የአክሲዮን ድርሻ በንግድ ሕጉ ድንጋጌዎች መሠረት በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ አስመዝግበን ይዘናል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪም ይህንን በማመን የፃፈው ደብዳቤ አለ፡፡ ስለዚህ የሥር ፍርድ ቤት የአክሲዮን ድርሻ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828(2) መሠረት አልተያዘም በማለት የሰጠው የሕግ ትርጉም መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርቧል፡፡

በተናጠል የቃል ክርክራቸውን ያሰሙት የአንደኛና የሁለተኛ ተጠሪ ጠበቆች በበኩላቸው አመልካች ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለማስያዝ ያደረገው ስምምነት የለም፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በባለአክሲዮኖች ስብሰባ ለመካፈል አመልካችን በፅሑፍ የጠየቁበት ደብዳቤ በስህተት የተፃፈ ደብዳቤ ነው፡፡ አመልካችም በስህተት የፃፍነው መሆኑን፣ አውቆ ዋናውን ደብዳቤ መልሶ ለሁለተኛው ተጠሪ ሰጥቶታል፡፡ ስለሆነም የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ የመያዣ ውል ሣይኖር አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ባለው የአክሲዮን ድርሻ ላይ የቀረበውን የቀዳሚነት የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ውድቅ ማድረጋቸው ተገቢ ነው፡፡ ትዕዛዙ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም የሚል ይዘት ያለው ሰፊ የቃል ክርክር አቅርበዋል፡፡

በሥር ፍርድ ቤት አመልካችና ተጠሪዎች ያደረጉት ክርክር የሥር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠው ትዕዛዝና በሰበር አመልካችና ተጠሪዎች በፅሑፍና በቃል ያደረጉት ክርክር በአጭሩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት ለመያዝ የሚደረገው የመያዣ ውል ሌሎች ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ለመያዝ በሚያስፈልገው ፎርማሊቲ መሠረት መፈፀም አለበት ወይ? የሚለው ነጥብ የክርክሩ መሠረታዊ ጭብጥ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

1. ከላይ የተያዘውን ጭብጥ ለመወሰን በመጀመሪያ የፍታብሔር ሕጉ፣ ስለ መያዣያ ውል /ፕሌጅ/ የደነገጋቸውን ድንጋጌዎች ባህሪና የተፈፃሚነት ወሰን፣ በዝርዝር መመርመር ያስፈልጋል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረቶች በመያዣያ ስለሚያዙበት ሁኔታ የመያዣው ውጤትና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2825 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2862 በዝርዝር ደንግጓል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ ግዙፍነት ያላቸውን ተንቀሣቃሽ ንብረቶች ብቻ ሣይሆን የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች እና ሌሎች ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች በመያዣነት ማስያዝ እንደሚቻል ይደነግጋል፡፡ የፍታብሔር ሕጉ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶች /ክሌምስ/ እና ግዙፍ ያልሆኑ ሌሎች ሃብቶች /ኢንታጀብልስ/ በመያዣነት ስለሚያዙበት ሁኔታና መያዣው ስለሚያስከትለው ውጤት ገዥ የሆኑ ልዩ ድንጋጌዎችን ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2863 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2874 ይደነግጋል፡፡

የአክሲዮን ድርሻ አንድ የተፈጥሮ ወይም ሕግ ወለድ ሰው ካፒታሉ አስቀድሞ በታወቀ በአክሲዮን በተከፋፈለና ለዕዳውም ንብረቱ ብቻ ዋስትና በመሆኑ የአክሲዮን ማህበር ውስጥ ያሉትን አክሲዮኖች ብዛትና ዋጋ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ባለ አክሲዮን በአክሲዮን ማህበሩ ውስጥ በባለቤትነት የያዛቸው አክሲዮኖች ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች ናቸው፡፡ በአገራችን ዕውቅና እና ጥበቃ የተሰጣቸው ሁለት አይነት አክሲዮኖች እንዳሉ የንግድ ሕግ ቁጥር 325 ንዑስ አንቀፅ 1 ይደነግጋል፡፡

የመጀመሪያው አይነት አክሲዮን ለአምጭው ተብሎ የተፃፈባቸው አክሲዮኖች ሲሆኑ እነዚህን አክሲዮኖች ለሌላ ሰው ለማስተላለፍም ሆነ በመያዣነት ለመያዝ እንደማንኛውም ተላላፊ የንግድ ወረቀት የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰነዱን አሳልፎ በመስጠት ያለአንዳች አይነት አሰራር /ፎርማሊቲ/ ማከናወን እንደሚቻል የንግድ ሕግ ቁጥር 340 ንዑስ አንቀፅ 1 እና ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2866(2) ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡

ሁለተኛው አይነት አክሲዮን የባለ አክሲዮኑ ስም የተፃፈበት አክሲዮን ነው፡፡ ስም የተፃፈበት አክሲዮን የአክሲዮን ማረጋገጫ ሰነዱን አሳልፎ በመስጠት ብቻ ለማስተላለፍና በመያዣነት ለማስያዝ አይቻልም፡፡ ስም የተፃፈበት አክሲዮን ለማስተላለፍም ሆነ በመያዣነት ለማስያዝ አክሲዮኖቹ ለሌላ ሰው የተላለፉ ወይም በመያዣነት የተያዙ መሆኑን በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚያስፈልግ ሕግ ቁጥር 341(2) እና የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865(1) ድንጋጌዎች ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት አክሲዮኖች የሁለተኛው ተጠሪ ስም የተፃፈባቸው አክሲዮኖች መሆናቸውን አመልካች በማስረጃነት ካቀረበው የአክሲዮን ድርሻ ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመረዳት ይቻላል፡፡ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች እንደማንኛውም ግዙፍነት ያላቸው ተንቀሣቃሽ ንብረት በመቁጠር የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሌሎች የውል ሕግ ጠቅላላ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ መወሰናቸው ከጅምሩ በአመልካችና በተጠሪዎች መካከል ያለው ክርክር ግዙፍነት የሌላቸው ሃብቶች (አክሲዮኖች) በመያዣነት መያዝን የሚመለከትና ለጉዳዩም ተፈፃሚነት ያላቸው ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2863 እስከ ፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2874 የተደነገጉትና አግባብነት ያላቸው የንግድ ሕግ ድንጋጌዎች መሆናቸውን ባለማገናዘብ የተሰጠ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉትን አክሲዮን ድርሻዎች የፍታብሔር ሕጉ የገንዘብ መጠየቂያ ሰነዶችና ግዙፍ ያልሆኑ ሌሎች ሃብቶችን ስለማስያዝ በሚለው ክፍል የደነገጋቸው መስፈርቶች በሚሟላት በመያዣነት ይዟቸዋል ወይስ አልያዛቸውም የሚለው በሁለተኛ ደረጃ በመታየት ያለበት ነጥብ ነው፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበት የአክሲዮን ድርሻ በመያዝ ሲያዝ የመያዣ ውሉ የሚከናወነው ይህንን መብት በማስተላለፍ በተደነገገው ሥርዓት ወይም /ፎርም/ መሠረት መሆን እንዳለበት ከፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ የባለአክሲዮኑ ስም የተፃፈበትን አክሲዮን ለሌላ ሰው ለማስተላለፍ ይህንኑ በአክሲዮን ማህበሩ ዋና መስሪያ ቤት በሚገኘው የአክሲዮን መዝገብ ማስመዝገብ እንደሚገባ የንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 ይደነግጋል፡፡

አመልካች የሁለተኛው ተጠሪ ስም የተፃፈባቸውን ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች ለመያዝ ይህንን በሕግ የተደነገገ ፎርማሊቲ ማሟላት ይገባዋል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት የአክሲዮን ድርሻዎች ውስጥ አመልካች ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለሰጠው ብር 40,000,000 /አርባ ሚሊዮን ብር/ ኦቨር ድራፍት ብድር መያዣ ይሆኑ ዘንድ ብር 475,000 /አራት መቶ ሰባ አምስት ሺ ብር/ ዋጋ ያላቸው አክሲዮኖች በአመልካች በመያዣነት የተያዙ መሆኑና መያዣው በአቢሲኒያ አክሲዩን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን አቢሲኒያ ባንክ ሚያዚያ 6 ቀን 1992 ዓ.ም ለአመልካች በአድራሻው ለሁለተኛው ተጠሪ በግልባጭ የፃፈው ደብዳቤ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ከአመልካች በኦቨር ድራፍት ለወሰደው ብር 10,000,000 /አስር ሚሊዮን ብር/ መያዣ ይሆኑ ዘንድ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት አክሲዮኖች ዋጋቸው ብር 600,000 /ስድስት መቶ ሺ ብር/ የሆኑ አክሲዮኖችን አመልካች በመያዣነት የያዛቸውና መያዣውም በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የአክሲዮን መዝገብ የተመዘገበ መሆኑን አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ሚያዚያ 4 ቀን 1992 ዓ.ም ለአመልካች በአድራሻ ለተጠሪ በግልባጭ የፃፈው ደብዳቤ ያስረዳል፡፡ ይኸም አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲንያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ አርባ ሶስት አክሲዮኖች በፍታብሔር

ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 341 አንቀፅ 2 የተቀመጠውን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት የያዘ መሆኑን ለማስረዳት የሚችል ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ተጠሪዎች የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር የሁለተኛው ተጠሪ የአክሲዮን ድርሻዎች በአመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑን በአክሲዮን መዝገብ ላይ የመዘገበው ያለ ሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ነው የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡ አቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ሁተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ አመልካች ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ላበደረው የኦቨር ድራፍት ብድር በመያዣነት የያዙ መሆኑን የመዘገበው ሁለተኛው ተጠሪ ሁለቱ እህት ኩባንያዎች ከአመልካች ለወሰዱት ብድር ያሉት የአክስዮን ድርሻዎቹ አስፈላጊውን ፎርማሊቲ አሟልቶ በመያዣነት እንዲያዙ እንዲያደርግ ግንቦት 26 ቀን 1991 ዓ.ም ለአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር በፅሑፍ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት መሆኑን ተጠሪዎች በማስረጃነት ይጠቅመናል ብለው ባቀረቡት የአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ግንቦት 14 ቀን 1999 ዓ.ም ከፃፈው ደብዳቤ በመግቢያው ላይ ተገልጿል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች ለሚና ትሬዲንግና ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ለሰጠው የኦቨር ድራፍት ብድር በፍላጐቱና በፈቃዱ በመያዣነት ያስያዘ መሆኑን "ኩባንያችን በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለውን የብር 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ ዋጋ ያላቸው አርባ ሶስት አክሲዮኖች ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ ከባንኩ ለተበደሩት ብድር በዋስትና ያስያዘ መሆኑ ይታወቃል" በማለት አመልካች ከአቢሲኒያ ባንክ የባለአክሲዮኖች ስብሰባ ለመካፈል እንዲፈቀድለት በቁጥር ጣትኩ 701/37/99 ህዳር 9 ቀን 1999 ዓ.ም የፃፈው ደብዳቤ ያረጋግጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ አክሲዮኖቹን በማያዣነት በአክሲዮን መዝገብ ውስጥ ሲመዘገብ ሁለተኛው ተጠሪ በግልባጭ እንዲያውቅ እያደረገ መሆኑን የቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃዎች ያሣያሉ፡፡ በአመልካች በኩልና ተጠሪዎች ክርክራቸውን ለማጠናከር ያቀረቧቸው የፅሑፍ ማስረጃዎች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያሉት አርባሶስት አክሲዮኖች በመያዣነት የያዘውና መያዣው በአክሲዮን መመዝገቢያ መዝገብ የተመዘገበው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት መሆኑን የሚያረጋግጥ ግልፅ የፅሑፍ ማስረጃ በቀረበበት ሁኔታ በመሆኑ ተጠሪዎች መያዣው በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን መዝገብ የተመዘገበው ከሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ስምምነት ውጭ ነው በማለት ያቀረቡትን ክርክር አልተቀበልነውም፡፡ ተጠሪዎች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ ለመሣተፍ እንዲፈቀድለት ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ በስህተት የተፃፈ ነው፡፡ የአመልካች የሥራ ኃላፊዎች ሁለተኛው ተጠሪ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ የሕጉን መስፈርት በሚያሟላ የመያዣ ውል ያልተያዘ መሆኑን በተፃፃፉት ፅሑፍ አረጋግጠዋል፡፡ ስለሆነም አክሲዮን ድርሻው በመያዣነት አልተያዘም ተብሎ እንዲወሰንልን የሚል ክርክር አቅርበዋል፡፡

የሁለተኛ ተጠሪ እህት ኩባንያዎች የሆኑት ስታር ቢዝነስ ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ሚና ትሬዲንግ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ለአመልካች በኦቨር ድራፍት ብድር ሲወስዱ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ያለው የአክሲዮን ድርሻ በመያዣነት እንዲያዙ የተስማማ መሆኑ በአመልካች የቀረቡት የፅሑፍ ማስረጃዎች ያረጋግጣሉ፡፡ አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያለውን የአክሲዮን ድርሻ መያዣ በማድረግ ለሁለቱ የንግድ ድርጅቶች የኦቨር ድራፍት ብድር ፈቅዶ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ብድሩን ወስደዋል፡፡ **ከዚህ** በተጨማሪ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ከአመልካች የወሰዱትን የኦቨር ድራፍት ብድር ፈቅዶ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ብድሩን ወስደዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁለቱ የንግድ ድርጅቶች ከአመልካች የወሰዱትን የኦቨር ድራፍት ብድር አልከፈሉም፡፡ ከዚህ ሁሉ ሂደት በኂላ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ያሉኝ የአክሲዮን ድርሻዎች አመልካች በመያዣነት የያዛቸው መሆኑን በመግለፅ የፃፍኩት ደበዳቤ በስህተት የተፃፈ ነው በማለት ያቀረበው ክርክር የሕግ ድጋፍና ተቀባይነት የሌለው ክርክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ሁለተኛው ተጠሪ አመልካች በአክስዮን ድርሻዎቹ ላይ የሕጉን መስፈርት የሚያሟላ የመያዣ ውል የሌለው መሆኑን በመግለፅ የባንክ ኃላፊዎች በፁሑፍ አረጋግጠዋል በማለት የሚከከራከረው የባንኩ ኃላፊዎች የውስጥ መፃፃፊያ ሚሞ በማስረጃነት በማቅረብ ነው፡፡ እነዚህ የውስጥ መፃፃፊያዎቹ በዚህ ጉዳይ የአስረጅነት ዋጋ የሌላቸው በመሆኑ ክርክሩ ተቀባይነት የለውም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአመልካች ኃላፊዎችና የሕግ ክፍል እርስ በርሳቸው በፅሑፍ የተለዋወጡት ሃሣብ በጉዳዩ ተፈፃሚነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ያላገናዘበና የሕግ አረዳድ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአጠቃላይ ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ ካለው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ የአክሲዮን ድርሻዎችን አመልካች በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 1 እና በንግድ ሕግ ቁጥር 341 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገውን መስፈርት በማሟላት በመያዣነት የያዛቸው ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካች የአክሲዮን ድርሻዎቹን በመያዣነት የያዘውና በአቢሲኒያ ባንክ /አ.ማ/ የአክሲዮን መዝገብ ያስመዘገበው የፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2865 ንዑስ አንቀፅ 2 መሠረት በሁለተኛው ተጠሪ ፈቃድና ሙሉ ስምምነት መሠረት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ግዙፍ ያልሆኑ ሃብቶች በመያዣነት በሚያዙበት ወቅት ገዥነት ያላቸውንና ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚገቡ የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ አመልካች የሁለተኛ ተጠሪን የአክስዮን ድርሻ በመያዣነት የያዘ ስለመሆኑ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2828 ንዑስ አንቀፅ 2 እና ሌሎች ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌዎችን የሚጠይቁትን ፎርማሊቲ ያላሟላ በመሆኑ ሕጋዊ ውጤት የለውም በማለት የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

3. አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካሉት የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆኑ አርባሶስት አክሲዮኖች የሕጉን ፎርማሊቲ በማሟላት በመያዣነት ይዟል፡፡ አመልካች በመያዣነት የያዛቸው አክሲዮኖች ላይ የቀዳሚነት መብት ይኖረዋል፡፡ አመልካች የቀዳሚነት መብት በሁለተኛው ተጠሪ ላይ ብቻ ሣይሆን በሶስተኛ ወገኖችም ላይ የፀና ነው፡፡ ስለሆነም አመልካች በመያዣነት በያዛቸው አክሲዮኖች ላይ ያለው የቀዳሚነት መብት ሁለተኛ ተጠሪን ከስሶ የፍርድ ባለመብት በሆነው አንደኛው ተጠሪ ላይም የሚሰራ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አመልካች በመያዣነት የያዛቸውን አርባሶስት አክሲዮኖች የሚያስገኙትን ትርፍ /ዲቪደንድ/ በፍታብሔር ሕግ ቁጥር 2867 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት የመቀበልና የቀዳሚነት መብት አለው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት እና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካች ሁተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ውስጥ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ በሆኑ አርባሶስት አክሲዮኖችና ከእነዚህ አክሲዮኖች እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር 2006/2007 ዓ.ም የሚገኘው ዲቪደንድ ለአንደኛው ተጠሪ የፍርድ ማስፈፀሚያ እንዲሆን የሰጡት ትዕዛዝ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ ስለሆነም ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ካለው የአክሲዮን ድርሻ አመልካች ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ በሆነው አርባ ሶስት አክሲዮኖችና እነዚህ አክሲዮኖች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 እና ከዚያ በኋላ ባስገኙት የአክስዮን ትርፍ /ዲቪደንድ/ በቀዳሚነት የመጠየቅና የመቀበል እና ለአበደረው ብድር መክፈያ የማድረግ መብት አለው፡፡ በመሆኑም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር የጠቀስናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች ሣያገናዝቡ አመልካች ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ ካለው የአክሲዮን ድርሻ በአርባሶስት አክሲዮኖችና በዲቪደንድ ላይ የሕጉን ፎርም ያሟላ የመያዣ መብት የለውም በማለት የሰጡት ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 62713 ግንቦት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝና የጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመዝገብ ቁጥር 38688 ሰኔ 25 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ለአስታር ቢዝነስ ግሩኘ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና ለሚና ትሬዲንግ ኃላፊቱ የተወሰነ የግል ማህበር በኦቨር ድራፍት ብድር ሲያበድር ሁለተኛው ተጠሪ በአቢሲኒያ ባንክ አክሲዮን ማህበር ካለው የአክሲዮን ድርሻ ዋጋቸው 1,075,000 /አንድ ሚሊዮን ሰባ አምስት ሺ ብር/ የሆነ አርባሶስት አክሲዮኖች በመያዣነት ይዟል፡፡ በእነዚህ አክሲዮኖች ላይ የቀዳሚነት መብት አለው ብለናል፡፡
3. አመልካች በመያዣነት የያዛቸውና ከላይ ዋጋቸው የተገለፀው አርባሶስት አክሲዮኖች እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር 2006/2007 እና ከዚያ ወዲህ ያስገኙትን የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ /ዲቪደንድ/ የመቀበል የቀዳሚነት መብት አለው ብለናል፡፡
4. አንደኛ ተጠሪ ለፍርድ ማስፈፀሚያ ማድረግ የሚችለው አመልካች በመያዣነት ያልያዛቸውን የሁለተኛው ተጠሪ አክሲዮኖችና ከእነርሱ የሚገኘው የአክሲዮን ድርሻ ትርፍ /ዲቪደንድ/ ብቻ ነው ብለናል፡፡

5. ለሰበር ያወጡትን ወጭ አመልካችና ተጠሪዎች ለየራሣቸው ይቻሉ፡፡
6. በትውስት የመጣው የከፍተኛው ፍርድ ቤት መዝገብ ይመለስ፡፡

ይኸ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምፅ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 43372

ሐምሌ 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- አቶ ደረሱ ዓለሙ - አልቀረቡም፡፡

**ተጠሪ**፡- አቶ ሙሊሣ ወርቁ - አልቀረቡም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍ ር ድ**

ጉዳዩ የተጀመረው በምስራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ተከሳሽ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ነበሩ፡፡ የክሱም ምክንያት በ10/8/98 ዓ.ም በተፃፈ የብድር ውል በ29/9/98 ዓ.ም ለመመለስ ብር 11,750 (አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ተበድረው በተባለው ቀን ካልከፈሉ እጥፍ አድርገው ብር 23,500(ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) ለመክፈል ገንዘቡን ተቀብለው ስላልከፈሉ በውሉ መሰረት ገንዘቡን እጥፍ አድርገው እንዲከፍሉ እንዲወሰን በማለት ውላቸውን ጨምሮ በአንድነትና በነጠላ እንዲከፍሉ የሚል ነው፡፡

ሁለተኛ ተከሳሽ የነበሩት ዋስ የብድሩን ገንዘብ በማመን ከዋናው ተበዳሪ ጋር ይከራከር በማለት መልስ የሰጡ ሲሆን አንደኛ ተከሳሽ የአሁኑ አመልካች ግን የተበደረውን ያህል ብቻ እንጂ እጥፍ ተደርጐ መክፈል እንደሌለባቸው በመግለጽ መልስ በመስጠት ተከራክረዋል፡፡

ግራ ቀኙን ያከራከረው ፍ/ቤት አመልካች የተበደሩትን ገንዘብ ወለድ በማድረግ 23,500 (ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) በውሉ መሰረት እንዲከፍሉ ዋና ተበዳሪው ካልከፈሉ ዋሱ እንዲከፍሉ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኙን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 337 መሰረት የሰረዘው ሲሆን ሰበር ሰሚ ችሎትም በተመሳሳይ ሁኔታ በማጽናቱ የቀረበ የሰበር አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ጥር 3 ቀን 2001 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት ቅሬታ መሰረት የብድሩ ገንዘብ እጥፍ ተደርጐ እንዲከፍል የመወሰኑን አግባብነት ለመመርመር ተጠሪን በማስቀረብ ግራ ቀኙ ክርክራቸውን በጽሑፍ አቅርበዋል፡፡

እኛም ክርክራቸውን እንደሚከተለው መርምረናል፡፡

ከግራ ቀኙ ክርክር በፍሬ ነገረ ረገድ የተረጋገጠውና የማይካካዱት 11,750.00 (አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሐምሳ ብር) አመልካች ከተጠሪ በብድር የወሰዱ መሆኑን ነው፡፡ አከራካሪ የሆነው የተጠቀሰው የብድር ገንዘብ በተባለው ቀን ባለመከፈሉ ምክንያት እጥፍ አድርጐ የመመለሱ ጉዳይ ነው፡፡ በመሰረቱ ተዋዋዮች የብድሩን ገንዘብ እጥፍ አድርጐ ማለትም መቶ ፐርሰንት ወለድ ለመክፈል ቢዋዋሉ የሕግ መሰረት ይኖራል ወይ? የሚለው ነጥብ ምላሽ ሊያገኝ የሚገባ ነው፡፡ ተዋዋዮች በወለድ የሚከፈለውን ገንዘብ በአመት በመቶ ከአስራ ሁለት በላይ እንዲሆን ለመዋዋል እንደማይቻል በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 2479/1/ የተመለከተ ከመሆኑም በላይ በወለድ የሚከፈለው ገንዘብ በመቶ አስራ ሁለት በላይ በዓመት እንዲሆን በጽሁፍ የተደረገ ውል ቢኖር እንኳ ተበዳሪው በመቶ ዘጠኝ ብቻ በአመት ወለድ መክፈል እንዳለበት

በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2479/3/ በአስገዳጅ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ አንፃር ተዋዋዮች የብድርን ገንዘብ እጥፍ አድርጎ ለመክፈል መስማማትን ሕጉ የማይፈቅድ መሆኑን ከፍ ሲል ከተጠቀሱ ድንጋጌዎች መገንዘብ ይቻላል፡፡

ተጠሪ በስር ፍ/ቤት በግልጽ የጠየቁት ዳኝነት አመልካች በ10/8/98 ዓ.ም በተፃፈ ውል በ29/9/98 ሊመልስልኝ በዚህ ቀን ሳይመልስ ቀኑን ካሳለፈ የተበደረውን ገንዘብ እጥፍ አድርጎ ሊከፍለኝ ብር 11,750(አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ተበድሮ እስካሁን አልመለሰልኝም፡፡ ስለዚህ በገቡት ግዴታ መሰረት እጥፍ አድርገው ብር 23,500(ሃያ ሦስት ሺህ አምስት መቶ) እንዲከፍሉ እንዲወሰንልኝ የሚል ነው፡፡ ፍ/ቤቱም እጥፍ ተደርጎ የመከፈሉን ጥያቄ ተቀብሎ በስምምነቱ መሰረት እጥፍ የተባለውን ወለድ ለማድረግ 23,500 ብር እንዲከፍል በማለት መወሰኑ ከፍ ሲል ስለወለድ አከፋፈል በሕጉ የተመለከተውን ድንጋጌ ያላገናዘበ ነው፡፡ የተጠሪ ጥያቄ በውሉ በተመለከተው ቀን ባለመከፈሉ ምክንያት ገንዘቡ እጥፍ ተደርጎ እንዲከፈላቸው እንጅ ክፍያው ስላዘገየባቸው ወለድ ተሰልቶ እንዲከፈላቸው አልጠየቁም፡፡ በፍ/ቤቶች መብትም ሆነ ግዴታ በፍርድ ሊረጋገጥ የሚችለው በሕግ በተመለከቱ ስርአቶች ብቻ እና በግልጽ በተጠየቀው ዳኝነት አንፃር ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ የብድርን ገንዘብ ከመነሻው እጥፍ አድርጎል ለመክፈል ውል ለመዋዋል ሕጉ የሚከለክል ሲሆን ከፍ ሲል ከተመለከቱት የሕግ ድንጋጌዎች መንፈስ ባፈነገጠ መልኩ የምእራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠቀሰውን ገንዘብ እንደወለድ እጥፍ አድርጎ ይክፈል በማለት የሰጠውን ውሳኔ ይግባኝ ሰሚም ሆነ ሰበር ሰሚ የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ማረም ሲገባቸው በማጽናት የሰጡት ውሳኔዎች መሰረታዊ የሕግ ትርጉም ስህተት የተፈጸመበት ነው ብለናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የምዕራብ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 18071 በ14/9/2000 ዓ.ም፣የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 52223 በ3/3/2001 ዓ.ም እና እንዲሁም ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 74254 በ28/5/2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጡት ውሳኔዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/መሰረት ተሻሽሏል፡፡ ይፃፍ፡፡
2. አመልካች 11,750(አስራ አንድ ሺህ ሰባት መቶ ሃምሳ) ስለመበደራቸውና ይህንኑ ብር ብቻ እንደሚከፍሉ ያመኑ በመሆኑ ከውሉ ጊዜ ማለትም ከ10/8/98 ዓ.ም እስከ 29/9/98 ዓ.ም ድረስ ያለውን የአንድ ወር ከ19 ቀን ብቻ 11,750 ብር የሚያስገኘውን ወለድ 9% በዓመት ስሌት ታስቦ ለተጠሪ እንዲከፈሉ በማለት ተወስኗል፡፡
3. ወጪና ኪሳራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ ብለን መዝገቡን ዘግተናል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 41388

ሐምሌ 30 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች** ፡-ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች** ፡- የኢትዮጵያ ልማት ባንክ - ነ/ፈጅ ትዕግስት አሰፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- 1. ከፍያለው ሞልቶት
2. የትምወርቅ አሰፋ } ቀረቡ

መዝገቡን መርምረን ተከታዩ ፍርድ ሠጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመረው በምዕራብ ሐረርጌ ከፍ/ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁን አመልካች በኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ላይ በመሠረተው ክስ መነሻ ነው፡፡ የአመልካች የክስ ይዘትም የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን ከሸክ ሁሴን ሚጨታ ድረስ ያለውን መንገድ ለማሻሻል በአደረገው እንቅስቃሴ መሠረት አመልካች ለሠጠው ብድር መያዣ የነበሩት በሚጨታ ከተማ ውስጥ የሚገኙ የማይንቀሣቀሱ ንብረቶች ውስጥ በአቶ ሚካኤል ከፍያለው ስም ተመዝግበው ያሉት የመኖሪያና የድርጅት ቤቶች መፍረሣቸውን፣ ንብረቶቹ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ለራሣቸውና ለአቶ መራቸው የማነ ከአመልካች ላይ ለወሠዱት ብድር መያዣ መሆናቸውን፣ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ለፈረሡት ቤቶች የሚከፈለውን ካሣ ለመያዣ ሠጪዎች ለመክፈል በዝግጅት ላይ መሆኑን አመልካች ገልፆ ይኸው አካል ከዚህ አድራጐት እንዲቆጠብ፣ ክፍያውን ለመያዣ ሠጪዎች ሣይሆን ለአመልካች እንዲከፍል እንዲደረግ ዳኝነት መጠየቁን የሚያሣይ ነው፡፡ ይኸው የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ የቀረበለት ፍ/ቤትም "ተከሣሹ" ባለሥልጣን መ/ቤት በተገቢው የክርክር ሂደት ባለመቅረቡ በስነ ሥርዓቱ መሠረት በሌለበት እንዲታይ አድርጐ የአመልካችን የዳኝነት ጥያቄ ተቀብሎ ወስኗል፡፡ ከዚህ በኋላ የአሁኑ ተጠሪዎች የካሣ ክፍያ እንዳይከፈልባቸው ውሣኔ ያረፈባቸውና በመያዣ ተይዘዋል የተባሉት ንብረቶች ህጋዊ ባለቤቶች መሆናቸውን፣ ከአመልካች ጋር ህጋዊ ወይም ከውል የመነጨ ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ዘርዝረው ቀደም ሲል የተሠጠው ውሣኔ እንዲነሣላቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 358 'ን' መሠረት በማድረግ አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎች አቤቱታ ለአመልካች እንዲደርሰው እና ግራ ቀኙ እንዲከራከሩ ከአደረገ በኋላ አመልካች ከተጠሪዎች ጋር የብድርም ሆነ የመያዣ ግንኙነት እንደሌለው ተረጋግጧል በሚል ምክንያት ቀድሞ የተሠጠውን ውሣኔ በማንሣት ለንብረቶቹ ይከፈል የተባለው ካሣ ለተጠሪዎች ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኋላ የስር ፍ/ቤት ውሣኔ ሙሉ በሙሉ ፀንቷል፡፡ የአሁን የሠበር አቤቱታ የቀረበውም በዚህ የበታች ፍ/ቤቶች ውሣኔ ባለመስማማት በመቃወም ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ህዳር 08 ቀን 2001 ዓ.ም. በፃፋት 7/ሠባት/ ገፅ የሠበር አቤቱታ በጉዳዩ ላይ በተሠጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ነው የሚሉባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ የአመልካች የሠበር አቤቱታ ተመርምሮ ክርክር ያስነሡት ንብረቶች በመያዣነት የተሠጠ በመሆኑ የካሣ ክፍያው ለእኔ ይገባል በማለት አመልካች ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው ባግባቡ መሆን አለመሆኑን ለመመርመር ሲባል ለሠበር ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ ይህ ሠበር ችሎትም የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሚያዝያ 15 ቀን 2001 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ሠምቷል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር የሥበር አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው የህግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የአመልካች የዳኝነት ጥያቄ ተቀባይነት ያጣው በህጉ አግባብ ነው ወይስ አይደለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ አግኝቶታል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የተጠሪዎች ልጅ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ለራሣቸው ለአቶ መራቸው የማነ ከአመልካች ላይ ለወሠዱት ብድር መያዣ ይሆኑ ዘንድ ለክርክሩ መነሻ የሆኑትን የመኖሪያና የድርጅት ቤቶችን መስማማታቸውን፣ የመያዣ ንብረቶች ስመ ሀብትም በዚህ ግለሠብ ስም የሚታወቅና የመያዣ ውሉም ንብረቱ በሚገኝበት የሚጨታ ልዩ ቀበሌ መመዝገቡ፣ ተጠሪዎች በአቶ ሚካኤል ከፍያለው ይታወቃል የተባለው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተሠጠ ነው በማለት የሚከራከሩና ይኸው ምስክር ወረቀት እስከአሁን ድረስ በተገቢው አካል እንዲሠረዝ ያላደረጉ መሆናቸውን ነው፡፡ እንግዲህ የአሁን ተጠሪዎች ልጅ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ራሣቸውና እና አቶ መራቸው የማነ ከአሁኑ አመልካች ላይ ለወሠዱት የብድር ገንዘብ በካርታ ቁጥር 005፣ 034 እና 084 ላይ የተመለከቱትን በሚጨታ ከተማ የሚገኙትን የመኖሪያና የድርጅት ቤቶች መያዣ መስጠታቸው፣ እነዚህ ንብረቶች የመያዣ ሠጪው ይዞታ ለመሆናቸው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት ከመቅረቡም በላይ የሚጨታ ልዩ ቀበሌም ለአመልካቹ ተጨማሪ ደብዳቤ ፅፎለት የመያዣ ውሉ ከተደረገ በኂላ የመያዣ ውል ምዝገባ ማካሄዱ በክርክሩ ሂደት የተረጋገጡ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የስር ፍ/ቤት የምስክር ወረቀቱን ዋጋ ሣይሠጠው ያለፈው የካርታ ቁጥር 005 በሐምሌ 1992 ዓ.ም.፣ የካርታ ቁጥር 034 በግንቦት ወር 1990 ዓ.ም. እንዲሁም የካርታ ቁጥር 005 በጥቅምት ወር 1989 ዓ.ም. ውስጥ የተሠጡ፣ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፉ፣ የደርግ መንግስትን የሚመለከትና በተለይም የከተማ ቦታ ስም፣ ወረዳ፣ የመሣሠሉትና በሚለው ላይ ስርዝ ያለው እውነትነቱ አጠራጣሪ ነው በማለት ነው፡፡ ከዚህ የስር ፍ/ቤት መደምደሚያ መገንዘብ የሚቻለው በወቅቱ በክልሉ የሚሠራው በኦሮምኛ ሆኖ የምስክር ወረቀቱ እንዴት በአማርኛ ሊሆን ቻለ ከሚል ጥርጣሬ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የምስክር ወረቀቱ ሐሰተኛ ስለመሆኑ በተጨባጭ የተረጋገጠ ነገር የለውም፡፡ በምስክር ወረቀቱ ላይ ያሉት እንደ ማህተም ያሉት ነገሮች የአስተዳደር ጽ/ቤት አይደሉም የሚል ግልፅና ተጨባጭ ምክንያት ስለመኖሩም የስር ፍ/ቤት አልገለፀም፡፡ ፍርድ ቤቱ ማህተሙ የአስተዳደር ጽ/ቤቱ አይደለም የሚል በቂ ምክንያት ካለውም ተቃራኒ ማስረጃ እንዲቀርብ ባደረገ ነበር፡፡ ለጉዳዩ ቀጥተኛ ኃላፊነት ያለውና ይመለከተዋል የተባለው የቀበሌ ጽ/ቤቱም ለአመልካች የፃፈው ደብዳቤ የይዞታ ምስክር ወረቀቱን አጠራጣሪነት የሚያሣይ አይደለም፡፡ በመሆኑም ተቃራኒ ማስረጃ ሣይቀርብና የማህተሙ ሀሰተኛ መሆን ሣይረጋገጥ በጥርጣሬ ብቻ የሚደርስ ድምዳሜ ህጋዊ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ስለሆነም አመልካች ለማስረጃነት ላቀረበው የከተማ ይዞታ ምስክር ወረቀት ዋጋ የማይሠጥበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

የምስክር ወረቀቱ ዋጋ አለው ከተባለ ደግሞ ለክርክሩ መነሻ የሆኑት ንብረቶች ህጋዊ ባለቤት መያዣ የሠጠው ግለሠብ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 ድንጋጌ መገንዘብ የምንችለው ጉዳይ ነው፡፡ የንብረቶቹ ህጋዊ ባለቤት ይኸው ግለሠብ መሆኑ ከተረጋገጠ ደግሞ ከንብረቶቹ ጋር ተያይዞ የሚጠየቀውን ማንኛውንም መብትና ጥቅም ህጉ ጥበቃ የሚያደርገው ለዚሁ ባለንብረት ነው፡፡ ተጠሪዎች በንብረቶቹ ላይ አቶ ሚካኤል ከፍያለው ይዟል የተባለውን የምስክር ወረቀት በተቃራኒ ማስረጃ አላስተባበሉም፤ ስልጣን ባለው አካልም እንዲሠረዝ አላደረጉም ወይም በንብረቶቹ ላይ በህጉ አግባብ ያቋቋሙት የባለሀብትነት መብት የለም፡፡ ይህ የሚያሣየውም ተጠሪዎች በንብረቶቹ ላይ ህጉ ጥበቃ የሚያደርግላቸው መብትና ጥቅም የሌላቸው መሆኑን ነው፡፡ ለክሱ መነሻ በሆነው ነገር ላይ መብትና ጥቅም የሌለው ወገን ደግሞ የዳኝነት ጥያቄ ማቅረብ የማይችል ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ ድንጋጌ ያስረዳል፡፡ በመሆኑም የተጠሪዎች የዳኝነት ጥያቄ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 33/2/ እና 359 ድንጋጌዎች ጋር ተዛምዶ ሲታይ ከመነሻውም ቢሆን ህጋዊ መሠረት የሌለው ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡

አመልካች የያዘው የመያዣ ንብረት በህጉ አግባብ የአቶ ሚካኤል ከፍያለው ነው እንጂ የይዞታ ምስክር ወረቀት በተጭበረበረ መንገድ የተያዘ ነው ከተባለም የመያዣ ውሉ ህጋዊ አይደለም ሊባል ይችል የነበረው አመልካች ከቅን ልቦና ውጪ በሆነ ሁኔታ መያዣውን መያዙን ሲረጋገጥ ነበር፡፡ ይህም በፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/2/ ድንጋጌ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የአስተዳደር ክፍል የማይንቀሣቀስ ንብረት ባለሀብት መሆኑን አውቆለት የባለሀብትነት የምስክር ወረቀት ከሠጠው ሠው ጋር የተደረገ የንብረት መያዣ ውል በህግ ፊት የፀና ሲሆን የምስክር ወረቀቱ የተሠጠበት ማስረጃ ፍርስ ሆኖ የተሠረዘ ቢሆንም በመያዣው የሚከራከረው ሠው በቅን ልቦና አለመሆኑ ካልተገለፀ በቀር የርስት መያዣው ውል

የሚፀና ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3051/1/ እና /2/ ድንጋጌዎች ያሣያሉ፡፡ በዚህም መሠረት የአመልካች መያዣ በህግ ፊት የማይፀናበት ህጋዊ ምክንያት የለም፡፡

ሲጠቃለልም የበታች ፍ/ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሠጡት ውሣኔ ከላይ የተመለከቱትን የህግ ድንጋጌዎችን ያላገዘበ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በምዕራብ ሐረርጌ ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ 04527 ሚያዝያ 09 ቀን 1999 ዓ.ም. ተሠጥቶ በኦሮሚያ ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ 55442 ጥቅምት 25 ቀን 2001 ዓ.ም. የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ መነሻ በሆኑ ንብረቶች ላይ አመልካች የፀና የመያዣ ውል ስላለው ለንብረቶቹ በሚከፈለው ካሣም መብት አለው ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
4. ህዳር 17 ቀን 2001 ዓ.ም. ተሠጥቶ የነበረው እግድ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ጽ/ሽ

የሰ/መ/ቁ. 39725

ሐምሌ 23 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካቾች፡-** 1. ወ/ሮ ዓለምሸት ካሣሁን - ቀረቡ፡፡

2. አቶ ብርሃኑ ካሣሁን

3. አቶ ዳንኤል ካሣሁን

**ተጠሪ፡-** አቶ ሽመልስ እንዳለ - ጠበቃ ግርማቸው ኢላላ - ቀረቡ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመዝገብ ቁጥር 05596 ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ እና የከፍተኛው ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 59564 ሚያዝያ 21 ቀን 2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት የሰበር አቤቱታ በመቅረቡ ነው፡፡

ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው፡፡ በፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት አመልካቾች ከሣሽ ተጠሪ ተከሣሽ በመሆን ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች የአባታቸው የአቶ ካሣሁን አስረስ ወራሽ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ በፍርድ ቤት የተሰጠ የወራሽነት ማስረጃ በማያያዝ ሟች አባታችን በህይወት በነበረበት ጊዜ ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. በተፃፈ የቤት ሽያጭ ውል ተከሣሹ ከአያታቸው አቶ ጥላሁን ሀይሌ በኑዛዜ ወራሽነት ያገኙትን በቀድሞ አጠራር በወረዳ 21 ቀበሌ 25 የቤት ቁጥር 424 የሆነውን በብር 100,000 /አንድ መቶ ሺህ ብር/ ገዝተዋል፡፡ ሆኖም የቤቱ ስመ ንብረት በተከሣሽ /ተጠሪ/ አያት ስም ያለ በመሆኑ የቤቱን ስመ ንብረት ወደራሳቸው ካዛውሩ በኋላ ካርታውን እንዲሰጡን ይወስንልን በማለት ክስ አቅርበዋል፡፡

ተጠሪ በተከሣሽነት ቀርበው ውል አልተዋዋልኩም፡፡ የከሳሾችን /የአመልካቾችን/ አባት ወክሎ በውሉ ላይ የተፈረመው ሰው ሟችን በመወከል ቤት ለመግዛት ስልጣን የሌላቸው ሰው ናቸው፡፡ ከእኔ ጋር 1989 የተደረገው ውል አባቴ ጋር 1987 የተደረገውን ውል የሚያጣቅሰው ነው፡፡ የቤቱን ሰነድ ለማስረከብ ግዴታ የገቡት ውሉ በተደረገ በአንድ ወር ውስጥ ስለሆነና ከሣሾች በአንድ ዓመት ውስጥ ውሉ እንዲፈፀምላቸው ያልተጠየቁ ስለሆነ ውሉን ለመፈፀም አልገደድም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ተከሣሽ /ተጠሪ/ የአሁን አመልካቾች /ከሣሾች/ በሽያጭ ውሉ ምክንያት የያዙትን ቤት እንዲለቁና ኪራይ እንዲከፍሏቸው ከዚህ በፊት በመዝገብ ቁጥር 3754 ክስ አቅርበው በአመልካቾች /ከሣሾች/ አባትና በተጠሪ /በተከሣሽ/ መካከል ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. የተደረገ የቤት ሽያጭ ውል ያለመሆኑ በፍርድ ውሣኔ ያገኝ በመሆኑ ተጠሪ /ተከሣሽ/ ውሉንና ፊርማቸውን በመካድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡ በሌላ በኩል አመልካቾች ውሉ ከተደረገበት ከሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሉ

እንዲፈፀምላቸው ያልጠየቁ በመሆኑ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ተከሣሽ /ተጠሪ/ ውሉን ተገድዶ የመፈፀም መብታቸውን አጥተዋል በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች በዚህ ውሣኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሣኔ አጽንቶታል፡፡ አመልካቾች ሐምሌ 18 ቀን 2000 ዓ.ም. በተፃፈ የሰበር አቤቱታ ተጠሪ አመልካቾች በውል የተረከቡትን ቤት እንዲያስረክቡትና የቤት ኪራይ እንዲከፍሉት ክስ አቅርቦ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የውሉን መደረግና የቤት ሽያጭ ውሉን አስመልክቶ ያቀረቡትን ክርክር ማስረጃ በመመዘን በአመልካቾች አባትና በተከሣሽ መካከል ሕጋዊ የቤት ሽያጭ ውል ያለ መሆኑ በመዝገብ ቁጥር 3754 መጋቢት 20 ቀን 1997 ዓ.ም ወስኗል፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ቤቱን በሕጋዊ ሽያጭ ውል ነው የያዛችሁት ቤቱን ለተጠሪ አታስረክቡም ኪራይም አትከፍሉም በማለት በሌላ መዝገብ ከወሰነ በኋላ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዛባ ትርጉም በመስጠት ውሉን በግዳጅ ለማስፈፀም አትችሉም በማለት የሰጠው ውሣኔ የሕጉን ድንጋጌ ይዘት፣ መንፈስና ዓላማ ያላገናዘበና የማይንቀሳቀስ ንብረት የሽያጭ ውል አፈፃፀም የሚያስተጓጉል የሕግ ትርጉም በመሆኑ በሰበር ታይቶ እንዲታረምልን በማለት አመልክተዋል፡፡

ተጠሪ በበኩላቸው ሚያዝያ 14 ቀን 2001 ዓ.ም. በተፃፈ መልስ አመልካቾች ውሉ በፍርድ ሀይል እንዲፈፀምላቸው የጠየቁት ውሉ ከተደረገ ከዘጠኝ ዓመት ከሁለት ወር ካለፈ በኋላ ነው፡፡ በሌላ በኩል የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3754 ውሣኔ ከሰጠ በሦስት ዓመት በኋላ ስለሆነ ውሉ በግዳጅ ይፈጽምልኝ ብለው የመክሰስ መብታቸውን ያጣሉ በማለት የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው የሕግ ትርጉም ስህተት የለበትም፡፡ ስለዚህ በሥር ችሎቱ የኖሩበትን ቤት ኪራይ ከፍለው እንዲያስረክቡ ውሣኔ ይስጥልኝ በማለት ተከራክረል፡፡ አመልካች በበኩሉ በዚህ ጉዳይ የሚሠራው የአሥር ዓመት የይርጋ ጊዜ የሚደነግገው የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1845 ድንጋጌ እንጂ የሥር ፍርድ ቤት የጠቀሰው የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 አይደለም፡፡ ተጠሪ በፍርድ የመጨረሻ ውሣኔ ያገኘውን ጉዳይ ከሥነ ሥርዓት ውጭ በማንሣት ሰበር ችሎቱ ቤቱን እንዲረከብና ኪራይ እንዲከፈለው እንዲወስንለት ያቀረበው ጥያቄ የሕግ መሠረት የሌለው በመሆኑ ተቀባይነት የለውም በማለት የመልስ መልስ ሰጥቷል፡፡

ከሥር የክርክሩ አመጣጥና አመልካቾችና ተጠሪዎች በሰበር ያደረጉት የጽሁፍ ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም ጉዳዩን መርምረናል፡፡ ጉዳዩን እንደመረመርነው የአመልካቾች አባትና በተጠሪ መካከል ሚያዝያ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. የተደረገው ውል በፍርድ ቤት ውሣኔና አስገዳጅነት እንዲፈፀምላቸው አመልካቾች ያቀረቡት ጥያቄ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም የሚለው ጭብጥ እልባት ማግኘት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከላይ ለተያዘው ጭብጥ እልባት ለመስጠት ይህ ችሎት የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 አተረጓጎም አስመልክቶ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38935 መጋቢት 3 ቀን 2001 ዓ.ም. የሰጠውን የሕግ ውሣኔና በዚህ መዝገብ ያለውን ልዩ ሁኔታ ማገናዘብ ያስፈልጋል፡፡ የማይንቀሳቀስ ንብረት የሸጠ ሰው ገዢው ውሉን በፍርድ ቤት ውሣኔ እንዲፈጽምለት ለመጠየቅ የሚችልበት የጊዜ ገደብ ያለፈበት ስለሆነ ውሉን ለመፈፀም አልገደድም የሚለውን መከራከሪያ ማቅረብ የሚችለውና ክርክሩ ተቀባይነት የሚያገኘው ውሉን ለመፈፀም ፈቃደኛ አለመሆኑን ለገዢ በማያሻማ ሁኔታ ያሣወቀ መሆኑን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት ሲችል እንደሆነ ከላይ በተገለፀው መዝገብ ትርጉም ተሰጥቶበታል፡፡ ስለዚህ ተጠሪ 1989 ዓ.ም. ጀምሮ አመልካቾች ቤቱን እንዲያስረክቡት ኪራይም እንዲከፍሉት ክስ ከማቅረቡ በፊት ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለአመልካቾች ያሣወቀ ስለመሆኑ የቀረበው ማስረጃ ባለመኖሩ 1989 ጀምሮ አመልካቾች ውሉ እንዲፈፀምላቸው ባለመጠየቃቸው መብታቸውን በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ታግዷል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት የለውም፡፡

ሻጭ የሽያጭ ውሉን ለመፈፀም ፈቃድና ፍላጎት የሌለው መሆኑን በማያሻማ መንገድ ለገዢ ከሚያሣውቅበት አንደኛው መንገድ የሽያጭ ውሉ እንዲፈርስ ለፍርድ ቤት የሚያቀርበው ክስ መሆኑ በሰበር መዝገብ ቁጥር 38935 ሻጭ ለገዢ በማያሻማ መንገድ ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን አሳውቋል የሚባለው ምን ምን ሁኔታዎች ሲሟሉ ነው የሚለውን ነጥብ ለመተንተን በሰጠው ምክንያት በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ሆኖም ሻጭ የቤት ሽያጭ ውሉ ይፍረስልኝ የሚል ክርክር ማቅረቡ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ አንፃር የሚኖረው ውጤት ምንድነው? የሚለው ነጥብ ውሣኔ ያላገኘ ነጥብ በመሆኑ በዚህ መዝገብ እልባት ማግኘት ያለበት ነጥብ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ሻጭ የውል ይፍረስልኝ ክስ ለፍርድ ቤት ማቅረቡ ውሉን ለመፈፀም ፍላጎት የሌለው መሆኑን ለገዢ በማያሻማ መንገድ ከማሣወቅ ያለፈ ምክንያትና ውጤት ያለው ተግባር ነው፡፡ ሻጭ ውሉ እንዲፈርስ ሲጠይቅ ውሉ ሕጋዊ በሆነ መንገድ ለማቋቋም የሚያስችሉ ጉድለቶች ያሉበት በሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች እንደ ሕግ ሆኖ ሊገዙበት የማይገባ መሆኑን የሚያሣዩ የውሉን ሕልውና ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባና የውል ሕጋዊነት በፍርድ ቤት ተመርምሮ ፈራሽ እንዲባል ወይም እንዲሠረዝ የሚቀርብ ነው፡፡ የውሉ ሕጋዊነትና ሕልውና ጥያቄ ተነስቶ በፍርድ ቤት በሚመረመርበት ጊዜ ገዢ ውሉ ሕጋዊ መሆኑን ከማሣየትና ከማስረዳት አልፎ ውሉ በግዳጅ እንዲፈጽምለት የመጠየቅ ግዴታ አይኖርበትም፡፡ ከዚህ አንፃር ውሉ በፍርድ ቤት ፈራሽ እንዲሆን ወይም እንዲሰረዝለት በውሉ የሚገደድበት ሁኔታ ይቋረጣል፡፡ በሌላ በኩል በክርክሩ ከተረታ ገዢ ሕጋዊ ተፈፃሚነትና አስገዳጅነት ባለው ውሉ ንብረቱን የገዛ መሆኑ ከሻጭ ጋር ባደረገው የውል ሰነድ ብቻ ሣይሆን በፍርድ ቤት ውሣኔ የተረጋገጠለት የፍርድ ባለመብት ይሆናል፡፡ ስለሆነም ገዢ ፍርድ ቤቱ ሕጋዊነቱንና አስገዳጅነቱን መርምሮ በፍርድ ያረጋገጠውን ውል እንዲፈጽምለት ሻጭን የመጠየቅ መብቱ በፍርድ ከተረጋገጠበት ጊዜ ጀምሮ በፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 384/ሀ/ በተደነገገው አስር ዓመት ጊዜ ውስጥ እንጂ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በተደነገገው የአንድ ዓመት የጊዜ ገደብ የሚገደብ አይደለም፡፡ ስለዚህ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀፅ 3 የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በዚህ ጉዳይ አግባብነት የለውም፡፡

በሌላ በኩል ፍርድ ቤቶች ለቀረበላቸው ጉዳይ የሚሰጡት ውሣኔ የተያዘውን ጉዳይ ለመቋጨት የሚችል መሆን እንዳለበት ከፍትሐብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 182 ንዑስ አንቀጽ /1/ ድንጋጌ ለመረዳት ይቻላል፡፡ በያዝነው ጉዳይ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 3754 የሰጠው ውሣኔና በዚህ ጉዳይ የሰጠው ውሣኔ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ እና ጉዳዩ በእንጥልጥል የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ የሥር ፍርድ ቤት ተጠሪ አመልካች ቤቱን እንዲመልስላቸውና ኪራይ እንዲከፍላቸው ያቀረቡት ጥያቄ ከአመልካች ጋር የገቡትን የቤት ሽያጭ ውል መሠረት በማድረግ ተቀባይነት የለውም በማለት በመዝገብ ቁጥር 3754 ወስኗል፡፡ አመልካች ያቀረቡት የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ ደግሞ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት በማድረግ ውድቅ አድርጓል፡፡ እነዚህ ውሣኔዎች ተጠሪም ቤቱን ለማስመለስ የማይችሉበት አመልካችም የቤቱ ባለሀብት በማይሆኑበት ሁኔታ ጉዳዩን በእንጥልጥል የሚያስቀሩ ናቸው፡፡ ስለሆነም አመልካች እና በተጠሪ መካከል ሕጋዊ አስገዳጅነት ያለው ውል እንዳለ በፍርድ ካረጋገጠ በኋላ አመልካች ያቀረቡትን የውል ይፈፀምልኝ ጥያቄ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 በመጥቀስ ውድቅ ማድረጉ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት በማለት ወስኗል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ውሉ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት ጥያቄ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 2892 ንዑስ አንቀጽ 3 ቀሪ አይሆንም ብለናል፡፡
3. ተጠሪ ከአመልካች ጋር ያደረጉትን ውል ለመፈፀም ይገደዳሉ ብለናል፡፡
4. ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

የሰ/መ/ቁ. 39803

ሐምሌ 2 ቀን 2001 ዓ.ም.

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋይ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- አቶ አለኸኝ ገ/ሕይወት - ጠበቃ አበባው መላኩ

**ተጠሪ፡-** እነ እማሆይ አጢነሽ በቀለ /3 ሰዎች/ - ጠበቃ ብናልፈው ነጋ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን የአሁን አመልካች በአዲስ አበባ ከተማ በየካ ክ/ከተማ ቀበሌ 11/12 ክልል የሚገኘውን ቁጥር 492 የሆነውን ቤት ሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ በ1974 ዓ.ም. በተደረገ የስጦታ ውል በስጦታ ያስተላለፉልኝ ስለሆነ የስጦታ ውሉ ይጽደቅልኝ የሚል አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤትም ስጦታውን በማጽደቅ ውሣኔ መስጠቱን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

ከዚህ በኂላም የአሁን ተጠሪዎች የሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ ሕጋዊ ወራሾች መሆናቸውን ገልጸው ፍ/ቤቱ ስጦታውን በማጽደቁ የሰጠው ውሣኔ መብታቸውን የነካ እንደሆነና የስጦታ ውሉም የተደረገው የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለከተ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ ፍ/ቤቱ የሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤትም ግራ ቀኙን አከራክሮ የስጦታ ውሉ በተጠቀሰው ድንጋጌ መሠረት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1720/1/ ላይ እንደተመለከተው እንደ ረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የፀና ውል ስላልሆነ ቀደም ሲል በ26/7/99 ዓ.ም. በዋለው ችሎት ስጦታው ሊጸድቅ ይገባል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ በማይጸና ውል ላይ ተመስርቶ ስለሆነ ውሣኔው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 360/2/ መሠረት ተሰርዟል በማለት ፍርድ ሰጥቷል፡፡

አመልካች በዚህ ፍርድ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ጉድለት የሌለው ነው በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ 337 መሠረት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታ ለዚህ ችሎት የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህም ችሎት አቤቱታውን መርምሮ የስጦታ ውሉ በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ እንደ ረቂቅ ከሚቆጠር በስተቀር የጸና አይደለም ተብሎ በሥር ፍ/ቤቶች መወሰኑ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443፣ 881 እና 882 አኳያ አግባብነት ለሰበር ችሎት ቀርቦ ሊወሰን እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን በቃል አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን አቤቱታው ለሰበር ችሎት ሊቀርብ ይገባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ጉዳዩ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

ተጠሪዎች አጥብቀው የሚከራከሩት የሟች ወ/ሮ ደለለኝ በቀለ ሕጋዊ ወራሾች ነን፣ አመልካች ስጦታ እንዲጸድቅላቸው ያቀረቡት አቤቱታ በፍ/ቤቱ ተቀባይነት ማግኘቱ መብታችንን የነካ ከመሆኑም በላይ ስጦታውም ቢሆን በሕግ አግባብነት ያልተደረገ ስለሆነ ይህንኑ ስጦታ ፍ/ቤቱ በማጽደቅ የሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል በማለት ነው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ስጦታው የፀና ስላልሆነ የቀድሞው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ወደሚል መደምደሚያ ሊደርስ የቻለው ስጦታው በማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የተደረገ እንደመሆኑ መጠን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ስለሆነ የፀና አይደለም የሚል ነው፡፡

በእርግጥ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ይዘት መገንዘብ እንደሚቻለው የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከቱ ውሎች በሕግ ፊት የፀኑ ለመሆን ሁለት ሁኔታዎችን ማሟላት ይገባቸዋል፡፡ በአንድ በኩል ውሉ በጽሁፍ መደረግ የሚገባው ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውሉ በአዋዋይ ፊት ወይም በፍርድ ቤት መዝገብ ፊት መከናወን ያለበት መሆኑ ነው፡፡

በሌላ በኩልም በአመልካችና በሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ መካከል ተደርጓል የተባለው የስጦታ ውል ሲሆን በማይንቀሳቀስ ንብረት ወይም በማይንስሳቀስ ንብረት ላይ መብትን የሚሰጥ ስጦታ በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ አሠራር ዓይነት ካልተደረገ ፈራሽ እንደሚሆን በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 ላይ ተመልክቷል፡፡ ግልጽ ኑዛዜ የሚደረግበት ሥርዓት ደግሞ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 881 ላይ የተመለከተ ሲሆን ኑዛዜ በአራት ምስክሮች ፊት ካልተነበበና ይህም ሥርዓት ስለመፈጸሙና ኑዛዜውም የተደረገበት ቀን በሰነዱ ላይ ካልተመለከተ እንደዚሁም ተናዛዡና ምስክሮቹ ወዲያውኑ ፊርማቸውን ወይም የአውራ ጣት ምልክታቸውን ካላደረጉበት ፈራሽ እንደሚሆን በሕጉ ላይ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይም በአመልካችና በሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ መካከል የተደረገው የቤት ስጦታ ውል ይህንን ሥርዓት አሟልቶ የተከናወነ ስለመሆኑ በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ መረጋገጡን መዝገቡ ያስረዳል፡፡

እንግዲህ በአንድ በኩል በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723/1/ ላይ እንደተመለከተው የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን የሚመለከቱ ውሎች ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጣቸው አካላት ፊት ካልተደረጉ የጸኑ ሊሆኑ እንደማይችሉ የተመለከተ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ የማይንቀሳቀስ ንብረትን በተመለተ የሚደረጉ የስጦታ ውሎች ይህንን ሥርዓት ተከትለው መከናወን እንዳለባቸው በፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 ላይም ሆነ 881 ላይ አልተመለከተም፡፡ እነዚህ ሁለት ድንጋጌዎች እርስ በርሳቸው ያልተጣጣሙ ከሆነ ገዢው ድንጋጌ መሆን ያለበት የትኛው ነው የሚለው ዕልባት የሚያሻው ነው፡፡

ከሕጉ አቀራረጽ እንደሚታየው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 1723 የሚገኘው ጠቅላላ ስለ ውሎች በሚመለከተው የፍትሐብሔር ሕጉ ምዕራፍ ስለ ውሎች አመሠራረት መሪ ደንቦች በሚደነግገው ክፍል ሥር ነው፡፡ በዚህ ጠቅላላ የውል ሕግ ድንጋጌ መሠረት የማይንቀሳቀስ ንብረትን የሚመለከት ማንኛውም ዓይነት ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ካልተደረገ የጸና ስለማይሆን ፈራሽ ሊሆን እንደሚችልና ለመብትም ሆነ ለግዴታ ምንጭ ሊሆን እንደማይችል መገንዘብ ይቻላል፡፡

ይሁንና የማይንቀሳቀስ ንብረትን ስጦታ በተመለከተ በተለይ በሚገዛው ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ቁ 2443 እና 881 ድንጋጌ መሠረት ይህ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት አልተመለከተም፡፡ በጠቅላላ ሕግና በልዩ ሕግ መካከል አለመጣጣም ወይንም ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ ልዩ ሕግ የበላይ ሆኖ ተፈፃሚነት ሊኖረው እንደሚችል /The Special prevail over the general/ ከሕግ አተረጓጎም መርህ መገንዘብ ይቻላል፡፡

ስለሆነም አመልካችና ሟች ወ/ሮ ደለለች በቀለ ያደረጉት የቤት ስጦታ ውል፣ ውል ለማዋዋል ሥልጣን በተሰጠው አካል ፊት ያልተደረገ ቢሆንም የማይንቀሳቀስ ንብረት ስጦታ በሚደረግበት ጊዜ ይህ ሥርዓት መከናወን እንዳለበት ለጉዳዩ አግባብነት ባለው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 2443 እና 881 ላይ ያልተመለከተ በመሆኑ የሥር ፍ/ቤቶች የፍትሐብሔር ሕ/ቁ. 1723/1/ በመጥቀሱ የስጦታ ውሉ የፀና አይደለም በማለት ይህንኑ መሠረት በማድረግ አስቀድሞ የተሰጠው ውሣኔ ሊሰረዝ ይገባል ሲሉ የሰጡት ውሣኔ ከሕግ አተረጓጎም መርህ አንፃር መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 35057 በ2/10/2000 ዓ.ም. የሰጠው ፍርድ፣ የፌዴራል ከ/ፍ/ቤትም በመ/ቁ. 68860 በ10/11/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. በአመልካችና በሚች ወ/ሮ ደለለኝ በቀለ መካከል የተደረገው ውል በሕግ አግባብ ስለሆነ የጸና ነው ተብሎ ተወስኗል፡፡
3. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በ26/7/99 ዓ.ም. የሰጠው ውሣኔ ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት ሊሰረዝ አይገባም ተብሎ ተወስኗል፡፡
4. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
5. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

# አፈፃፀም

የሰ/መ/ቁ. 31963

ጥቅምት 20 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** አቶ ዓብዱልሐኪም ሁሴን - ከጠበቃ ወ/ሥላሴ ብርቱ ጋር ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** 1. አቶ ቀነኒ ሁንዴ - ከጠበቃ ጋሻው ተገኝ ጋር ቀረቡ

2. ላሊበላ ኢንጀነሪንግ - አልቀረበም

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን ክርክሩም የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም የሚሸጥበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡

በዚህም መሠረት በአንደኛ ተጠሪና በሁለተኛ ተጠሪ መካከል የነበረው የፍርድ አፈፃፀም ክርክር ቀጥሎ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነ ቤት በሐራጅ ተሸጦ ለሁለተኛ ተጠሪ መከፈል የሚገባው ዕዳ እንዲከፈል የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቶ ይኸው ቤት ለአሁን አመልካች ከተሸጠ በኂላ አንደኛ ተጠሪ የሐራጅ ሽያጩ በሚካሄድበት ጊዜ ግዙፍ የሆነ ጉድለት የተፈፀመ ስለሆነ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት አቤቱታ አቅርበው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ንብረትነቱ የአንደኛ ተጠሪ የሆነው ቤት የተሸጠው ከግምት በላይ ከመሆኑም በላይ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት በማይንቀሣቀስ ንብረት ላይ የተደረገ ጨረታ ሊፈርስ የሚችለው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይንም የማታለልና የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሞ የተገኘ ከሆነና ይህም አቤቱታ በሚያቀርበው ወገን ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ከተረጋገጠ ነው፤ በተያዘው ጉዳይ ተገቢ ያልሆነ ተግባር ተፈጽሟል ቢባል እንኳን አንደኛ ተጠሪ በዚህ ድርጊት ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ ስለሆነ የሐራጅ ሽያጩ እንዲፈርስ የቀረበው አቤቱታ አግባብነት የለውም በማለት ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

አንደኛ ተጠሪ በዚሁ ውሣኔ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የአሁን አመልካችም በክርክሩ ጣልቃ እንዲገቡ ተፈቅዶላቸው ግራ ቀኙን እንደዚሁም የጣልቃ ገቡን ክርክር መርምሮ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 423/መ/ መሠረት ፍ/ቤቱ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ በሚወጣበት ጊዜ ገዥው ንብረቱን ከመግዛቱ በፊት ማወቅ ይገባዋል ተብሎ የሚገመተውን ማንኛውንም ዝርዝር ሁኔታ በትክክል መግለጽ እንዳለበት የተመለከተ ሲሆን ይሁን እንጂ የፍርድ አስፈፃሚው ተወካይ ከተጫራቾች ለሽያጭ የቀረበው ቤት የፍ/ባለእዳ የግል ንብረት ነው ወይስ የመንግሥት በማለት ለቀረበለት ጥያቄ "የቀበሌ ወይም የኪራይ ቤቶች" ሊሆን ይችላል በማለት በሐራጅ ስለሚሸጠው ቤት ትክክለኛውንና አስፈላጊ የሆነውን መረጃ ለገዥዎች አለመስጠቱ እንደዚሁም የአሁን አመልካች በጨረታው ለመሣተፍ ከመጡት ሰዎች ለተወሰኑትም ቢሆን ቤቱን ከአሁን አንደኛ ተጠሪ ላይ የተከራዩት መሆኑን በመግለጽ እንዳይጫረቱባቸው ለዚህም ውለታ ብር 1000(አንድ ሺህ) እንደሚሰጡ ይናገሩ እንደነበር በምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑና በአጠቃላይ ሲታይም በጨረታው ከፍተኛ ዋጋ ሊቀርብ ባለመቻሉና ይህም በቀጥታ ተጎጂ የሚያደርገው ይግባኝ ባይን /የአሁን አንደኛ

ተጠሪን/ ስለሆነ የሥር ፍ/ቤት እነዚህን ግድፈቶች በአግባቡ ሣይመለከት ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ ተገቢ አይደለም በሚል የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ ሽሯል፡፡

በዚህ ላይ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትም ይህንኑ ውሣኔ በመቀበል ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ ለማስለወጥ ሲሆን ይህም ችሎት የሐራጅ ሽያጩ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ያለበት ስለሆነ ሊፈርስ ይገባል ተብሎ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት መወሰኑ ለሰበር ቀርቦ ሊመረመር እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪዎችን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡

በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከላይ የተመለከተው ሲሆን የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ እንደሚከተለው ተመርምሯል፡፡

አንድ የማይንቀሣቀስ ንብረት በፍርድ አፈፃፀም በሐራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሽያጩ አካሄድ ጉድለት የተፈፀመ ስለሆነ ሐራጁ ሊፈርስ ይገባል የሚለው ወገን አቤቱታውን በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት ማቅረብ የሚጠበቅበት ሲሆን የዚህ ድንጋጌ ይዘትም፡-

"በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት የማይንቀሣቀስ ንብረት የተሸጠ እንደሆነ የፍርድ ባለገንዘቡ ወይም ከሽያጩ ገንዘብ ድርሻ ያለው ወይም የንብረቱ ተካፋይ የሆነ ወይም በንብረቱ መሸጥ ምክንያት መብቱ የሚነካ ማናቸውም ሰው በአሻሻጡ ሥርዓት ላይ ግዙፍ የሆነ ጉድለት ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር ወይም የማታለልና የማጭበርበር ተግባር ተፈጽሟል በማለት ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ማመልከቻ ለማቅረብ ይችላል፡፡

ስለሆነም የተጠቀሰው ተግባር በአመልካቹ መብት ላይ ቀጥታ ጉዳት ያደረሰ መሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ሽያጩ እንዲፈርስ ወይም እንዲታገድ ለማዘዝ አይቻልም"፡፡ በሚል ይነበባል፡፡

በተያዘው ጉዳይ አንደኛ ተጠሪ የሐራጅ ሽያጩ ሊፈርስ ይገባል በማለት አቤቱታቸውን ለፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ያቀረቡት በሐራጅ እንዲሸጥ የታዘዘው የቤት ቁጥር 236 ሆኖ ሣለ የተሸጠው ግን የቤ.ቁ. 244 ተብሎ ነው፤ የሐራጅ ሽያጩ በሚከናወንበት ጊዜም ተጫራቾች "ቤቱ የቀበሌ ነው ወይንስ የኪራይ ቤቶች" ብለው ሲጠይቁ አጫራቹ "የቀበሌ ወይንም የኪራይ ቤቶች" ይሆናል ብሎ የተናገረ ከመሆኑም በላይ ቤቱን የገዛው ሰው ሌሎች ተጫራቾች ብልጫ ገንዘብ ሰጥተው እንዳይጫረቱ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ) በቼክ እንደሚሰጣቸው ተናግሯል የሚሉትን በምክንያትነት በመጥቀስ ነው፡፡

በፍርድ አፈፃፀም ማንኛውም ንብረት በሐራጅ እንዲሸጥ በሚወሰንበት ጊዜ የሐራጅ ሥርዓቱ የሚከናወንበት ሁኔታ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 423 ላይ የተዘረዘረ ሲሆን በዚህም ድንጋጌ መሠረት ገፎው በሐራጅ ስለሚሸጠው ንብረት ማወቅ ስለሚገባው ዝርዝር በሐራጅ ማስታወቂያው መጠቀስ እንዳለበት ተመልክቷል፡፡

በፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ክርክር ሲደረግ የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያው የቤ.ቁ. 244 "ን" እንደሚመለከት ለተጫራቾች ይፋ ሆኖ የተሸጠው ግን የቤት ቁጥር 236 ስለመሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ሆኖም ግን በሐራጅ ማስታወቂያው ሽያጩ የሚመለከተው የቤት ቁጥር 244"ን" እንደሆነ ቢጠቀስም በፍርድ አፈፃፀም መምሪያ በኩል የተገመተውና ገፎዎችም እንዲመለከቱት ተደርጎ የተጫረቱት በማስታወቂያው ላይ የተመለከተውን የቤ.ቁ. 244"ን" ሣይሆን ቁጥር 236"ን" እንደሆነም ጭምር መረጋገጡን ተገንዝበናል፡፡ ይህ ሁኔታ በአፃፃፍ ስህተት ምክንያት የተፈጠረ መሆኑን መገንዘብ የሚቻል ሲሆን አንደኛ ተጠሪም በዚህ ስህተት ምክንያት ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 መሠረት ቀጥተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ አላስረዱም፡፡

ሐራጅ አስፈፃሚው ቤቱ የቀበሌ ወይንም የኪራይ ቤቶች ይሆናል ብሎ ስለመናገሩ አንደኛ ተጠሪ ባቀረቧቸው ምስክሮች የተረጋገጠ ቢሆንም ይህ ሁኔታ ተጫራቾችን እንዳይጫረቱ ስለማድረጉና በዚህም ሣቢያ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑ በማስረጃ አላረጋገጡም፡፡ ምክንያቱም ሕጉ በአሻሻጡ ሂደት ግድፈት /irregularity/ እንዳይኖር የሚከላከለውን ያህል ይህ ተፈጽሟል የሚባል ግድፈት በአመልካቹ መብት ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሰ ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር ጨረታው መፍረስ እንደማይገባው እኩል ጥበቃ ስለሚያደርግ ነው፡፡ ንብረቱን የገዙት ተጫራች /የአሁን አመልካች/ ያለ

ተቀናቃኝ ብቻቸውን ለመግዛት ባላቸው ፍላጎት ሌሎች ተጫራቾች እንዳይጫረቱ ለእያንዳንዳቸው ብር 1000(አንድ ሺህ) በቼክ እንደሚሰጡ ቃል ገብተዋል የተባለውን በተመለከተ አንደኛ ተጠሪ ካቀረቧቸው ምስክሮች መካከል የተወሰኑት ይህ ፍሬ ነገር ሲነገር መስማታቸውን በመጠቀስ ለፍ/ቤቱ የምስክርነት ቃል መስጠታቸውን ከመዝገቡ ተረድተናል፡፡

በሌላ በኩልም ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት የተሸጠው በ2ኛ ጨረታ ሲሆን 2ኛ ጨረታ በሚከናወንበት ጊዜም የሐራጅ ሽያጩ የሚደረገው በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 428 መሠረት ነው፡፡ ከዚህ ድንጋጌ አኳያም ንብረቱ የሚሸጠው በሁለተኛው ጨረታ ጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ሁለተኛ የሐራጅ ማስታወቂያ ሲወጣ 44 ሰዎች በጨረታው ተመዝግበው እንደነበር 37 ሰዎች ደግሞ በጨረታው ተካፋይ እንደነበሩና በመጨረሻም 10 ከፍተኛ ዋጋ በሰጡ ተጫራቾች መካከል ፉክክሩ ቀጥሎ አመልካች ብር 101.000/ አንድ መቶ አንድ ሺህ/ በመስጠት ጨረታውን እንዳሸነፉና የቤቱ የግምት ዋጋም ብር 88,830 /ሰማንያ ስምንት ሺህ ስምንት መቶ ሠላሣ/ እንደነበር ከመዝገቡ ተገንዝበናል፡፡

ከዚህም የተረዳነው ለጨረታው ከተመዘገቡት 44 ሰዎች መካከል 37 ሰዎች በጨረታው ተሣትፈው መገኘታቸውና በመጨረሻም 10 ሰዎች ቀርተው ጨረታውን መቀጠላቸው ሲታይ አመልካች ሌሎች ሰዎች እንዳይጫረቱ የብር 1000(አንድ ሺህ) ቼክ ለመስጠት ቃል ገብተዋል ተብሎ በአንደኛ ተጠሪ ምስክሮች የተነገረው ጥርጣሬ ውስጥ የሚገባ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም ሌላ በዚህ ምክንያት አንደኛ ተጠሪ ቀጥተኛ የሆነ ጉዳት የደረሰባቸው ስለመሆኑም አላስረዱም፡፡

ሲጠቃለልም አንደኛ ተጠሪ ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት በምክንያትነት የጠቀሷቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 445 ላይ እንደተመለከተው በመብታቸው ላይ ቀጥተኛ ጉዳት ያደረሱባቸው ስለመሆኑ ያላስረዱ መሆኑን የተገነዘብን ስለሆነ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ አግባብነት ያለው ሆኖ ሣለ ነገር ግን የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት የሥር ፍ/ቤትን ውሣኔ በመሻር የሰጠው ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 21375 በ8/2/98 ዓ.ም ጨረታው ሊፈርስ አይገባም በማለት የሰጠው ውሣኔ በአግባቡ ስለሆነ አጽንተነዋል፡፡
2. የፌዴራል ከ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 42380 ኀዳር 26 ቀን 1999 ዓ.ም ጨረታው ሊፈርስ ይገባል በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሽረነዋል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 35018

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ስላሴ

ሡልጣን አባተማም

**አመልካች**፡- በዛብህ አበበ - ቀረበ፡፡

**ተጠሪ**፡- የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ - ሕይወት ጥላሁን ቀረበ፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

አከራካሪው ጉዳይ ቀደም ሲል በተሰጠው ውሳኔ መሰረት የተጀመረውን የአፈጻጸም ሂደት የሚመለከት ነው፡፡ ከመዝገቡ እንደሚታየው የአፈጻጸሙን ክርክር የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በቀጠሮው ቀን የፍርድ ባለመብት (የአሁኑ አመልካች) ጠበቃ አልቀረበም በሚል ምክንያት በመስጠት መዝገቡን ዘግቷል፡፡ ይህን ተከትሎ የቀረበለትን የመዝገብ ይከፈትልን ጥያቄም ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ ይግባኝ የቀረበለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም መዝገቡ አይከፈትም በመባሉ የተፈጸመ ስህተት(ጉድለት) የለም ብሏል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

ይህ የሰበር ችሎትም አመልካች ጥር 10 ቀን 2000 ዓ.ም በጻፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሰረት በማድረግ ተጠሪን አስቀርቦ ክርክሩን ሰምቶአል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የአፈጻጸም መዝገቡ የተዘጋበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በዚህ መሰረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ (ትእዛዝ) እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው ለአቤቱታው መነሻ የሆነው ትእዛዝ የተሰጠበት መዝገብ ቀደም ሲል የተሰጠውን ውሳኔ ለማስፈጸም ሲባል የተከፈተ ነው፡፡ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መዝገቡን የዘጋው የፍርድ ባለመብቱ ጠበቃ በቀጠሮው ቀን አልተገኘም በሚል ብቻ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ግን ለምን ዝም ብሎ አይጠብቅም ነበር ወይም ተለዋጭ ቀጠሮ አይሰጥም ነበር ሊባል ስለማይቻል በመዝጋቱ ረገድ ስህተት ነበር ማለቱ ተገቢ አይሆንም፡፡ በሌላ በኩል ግን አመልካች እንደፍርዱ/ውሳኔው/ አልተፈጸመልኝም የሚል እስከሆነ ድረስ መዝገቡ ከነጭራሹ አይከፈትልህም (አይንቀሳቀስም) የሚባልበት የሕግ ምክንያት አይኖርም፡፡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 384 እንደተደነገገው የአፈፃፀም ጥያቄ እንደገና ለማንቀሳቀስ የማይቻለው በሕጉ እንደተመለከተው በይርጋ ቀሪ ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ አመልካች ያቀረበው የአፈፃጸም ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ሆኗል አልተባለም፡፡ በመሆኑም ያልተፈጸመ ፍርድ አለ እስከተባለ ድረስ መዝገቡ ተከፍቶ አፈጻጸሙ የማይቀጥልበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አቤቱታ የቀረበበት ትእዛዝ ከዚህ አንጻር ሲታይ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡

## ው ሳ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 20286 ሰኔ 5 ቀን 1999 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ እና ይህን ትእዛዝ በማጽናት በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 57130 ጥቅምት 13 ቀን 2000 ዓ.ም የተሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 348/1/ መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተከፈተው የአፈፃጸም መዝገብ ተከፍቶ(ተንቀሳቅሶ) አፈጻጸሙ ይቀጥል በማለት ወስነናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራን በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 21359

ጥቅምት 28 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሠ ይርጋ

አልማው ወሌ

ፀጋዬ አስማማው

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የኢት/ያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን - ነ/ፈጅ ዝግአለ አሰፋ - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** እነ አቶ ተገኝ ማንደፍሮ /ሁለት ሰዎች/ - አልቀረቡም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የተጀመው በድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር አሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪዎች ከሣሽ፣የአሁኑ አመልካች ደግሞ ተከሣሽ ነበሩ፡፡

የአሁኑ ተጠሪዎች ሠኔ 05 ቀን 1994 ዓ.ም በተፃፈ የክስ ማመልከቻ ተከሣሽ መ/ቤት ቀደም ብሎ ከደንበኞች ከሚሠበሰበው የቆጣሪ ገንዘብ በኮሚሽን እየታሰበ ደመወዝ ሲከፍላቸው ከቆየ በኋላ የአከፋፈሉን ሥርዓት በመለወጥ የኮሚሽን ክፍያውን ከማቋረጡም በተጨማሪ መደበኛ ደመወዝ እንዲስተካከልም የህብረት ስምምነቱ መሠረት ተደርጎ ቃለ ጉባዔ ተይዞ መጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም እንደቅጥር ዘመን ደረጃና ደመወዝ እንዲስተካከል መወሰኑንና ሌሎች መሠል ሠራተኞችም በክልላቸው አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ ክስ አቅርበው በአዋጅ ቁጥር 42/1985 መሠረት የደረጃም ሆነ የደመወዝ መስተካከል የተፈፀመላቸው መሆኑን በመግለጽ ጉዳያቸው አንድና ተመሣሣይ በመሆኑ ትእዛዝ እንዲሰጥላቸው ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ አመልካች በተከሣሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ የገንዘብ አሠባሰብ ሥርዓት ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ መለወጡን በመግለጽ የከሣሾች ደመወዝና የደመወዝ ማስተካከያ ጥያቄ ስድስት ወር ውስጥ ሣይቀርብ ከሁለት ዓመት በኋላ የቀረበ በመሆኑ በይርጋ ቀሪ ሊሆን እንደሚገባ፣ የመጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም ቃለ ጉባዔም በአዲስ አበባና አካባቢው ለሚሠሩት ሠራተኞች የሚሠራ ከመሆኑም በላይ የይርጋ ማቋረጫ ምክንያት ሊሆን እንደማይገባ በመግለጽ ክሱ በብይን ውድቅ ሊሆን ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡ ጉዳዩ የቀረበለት ቦርድም የግራ ቀኙን ክርክር ከተመለከተ በኋላ የተጠሪዎች ክስ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ 162 መሠረት በይርጋ ቀሪ ነው በማለት ወስኖ በዚህ ውሣኔ ያልተስማሙት የአሁኑ ተጠሪዎች ይግባኛቸውን ለድሬዳዋ ከፍተኛ ፍ/ቤት አቅርበው ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኋላ የተጠሪዎች ጥያቄ የውሣኔ ይፈፀምልኝ ሁኖ እያለ በይርጋ መታየቱ አግባብ አይደለም፣ በውሣኔው መፈፀም ዙሪያም ሆነ በውሣኔው ላይ የቀረበ መቃወሚያ ወይም የተያዘ ጭብጥ የለም በማለት ተጠሪዎች በጥያቄአቸው መሠረት በአመልካች ድርጅት ሊፈፀምላቸው ይገባል ሲል የቦርዱን ውሣኔ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ የከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 30 ቀን 1997 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩን በአፈፃፀም ሊታይ የሚገባው ነው፤ ማለቱ የተጠሪዎችን የስር ክስ ማመልከቻ በአግባቡ ያላገናዘበ መሆኑን፣ ለፍ/ቤቱ በይግባኝ ሰሚነቱ በአዋጅ የተሰጠው ስልጣን የቦርዱን ውሣኔ ለመሻር የሚያስችል አለመሆኑን በመዘርዘር ውሣኔው የሥነ-ሥርዓት ሕጉንና በስራ ላይ የነበረውን የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ድንጋጌዎችን ያላገናዘበ ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል በማለት ተከራክሯል፡፡ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ተደርጎም ሠኔ 05 ቀን 2000 ዓ.ም በተፃፈ ማመልከቻ የአመልካችን የሠበር አቤቱታ የቅሬታ

ነጥቦች መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማያሣዩ መሆናቸውን በሥነ-ሥርዓት ጉድለት ብቻ የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት ውሣኔ የሚሻርበት ሕጋዊ ምክንያት የሌለ መሆኑን በመዘርዘር መልሣቸውን አቅርበዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም ጉዳዩን ከመዝገቡ ግልባጭ፣ ከግራ ቀኙ የጽሑፍ ክርክርና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡ እንደመረመረውም የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ መሻሩ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ ለመሻር ምክንያት ከአደረጋቸው ነጥቦች አንዱ ተጠሪዎች ለቦርዱ ያቀረቡት ጥያቄ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ይሠሩ የነበሩት/101/አንድ መቶ አንድ/ ሠራተኞች አቅርበው ያስወሠኑት ውሣኔ መብቱ የሚመለከተን ስለሆነ በክርክሩ ተካፋይ ባንሆንም ተፈፃሚ ሊሆንልን ይገባል የሚል በመሆኑና በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/4/ መሠረትም ተቀባይነት ያለው ነው በሚል ነው፡፡ ይህም የሚያሣየው የተጠሪዎች አቤቱታ ቀጥታ ክስ ሣይሆን የአፈፃፀም ክስ የነበረ ስለመሆኑ ከፍተኛው ፍ/ቤት ማመኑን ነው፡፡

ይሁን እንጂ ተጠሪዎች ለቦርዱ ክሣቸውን ሲመሠርቱ ሌሎች ተመሣሣይ ስራ በአዲስ አበባና አካባቢው የሚሠሩ እነ አቶ አያሌው ልዑልሰገድ /101 ሠዎች/ የተባሉ ሠራተኞች በክልላቸው በሚገኘው የአሠሪና ሠራተኛ ጉደይ ወሣኝ ቦርድ ጥያቄያቸውን አቅርበው ማስወሰናቸውን ከመግለጽ ውጪ በሌሎች ሠራተኞች ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው በግልጽ ዳኝነት መጠየቃቸውን የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡ በሌሎች ተመሣሣይ በሌላ አካባቢ የተሰጠ ውሣኔ እንዲፈፀምላቸው ዳኝነት ጠይቀው የነበሩ ስለመሆኑም ተጠሪዎች ያቀረቡት ክርክር የለም፡፡ ይህ ችሎት መገንዘብ የቻለው የተጠሪዎች ጥያቄ በዋናው ክርክር የተሰጠውን ውሣኔ ቦርዱ እንዲያስፈጽምላቸው የቀረበ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር አለመሆኑን ነው፡፡

በመሠረቱ የአንድ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር አጀማመር "ሥርዓት" በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.378/1/ ስር ተመልክቷል፡፡ የዚህ የሥነ ሥርዓት ድንጋጌ የፍርድ ባለመብት በፍርዱ መሠረት እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ማመልከቻ ለፍ/ቤቱ ሲያቀርብ የፍርድ አፈፃፀም ክርክር እንደሚጀምርና የአፈፃፀም ጥያቄ የቀረበበት ጉዳይ በፍርድ የበሰለ ወይም የተፈረደ ፍርድ መኖሩን የሚያሣይ ማመልከቻ መያዝ እንደአለበት ያስገነዝባል፡፡ በያዝነው ጉዳይ ይህንኑ ሥርዓት አሟልቶ የቀረበ ማመልከቻ ስለመኖሩ የክርክሩ ሂደት አያሣይም፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 5/4/ ለውሣኔው መሠረት ማድረግ ይችል የነበረው የተጠሪዎች ጥያቄ ከላይ በተጠቀሰው የአፈፃፀም ሥነ ሥርዓት አጀማመር ቢሟላ እና ውሣኔውን ለማስፈፀም የእነ አቶ አያሌው ሉዑልሰገድ /101 ሠዎች/ ጉዳይ ተመልክቶ ውሣኔ የሰጠው በአዲስ አበባና አካባቢው የሚገኘው የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የአፈፃፀም የውክልና ሥልጣን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 371 እና 372 መሠረት ሰጥቶት በሆን ነበር፡፡ ከዚህ የውክልና የውሣኔ አፈፃፀም ውጪ ፍርድ ያልሰጠ ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት ወይም ወሣኝ አካል የተሰጠ ፍርድ በራሱ የሚያስፈጽምበት ሥነ ሥርዓት የለም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378/1/ ድንጋጌ የሚያሣየውም የፍርድ ማመልከቻ መቅረብ ያለበት ፍርዱን ለፈረደው ፍ/ቤት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍ/ቤት የተጠሪዎች ጥያቄ የአፈፃፀም ማመልከቻ ነው ቢል እንኳ ፍርዱን ለማስፈፀም የሚያስችለው የሥነ-ሥርዓት መሠረት የለውም፡፡

ከዚህም በላይ የከፍተኛው ፍ/ቤት የቦርድን ውሣኔ የሻረው የስር ክርክሩ በተጀመረበት ወቅት ተፈፃሚነት የነበረው አዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 154/2/ ከሰጠው ስልጣን ውጪ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 188/4/ ድንጋጌ የሚያሣየው አዋጁ ከመጽናቱ በፊት በስር ክርክር ሰሚ አካላት በመታየት ላይ የነበሩ የስራ ክርክሮች በወቅቱ ተፈፃሚነት በነበረው ሕግ መሠረት በተጀመረበት ሥርዓት ፍፃሜ ሊያገኙ እንደሚገባ ነው፡፡ በመሆኑም ከፍተኛ ፍ/ቤት የቦርዱ ውሣኔ የሕግ ስሕተት ያለበት መሆኑን ካመነበት መያዝና ዕልባት ሊያገኝ የሚገባውን ጭብጥ በመመሥረት ለቦርዱ መመለስ ሲገባው የቦርዱን ውሣኔ በመሻር የራሱን ውሣኔ መስጠቱ በሕግ ተለይቶ ስልጣን ባልተሰጠበት ሁኔታ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ ስለሆነም ከላይ በተመለከቱት ምክንያቶች መሠረት የከፍተኛው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረታዊ የሆኑ የሕግ ስህተቶች የተፈፀሙበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በሌላ በኩል ከፍተኛው ፍ/ቤት የቦርዱን ውሣኔ የሻረው በክርክሩ ወቅት መታየትና መወሰን የነበረው ጭብጥ የይርጋ ጥያቄ አለመሆኑን በመግለጽና በአዋጁ ላይ የተመለተው የይርጋ ጊዜም ጉዳዩን የማይመለከት ነው ሲል ነው፡፡

ከዚህም መረዳት የሚቻለው ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪዎችን ጥያቄ የአፈፃፀም ነው በማለቱ ይርጋውንም ከዚሁ አንፃር መመልከቱን ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ችሎት ከላይ እንደገለፀው ጉዳዩ የአፈፃፀም ጥያቄ ሣይሆን የቀጥታ ክስ መሆኑን ተረድቷል፡፡ ጉዳዩ የቀጥታ ክስ ነው ከተባለ ደግሞ አግባብነት ያለው የይርጋ ጊዜ ከአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ሕግ አኳያ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡ የከፍተኛው ፍ/ቤት ጉዳዩ የቀጥታ ክስ መሆኑን በመገንዘብ የይርጋ ክርክሩንም ከዚህ አኳያ በማየት እንደገና እንዲወስን ጉዳዩን መመለሱ ሥነ-ሥርዓታዊ ነው ቢባልም ጉዳዩ ከወሰደው ጊዜ አኳያ የይርጋ ጥያቄውን ይህ ችሎት እንዲመረምር እና ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥ ማድረጉ የሥነ ሥርዓት ሕጉን ዓላማ ሊያሣካ የሚችል ሆኖ በመገኘቱ ጉዳዩን በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

ለተጠሪዎች ደመወዙ በኮሚሽን ይከፈል የነበረው አሠራር ቀሪ የሆነው ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ስለመሆኑ አመልካች ጠቅሶ የተከራከረ ሲሆን ተጠሪዎች ጉዳዩ በእናት መሥሪያ ቤት ተይዞ መቆየቱን ከመግለጽ ውጪ የተለየ የክርክር ነጥብ አላቀረቡም፡፡ በመሆኑም ደመወዙን በኮሚሽን ሲያስከፍል የነበረው አሠራር ቀሪ የሆነው ከ1991 ዓ.ም መጨረሻ ጀምሮ ስለመሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ጊዜው መቆጠር ያለበት ከመጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም ቃለ ጉባዔ ጀምሮ መሆኑንና ለይርጋ ጊዜው አቆጣጠር መቋረጫ የሆነ ሕጋዊ ምክንያት እንዳላቸውም በመጥቀስ ተከራክረዋል፡፡

በመሠረቱ በአዋጅ ቁጥር 42/85 አንቀጽ162/1/ ላይ በግልጽ እንደተመለከተው በቅጥር ላይ ከተመሠረተ ግንኙነት የመነጨ ማንኛውም ክስ የጊዜ ገደቡ በአዋጁ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሕግ በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በቀር የመብቱን ጥያቄ ለማቅረብ ከሚቻልበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ በይርጋ የሚታገድ ይሆናል፡፡ የተጠሪዎች ጥያቄ ደረጃና ደመወዝ እንዲስተካከል ሆኖ ለቦርዱ ክስ የቀረበው ሰኔ 05 ቀን 1994 ዓ.ም የደመወዝ በኮሚሽን የክፍያ አሠራር ከተለወጠ ከሁለት ዓመት በላይ ቆይቶ ነው፡፡ ተጠሪዎች የይርጋ ጊዜ ገደቡ ተፈፃሚነት የለውም በማለት የሚከራከሩት አሠሪው መ/ቤት በገንዘብ ሰብሣቢነት ለተመደቡን ሠራተኞች እንደማንኛውም የድርጅቱ ሠራተኞች እኩል ክፍያ እንድናገኝ በቃለ ጉባዔ ከእናት ማህበራችን ጋር በመደራደር ላይ ስለነበር ከዋናው መ/ቤት እስከሚላክ ድረስ እንድንጠባበቅ በመደረጉ ከአቅም በላይ በሆነ ችግር ነው በማለት ነው፡፡ በእርግጥ የአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌ አንድ የስራ ክርክርን የሚመለከት ክስ የይርጋ ጊዜ አልፎ ቢቀርብ እና ለጊዜው ማለፍ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት መሆኑ በተገቢው ውሣኔ ሠጪ አካል ከተረጋገጠ ክሱ ሊቀርብ የሚችል መሆኑንና የተጠቀሰው ምክንያት በተወገደ በአስር ቀን ውስጥ ካልቀረበ ግን ተቀባይነት የሌለው መሆኑን ያስረዳል፡፡ ይሁን እንጂ ተጠቃሽ ድንጋጌ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሰጠው ትርጉም የለም ድንጋጌው ከአቅም በላይ ሊሠኙ የሚችሉ ምክንያቶችን ያላመለከተ መሆኑም በግልጽ ይታያል፡፡ ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ትርጓሜንና አመላካች ምክንያቶች ምን እንደሆኑ ከፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1792 እና 1793 ድንጋጌዎች አኳያ መመልከት የሚቻል ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት በ/ቁ. 16648 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በዚህም መሠረት የስራ ክርክር ክስ በጊዜው ያልተመሠረተው በፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እና 1793 በተመለከተው አኳኋን መሆኑ ከተረጋገጠ ጊዜው ያለፈበት ክስ ተቀባይነት እንደሚኖረው ተሠምሮበታል፡፡

የአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌ ከ"አቅም በላይ የሆነ ምክንያት" ትርጓሜ ያልሰጠና አመላካች ሁኔታዎችን ያላስቀመጠ ቢሆንም እንደ "በቂ ምክንያት" ተደርገው የሚወሰዱትን ምክንያቶችን አመልክቷል፡፡ እነዚህም ምክንያቶች የሠራተኛው መታመም፣ የሠራተኛው በትእዛዝ ከመደበኛ የመኖሪያ ስፍራ ውጭ መዛወር እና የሠራተኛው ከብሔራዊ ጥሪ ላይ መገኘት መሆናቸውን ገልፃል፡፡ ከድንጋጌው መንፈስ መረዳት የሚቻለውም እነዚህ ምክንያቶች መኖራቸው በበቂና አጥጋቢ ማስረጃ ማረጋገጥ ጊዜው ያለፈበትን የስራ ክርክር ክስ ለመቀበል የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡

በእጃችን ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ ተጠሪዎች ለቦርዱ አቅርበውት የነበረው ክስ አመልካች መ/ቤት ቀድሞ ይከተል የነበረውን የደመወዝ ክፍያ አሠራር በመለወጥ አዲስ አሠራር መከተሉንና ሌሎች ሠራተኞችም በሌላ አካባቢ በሚገኘው ቦርድ ጉዳያቸውን አቅርበው ማስወሰናቸውን መጋቢት 27 ቀን 1993 ዓ.ም በተደረገው ቃለ ጉባዔም አገልግሎታቸውን ያገናዘበ የደመወዝ ማስተካከያ እንዲደረግ በመ/ቤቱ ፐርሶኔል ዳሬክተር ቢሮ ተሰብስበው መወሰኑን ይህ ውሣኔም ከእናት መ/ቤት ምላሽ እስከሚሠጠው እንዲጠባበቁ መደረጉ ከአቅም በላይ "የሆነ" ምክንያት መሆኑን በመጥቀስ የተከራከሩ ሲሆን አመልካች ክሱ በይርጋ ሊታገድ ይገባዋል በማለት ተቃውሞውን አቅርቦ ተከራክሯል፡፡ ከዚህም መገንዘብ የሚቻለው ጉዳይ በእናት መ/ቤት ተይዟል ተብሎ ምላሹን እንዲጠባበቁ መደረጉ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው?

ወይንስ አይደለም? የሚለው ጥያቄ ከላይ ከተሰጠው ትርጉም አኳያ መታየት እና ምላሽ ማግኘት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በመሆኑም ከፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1792 እና 1793 እንዲሁም ከአዋጅ ቁጥር 42/1985 አንቀጽ 166 ድንጋጌዎች መንፈስ አንፃር ሲታይ ጉዳዩ በእናት መ/ቤት ምላሽ እንዲሰጥበት የመባሉ ምክንያት ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ለማለት የሚያስችል አለመሆኑን ይህ ችሎት ያምናል፡፡ ምክንያቱም ክሱ ቀድሞ ሊታሰብ የማይችል እና ተጠሪዎችም ፍፁም የሆነ መሰናክል የገጠማቸው መሆኑን የሚያሣይ፣ይልቁንም በሕጉ መሠረት መብታቸውን በተገቢው የስራ ክርክር ሰሚ አካል ፊት አቅርበው ተገቢውን ዳኝነት ለመጠየቅ ሠፊ እድል የነበራቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በመሆኑም ጉዳዩ በእናት መ/ቤት መያዙ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ነው ተብሎ የሚፈረጅበትን የሕግ መሠረት አላገኘንም፡፡ ከዚህም በላይ ጉዳዩ በእናት መ/ቤት መያዙን የተጠሪዎች አቤቱታ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ እንዲያስፈጽም ስልጣን በተሰጠው አካል ቀርቦ የነበረ በመሆኑ የይርጋ ዘመን አቆጣጠር የሚያቋርጠው ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅን እንዲያስፈጽም ስልጣን የተሰጠው አካል ማን እንደሆነ እና አሠሪ መ/ቤት ወሣኝ አካል አቤቱታ ማቅረብ አዋጅን እንዲያስፈጽም ስልጣን ለተሰጠው አካል አቤቱታ እንደማቅረብ የማይቆጠር ስለመሆኑ ይህ ሰበር ችሎት ከላይ በተጠቀሰው የመ/ቁ. 16648 የሕግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡ በመሆኑም ተጠሪዎች አቤቱታቸውን በአመልካች መ/ቤት የፕሮሶኔል ዳሬክተር ቢሮ በመሰብሰብ አስወስነው ምላሹን ከእናት መ/ቤት በመጠባበቅ የፈፀሙት ድርጊት የይርጋ ጊዜ አቆጣጠርን የሚያቋርጠው ሁኖ ስላላገኘን በዚህ ረገድ ያቀረቡት ክርክር ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ በዚህም መሠረት ቦርዱ የተጠሪዎች ጥያቄ በይርጋ ቀሪ ነው በማለት የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የለበትም ብለናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1/ የድሬዳዋ ፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 00762 ሐምሌ 01 ቀን 1997 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡

2/ የድሬዳዋ ጊዜያዊ አስተዳደር አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ በመ/ቁ. 239/94 ጥቅምት 20 ቀን 1995 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሠረት ፀንቷል፡፡

3/ ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰበር መ/ቁ. 32143

ጥቅምት 18 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ተሻገር ገ/ሥላሴ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** መሐመድ እስማኤል ተርቢ

**ተጠሪ፡-** መሐመድ አሕመድ ኑር

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ በአፈፃፀም ደረጃ ያለውን ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ አመልካች ተጠሪ ገንዘብ ይከፍለው ዘንድ ያስወሰነ የፍርድ ባለመብት ነው፡፡ እንደውሣኔው ለማስፈፀምም የአፈፃፀም መዝገብ አስከፍቶ ገንዘቡን ገቢ ለማድረግ ሲባል የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶበት ገዢ አልተገኘለትም የተባለውን የተጠሪን ቤት እንዲረከብ አሣዝዞአል፡፡ ከመዝገቡ እንዳየነው ተጠሪ በዚህ ላይ ለበላይ ፍ/ቤቶች ይግባኝ አቅርቦ የነበረ ቢሆንም ክርክሩ ተቀባይነት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙን የጀመረው በሶማሌ ብ/ክ/መ/የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የተጠሪን ቤት አመልካች እንዲረከብ በድጋሚ አዟል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የክልሉ ጠቅላይ /ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ተጠሪ እና ሌሎች ስድስት ሰዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርበውልኛል በማለት የቀድሞ ውሣኔውን /የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ውሣኔ በማጽናት ሰጥቶት የነበረውን/ በመለወጥ አመልካች ቤቱን ሊረከብ አይገባም በማለት ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ላይ ነው፡፡

እኛም አመልካች ሐምሌ 24 ቀን 1999 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ክርክሩን ሰምተናል፡፡ ተጠሪ በተደረገለት ጥሪ መሠረት ባለመቅረቡ ክርክሩ እሱ በሌለበት ነው የተሰማው፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው የስር ፍ/ቤት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት የቀረበለትን መቃወሚያ ያስተናገደበትን እና የቀድሞውን ውሣኔ የሻረበትን አግባብ ለመመርመር ነው፡፡ በመሆኑም ይህን ነጥብ ለስር ፍ/ቤቶች ከቀረበው ክርክር፣ ከአመልካች አቤቱታ እና አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እንዲሁም ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምናየው ተጠሪ ለአመልካች የሚከፍለው ገንዘብ አለ ተብሎ የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ ይህን ገንዘብ ለማስከፈል ሲባልም ንብረቱ ነው በተባለው ቤት ላይ የአፈፃፀም ትእዛዝ ተሰጥቷል፡፡ ይህን የአፈፃፀም ትእዛዝ በመቃወም ለሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርቦ የተለየ ትእዛዝ /ውሣኔ/ አሰጥቶ የነበረ ቢሆንም አመልካች ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት ባቀረበው አቤቱታ መነሻነት ክርክር ከተደረገ በኂላ አፈፃፀሙ የከፍተኛው ፍ/ቤት በሰጠው ትእዛዝ መሠረት እንዲቀጥል ተወስኗል፡፡ ይህ ሁሉ ከሆነ በኂላ ነው ተጠሪ ተቀዋሚ በመሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት ለሰበር ችሎቱ አቤቱታ ያቀረበው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት አቤቱታ /መቃወሚያ/ የሚቀርበው ቀደም ሲል የተሰጠን ውሣኔ ለመቃወም ነው፡፡ መቃወሚያውን ማቅረብ የሚችሉትም ቀደም ሲል በተደረገው ክርክር ተካፋይ ያልነበሩት ወገኖች ናቸው፡፡ ተጠሪ ቀደም ሲል በተደረገው የአፈፃፀም ክርክር ተካፋይ የነበረ እና የተወሰነበት ሰው ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በኂላ ተቃዋሚ ሆኖ የሚቀርብበት አግባብ የለም፡፡ ሌሎቹ ሰዎችም ተቃዋሚ ሆነው የቀረቡት የአፈፃፀም ትእዛዝ የተሰጠበት ንብረት

የተጠሪ ብቻ ሣይሆን የውርስ ሃብት ነው በሚል እንደሆነ ከመዝገቡ ተመልክተናል፡፡ በእርግጥ እነሱ እንደሚሉት ንብረቱ የእነሱም የውርስ ሃብት ከሆነ የአፈፃፀም መዝገቡ ለተከፈተበት የከፍተኛው ፍ/ቤት በጊዜው ሊያቀርቡ ይችሉ /ይገባቸው/ ነበር፡፡ በአፈፃፀም በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ መብት አለን ባዮች አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት ሆኖ ማቅረብ ያለባቸውም ሣይዘገዩ እንደሆነ በዚሁ ቁ. 418/1/ ተመልክቶአል፡፡ በያዝነው ጉዳይ እንደምናየው ሰዎቹ አቤቱታቸውን ያቀረቡት አፈፃፀሙን ለያዘው ለከፍተኛው ፍ/ቤት ሣይሆን የመጨረሻ ውሣኔ ለሰጠው ለሰበር ችሎቱ ነው፡፡ ከዚህም በላይ በንብረቱ ላይ ከተጠሪ ጋር የጋራ መብት አለን ባዮች ሆነው ሣለ ተጠሪ በከፍተኛው ፍ/ቤት ከአንዴም ሁለቴ በጠ/ፍ/ቤት እና በሰበር ችሎትም እንደዚሁ በክርክር በቆየበት ጊዜ ተቃዋሚ ሆነው አልቀረቡም፡፡ ይህም ሲታይ ለረዥም ጊዜ በንብረቱ ላይ መብት አለን በማለት መቃወሚያ ሣያቀርቡ ዝም ብለው መቆየታቸውን ያስገነዝባል፡፡ በዚህ ሁኔታ የቀረበን አቤቱታ ፍ/ቤቱ እንደማይመረምረው በተጠቀሰው ድንጋጌ ተመልክቶአል፡፡ በመሆኑም አቤቱታው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418 መሠረት እንደቀረበ ይቆጠር እንኳን ቢባል ያለበቂ ምክንያት በመዘግየቱ የተነሣ የሚመረመርበት የሕግ ምክንያት የለም፡፡ ሰበር ችሎቱ የሰጠው ውሣኔም ከዚህ አንፃር ሲታይ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ሊባል የሚችል ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. አቤቱታ የቀረበበት በሶማሌ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በመ.ቁ. ኤም.ጂ. 12/99 ሰኔ 20 ቀን 99 ዓ.ም የተሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 418/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡
2. በአመልካች እና በተጠሪ መካከል ያለው የአፈፃፀም ጉዳይ የጅጅጋ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 15/95 ሰኔ 26 ቀን 1998 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሠረት ይቀጥል ብለናል፡፡
   መዝገቡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 37503

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሂሩት መለሠ

ታፈሰ ይርጋ

በላቸው አንሺሶ

አልማው ወሌ

**አመልካች**፡- አቶ ወልደዮሐንስ ሀብትየስ - ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- ወ/ሮ ያምሮት ሸዋረጋ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ቀጥሎ የተመለከተው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ይህ ጉዳይ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን የአሁን አመልካች አቶ ተክሉ በቀለ በተባሉ ግለሰብ ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት ክስ የሟች ወ/ሮ እልፍነሽ በቀለ የሕግ ባል ነኝ፡፡ ሟች ባለቤቴ በሕይወት እያለች ሁለት ልጆችን የወለድን ሲሆን በአዲስ አበባ ከተማ በወረዳ 19 ቀበሌ 58 ክልል ባለቤቴ ከባንክ ገንዘብ ተበድራ ቤት ሠርታለች፡፡ ይህም ቤት የሟችና የእኔ የጋራ ቤት ሲሆን ተከሣሽ ምንም መብት ሣይኖራቸው ቤቱን ይዘው የሚገኙ ስለሆነ ለቀው እንዲያስረክቡኝና ኪራይም እንዲከፍሉኝ ይወሰንልኝ በማለት ጠይቀው ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ ከሣሽም ተከሣሽም የሟች ባል እንደነበሩ ተረጋግጧል ካለ በኋላ የቤቱ ግማሽ የሚስት ድርሻ ሆኖ ቀሪውን ግማሹን ደግሞ ሁለቱ የሟች ባሎች ድርሻቸው ስለሆነ በዚሁ መሠረት ከሣሽ የቤቱን ¼ኛው ይገባቸዋል በማለት ውሣኔ ሰጥቷል፡፡

ይህ ውሣኔም በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንደፀና ከመዝገቡ መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በኋላም አመልካች አፈፃፀም ቀጥለው በክርክሩ ሂደት የፍርድ ባለእዳ የነበሩት አቶ ተክሉ በቀለ በመሞታቸው ምክንያት ባለቤታቸው የሆኑት የአሁን ተጠሪ በፍርድ ባለእዳነት ተመዝግበው አፈፃፀሙን የያዘው የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ፍርዱን በምን መልኩ ማስፈፀም እንዳለበት ፍርዱን ለሰጠው ችሎት ማብራሪያ ጠይቆ የቤቱ ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ በመክፈል በዚሁ መልኩ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ አፈፃፀሙን የያዘው ችሎትም በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ቤቶችን የቤት የገበያ ግምት የሚሰጠው የሚመለከተው የአስተዳደር ክፍል ሲሆን በዚሁ መሠረትም የፍርድ አፈፃፀም መምሪያ ከዚሁ አካል ግምቱን አስቀርቦ የባለመብትን ድርሻ ¼ ከባለእዳዎች ላይ ከሚያስከፍል ውጭ ውሣኔውን ከሰጠው ፍ/ቤትና በይግባኝ ሰሚው ፍ/ቤት እንዲፈፀም ከተሰጠው ትእዛዝ በመውጣት በሐራጅ ተሸጦ ለባለመብት እንዲከፈላቸው የሚያደርግበት ሥርዓት ስለሌለ የፍርድ ባለመብት በዚህ መልኩ እንዲፈፀምላቸው ያቀረቡት አቤቱታ ተቀባይነት ስለሌለው በፍርድ አፈፃፀም በኩል የተየዘውን ድርሻቸውን ይውሰዱ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

የፍርድ ባለመብት በዚሁ ትእዛዝ ቅሬታ አድሮባቸው የይግባኝ ቅሬታቸውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ሲሆን የሥር ፍ/ቤት ትእዛዝ ጉድለት የሌለው ነው በማለት ይግባኙን ሠርዟል፡፡

የሰበር አቤቱታውም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ሲሆን ይህ ችሎትም አቤቱታውን መርምሮ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለአመልካች ይከፈላቸው ተብሎ ፍርድ በተሰጠበት ሁኔታ የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ከሚመለከተው አስተዳደር

ክፍል የተላከለትን ግምት መሠረት በማድረግ ፍርዱ እንዲፈፀም በማለት የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ተጠሪ ባሉበት ለሰበር ቀርቦ ሊታይ እንደሚገባው በማመኑ ተጠሪን በመጥራት ግራ ቀኙን አከራክሯል፡፡ በአጠቃላይ የክርክሩ ይዘት ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ሲሆን የሰበር አቤቱታውም ያስቀርባል ከተባለበት ነጥብ አኳያ ተመርምሯል፡፡

ከፍ ብሎ እንደተጠቀሰው የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት ውሣኔ የሰጠው የፍርድ ባለመብት /የአሁን አመልካች/ የቤቱን ወቅታዊ ዋጋ ¼ ሊከፈላቸው ይገባል በማለት ነው፡፡ የከተማው አስተዳደር ቤቱን አስመልክቶ የሚሰጠው የዋጋ ግምትና ወቅታዊ ዋጋ ልዩነት እንዳላቸው መገመት አያዳግትም፡፡ ስለሆነም ፍ/ቤቱ የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ ¼ኛው ለፍርድ ባለመብቱ ሊከፍል ይገባል በማለት ውሣኔ እስከሰጠ ድረስ ወቅታዊ ዋጋውን የሚወስነው በሐራጅ በሚደረግ ሽያጭ ስለሆነ በዚሁ መልኩ ፍርዱን ማስፈፀም ከውሣኔው እንደማፈንገጥ የሚቆጠር አይሆንም፡፡

በሌላ በኩልም በዚህ ችሎት ክርክር ሲደረግ ይሄው ለክርክሩ ምክንያት የሆነው ቤት በሌላ የአፈፃፀም መዝገብ በሐራጅ እንዲሸጥ ታዞ በብር 364,000 ሐምሌ 9 ቀን 2000 ዓ.ም እንደተሸጠ ግራ ቀኙ ወገኖች ተማምነውበታል፡፡ ይህም የቤቱ ወቅታዊ ዋጋ መሆኑን የሚያሣይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስለሆነም የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የሰጠው ትእዛዝ ከፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 373 አኳያ ተገቢነት የሌለውና የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

## ት ዕ ዛ ዝ

1. የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 65156 ኅዳር 27/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤትም በመ.ቁ. 61890 በ16/7/2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ከቤቱ ሽያጭ ላይ ለአመልካች ሊደርሳቸው የሚገባው ¼ኛ ድርሻ ብር 91.000 /ዘጠና አንድ ሺህ/ እንዲከፈላቸው ፍርዱንም የፌዴራል መ/ደ/ፍ/ቤት እንዲያስፈጽም ታዟል፡፡
3. ግራ ቀኙ ወጭና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡
4. መዝገቡ ተዘግቶ ወደ መ/ቤት ተመልሷል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ተ.ወ

የሰ/መ/ቁ. 39175

መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- ወ/ሮ በለጡ ጋሼ - ቀረቡ

**ተጠሪዎች**፡- እነ አንዱአለም ቴድሮስ /3 ሰዎች/ - ጠበቃ ዘውዱ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ነበር፡፡ መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ለሰበር የቀረበው አመልካች የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመዝገብ ቁጥር 4931 የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት እና ሰበር ሰሚ ችሎት ማጽደቃቸው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለበት፡፡ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ስላመለከቱ ነው፡፡

የአቤቱታቸው ምክንያት የከፍተኛው ፍርድ ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው የአፈፃፀም ትእዛዝ ነው፡፡ የከፍተኛው ፍርድ የአሁን አመልካች በፍርድ የሚፈለግባቸውን ገንዘብ ከፍለው ያልቀረቡ በመሆኑ ቀደም ሲል በተሰጠው ትእዛዝ መሰረት ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ይህ ትእዛዝ መሰረታዊ ስህተት አለበት በማለት ይግባኝ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የከፍተኛው ፍርድ ቤት የሰጠውን የአፈፃፀም ትእዛዝ አጽንቶታል፡፡

አመልካች የአፈፃፀም ትእዛዝ መሰረታዊ የሕግ ስህተት አለበት በማለት የሰበር አቤቱታ ለክልሉ ሰበር ችሎት አቅርበው የሰበር ችሎቱ የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የለም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ ቤቱ ሁለት ጊዜ በጨረታ፣እንዲወጣ ሣያደርግ ባለእዳዎች እንዲረከቡት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ ይህም መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው፡፡ የመጀመሪያው ጨረታ፣በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 426 መሰረት ለሰላሣ ቀናት በአየር ላይ ባለመዋሉ ፍርድ ቤቱ ሰርዞ ድጋሜ ጨረታ እንዲወጣ አዝዟል፡፡ ከዚያ በኋላ ቤቱ በህጉ መሰረት ለጨረታ ያቀረበው አንድ ጊዜ ሆኖ እያለ፣ሁለት ጊዜ ለጨረታ ወጥቶ ገዥ እንዳልተገኘ በመቁጥር የተሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት፣ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ሊታረምልኝ ይገባል በማለት አመልክታለች፡፡

ተጠሪዎች በበኩላቸው ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለጨረታ ቀርቦ የነበረ ሲሆን ታህሣስ 4 ቀን 1999 ዓ.ም እና ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ባለመገኘቱ ነው እኛ እንድንረከብ ፍ/ቤቱ ትእዛዝ የሰጠው፡፡ ስለሆነም በህጉ መሰረት የተሰጠ የአፈፃፀም ትእዛዝ ስለሆነ መሰረታዊ የህግ ስህተት የለበትም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካች አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት ቤቱን ይሸጥ ካለ በኋላ ብር 8000(ስምንት ሺ.ህ) በችሎት እንዲከፍል አድርጓል፡፡ ከዚህ በኋላ ቤቱ ይረከቡ ማለት መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት በማለት የመልስ መልስ ሰጥተዋል፡፡ ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም መዝገቡን መርመረናል፡፡ መዝገቡን እንደመረመርነው ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም ለሐራጅ ቀርቦ ነበር በማለት ያቀረቡትን ክርክር

ስንመረምረው፣ቤቱ ለሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣበት ትእዛዝ ከተሰጠ በኋላ በአፈፃፀም የተሰጠው ትእዛዝ መብታችንን ይነካል የሚሉ ጣልቃ ገቦች በመቅረባቸው ጨረታው ሂደት አፈፃፀሙን በያዘው ፍርድ ቤት የእግድ ትእዛዝ በመስጠቱ ምክንያት የተቋረጠ መሆኑን፣የከፍተኛው ፍርድ ቤት መጋቢት 5 ቀን 1998 ዓ.ም ከሰጠው ትእዛዝ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ተጠሪዎች ቤቱ የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የጨረታ ማስታወቂያ ወጥቶበት ለሐራጅ ቀርቧል በማለት ያቀረቡት ክርክር ተገቢነት ያለው ሆኖ አላገኘውም፡፡

ከፍተኛው ፍ/ቤት የጣልቃ ገቦቹን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ የተቋረጠው የሐራጅ ሂደት እንዲቀጥልና ቤቱ ታህሣስ 10 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ እንዲቀርብ፣የጨረታው ማስታወቂያ እንዲወጣ ጥቅምት 20 ቀን 1999 ዓ.ም በሰጠው ትእዛዝ መሰረት የሐራጅ ማስታወቂያው ታህሣሥ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቷል፡፡ ፍርድ ቤቱም የሐራጅ ማስታወቂያው በአየር ላይ ለሰላሣ ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ በፍትሐብሔር ስነ ስርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገ መሆኑን በመግለጽ ይህንን ስርአት ባሟላ መልኩ ቤቱ በሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ለሐራጅ ሽያጭ እንዲቀርብ ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ የሐራጅ ማስታወቂያውም ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ ገዥ አልቀረበም ስለዚህ ቤቱን እንድንረከብ በማለት የፍርድ ባለመብት በጠየቁት መሰረት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ በማለት ጥር 24 ቀን 1999 ዓ.ም ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

ከዚህ በኋላ የከፍተኛው ፍርድ ቤት የፍርድ ባለመብት የሆኑት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ በተደጋጋሚ ትእዛዝ ሲሰጥ ቆይቶ ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም አመልካች በፖሊስ ተይዘው እንዲቀርቡ አድርጓል፡፡ በዚህ ቀን አመልካች ብር 8000(አምስት ሺህ ብር) የከፈለ ሲሆን ቀሪውን እዳ አጠቃልላ ከፍላ እንድትቀርብ በማለት ለሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡ አመልካች ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም እዳውን አጠቃልለው ከፍለው ባለመቅረባቸው፣የከፍተኛው ፍ/ቤት የፍርድ ባለመብት ቤቱን እንዲረከቡ የሚል ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡

አፈፃጸሙን የያዘው የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ ትእዛዝ የሰጠው በሕጉ የተቀመጠውን፣ሥርዓት በማሟላት አይደለም፡፡ ምክንያቱም የካቲት 30 ቀን 1998 ዓ.ም የተደረገውን የሐራጅ ሒደት ራሱ ፍርድ ቤቱ አግዶታል፡፡ ከዚህ በኋላ የሚከናወኑ የሐራጅ ሂደቶች እንደ አዲስ መደረግ ያለባቸው ናቸው፡፡ ጥር 10 ቀን 1999 ዓ.ም የተከናወነው፣ሐራጅ የሐራጅ ማስታወቂያው ጥር 3 ቀን 1999 ዓ.ም ወጥቶ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 የተደነገገውን አስገዳጅ ስርአት ያላሟላና የሐራጅ ማስታወቂያው ሰባት ቀን ብቻ በአየር ላይ ውሎ የተፈፀመ በመሆኑ ፍርድ ቤቱ ይህ ስርአት ያልተሟላ መሆኑን በማየት ሰርዞታል፡፡

ቤቱ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 426 መስፈርት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶ ለሐራጅ ያቀረበው አንድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ የፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 መሰረት የፍርድ ባለመብቱ እንዲረከብ የሚያደርገው የሕጉን ስርአት በተከተለና ባሟላ ሁኔታ ሁለት ጊዜ የሐራጅ ማስታወቂያ ወጥቶና ቤቱ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ ሣይገኝ ሲቀር ብቻ ነው፡፡ በያዝነው ጉዳይ ቤቱ በትክክለኛው መንገድ ለሐራጅ የቀረበው ጥር 23 ቀን 1999 ዓ.ም ብቻ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ቤቱ በድጋሚ ለሐራጅ እንዲቀርብና የሕጉን ስርአት ባሟላ ሁኔታ የሐራጅ ማስታወቂያ እንዲወጣ ሣያደርግ ቀደም ብለው ያወጣውንና የህጉን አስገዳጅ ሁኔታ የማያሟላውን የሐራጅ ስርአት፣ እንደትክክለኛ ሐራጅ በመቁጠር ቤቱ ሁለት ጊዜ ለሐራጅ ቀርቦ ገዥ አላገኘም በማለት ተጠሪዎች ቤቱን እንዲረከቡ የሰጠው ትእዛዝ በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ሕግ ቁጥር 428 ንኡስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ የሚጥስ በመሆኑ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የስር ፍርድ ቤት ተጠሪዎች ቤቱን ይረከቡ በማለት የሰጠውን ትእዛዝ በመተው አመልካች እዳቸውን በጥሬ ገንዘብ እንዲከፍሉ የፈቀደና በዚህም መሰረት አመልካች ሰኔ 8 ቀን 1999 ዓ.ም ስምንት ሺ ብር/8000/ በችሎት የከፈሉ መሆኑን የፍርድ ቤቱ ትእዛዝ ያሣያል፡፡ ከዚህ በኋላ አፈፃጸሙ በማይንቀሣቀስም ንብረት ላይ እንዲቀጥል ለማድረግ ካስፈለገ፣የአፈፃፀም ስርአቱን እንደ አዲስ በቤቱ ላይ እንዲቀጥልና የሐራጅ ማስታወቂያ ማውጣት ሲገባው የተተወና የተቋረጠውን የአፈፃፀም ስርአት በማስታወስ ቤቱን ተጠሪዎች እንዲረከቡ በማለት የሰጠው ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ ግድፈት ያለበት ነው፡፡ በመሆኑም የከፍተኛ ፍርድ ቤት አፈፃፀሙን ሲመራ የጣሳቸውን አስገዳጅ የስነ-ሥርአት ድንጋጌዎች እያሉ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎትና ሰበር ችሎት ትእዛዙን ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው በማለት ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ሐምሌ 18 ቀን 1999 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ ሙሉ በሙሉ ተሽሯል፡፡
2. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
3. የሲዳማ ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች በፍርድ የተወሰነባቸውን የቀረባቸውን እዳ ለመክፈል የሚችሉ ከሆነ እንደ ክሱ እንዲያደርግ አመልካች እዳውን ለመክፈል ካልቻሉ፣ቤቱ የሕጉን ሥርአት በጠበቀ ሁኔታ በሐራጅ ተሸጦ የተጠሪዎች እዳ እንዲከፈል ያደርግ ዘንድ ጉዳዩን በፍትሐብሔር ሥነ ሥርአት ህግ ቁጥር 343/1/ መሰረት መልሰን ልከንለታል፡፡
4. በዚህ ፍ/ቤት ያወጡትን ወጭና ኪሣራ ለየራሳቸው ይቻሉ፡፡

ይህ ፍርድ በፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት መጋቢት 24 ቀን 2001 ዓ.ም በሙሉ ድምጽ ተሰጠ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰ/መ/ቁ. 39485

መጋቢት 17 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ታፈሰ ይርጋ

ፀጋዬ አስማማው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** የህፃን ሰላማዊት ቴዎድሮስ ሞግዚት - ወ/ሮ ፍርቱና ገ/መድህን ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** መምህር ሚካኤል ግደይ - የቀረበ የለም፡፡

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የፍርድ አፈፃፀምን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ አመልካች በ17/07/1999 ዓ.ም በፃፉት የአፈፃፀም ክስ በ06/07/1999 ዓ.ም በተሰጠው ውሣኔ መሰረት እንዲፈጸምላቸው ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀው በአሁኑ ተጠሪ ላይ በማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመሰረቱት የአፈፃፀም ክስ መነሻ ሲሆን የአሁኑ ተጠሪም በፍርድ ባለእዳነታቸው ቀርበው ፍርዱን እንዲፈጽሙና የማይፈጽሙበት ምክንያት ካለም እንዲያስረዱ ተደርገው በዋናው ጉዳይ በተሰጠው ውሣኔ መሰረት መኪናዋን ለፍርድ ባለመብት ለሆኑት ለአሁኗ አመልካች እንዲያስረክቡ ታዝዞ አረካካቢ አካልም ተመድቦና መኪናዋ ላይ ጉድለዋል የሚባሉትን እቃዎችን ከዋጋ ግምት ዝርዝር ጋር ለፍ/ቤቱ እንዲገልጽ ተደርጐ ይኸው ከተፈፀመ በኂላ የአፈፃፀም ከሣሽ የነበሩት አመልካች መኪናዋን ከእነጉድለቷ ተረክበዋል፡፡ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤትም በመኪናዋ ላይ ጉደሉ የተባሉት እቃዎች በውሣኔ መኪናዋ ላይ እንዳሉ አረጋግጦ መወሰኑንና የጐደሉትም መኪናዋ በአፈፃፀም ተከሣሽ እጅ እንዳለች በርክክቡ ወቅት መሆኑን አረጋግጦ በርክክቡ ወቅት ጉድሎ የተገኙትን ዝርዝር ንብረቶች በአይነታቸውና በብዛታቸው የሚጨርሱትን ዋጋ በዋጋ ማቅረቢያ ፕሮፎርማ ከሦስት የተለያዩ ድርጅቶች እንዲሰባሰብ አድርጐ ጉደሉ የተባሉት የመኪና እቃዎች ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን አረጋግጦ ይህንኑ ገንዘብ አፈፃፀም ተከሣሽ ለአፈፃፀም ከሣሽ እንዲተኩላቸው በማለት ትእዛዝ ሰጥቷል፡፡ በዚህ ትእዛዝ የአሁኑ ተጠሪ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለትግራይ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኛቸውን አቅርበው ይኸው ፍ/ቤት ግራ ቀኙን ከአከራከረ በኂላ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ጉደሉ በተባሉት የመኪና እቃዎች ላይ የሰጠው ትእዛዝ መኪናዋ በቀጥታ ክስ ጊዜ ተገምታ የቀረበችበትንና በውሣኔው ላይም መኪናውን ከሣሽ ትረከብ ተብሎ ከተወሰነው ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ አፈፃፀሙ የተመራው ከስነ ስርአት ውጪ መሆኑን ጠቅሶ ጉደሉ ለተባሉት የመኪናዋ እቃዎች የአሁኗ አመልካች ሊከፍላት የሚገባው የገንዘብ መጠን በዋናው ክስ ጊዜ የተጠቀሰው ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ነው በማለት የስር ፍ/ቤትን ትእዛዝ በመሻር ወስኗል፡፡ የአሁኗ አመልካች በዚህ ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን ለክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት ስላላገኙ በዚህ ችሎት የሰበር አቤቱታቸውን አቅርበዋል፡፡

አመልካች ሐምሌ 21 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት 2/ሁለት/ ገጽ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍ/ቤቶች ትእዛዝ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉባቸውን ምክንያቶችን ዘርዝረው አቅረበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ በዋናው ጉዳይ በተወሰነው ውሣኔ መኪናዋን እንዲረከብ የሚል ሆኖ እያለና በርክክቡ ወቅትም የመኪናዋ እቃዎች በተጠሪ መጉደላቸው የተረጋገጠ መሆኑን አፈፃፀሙን የያዘው የስር ፍ/ቤት በገለፀበት ሁኔታ በዋናው ክስ ላይ የመኪናዋን ዋጋ ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ብለሽ ገምተሻል ተብሎ የእቃዎችን የገበያ ዋጋ ባላገናዘበ መልኩ የስር ፍ/ቤት ትእዛዝ መሻሩ ያላግባብ ስለሆነ ሊታረም ይገባዋል በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ

ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል ተብሎ የግራ ቀኙ የቃል ክርክር የካቲት 26 ቀን 2001 ዓ.ም በዋለው ችሎት ተደምጧል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር አጠር ባመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የግራ ቀኙን ክርክር የሰበር አቤቱታው ከቀረበበት ትእዛዝና አግባብነት ካላቸው የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መረምረናል፡፡ እንደመረመርነውም የመኪናዋ ርክክብ ሲፈጸም መጉደላቸው የተረጋገጡትን እቃዎችን ለመተካት የታሰበው የእቃዎች ዋጋ ውድቅ ሁኖ የእቃዎቹ ዋጋ ሊሆን የሚገባው የዋናው ጉዳይ ክስ ሲመሰረት በአመልካች የተገለፀው ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ የተቻለው የአሁኗ አመልካች በቀጥታ ክስ ወቅት መኪናውን የገመቱት በብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ሁኖ የጠየቁት ዳኝነት መኪናዋን እንዲረከቡ ይወሰንላቸው ዘንድ መሆኑን፣በቀጥታ ክስ ወቅት የተሰጠው ውሣኔም አመልካች መኪናዋን እንዲረከቡ የሚል መሆኑንና በአፈፃፀም ወቅት አመልካች መኪናዋን ሲረከቡ የጐደሉት የመኪና እቃዎች ተረጋግጠው በወቅቱ የገበያ ዋጋም የጐደሉትን እቃዎች ለመተካት ዝቅተኛው የጨረታ ዋጋም ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ብር) መሆኑን ነው፡፡

በመሰረቱ የአፈፃፀም ክስ የሚቀርበው በውሣኔው መሰረት እንዲፈጸም ስለመሆኑ ከ1958ቱ የፍትሐብሔር ሥነ ስርአት ህግ ሰባተኛ መጽሐፍ ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመመልከት የምንገነዘበው ጉዳይ ነው፡፡ አከራካሪውና ምላሽ የሚያስፈልገው ጉዳይ በቀጥታ ክስ ወቅት የተገመተ የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቀት ንብረቱ በዓይነት ካልተገኘ እና ንብረቱን በዓይነት ለመተካት የንብረቱ ዋጋ ቀድሞ ከተገመተው ግምት በልጦ ሲገኝ አፈፃፀሙ ሊሆን የሚገባው በቀድሞው ግምት ወይስ ንብረቱን በዓይነት ለመተካት በሚያስችል የወቅቱ ተገቢ ዋጋ? የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ሊገኝ የሚችለው በቀጥታ ክስ ወቀት የተሰጠውን ውሣኔ እና የገበያን ተለዋዋጭ ባህርይ ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ሲቻል ነው፡፡ እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ የመስጠት ሥልጣን ያለው መሆኑም ሊስተዋል ይገባል፡፡ በመሆኑም በቀጥታ ክስ ወቀት የነበረው የንብረት ግምት በአፈፃፀም ወቅት ንብረቱ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረበት ሁኔታ ጉድሎ መገኘቱ ከተረጋገጠ በዓይነት ለፍርድ ባለመብቱ እንዲያስረክብ እስከተወሰነ ድረስ የጐለውን የንብረቱን ክፍል እንዲተካ ማድረግ በዋናው ፍርድ ከተሰጠው ውሣኔ ውጪ ሊባል የሚችልበት ምክንያት የለም፡፡ የመኪና እቃዎች ዋጋ ከፍና ዝቅ የሚል መሆኑ እየታወቀም አንዴ ተገምቶ የቀረበ ዋጋ ሁል ጊዜ ተቀባይነት አለው ለማለት አይቻልም፡፡ የፍርድ ባለመብት ንብረቱን በዓይነት እንዲረከብ ከተወሰነ እና የፍርድ ባለእዳው እንደፈርዱ የማይፈጽምበት ምክንያት ያለመኖሩ ሲረጋገጥ የፍርድ ባእዳው ንብረቱን በዓይነት እንዲያስረክብ፣ በዚህ ወቅትም ለአፈፃፀሙ ተስማሚ የሆነ መንገድ መከተል የፍርድ አፈፃፀም ስርአት የግድ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ ውጪ አንድ ፍርድ ለፍርድ ባለመብት እንደፍርዱ ተፈጽሞለታል ለማለት አይቻልም፡፡ በመሆኑም በትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት ለክርክሩ ምክንያት የሆነችው መኪና ጐደሉ የተባሉትን እቃዎች በተመለከተ ለአመልካች እንዲተካላቸው ፕሮፎርማ እንዲሰባሰብ በማድረግ ዝቅተኛው ዋጋ እንዲከፈል ማድረጉ የአፈፃፀም ክስ አቀራረብና የአፈፃፀም ውሣኔ አሰጣጥ ሥርአትን ባልተከተለ አኳኋን ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ ይልቁንም የዚህ ፍ/ቤት አካሄድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለቱትን ድንጋጌዎችንና መኪናዋ በፍርድ ባለእዳ እጅ በነበረችበት ወቅት እቃዎቹ የመጉደላቸውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው፡፡ ጉዳዩን በይግባኝ የተመለከተው የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ውሣኔ ግን አመልካች በዋናው ፍርድ መኪናዋን እንዲረከቡ የተወሰነውን ውሣኔ እና የመኪና እቃዎች የገበያ ዋጋን ተለዋዋጭነት እንዲሁም አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ለአፈፃፀሙ ተስማሚ በሆነ መንገድ ፍርዱ እንዲፈጸም ትእዛዝ ለመስጠት ስልጣን ያለው መሆኑን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 392/1/ ያስቀመጠውን መንገድ ያላገናዘበ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ችሎትም ይግባኝ ሰሚው ችሎት የሰጠውን ትእዛዝ ሣያርም መቅረቱ ባግባቡ ሁኖ አልተገኘም፡፡ ሲጠቃለልም መጋቢት 06 ቀን 1999 ዓ.ም በተሰጠው ዋና ውሣኔ ላይ የሰሌዳ ቁጥር ትግ 03-00778 መኪና አመልካች እንዲረከቡ ከተወሰነ በኋላ በአፈፃፀም ደግሞ መኪናውን ሣይሆን ብር 30,000.00(ሰላሳ ሺህ ብር) ይከፈላት ተብሎ መወሰኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 378 እና 392 ስር የተመለከቱትን ድንጋጌዎች ባላገናዘበ መልኩ በመሆኑ ውሣኔው መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በትግራይ ብ/ክ/መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ. 23377 ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በዚሁ ፍ/ቤት ሰበር ችሎት በፍ/መ/ቁ. 25095 ሰኔ 26 ቀን 2000 ዓ.ም በትእዛዝ የፀናው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. የትግራይ ብ/ክ/መንግስት የማእከላይ ዞን ከፍ/ፍ/ቤት በመ/ቁ. 08699 የካቲት 17 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ትእዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ፀንቷል፡፡
3. ለጐደሉት የመኪና እቃዎች ለተጠሪ ለአመልካች ብር 66,520.00(ስልሳ ስድስት ሺህ አምስት አቶ ሃያ ብር) ሊከፍሉ ይገባል ብለናል፡፡
4. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ

የሰበር መ/ቁ. 38041

መጋቢት 22 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** ታደሰ ገ/መስቀል - ወኪል በላይነሽ ሽፋው ቀረበች

**ተጠሪዎች**፡- 1/ ሙሉጌታ ዘካርያስ

2/ ወ/ሮ አበቡ ገበያው

3/ መሐመድ ይማም - ወኪልም ነው ቀረበ

4/ ዘውዴ ይማም

5/ ወ/ሮ ሩቅያ ይማም

6/ ወ/ሮ ዘይነባ ይማም

7/ ወ/ሮ አሚናት ይማም

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ በአፈፃፀም ደረጃ ያለ የፍትሐብሔር ክርክር የሚመለከት ነው፡፡ የጉዳዩ ታሪክ እንደሚያመለክተው በውርስ ንብረት ክፍፍል መነሻነት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በአንድ በኩል፣ ከሦስተኛ እስከ ሰባት ድረስ ያሉት ተጠሪዎች ደግሞ በሌላ በኩል በመሆን ክርክር ከተደረገ በኂላ፣ በወቅቱ ከሣሾች የነበሩት ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ያሉት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ አስወስነው የፍርድ ባለመብት ሆነዋል፡፡ ይህን ውሣኔ መሠረት በማድረግም የአፈፃፀም መዝገብ ያስከፈቱ ሲሆን፣ በዚህን ጊዜም አመልካችንም የአፈፃፀም ተከሣሽ አድርገውት እንደነበር እና ፍ/ቤቱ ግን አመልካች ተከሶ የተፈረደበት የፍርድ ባለእዳ አይደለም በማለት ከአፈፃፀም ክሱ ውጪ እንዳደረገው ተገንዘበናል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አመልካች ለአንደኛ እና ለሁለተኛ ተጠሪዎች ገንዘብ አበድሮ የነበረ በመሆኑ እና የውርስ ሃብት ነው ተብሎ ተጠሪዎች የሚከራከሩበት ቤትም በመያዣ ይዞ ስለነበር ይህን የብድር እና የመያዣ ውል መነሻ በማድረግ በአንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን በመክሰስ ቤቱን እንዲረከብ በፍ/ቤት አስወስኖአል፡፡ አመልካች ይህን ውሣኔ ያሰጠው በ1993 ዓ.ም ሲሆን፣ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በአንደኛ እና በሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ ያስወሰኑት በ1997 ዓ.ም እንደሆነ መዝገቡ ያመለክታል፡፡

አመልካች በአፈፃፀም መዝገቡ ተጣምሮ መከሰሱን እንዳየ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ቤቱን በተመለከተ ያሰጡት ውሣኔ መኖሩን ስላወቀ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 358 መሠረት መቃወሚያ አቅርቦ ክርክር ከተካሄደ በኂላ ቤቱ በመያዣ የያዘው ከመሆኑም በላይ፣ በፍርድም ለሱ ይገባል ስለተባለ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ ለተጠቀሱት ተጠሪዎች ሊሰጥ አይገባም በሚል ተወስኖለታል፡፡ በዚህም በተጠሪዎች መካከል በተደረገው ክርክር መሠረት

ተሰጥቶ የነበረው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ ከዚህ በኋላ ከሦስተኛ እስከ ሰባተኛ ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 360/2/ መሠረት የተሰጠውን ውሣኔ በመቃወም በአማራ ብ/ክ/መ/ ለደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ አቅርበው የነበረ ሲሆን፣ በስር ወረዳ ፍ/ቤት የተሰጠው ውሣኔ ጉድለት የለበትም በሚል ይግባኛቸው ሣይስተናገድ ቀርቶአል፡፡ በመጨረሻም አመልካች እና አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎችን መልስ ሰጭ በማድረግ ለክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ይግባኝ በማቅረባቸው በዚህ ደረጃም ክርክሩ ተሰምቶአል፡፡ በመቀጠልም ፍ/ቤቱ በበታች ፍ/ቤቶች የተሰጡትን ውሣኔዎች በመሻር አመልካች በቤቱ ላይ መብት የለውም፡፡ ቤቱ በተጠሪዎች መካከል ይከፋፈል በማለት ወስኖአል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ላይ ነው፡፡

በበኩላችንም አመልካች ግንቦት 26 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፈው ማመልከቻ ያቀረበውን አቤቱታ መሠረት በማድረግ ተጠሪዎችን አስቀርበን ክርክሩን ሰምተናል፡፡ አቤቱታው በሰበር ችሎት እንዲታይ የተወሰነው አመልካች ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 ክርክር ባስነሣው ቤት ላይ የሰጠው ውሣኔ በይግባኝ ባልተሻረበት ሁኔታ የጠ/ፍ/ቤቱ በተጠሪዎች መካከል የነበረውን ክርክር ሲመረምር በመ.ቁ. 14/93 ላይ የተሰጠውን ውሣኔ የመሻሩን አግባብነት ለመመርመር ተብሎ ነው፡፡ በዚህ መሠረትም ይህን ነጥብ ከግራ ቀኝ ወገኖች ክርክር፣ አቤቱታ ከቀረበበት ውሣኔ እና ከሕጉ ጋር አገናዝበን መርምረናል፡፡

እንደምንመለከተው አመልካች በመ.ቁ. 14/93 ጥር 24 ቀን 1993 ዓ.ም ባስወሰነው መሠረት ለክርክሩ መንስኤ በሆነው ቤት ላይ የፍርድ ባለመብት ሆኖአል፡፡ ውሣኔው የተሰጠው ከሱ ገንዘብ በተበደሩት እና ቤቱንም በመያዣ በሰጡት አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች ላይ በመሠረተው ክስ መነሻነት ነው፡፡ ይህ ፍርድ ለየትኛውም ፍ/ቤት በይግባኝ ቀርቦ አልተሻረም፡፡ ከሦስት እስከ ሰባት ድረስ የተጠቀሱት ተጠሪዎች ይህን አመልካች በመክሰስ በቤቱ ላይ መብት አላገኙም፡፡ ከዚህ የተነሣም አመልካች ቤቱን ያስረክባቸው ዘንድ የሚያስገድዱበት ምንም የሕግ ምክንያት የለም፡፡ አመልካች በቤቱ ላይ ያገኘው በፍርድ ላይ የተመሠረተ የባለቤትነት መብት በተመሣሣይ ሁኔታ በፍርድ ሃይል እስካልተነሣ ድረስ ምን ጊዜም የቤቱ ባለቤት ሆኖ የሚቀረው አመልካቹ ነው፡፡

የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በስር ወረዳ ፍ/ቤትም ሆነ በከፍተኛ ፍ/ቤት በተሰጠው አመልካችን የቤቱ ባለቤት ባደረገው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አልቀረበለትም፡፡ ቤቱ የአመልካች አይሆንም በማለት የወሰነው በይግባኝ ያልቀረበለትን ውሣኔ ተፈፃሚነት የሚኖረው ውሣኔ አይደለም የሚል ትችት በመስጠት እንደሆነ ከውሣኔው ይዘት ለመገንዘብ ችለናል፡፡ በመሠረቱ በሕግ አግባብ በፍ/ቤት የተሰጠን ውሣኔ የሞራልን ወይም የሕሊናን አስተሳሰብ መሠረት በማድረግ ዋጋ አልባ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ በየትኛውም መለኪያ ተቀባይነት የሚኖረው አይደለም፡፡ በተያዘው ጉዳይ እንደሚታየው አንደኛ እና ሁለተኛ ተጠሪዎች በክስ እንደሌሎቹ ተጠሪዎች በቤቱ ላይ የውርስ መብት እንደነበራቸው ተመልክተዋል፡፡ ቤቱን ለብድር በመያዣነት ለአመልካች የሰጡትም በእነሱ እጅ ስለነበረ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ለምን እነሱ ብቻቸውን በመያዣነት ሰጡ ብሎ መጠየቁም አግባብ ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ከዚህ ሁሉ በፊት አመልካች ቤቱን በፍርድ የሱ እንዲሆን አድርጓል፡፡ በመሆኑም ሌሎችም የውርስ መብት አላቸው ስለተባለ ብቻ ያለምንም ሕጋዊ ምክንያት ፍርዱ ተፈፃሚ እንዳይሆን ወይም ማምከን አይቻልም፡፡ ሲጠቃለል የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በዚህ ረገድ የሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. የአማራ ብ/ክ/መ/ጠ/ፍ/ቤት በመ.ቁ. 311/2000 ግንቦት 12 ቀን 2000 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁ. 348/1/ መሠረት ተሽሮአል፡፡ የደቡብ ወሎ መስተዳደር ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የደሴ ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት የሰጡአቸው ትእዛዝና ውሣኔ ፀንተዋል፡፡
2. አመልካች ጥር 24 ቀን 93 ዓ.ም በመ.ቁ. 14/93 በተሰጠው ውሣኔ በቤቱ ላይ ባለመብት ስለሆነ ለተጠሪዎች ሊያስረክብ አይገደድም ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ በተመለከተ ግራ ቀኝ ወገኖች የየራሣቸውን ይቻሉ፡፡ መዝገቡ ይመለስ፣፣

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ተ.ወ

## የሰበር ችሎት የህግ ትርጉም የሰጠባቸው ውሣኔዎችን /ከቅጽ 1 - 7 / ዝርዝር የሚያሳይ ሰንጠረዥ

**ቅጽ - 1**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | 18180 | የኬ.ኬ ብርድ ልብስ ፋብሪካ መሰረታዊ ሰራተኞች ማህበር እና የኬ.ኬ ጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ | የአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ የዳኝነት ስልጣን፣ የሰራተኛ ቅነሳ ጉዳይን በሚመለከት ስለሚነሳ ክርክር<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 138(1),147 | ሐምሌ 29/1997 |
| 2 | 15493 | አቶ ጳውሎስ ሩምቾ እና ወ/ሮ ጫልቱ መርዳሳ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845,2024 | ሐምሌ 29/1997 |
| 3 | 17361 | ወ/ሮ ጋዲሴ ኢርጌ እና ወ/ሮ ወርቅአንጥፉ በቀለ | በስነ-ስርዓት ህጉ የጊዜ ገደብን በሚመለከት የተቀመጡ ድንጋጌዎችን ፍ/ቤት በራሱ አነሳሽነት ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.49, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856 | ሐምሌ 25/1997 |
| 4 | 17352 | ዋዜማ የልብስና ሽራ ምርቶች ኃ/የተ/ የግ/ ማህበር እና የነገው ሰው ትምህርት ቤት | ተገቢው ዳኝነት ክፍያ ሳይፈፀም በፍ/ቤት በቀጠለ ክርክር ስለሚፈፀም ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.215,320(2),207,211(2) | ሐምሌ 28/1997 |
| 5 | 14605 | የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት እና እነ ኮሜት ትራንስፖርት ድርጅት (ስድስት ሰዎች) | በመንገዝ ላይ የነበሩ ዕቃዎች መጎዳት በሰው ላይ ሊደርስ ይችል የነበረን የግጭት አደጋ ለማስወገድ በተወሰደ ርምጃ የደረሰ የመኪና መገልበጥ ከዓቅም በላይ በሆነ ምክንያት የደረሰ ጉዳት ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 590,591, የፍ/ብ/ህ/ቁ.1792 | ሐምሌ 29/1997 |
| 6 | 17068 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ሚ/ር ቢሮኒ አቲክፖ | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1856,2024, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 89 | ሐምሌ 19/1997 |
| 7 | 14974 | ወ/ት ማህሌት ገ/ስላሴ እና እነ አቶ መንግስቱ (ሁለት ሰዎች) | አንድ ተወካይ በወካዩ ላይ ባቀረበው ክስ ወካዩን ወክሎ መከራከር ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2188, 2189, 2208, 2209, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 57,58 | ሐምሌ 28/1997 |
| 8 | 14184 | አቶ ውርጌሳ ታደሰ እና እነ አቶ መለሰ ተካ (ዘጠኝ ሰዎች) | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 73 | ሐምሌ 29/1997 |
| 9 | 14047 | ዶ/ር ዳንኤል አለሙ እና እነ ወ/ሮ ሮማን ወርቅ የማነብርሃን (ሦስት ሰዎች) | በህግ ግምት የሚሸፈንን የፍሬ ነገር ክርክር በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያነሱትም ፍ/ቤቱ የህግ ግምቱን ተፈፃሚ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1856, 2024 | ሐምሌ 28/1997 |
| 10 | 15835 | ሼል ኢትዮጵያ አ/ማ እና ወ/ሮ አስቴር ብርሃነ ስላሴ | ጉዳዩ መልስ ለመቀበል በተቀጠረ ቀን የተከሳሽ አለመቅረብ ስለሚኖረው ውጤት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70,233 | ሐምሌ 29/1997 |
| 11 | 15992 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና ወ/ት ሶስና አስፋው | በህግ የተደነገገው የውል አፃፃፍ /ፎርም/ የተሰጠ ደንብ አለመፈፀም ስለሚያስከትለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719, 1720 (1), 1723, 1726, 1727, 1845 | ሐምሌ 19/1997 |
| 12 | 17191 | ወ/ሮ አስቴር አርአያ እና አቶ ግርማ ወይጆ | በአንዳንድ ውሎች የተመለከተን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ለመቀነስ ፍ/ቤት ስላለው ስልጣን<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711, 1731, 1676(2), 2635, 2640, 2646 | ሐምሌ 29/1997 |

**ቅጽ 2**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 13 | 13223 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና አቶ አስፋው አበበ | ይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት በተከራካሪ ወገኖች ባይቀርብለትም ተገቢ በሆነ ጊዜ ማንኛውም ዓይነት ሰነድ ወይም ምስክር ወይም ሌላ አይነት ማስረጃ በተጨማሪ እንዲቀርብለት መስጠት ስላለበት ትዕዛዝ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 182(2) 342, 345(1)(ለ) | ጥቅምት 9/1998 |
| 14 | 14414 | የጊምቢ ከተማ አስተዳደር ጽህፈት ቤት እና ወ/ሮ መረርቱ ፈቃዱ | በሕዝብ አስተዳደር አካል ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ ከመ/ቤቱ ጋር ባለው ስራ ክርክር የአዋጅ ቁ. 42/85 ተፈፃሚ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀጽ 2(1),3(2)(ሠ) | ጥቅምት 1/1998 |
| 15 | 15270 | የመቶ አለቃ ተሻገር አስታጥቄ እና አቶ አዊል አው አብዲ | በከተማ ቦታ ላይ ስለሚኖር መብት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33(2), 231, (1)(ሀ), አዋጅ ቁ.47/67 | ጥቅምት 28/1998 |
| 16 | 15410 | አቶ ተሾመ ጅፋር እና የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | አጠቃላይ የአሰሪን የደመወዝ ጭማሪ አወሳሰን ስርዓትን ሳይሆን የግል ጥቅምን መሰረት አድርጎ የሚቀርብን የደመወዝ ጭማሪ ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 147 | ጥቅምት 1/1998 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 17 | 16273 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገንታ ገምአ | ላልተወሰነ ጊዜ የተቀጠርኩ እንደሆንኩ ብቻ ይወሰንልኝ በሚል የሚቀርብ ጥያቄን የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ እና የግል ጥቅምን መሰረት አድርጉ የሚቀርብን የጥቅማጥቅም ክስ የማየት ስልጣን የስራ ክርክር ችሎት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 9,10, 138, 142, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33 | ጥቅምት 22/1998 |
| 18 | 16624 | ወ/ት አጅጋየሁ ተሾመ እና የእቴነሽ በቀለ ሞግዚት ወ/ሮ እታገኝ ዘነበ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) መሰረት ዳኝነት እንደገና እንዲታይ ጥያቄው የሚቀርበው ይግባኝ ከመቅረቡ በፊት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6(1) | ጥቅምት 18/1998 |
| 19 | 16720 | ወ/ሮ አበራሽ ጉቱ እና እነ የመካከለኛው አዋሽ እርሻ ልማት ድርጅት (አራት ሰዎች) | በከፊል የፍርድ ባለመብት የሆነ ሰው ባለመብት የሆነበት የፍርድ ክፍል እንዲፈፀምለት የአፈፃፀም ክስ ካቀረበ በኋላ በመጀመሪያ የፍርድ ባለዕዳ የሆነበትን ፍርድ በይግባኝ አሸሮ የፍርድ ባለመብት ሲሆን አዲስ የአፈፃፀም መዝገብ መክፈት ሳያስፈልገው ቀደም ሲል የተከፈተው የአፈፃፀም መዝገብ ቢዘጋም እንኳን ማንቀሳቀስ ስለመቻሉ እና በአፈፃፀም ደረጃ ወለድ የሚከፈለው በዋናው ፍርድ ወለድ እንዲከፈል ከተወሰነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378(3)(ሰ) | ጥቅምት 22/1998 |
| 20 | 16896 | ዘምዘም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር እና የኢሊባቦር ዞን ትምህርት መምሪያ | የተዋዋዮች በውሉ አለመግባባት ሲፈጠርና ጉዳዩን በገላጋይ ዳኞች እንዲታይ ሲስማሙ ፍ/ቤት ይህንን ስምምነት ማስፈፀም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1711,1731(1) | ጥቅምት 16/1998 |
| 21 | 17077 | ዝቋላ ስቲል ሮሊንግ ሚል እና አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የዕዳ መክፈያ ጊዜ ካለፈ በኋላ ባለገንዘቡ ለባለዕዳው የሚያደረገው የዕዳ ክፍያ ጊዜ ማራዘም ዋሱን ከዋስትናው ነፃ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1928(1)እና(2) | ጥቅምት 14/1998 |
| 22 | 17189 | የሸቀጦች ጅምላ ንግድና አስመጭ ድርጅት እና አቶ ንጉሴ ዘለቀ | በአሰሪ "ገንዘብ" ላይ ሰራተኛው ያደረሰው ጉዳት በአሰሪው "ንብረት" የደረሰ ጉዳት ስለመሆኑ እና ሰራተኛ የስራ ውሉ ተቋርጦ ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 27(1) (በ), 53(1),54 | ጥቅምት 17/1998 |
| 23 | 17429 | ወ/ሮ ሎሚ ሆርዶፋ እና አቶ ተስፋዬ ከበደ | በግልጽ በሚደረግ ኑዛዜ ኑዛዜው መነበቡን የሚያመለክት ከሆነ በግልጽ "ተነቧል" የሚል ቃል አለመኖሩ ኑዛዜውን ፈራሽ የሚያደርግ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | ጥቅምት 21/1998 |
| 24 | 17533 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና ሙሉ ብርሃን | የጉምሩክ ባለስልጣን በህጉ መሰረት የጉምሩክ ስነ ስርዓት ያልተፈፀመበት ዕቃ ከጉምሩክ መጋዘን እንዳይወጣ በማድረጉ ወይም ዴክላራሲዮን ባለመስጠቱ ምክንያት በዕቃው ባለቤት ላይ ለሚደርስ ጉዳት ኃላፊ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 2(18), 43(1) (ሀ) | ጥቅምት 18/1998 |
| 25 | 17712 | የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት እና የወ/ሮ ሳዲያ እስማኤል ወራሾች | በተሰረዘ የባለሀብትነት ምስክር ወረቀት የሚገኝ የባለሀብትነት መብት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1), 1196 (1) | ጥቅምት 16/1998 |
| 26 | 18307 | ንብ ትራንስፖርት አ.ማ. እና አቶ ተገኑ መሸሻ | በድርጅት ውስጥ የስራ መሪ የሆነ ሰራተኛ ከአሰሪው ጋር ያለው የስራ ክርክር የሚገዛው በፍትሐብሔር ህጉ የስራ አገልግሎት መስጠትን ስለሚመለከቱ ውሎች ክፍል በተመለከቱት ድንጋጌዎች ስለመሆኑ እና የስራ ውሉ ተቋርጦ የስራ መሪው ስራ ላልሰራበት ጊዜ ደመወዝ የሚያገኝበት የህግ ምክንያት ስላለመኖሩ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2534, 2540 ,2541(1) | ጥቅምት 25/1998 |

**ቅጽ 3**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሳኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 27 | 15815 | አርሲ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ሰለሞን አበበ | የስራ ውሉ በህግ ወጥ መንገድ የተቋረጠ የስራ መሪ ስለሚያገኘው መፍትሔ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2570, 2573, 2574,2571 | ታህሳስ 10/1998 |
| 28 | 16648 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ አንለይ ያየህ (ሃያ ሰባት ሰዎች) | ስለ ስራ ክርክር የይርጋ ጊዜ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162,163,164,165,166, አዋጅ ቁ. 377/96 | ታህሳስ 20/1998 |
| 29 | 17483 | የኦሮሚያ ገጠር መንገዶች ባለሥልጣን እና ወ/ሮ ሮማን ደምሴ | የስራ ውል በህገ ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል የሚቀርብ ክስ መቅረብ ስላለበት የጊዜ ገደብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 162(1) | ታህሳስ 20/1998 |
| 30 | 11924 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ወ/ት ትዕግሥት ወርቁ | ለተወሰነ ጊዜ ወይም ላልተወሰነ ጊዜ የስራ ውል ስለማድረግ<br>አዋጅ ቁ.42/85 አንቀፅ 9,10 እና 24 | ህዳር 15/1998 |
| 31 | 14057 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና አቶ ጌታሁን ኃይሉ | አንድ ሰራተኛ የስራ ውሉ ሲቋረጥ ያልተጠቀመበት የአመት እረፍት ቀናት በገንዘብ ተቀይሮ ስለሚከፈልበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 79(2)እና (5), 77(5),77(3) | ጥቅምት 30/1998 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 32 | 16270 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ መሐሪ ማታ | በመኪና ግጭት ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳት ካሣ ለማግኘት የመኪናው ባለቤት ጥፋት እንዳለበት ማስረዳት የማይኖርበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2066(2),2086(2),2081,2091,2102 እና 2092 | ታህሳስ 17/1998 |
| 33 | 18581 | በአዲስ አበባ እስላማዊ ድርጅት የአወሊያ ጤና ጥበቃ እና ሲ/ረ ቀቡላ ከድር | በህገ ወጥ መንገድ የስራ ውሉ የተቋረጠ ሰራተኛ ወደ ስራ እንዲመለስ ስለሚወሰንበት የህግ አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 23(1),43(3),40(1) እና (2),44 | ህዳር 20/1998 |
| 34 | 15631 | እነ የሻረግ መንግስት (ሁለት ሰዎች) እና እማሆይ የሻረግ ፈረደ | የወራሽነት ጥያቄን ለማቅረብ ስለተወሰነ ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1001(2),1168,1845,1853 | ታህሳስ 17/1998 |
| 35 | 15551 | ዮናይትድ ቴክኒካል ኢኩፕመንት ኩባንያ እና የኢትዮጵያ መተርና መሐንደስነት ኩባንያ | ውል እንዲፈርስ ከተወሰነ በኋላ ተዋዋዮች ወደነበሩብት እንዲመለሱ የሚወሰነው በውሉ መሰረት የተሰራውን ስራ ለማፍረስ የማይቻል ወይም አስቸጋሪ ካልሆነ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1716(1), 1815,1816 እና 1817 | ጥቅምት 29/1998 |
| 36 | 16062 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና ወ/ሮ አረጋሽ ከበደ | ከውል ውጭ በደረሰ ጉዳት ካሣ በመጠየቅ የሚቀረብ ክስ መቅረብ ስለሚኖርበት ጊዜ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1),2143(2) | ህዳር 19/1998 |
| 37 | 14554 | ወ/ሮ ጽጌ አጥናፌ እና ባላምባራስ ውቤ ሽበሽ | ፍርድ ቤት በአስተዳደር አካል የተሰጠ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተርን የመሰረዝ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808(2),1198(2) | ታህሳስ 20/1998 |
| 38 | 15672 | አቶ ታደለ ገለቻ እና አቶ ውድመጣስ ኑሮ | ንብረት በሐራጅ ስለሚሸጥበት የህግ አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 442 | ታህሳስ 27/1998 |
| 39 | 16301 | ተገኝ እንግዳ እና አስናቀች ኬዳኔ | መጥሪያ አደራረስን አስመልክቶ የሚቀርብ ጥያቄ ስለሚስተናገድበት መንገድ<br>የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ. 99, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 103,105 | ህዳር 2/1998 |
| 40 | 10797 | ሼክ መሐመድ ሁሴን አላሙዲ እና እነ ወ/ሮ ሻዲያ ናዲም (ሦስት ሰዎች) | ባለቤቱና መጠኑ ተለይቶ የታወቀውንና ለባለቤቱ እንዲመለስ በወንጀል ጉዳዩ በፍርድ የተወሰነው ገንዘብ እውነተኛ ባለቤት በቀረበ ጊዜ በቀጥታ የሚመለስ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378 | ታህሳስ 27/1998 |
| 41 | 18199 | ዶ/ር ምናሴ እሸቴ እና እነ ግርማ አያና ( ሰባት ሰዎች) | በጨረታ ለገዛው ንብረት ገገር ዋጋውን ሳይከፍል ወይም ግዴታውን ሳይፈጽም ከቀረ ፍርዱን የሚያስፈጽመው ፍ/ቤት ሊከተለው ስለሚገባው ስነ-ስርዓት<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 429 | ህዳር 7/1998 |
| 42 | 16378 | የ10 አለቃ ጌታቸው ባዩ እና የቤ/ጉ/ክ/መ ማህበራዊ ዋስትና ባለስልጣን | የመንግስት ሰራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ሌላ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ መስራቱ ስለሚኖረው ውጤት<br>ድንጋጌ ቁጥር 46/53, አዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ታህሳስ 17/1998 |
| 43 | 18342 | የማህበራዊ ዋስትና ባለሥልጣን እና እነ አቶ ብርሀኑ ሀሩይ (ሁለት ሰዎች) | የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ ይግባኝ የማይባልበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.38/88 አንቀፅ 11(1) የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 4 | ታህሳስ 17/1998 |
| 44 | 14699 | የኢንጂነር ወርቁ መኮንን ወራሾች እና የቦሌ ክፍለ ከተማ ገቢዎች መምሪያ | ገቢን ለመፍጠር የሚወጣን ወጪ በትክክለኛ ሰነድ እንዲረጋገጥ ህጉ ስለሚያስቀምጠው ሁኔታ<br>ደንብ ቁጥር 258/55 አንቀፅ 29 | ህዳር 7/1998 |

**ቅጽ 4**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 45 | 20885 | የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ገቢሳ የማነ | ለተወሰነና ላልተወሰነ ጊዜ ስለሚደረግ የስራ ውል<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ጥር 3/1999 |
| 46 | 15531 | የኢት/ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ አዱኛ ገመዳ | የአሰሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | የካቲት 6/1999 |
| 47 | 21730 | ወ/ሮ ፍሬህይወት እርቁ እና የኢት/ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን | ወደ ሥራ እንዲመለስ የተወሰነለት ሰራተኛ የሚከፈለው ውዝፍ ደሞዝ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | መጋቢት 11/1999 |
| 48 | 21119 | ቃሊቲ ምግባ አክሲዮን ማህበር እና ማስተዋል ጫኔ | የህመም ፈቃድ ጊዜ አቆጣጠር<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ (2) | መጋቢት 18/1999 |
| 49 | 21961 | አቶ ግርማ ነጋሽ እና ቢግ ትሬዲንግ ኃ/የተ/የግል ማህበር | የስራ ውልን ስለማቋረጥ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) ሐ | መጋቢት 18/1999 |
| 50 | 20457 | የኢት/ንግድ ባንክ እና ወ/ሮ አለሚቱ ሞገስ | የስራ ውል በተቋረጠ ጊዜ ስራ ላልተሰራበት ውዝፍ ደሞዝ የሚከፈል ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43,53(1), 54 | መጋቢት 20/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 51 | 24153 | አቶ መንግስቱ አባተ እና የባህር ትራንዚት ድርጅት | ስለ መሠረታዊ የህግ ክርክር<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1)ሐ | መጋቢት 26/1999 |
| 52 | 16653 | ግዮን ሆቴሎች ድርጅት እና ወ/ሮ ስለእናት ወርቅነህ | የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ወሳኝ ቦርድ ስልጣን | መጋቢት 27/1999 |
| 53 | 25526 | መምህር ጥላሁን አስፋው እና አዲስ ኮሌጅ | ሰራተኛው በየአመቱ ውሉ እየታደሰ ሲሰራ መቆየቱና የሰራተኛው የቅጥር ውል በጊዜ የተገደበ መሆኑ ብቻ ለተወሰነ ጊዜ ተቀጣሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 9,10 | ሚያዝያ 16/1999 |
| 54 | 15662 | የኢት/ልማት ባንክ እና ሐዲ አብዲራህማን ቴሲሳ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 55 | 19081 | አቶ ዓሊ ቃሌብ አህመድ እና እነ አቶ ሚሊዮን ተፈራ (ሦስት ሰዎች) | ባልተነጣጠለ ኃላፊነት የተገናኙ ተከሳሾች በአንድ ላይ በተከሰሱ ጊዜ አንዱ ተከሳሽ የሚያነሳውን የይርጋ መቃወሚያ በሌሎች ላይ ስላለው ውጤት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677,1901 | መጋቢት 18/1999 |
| 56 | 23320 | አቶ ገብሩ አብሴ እና እነ የአቶ ሁሴን አብዲረህማን ወራሾች (ሦስት ሰዎች) | የኪራይ ውል በአከራይና በተከራይ መካከል የሚደረግ ስለመሆኑ | መጋቢት 20/1999 |
| 57 | 14493 | የኢት/ልማት ባንክ እና አቶ ሚደቅሳ ቱለማ | ውለታዎች ግልጽ በሆኑ ጊዜ ዳኞች ግልጽ ከሆነው በመራቅ የተዋዋዮች ፈቃድ ምን እንደነበር ለመተርጐም ስላለመቻላቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2298,1733 | መጋቢት 13/1999 |
| 58 | 18786 | ወ/ሮ አለሚቱ አግዛቸው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ዝናሽ ሐይሌ | የውል አብዛኛው ግዴታ በተፈፀመ ጊዜ የተወሰነ ቀሪ ገንዘብ አለመከፈሉ ውሉን ለማፍረስ የሚያበቃ መሰረታዊ የሆነ የግዴታ መጣስ የሚያሰኝ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1), 1785(2), 1789 | ሚያዝያ 18/1999 |
| 59 | 21448 | ወ/ሮ ጉርፌ ወርቅነህ እና እነ ወ/ሮ አበራሽ ዱባርጌ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ሽያጭ ውል በአዋዋይ ወይም በፍርድ ቤት ፊት መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1727 ,2877, 2878 | ሚያዝያ 30/1999 |
| 60 | 15557 | ወ/ሮ አልማዝ ዓለማየሁ እና አቶ ብርሀኑ ተሊላ | በአፈፃፀም ጉዳይ በስህተት በፍ/ባለመብት እጅ ስለገባ የከተማ መሬት ይዞታ | መጋቢት 11/1999 |
| 61 | 22260 | የጎንደር ከተማ አገልግሎት ጽ/ቤት እና እነ ወ/ሮ ገደሪፍ ውብነህ (ሦስት ሰዎች) | የወጪና ኪሣራ አወሳሰን<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 463 | መጋቢት 18/1999 |
| 62 | 17984 | የጌዲዮን ዞን ፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት እና ወ/ሮ አስናቀች ታደሰ | ጉድለት ያለበት ሀራጅ ቀሪ ሲደረግ ሻጭና ገገርን ወደነበሩበት ለመመለስ ስላለመቻል<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1817(1) እና (2) | መጋቢት 20/1999 |
| 63 | 19205 | አቶ ሽኩር ሲራጅ እና አቶ ሙላት ካሣ | አንድ ፍርድ ተፈፀመ ሊባል የሚገባው ለፍርድ ቤቱ ገቢ የተደረገ ገንዘብ ለፍርድ ባለመብቱ ሲደርሰው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 395 | መጋቢት 25/1999 |
| 64 | 19479 | ወ/ሮ አመለወርቅ ገለቱ ወራሾች እና እነ አቶ ቢሻው አሻሜ (አራት ሰዎች) | አከራካሪ የሆነው ቤት የግልም ሆነ የጋራ ቤቱ ያረፈበት ቦታ የመንግስት በመሆኑ ከቤቱ ተነጥሎ እንዲገመትና አስፈላጊም ከሆነ እንዲሸጥ የሚያደርግ ውሣኔ መሬትን የመንግስት ለማድረግ የወጣውን ሕግ የሚፃረር ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት 20/1999 |
| 65 | 16109 | አቶ ከበደ አርጋው እና የኢት/ንግድ ባንክ | የሽያጭ ውል በሶስተኛ ወገኖች ላይ ውጤት እንዲኖረው ተዋዋዮች  ውላቸውን በመዝገብ እንዲፃፍ ከማድረግ የዘለለ ግዴታ የማይጥልባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1587, 1620, 1613, 2878 | ሚያዝያ 12/1999 |
| 66 | 14094 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት<br>እና<br>የአቶ ሰለሞን ወረዳ ወራሽ | ለረጅም አመታት በመንግስት እጅ የነበረ ቤትን በተመለከተ ባለቤት ነኝ የሚል ወገን ቤቱ በአዋጅ ቁ. 47/67 የተፈቀደለት መሆኑን ወይም ያለአግባብ ከአዋጅ ውጪ ተወስዶብኛል የሚል ከሆነም ለሚመለከተው አካል ጥያቄውን አቅርቦ ውሣኔ አግኝቶ ባለመብት ስለመሆኑ ማስረዳት ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195, አዋጅ ቁ 47/67,ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 33/2/ | ሚያዝያ 18/1999 |
| 67 | 17937 | ወ/ሮ ድንቂ ተድላ<br>እና<br>አቶ አባተ ጫኔ | ጋብቻ በአንደኛው ተጋቢ ሞት ምክንያት በፈረሰ ጊዜ የጋራም ሆነ የግል ንብረት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መጠየቅ እንዳለበት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677 መሠረት በቁ. 1845 ላይ የተቀመጠው ይርጋ ተፈፃሚ ስለመሆኑ<br>ፍ/ብ/ህ/ቁ. 17,68, 100,1677,1845 | መጋቢት 20/1999 |
| 68 | 20938 | ወ/ሮ ሽዋዬ ተሰማ እና ወ/ሮ ሣራ ልነጋነ | ስለ ጋብቻ መፍረስ | ሚያዝያ 11/1999 |
| 69 | 22243 | ወ/ሮ ደሐብ ሰኢድ እና አቶ አብርሃም ካሣ | ልጅነትን ስለማስረዳት<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 126(1),143(መ) እና (ሠ) | ሚያዝያ 16/1999 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 70 | 17058 | አቶ አንበሶ ወ/ገብርኤል እና አቶ መሣይ መኮንን | ኑዛዜ ህጋዊ ነው መባሉ ሌሎች ሰዎች በሰነዱ ላይ ተቃውሞ ካላቸው ጉዳዩ በዳኝነት መታየትን የሚከለክል ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881, 884, 892, 996-1000, ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | መጋቢት 25/1999 |
| 71 | 22712 | አቶ እንደሻው በቀለ<br>እና<br>እነ ወ/ት አይናለም ያለው<br>( ሁለት ሰዎች) | የኑዛዜ እያንዳንዱ መስፈርት መሟላት መመዘን የሚገባው የኑዛዜውን አጠቃላይ ሁኔታ በመመልከትና ተናዛዥም ሆነ ምስክሮች /እማኞች/ በኑዛዜ ባሰፈሩት ቃላትና ሃረጐች ሊሰጡ የሚችለውን ትርጉም ግምት ውስጥ በማስገባት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 881 | ሚያዝያ 9/1999 |
| 72 | 22162 | አፍሪካ ኢንሹራንስ እና አቶ ብስራት ጉላ | መድን ሰጭ የካሣን ክፍያ በተመለከተ በመድን ውሉ ላይ ከተመለከተው በላይ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ | ሚያዝያ 9/1999 |
| 73 | 23339 | የኢት/ጉምሩክ ባለሥልጣን እና እነ አበሮ ኢርጋኖ | የጉምሩክ ባለስልጣን ሰራተኞች የፌዴራል ገቢዎች ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የሚተዳደሩ ስለመሆናቸው<br>አዋጅ ቁ. 368/95 አንቀፅ 6(2)ለ | መጋቢት 13/1999 |
| 74 | 16195 | የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና እነ ልዕልት ተናኘወርቅ ኃ/ስላሴ (ስድስት ሰዎች) | ሚኒስቴር መ/ቤቶች ስራቸውን በሚያከናውኑበት ወቅት የፈፀሙትን ስህተት ማረምና ማስተካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ ስልጣን ስር የሚወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 4187 አንቀፅ 11(1), አዋጅ ቁ.47/67 አንቀፅ 21(2) የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 74(4) | ሚያዝያ 11/1999 |
| 75 | 22317 | የምስራቅ ጉምሩክ የሐረር ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ<br>እና<br>አቶ አብዱ አሉ አዩ | የጉምሩክ ባለስልጣን በኮንትሮባንድ ወደ ሀገር የሚገቡትን ወይም ከሀገር የሚወጡትን እቃዎች እንቅስቃሴ የመቆጣጠር፣ የሚንቀሳቀሱ እቃዎችንና ማጓጓዣዎችን የመያዝና አስፈላጊ እርምጃዎችን የመውሰድ ስልጣን የተሰጠው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 60/89 አንቀፅ 5-6 የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2010(2) | ሚያዝያ 18/1999 |
| 76 | 12025 | አቶ ምናሴ አልማው እና ዓቃቤ ህግ | ጥብቅና ፈቃድ ከተሰረዘ በኋላ የጥብቅና ስራ እሰራለሁ ብሎ ገንዘብ መቀበል የማታለል ወንጀል ስለመሆኑ<br>የ1949 ወንጀለኛ መቅጫ ህግ ቁ.656(ሀ) እና (ለ) | መጋቢት 18/1999 |

**ቅጽ 5**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 77 | 17320 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና ዶ/ር ሻውል ገብሬ (ሁለት ሰዎች) | ንብረትን ለመሸጥ ለመለወጥ ብሎም ለሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ በሚል የተሰጠ ውክልና ንብረቱን በመያዣነት ለማስያዝ የሚያስችል ስልጣን እና ችሎታን የሚያጐናጽፍ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3049(2),2206(1) | መጋቢት 18/2000 |
| 78 | 20809 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና ወ/ሮ አለምነሽ ሃይሌ | በባለስልጣን ፊት በተረጋገጡ ሰነዶች ላይ ያሉትን ፊርማዎችና የሰነዶቹን ይዘት ማስተባበል ስላለመቻሉ | ሐምሌ 10/2000 |
| 79 | 23861 | ሊቀ ስዩማን አሰፋ ባሻህውረድ እና የሣህሊተ ምህረትና ክርስቶስ ሣምራ ደብር አስተዳደር | ወኪል የሆነ ሰው ውክልናውን በሚገባ እስካሳየ ድረስ በማመልከቻው ላይ የራሱን ወይም የወካዩን ስም አስቀድሞ መፃፉ ወኪልነቱን ለውጦ ባለቤት የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 58 | ጥቅምት 14/2000 |
| 80 | 26399 | አቶ ኃ/ማርያም ባዩ እና እነ አቶ ሣሙኤል ጉሣዬ (አምስት ሰዎች) | የውክልና ስልጣኑ ቀሪ ከተደረገበት እንደራሴ ጋር በቅን ልቦና ውል ፈፅመው በተገኙ ጊዜ ውሉ እንዲፈርስ ሳይወሰን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1808, 1816, 2191(2), 2193 | ህዳር 5/2000 |
| 81 | 32241 | ወ/ሮ ካሰች ተካልኝ<br>እና<br>እነ አቶ ኃ/ማርያም አበበ<br>(ሁለት ሰዎች) | • እንደራሴ የሆነ ሰው የውክልና ስልጣኑን መሠረት በማድረግ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞች (Conflict of interest) ማስወገድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ከእንደራሴው ጋር ውል የፈፀመው ሦስተኛ ወገን እንደራሴው የውክልና ስልጣኑን በሚያከናውንበት ጊዜ ተቃዋሚ ጥቅሞችን የማስወገድ ግዴታውን አለመወጣቱን ማወቁ ወይም ማወቅ የሚገባው መሆኑ ያደረጉትን ውል ፈራሽ ስለማድረጉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2187(1) | መጋቢት 9/2000 |
| 82 | 21355 | አንበሳ የከተማ አውቶብስ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አንበሳ ኢንሹራንስ ኩባንያ | የመልካም ሥራ አፈፃፀም ዋስትና የሰጠ ወገን ከዋናው ውል አለመፅናት ጋር በተያያዘ የዋስትና ውሉ እንዲፈርስ ሊጠይቅ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1923(2) | ሐምሌ 3/2000 |
| 83 | 25115 | አቶ ማሞ ጉበና እና አቶ ወርቅነህ ተክለማርያም | ተራ ዋስ የሆነ ሰው ከባለዕዳው ጋር ተጣምሮ ክስ በቀረበበት ጊዜ ከገባው የዋስትና ግዴታ ሙሉ በሙሉ ከኃላፊነት ነፃ ሊደረግ የሚችለው ዋናው ባለዕዳ ግዴታውን ለባለገንዘቡ ከመወጣቱ ጋር በተያያዘ ስለመሆኑ | ጥቅምት 5/2000 |
| 84 | 26565 | ግሎባል ኢንሹራንስ /አ.ማ/<br>እና<br>ንብ ትራንስፖርት /አ.ማ/ | ሊፈጠር ወይም ሊከሰት እንደሚችል ቀድሞ ሊገመት ወይም ሊታሰብና ጥንቃቄ ሊደረግበት የሚቻል ሁኔታ ድንገተኛ ደራሽ ቢሆን እንኳ ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ (Force majeure) ተብሎ የማይወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 1792(2) | ጥቅምት 19/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 85 | 17742 | ወ/ሮ አበበች ታደሰ እና እነ አስር አለቃ ሲሳይ ካብትህይመር (አራት ሰዎች) | በህግ በተቋቋመ ፍርድ ቤት የሚያስችል ማንኛውም ዳኛ ውል የማዋዋል ስልጣን ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1678(ለ) እና 1715 | መጋቢት 2/2000 |
| 86 | 23921 | ወ/ሮ ዘለቃሽ መንግስቱ እና አስር አለቃ ታደሰ ወርቁ | የስጦታ ውሉ በስጦታ ተቀባዩ ላይ ግዴታ ያልጣለ ቢሆንም እንኳን ስጦታ ሰጪው በድህነት ላይ መሆኑ ከተረጋገጠ ተቀባዩ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2458(1) | ጥቅምት 12/2000 |
| 87 | 32337 | ወ/ሮ ፀሐይነሽ ይህደጐ እና እነ ወ/ሮ ትሕሽ በርሔ | “የቁም ኑዛዜ ስጦታ” ተራ የክፍያ ደንብ እንጂ ሌሎች ወራሾች ያላቸውን ውርሱን የመካፈል መብት የማይገድብ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 913 | ግንቦት 21/2000 |
| 88 | 22891 | ወ/ሮ ማና ኃ/ሚካኤል እና እነ አቶ ገ/ማርያም ከበደው (ሁለት ሰዎች) | በጋብቻ ወቅት በአንደኛው ተጋቢ ምክንያት የተፈጠረ ዕዳ ለጋራ ጥቅም መዋሉ በተረጋገጠ ጊዜ የዕዳው ወደ የጋራ ንብረት ወይም ወደ ሌላኛው ተጋቢ የግል ንብረት በመሄድ ሊከፈል የሚችለው በፍርድ አፈፃፀም ላይ ስለመሆኑና ከዚህ ጋር በተያያዘ በሌላኛው ተጋቢ ላይ ዕዳውን መሠረት በማድረግ ክስ ሊመሰረትበትም ሆነ ፍርድ ሊሰጥበት የማይገባ ስለመሆኑ | ህዳር 24/2000 |
| 89 | 31737 | አቶ ገብሩ ገ/መስቀል እና  ቄስ ገ/መድህን ረዳ | በፍ/ብ/ህ/ቁ. 2472 መሠረት በባንክ የተሰጠ የሃዋላ ወረቀት ብድርን ለማስረዳት ስለመቻሉ | የካቲት 27/2000 |
| 90 | 24173 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት እና ወ/ሮ አይዳ ሐሰን | በኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት የተላከ ፖስታ /ዕቃ/ በመጥፋቱ፣ መሠረቁ፣ በመበላሸቱ፣ ወዘተ ምክንያት ካሣ የሚጠየቀው መጠኑም የሚወሰነው የፖስታ አገልግሎት ሕግን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 24/58 መሠረት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 24/58 አንቀፅ 50,51,53 እና 54 | ህዳር 11/2000 |
| 91 | 24574 | የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተ/ቤ/መ/ፖ/ጠ/ጽ/ቤት እና አቶ ይትባረክ ሣህሉ | በግልፅ ዳኝነት ተጠይቆበት ውሣኔ ሳይሰጥበት የታለፈ ጉዳይ እንደተነፈገ ይቆጠራል የሚለው የሥነ- ሥርዓት ህግ ድንጋጌ ሊተረጐም የሚችልበት አግባብ | ህዳር 11/2000 |
| 92 | 25434 | የአዲስ አበባ ውሀና ፍሳሽ ባለስልጣን እና ፋሬተርስ ኢንተርናሽናል ኃ/የተ/የግል ማህበር | በውል ውስጥ አጠራጣሪና ግልፅነት የጐደላቸው ጉዳዬች በፍ/ብ/ህ/ቁ.1738 መሠረት እልባት ሊሰጣቸው የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1738 | መጋቢት 25/2000 |
| 93 | 29369 | በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የሆለታ የግብርና ምርምር ማዕከል እና አቶ ተመስገን አድነው | • የባለዕዳው ቀጥተኛ የውል ፈፃሚነት ከውሉ ባህሪ አኳያ ማስፈፀም አለመቻል ውሉ እንዲሰረዝ መጠየቅ ሳያስፈልግ ኪሣራ ካለ መጠየቅ ስለመቻሉ<br>• በውል መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ ወገንን አስገድዶ ለማስፈፀም የማይቻል በሆነ ጊዜ በውሉ ግዴታውን የተወጣው ወገን ውሉ ባለመፈፀሙ ምክንያት የደረሰውን ኪሣራ ለመጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771(1) እና (2) | መጋቢት 9/2000 |
| 94 | 19338 | ዘይነባ ሐሰን እና ፍሬው ተካልኝ | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ተጐጂ የሆነ ወገን የወደፊት ህይወት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖር ስለመሆኑ ምክንያታዊ እርግጠኝነት ያለ እንደሆነ ዳኞች ለተጐጂው የሚከፈለውን ካሣ በርትዕ መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2102 | መጋቢት 2/2000 |
| 95 | 21296 | የኔዘርላንድ ልማት ድርጅት እና ውበት አድባሩ | የፍ/ብህ/ቁ. 2089 ተፈፃሚ ሊሆን የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(1) እና (2) | ታህሳስ 1/2000 |
| 96 | 22509 | አቶ ግርማ ኃ/ጊዮርጊስ እና ዳርጊ ሰምሮ | የቀረበን ክስ ለማስረዳት አግባብነት የሌለው ማስረጃን መሠረት በማድረግ የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ | ጥቅምት 7/2000 |
| 97 | 24818 | ይልቃል በእውቀቱ እና ስዩም አባዲ | ጥቅም በሌለው ግንኙነት በመኪና ተሣፍሮ ሲሄድ አደጋ በመድረሱ ምክንያት ጉዳት የደረሰበት ሰው ካሣ ሊጠይቅ የሚችለው የመኪናው ባለቤት ወይም ጠባቂው ጥፋት መፈፀሙን በማስረዳት ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2089(2) | የካቲት 4/2000 |
| 98 | 27565 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ደምሴ ወርቅነት (ሁለት ሰዎች) | ጉዳት ሊካስ የሚገባው ለደረሰ ጉዳት ብቻ ሳይሆን በጉዳቱ ምክንያት ለሚመጣ ኪሣራ ጭምር ስለመሆኑ | ታህሳስ 1/2000 |
| 99 | 27623 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ሮ ውባየሁ አበበ | • የማህበራዊ ዋስትና መብት ጥቅምን በሚመለከት የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ እንጂ መደበኛ ፍርድ ቤቶች የመዳኘት የሥረ ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>• የማህበራዊ ዋስትና ይግባኝ ሰሚ ጉባኤ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 38/88 አንቀፅ 5,8 እና 11 | ህዳር 24/2000 |
| 100 | 28612 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለስልጣን | ለደረሰ ጉዳት ሃላፊ የተባለ ሰው ላደረሰው ጉዳት ካሣ አይከፍልም ሊባል የሚችልበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2091 | የካቲት 25/2000 |
| 101 | 28750 | የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለስልጣን እና | ከውልና ከውል ወጪ በሆነ ግንኙነት ከሁለት የተለያዩ የክስ ምክንያቶች የሚመነጭ ኃላፊነትን መሠረት በማድረግ በአንደኛው ግንኙነት ብቻ ተጠያቂ የሆነን ወገን ሁለቱን የኃላፊነት ምክንያቶች መሠረት በማድረግ ካሣ እንዲከፍል | ህዳር 24/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በአንድነትና በነጠላ ሊጠየቅ ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2035, 1896 | |
| 102 | 28865 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ካሣ ግዛው | ንብረትን ከመስሪያ ቤት በኃላፊነት የተረከበ ሰው ንብረቱ በጠፋ ጊዜ ከንብረቱ መጥፋት ጋር በተያያዘ ጥፋት ያልፈፀመ መሆኑን ወይም ንብረቱ ከሥራ ሰዓት ውጪ የጠፋ መሆኑን የማስረዳት ሸክም ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2027 | ህዳር<br>24/2000 |
| 103 | 30032 | የአማራ ክልል ፍትህ ቢሮ<br>እና<br>ወ/ሮ ምንትዋብ የኔነህ | በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረት የክልሉ መንግስት ቋሚ ሠራተኛ በስራ ላይ በደረሰበት ጉዳት የሞተ እንደሆነ ለተተኪዎች የጡረታ አበል እንጂ ሌላ ተጨማሪ ካሣ ሊከፈል የሚችልበት አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል አዋጅ ቁ.74/1994 አንቀፅ 46(5) (ሀ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 104 | 30442 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ሰሜን ምዕራብ ሪጅን እና ወ/ሮ ድንቋ አመኔ | • ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት የሞት አደጋ በደረሰ ጊዜ የሟች የቅርብ ዘመዶች ሊኖራቸው የሚችለው መብት እና<br>• የደረሰውን የሞት አደጋ ተከትሎ የሚቀርብ የቀለብ ጥያቄ ሊስተናገድ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095 807, 812 | ህዳር<br>3/2000 |
| 105 | 31099 | የተንዳሆ እርሻ ልማት አ/ማ<br>እና<br>ወ/ሮ ርሻን አለማየሁ | ሟች ከመሞቱ በፊት ቀለብ የማይሰፈርለት ግለሰብ በሟች ሞት ምክንያት የጉዳት ካሣ በቀለብ መልክ እንዲከፈለው ለመጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095, 2069(1) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 106 | 32144 | ግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር<br>እና<br>ወ/ሮ ኢልሻ ሲራጅ | • በሞት ምክንያት ቀረ የሚባል ጥቅም የሚሰላው ከጠቅላላው የሟች ደሞዝ ላይ የሚቀነሱት በህግ የታወቁት ተቀናሾች ተቀንሰው የሚገኘውን የተጣራ ገቢ መሰረት በማድረግ ስለመሆኑ<br>• የህሊና ካሣ ከአንድ ሺህ ብር ሊበልጥ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2116 | መጋቢት<br>23/2000 |
| 107 | 32250 | ወ/ሮ አስናቀ ወ/ማሪያም እና እነ አቶ ከተማ ተሰማ<br>(ሁለት ሰዎች) | በሞት አደጋ ምክንያት የተቋረጠ የመተዳደሪያ ጥቅም ጋር በተያያዘ በየወሩ የሚከፈል ካሣ አከፋፈል ስርአት በፍርድ ቤት የተወሰነውን ካሣ አጠቃሎ በባንክ ወይም በሌላ የገንዘብ ተቋም በማስቀመጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2095(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 108 | 33975 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ አበበች ስዩም | የመሬት ይዞታ ባለቤት የሆነ ሰው ለህዝብ ጥቅም በሚል ይዞታውን በተጨባጨ እንዲለቅ ባልተደረገበት ሁኔታ ሊጠይቅ የሚችለው የካሣ ክፍያ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.455/97 አንቀፅ 7(1) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 109 | 34138 | እነ ሲስተር ገነት ጌታቸው (ሁለት ሰዎች) እና<br>ወንድወሰን ኃይሉ ወልደ ማሪያም | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት የደረሰበት ሰው ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ በደሞዝ ረገድ የቀረበት ጥቅም (ገቢ) መኖሩ ከተረጋገጠ ሊካስ የሚገባ ስለመሆኑ | ግንቦት<br>26/2000 |
| 110 | 34906 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን የምስራቅ ሪጅን ጽ/ቤት<br>እና ወ/ሪት ፍሬሕይወት እርቄ | በሥራ ግንኙነት ውስጥ የቅርብ አለቃ የሆነ ሰው በሥሩ ያሉ ሠራተኞችን አስመልክቶ ለበላይ ኃላፊዎች የሚፅፈውና የሚልከው ሪፖርት ሥም ከማጥፋት ጋር በተያያዘ የፍትሐብሔር ሃላፊነት ሊያመጣበት የማይችል ስለመሆኑ | ግንቦት<br>5/2000 |
| 111 | 21740 | ወ/ሮ አስረስ መስፍን እና ወ/ሮ ውብነሽ ታከለ | የጋብቻ ጽሁፍ በሌለ ጊዜ ጋብቻ መኖሩን ለማስረዳት የሚቻለው የባልና ሚስትነት ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 699(1), (2) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 112 | 23021 | ወ/ሮ አበባ ወርቅ ጌታነህ<br>እና<br>ወ/ሮ ዋጋዬ ኃይሌ | በፍቺ ጋብቻ ከፈረሰ በኂላ የቀድሞ ተጋቢዎች እንደ ገና አብሮ መኖር የትዳር ሁኔታ መኖሩን የሚያስገነዝብ ከሆነ ጋብቻ መፈፀሙን የህግ ግምት መውሰድ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 96 እና 97(1) | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 113 | 23493 | ወ/ሮ እንማው ዘገየ እና ወ/ሮ ወርቂ መኮንን | በፍርድ ቤት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የሟች ባለቤቶችን እኩል የጡረታ አበል የመከፈል መብት የሚሰጥ ስለመሆኑ | ሰኔ<br>26/1999 |
| 114 | 23632 | ወ/ሮ ፀዳለ ደምሴ<br>እና<br>አቶ ክፍሌ ደምሴ | ወላጆች ለህፃናት ልጆቻቸው ሞግዚትና አስተዳዳሪ የመሆን መብታቸው ሊከበር የሚችለው ለህፃናቱ ጥቅምና ደህንነት እስከሰሩ ወይም ሊሰሩ የሚችሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ሲቻል ብቻ ስለመሆኑ<br>የደቡብ/ብ/ብ/ሕ/ክ/መንግስተ የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 75/96 አንቀፅ 235(1), የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 36(2) | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 115 | 24625 | ወ/ሮ ሳድያ አሕመድ እና ወ/ሮ ሊህማ አሊ | በህግ ፊት ያልፈረሰ በጋብቻ ላይ ጋብቻ በፈፃሚው ሞት ምክንያት የፈረሰ እንደሆነ የጋራ ሀብትን ሁለቱ ባለቤቶች ግማሹን ለሁለት ቀሪውን ግማሽ ልጆች የሚካፈሉ ስለመሆኑ | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 116 | 25005 | መኮንን በላቸው እና ወ/ሮ አለሚቱ አደም | በጋብቻ ውል ላይ የግል ተብሎ ያልተመለከተና ጋብቻ ከመፈፀሙ በፊት ግንባታው የተጀመረ ቤት ግንባታው የተጠናቀቀው በጋብቻ ወቅት ከሆነ የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) , 63(1) | ህዳር<br>3/2000 |
| 117 | 25281 | ወ/ሮ መሠረት ፍስሐ<br>እና<br>አቶ ቀልቤሣ አለሙ | የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው በሚል የተወሰነ መኖሪያ ቤት ጋር በተያያዘ አንደኛው ተጋቢ ቤቱ የተሰራበትን መሬት (ቦታ) ከጋብቻው በፊት የተመራ በመሆኑ ሌላኛው ተጋቢ የቤቱን ግማሽ ዋጋ ተቀብሎ እንዲለቅ በሚል የሚሰጥ ውሣኔ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 92 | ጥር<br>29/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የፍ/ብ/ህ/ቁ. አንቀፅ 1131,1132 | |
| 118 | 25588 | መርየንሃሰን ዑመር እና መውሊድ ተኽልእስማን | አንድ ፍርድ ቤት የቀረበለትን ጉዳይ የመዳኘት ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ማረጋገጥ ያለበት ጉዳዩን ማየት ከመጀመሩ በፊት እንጂ ውሣኔ ከሰጠ በኋላ ስላለመሆኑ | የካቲት 6/2000 |
| 119 | 26839 | ወ/ሮ አስካለ ለማ<br>እና<br>ሣህለ ሚካኤል በዛብህ | ጋብቻ ከመመስረቱ በፊት የግል የነበረ ሃብት ከጋብቻ በኃላ የጋራ ከሆነ ንብረት ጋር ተቀላቅሎ በተገኘ ጊዜ የግል የሆነው ንብረት ተለይቶ የግሉ ለሆነው ተ.ጋቢ. ሊሰጥ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 57,86(1) | ህዳር 10/2000 |
| 120 | 26953 | አቶ ብዙነህ ጨርቆሴ እና ወ/ሮ መዓዛ እንግዳዬ | በጋብቻ/በትዳር ላይ/ ከተ.ጋቢ.ዎች መካከል በአንደኛው ተ.ጋቢ. አማካኝነት በካሣ መልክ የተገኘ ሃብት የጋራ ሃብት/ንብረት/ ተደርጐ የሚቆጠር ስለመሆኑ | ህዳር 13/2000 |
| 121 | 27697 | አቶ ርዕሶም ገ/መድህን እና ወ/ሮ አልማዝ ጊላ ሚካኤል | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የጋራ ንብረት የተሸጠ ቢሆንም የሽያጩ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል እንደሚገኝ ካልተረጋገጠ ለጋራ ትዳር ጥቅም እንደዋለ የህግ ግምት የሚወሰድበት ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 -93 | ጥቅምት 19/2000 |
| 122 | 27869 | ፍቅርና ሠላም ኃ/የተ/የግ/ማ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ መሠረት ኃይሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • የማይንቀሳቀስ ንብረት ለንግድ ማህበር በመዋጮ መልክ የተሰጠ ሆኖ ሲገኝ የንብረቱ ስም በኩባንያው ተመዝግቦ ያለመገኘቱ በ3ኛ ወገኖች ላይ መቃወሚያ ለመሆን የማይችል ቢሆንም ንብረቱ በአይነት መዋጮ መሰጠቱን የሚያስቀረው ስላለመሆኑ<br>• የጋራ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ያለ አንደኛው ተ.ጋቢ. ፈቃድ ለንግድ ማህበር በዓይነት መዋጮ የተሰጠ እንደሆነ ንብረቱ የባልና ሚስቱ የጋራ ንብረት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 517(ሠ),(ረ)<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 68(1), 69(2) | ህዳር 10/2000 |
| 123 | 29343 | እነ ወ/ሮ አምሳለ ተፈራ (ሁለት ሰዎች) እና ወ/ት አበባ አድማሱ | ተ.ጋቢ.ዎች በጋብቻ ወቅት የተፈራ ቤታቸውን በትርፍነት ለመንግስት ያስረከቡ እንደሆነ የአንደኛው ተ.ጋቢ. የግል ንብረት የሆነን ቤት ያለምንም ተጨማሪ ስምምነት የጋራ የሚያደርገው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67 አንቀፅ 11(1) | ሚያዝያ 7/2000 |
| 124 | 29402 | ወ/ሮ ሐዳስ ታረቀ እና የ፶ አለቃ አስመላሽ ኃይለስላሴ | ቤት የጋራ ሃብት ነው ከተባለ ቤቱ የተሰራበት መሬት ላይ የጋራ ባለሃብቶቹ እኩል የመጠቀም መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ | ጥቅምት 19/2000 |
| 125 | 30959 | እነ ወ/ሮ ተወዳጅ ገ/ሥሌሴ (ሁለት ሰዎች) እና<br>እነ አቶ ዘለቀ ዘውዴ( ሁለት ሰዎች) | • ሚች በኑዛዜው አንድን ሰው ልጄ አይደለም በማለት መግለፅ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማፍረስ የሚያበቃ ስላለመሆኑ<br>• በቤተሰብ ህጉ ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቻልበት አግባብ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154,156,157 | ታህሳስ 1/2000 |
| 126 | 31430 | ወ/ሮ አዲስአለም አከለ እና የመቶ አለቃ አክሊሉ አበበ | ጋብቻ ፀንቶ ባለበት ጊዜ የሚገኝ ድጐማ የባልና ሚስቱ የጋራ ሀብት ስለመሆኑ<br>የአማራ ብ/ክ/መ የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 73(1) እና (2) | ሚያዝያ 7/2000 |
| 127 | 31891 | እነ አቶ አንለይ እንየው (ሰባት ሰዎች) እና ወ/ሮ መሬም ጠሃ | የተ.ጋቢ.ዎች ተለያይቶ ለረዥም ጊዜ መኖርና በዚህም ጊዜ ሌላ ትዳር መስርቶ መገኘት የቀድሞው ጋብቻ በህጋዊ መንገድ ተቋርጧል የሚያስብል ስለመሆኑ /የሰ/መ/ቁ. 14290/ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 128 | 31946 | ወ/ሮ ዘውዲቱ ጌታቸው እና ተመስገን ደሳለኝ | የጋብቻ ውል በህግ አግባብ አልተደረገም በሚል ተቃውሞ ያቀረበ ተ.ጋቢ. በውሉ መሠረት ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 34(2), 35(2) እና 9(1) | ግንቦት 14/2000 |
| 129 | 32130 | እነ እማዋይሽ ካሣ (ስድስት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ አስቴር አህመድ | አንድን ሰው አባት ነው ብሎ ለማለት ለልጅ እንክብካቤ ማድረጉና ልጁም በእሱ ስም መጠራቱ ብቻ ሣይሆን ግለሰቡ ድርጊቱን አባት ነኝ ከሚል ስሜትና መንፈስ በመነጨ ያደርግ የነበረ መሆኑ መረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክ/መ/ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁ. 79/95 አንቀፅ 154(ሐ)(ሠ) | መጋቢት 18/2000 |
| 130 | 33411 | ወ/ሮ ሙሉብርሃን አባዲ እና አለቃ ኪሮስ ገብሩ | ተ.ጋቢ.ዎች ጋብቻቸው ፀንቶ ባለበት ወቅት የገዙት ንብረት በስማቸው ያልዞረ ቢሆንም እንኳን ንብረቱ የእኔ ነው በሚል የቀረበ የ3ኛ ወገን ተቃውሞ እስካልቀረበ ድረስ ንብረቱ የጋራ ሀብት ተደርጐ የሚወሰድና ሊከፋፈል የሚገባ ስለመሆኑ | መጋቢት 25/2000 |
| 131 | 33440 | ወ/ሮ ኪሮስ ገ/ማርያም እና አቶ ግርማ ገብረ ስላሴ | • ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ ጥያቄ ሥልጣን ባለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሊስተናገድ የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ልጅነትን ለማረጋገጥ የሚቀርብ የልደት ምስክር ወረቀት ተቃውሞ የማይቀርብበት የመጨረሻ ማስረጃ ተደርጐ ሊወሰድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 154 | ሚያዝያ 21/2000 |
| 132 | 33875 | ወ/ሮ የሻረግ አባተኩን እና ወ/ሮ መሠረት አድማሱ | ጋብቻ በባህላዊ መንገድ ተመስርቷል ለማለት የሚቻልበት አግባብና መመስረቱን ማስረዳት የሚቻልበት ሁኔታ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 4 እና 97(2) | መጋቢት 25/2000 |
| 133 | 34149 | እነ ወ/ሮ ዘለቃሽ በቀለ እና አቶ አለሙ በቀለ | የአንድ ሰው አባት ነኝ በሚል የሚቀርብ ሰው አባትነቱን በህግ አግባብ በማስረጃ ማስረዳትና ማረጋገጥ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 147(1), 97(2) | መጋቢት 25/2000 |
| 134 | 34387 | አቶ ከበደ መሔ እና ወ/ሮ ፋናዬ ብዙነህ | የጡረታ አበል እንደማንኛውም ገቢ የባልና ሚስት የጋራ ንብረት ተደርጐ የሚወሰድ ስላለመሆኑ | ግንቦት 14/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 135 | 35376 | እነ አቶ ዳንኤል አሰፋ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>ወ/ሮ ሔለን ውበቱ | ከጋብቻ በፊት የተፈራ ንብረት ላይ ያለን ዕዳ ለመወጣት ከጋብቻ በኃላ ከባልና ሚስት የጋራ ገንዘብ መከፈሉ ንብረቱን የጋራ ንብረት የማያደርገው ስለመሆኑ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 62(1) እና 70(1) | ግንቦት<br>28/2000 |
| 136 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማ<br>እና<br>እነ ባህሩ አብርሃም (አስራ ሁለት  ሰዎች) | የአክስዮን ማህበር አባላት የአክስዮን አስተዳዳሪዎች መብታቸውን በሚጐዳ መልኩ መስራታቸውን ማረጋገጥ ከቻሉ በቀጥታ መክሰስ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>የንግድ ህግ ቁ. 367 | ሐምሌ<br>10/1999 |
| 137 | 25306 | አቶ ተስፋዬ ገለቴ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ገንዘብን በአደራ ለማድረስ የተቀበለ ባንክ አደራ አስቀማጩ ይሰጥልኝ ላለው ሰው እስካልሰጠ ድረስ በኃላፊነት ሊጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 898(1) | ህዳር<br>12/2000 |
| 138 | 27161 | አቶ ኤልያስ ከፈለ<br>እና<br>እነ አቶ ከድር አህመድ (አራት ሰዎች) | የክሱ መሠረት የሆነው ጉዳይ መቅረቱን በክሱ ሂደት በማንኛውም ደረጃ የተረዳ ፍ/ቤት ክሱን መሰረዝ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 280 | ህዳር<br>12/2000 |
| 139 | 28923 | የባህርዳር ጨርቃ ጨርቅ አክሲዮን ማህበር እና<br>.እነ የባህር ዳር ልዩ ዞን አስተዳደር          (ሁለት ሰዎች) | የመንግስት ልማት ድርጅት ወደ አክሲዮን ማህበራት ሲቀየር በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ያልታወቀና ውሣኔ ያልተሰጠበት እንኳን ቢሆን የልማት ድርጅቱ ዕዳ ወደ አክሲዮን ማህበር የማይተላለፍ ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 208/92 አንቀፅ 5(1), 6(1)ሐ | ግንቦት<br>7/2000 |
| 140 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬተይዜሽንና የመንግስት ልማት ድርጅት ተቆጣጣሪ እና የአቶ ኑርበዛ ተረጋ ወራሾች | በፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲም ሆነ በኤጀንሲው ስራ አመራር ቦርድ ቀርቦ ውሣኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ለማየት ፍ/ቤቶች ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ.110/87 አንቀፅ 4(1) እና 5(3) | ህዳር<br>3/2000 |
| 141 | 27548 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ቆፀላ መርሻ (ሁለት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር አጠራጣሪነቱ በታወቀ ጊዜ ከሚመለከተው አካል ተገቢውን ማብራሪያና ማስረጃ ሳይጠየቅ የሚሰጥ ውሣኔ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1196(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 142 | 29822 | የወረዳ 6 ቀበሌ 02 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>ወ/ሮ በቀለች አማረብህ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት የምስክር ወረቀት ስልጣን ላለው የአስተዳደር ክፍል መመለስና መሰረዝ ጋር በተያያዘ ፍ/ቤቶች የባለቤትነት ደብተሩ እንዳይመለስ በሚል ውሣኔ ለመስጠት የማይችሉ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ 1196(1) | ግንቦት<br>28/2000 |
| 143 | 29860 | ወ/ሮ አስናቀች ሲሻው<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አሰለፈች ከተማ (አራት ሰዎች) | በአዋጅ ቁጥር 47/67 መሠረት የባለቤትነት መብት ለመንግስት የተላለፈ መሆኑን እንደመከራከሪያ በማንሳት መሟገት የሚችለው የሚመለከተው የመንግስት አካል እንጂ ግለሰብ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ 47/67 አንቀፅ 13(1) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 144 | 31490 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ሴርኮ እስራኤላዊያን | ተከሳሽ የሆነ ወገን ካቀረባቸው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች መካከል ፍ/ቤቱ አንዱን ብቻ መሠረት በማድረግና ሌሎቹ ላይ ብይን ሣይሰጥ ክሱን ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ብይን ባልተሰጠባቸው መቃወሚያዎች ላይ ይግባኝ ማቅረብ የማይጠበቅበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 244,341 | ሚያዝያ<br>2/2000 |
| 145 | 31682 | አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ ዘላለም ይልማ ባልቻ<br>( ሦስት ሰዎች) | ተወርሰዋል ተብለው በመንግስታዊና ህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ሥር ያሉ ቤቶች ጋር በተያያዘ ይመለሱልኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መሠረት በማድረግ ፍ/ቤቶች መወረስና አለመውረስን በተመለከተ ማስረጃዎችን መርምሮ ውሣኔ ለመስጠት ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>አዋጅ ቁ.110/87 | መጋቢት<br>12/2000 |
| 146 | 32376 | አቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሽዋንግዛው | የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በባለቤትነት የሚያስተዳድራቸው ቤቶች ላይ የባለቤትነት /የባለቤትነትን መፋለም/ ክርክር በተነሣ ጊዜ ጉዳዩን  የማየት የስረ ነገር ስልጣን የማይኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 147 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | በክርክር ተካፋይ እንዲሆን የሚያስፈልግ ወገንን ተከራካሪ ወገኖች እንዲገባ ያልጠየቁ ቢሆንም ፍ/ቤቶች ይህንኑ ወገን በራሳቸው ተነሣሽነት በክርክሩ ተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ<br>28/2000 |
| 148 | 22857 | እነ አቶ ተክሌ ደግፌ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ አቶ በፍቃዱ ኃይሌ<br>(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ ሂደት ላይ ያለ ጉዳይን ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በክርክሩ ማናቸውም ደረጃ ላይ ጉዳያቸው በፍርድ ቤት ወይም ከፍርድ ቤት ውጪ በእርቅ እንዲያልቅ ለመጠየቅ የሚችሉ ስለመሆናቸው<br>• በፅሁፍ ተዘጋጅቶ የቀረበ የእርቅ ስምምነት ለፍ/ቤት በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ስምምነቱ ለህግና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑን አረጋግጦ በፍ/ቤት የተያዘውን ጉዳይ ማቋረጥ የሚገባው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 274(1),275,(1),277(1) | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 149 | 25912 | አቶ ብሩ ቆርቾ  እና  አቶ ክፍሌ ሐብደታ | የግልግል ስምምነት እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3312 | ሚያዝያ<br>2/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 150 | 29386 | ወ/ሮ ወለላ ተሰማ<br>እና<br>እማሆይ በላይነሽ መለሰ | ከወራሾች መካከል አንዱ በሌለበት የተካሄደ የንብረት ክፍፍል በሌለበት ክፍያው የተፈፀመበት ወራሽ በሚያቀርበው አቤቱታ መነሻነት ሊፈርስ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1080 | የካቲት 25/2000 |
| 151 | 30536 | ወ/ት አለምነሽ ዋቅቶላ እና አቶ ይልቃል ጌጤ (ሁለት ሰዎች) | ከውል ውጪ በሆነ ግንኙነት ጉዳት ሳደረሰ ወገን የመድን ሽፋን የሰጠ አካል በሃላፊነቱ መጠን ለተጐጂው መካሱ ተጐጂው በጉዳት አድራሹ ላይ የሚያቀርበውን ተጨማሪ (ቀሪ) የካሣ ጥያቄ የሚከለክል ስላለመሆኑ | መጋቢት 23/2000 |
| 152 | 20036 | ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ሮ ወለተብርሃን ካሣዬ | ጋብቻ የትዳር ሁኔታ መኖሩን በማስረዳት ለማሳየት /ለማረጋገጥ/ የሚቻል ስለመሆኑና ይህንንም ለማስረዳት ማንኛውም ዓይነት ማስረጃ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 95,96 እና 97 | ግንቦት 16/1998 |
| 153 | 25899 | የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ እና ወ/ር ስዩም ካሣ | የመንግስት ሠራተኛ ጡረታ ከወጣ በኋላ ተመልሶ ደሞዝ በሚያስገኝ የመንግስት ስራ ላይ ከተቀጠረ የቅጥሩ ሁኔታ በጊዜያዊነትም ሆነ በቋሚነት ከደሞዝ በተጨማሪ የወሰደውን የጡረታ አበል መመለስ ያለበት ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 209/55 አንቀፅ 30(2) | ግንቦት 28/2000 |
| 154 | 26480 | የኮተቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ<br>እና<br>አቶ ቢንያም አለማየሁ | ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ አስተዳደራዊ ውሣኔ የተሰጠባቸው ጉዳዩችን አይተው ለመወሰን ስልጣን ያልተሰጣቸው ስለመሆኑ<br>አዲስ አበባ አስተዳደር ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 12/91 አንቀፅ 9(4) | ጥቅምት 14/2000 |
| 155 | 28883 | ግሎባል ሆቴል ኃ/የተ/የግል ማህበር<br>እና<br>ሚስተር ኒኮላ አስፓፓቻት ዚስ | ከተከራካሪ ወገን አንዱ የውጭ ሀገር ዜጋ ስለሆነ ብቻ ክርክሩ ሁልጊዜ የግለሰብ አለማቀፍ ሕግ ጥያቄ ያስነሳል ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 11(2)ሀ | ህዳር 26/2000 |
| 156 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ግርማቸው ይላላ (ሁለት ሰዎች) | በክፍለ ከተማ ስልጣን ክልል ውስጥ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ክፍለ ከተማው ጣልቃገብቶ የመከራከር መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የአዋጅ ቁ. 361/95 አንቀፅ 10(2),30<br>አዋጅ ቁ. 18/97 አንቀፅ | ሚያዝያ 14/2000 |
| 157 | 30298 | አቶ የሲወንድም አቡሕይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | ጠፋ የተባለ ሰው በተመለሰ ጊዜ ንብረቶቹ የተሸጡ ከሆነ ለማግኘት መብት የሚኖረው የንብረቶቹን የሽያጭ ዋጋ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171(1) | ጥር/2000 |

**ቅጽ 6**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 158 | 08751 | ወ/ሮ አበበች በጅጋ እና እነ ዶ/ር ተስፋዬ አካሉ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ፍርድ ከተሰጠ በኋላ አዲስ ማስረጃ ተገኝቷል በሚል የተሰጠው ፍርድ በድጋሚ ሊታይ የሚችልበት አግባብ<br>• ውሣኔ ያልተሰጠበት ጉዳይ በድጋሚ ዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ሊቀርብበት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 6 | ግንቦት 26/2000 |
| 159 | 19142 | አቶ መላኩ ማሞ እና እነ ወ/ሮ ፈለቀች ማሞ<br>( ሦስት ሰዎች) | የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ጋር በተያያዘ በሚሰጥ ብይን ላይ ፍ/ቤቱ በሥረ- ነገር ረገድ የመጨረሻ ውሣኔ ሣይሰጥ የይግባኝ አቤቱታ ለማቅረብ የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320 (3) | ጥቅምት 26/2000 |
| 160 | 20465 | አዋሽ ኢንተርናሽናል ኩባንያ እና<br>ፀሐይ ዮሐንስ የህፃን ተመስገን ቱጂ ሞግዚትና አሳዳሪ | በአዋጅ ቁጥር 322/95 መሠረት የቤንሻንጉልን ጨምሮ የአምስት ክልሎች ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች የክልል ከፍተኛ ፍ/ቤቶች ባላቸው የውክልና ስልጣን ያዩዋቸውን የፌዴራል ጉዳዩች በይግባኝ ተቀብለው የማየት ስልጣን ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 322/95, የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 80(2) | ሰኔ 26/2000 |
| 161 | 21270 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>ወ/ሮ ወይንሸት አበራ | አንድ ንብረት በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ከመታገዱ በፊት በባንክ በመያዣነት የተያዘ እንደሆነ ባንኩ በህግ ተሰጠው መብት መገልገል ይችል ዘንድ ፍ/ቤት የሰጠውን የእግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 158, አዋጅ ቁ. 97/90 | ሐምሌ 30/1999 |
| 162 | 22556 | ታደሰ አብዛ እና እነ የአቶ ጉሳዬ ሩገቶ ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | በክርክር አመራር ሂደት የተከራካሪ ወገኖች የመሰማት መብት ተግባራዊ መደረግ ያለበት ስለመሆኑ | ጥቅምት 14/2000 |
| 163 | 22603 | የድሬዳዋ ጊዜ/አስ/ቀበሌ 20 ጽ/ቤት | ተከራካሪ ወገኖች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች ልዩነት ያላቸው በመሆናቸው ጥርጣሬን የፈጠሩ እንደሆነ ፍ/ቤት ተጨማሪ | ሐምሌ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | እና<br>ወ/ሮ ሽሪፍ አሊ | ማስረጃ እንዲቀርብ በማድረግ ጥርጣሬ ያለበትን ጉዳይ አጥርቶ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 255,257 | 26/1999 |
| 164 | 23363 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ አቶ ፈርሀን አህመድ (ሦስት ሰዎች) | የመድን ሰጪ አካል ኃላፊነት በመድን ሽፋን ፖሊሲው ላይ ከተጠቀሰው የገንዘብ መጠን በላይ ሊሆን የማይችል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 665(2) | ግንቦት<br>26/2000 |
| 165 | 23628 | ሶሎ ሲርካርና ኤ.ኤስ እና እነ.ጌትያን ኃ/የተ/የግል ኩባንያ (ሁለት ሰዎች) | በውጭ ሀገር ተመዝግቦ የህግ ሰውነት ያገኘ ኩባንያ በኢትዮጵያ የንግድ ምልክት ምዝገባ ጥያቄ አቅርቦ በሂደት ላይ ያለ መሆኑ በውጭ አገር ያገኘውን የህግ ሰውነት ቀሪ የሚያደርገው ስላለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 100 | ጥቅምት<br>21/2000 |
| 166 | 23692 | አዋሽ ኢንሹራንስ ኩባንያ<br>እና<br>እነ አሊ መሐመድ | • የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 43 ሊተረጐም የሚችልበት አግባብና አፈፃፀሙ<br>• በሦስተኛ ወገን ተከሳሽነት በክርክር ውስጥ እንዲገባ የተደረገ ወገን ከተከሳሽ ጋር ከመሟገት በቀር ተከሳሹን ተክቶ ከሣሽን መከራከር አይችልም ሊባል የማይቻል ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 687, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2), 43 | ሐምሌ<br>03/1999 |
| 167 | 23744 | አቶ በቀለ በድዬ እና እነ ወጋገን ባንክ አዋሳ ቅርንጫፍ (ሦስት ሰዎች) | ዳኝነት ሣይከፈል በነፃ ክስ እንዳቀርብ ይፈቀድልኝ በሚል አቤቱታ አቅርቦ ጥያቄው በፍ/ቤት ትዕዛዝ /ውሣኔ/ ውድቅ የተደረገበት ተከራካሪ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 320(1), (3) | ሐምሌ<br>26/1999 |
| 168 | 23769 | ኢንጅነር ጋሪፉፉ እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂ ጥናት ኢንስቲትዮት | ከአገልግሎት ብዛት ከጥቅም ውጭ የሚሆኑና ሊያስረክባቸው የማይችሉ ዕቃዎች ላይ የዋጋ ግምታቸውን መጠየቅ የክሱ ምክንያት ቀሪ በሆነ ነገር ላይ ክስ እንደመመስረት የሚቆጠር ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 169 | 24111 | የቂርቆስ ክ/ከተማ የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>ወ/ሮ የዕለተወርቅ ገ/አብ | የተከሳሽን መልስ ለመቀበል ቀጠሮ በተያዘበት ዕለት ተከሳሽ ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሳሹ ሊያጣ የሚችለው መልሱን በፁሁፍ የማቅረብ መብቱን ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 70(ሀ), 195 | የካቲት<br>11/2000 |
| 170 | 24627 | ዶ/ር ቤተልሄም ታደሰ እና የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | ከቤት ባለቤትነት ክርክር ጋር በተያያዘ ለክርክር ምክንያት የሆነው ቤት በመመሪያ፣ በቀላጤ ወይም በቃል ትዕዛዝ ከግለሰቦች የተወሰደና በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያለ መሆኑ ካልተገለፀ በስተቀር ጉዳዩን ለማስተናገድ ፍ/ቤቶች ስልጣን የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/ 87 አንቀፅ 3(1) | ሚያዝያ<br>30/2000 |
| 171 | 24775 | ማታዶር አዲስ ጐማ<br>እና<br>ቢተው ረታ | ተከሳሽ መልስ እንዲያቀርብ በታዘዘበት ዕለት ባለመቅረቡ ብቻ ጉዳዩ በሌለበት እንዲታይ በሚል የሚሰጥ ትዕዛዝ አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 241(1), 233 | ጥቅምት<br>21/2000 |
| 172 | 25026 | ወ/ሮ ሁዳ መሐመድ<br>እና<br>ሃጂ አህመድ አህመዲን | ተከሳሽ በራሱ ቸልተኝነት በታችኛው ፍርድ ቤት መከራከሪያ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ነጥቦችን በስር ፍርድ ቤት ባላነሳበት ሁኔታ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውሣኔ መስጠት የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 328(2) እና 182(2) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 173 | 25890 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት እና እነ ዝናሽ አሰፋ (ሁለት ሰዎች) | ሌሎች ተከራካሪዎች በፍርድ ቤት በማካሄድ ላይ ባሉት ክርክር ያገባኛል የሚል 3ኛ ወገን ከውሣኔ በፊት ጣልቃ ገብቶ ለመከራከር የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 41 | መጋቢት<br>18/2000 |
| 174 | 26670 | አዲስ አለም ሲሳይ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ልማት ባንክ | ባለገንዘብ በፍርድ አፈፃፀም ከፍርድ ባለዕዳው የተረከበው ንብረት ከዕዳው በላይ ከሆነ ልዩነቱን ሊከፍል የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 428(2) | ህዳር<br>03/2000 |
| 175 | 27739 | አቶ ድንቁ ገላው<br>እና<br>ወ/ሮ ዋለ እሸቴ | ከመሬት ሽያጭ ውል ጋር በተያያዘ የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለውና በፍ/ቤት ሊስተናገድ የማይችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(2) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 176 | 27808 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ ማይገነት ብርሃኑ (ሁለት ሰዎች) | ከፍርድ በፊት የሚሰጥ የማገጃ ትዕዛዝ በክርክሩ ተካፋይ ያልሆነን ወገን የእግድ ትዕዛዙ ከመስጠቱ በፊት ያገኘውን መብት የማይነካ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 153 (2) | የካቲት<br>7/2000 |
| 177 | 28522 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ የሞያሌ ከተማ አስተዳደር ጽ/ቤት (አራት ሰዎች) | ውሣኔ የተሰጠበትና አዲስ ክስ የቀረበበት ክርክር የሥረ ነገር እና የተያዘው ጭብጥ የተለያየ ከሆነ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ነው ለማለት የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ህዳር<br>3/2000 |
| 178 | 28802 | እነ ወ/ሮ በየነች ይገዙ እና አቶ ሳሙኤል ዝቅአርጋቸው | በክስ በተጠየቀውና በታመነው መሰረት ውሣኔ መስጠት የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182(2) | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 179 | 29738 | የአፓርታማ 79/6 የመኖሪያ ቤት ኅብረት ሥራ ማህበር እና የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት እና ወ/ት ዘርአዳም | የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውን ጉዳዮች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በይግባኝ አይቶ መወሰን የማይችል ስለመሆኑ | ግንቦት<br>14/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አሰገኘኝ | አዋጅ ቁ. 25/88 አንቀፅ 10(1) | |
| 180 | 29761 | እነ አቶ ዳባ ደበሌ (አምስት ሰዎች) እና እነ የአቶ ደበበ ተፈራ ወራሾች (ሁለት ሰዎች) | ያላግባብ በመንግስት የተወረሰ ንብረትን ለማስመለስ ሲባል የሚቀርበው የፍትሐብሔር ክርክር በአዲስ አበባ ከተማ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ስር የማይወድቅ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ሀ) | ጥቅምት 14/2000 |
| 181 | 29780 | እነ ወ/ሮ ሙሉነሽ አለሙ እና ወ/ሮ ከተማሽ ቸርነት | አስቀድሞ ውሣኔ ከተሰጠበት ጉዳይ ጋር በተያያዘ ሌላ የክርክር ጭብጥ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ጥር 29/2000 |
| 182 | 30631 | ወ/ሮ ዘቢዳ ሙሣ እና እነ ወ/ሮ አሻ የሱፍ (ሁለት ሰዎች) | በህገ ወጥ መንገድ ተወስዷል /ከአዋጅ ውጭ ተወርሷል/ የተባለ ቤትን ባለቤትነት በማጣራት ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87 | ህዳር 10/2000 |
| 183 | 30704 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ በቀለ ወ/ማሪያም ወራሾች<br>(ሦስት ሰዎች) | • አዋጅ ቁጥር 47/67"ን" መሠረት አድርጐ የምርጫ ቤቱ ተወስዷል /ተወርሷል/ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ለኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ ቀርበው መወሰን ያለባቸው ስለመሆኑ<br>• በመንግስታዊና በህዝባዊ ተቋማት ቁጥጥር ስር ያሉ ቤቶች ይመለሱልኝ እንዲሁም ውዝፍ ኪራይ ይከፈለኝ በሚል የሚቀርቡ አቤቱታዎች ላይ ውሣኔ መስጠት የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ እንጂ የፍ/ቤት ስልጣን ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 110/87, አዋጅ ቁ. 47/67 | መጋቢት 18/2000 |
| 184 | 31547 | አቶ ኪዳኔ ገ/ጊዮርጊስ እና ወ/ሮ አብርሃ ተስፋሁን | ተከራካሪ ወገኖች በግልጽ ባላመለከቱት ነገር ላይ ተመስርቶ ውሣኔ መስጠት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.182 | መጋቢት 7/2000 |
| 185 | 31833 | ሀጅ አብዱልቃድር አህመድ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ደስታ ገ/ዮሐንስ (ሁለት ሰዎች) | በቤት ላይ የተደረገ እድሳትና ለውጥ ምን ያህል የመጠንና የአይነት ለውጥ እንዳመጣ ክርክር በተነሣ ጊዜ ልዩ አዋቂ መድቦ በማስጠናት መወሰን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 136 | ግንቦት 14/2000 |
| 186 | 32147 | አቶ መሐመድ አብዱ<br>እና<br>አቶ አብዱራሂም አብዲ | የክስ ምክንያት የሌለው አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው በመሆኑ ተከሳሽ የሆነውን ወገን መጥራት ሳያስፈልግ መዝገቡ ሊዘጋ የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231(1) (ሀ) | መጋቢት 9/2000 |
| 187 | 32376 | የአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከ/ቀ/10/11 አ/ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሸዋንግዛው | ከቤት ጋር በተያያዘ የሚቀርቡ ባለቤትነትን የመፈለም ክስ ለማየት የአዲስ አበባ ከተማ ነክ ፍርድ ቤቶች የስረ-ነገር ስልጣን የሌላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.361/95 አንቀፅ 41(ረ) | ግንቦት 19/2000 |
| 188 | 32638 | የቂርቆስ ክ/ከተማ መሠረተ ልማትና ቤቶች ጉዳይ ጽ/ቤት እና እነ አቶ ይርጋ ንጋኔ (አራት ሰዎች) | ወደ ክርክር መግባት ያለበት አካል በክርክሩ ተሳታፊ ሳይሆን የተወሰነው ውሣኔ መብቱን የሚነካ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔው ከመፈፀሙ በፊት ውሣኔው እንዲነሳና ክርክሩ እርሱ ባለበት እንዲቀጥል መጠየቅ የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358 | መጋቢት 12/2000 |
| 189 | 33606 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና እነ አቶ ደጀኔ አበበ (አምስት ሰዎች) | በጊዜያዊነት የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ቀርቦ ውድቅ ከተደረገ በኋላም ቢሆን በድጋሚ በተመሳሳይ ሁኔታ የተሰጠው የእግድ ትዕዛዝ እንዲነሣ ጥያቄ ሊቀርብ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 158 | የካቲት 20/2000 |
| 190 | 34249 | እነ አቶ ዋለልኝ ንጉሱ<br>እና<br>እነ አቶ አለሙ ወንድሙ | ለክርክር እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ የሚታመን ወገን በመካሄድ ላይ በሚገኝ ክርክር ተካፋይ እንዲሆን መደረግ ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 40(2) | ሚያዝያ 28/2000 |
| 191 | 34313 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን<br>እና<br>ከበደ ታደሰ | የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብ ተከሳሽ ኃላፊነት የሚመነጨው ከተከሳሹ ኃላፊነት ስለመሆኑ እና የሦስተኛ ወገን ተከሳሽ ተጠያቂ የሚሆነው ከህግ ወይም ከውል የመነጨ ግዴታ ሲኖር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.43(1) | መጋቢት 25/2000 |
| 192 | 35403 | አቶ አብዱልነጠፍ ሙሔ<br>እና<br>እነ ትዕግስት በርሃ<br>(ሁለት ሰዎች) | • ተከሳሽ ቀርቦ ያልተከራከረው በበቂ ምክንያት ማለትም መጥሪያ ሳይደርሰው መሆኑ ከተረጋገጠ የተወሰነውን ውሣኔ በማንሳት ግራ ቀኙን ማከራከር የሚገባ ስለመሆኑ<br>• ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆነን ወገን መከላከያ ክርክር ሳይሰማ በማለፍ ውሣኔ ለመስጠት የሚችለው ተከራካሪው በችሎት ሳይቀርብ የቀረው በቂ ባልሆነ ምክንያት መሆኑን በቀረቡለት ማስረጃዎች ማረጋገጥ ሲችል ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ.78 | ግንቦት 14/2000 |
| 193 | 22008 | የኪራይ ቤቶች አ/ድርጅት እና እነ አቶ ኦላና ጥርቅ ( ሦስት ሰዎች) | መክፈል የማይገባውን የከፈለ ወገን እንዲመለስለት መጠየቅ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.2164 | ሐምሌ 3/1999 |
| 194 | 22297 | የጀሚ ከተማ የአካባቢ አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>አቶ ሸዋረገድ አድበር | በፍ/ብሔር ክርክር ሂደት ማን ክርክር መጀመርና ማስረዳት እንዳለበትና የተሻለ ማስረጃ ከማቅረብ አንፃር ለማን ፍርድ ሊሰጥ እንደሚገባ በተመለከተ አግባብነት ያላቸውን የህግ መርሆዎች ወደጐን በመተው የሚሰጥ ውሣኔ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ | ሐምሌ 24/1999 |
| 195 | 22469 | የጀጀጋ ደብረ መዊዕ ቅዱስ ሚካኤል ቤ/ክ እና እነ አዳነት | • የህዝብ የሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ሊረጋገጥ የሚችልበት አግባብ | ሐምሌ |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | መንግስቱ (ሰባት ሰዎች) | • የቤተክርስቲያንን የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነት ለማረጋገጥ የባለቤትነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ አስገዳጅ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1578 | 5/1999 |
| 196 | 22719 | የአ/አ ከተማ አስተዳደር ሥራና ከተማ ልማት ቢሮ ተተኪ<br>የመሬት ልማትና አስተዳደር ባለስልጣን<br>እና<br>አቶ ነጋሽ ዱባለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለቤትነትን አስመልክቶ በሚመለከተው አካል የሚሰጠው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከተሰረዘ በኋላ በቤቱ ላይ መብት ወይም ጥቅም አለኝ በሚል የሚቀርብ አቤቱታ ተቀባይነት የማይኖረው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195 | ጥቅምት<br>14/2000 |
| 197 | 23608 | የኢትዮጵያ ፕራይቬታይዜሽና የመንግስት ልማት ድርጅት<br>እና<br>አቶ ኑርበዛ ተረጋ | • የፕራይቬታይዜሽን ኤጀንሲ በሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ሊቀርብ የሚችለው ለኤጀንሲው የስራ አመራር ቦርድ እንጂ ለፍ/ቤት ስላለመሆኑ<br>• የኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና አሣሪ (Binding) ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.110/87 | ህዳር<br>3/2000 |
| 198 | 24269 | የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር እና<br>ተክለማሪያም መኮንን | • ግለሰቦች በከተማ ቦታ የመጠቀም /የመያዝ/ መብት የሚኖራቸው አግባብ ባለው መንግስት አካል /ባለሥልጣን/ ተፈቅዶ ሲሰጣቸው ስለመሆኑ<br>• ከሚመለከተው ባለስልጣን ፈቃድ ሳይኖር የተሰራ የከተማ ቤት ህጋዊነት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 292/78 አንቀፅ 7(1) | ህዳር<br>24/2000 |
| 199 | 26130 | አቶ ገ/እግዚያብሔር ከበደው<br>እና<br>ወ/ት ሰላማዊት ወ/ገብርኤል | • የከተማ ቦታ በግል ባለቤትነት ሊያዝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• ግለሰቦች በመሬት ላይ ሊኖራቸው የሚችለው የይዞታ መብት እንጂ የባለቤትነት መብት ስላለመሆኑ<br>• ከጋብቻ በፊት በአንደኛው ተጋቢ የግል ይዞታ ሥር የነበረ መሬት ላይ በጋብቻ ወቅት የጋራ ቤት የተሰራ እንደሆነ ተጋቢዎቹ በመሬቱ ይዞታም ሆነ በቤቱ ላይ እኩል መብት የሚኖራቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 47/67<br>የኢ...ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 40(3)<br>የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀፅ 85 | የካቲት<br>4/2000 |
| 200 | 27506 | እነ ሣሙኤል ውብሸት<br>እና<br>ብዙነህ በላይነህ | • ሁከት እንዲወገድ በሚል በቀረበ ክስ ላይ ተከሳሽ የሚያነሳው ባለቤትነትን የተመለከተ ክርክር አግባብነት የሌለው ስለመሆኑ<br>• ሁከት ይወገድልኝ በሚል ክስ በቀረበ ጊዜ ፍ/ቤቱ ሊይዝ የሚገባው ጭብጥ ሁከት ተፈጥሯል ወይስ አልተፈጠረም የሚል ጥያቄ አዘል መሆን ያለበት ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>19/1999 |
| 201 | 27600 | ሕብረት ባንክ አክሲዮን ማህበር እና<br>እነ አቶ ጀማል መሐመድ<br>(ሁለት ሰዎች) | በመያዣ በተያዘ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ በማሻሻልም ሆነ ሌሎች አዲስ የሚሰሩ ስራዎች መያዣው የሚያጠቃልላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.3066 | ታህሳስ<br>06/2000 |
| 202 | 29005 | አቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና እነ ግርማቸው ይላላ<br>(ሁለት ሰዎች) | በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሥር የሚገኙና በየክፍለ ከተማው የተደራጁ የመሬት አስተዳደር ጽ/ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ስለመሆኑና በስልጣን ክልላቸው ሥር በሚነሱ ክርክሮች ተካፋይ የመሆን መብት ያላቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 36/95 አንቀፅ 10(2)<br>አዋጅ ቁ. 1/95 /አዋጅ ቁ. 18/97 | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 203 | 30101 | አቶ ገዛኸኝ አድነው እና እነ ወ/ሮ ዳሳሽ ባይነሳኝ<br>(ሦስት ሰዎች) | በሌላ ሰው የመሬት ይዞታ ላይ በባለይዞታው ፈቃድ ህንፃ የሠራ ሰው የህንፃውን ግምት ተቀብሎ ህንፃውን ለማስረከብ የማይገደድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1179(1) እና (2) | ህዳር<br>24/2000 |
| 204 | 30461 | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን እና አቶ ኢሣ መሐመድ | የኢትዮጵያ መንገዶች ባለስልጣን መሬትና ድንጋይ ነክ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብቶችን በነፃ መጠቀም የሚችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 80/89 አንቀፅ 6(18) | ህዳር<br>3/2000 |
| 205 | 33499 | አዋሳ እርሻ ልማት ድርጅት እና አቶ ዶቶር ደሌቦ | ለጊዜው ለመኖሪያነት የተሰጠ ቦታ ላይ ሳያስፈቅዱ ቤት መስራት የተሰራውን ቤት በገንቢው ወጪ እንዲፈርስ የሚያስደርግ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1178(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 206 | 33711 | በቀድሞ ወረዳ 3 ቀበሌ 07 አስተዳደር ጽ/ቤት<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ክብርነሽ ቀደመ | የቤት ባለቤት ሳይሆን ወይም ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ለኪራይ የተከፈለ ገንዘብ እንዲመለስ የሚቀርብ አቤቱታ የህግ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ | መጋቢት<br>23/2000 |
| 207 | 33831 | ሃሰን ኢብራሂም እና ኢብራሂም ይመር ሃሰን | በህግ በግልጽ የተረጋገጠ መብት እያለ በህሊና ግምት ላይ የተመሰረተ ፍርድ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ<br>14/2000 |
| 208 | 33924 | ወ/ሮ ገብርኤላ ኒኮላቶማስ<br>እና | ከቤት ባለቤትነት ጋር በተያያዘ ክስ የሚያቀርብ ሰው የባለቤትነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ካላቀረበ በስተቀር ሁልግዜም ቢሆን በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ሊኖረው አይችልም ብሎ ለመደምደም የማይቻል ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>16/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | የኪራይቤቶች ኤጀንሲ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1195(1) | |
| 209 | 34406 | ወ/ሮ መገርቱ ነጋሣ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ ፀሃይ ልጋ | ያላግባብ መበልፀግ ጋር በተያያዘ የሚነሳ የካሣ ጥያቄ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የይርጋ ደንብ ከውል ውጭ በሚደርስ ሃላፊነት ሥር የተመለከተው የይርጋ ዘመን ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2143(1) | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 210 | 20295 | አቶ ደጀኔ ለገሠ<br>እና<br>እነ አቶ መላኩ ጌታቸው | ወራሽነትን ካረጋገጡ በኋላ ንብረት ተይዞብኛል ይመለስልኝ የሚል ጥያቄ ከሦስት አመት በኋላ በይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ሐምሌ<br>5/1999 |
| 211 | 25567 | ወ/ት አይናለም አበበ<br>እና<br>አቶ ደገፉ ጉርሙ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000 ወራሽ ነኝ ወይም ወራሽነቴ ይረጋገጥልኝ ከሚል ጥያቄ ጀምሮ የውርስ ንብረት ያለ አግባብ ተይዞብኛል በሚል ለሚቀርብ አቤቱታ ጭምር ተፈፃሚነት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 999, 1000 | ህዳር<br>12/2000 |
| 212 | 25664 | አቶ ተገኝ ይማም<br>እና<br>እነ አቶ ካሣሁን ደሳለኝ | በወራሾችና ወራሽ ባልሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሳ የውርስ ንብረትን የተመለከተ ክርክር በአሥር ዓመት ይርጋ የሚታገድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 213 | 26422 | ወ/ሮ ስንልሽ ማዘንጊያ<br>እና<br>እነ አቶ ተስፋ ማዘንጊያ | ከውርስ ሀብት ጋር በተያያዘ ወራሽ ነኝ የሚል ወገን መብቱንና የውርስ ንብረቶቹ በሌላ ወራሽ መያዛቸውን ካወቀ ከሦስት ዓመት በኋላ የሚያቀርበው የወራሽነት ክስ ተቀባይነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(1) | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 214 | 28686 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ግዛው መንጀታ | ውል የመጣስ ተግባር ተጀምሮ ያልቆመ ይልቁንም በመቀጠል ላይ ያለ ተግባር መሆኑ በማናቸውም ጊዜ ግዴታን ለመጠየቅ የሚያስችል ስለመሆኑና በይርጋ ታግዷል ለማለት የማያስችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1845, 1846 | ህዳር<br>24/2000 |
| 215 | 28997 | ስለ አሶሳ ዞን ግብርና እና ትምህርት መምሪያ የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል መንግስት ፍትህ ቢሮ<br>እና በላይ ወርቁ | የመብት ጥያቄን ከፍርድ ቤት ውጪ ላሉ አስተዳደር አካላት ማቅረብ የይርጋ ጊዜን የማያቋርጥ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ.1851(ለ) | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 216 | 29920 | የባህር ዳር ጨ/ጨ/አ/ማኀበር እና አቶ አመሸ ሰይድ | ዳኝነት የተጠየቀበት ነገር ተቀባይነት ሣያገኝ የታለፈ እንደሆነ እንደተከለከለ የሚቆጠር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5(3) | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 217 | 31185 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | ይርጋ በተቋረጠ ጊዜ ቀድሞ የነበረው የይርጋ ጊዜ እንደ አዲስ መቆጠር የሚጀምር ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1852(1) | ግንቦት<br>12/2000 |
| 218 | 31217 | የቴሌኮምኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና አቶ ጫሊ ሐሰን | የደሞዝ ጭማሪና ቦነስን የተመለከተ ክስ በስድስት ወር ውስጥ አለመቅረቡ መብቱን በይርጋ የሚያሳግድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162(3) | ግንቦት<br>14/2000 |
| 219 | 31857 | መሐመድ አብደላ<br>እና<br>የድሬዳዋ ኢትዮ ጂቡቲ ምድር ባቡር | የአሰሪ የስራ ስንብት እርምጃ የመውሰድ መብት ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ጉዳይ ከተከሰተበት ጀምሮ በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ ተግባራዊ ካልሆነ መብቱ በይርጋ የሚቀር ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/97 አንቀፅ 27(3) | መጋቢት<br>17/2000 |
| 220 | 32788 | የኢትዮጵያ እህል ንግድ ድርጅት<br>እና<br>አቶ ግርማ ተገኝ | አሠሪ የሠራተኛን መብት በጽሁፍ ያወቀ መሆኑ ሠራተኛው በሚያቀርበው አቤቱታ ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የይርጋ ገደብ የሚያቋርጥ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 164(3) | መጋቢት<br>18/2000 |
| 221 | 34011 | እልፍነሽ አማረ እና አቶ ግርማ አማረ | ቤት በፍ/ብሔር ህጉ ውስጥ እንደ ርስት የማይቆጠርና የይርጋ መርሆ ተፈፃሚ የሚሆንበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000(2) | መጋቢት<br>25/2000 |
| 222 | 31748 | ይስማው ድረስ<br>እና<br>ይበልጣፍ ፍቅር | ክርክር የቀረበበትን ጉዳይ የሚገዛው የህግ ክፍል ይርጋን አስመልክቶ በተለይ የሚያስቀምጠው የጊዜ ገደብ በሌለ ጊዜ የአስር ዓመት የይርጋ ጊዜ ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | የካቲት<br>18/2000 |
| 223 | 18832 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>እነ አቶ ከበደ ቱሉ<br>(ስድስት ሰዎች) | ለተወሰነ ጊዜ የተቀጠረ ሠራተኛ የተወሰነው ጊዜ ከማብቃቱ በፊት የስራ ውሉ ያለ በቂ ምክንያት ከተቋረጠ ሠራተኛው የውሉ ጊዜ ወይም ስራው እንኪያልቅ ቢቆይ ያገኘው የነበረውን ደሞዝ የሚያህል ደሞዝ የሚከፈለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 42/85 አንቀፅ 43(4)(ለ) | ህዳር<br>3/2000 |
| 224 | 20416 | አቶ ቢንያም ገረመው<br>እና<br>የቻይና መንገድና ድልድል ስራ ድርጅት | ፍርድ ከመሰጠቱ በፊት በማናቸውም ጊዜ ፍርድ ቤት ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው የክሱ መሻሻል ወይም የክርክሩ መለወጥ ነገሩን ይበልጥ የሚያብራራ ወይም ትክክለኛ ፍትህ ለመስጠት የሚረዳ ከሆነ ክሱ እንዲሻሻልና ክርክሩ እንዲለወጥ ሊፈቀድ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 91 | ታህሣሥ<br>8/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 225 | 21329 | የኢትዮጵያ ቴሌኮሚኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና እነ አቶ በቀለ ኩምሳ | የሥራ መሪ የሆነ ሰው የሥራ ውሉ ተቋርጧል በሚል ሣይሰራ ለቆየበት ጊዜ ውዝፍ ደመወዝ ሊከፈለው የሚችልበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ | ጥቅምት 19/2000 |
| 226 | 22275 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>አቶ ኃይሌ ገ/ሥላሴ | • አሰሪ የሥራ ውሉ ዘመን ከማለቁ በፊትም ቢሆን በቂና ህጋዊ ምክንያት ካለው የሠራተኛን የሥራ ውል ሊያቋርጥ ስለመቻሉ<br>• በበቂ ምክንያት የተደረገ የሥራ ውል ማቋረጥ ማስጠንቀቂያ አልተሰጠም በሚል ህገ-ወጥ ስንብት ነው ሊባል የማይችል ስለመሆኑ<br>• በአንድ ድርጅት ውስጥ ያለን የስራ መደብ በሌላ ሦስተኛ ወገን እንዲከናወን አስተላልፎ መስጠት (out sourcing) የሥር ውል ለማቋረጥ ሕጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 35 | ሐምሌ 10/1999 |
| 227 | 25317 | ጥቁር አባይ ትራንስፖርት እና ደሳለኝ አብርሃ | በህገ ወጥ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ በሞተ ጊዜ ለጥገኞቹ ክፍያ የሚፈፀምበት አግባብ<br>አዋጅ ቁ. 377/ 96 አንቀፅ 39(2),110(2), 40 | ህዳር 10/2000 |
| 228 | 25511 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ እና አቶ አብራራው ከፍያለው | በህጋዊ መንገድ የሥራ ውሉ የተቋረጠበት ሠራተኛ የሥራ ስንብት ክፍያ የማግኘት መብት የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋድ ቁ. 377/96 አንቀፅ 39 | ጥቅምት 2/2000 |
| 229 | 26077 | አቶ አይናለም ባይሌ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በአሰሪና ሠራተኛ ህጉ ከተደነገገው ይልቅ በአሰሪና ሠራተኛው መካከል የሚደረገው የህብረት ስምምነት ለሠራተኛው የተሻለ መብትና ጥቅም የሚያስገኝ በሆነ ጊዜ የህብረት ስምምነቱ ተፈፃሚ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 134(2) | ሐምሌ 12/1999 |
| 230 | 27704 | ድራጋዶስ ጂ እና ፒ የመንገድ ስራ ድርጅት<br>እና<br>አብዲ ሁሴን | የሥራ ውሉ በህገ-ወጥ መንገድ ተቋርጧል በሚል ወደሥራ  እንዲመለስ የተወሰነለት ሠራተኛ ካልሆነ በስተቀር ውዝፍ ደመወዝ የማይከፈል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 43(5) | ጥቅምት 5/2000 |
| 231 | 27959 | የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት<br>እና<br>አቶ አሊ መሐመድ | • አንድ ሠራተኛ የሥራ ውሉ ተቋርጦ ለነበረበት ጊዜ የዓመት ዕረፍት ሊያገኝ የማይችል ስለመሆኑ<br>• የዓመት ፈቃድ ከሁለት ዓመታት በላይ ሊተላለፍ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 79(5) | ህዳር 3/2000 |
| 232 | 29692 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እና እነ አቶ አለማየሁ ከበደ | አሠሪ ቋሚ ስራ ሆኖ እየተቋረጠ አልፎ አልፎ የሚሰራ ስራ እንዳለቀ የሠራተኛን ውል ለማቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ | ጥቅምት 12/2000 |
| 233 | 29740 | አቶ ስሜነህ ተክሉ እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ | ፍርድ ቤቶች በቀረበ ክስ ላይ የዕዳ ማቻቻል ጥያቄ በተነሣ ጊዜ ማስረጃዎችን በመመርመር ተገቢውን ውሣኔ መስጠት ያለባቸው ስለመሆኑ | ሚያዝያ 2/2000 |
| 234 | 29866 | ቻይና ዋንቦ ኢንጅነሪንግ ኮርፖሬሽን እና ወርቅነህ ምህረቴ | የውክልና ስልጣን ማስረጃ በወካይና በተወካይ መካከል የቅጥር ውል ስለመኖሩ የሚያስረዳ ስላለመሆኑ | ግንቦት 7/2000 |
| 235 | 29949 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን እና አቶ ዋሲሁን አዳነ | ፍርድ ባልተሰጠበት ጉዳይ ላይ የሚሰጥ የአፈፃፀም ትዕዛዝ ተገቢነት የሌለው ስለመሆኑ | ሐምሌ 19/1999 |
| 236 | 30956 | የወረዳ 5 አጠቃላይ ነጋዴዎች ማህበር እና አቶ በድሉ ጫላ | ዳኝነት ባልተጠየቀበት ጉዳይ ላይ ውሣኔ መስጠት አግባብ ስላለመሆኑ | ሚያዝያ 9/2000 |
| 237 | 31402 | የኢትዮጵያ አገር አቋራጭ ከፍተኛ አውቶብስ የግል ባለንብረቶች ማህበር እና አቶ አያሌው ይርጉ | በጡረታ የተገለለን ወይም የጡረታ ዕድሜው ያለፈን ሠራተኛ ወደ ሥራ መልስ ተብሎ አሰሪ የሚገደድበት የህግ አግባብ የሌለ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 24(3)<br>አዋጅ ቁ. 345/95 አንቀፅ 12(1)(ሐ) | ሚያዝያ 30/2000 |
| 238 | 32545 | አቶ ግርማ ሽፈራው<br>እና<br>የክርስቲያን በጐ አድራጐት ልማት ድርጅት | የፕሮቪደንት ፈንድ ባለመብት የሆነ ሰው በአስር አመት ውስጥ መብቱን  ካልጠየቀ መብቱ በይርጋ ቀሪ የሚሆን ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 162<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1677(1),1845 | ግንቦት 14/2000 |
| 239 | 33314 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ አለማየሁ ወልዴ<br>(አስር ሰዎች) | በአዋጅ ቁጥር 97/90 መሠረት ሥራውን በማከናወን ላይ የነበረን ፋብሪካ የተረከበ ባንክ ከሠራተኞች መብቶች ጋር በተያያዘ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲሰጥ ሊገደድ የማይችል ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 16<br>አዋጅ ቁ. 97/90 | ግንቦት 28/2000 |
| 240 | 33513 | የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና<br>ዘውዴ ተናኘ | በአንድ የስራ መደብ ላይ በቋሚነት የደረጃ እድገት ይሰጠኝ በማለት የሚቀርብ ክስን ለማየት የክልል ፍርድ ቤት የዳኝነት ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 138 | ጥር 27/2000 |
| 241 | 34588 | የኢትዮጵያ ኤሌትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን<br>እና | በወንጀል ጉዳይ ተከሶ ነፃ የተባለ  ሰው በፍትሐብሔር ረገድ ከቀረበበት ክስም የግድ ነፃ ይሆናል ወደሚል ድምዳሜ ሊያደርስ የሚችል ስላለመሆኑ | ግንቦት 5/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ደረጀ ወልደ ኪዳን | አዋጅ ቁ.377/96 አንቀፅ 27 | |
| 242 | 35440 | የዋልያ አገር አቋራጭ አውቶቡስ ድርጅት<br>እና<br>ብርሃኑ አለሜ | ከሠራተኞች ማህበር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር በአሰሪ የሚደረግ የሠራተኞች ቅነሳ የህግ አግባብ ያለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 28(1) | ግንቦት<br>19/2000 |
| 243 | 29415 | ዋተር አክሽን እና ይልማ አሰፋ | አዲስ ወደ ተዛወሩበት ቦታ በመሄድ ስራ አለመጀመር እና ለአምስት ተከታታይ የስራ ቀናት በስራ ገበታ ላይ አለመገኘት በአሰሪው አነሳሽነት የስራ ውልን ለማቋረጥ በቂና ህጋዊ ምክንያት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(2)(ለ) | ጥር<br>27/2000 |
| 244 | 32822 | ጂ.ሰቨን የንግድና ኢንዱስትሪ የመኸር ቃጫ ውጤቶች<br>ፋብሪካ እና መኮንን አበራ | ያለ በቂ ምክንያት ከስራ መቅረት አሠሪ የስራ ውልን ለማቋረጥ የሚያስችለው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 377/96 አንቀፅ 27(1) (ለ) | ጥር<br>27/2000 |
| 245 | 32229 | መሪጌታ ልሣነወርቅ በዛብህ<br>እና<br>ጠቅላይ ቤ/ክህነት ጽ/ቤት | የዳኝነት ስልጣን ሳይኖር የተሰጠ ውሣኔ መሻር ሳያስፈልገው ጉዳዩ ስልጣን ወዳለው አካል ቀርቦ መታየት የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 5 | ሚያዝያ<br>30/2000 |

**ቅጽ 7**

| ተ.ቁ | የሰ/መ/ቁ. | ተከራካሪ ወገኖች | የህግ ትርጉም የተሰጠበት ጉዳይ | ውሣኔው የተሰጠበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 246 | 12719 | ሉክሰር የቱሪስትና የጉዞ ወኪል ኃላ/የተ/የግ/ማህበር<br>እና<br>ብሩኔይስ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር | በሁለት ወገኖች መካከል የተፈረመ ሰነድን እንደ ህጋዊ ስምምነት ለመውሰድ የፈራሚ ወገኖችን ሃሳብና ፍላጐት መመርመር አስፈላጊ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1734, 1952/1/ | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 247 | 20232 | አቶ ትዕግስቱ ብዛ<br>እና<br>አቶ ይሃ ይብሬ | የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች የተዋዋይ ወገኖች መብትና ግዴታዎች የሚፈጠሩባቸውና የሚረጋገጡባቸው በመሆናቸው የውል ህግ መሰረታዊ ድንጋጌዎች መሟላታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁ. 715, የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 1706, 1679 | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 248 | 23609 | የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ<br>እና አቶ አሰበወርቅ ዘገዬ | የስራ መሪ የሥራ ውል ያለአግባብ በተቋረጠ ጊዜ የስራ መሪው ሊያገኝ ስለሚገባው ልዩ ልዩ ክፍያዎች እና ጥቅማጥቅም<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2573, 2574/2/, 2570/2/, 2577, 2562 | ታህሳስ<br>15/2000 |
| 249 | 30298 | አቶ የሺወንድም አቡሃይ<br>እና<br>አቶ አየነው ማለደ | የመጥፋት ውሣኔ የተሰጠበት ሰው ንብረቱ ወደ 3ኛ ወገን የተላለፈ በሆነ ጊዜ የንብረቱን ዋጋ የማግኘት መብት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 171 | ጥር<br>20/2000 |
| 250 | 16218 | የኢትዮጵያ ልማት ባንክ<br>እና<br>እነ ወ/ሮ አስካለ ሁንዴ(ሁለት ሰዎች) | ባንኮች ከሚሰጡት ብድር እና የመያዣ ውል ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች አዋጅ ቁ. 97/90"ን" ዓላማ እንዲሁም አዋጁን ለማስፈፀም በባንኮች የሚወጡትን የፎርክሎዥር መመሪያዎችና አግባብነት ያላቸውን ህጋጋት ግምት ውስጥ በማስገባት እልባት ማግኘት ያለባቸው ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 97/90 አንቀጽ 3 እና 4, አዋጅ ቁ. 216/92 | መጋቢት<br>16/2000 |
| 251 | 25863 | የኢት/ልማት ባንክ እና የኢት/ንግድ ባንክ (ሁለት ሰዎች) | ለባንክ በመያዣነት በተሰጠ የማይንቀሳቀስ ንብረት ላይ የሚኖር የቀዳሚነት መብት<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3088, 3052, 3081,3059 | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 252 | 29269 | የኢት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>እነ አቶ ዋለልኝ አያሌው(ሁለት ሰዎች) | • በፍርድ የተቋቋመ መያዣ ላይ ፍርዱ እንዲሰጥ ያደረገው ባለገንዘብ መያዣ በሆነው ንብረት ላይ የቀዳሚነት መብት ያለው ስለመሆኑ እና<br>• የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403 ተፈፃሚነት የአንድ ፍርድ ባለዕዳ ንብረት በእርሱ ላይ የቀረቡትን ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት የሚያሟላ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ክፍፍሉ ጋር በተገናኘ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3041, 3044, 3059/1/, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 403,154 | ጥቅምት<br>15/2000 |
| 253 | 29375 | የት/ንግድ ባንክ<br>እና<br>ተስፋዬ ገ/ጊዮርጊስ | የማይንቀሳቀስ ንብረት በመያዣነት ከተሰጠ በኋላ በማይንቀሳቀሰው ንብረት ላይ የሚደረግ ማናቸውም የማሻሻል ሥራ የመያዣ ውሉ አካል ተደርጐ የሚወሰድ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3066 አዋጅ ቁ. 97/90 | ጥቅምት<br>19/2000 |
| 254 | 33295 | ወ/ሪት ብርሃኔ አበበ እና እነ አቶ ማርቆስ ተርፋ (አራት ሰዎች) | የማይንቀሳቀስ ንብረት መያዣ በማንኛቸውም ሰነድ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ከተፃፈበት ቀን አንስቶ የማይንቀሳቀሰው ንብረት በሚገኝበት አገር ባለው በማይንቀሳቀስ ርስተ መዝገብ ካልተፃፈ በቀር ምንም አይነት ውጤት የማያስገኝ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 3052, 3053,1605, 1607, 1606 | ግንቦት<br>21/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 255 | 23024 | ወ/ሮ ፋጤ በሽር እና መልዓከ ገነት ዮሐንስ አምባው<br>እና<br>የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ | በጣልቃ ገብነት ተሳታፊ ሆኖ የፍርድ ተጠቃሚ የሆነ ወገን ዋና ተከራካሪ ከሆኑት ወገኖች መካከል በአንዱ አነሣሽነት ጉዳዩ በይግባኝ በሚታይበት ጊዜ በሥር ፍርድ ተጠቃሚ የሆነው ጣልቃ ገብ ባልተጠራበት ሁኔታ የሚሰጥ ውሣኔ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 40/5/"ን" የሚፃረር ስለመሆኑ | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 256 | 24221 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና 4እነ ወ/ሮ አረጋሽ አምደሚካኤል | ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር ጋር የተደረገን የኪራይ ውል መሰረት በማድረግ የተያዘ ቤትን ያለአከራዩ ፍቃድ ለሌላ ወገን ማስተላለፍ ለኪራይ ውሉ መሰረዝ በቂ ምክንያት ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 257 | 25938 | ኪራይ ቤቶች አስተዳደር ድርጅት እና<br>የአቶ ገ/ሕይወት ከ7ዶም ወራሾች<br>(ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል የተለየ ፎርም መከተል እንዳለበት የሚያስገድድ የህግ ድንጋጌ የሌለ ስለመሆኑ እና በሁለት ተዋዋይ ወገኖች መካከል የሚፀና ውል /ህጋዊ ውጤት ያለው ውል/ ለመመስረት በሁለቱም መካከል ስምምነት መኖሩ ብቻ በቂ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1719/1/,1719-1930, 2898/3/ | መጋቢት<br>25/2000 |
| 258 | 28025 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>አቶ ታደለ አበበ | ላልተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ለተከራዩ በሚሰጥ ማስታወቂያ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ የሚችል ስለመሆኑ እና የኪራይ ውሉን ለማቋረጥ/ለማፍረስ ለተከራዩ ማስታወቂያ /ማስጠንቀቂያ/ መስጠት አስገዳጅ ቅድመ ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966/1/ | ጥር<br>20/2000 |
| 259 | 31601 | ወ/ሮ መዓዛ ይሕደጐ እና እነ አየለ ወልዴ (ሁለት ሰዎች) | የኪራይ ውል ተቋርጦ ውዝፍ ኪራይ እንዲከፈለኝና ቤቱንም ልረከብ በሚል የሚጠየቅ ዳኝነት የኪራይ ገንዘብ የተጠየቀበትን ቤት ግምት ጭምር ታሳቢ ተደርጐ የዳኝነት ክፍያ ሊቀርብበት የሚገባ ስላለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 361/95, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 227/2/, 226 | የካቲት<br>11/2000 |
| 260 | 31634 | ኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>እነ የአቶ ወርቁ ሚስት ወ/ሮ ጽጌ በየነ<br>(ሰባት ሰዎች) | መጠየቅ ከሚገባው ቀን ጀምሮ እስከ 2 ዓመት ድረስ ሳይከፈል የቀረ የኪራይ ዕዳ እንደተከፈለ የህግ ግምት ይወስድበታል ማለት ባለገንዘቡ /አከራዩ/ ክስ መስርቶም ቢሆን ዕዳውን ለማሰብሰብ የማይችል መሆኑን ለማመላከት እንጂ ተከራዩ /ባለዕዳው/ ግዴታውን እንደተወጣ የሚያስቆጥረው ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2024/መ/ | መጋቢት<br>4/2000 |
| 261 | 32521 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ እና ዳባ ኢጃቶ | የታወቀ የኪራይ ውል ግንኙነት ሳይኖር ወይም ባለቤት ሳይሆኑ በማይንቀሳቀስ ንብረት መገልገል የተገለገለውን ወገን በንብረቱ በበለፀገው መጠን ኃላፊ የሚያደርገው ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>7/2000 |
| 262 | 34456 | የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>ወ/ት ደብሪቱ ወልደሃና | ለተወሰነ ጊዜ የተደረገ የኪራይ ውል ውሉ የተደረገበት ጊዜ ካለቀና ውሉ ወደ ያልተወሰነ ጊዜ ከተቀየረ የኪራይ ውሉን በማናቸውም ጊዜ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ማቋረጥ የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2966 | ግንቦት<br>14/2000 |
| 263 | 18380 | አቶ ማሞ ደምሴ እና እነ አቶ አያሌው ገ/እግዚአብሔር<br>(ሁለት ሰዎች) | ውል ይጽደቅልኝ በሚል ለፍ/ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የክስ ምክንያት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 231/1//ሀ/ | ጥቅምት<br>5/2000 |
| 264 | 22448 | ኦርቢስ የንግድና ቴክኒክ ክፍል አ/ማህበር እና አቶ ሙሉነህ ካሰ | ፍርድ እንዲፈፀም ለመጠየቅ ችሎታ ያለው ፍርድ የተፈረደለት ሰው /ወገን/ ብቻ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 378/1/ | ጥቅምት<br>28/2000 |
| 265 | 22860 | ሰንላይት ኢንዱስትሪና ማከፋፈያ ኩባንያ<br>እና<br>አቶ ካሣዬ ዘውደ | አንድ ግዴታ መኖሩን ለማስረዳት ህጉ የተለየ ማስረጃ እንዲቀርብ ያዘዘ ካልሆነ በቀር ግዴታው መኖሩን በጽሁፍ፣ በምስክር፣ በህሊና ግምት በተከራካሪው ወገን እምነት ወይም በመሃላ ማስረዳት የሚቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2002 | የካቲት<br>18/2000 |
| 266 | 23331 | ጀማል ሐሚድ እና እነ ወ/ሮ ለተሃይማኖት ተክሌ<br>(አምስት ሰዎች) | በህግ ፀንቶ ያለ የሽያጭ ውልን መሰረት በማድረግ የተገኘ መብት ውሉ ፈራሽ እስካልተደረገ ድረስ የሚቀጥል ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 267 | 24974 | እነ አቶ ፈቃዱ ደሬሴ (ሁለት ሰዎች) እና እነ አቶ ንጉሴ ወርቁ<br>(ሁለት ሰዎች) | በውል ከተገባ ግዴታ አመዛኙ ክፍል ተፈፀመ ወይም/እና አይነተኛ የሆነ የውል መጣስ ተከስቷል ለማለት ባልተቻለ ጊዜ ውል እንዲሰረዝ ለመወሰን የማይቻል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1771,1784, 1785 | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 268 | 26996 | አቶ በቀለ ደቦጭ እና እነ ወ/ሮ አዛለች ደሣለኝ (ሰባት ሰዎች) | ውል የተደረገበት ጉዳይ ሊፈፀም የማይችል ሆኖ በተገኘ ጊዜ ተዋዋይ ወገኖችን ወደ ነበሩበት ቦታ የመመለስ ውጤት ያለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1715, 1815 | የካቲት<br>18/2000 |
| 269 | 27349 | ብሔራዊ የኢትዮጵያ ኢንሹራንስ ኪባንያ እና ዘላቂ ግብርና ተሐድሶ ኮሚሽን | ተዋዋይ ወገኖች በመካከላቸው የሚፈጠርን አለመግባባት በስምምነት ወይም ደግሞ በአስታራቂ አማካኝነት ለመፍታት የተስማሙ ከሆነ ይኼው ስምምነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1765, 1731/1/ | ታህሳስ<br>8/2000 |
| 270 | 28663 | አቶ ካሣሁን ገዛኸኝ እና ወ/ሮ አልማዝ ወልዴ | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658 ተጋቢ ወገን ከሦስተኛ ወገን ጋር ያደረገውን ውል ለማፍረስ ምክንያት ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 658, 686 | ጥር<br>27/2000 |
| 271 | 29233 | አቶ ሙሂዲን ፋሪስ እና አቶ እያሱ በዕደ ማርያም | በተዋዋይ ወገኖች መካከል የተደረገ ስምምነት በፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723 መሰረት የተሟላ አይደለም በሚል ውሣኔ ሲሰጥ ተዋዋይ የነበሩ ወገኖች በፍ/ብ/ህ/ቁ 1815 መሰረት ወደ ነበሩበት ቦታ እንዲመለሱ መወሰን ያለበት ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1723, 1720/1/, 1815 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 272 | 32222 | አቶ መሐመድ ኢብራሂም እና አቶ ታይደር ማች | ያልነበረ ቤትን ሠርቶ ለማስተላለፍ በሚል የሚደረግ ስምምነትን በተመለከተ | የካቲት |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2876, 1723, 3019, 3020/2/ | 4/2000 |
| 273 | 32899 | ወ/ሮ አስካለ ማርያም ታደሰ እና አቶ ተሾመ ካሣዬ | የመሬት አስተዳደር ባለስልጣን የማይንቀሳቀስ ንብረቶችን በተመለከተ የተደረገ የሽያጭ ውል ተቀብሎ ከማይንቀሳቀስ ሀብት መዝገብ ላይ ከማያያዝና ከመፃፍ በስተቀር የሽያጭ ውሉን የማዋዋልና የማረጋገጥ ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ | ግንቦት 21/2000 |
| 274 | 23322 | ወ/ሮ አዳነች ወርዶፋ እና እነ ወ/ሮ አስናቀች ወርዶፋ | የውርስ ሀብት አጣሪ የንብረት ባለቤትነትን የመወሰን ስልጣን የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 956 | ሰኔ 19/2000 |
| 275 | 25869 | ወ/ሮ አየለች አልታዬ<br>እና<br>ወ/ሮ አስናቀች አየለ | የማይንቀሳቀስ ንብረት የጋራ ባለሀብት የሆኑ ሰዎች ንብረቱን በአይነት ለመከፋፈል ባልቻሉ ጊዜ ንብረቱ በሃራጅ ተሸጦ ገንዘቡን መካፈል ያለባቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1272, 1273 | ሰኔ 19/2000 |
| 276 | 30158 | እነ ወ/ሮ ፀሐይነሽ አደም ሞግዚት ሐይሉ ሲሳይ<br>እና<br>የኮ/ል እሸቱ ተስፋዬ ወራሾች | በፍ/ብ/ህጉ ውስጥ "ከዘር የወረደ ርስት" በሚል የተቀረበው አገላለጽ በህገ-መንግስቱ የተሻረ ወይም ተፈፃሚነት የሌለው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1000/2/ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 40 | ሰኔ 19/2000 |
| 277 | 32414 | ወ/ሮ ባዩሽ ደጀኔ እና እነ ወ/ሮ ሃሳብከፋይ ጌራወርቅ<br>(ሁለት ሰዎች) | ኑዛዜ ፈራሽ ነው ይባል በሚል የሚቀርብ ክስ እና የተሰጠ የወራሽነት የምስክር ወረቀት እንዲሰረዝ በሚል የሚቀርብ ተቃውሞ የተለያዩ ይዘትና ውጤት ያላቸው ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 996/1/, 998/1/, 973, 996/2/ | ሰኔ 24/2000 |
| 278 | 34076 | ወ/ሮ ዘነበወርቅ ወልዱ ፀጋ እና እነ እማሆይ ድብቅነሽ ግዛው<br>(ሁለት ሰዎች) | የውርስ ሃብቶች በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ በሆነ ጊዜ የሚነሱ ክርክሮች የውርሱ ክፍያ በተጀመረበት ቦታ ለሚገኝ ፍ/ቤት የሚቀርቡና የሚስተናገዱ ስለመሆናቸው<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 23 | ሰኔ 10/2000 |
| 279 | 24703 | የኢትዮጵያ መድን ድርጅት<br>እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ብ/ክ/መ/ት/ቢሮ | በህግ ተቀባይነት ያለው የኢንሹራንስ ውል የሚቋቋምበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 1725, 1727 የንግድ ህግ ቁጥር 651, 654, 657 | ሚያዝያ 9/1999 |
| 280 | 22069 | የአማራ ብ/ክ/መንግስት ፍትሕ ቢሮ እና አቶ አስማማው አራጌ | በወንጀል ህግ የሃሳብ ክፍል የሚረጋገጠው ከወንጀል ድርጊት አፈፃፀሙ በመነሳት ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522 /1/ /ሀ/ | ጥቅምት 28/2000 |
| 281 | 22452 | የኦሮሚያ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ እና አሣምነው ገ/መስቀል | በወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ ሥር የተመለከቱት የወንጀል ማቋቋሚያ ነጥቦች ለየራሳቸው የሚቆሙ ስለመሆናቸው<br>የወ/መ/ህ/ቁ. 522/1/ /ሀ/ | ሐምሌ 30/2000 |
| 282 | 23855 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አቶ ፀጋሁን መንግስቱ | የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ሳይፈፀምበት የመንግስት ቀረጥ ያልተከፈለበት መኪና ይዞ የተገኘ ግለሰብ በወንጀል ተከስሶ ጥፋተኛ ያልተባለ ቢሆንም ግለሰቡ ተገቢውን ቀረጥ ከፍሎ መኪናውን መረከብ አልያም ደግሞ መኪናው መወረስ ያለበት ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 60/89 አንቀጽ 74 አዋጅ ቁ. 388/95 አንቀጽ 80/3/ | ጥቅምት 26/2000 |
| 283 | 24278 | ሰለሞን ሄርጳቦ<br>እና የደ/ብ/ብ/ ሕ/ክ/መ/ የሥ/ፀ/ሙ/ኮ/ዓ/ሕግ | በአዋጅ ቁ. 214/74 አንቀጽ 13/1/ መሠት የተከሰሰ ሰው ጥፋተኛ ሊባል የሚችለው እንዲጠብቃቸው በአደራ የተረከባቸውን ወይም በሥራው አጋጣሚና ምክንያት በእጁ የገቡትን ንብረቶች የወሰደው/የሰወረው/ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለማግኘት የሆነ እንደሆነ ስለመሆኑ | ህዳር 10/2000 |
| 284 | 28952 | የጉምሩክ ዓቃቤ ሕግ<br>እና<br>አቶ ባንቲ ታኤራ | በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/ መሠረት ከሣሽ አቅርቦት የነበረውን ክስ ካነሣ በኋላ እንደገና ክሱን ለመቀጠል የሚችል ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 122/2/, /5/ | መጋቢት 16/2000 |
| 285 | 29325 | ኤርምያስ ካሣ ተፈራ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ክስ የቀረበበት ሰውን አስመልክቶ ጉዳዩ በሌለበት ነው የታየው ሊባል የሚችልበት አግባብ<br>የወ/መ/ሥ/ሥ/ቁ. 161/1/ | የካቲት 18/2000 |
| 286 | 31734 | አቶ አስናቀ በቀለ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ተከሶ የተያዘ ሰው ዋስትና በጠየቀ ጊዜ ፍ/ቤት ተከሳሹ ተመልሶ ሊቀርብ አይችልም የሚል ግምት ለመውሰድና ዋስትናን ለመከልከል በቂ ምክንያት የሚያስፈልግ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ. 67/ሀ/ | ጥቅምት 15/2000 |
| 287 | 34077 | አቶ ሰይድ ይመር እና የአማራ ክልል ሥነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን | በወንጀል የተከሰሰ ሰው የሚያነሳው የዋስትና ጥያቄ መታየት ያለበት ሊወሰንበት ከሚችለው ቅጣት አንፃር ስለመሆኑ | መጋቢት 9/2000 |
| 288 | 34280 | አቶ ግርማይ ደስታ እና ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ቅጣት ሊገደብ የሚችልበት አግባብ<br>የወንጀል ህ/ቁ. 192,194 | ግንቦት 14/2000 |
| 289 | 34521 | የአማራ ብ/ክ/መ/ፍትሕ ቢሮ እና ስንታየሁ ተፈራ | በወንጀል ህግ ቅጣትን በልዩ የህጉ ክፍል ከተወሰነው መነሻ ዝቅ አድርጐ በማቅለል ለመወሰን የሚቻልበት አግባብ<br>የወ/ህ/ቁ. 184, 179 | ሰኔ 3/2000 |
| 290 | 35611 | ሻለቃ ታደሰ ካሕሳይ እና የፌዴራል ዓቃቤ ሕግ | በወንጀል ህግ ጉዳዩን ለመስማት በተቀጠረበት ዕለት አቤቱታ አቅራቢው ባልቀረበ ጊዜ አቤቱታው እንዲሰረዝ የሚደረገው አቤቱታ አቅራቢው ጉዳዩን በትጋት ያልተከታተለ ወይም በቸልተኝነት የተወው መሆኑ ሲረጋገጥ ስለመሆኑ<br>የወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ 193/1/ | ሰኔ 19/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 291 | 18809 | አቶ ሚሊዮን ዑመር<br>እና<br>ዮፌዴራል የአገር ውስጥ ገቢ ባለስልጣን | በደንብ ቁጥር 75/1993 ኮምፒዮተርን ጨምሮ ከተለያዩ መሳሪያዎች ህንፃዎችና ሌሎች ዕቃዎች ኪራይ በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ለመሰብሰው የተደነገገው መኪናን በማከራየት የሚገኝን ገቢ የሚያካትት ስለመሆኑ<br>ደንብ ቁጥር 75/93 አንቀጽ 2/9/ ደንብ ቁጥር 78/94 አንቀጽ 24/2/ /ሸ/ | ሰኔ<br>12/2000 |
| 292 | 19258 | አቶ ተክሌ ዋቅጅራ እና አቶ ሾንጣ ጉቡ | የተወሰነ ኃላፊነት ያለው የግል ማህበር መዋጮ መከፈል ያለበት ማህበሩ ሲቋቋም እንጂ ተቋቁሞ ሥራው ከተጀረ በኂላ ስላለመሆኑ | ሐምሌ<br>12/1999 |
| 293 | 23389 | የአማኑኤል ፀጋ የንግድ ሱቆች አ/ማኀበር እና እነ ባህሩ አብርሃም (ሁለት ሰዎች) | የአክሲዮን ማህበር አባላት መብታቸውን የሚነካ ድርጊት በማህበሩ አስተዳዳሪዎች በተከናወነ ጊዜ በቀጥታ አስተዳዳሪዎቹን ሊከሱ ስለመቻላቸው<br>የንግድ ህ/ቁ. 364,365,367 | ሐምሌ<br>10/1999 |
| 294 | 28923 | የባህር ዳር ጨ/ጨ አክስዮን ማሕበር እና የባህር ዳር ልዩ አስተዳደር እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ | የመንግስት የልማት ድርጅቶች ወደ ግል ይዞታ ከመቀየራቸው በፊት ያለባቸውን የዕዳ ክርክር በኃላፊነት ይዞ መከራከር ያለበት የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባላደራ ቦርድ ስለመሆኑ<br>አዋጅ ቁ. 208/1992 አንቀጽ 5/1/, 6/1/ /ሐ/, አዋጅ ቁ. 182/1992 | ግንቦት<br>7/2000 |
| 295 | 10489 | የስራና ከተማ ልማት ሚ/ሮ ተተኪ መሠረተ ልማት ሚ/ር<br>እና<br>የቀድሞ ብሐራዊ መሐንዲሶችና ሥራ ተቋራጮች ኃ/የተ/የግ/ማ | በበጀት የሚተዳደር የመንግስት መስሪያ ቤት የፍርድ ባለዕዳ ሆኖ ሲገኝ ውሣኔውን ለማስፈፀም ለሌላ ጉዳይ በበጀት የተያዘውን እና የሰራተኛ ደመወዝን የሚያካትተውን ገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ወጪ ሆኖ እንዲከፈል ለማዘዝ ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 404 | ሐምሌ<br>24/1999 |
| 296 | 18576 | ወ/ሮ ደስታ መኮንን<br>እና<br>ወ/ት መሰሉ ጌታሁን | የውርስ ማጣራት ሪፖርት ከፀደቀ ወይም በፍ/ቤት ተቀባይነት ካገኘ በኂላም ቢሆን እንደ ፍርድ ተቆጥሮ በቀጥታ የአፈፃፀም አቤቱታ ሊቀርብበት ስላለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 944, 946, 956, 960, 996 | ግንባት<br>26/2000 |
| 297 | 19283 | ወ/ሮ መድሐኒት ኃይሉ<br>እና<br>የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ | ባንክ ለሰጠው ብድር በመያዣነት እጁ ያስገባውን የተበዳሪ ንብረት በመጀመሪያም  ሆነ በሁለተኛው የሃራጅ ጨረታ ለሽያጭ አቅርቦ ገዢ ያልተገኘ እንደሆነ ንብረቱን ሊያስቀር የሚችለው ለመጀመሪያው ጨረታ መነሻ በተሰጠው የዋጋ ግምት መሰረት ስለመሆኑ | መጋቢት<br>9/2000 |
| 298 | 22481 | አቶ ክፍሌ ወልዴ<br>እና<br>ፔትራም ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር | በሀራጅ ጨረታ የአሻሻጥ ስርዓት ላይ "ግዙፍ የሆነ ጉድለት" ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ተግባር እንደተፈፀመ ሊቆጠር የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 422/3/, 428/5/, 455, 428/1/ | መጋቢት<br>4/2000 |
| 299 | 22930 | ወ/ሮ ታድሬ አባተ<br>እና<br>ወ/ሮ ዓለም ገ/የሱስ | ባልና ሚስት በፍቺ ከተለያዩና የንብረት ክፍፍል ከተደረገ በኂላ ከአንደኛው ተጋቢ የግል ተግባር የሚመነጭ ዕዳ አፈፃፀም የተጠየቀው /የቀረበው/ ከፍቺ በኂላ እስከሆነ ድረስ ለዕዳው ምክንያት ከሆነው ተጋቢ ብቻ የሚጠየቅ ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>30/2000 |
| 300 | 23733 | እነ ሃፍቶም ገ/እራሃ (ሁለት ሰዎች)<br>እና<br>እነ ሙሉ ካሣ (አራት ሰዎች) | ከንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ በዋናው ጉዳይ አከራካሪ የሆነው ንብረት መካፈል ከተቻለ እንዲካፈል ካልሆነ ደግሞ በባለሙያ ተገምቶ እንዲካፈሉ በሚል የተሰጠን ፍርድ መነሻ በማድረግ የአፈፃፀም ችሎት /ፍ/ቤት/ ከተከራካሪ ወገኖች መካከል አንደኛው ግምቱን ከፍለው ንብረቱን እንዲያስቀሩ በሚል ትዕዛዝ ለመስጠት የማይችል ስለመሆኑ | ህዳር<br>24/2000 |
| 301 | 23989 | አቶ ደስታ ሠርዳ እና<br>የመተከል ዞን ፍትህ መምሪያ | የማይንቀሳቀስ ንብረት ስመ ንብረት /ባለቤትነት/ ከሻጭ ወደ ገዥ ያለመዛወሩ ብቻ ሦስተኛ ወገኖች በሻጭ ላይ ሽያጭ የተካሄደበት ንብረት ላይ የጀመሩት አፈፃፀም እንዲቀጥል ለማስደረግ በቂ ሁኔታ ስላለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ህ/ቁ. 2878 | ታህሳስ<br>17/2000 |
| 302 | 25031 | ወ/ሮ አልታየወርቅ ኃ/ማርያም እና<br>አቶ ዓለማየሁ ገለቱ | በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418 መሰረት አቤቱታ ሊቀርብ የሚችልበት አግባብ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358,418 | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 303 | 26553 | የባህርዳር ልዩ ዞን ገንዘብ መምሪያ እና የኮንስትራክሽንና ቢዝነስ ባንክ እና<br>ሙክታር መሐመድ | • የማይንቀሳቀስ ንብረት በሃራጅ በሚሸጥበት ጊዜ በሃራጅ እንዲሸጥ የሚወጣው ማስታወቂያ ለ30 ቀናት መቆየት ያለበት ስለመሆኑ<br>• ንብረቱ በመያዣ የተያዘ እንደሆነም የመያዣው ልክ ምን ያህል እንደሆነ በጨረታ ማስታወቂያ ላይ መገለጽ ያለበት ስለመሆኑ<br>• ሽያጩ ባልተገባ መንገድ ተከናውኗል ከተባለም ጨረታው በድጋሚ  መካሄድ ያለበት ስለመሆኑ<br>• በመያዣ የተያዘን ንብረት በሌላ ባለገንዘብ ጠያቂነት እንዲሸጥ ሊደረግ ስለመቻሉ<br>የፍ/ብ/ሕ/ቁ. 3059/1/, 3084, የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418, 426, 423/2/ /ለ/, 445-447, 415 | ሐምሌ<br>3/1999 |
| 304 | 27574 | ወ/ሮ አለሚቱ ተረፈ እና የትግል ፍሬ ልብስ ስፌት ማኀበር | በሽምግልና ጉባኤ አማካኝነት የተሰጠ ውሣኔ በፍ/ቤት ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 215/1/, 319/2/ | ጥቅምት<br>26/2000 |
| 305 | 28019 | አቶ ብርሀኑ ገ/እግዚአብሔር እና ወ/ሮ ገርጊስ ናይዝጊ | ፍርድን በአግባቡ ውጤት ለመስጠት የአፈፃፀም ችሎት የፍርዱን ትክክለኛ ቃል እና መንፈስ መከተል ያለበት ስለመሆኑ | ታህሳስ<br>1/2000 |
| 306 | 28154 | የኪራይ ቤቶች ኤጀንሲ<br>እና<br>የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ | በተያዘ ወይም በተከበረ ንብረት ላይ 3ኛ ወገኖች መብት ያቋቋምን ስለሆነ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም በሚል አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ፍ/ቤት ተከራካሪ የሆኑ ወገኖች በአቤቱታው ላይ ያላቸውን ክርክር በቅድሚያ በመስማት መወሰን ያለበት ስለመሆኑ | ሚያዝያ<br>14/2000 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | | የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 418/1/, 419 | |
| 307 | 29344 | ወ/ሮ ዝማም ህሉፍ<br>እና<br>አቶ መረሣ ገ/ዮሐንስ | ውሣኔን የሚያስፈጽም ፍ/ቤት በውሣኔው መሰረት ከማስፈፀም ወጪ በአፈፃፀም ጊዜ ዋናውን ፍርድ ሊለውጥ የሚችልበት የህግ መሰረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | ግንቦት<br>5/2000 |
| 308 | 29653 | አቶ ነጋ ደምሴ<br>እና<br>ሃምሳ አለቃ አዲሱ ደምስ | በዋናው ክርክር ገብቶ ተከራክሮ ውሣኔ ያላገኘ ተከራካሪ ወገን በአፈፃፀም ጊዜ ውሣኔ እንዲፈፀምለት ጥያቄ የሚያቀርብበት የህግ መሠረት የሌለ ስለመሆኑ<br>የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ. 358, 418 | መጋቢት<br>9/2000 |
| 309 | 33760 | ሐጂ ታጁ ለገሠ<br>እና<br>የጎንደር ከተማ የመሃል አራዳ ቀበሌ አስተዳደር | የንግድ ድርጅት /መደብር/ ላይ ያለ መብት የድርጅቱ ንግድ የሚካሄድበትን ቤት የኪራይ መብት የሚያካትት ስለመሆኑ<br>የንግድ ህግ ቁጥር 127 | መጋቢት<br>18/2000 |